# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች

## ቅጽ-10




የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

ህዳር 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

## ቅጽ - 10

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

ህዳር 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ



# የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት መልዕክት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሠጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት እንደሚኖረው፤ በዚህ ረገድ የሚሠጡ የሰበር ውሣኔዎችን ፍርድ ቤቱ አሣትሞ ማሠራጨት እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ሥር ተደንግጓል፡፡ በዚሁ መሠረትም እስካሁን ድረስ አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸው ፍርዶች ከቅጽ 1 እስከ ቅጽ 7 ድረስ በማሣተም ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲሠራጩ ተደርገዋል፡፡

እነዚህ ፍርዶች የሀገራችን ፍርድ ቤቶች የሚሠጧቸው ፍርዶች ወጥነትና ተገማችነት እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ የማይናቅ ሚና እየተጫወቱ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህን ቀጣይ ለማድረግ ቅጽ 8፣ 9 እና 10 እነሆ ለሕትመት በቅተዋል፡፡

አስገዳጅ የሰበር ውሣኔዎች ሥራ ላይ ከዋሉ አጭር ጊዜያቸው ነው፤ በአንፃራዊነት የብቃትም ሆነ የልምድ ውሱንነቶች በመኖራቸው እነዚህ እጥረቶች በሰበር ፍርዶቻችን ላይ አልፎ አልፎ መንፀባረቃቸው አልቀረም፡፡ በዚህ መስክ የረጅም ዘመናት ታሪክ ያሏቸው ሀገሮችም በተመሣሣይ ሁኔታ ውስጥ ያለፉ በመሆናቸው እኛም አቅማችንን በማጠናከር የእነዚህን አገሮች ተሞክሮዎች በማገናዘብና የሀገራችን የሕግ ባለሙያዎች በፍርዶቻችን ላይ የሚሠጡትን ገንቢ አስተያየቶችና ትችቶች ግብዓት በማድረግ ኃላፊነታችንን በአግባቡ ለመወጣት ጥረታችን እንደሚቀጥል በዚህ አጋጣሚ እየገለጽሁ የሕግ ትምህርት ቤቶቻችን፣ ሌሎች የሕግ ባለሙያዎችና ህብረተሰቡ በአጠቃላይ ለጥረታችን እውን መሆን የማይተካ ድርሻ አላቸውና ከጎናችን እንዲቆሙ ጥሪየን አስተላልፋለሁ፡፡

ተገኔ ጌታነህ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ፕሬዝዳንት

# በ2002 ዓ.ም የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች

## ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ቤተሰብ** | | | | 1 |
| 1 | በጋብቻ ውል ላይ ባልና ሚስት "መተዳደሪያችን" ነው በሚል ያመለከቷቸው ንብረቶች የጋራ ንብረት ተደርገው የሚቆጠሩ ስለመሆናቸው | 38544 | አቶ ብሩክ ኃ/እየሱስ እና ወ/ሮ ፋናዬ አበበ | ጥቅምት 5/2002 | 2 |
| 2 | • በጋብቻ ላይ የተደረገ ጋብቻ ከጅምሩ ውጤት አልባ ነው (void ab initio) ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ<br>• የጋብቻ ውል ተጋቢዎች ንብረታቸውን በተመለከተ ጋብቻው የሚያስከትለውን ውጤት ስምምነት የሚያደርጉበት ሰነድ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 42,44,33,11 | 39408 | አርጋው አባቼ እና የወ/ሮ አስቴር አበጋዝ ወራሾች (ስድስት ሰዎች) | ጥቅምት 24/2002 | 4 |
| 3 | የውርስ ሀብትድርሻ ክፍፍል ጥያቄ በይርጋ የሚታገድበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1080(3) | 40418 | ተስፋዬ ሞላ እና እነ እሸቱ ምነ (ሦስት ሰዎች) | ጥቅምት 10/2002 | 6 |
| 4 | አባትነት በፍርድ ውሣኔ ሊታወቅ የሚችልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 43 | 42682 | እነ ወ/ሮ ፋንታነሽ በላይ (ሦስት ሰዎች) እና ሞላ ደምሴ | ጥቅምት 10/2002 | 8 |
| 5 | ፀንቶ ባለ ጋብቻ ውስጥ የተወለደ ልጅ አባት በጋብቻ ውስጥ ባል የሆነው ወገን ስለመሆኑና የዚህን ሰው አባትነት ለመቃወም የሚቻልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 144,126,167,168,173 | 40624 | እነ ወ/ሮ መብራት ታደሰ (አራት ሰዎች) እና አቶ ኤፍሬም ዘውዴ | ጥቅምት 12/2002 | 10 |
| 6 | የጋራ የሆነን የውርስ ሀብት ከፍቃዱ ውጪ እንዲሸጥ የተደረገበት ወራሽ ከሽያጩ ዋጋ ድርሻውን ለማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1266,1060(1) | 41857 | አሕመድ ሑሴን እና እነ ወ/ሮ የኔዓለም ተመስገን (ሦስትሰዎች) | ጥቅምት 24/2002 | 13 |
| 7 | አባትነት በፍርድ ውሣኔ ሊታወቅ የሚችልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 43 | 42682 | እነ ወ/ሮ ፋንታነሽ ሲሳይ (ሦስት ሰዎች) እና ሞላ ደምሴ | ጥቅምት 10/2002 | 15 |
| 8 | ከጋብቻ በፊት የግል የነበረ ንብረት በተጋቢዎች የጋብቻ ውል መነሻነት የጋራ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ | 42766 | እነ ወ/ት ሠናይት ኃ/ማሪያም እና ወ/ሮ አበበች ወርቁ | ጥቅምት 10/2002 | 17 |
| 9 | ልጅነትን በማረጋገጥ በፍ/ቤት የሚሰጥ ውሣኔ የህግ ግምት የሚፈጥር እንጂ አስገዳጅነት ያለው እና የመጨረሻ ማስረጃ ተደርጐ መወሰድ የሌለበት ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154,155,156,157 | 42648 | ወ/ሮ ዘነበች በያን እና ወ/ት ብርቅነሽ ከበደ | ታህሣሥ 6/2002 | 19 |
| 10 | አባትነት በህግ አግባብ ሊታወቅ የሚችልባቸው ሁኔታዎች<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 126,1(1),(2),128(1),130(2),125,106(1), የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 35(2) | 44612 | ወ/ሮ ዘውዴ ወ/ጊዮርጊስ እና ወ/ት ኤልሣቤጥ ኪዳኔ | ጥቅምት 10/2002 | 21 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 11 | • በውርስ ሕግ ውስጥ የተመለከቱ የይርጋ ድንጋጌዎች ሊተረጐሙ የሚችሉበት አግባብ<br>• የወራሽነት መብትን በሕግ በተመለከተ ጊዜ ውስጥ ያረጋገጡ ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996,1000(1),1000(2),1060,1062 | 38533 | እነ ወ/ሮ ጽጌ ወልደመስቀል (ስድስት ሰዎች) እና አቶ ስዩም ክፍሌ | ህዳር 8/2002 | 24 |
| 12 | ልጅነት ሊረጋገጥ የሚችልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 156,168,158,169 | 42569 | እነ የዳግማዊ ታዲዩስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ (ሁለት ሰዎች) እና<br>የሃና ታዲዮስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ | ታህሣሥ 212002 | 27 |
| 13 | ኑዛዜ ሊተረጐም የሚገባው ቃላቶቹና መልዕክቱ ግልፅ ሣይሆን ሲቀር ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 810(2) | 47487 | አቶ ሐይለራጉኤል ደበላ እና<br>እነ ወ/ሪት አለምፀሐይ ፈለገ (ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 27/2002 | 30 |
| 14 | የስጦታ ውል ሊተረጐም የሚገባው በውሉ ውስጥ የሚገኘን አንድ ሃረግ ነጥሎ በማውጣት ሳይሆን የውሉን አጠቃላይ ይዘት በመመልከት ስለመሆኑ | 41893 | ወ/ሮ ዮዲት ኃይሉ እና እነ ወ/ሪት ገነት አረጋይ (ሦስት ሰዎች) | ታህሣሥ 21/2002 | 33 |
| 15 | የምትክ ወራሽነት ተጠቃሚዎችን ስለመለየት<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 842,843,844(3) | 47957 | እነ አቶ ተፈሪ ሐጐስ<br>(ሦስት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ተስፋይ ገ/እግዚአብሔር | ጥር 5/2002 | 36 |
| 16 | • የስጦታ ውል ገደብ ያለበት ወይም ግዴታ የተጣለበት እንደሆነ በውሉ ውስጥ የተመለከተው ግዴታ አልተፈፀመም በሚል ፈራሽ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>• በፍ/ብ/ህ/ቁ. 244(1) ላይ የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ በስጦታ ውል ውስጥ የተመለከተ ግዴታ አልተፈፀመም በሚል ውሉ እንዲፈርስ ሲጠየቅ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2452(1),2464(1),2441(1) | 42346 | እነ አቶ ፍስሐ መንግስቱ<br>(ሁለት ሰዎች)<br>ወ/ሮ አለምነሽ ፍስሐ | የካቲት<br>9/2002 | 38 |
| 17 | የጉዲፈቻ ስምምነት የሕፃናትን ጥቅምት ለማስጠበቅ ሲባል ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 195(2) | 44101 | ሚስስ ፍራንስዊስ ፖስተር<br>እና<br>እነ ሚ/ር ዱክማን ቬኖ<br>(ሁለት ሰዎች) | የካቲት 24/2002 | 41 |
| 18 | የውርስ ንብረት በሆነ ቤት ላይ ድርሻ አለን የሚሉ ወገኖች ንብረቱን ህጋዊ የሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ይዞ ከነበረ ሰው በመግዛት ስመ ሀብቱን ወደራሱ ስም አዛውሮ የሚገኘን ሰው ለመጠየቅ የማይችሉ ስለመሆኑ | 46527 | ወ/ሮ ገነት በቀለ እና ወ/ሮ ትዕግስት አሰፋ | የካቲት 24/2002 | 44 |
| 19 | ከውርስ ጋር በተያያዘ በቤት ላይ ህጋዊ መብት የሌለው ሰው ሽያጭ አከናውኖ ሲገኝ ትክክለኛው ባለሃብት መብቱን ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጐ የገዛውን ገዥ ሣይሆን ሻጩን ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 997,2882, 2884,1060(1),1266 | 47378 | አቶ አለማየሁ ከተማ እና እነ ወ/ሮ ላቀች አይተንፍሱ<br>(ሦስት ሰዎች) | የካቲት 24/2002 | 46 |
| 20 | ኑዛዜ በፍ/ቤት መፅደቁ በንብረት ላይ ያለ የባለቤትነት መብትን የሚያረጋግጥ ስላለመሆኑ | 42482 | እነ አቶ ፍሬዘውድ ተካ ጉጂ (ሁለት ሰዎች) እና<br>አቶ ሰለሞን ኃ/ማሪያም | የካቲት<br>3/2002 | 49 |
| 21 | የልጆች ቀለብ አከፋፈል ሁኔታ ጋር በተያያዘ ክፍያ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ | 45819 | አቶ ካሣ ፋንታ እና ወ/ሮ እስካዳር ግጨው | የካቲት<br>12/2002 | 51 |
| 22 | በትዳር ወቅት የተወሰደ ብድር የአንደኛው ተጋቢ ፈቃድ የሌለበት ቢሆንም ፈቃዱን ያልሰጠው ተጋቢ የብድር ስምምነቱ እንዲፈርስ ያላደረገ እንደሆነ ወይም ደግሞ ለትዳር ጥቅም አለመዋሉን ማስረዳት ያልቻለ ከሆነ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የህግ ግምት የሚወሰድ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68(መ) | 45202 | አቶ ድንቁ ወርዶፋ<br>እና<br>ወ/ሪት ኤደን ድንቁ ወርዶፋ | መጋቢት 8/2002 | 53 |
| 23 | በተጭበረበረ መንገድ ወራሽነትን አሳውጆ የውርስ ንብረት አካል የሆነን ቤት ስመ ሃብት ወደ ራሱ አዙሮ የሚገኝ ሰው ጋር የሽያጭ ውል በተደረገ ጊዜ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ በሚል ትክክለኛ ወራሾች የሚያቀርቡት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍብ/ህ/ቁ. 2882, 2884, 997 | 45370 | እነ አቶ ዳንኤል አበበ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ሙሉ ወልደየስ (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 21/2002 | 56 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 24 | የስጦታ ውል ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠሩ 10 (አስር) ዓመታት ውስጥ ለአፈፃፀም ያልቀረበ እንደሆነ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1676(1),1845 | 42691 | አቶ አደፍርስ በቀለ እና አቶ ይቁም በቀለ | መጋቢት 22/2002 | 59 |
| 25 | • በውርስ ሕግ ውስጥ የተመለከቱ የይርጋ ድንጋጌዎች ሊተረጐሙ የሚችሉበት አግባብ<br>• የወራሽነት መብትን በሕግ በተመለከተ ጊዜ ውስጥ ያረጋገጡ ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996,1000(1)1002,1060,1062 | 44237 | እነ ወ/ሮ ሙሉሸዋ ቦጋለ<br>(አራት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ መስፍን ቦጋለ | መጋቢት 20/2002 | 61 |
| 26 | ሞግዚት የሆነ ሰው በሞግዚትነት የሚያስተዳድራቸውን ልጆች ሀብት የሆነን ንብረት ለልጆቹ መልካም አስተዳደግ ሲል ሊሸጠው የሚችል ስለመሆኑ<br>የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ ቤተሰብ ህግ አንቀፅ 292 | 46490 | እነ ወ/ሮ ቦጋለች ደባልቄ<br>(አራት ሰዎች) እና<br>ወ/ሮ መሠረት በለጠ | መጋቢት 21/2002 | 64 |
| 27 | በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ላይ የተደረገ የሽያጭ ውል በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ አለመፍረሱ ስለሚያስከትለው ውጤት | 51295 | አቶ ዮሐንስ ጡእማይ<br>እና<br>ወ/ሮ ምህረት ገብሩ | መጋቢት 6/2002 | 66 |
| 28 | ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው ባለስልጣን ፊት የሚደረግ ኑዛዜ በህግ የተቀመጠውን ፎርማሊቲ አሟልቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 882 | 49851 | ወ/ሮ ታሪኳ አበበ የህፃን ሮቤል ንጉሤ ሞግዚት<br>ተጠሪ፡የለም | ሚያዝያ 4/2002 | 68 |
| 29 | ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ የሆነ ሰው እና ከህግ ውጪ ከውርስ የተነቀለ ያለኑዛዜ ወራሽ የውርስ ሃብትን ሊከፋፈሉ የሚችሉበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 939(3) ,850,,911(1) 912(1) | 43069 | አቶ አማረ ረታ እና አቶ ሰለሞን ካሣዬ | ሚያዝያ 6/2002 | 70 |
| 30 | የጉዲፈቻ ውል እንዲፈርስ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 195(1),(2) | 52691 | እነ ቤተ ዛታ ችልድረንስ ሆም አሶሴሽን<br>(ሦስት ሰዎች)<br>ተጠሪ፡የለም | ሚያዝያ 22/2002 | 72 |
| 31 | ኑዛዜ መኖሩን የማስረዳት ሸክም (ግዴታ) የተጠቃሚዎች ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 896,897 | 53279 | ወ/ሮ ትእግስት ግርማ የእነ አቤል ወርቁ ሞግዚት እና<br>አቶ ኤፍሬም መንግስቱ | ሰኔ 8/2002 | 74 |
| 32 | በኑዛዜ የውርስ ሀብት ክፍፍል መደረግ ጋር በተያያዘ ወራሽ የሆነ ወገን ሊደርሰው ከሚገባው የውርስ ሀብት መጠን ከአንድ አራተኛ በታች እንዲደርሰው የተደረገ መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ኑዛዜውን እንዲፀና በማድረግ የተናዛዡን ፍላጐት ማክበርና መጠበቅ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ<br><br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 910, 913 1123(1) | 50901 | ወ/ሮ እልፌ ኃይሌ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ትዕግስት ደበሌ<br>(ሦስት ሰዎች) | ሰኔ 10/2002 | 76 |
| 33 | በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ስለመኖሩ ለማስረዳት የሚችሉት በግንኙነቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ብቻ ናቸው ለማለት የሚያስችል የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 98,99,106 | 46613 | ወ/ሮ ኑኑ ሽህሞሎ<br>እና<br>ወ/ሮ አሰገደች ጫኔ | ሰኔ 24/2002 | 79 |
| 34 | በተከራካሪ ወገኖች ዳኝነት የተጠየቀበትን ጉዳይ ፍ/ቤቶች በግልፅ በመቀበል ወይም ባለመቀበል ወሣኔ ሊሰጡበት የሚገባ ስለመሆኑ | 51866 | ወ/ሮ ደጅይጥኑ አለማየሁ እና ወ/ሮ አዛለች ደበበ | ሐምሌ 2/200 | 81 |
| 35 | ከኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ ከጋብቻ በፊት በአንደኛ ተጋቢ በተደረገ ምዝገባ የተነሣ የቤት ዕጣው የወጣው ብሎም የቤት ሽያጭ ውል የተደረገው በጋብቻ ወቅት መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ለቤቱ መገኘት ምክንያት የሆነው ተጋቢ ቤቱ የግል መሆን አለበት በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(2) | 51893 | እንዳልካቸው ዘለቀ<br>እና<br>ወ/ሮ ብዙዓለም መንግስቱ | ሐምሌ 8/2002 | 83 |
| 36 | በፍ/ቤት የተሰጠ የኑዛዜ ወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የውርስ ሃብት ማጣራት ሳይደረግ የተሰጠ ነው በሚል ምክንያት ብቻ ሊሰረዝ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ | 50836 | ወ/ሮ ቅድስት ተካ<br>እና<br>ወ/ሮ የኔነሽ ተካ | ሐምሌ 13/2002 | 85 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 37 | ከውርስ ሃብት ክፍፍል ጋር በተያያዘ ተጠቃሚው በኢንሹራንስ ውል ላይ ባልተገለፀበት ጊዜ የሟች ባል ወይም ሚስት የኢንሹራንስ ገንዘቡን ከወራሾች ጋር ሊካፈሉ የሚችሉበት አግባብ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 705,701(1)(ሀ)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 827 | 44561 | ወ/ሮ ገነት በላይ<br>እና አቶ ያፌት ተክሉ | ሐምሌ 28/2002 | 87 |
| 38 | ከውርስ ሃብት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የውርስ ሃብቱን በእጅ አድርጉ በመገልገል ላይ ያለ ተከራካሪ የሆነ ወራሽ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት በጋራ ይዞ የቆየ ሰው ላይ የሚያነሳው የውርስ ጥያቄ በይርጋ ታግዷል ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ | 44025 | እነ ወ/ሪት ፀሐይ ሐይሌ (አራት ሰዎች) እና ወ/ሮ ፈልቃ ቤኛ | ሐምሌ 22/2002 | 95 |
| 39 | ወራሽ የሆነ ወገን በውርስ ሃብት ክፍፍል ድርሻው ላይ ከሩብ የበለጠ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን በመግለፅ አውራሽ ባደረገው ኑዛዜ መሠረት ክፍፍል እንዳይፈፀም መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1123(1) | 47622 | ወ/ሮ ትዕግስት ነጋሽ እና እነ ወ/ሮ መንበረ ስላሴ ተኸሌ<br>(አምስት ሰዎች) | ሐምሌ 30/2002 | 97 |
| 40 | የምትክ ወራሽነት ተጠቃሚዎችን ስለመለየት<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 842,843,844(3) | 45587 | እነ ወ/ሮ አተረፈች ዘውደ<br>(ሁለት ሰዎች)<br>እና አቶ ዘውዱ ወሰኔ | ሐምሌ 29/2002 | 100 |
| 41 | በተዘዋዋሪ መንገድ ተወላጅን ከውርስ ያለ በቂ ምክንያት መንቀል የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 938,842,915 | 42546 | አቶ ተስፋልደት ኪዳኔ<br>እና እነ ወ/ሮ ዘሀቡ ይመር<br>(ሦስት ሰዎች) | ሐምሌ 28/2002 | 103 |
| | **ውል** | | | | 107 |
| 42 | በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ እስከ አሥር ዓመት ድረስ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058 | 44800 | አቶ አብዱራዛቅ ሐሚድ እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ጥቅምት 05/2002 | 108 |
| 43 | ውል በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነትና የመተማመን ግንኙነት መሠረት በማድረግና ጉዳዮቹ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ሥርዓት በመከተል በቅን ልቦና ሊተረጐም የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1732(1) | 42897 | አቶ አየለ ሐብተየስ እና እነ ሚ/ር ኖቼራ ጃካርሎ<br>(ሁለት ሰዎች) | ህዳር 10/2002 | 110 |
| 44 | ለጨረታ ማስከበሪያ በሚል የሚያዝ ገንዘብ ጨረታውን ባዘጋጀው አካል ሊወሰድ የሚችለው ተወዳዳሪው ጨረታውን ባሸነፈው መጠን ሆኖ በጨረታው መሠረት ውል ለመፈፀም ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ | 40947 | አቶ መዝገቡ መድህኔ እና<br>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር | ህዳር 15/2002 | 113 |
| 45 | ተከራካሪ ወገኖች ባላነሱበት ሁኔታ ፍ/ቤት የውል አፃፃፍ ሥርዓትን (ፎርማሊቲን) መሠረት በማድረግ በግራ ቀኝ ወገኖች መካከል የተካሄደን ውል ፈራሽ ነው በሚል የሚሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723,1808(2) | 43825 | የህፃን ኮከቤ ተረፈ ሞግዚትና አስተዳዳሪ እና እነ አቶ አያሌው ካሳዬ<br>(ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 6/2002 | 115 |
| 46 | • የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2026(1) ለባንኮችና ለደንበኞቻቸው መብት ልዩ ጥበቃ የሚያደርገው የፍ/ብ/ሀ/ቁ. 2473(2) ድንጋጌ ዋጋ በሚያሳጣ መንገድ ተፈፃሚ ሊሆን የማይገባ ስለመሆኑ<br>• የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2026(1) በባንኮችና በሌሎች አበዳሪ ተቋማት እና ደንበኞቻቸው መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተፈፃሚነት የሌለው የህግ ድንጋጌ ስለመሆኑ<br>• ባንኮች ለደንበኞቻቸው ያበደሩትን የብድር ወለድ ያልተከፈለ መሆኑን በሰው ምስክር፣ የሰነድና ሌላ ማስረጃ በማቅረብ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(1) ስር የተደነገገውን የህሊና ግምት ለማስተባበል የሚችሉ ስለመሆኑ | 29181 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>አቶ ልየው ቸኮል<br>(ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 20/2002 | 117 |
| 47 | በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 2024/ረ/ መሰረት እንደተከፈለ ሊቆጠር የሚችለው በብድር የተሰጠ ገንዘብ ሳይሆን የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ ክፍያ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 | 35758 | እነ አቶ ገብረመድኅን አየናቸው (ሁለት ሰዎች)<br>እና አቶ ሰብስቤ ኃይሌ | ታህሣሥ 20/2002 | 123 |
| 48 | የወለድ አግድ ውል ህጋዊ ነው ሊባል የሚችለው የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ መቋቋምን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን በመከተል የተደረገ እንደሆነ ስለመሆኑና በዚህ መሰረት ያልተደረገ መሆኑ ውሉን ፈራሽ ሊያደርገው የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3118,3045,3052 | 45422 | እነ አቶ ፈታኒ ባየህ<br>(ሰባት ሰዎች)<br>እና እነ ወ/ሮ አስራት ባየህ<br>(ሦስት ሰዎች) | ጥር 13/2002 | 127 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 49 | የስልክ አገልግሎት ከማግኘት ጋር በተያያዘ በአገልግሎት የክፍያ መጠን ላይ በአገልግሎት ሰጪውና በአገልግሎት ተቀባዩ መካከል አለመግባባት በተፈጠረ ጊዜ የተጠየቀው የአገልግሎት ሒሳብ በእርግጥም ስልኩን በይዞታው ስር አድርጐ የሚጠቀምበት ወገን በተገለገለው መጠን የተመዘገበ ስለመሆኑ በባለሙያ እንዲጣራ በማድረግ እልባት መስጠት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1732 | 48967 | አቶ ሳዲቅ ሐሰን<br>እና<br>የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን | ሰኔ30/2002 | 130 |
| 50 | መዋዕለ ነዋይን በማፍሰስ ግንባታን ለማካሄድ የከተማ ቦታን ከመንግስት ተረክቦ ግንባታን በተገቢው ጊዜ ለማጠናቀቅ አለመቻል ሊያስከትል የሚችለው ውጤት<br>የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ደንብ ቁ. 41/97 አንቀፅ 8(3)<br>የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ አዋጅ ቁ. 51/94 | 46052 | ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዩርጊስ<br>እና<br>የቦንጋ ማዘጋጃ ቤት ከፋ ዞን | ጥር 19/2002 | 133 |
| 51 | ከቤት ኪራይ ውል ጋር በተያያዘ የኪራይ ውልን ለማቋረጥ በቂ ናቸው ሊባሉ የሚችሉ ተከራይ የሚፈፅማቸው የግንባታ አይነቶች<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2953,2954,1732 | 46394 | ወ/ሮ ስንቄ መስፍን እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | የካቲት 11/2002 | 136 |
| 52 | ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገኖች ወለድን አስመልክቶ በውላቸው ካመለከቱት ሃሳብ ውጪ የራሱን ስሌት መሠረት በማድረግ ውሣኔ መስጠት ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ/. 1731,2478 | 45559 | የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ (አ.ማ)<br>እና እነ የአቶ ኃይሉ ፈይሳ ወራሾች<br>(ሁለት ሰዎች) | የካቲት 25/2002 | 138 |
| 53 | ከሽያጭ ጋር በተያያዘ ውል ሲመሰረት ጉድለት የነበረበት መሆኑ ቢረጋገጥም ከውሉ መመስረት በኋላ በተሸጠው ንብረት ላይ ተዋዋይ ወገኖች ተጨማሪ ግንባታ ያካሄዱና ወደ ነበሩበት ለመመለስ አዳጋች ሁኔታ ያለ መሆኑ ከታመነ ውሉ ሊፀና የሚገባው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1817(1) | 47800 | ወ/ሮ እመቤት ደርበው እና አቶ ታደሰ ሰዳማ | የካቲት 25/2002 | 140 |
| 54 | ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚቆጠር የኪራይ ውል አከራይ የሆነ ወገን ለተከራይ ማስታወቂያ በመስጠት ምክንያቱን መግለፅ ሳያስፈልገው የኪራይ ውሉን ሊያቋርጥ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966(1) | 40336 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና<br>የወ/ሮ አሰገደች ካሣሁን ወራሽ ሄኖክ ሣሙኤል | መጋቢት 22/2002 | 142 |
| 55 | በሌላ ሰው ድካም ወይም የሌላ ሰው ሃብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አላግባብ ጥቅም ባገኘበት መጠንና ባደረሰው ጉዳት መጠን ኪሣራ ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2162 | 43881 | ወ/ሮ ፎዚያ ሁሴን እና አቶ ውብሸት ተ/ወልድ | መጋቢት 10/2002 | 144 |
| 56 | ከሳሽ የሆነ ወገን ክስ ለማቅረብ ምክንያት የሆኑትን ሁሉ በአንድ ላይና በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ለመክሰስ የሚችል (የሚገባው) የነበረ ቢሆንም ሊጠይቅ ይገባው ከነበረው ቀንሶ ያቀረበው በፍ/ቤት ፈቃድ የሆነ እንደሆነ የቀረው መብት ላይ በድጋሚ ክስ ለመመስረት የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(4) | 43992 | እነ አቶ ይልማ አንበሴ (አራት ሰዎች)<br>እና እነ ወ/ሮ እመቤት መንገሻ<br>(አምስት ሰዎች) | መጋቢት 6/2002 | 146 |
| 57 | ከሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ሻጭ የሚያቀርበው የውል ይፍረስልኝ ክስ ገዥ ውል እንዲፈፀምልኝ በሚል ሊያቀርብ የሚችለው አቤቱታ ላይ የሚቆጠረውን የይርጋ ጊዜ የሚያቋርጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845,1851 | 43636 | ወ/ሮ አልማዝ ተሰማ<br>እና<br>እነ አቶ በየነ ወ/ሚካኤል<br>(ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 22/2002 | 150 |
| 58 | የኪራይ ውልን መሠረት በማድረግ ቤትን የያዘ ወገን የኪራይ ውሉን በቅድሚያ ሣያስፈርስ የባለቤትነት ጥያቄን መሠረት በማድረግ በኪራይ ውሉ አልገደድም በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | 46947 | አቶ ዘነበ ኃ/ማሪያም እና እነ ወ/ሮ አባይነሽ ዘለቀ<br>(ሦስት ሰዎች) | መጋቢት 7/2002 | 152 |
| 59 | ከእጅ በእጅ ሽያጭ ጋር በተያያዘ ገዢ የሽያጩን ዋጋ የከፈለበትን ደረሰኝ ይዞ መገኘቱ የገዛውን ንብረት እንደተረከበ የሚያሳይ የመጨረሻ (conclusive) ማስረጃ ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2266,2278(1) እና (2) | 45545 | ወ/ሮ ሸዋዬ ኑርዬ<br>እና<br>ምን አዩ ኃ/የተ/የግል ማህበር | መጋቢት 22/2002 | 154 |
| 60 | በፍ/ብሔር ጉዳይ ህጋዊ ጥበቃ ሊደረግለት የሚችል ዋስትና የሚደረግበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1922 | 47971 | ወ/ሮ ጅቦኒ ቱና እና ወ/ሮ ብርቂ ኢርክታ | ሚያዝያ 5/2002 | 157 |
| 61 | ከኪራይ ውል ጋር በተያያዘ ተከራይ የሆነ ወገን የተርን ኦቨር ታክስ የመክፈል ግዴታ በህግ የተጣለበት እንደሆነ አከራይ የሆነው ወገን ይህንኑ ክፍያ ለመፈፀም ይቻል ዘንድ ተከራዩን ለመጠየቅ ስለመቻሉ<br>አዋጅ ቁ. 308/95 አንቀፅ 2(3,5,7,8,9,12),6 | 48358 | አቶ ብርሃነ ገብረሐይሉ<br>እና<br>አንሲዩን ኮንትር ላፋም | ሚያዝያ 7/2002 | 159 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 62 | • አንድ ሰው ብድሩን አለመክፈሉን አምኖ በሚከራከርበት ሁኔታ የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 2024(ረ) ተፈፃሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ<br>• 2024(ረ) ዋና ብድርን ሣይሆን ለብድር የሚከፈል ወለድን የሚመለከት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(ረ) | 44691 | አቶ ሽባባው ወሌ<br>እና<br>አቶ ሙሉጌታ ዓባይ | ሚያዝያ 8/2002 | 161 |
| 63 | አንድ ውል ህግን የሚፃረር /የሚቃረን/ ነው በሚል እንዲፈርስ የሚቀርብ ጥያቄ በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 | 48094 | እነ ሙና እንድሪስ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ልማት ባንክ | ግንቦት 10/2002 | 163 |
| 64 | በአሰሪና ሠራተኛ መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት አሰሪው ሠራተኛው በውጭ አገር ትምህርቱን እንዲከታተል ለማስቻል የሚያስፈልጉ ወጭዎችን ደመወዝን ጨምሮ ለመክፈል ሠራተኛው ደግሞ ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ አሠሪውን ለማገልገል ውል ገብቶ ሠራተኛው ግዴታውን ለመፈፀም ያልቻለ በሆነ ጊዜ አሠሪው የጉዳት ኪሣራ የመጠየቅ / የመክፈል/ መብት ያለው ስለመሆኑ | 49453 | የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት እና አቶ ተፈሪ ማሞ | ግንቦት 19/2002 | 166 |
| 65 | የሽያጭ ውል በህግ የተቀመጠውን የአፃፃፍ ሥርዓት ባለመከተሉ ፈራሽ ሲሆን ንብረት የመመለስ ግዴታ ያለበት ወገን ንብረቱን ለውጦ ወይም በንብረቱ ላይ ወጪ አውጥቶ ከሆነ ባወጣው ወጪ መጠን ሊጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1818 | 49326 | ወ/ሮ እታፈራሁ ኃ/ማሪያም እና እነ መምህር በቀለ ታችበሌ<br>(ሁለት ሰዎች) | ሰኔ 28/2002 | 168 |
| 66 | በፍ/ብሔር ጉዳይ (ክርክር) የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ/. 1846 | 42700 | የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት እና  አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ | ሐምሌ 12/2002 | 170 |
| 67 | የእቁብ ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ በይርጋ ደንብ የሚገዛ እንጂ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2024 ሥር በተመለከተው የህሊና ግምት የሚሸፈን ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 | 46019 | የአቶ ደሣለው ፋንታ ወራሾች<br>እነ ሙሉጌታ ደሣለው እና አየለ ደበላ | ሐምሌ 20/2002 | 173 |
| 68 | አንድ የስጦታ ውል በኃይል ወይም በተንኮል ተግባር ተደርጓል በሚል ስለሚፈርስበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2442(3),1698,1699,1704,1706 | 49900 | እነ ወ/ሮ ሐመልማል ዓለሙ(ሁለት ሰዎች)<br>እና ወ/ሮ ሀረገወይን ዘለቀ | ሐምሌ 19/2002 | 176 |
| | **አፈፃፀም** | | | | 180 |
| 69 | የውርስ ንብረት በጨረታ እንዲሸጥ ለማድረግ መነሻ ዋጋን ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1083,1084 | 43888 | አቶ ፀሐይ ወንድም እና እነ አቶ አያለው መለስ (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 23/2002 | 181 |
| 70 | አንድ ተጋቢ በግሉ ያመጣው ዕዳ ከሌለኛው ተጋቢ የጋራ ንብረት እንዲከፈል የሚደረገው ዕዳውን ያመጣው ተጋቢ ዕዳውን ለመክፈል አለመቻሉ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>የደቡ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ እና የፌዴራል መንግስት የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ | 39837 | አቶ ስመንጉስ አሰፋ<br>እና<br>መ/ት ምህረት ክበበው | ግንቦት 3/2002 | 183 |
| 71 | አንድ ንብረት በፍርድ አፈፃፀም የተነሣ ሊያዝ የሚችለው በተሰጠው ፍርድ ባለዕዳ የሆነው ወገን ሃብት መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ | 46143 | ወ/ሮ ድልበኔ ራሕመቶ እና እነ የባህር ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት(ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 2/2002 | 185 |
| | **ወንጀል** | | | | 187 |
| 72 | የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የንግድ ድርጅት ሠራተኛ፣ ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም ድርጅቱ በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦባቸው ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀፅ 56(1)(3)<br>አዋጅ ቁ. 609/2001 አንቀፅ 50(ለ)(1),22(1)<br>የወንጀል ህግ አንቀፅ 23(3),34(1) | 48850 | እነ አቶ ታረቀኝ ገ/ጊዮርጊስ<br>(ሦስት ሰዎች)<br>እና<br>የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ታህሣሥ 8/2002 | 188 |
| 73 | በግድያ ወንጀል የተከሰሰ ሰው የፈፀመው የግድያ ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1) (ሀ) ሥር የሚያስጠይቅ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ<br>የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1)(ሀ),84,86 | 45927 | የኦሮሚያ ክልል ዓቃቤ ሕግ<br>እና<br>መሰረት መኮንን | ጥር 19/2002 | 191 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 74 | በወንጀል ጉዳይ የቀረበ ክስ በዐቃቤ ህግ ምስክሮች ተሟልቶ አለመቅረብ የከሳሽ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብት ተጠብቆ መዘጋት በቀረበው ወንጀል ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን የይርጋ ጊዜ ተግባራዊ ከመሆን የሚያግደው ስላለመሆኑ | 45572 | ወ/ሮ ዘነበች ሽብሩ እና ፌ/ዐ/ህግ | የካቲት 26/2002 | 194 |
| 75 | ህጋዊ መካላከልን ከመጠን በማሳለፍ የተፈፀመ የሰው መግደል ተግባር በወንጀል ህግ ቁጥር 541(ሀ) የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 540, 541 | 43501 | እነ ረዳት ሳጅን ሺጋ ተካ ሞላ (ሦስት ሰዎች) እና የኦሮሚያ ክልል ዓ/ሕግ | መጋቢት 15/2002 | 195 |
| 76 | በወንጀል ሕግ ቁጥር 543 እና 567 መሰረት አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ሊጠየቅ ስለሚችልበት አግባብ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543,567 | 44235 | ቂስ ጌታቸው ተሾመ<br>እና ዓቃቤ ሕግ | መጋቢት 28/2002 | 199 |
| 77 | አንድ ሰው የማታለል ተግባር ፈፅሟል በሚል በወንጀል ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 692(1) | 46189 | ሐረገወይን ተፈራ እና ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ | ሚያዝያ 20/2002 | 201 |
| 78 | ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ የዘወትር ፀባይ መልካም የነበረ መሆኑ በተናጠል (በራሱ) ቅጣትን ለማቅለል የሚያስችል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 82(1) (ሀ) | 53612 | እነ አቶ ፍስሐ ዓባይ(ሁለት ሰዎች) እና የገቢዎችና ጉምሩክ ዓ/ህግ | ሚያዝያ 25/2002 | 203 |
| 79 | በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ከተሰጠ በኂላ ወንጀለኛው በይቅርታ የተለቀቀ መሆኑ አስቀድሞ የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ እንዳልነበረ የሚያስቆጥር (በሪከርድነት እንዳይያዝ የሚያደረግ) ስላለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 230 | 41248 | ቡርቂሶ ዋቶ<br>እና<br>ዐቃቤ ሕግ | ሰኔ 23/2002 | 206 |
| 80 | በሥር ፍ/ቤት የተሰጠ የቅጣት ውሣኔ ላይ አነሰ ወይም በዛ በሚል በግልፅ ይግባኝ ባልተጠየቀበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅጣትን ከፍ ወይም ዝቅ በማድረግ ውሣኔ ሊሰጥ የማይገባ ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(መ) | 48617 | ተስፋዬ አደላ<br>እና<br>ዐቃቤ ሕግ | ሰኔ 18/2002 | 208 |
| 81 | • ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተከራካሪ ወገኖች የማስረዳት ሸክማቸውን ተወጥተዋል ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>• በፍ/ቤት ፊት ቃለ- መሃላ በመፈፀም የተሰጠ የምስክር ቃል እውነት ነው በሚል የሚወሰደው ግምት ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 111 | 51706 | አቶ ግርማ ትኩ<br>እና<br>የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | ሐምሌ 21/2002 | 210 |
| | **ንብረት** | | | | 218 |
| 82 | የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ ተስጥቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3041,3052 | 38681 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እማሆይ ፀሐይቱ አምበሉ | ጥቅምት 3/2001 | 219 |
| 83 | ለረጅም ጊዜ በመንግስት ቁጥጥር ሥር የነበረ ቤትን ይለቀቅልኝ በሚል አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተፈቀደለት ስለመሆኑ ወይንም ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሳኔ አግኝቶ ባለመብትነቱን ሳያረጋግጥ የሚያቀርበው ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 47/67 | 45161 | እነ እናኑ ጆንበሬ<br>(ሁለት ሰዎች)<br>እና የደሴ ከተማ ቀበሌ 03 ጽ/ቤት | ታህሣሥ 24/2002 | 222 |
| 84 | የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ የመፋለም ክስ በይርጋ ቀሪ ነው (ቀሪ ሆኗል) ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1677,1845,1206,1188-1192 | 43600 | ዳዊት መስፍን<br>እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ጥር 05/2002 | 224 |
| 85 | የአዋጅ ቁጥር 47/67 በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጠን ካርታ መሰረት በማድረግ ክሥ ለመመስረት የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 47/67 | 48699 | አቶ አምሣለ ጀመሪ<br>እና አቶ ፍርዱ ገበያሁ | ሚያዝያ 21/2002 | 228 |
| 86 | በአንድ ቤት ውስጥ ሲኖር ያልነበረ ወይም ቤቱን በእጁ አድርጐ ሲያዝበት ያልነበረ ሰው የሚያነሣው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149 | 43081 | አቶ ሣሙኤል ጦኖሮ እና እነ ወ/ሮ አይሻ አርጌሳ (አራት ሰዎች) | ግንቦት 6/2002 | 231 |
| 87 | በሃይል ቤቱ ተይዞብኛል እንዲለቀቅልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ነው ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1206,1149 | 42861 | ወ/ሮ አጤነሽ አበበ<br>እና<br>አቶ ማንተጋፋቶት አጥላው | ሰኔ 28/2002 | 233 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 88 | • አንድን ንብረት በአደራ ለማስተደደር (ለመጠበቅ) የተረከበ ወገን አደራ ሰጪው ንብረቱ እንዲመለስ በጠየቀው ጊዜ ወዲያውኑ መመለስ ያለበት ስለመሆኑ<br>• ንብረትን በአደራ የሰጠ ወገን ንብረቱ እንዲመለስለት ከመጠየቅ ጋር በተያያዘ በህግ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ (ይር.ጋ)የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2781 (1)(2),2779, 2989(1) | 48048 | ወ/ሮ ገብርኤላ ኒካላ ቶማስ ናክሶ<br>እና<br>የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ሐምሌ 22/2002 | 235 |
| 89 | ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ የጉዳት ኪሣራን ጉዳት ለሚደርስበት ወገን በመክፈል የመንገድ መተላለፊያ ( servitude right) መብት ሊከበር የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1221 | 48783 | ወ/ሮ ሶፊያ ሁሴን እና እነ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት<br>አስተዳደር (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 27/2002 | 237 |
| | **ከውል ውጭ ኃላፊነት** | | | | 239 |
| 90 | የጉዳት ኪሣራ የሚከፈለው ጉዳት ስለመድረሱ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2090,2091 | 39601 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና<br>ገዛኸኝ መንግስቱ | ጥቅምት 5/2002 | 240 |
| 91 | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ገቢ ያልነበረው መሆኑ በርትዕ ሊከፈለው የሚገባውን ካሣ የሚያስቀር ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102 | 42962 | አቶ አየለ አድማሱ<br>እና<br>አቶ አጀቡ ሹሜ | ታህሣሥ 28/2002 | 242 |
| 92 | በወንጀል ጉዳይ ተከስሶ ጥፋት የሌለበት መሆን በራሱ በተመሳሳይ ጉዳይ በፍትሐብሔር ከቀረበ ክስ ነፃ ለመውጣት እንደ በቂና የመጨረሻ መስፈርት የሚወሰድ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2149 | 43843 | ዶ/ር ተስፋነሽ በላይ<br>እና<br>አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ | መጋቢት 21/2002 | 244 |
| 93 | ለተወሰነ ጊዜም ሆነ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛ ከውል ውጭ በሆነ ግንኙነት በሥራ ወቅት በሌሎች ሰዎች ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት አሠሪ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2130, 2131, 2132 | 45735 | አቶ ደረጀ ቸርነት<br>እና<br>ወ/ሮ ሕይወት የኃላሸት | መጋቢት 21/2002 | 247 |
| 94 | በአሰሪና ሠራተኛ ክርክር ችሎት ሠራተኛው የፈፀመው ድርጊት ከሥራ ለማሰናበት በቂ አይደለም ተብሎ መወሰኑ አሰሪው በሠራተኛው ላይ በፍ/ብሔር ጉዳይ ሊያቀርብ የሚችለውን ክስ የሚያስቀር የመጨረሻ ፍርድ /ውሣኔ/ ስላለመሆኑ | 44588 | የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እና<br>እነ ኃይለየሱስ ቱኪ<br>(አራት ሰዎች) | ሚያዝያ 4/2002 | 251 |
| 95 | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ህይወቱ ካለፈ ሰው ጋር በተገናኘ የሚከፈለው የጉዳት ካሣ መብቱን የሚጠይቀው ሰው ዕድሜ ከአስራ ስምንት ዓመት በላይ በመሆኑ የተነሣ ብቻ ካሳው ሊከፈለው አይገባም ለማለት የሚያስችል የሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2095/1/ | 50225 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>እነ ወ/ት ዝናሽ አሰፋ<br>(ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 5/2002 | 253 |
| | **የዳኝነት ስልጣን** | | | | 255 |
| 96 | የአ.አ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ደብተርን ለመሰረዝ የሚያስችል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ | 34665 | እነ አቶ ናትናኤል ዘውገ (ሁለት ሰዎች)እና እነ ወ/ሮ እግዜሩ ገ/ህይወት(ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 12/2002 | 256 |
| 97 | የከተማ ቦታ ያለአግባብ ተወስዶብኝ በሊዝ ለሌላ ተሰጥቷል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የቦታውን መውሰድ ውሣኔ ለሰጠው አካል በቅድሚያ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑና በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ለቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ ያለበትና ይኼው አካል የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 272/1994 | 46220 | የደቡብ ክልል የሐዋሣ ከተማ ማዘጋጃ ቤት<br>እና የሐዋሳ ደብረ ምህረት ቅ/ገብርኤል ገዳም | ጥር 18/2002 | 258 |
| 98 | በውጪ አገር ሕግ መሰረት የተቋቋመና በኢትዮጵያ ውስጥ ያልተመዘገበ የንግድ ድርጅት ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት በኢትዮጵያ ፍ/ቤት ቀርቦ ሊዳኝ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 27(1), አዋጅ 25/88 አንቀጽ 11(2)(ሀ) | 42928 | የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና ድራጋዶስ ኮንስትራክሽን | ጥር 12/2002 | 260 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 99 | በብልጫ የተከፈለ የቀረጥ ገንዘብ ለባለገንዘቡ ሊመለስ የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 53(1),55 | 42866 | ብርሃነ ጥዑም እና የጉምሩክ ባለስልጣን | መጋቢት 20/2002 | 262 |
| 100 | የሥራ መደብ ወይም እድገት ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የወል የሥራ ክርክርን የሚመለከት ስለመሆኑ | 48111 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ቂጤሳ ገብሬ | ሚያዝያ 13/2002 | 265 |
| 101 | በውድድር አሸንፌ ያገኘሁትን የሥራ መደብ እድገት ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ የሥራ ክርክር የግል የሥራ ክርክር በመሆኑ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ የሚታይ ሰላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 | 52600 | የኢትዮጵያ ቆዳ አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ ኃይሌ | ሚያዝያ 12/2002 | 267 |
| 102 | የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች በከተማው የሚገኝ ቤት ባለቤትነቱ የማን ነው ከሚል ጉዳይ ጋር ተያይዞ የሚነሣ ክርክርን ለማየት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 416/19 አንቀፅ 33 | 47134 | የድሬዳዋ አስተዳደር ቀበሌ 06 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ፋንታዬ ምትኩ | ግንቦት 6/2002 | 269 |
| 103 | • የክርክሩ የገንዘብ መጠን ከ5000 ብር በታች የሆነ ጉዳይን በሙሉ ተቀብሎ ለማስተናገድ የአዲስ አበባ ከተማ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች በሕግ ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ<br>• የሥረ-ነገር ሥልጣን በሕግ ባልተሰጠው የዳኝነት አካል (ፍ/ቤት) የተሰጠ ፍርድ የማይፀና ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(6),5(9)<br>አዋጅ ቁ. 361/95 | 52041 | የእርሻ መሣሪያዎችና የቴክ/አ/ማህበር<br>እና<br>የኢት/መድን ድርጅት | ሰኔ 29/2002 | 272 |
| 104 | በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ የንግድ ማህበር (ድርጅት) ጋር በተያያዘ የሚነሣ ክርክርን ለማስተናገድ ስልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 5(6) | 43912 | አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና እነ የአቶ ኢብራሂም ሙሣ ወራሾች (ሁለት ሰዎች) | ሰኔ 15/2002 | 274 |
| 105 | በሰዎች ወይም በሚንቀሳቀስ ሀብት ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሣ ለማግኘት የሚቀርብ ክስን ለማስተናገድ የግዛት ክልል ሥልጣን ስለሚኖረው ፍ/ቤት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 27 | 48018 | አቶ ተከተል ዘካሪያስ እና እነ ወ/ሮ አስቴር ታደሰ(ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 7/2002 | 276 |
| 106 | በሸሪአ ፍ/ቤት በሚካሄድ ክርክር ላይ ጣልቃ ገብቶ መከራከር በፍ/ቤቱ ለመዳኘት ስምምነትን እንደመስጠት የሚያስቆጥር ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 188(92) አንቀፅ 5(1) | 45806 | አቶ ፍፁም በረታ እና እነ ወ/ሮ ሶፊያ ዱላ(አራት ሰዎች) | ሐምሌ 8/2002 | 278 |
| 107 | • በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ እጅግ አስፈላጊ የህዝብ አገልግሎት ድርጅቶች ተብለው ከተዘረዘሩት ተቋማት ጋር ተያይዞ የሚቀርብ የሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅም ጥያቄን የያዘ የውል የሥራ ክርክር ካልሆነ በስተቀር የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ለማስተናገድ የሥረ- ነገር ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ<br>• መሰል ጉዳዬችን ለማየት በህግ ስልጣን የተሰጠው በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚሰየም ቦርድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 466/97 አንቀፅ 2(2)<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 142(1)(ሀ),(2),(3),136(2) | 49152 | የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት መሠረታዊ ሠራተኛ ማህበር<br>እና<br>የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት | ሐምሌ 7/2002 | 282 |
| | **ባንክና ኢንሹራንስ** | | | | 286 |
| 108 | በብድር ለተሰጠ ገንዘብ በመያዣነት የተያዘ ንብረት መድን የተገባለት ሆኖ አደጋ የደረሰበት እንደሆነ አበዳሪው ንብረቱን በመያዣ የያዘበት ብድር ዋጋ ዋስትና ከተገባለት የገንዘብ መጠን ያነሰ እንኳን ቢሆን መድን ሰጪው እንዲከፍለው ሊጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2858 | 38572 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ጥቅምት 17/2002 | 287 |
| 109 | ባንክ በመያዣ መልክ የያዘውን የተበዳሪ ንብረት በአዋጅ ቁ. 97/90 መሠረት በመሸጥ ላይ እያለ በሌላ በኩል ደግሞ በተበዳሪው ላይ በፍ/ቤት ክስ መስርቶ ዕዳው እንዲከፈለው ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ | 44164 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>አቶ ሐሰን ኢብራሂም | ታህሣሥ 8/2002 | 290 |
| 110 | የኢንሹራንስ ውልን መሠረት በማድረግ የሚቀርብ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 674(1),754(1) | 46778 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ | የካቲት 24/2002 | 293 |
| 111 | የመድን ሰጭ ኃላፊነት በመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን ሊበልጥ የማይችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 665(2) | 46808 | አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ እና ወ/ሮ ጫልቱ ሚደግሳ | ሚያዝያ 6/2002 | 295 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 112 | ለአንድ ንብረት መድን የገባ ሰው በንብረቱ ላይ የደረሰው ጉዳት ሙሉ ውድመት ሲባል የሚችል ቢሆንም ካሣ ሊከፈለው የሚችለው ጉዳት በደረሰ ጊዜ ዕቃው ከሚያወጣው ዋጋ ሳይበልጥ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 678 | 48698 | አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ<br>እና<br>አቶ ሣሙኤል አለሙ | ግንቦት 19/2002 | 297 |
| 113 | መድን ሰጪ የሆነ ወገን በመድን ገቢው እግር በመተካት ባለዕዳ የሆነ ወገን ላይ ጥያቄ ባነሣ ጊዜ ባለዕዳው ከመድን ገቢው ጋር የሚፈጠር አለመግባባትን ከፍርድ ቤት ውጪ በሽምግልና ለመጨረስ የተስማማን በመሆኑ መድን ሰጪው በፍርድ ቤት ክስ መስርቶ ሊጠይቅ አይችልም በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 683(1) | 39902 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ | ሰኔ 18/2002 | 300 |
| 114 | አስቀድሞ የተደረገ ነገር ግን ባለመታደሉ ምክንያት የተቋረጠ (ያበቃ)ን የመድን ውል መሠረት በማድረግ ሊጠየቅ የሚችል የጉዳት ካሣ ስላለመኖሩ<br>የንግድ ህግ ቁ. 666(2) እና (3) | 52910 | አቶ አንዳርጌ ታደሰ<br>እና<br>የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ሐምሌ 28/2002 | 302 |
| | **ጉምሩክ(ግብር)ታክስ** | | | | 304 |
| 115 | • የንግድ ቤቶችን የማከራየት እንቅስቃሴ ከታክስ ነፃ ከሆኑ ግብይቶች የማይመደብ ስለመሆኑ<br>• የንግድ ቤት ኪራይ የመክፈል ግዴታ ያለበት ወገን የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀፅ 8 | 39574 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ምልእተ ፀጋ ቢዘን<br>(ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 3/2002 | 305 |
| 116 | የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያልተከፈለን ቀሪ ቀረጥ ሊያስከፍል የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ.60/89 አንቀፅ 57(1),48,53(1) | 45882 | የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና እነ ወ/ሮ እጅጋየሁ አራምዴ (ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 6/2002 | 307 |
| 117 | የጉምሩክ አዋጅን በመተላለፍ ከሚፈፀም የወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ የኮንትሮባንድ ተግባር ሃይልን በመጠቀም ወይም ከሌሎች ጋር በማበር የተፈፀመ እንደሆነ አዋጅ ቁ. 60/89 ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ | 44862 | አሸናፊ አበበ እና የጉምሩክ ባለስልጣን | ጥር 5/2002 | 310 |
| 118 | የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ ወንጀል ፈፅሟል በሚል የተጠረጠረ ሰው ክስ ሲቀርብበት የሚገባውና ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዲሱ የወንጀል ህግ ሣይሆን በጉምሩክ አዋጆች መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 60/89 | 48693 | ነኢማ አወል እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ጥር 5/2002 | 312 |
| 119 | የንግድ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው የድርጅቱን አስተዳደራዊ ሥራ ለሌላ ሰው የወከለ መሆኑ ድርጅቱ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት በመፈፀም ወንጀል ጥፋተኛ በተባለ ጊዜ ከሚቀርብበት የወንጀል ተጠያቂነት ነፃ የማያደርገው ስለመሆኑ | 54061 | አቶ መስፍን ሽፈራው እና የኢትዮጵያ ገቢዎች ባለስልጣን | ሚያዝያ 26/2002 | 314 |
| 120 | • የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሕግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባሩን በተገቢው ጊዜና ሁኔታ ባለማከናወኑ በሌላ ሰው ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>• የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሕግ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት ግዴታውን ለመወጣት ሲንቀሳቀስ በቁጥጥሩ ሥር አድርጎት ከሚቆየው ንብረት ጋር በተያያዘ የተቋረጠ ጥቅም ወይም የጉዳት ካሣ ሊከፍል የሚችልበት የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ 60/98 አንቀጽ 6(5), 58,74<br>አዋጅ ቁ 368/95 አንቀጽ 78 | 49889 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ዛኪ ሰይድ | ሰኔ 28/2002 | 316 |
| 121 | የግብር ይግባኝ ጉባኤ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜና ስሌቱ<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 43(1) | 48621 | አቶ አብደላ ሁሴን ከለር<br>ላብራቶሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን | ሰኔ 30/2002 | 319 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ውክልና** | | | | 322 |
| 122 | ባንክ በሐዋላ ለማድረስ የተቀበለውን ገንዘብ ለተገቢው ሰው አልደረሰም በሚል ኃላፊነት አለበት ሊባል የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ እና የተለመደውን አሰራር ሳይከተል የቀረ እንደሆነ ወይም መጭበርበሩ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ | 48269 | አቶ ሽረፈዲን አብደ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | የካቲት 24/2002 | 323 |
| 123 | ወኪል የሆነ ሰው የውክልና ሥራውን በሚሰራበት ጊዜ የራሱን ወይም ከራሱ ጋር ቤተሰባዊ ወይም ሌላ ጥብቅ ግንኙነትና ትስስር ያለው ሰውና የወካዩ ጥቅም ሊጋጭ የሚችልበት አጋጣሚ እንዳይፈጠር መከላከል ያለበት ወይም በተፈጠረ ጊዜ አስቀድሞ ለወካዩ ማሳወቅ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1)2198,2208,2209 | 50440 | አቶ ሃብቱ ወልዱ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ መሰሉ ደስታ<br>(ሁለት ሰዎች) | ግንቦት 16/2002 | 325 |
| | **የንግድ ሕግ** | | | | 328 |
| 124 | • የእሽሙር የሽርክና ማህበር ተመስርቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>• በግለሰቦች መካከል በውል የሚፈጠር የሽርክና ማህበር የንግድ ሕግ በሚያዘው መሰረት አይነቱ ተለይቶ ተመዝግቦ የማይገኝ በሆነ ጊዜ እንደ የእሽሙር የሽርክና ማህበር ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ሕግ ቁጥር 211,212,219 | 46358 | ወ/ሮ ብርሃን ፀጋዬ እና እነ አቶ ሚካኤል ፋስሐ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 25/2002 | 329 |
| 125 | ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማህበር ሥራ አስኪያጅ የሆኑ ሰዎች ማህበሩን ሲያስተዳድሩ በሰሩት ያልተገባ ስራ ምክንያት በኃላፊነት ሊጠየቁ የሚችሉበት አግባብ<br>የንግድ ሕግ ቁጥር 580 | 39608 | ወ/ሮ አስቴር አርአያ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አምሳለ በላይ<br>(ሁለት ሰዎች) | የካቲት 11/2002 | 331 |
| | **አእምሯዊ ንብረት** | | | | 334 |
| 126 | አንድን መፅሐፍ ከተፃፈበት ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ የተረጐመ ሰው እንደ ድርሰት አመንጪ ተቆጥሮ የሞራልና የቁሣዊ ጉዳት ሊወሰንለት ስለመቻሉ<br>አዋጅ ቁ.410/96 አንቀፅ 2(2),6(1) | 44520 | አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት<br>እና<br>ዶ/ር ጌታሁን ሽብሩ | ጥቅምት 10/2002 | 335 |
| | **ልዩ ልዩ** | | | | 338 |
| 127 | ለዋስትና የተያዘ ገንዘብን የአስያዡን ማንነትን ማረጋገጥ እስከተቻለ ድረስ ገንዘቡን  ያስያዘበት ደረሰኝ ኮፒን ያቀረበ እንኳን ቢሆን የተያዘው ገንዘብ መመለስ ያለበት ስለመሆኑ | 53459 | አቶ ማሞ ገ/ማሪያም<br>ተጠሪ፡የለም | ሚያዝያ 12/2002 | 339 |
| 128 | • በአስፈፃሚ አካላት የሚወጡ የተለያዩ መመሪያዎች በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው የወጡ ወይም በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጁ አለመሆናቸው  ህጋዊ ውጤት እንዳይኖራቸው የሚከለክል ስላለመሆኑ<br>• አዋጅን መሠረት በማድረግ የወጡ መመሪያዎችን የሚፃረር ድርጊት መፈፀም በኃላፊነት ሊያስጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 83/86 አንቀፅ 39(2),1, 2, 59(1)(ሽ)<br>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁ. ሲቲጂ 001/97 | 43781 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ ዳንኤል መኮንን | ሐምሌ 14/2002 | 341 |
| 129 | • የሕግ ክርክሮችን በሰበር ማየት /ማስተናገድ/ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠ ስልጣን (power) ስለመሆኑ<br>• በግልግል ዳኝነት (arbitration) የታየ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተዋዋይ ወገኖች የይግባኝ መብትን ለማስቀረት የሚያደርጉት ስምምነት ጉዳዩን በሰበር ችሎት ከመታየት የማያግድ ስለመሆኑ (ከዚህ ቀደም በሰበር ችሎት የተሰጠው የሕግ ትርጉም የተለወጠ ስለመሆኑ፡፡)<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3 (ሀ), አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 (4), አዋጅ ቁጥር 25/88, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.  350(2) 351 እና 356 | 42239 | ብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኃ/የተ/የግ/ ኩባንያ እና<br>ዳን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ | ጥቅምት 20/2003 | 346 |

# ቤተሰብ

የሰ/መ/ቁ. 38544

ጥቅምት 05 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሴ

**አመልካች፡-** አቶ ብሩክ ኃ/እየሱስ - ጠበቃ ዘውዱ ወራሣ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ፋናዬ አበበ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብሔር ብሄረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በወናጐ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በዚሁ ፍርድ ቤት አመልካች የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ ከአሁኑ አመልካች ጋር የመሰረቱት ጋብቻ እንዲፈርስላቸው፣የጋብቻ ውጤት የሆነው ንብረትም ክፍፍሉ እንዲፈጸም የንብረቱን ዓይነትና ግምቱን ዘርዝረው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኂላ ጋብቻው እንዲፈርስ አድርጐ ንብረቱን በተመለከተም ተገቢ ነው ያለውን ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ውሣኔውም እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የስር ፍርድ ቤቶች በዲላ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ የሚታወቅ ዋና መኖሪያ ቤት የባልና ሚስት የጋራ መሆናቸው ስለተረጋገጠ ከስድስት ሰርቪስ ቤቶች ጋር ፍቺ ከተሰጠበት ጀምሮ የተገኘ ጥቅም እና ቤቶቹ ተሽጠው እንዲከፋፈሉ በማለት በሰጡት ውሣኔ ክፍል ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት መተዳደሪያችን ሆኖ ስለመዋዋላችን በ25/11/1987 ዓ.ም በተፃፈ የጋብቻ ውል ተገልጾ እያለና ተጠሪም ክስ ሲመሰርቱ የግል ሐብቴ ነው እሷን አይመለከታትም ብሎ የተዋዋለው ሐይለ ቃል ባለመኖሩ ቤቱ የጋራ ነው የሚል ዳኝነት ጠይቀው እያለ ከጋብቻ በፊት የተፈራውን ንብረት የባልና ሚስት የጋራ ነው በማለት መወሰኑ የደቡብ ብሔር ቤሔረሰቦችን ብሔራዊ ክልልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግን አንቀጽ 66 ድንጋጌና የተዋዋይ ወገኖችን ሐሳብና ፍላጐት ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመ ነው ተብሎ ሊሻር ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ተጠሪ ቀርበው ሐምሌ 17 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሳቸውን አቅርበዋል አመልካች በበኩላቸው መስከረም 11 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚገባ መልኩ መርምሮታል እንደመረመረውም በዲላ ከተማ ቀበሌ 02 የሚታወቅ ዋና መኖሪያ ቤት ከ6/ስድስት/ ሰርቪስ ቤቶች ጋር ፍቺ ከተሰጠበት እለት ጀምሮ ጥቅምና ቤቶቹ የባልና ሚስት የጋራ ሐብት ናቸው፤ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት አመልካችና ተጠሪ ጋብቻ ከመመስረታቸው በፊት የተሰራ መሆኑን በ25/11/1987 በተደረገው የጋብቻ ውል ቤቱን መተዳደሪያቸው በማድረግ መስማማታቸውን ነው፡፡

በመሰረቱ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው የሚያገኟቸው ንብረቶች በጋብቻ ዘመንም የግል ሆነው ይቀራሉ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት ንብረቶቹ በጋብቻ ውል የጋራ እንዲሆኑ ስምምነት ከሌለ ብቻ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ የሆነውን የጋብቻ ውሉ በሕግ ፊት ያለው ተፈፃሚነት ሣይሆን በጋብቻ ውሉ የተገለፀው "መተዳደሪያችን" የሚለው ቃል ቤቱ የጋራ ስለመሆኑ ባልና ሚስት መስማማታቸውን ያሳያል ወይስ አያሳይም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ አደረግን የሚሉት የጋብቻ ውል መተዳደሪያችን ብሎ ከሚገልፃቸው ንብረቶች ውስጥ ከአከራካሪው ቤት በተጨማሪ የአመልካች ደመወዝና ብር 10,000.00(አስር ሺህ) ጥሬ ገንዘብ ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ንብረቶች ለማንኛውም የቤተሰቡ ወጪ የሚውሉ መሆኑ ይታመናል፡፡ አመልካችና ተጠሪ ይህንኑ ጥሬ ገንዘብና ቤቱን እየተጠቀሙ ለአስራ አንድ ዓመታትም አንድ ላይ ኖረዋል፡፡ እንግዲህ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች እነዚህ ከሆኑና የጋብቻ ውሉ ይዘት ትርጉም አከራካሪ ከሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎችን የግራ ቀኙ ፍላጐት ምን እንደነበር መመርመር የግድ ይሏል፡፡

በመሰረቱ በውል ውስጥ የተጠቀሱት ቃላትና ድንጋጌዎች ግልጽ ባልሆኑ ጊዜ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1732፣1735-1738 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ስር በሰፈሩት ደንቦች መሰረት መተርጐም የተፈቀደ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ደንቦች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1734 እና 1736 ሲሆኑ ተዋዋዮች ውላቸውን ከመዋዋላቸው አስቀድሞ ወይም ከተዋዋሉ በኋላ የነበሩበትን ሁኔታዎች፣የፈጸሙትን ተግባር በማመዛዘንና ሐሣባቸውን ምን እንደነበር ለማወቅ መሞከር እና የውሎችን ቃሎች አንዱን ከአንዱ ጋር እያዛመዱ በመመልከት ለውሉ ጉዳይ አግባብ ያለውን ትርጉም መስጠት ተገቢ ስለመሆኑ ተጠቃሽ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካችና ተጠሪ በ25/11/1987 ዓ.ም አደረግን የሚሉት የጋብቻ ውል መተዳደሪያችን ብሎ ከሚገልፃቸው ንብረቶች ውስጥ ከአከራካሪው ቤት በተጨማሪ የአመልካች ደመወዝና ብር 10,000(አስር ሺህ) ጥሬ ገንዘብ ይገኙበታል፡፡ እንደሁም ይህንኑ ጥሬ ገንዘብና ቤቱን እየተጠቀሙ ለአስራ አንድ ዓመታትም አንድ ላይ ኖረዋል፡፡ በመሆኑም አመልካችና ተጠሪ የጋብቻ ውሉን በተዋዋሉበትና ከተዋዋሉ በኋላ የነበሩበት ሁኔታ እና ጥሬ ገንዘቡንም ለመተዳደሪያቸው አድርገው የተዋዋሉ መሆናቸው መተዳደሪያ የሚለውን ቃል በጋብቻ ውሉ የተጠቀሙበት አከራካሪውን ቤት የጋራ ከማድረግ ፍላጐት ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ትርጉም ሊሰጠው የሚገባው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከፍቺ በኋላ በቤቱ የተገኘ ጥቅምም ከጋራ ንብረት የተገኘ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ተጠሪ የማያገኙበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳይ ላይ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በወናጐ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 00372 ኅዳር 27 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 0279 የካቲት 07 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲሁም በደ/ብ/ብ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 21204 ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 39408

ጥቅምት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አርጋው አባቼ - ጠበቃ ደገፉ ምሶኔ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ አስቴር አበጋዝ ወራሾች - እነ ወ/ሪት ንግስት አርጋው (ስድስት ሰዎች)

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጋብቻን በፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተነሣውን የንብረት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የባልና ሚስት የጋራ ሐብት ነው ወይስ የባልየው የግል ንብረት? በሚል ክርክር ከተነሣባቸው ንብረቶች አንዱ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 20 ቀበሌ 45 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥር 629 የሆነው የመኖሪያ ቤት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ከሁለቱ ወገኖች የቀረበውን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ቤቱ ጋብቻው ከመመስረቱ በፊት አመልካች የሰራው የግል ሐብቱ ነው በማለት የወሰነ ሲሆን፣ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግን ቤቱ የተሰራው ከጋብቻ በኋላ (በጋብቻው ወቅት) መሆኑን በማስረጃ አረጋግጫለሁ በማለት ቤቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብት ነው ብሎአል፡፡ በመጨረሻ በይግባኝ ጉዳዩን ያየው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ጥር 15 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አከራካሪው ቤት ከጋብቻ በፊት የነበረ ንብረት ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት የተደረገው ክርክር እያሳየ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ቤቱ የአመልካች የግል ንብረት አይደለም በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራካሪው ቤት የአመልካች የግል ሃብት ነው በማለት ቢወስንም፤ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግን አልተስማማም፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት ቤቱ የተጋቢዎቹ የጋራ ሃብት ነው ለማለት የበቃው ቤቱ የተሰራው አመልካች እንደሚለው ከጋብቻ በፊት ሳይሆን፣ጋብቻው ከተመሰረተ በኋላ በ1966 እንደሆነ በከተማው አስተዳደር የሚገኘውን የቤቱን ማህደር አስቀርቤ አረጋግጫለሁ በማለት ነው፡፡ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም ይህንኑ በማረጋገጥ ውሳኔውን አጽንቶአል፡፡ እንግዲህ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃም ሆነ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶቹ ውሳኔ የተመሰረተው ተሰማ በተባለው ማስረጃ ላይ ነው፡፡ በማስረጃ አመዛዘን ረገድ የተሻለ መደምደሚያ የደረሰው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው ለማለት የሚያስችል የሕግ ምክንያትም የለም፡፡ ይልቁንም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት እንዲያይ ተጠይቆ ያላየውን (አላይም በማለት ያለፈውን) በአስተዳደር ክፍሉ የሚገኘውን የቤቱን ማህደር አስቀርቦ የመረመረ በመሆኑ የተሻለ ስራ ሰርቶአል የሚባለው ይሄው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ ስለዚህም በዚህ ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለ ለማለት የሚያስችል ምክንያት አላገኘንም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43510 ሚያዝያ 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 31893 ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቶአል፡፡
2. አከራካሪው ቤት የግል ሐብትህ ነው ይባልልኝ በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት አለማግኘቱ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡
4. የካቲት 16 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቶአል፡፡ ይፃፍ፡፡
   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 40418

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- ተስፋዬ ሞላ - ቀረበ

**ተጠሪዎች**፡- 1. እሸቱ ሞላ

2. ወ/ሮ እመቤት ሞላ - ቀረበች

3. የጌታቸው ሞላ ወራሾች ሞግዚት ተዘራ ስጠኝ - ቀረበች

መዝገቡን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን በማጽናት ሐምሌ 24 ቀን 2000 ዓ.ም በመ/ቁ. 35810 በሰጠው ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ጉዳዩ የውርስ ሃብት ክፍፍልን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ ሲጀመር ከሳሽ የነበረው አመልካች ነው ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረተው በውር አጣሪ ተጣረቶ ከቀረበው የውርስ ሃብት ላይ ድርሻዬን ያካፍሉኝ በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎችም ለቀረበው ክስ መልስ የሰጡ ሲሆን፣1ኛ ተጠሪ ክሱን አልተቃወመም፡፡ ከሣሽ ድርሻውን ይውሰድ ብሎአል፡፡ ተጠሪዎች ግን ክሱ በይርጋ ቀሪ ስለሆነ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚለውን መቃወሚያ በመቀበል ክሱን በመሰረዝ ብይን ሰጥቶአል፡፡ በዚህ ብይን ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም ብይኑ ጉድለት የለበትም በማለት የይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ነሐሴ 30 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪዎች ያነሱት የይርጋ መቃወሚያ ቀደም ሲል ውርሱ ሲጣራ በነበረበት ወቅት እልባት አግኝቶ እያለ እንደገና ተነስቶ ተቀባይነት የማግኘቱን አግባብነት ለመመረመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ እንደሚያሳየው ጉዳዩን በሚመለከት ሁለት መዝገቦች ተከፍተዋል፡፡ የመጀመሪያው መዝገብ ውርስ እንዲጣራ የቀረበውን ጥያቄ የተስተናገደበት ሲሆን፣ሁለተኛው ደግሞ ውርሱ ተጣርቶ በውርስ አጣሪው የቀረበውን ሪፖርት መሰረት በማድረግ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ የቀረበበት ነው፡፡ ሌላው ከክርክሩ ሂደት የተገነዘብነው የውርስ ይጣራ ጥያቄ የቀረበው በአመልካቹ ሲሆን፣በዚህን ጊዜም የይርጋ መቃወሚያ ቀርቦ እንደነበር እና ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤት ግን መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ ውርሱ እንዲጣራ ትእዛዝ ሰጥቶ በዚሁ መሰረት መፈጸሙን ነው፡፡ አመልካች የይርጋው መቃወሚያ ሁለት ጊዜ ነው የታየው የሚል የመከራከሪያ ነጥብ ያነሳውም ይህን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

እንደምንመለከተው ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ቀደም ሲል ተነስቶ ውድቅ የተደረገ ስለመሆኑ አከራካሪ አልሆነም፡፡ የውርስ ማጣራት ሂደቱ ተጠናቆ አጣሪው ሪፖርቱን ከፍ/ቤት ያቀረበው ጥር 29 ቀን 1999 ዓ.ም ሆኖ አመልካች የንብረት ክፍፍል ጥያቄ(ክስ) ያቀረበው ደግሞ መጋቢት 3 ቀን 1999 ዓ.ም እንደሆነ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ብይን ላይ ተመልክቶአል፡፡ ይህም ማለት አመልካች ክሱን የመሰረተው ክፍያውን ካወቀ አንድ ዓመት ከማለፉ በፊት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1080 በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት ጥያቄው በይርጋ ቀሪ አልሆነበትም፡፡ ሲጠቃለል አውራሹ ከሞቱበት ቀን አንስቶ የታሰበው የይርጋ ጊዜ የውርስ ይጣራልኝ ክስ በቀረበ ጊዜ ተነስቶ ውድቅ በመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 አንፃር ሲታይ በድጋሚ የሚቀርብበት የሕግ ምክንያት የሌለ ስለሆነና የውርስ አጣሪው ባቀረበው ሪፖርት መሰረት የቀረበው የንብረት ልካፈል ጥያቄም በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1080/3/ የተደነገገው የአንድ ዓመት የጊዜ ወሰን ከማለፉ በፊት የቀረበ በመሆኑ ጥያቄው/ክሱ/ በይርጋ ቀሪ ነው በሚል በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 53613 ጥር 26 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 35810 ሐምሌ 24 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው የንብረት ልካፈል ክስ በይርጋ ቀሪ አልሆነም በማለት ወስነናል፡፡
3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን ክሱ በቀረበበት መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ ግራ ቀኝ ወገኖች በጉዳዩ ሥረ-ነገር ላይ የሚያቀርቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ የመሰለውን ውሳኔ ይስጥ በማለት ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1/ መሰረት ይመለስለት ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 42682

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካቾች፡-** 1. ወ/ሮ ፋንታነሽ ሲሳይ ሙላቴ - ቀረቡ

2. አለሙ ደምሴ

3. ወ/ሪት ትእግስት ደምሴ

**ተጠሪ፡-** ሞላ ደምሴ ቀረበ - ጠበቃ ፋንታ አየለ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ልጅነትን ለማረጋገጥ በቀረበው ጥያቄ ላይ ተመስርቶ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ቀደም ሲል ለፍ/ቤት ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የሟች ደምሴ ፀጋዬ ልጅ መሆኑ ተረጋግጦ ተወስኖ ነበር፡፡ አመልካቾች ክርክሩ ውስጥ የገቡት ውሳኔውን በመቃወም እንዲሻርላቸው በመጠየቃቸው ነው፡፡ ተቃውሞአቸውም ተጠሪ የሟች ልጅ አይደለም የሚል ስለነበር፤ መቃወሚያው የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪን በማስቀረብ የግራ ቀኝ ወገኖቹን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም በተጠሪ በኩል የቀረበው የሰው እና የሰነድ ማስረጃ በእርግጥም የሟች ልጅ እንደሆነ አረጋግጦአል፡፡ ተቃዋሚዎች ይህን ማስረጃ ማስተባበል አልቻሉም በማለት የቀድሞው ውሳኔውን አፅንቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኂላ ተጠሪ የሟች ልጅ ነው በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካቾች ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተፈጽሞአል የሚሉትን ስህተት በመግለጽ ውሳኔው ይሻርላቸው ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው ተጠሪ የሟች ልጅ ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 143 አንፃር ሲታይ አግባብነት ያለው ነው ወይስ የለውም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የተሰማው የግራቀኝ ወገኖች ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራቀኝ ወገኖችን ያከራከረው የልጅነት ጥያቄ በተመለከተ ማስረጃዎችን ሰምቶአል፡፡ በሰማው ማስረጃም ሟች (አባት ነው የተባለው ሰው) ተጠሪን እንደልጁ በማድረግ ሲንከባከብ እንደነበር፣ ትምህርት ቤት ወስዶ እንዳስመዘገበው፣ ከቤተሰቦቹ ጋር በመቀላቀል ያኖረው እንደነበር ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ አመልክቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቾች በተጠሪ በኩል የተሰማውን ማስረጃ ሊያስተባብሉ እንዳልቻሉ በትችቱ ገልጾአል፡፡ በመጨረሻም በማስረጃ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ (አዋጅ ቁ 213/92) አንቀጽ 143(ሠ) መሠረት አባትነትን ለማረጋገጥ በቂ ምክንያት እንደሆነ በመገንዘቡ ተጠሪ የሟች ልጅ ነው በማለት እንደወሰነ ተገንዝበናል፡፡ አመልካቾችም ቢሆኑ እየተከራከሩ ያሉት የሥር ፍ/ቤት አረጋግጫለሁ ያለውን ፍሬ ነገር አላረጋገጠም በማለት

ሳይሆን፣ ተጠሪ ተወልጃለሁ የሚለው ከጋብቻ ውጪ በተፈጸመ የግብረስጋ ግንኙነት በመሆኑ ይህንኑ ግንኙነት በማያጠራጥር ሁኔታ ማስረዳት ሲገባው አላስረዳም በማለት እንደሆነ ከአጠቃላይ የክርክራቸው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 143 "በፍርድ ስለሚነገር አባትነት" በተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይዞአል፡፡ እነዚህም ከንኡስ አንቀጽ(ሀ) እስከ (ሠ) ድረስ ያሉት ሲሆኑ፣ አመልካቾች በመከራከሪያነት ያነሱት ነጥብ በንኡስ አንቀጽ (መ) በተመለከተው ድንጋጌ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የልጁ እናትና አባት የተባለው ሰው በሕግ የታወቀ ግንኙነት ባይኖራቸውም፤ በሕግ በተመለከተው የእርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በግብረሥጋ ግንኙነት አብረው የኖሩ መሆናቸው ከተረጋገጠ አባትነትን በፍርድ ውሳኔ ሊታወቅ እንደሚችል ስለሚያመለክት እንደሌሎቹ ድንጋጌዎች አንደኛው አባትነትን በፍርድ ውሳኔ የማወቂያ ዘዴ (ሁኔታ) ነው፡፡ ይህ ማለት ግን በዚህ ድንጋጌ የተመለከተው ሁኔታ ባለመረጋገጡ ብቻ አባትነትን በፍርድ ውሳኔ ማወቅ አይቻልም ማለት አይደለም፡፡ በተጠቀሰው አንቀጽ 143 መሠረት አባትነትን በፍርድ ውሳኔ ማወቅ የሚቻለው ከንኡስ አንቀጽ (ሀ) እስከ (ሠ) ካሉት ድንጋጌዎች ውስጥ በአንዱ የተመለተው ሁኔታ ሲሟላ ነው፡፡ በመሆኑም ቀጣይነት የግብረሥጋ ግንኙነት ስለመኖሩ ተጠሪ በማስረጃ አላረጋገጠም የሚለው የአመልካቾች ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ስናጠቃልለው የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪን የሟች ልጅ ነው በማለት በሰጡት ውሳኔ የተፈጸመ የሕግ ስህተት የለም ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 27622 ጥቅምት 1 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 63272 ህዳር 4 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት አፅንተናል፡፡
2. ተጠሪ የሟች ልጅ ነው መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ.40624

ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች፡-** 1. ወ/ሮ መብራት ታደሰ - ጠበቃ አቶ አድማሡ መዓዛ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ትዕግስት ዘውዴ

3. አቶ አንተነህ ዘውዴ

4. አቶ ቢኒያም ዘውዴ

**ተጠሪ፡-** አቶ ኤፍሬም ዘውዴ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት መስከረም 13 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መሠረታዊ መነሻ የአሁን ተጠሪ ሟች አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ወላጅ እናቱን ወ/ሮ አድማስወርቅ ጥላሁንን አግብተው ሲኖሩ የተወለደ በመሆኑ የሟች አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅና ወራሽ መሆኑ በፍርድ እንዲረጋገጥለት ያቀረበውን አቤቱታና ማስረጃ በመመርመር ተጠሪ የሟች ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅና ወራሽ ነው በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን ውሣኔ ከሰጠ በኂላ የአሁን አመልካቾች በተቃዋሚነት ቀርበው ሟች አቶ ዘውዴ በእሱፈቃድ 1940 ዓ.ም ለትምህርት ወደ አሜሪካ ሄደው ለሰባት ዓመታት እዚያው የቆዩ ስለሆነ 1945 ተጠሪን ሊወስዱ አይችሉም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሟች ዘውዴ በእሱፈቃድ ከሁለተኛ፣ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪ ውጭ ሌላ ልጅ የሌላቸው መሆኑን ጥር 18 ቀን 1990 ዓ.ም ኑዛዜ ያደረጉ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አቶ ኤፍሬም ዘውዴ (ተጠሪ) የሟች ልጅ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ እንዲያነሣልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው የአመልካቾች ፍርዱን ለመቃወም ያቀረቡት ማመልከቻ ደርሷቸው አቶ ዘውዴ በእሱፈቃድ 1944 ዓ.ም ተመልሰው በመምጣት ወ/ሮ አድማስወርቅ ሚስታቸውን ጠይቀው ተመልሰዋል፡፡ እኔም ተረግዤ ተወልጃለሁ፡፡ የመቃወም አመልካቾች የእኔ ወላጅ እናት ወ/ሮ አድማስወርቅ ጥላሁንና አቶ ዘውዴ በእሱፈቃድ በባልና ሚስትነት ተጋብተው አልኖሩም ብለው ባልተቃወሙበት ሁኔታ የሟች ልጅ ልጅ መሆኔ ህግ ግምት የሚያዝበትን ጉዳይ በምስክር ለማፍረስ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም የአመልካቾችንና የተጠሪን ማስረጃ ከሰማ በኂላ የተጠሪ ማስረጃ ሚዛን የሚደፋና ተዓማኒነት ያለው የአመልካቾች ማስረጃ ተዓማኒነት አጠራጣሪ መሆኑን በማገለፅ ቀደም ሲል የሰጠሁትን ውሣኔ የሚነሳበት ምክንያት የለም በማለት የአመልካቾችን መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካቾች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካቾች ተጠሪ አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ አሜሪካን አገር ለትምህርት ሄደው ባሉበት ተወለድኩ ያሉ በመሆናቸውና በመጀመሪያ እኔ ከተወለድኩ በኂላ ለትምህርት ሄዱ ያሉ ሲሆን በኂላ በእረፍት መጥተው ነው

የተረገዘኩት በማለት ያቀረቡት ክርክር የሥር ፍርድ ቤት ተቀብሎ መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑ አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ተጠሪን ለማሣደግ ያደረጉት ተሣትፎ የሌለ በመሆኑና ተጠሪም ይህንን ያላስረዳ በመሆኑ ከሁሉም በላይ አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ባደረጉት ኑዛዜ ከሁለተኛ ሶስተኛ እና አራተኛ አመልካቾች ውጭ ልጅ የሌላቸው መሆኑን ያደረጉት ኑዛዜ በቂና አሳማኝ ማስረጃ ሆኖ እያለ ተጠሪ የሚች አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅ ነው ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው እኔ የተወለድኩት በወላጅ እናቴና በሚች ዘውዴ በሱፈቃድ መካከል ህጋዊ ጋብቻ ባለበት ጊዜ ውስጥ በመሆኑ የሚች ልጅ መሆኔ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ የተረጋገጠ ነው፡፡ አመልካቾች ይህንን የህግ ግምት ለማስተባበል በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 144 የተደነገጉትን ሁኔታዎች ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ኑዛዜ የእኔን ልጅነት ለማሰረዝ የሚችል አይደለም የዚህ አይነት ይዘት የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካቾች ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያም ሆነ በሰበር አቤቱታቸው የተጠሪ ወላጅ እናት ወ/ሮ አድማስወርቅ ጥላሁን ከሚች አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ጋር የጋብቻ ግንኙነት አልነበራቸውም፡፡ ተጠሪ የተወለደው የሁለቱ ጋብቻ ከፈረሰ በኂላ ነው የሚል መቃወሚያ አላቀረቡም፡፡ አመልካቾች ተጠሪ የተወለደው አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ለትምህርት አሜሪካ ሄደው ባለበት ጊዜ ነው በማለት አጥብቀው የሚያቀርቡትን ክርክር አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ በአንድ ወንድና አንዲት ሴት መካከል ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የተወለደ ልጅ አባቱ ነው የሚባለው ባልዬው እንደሆነ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 126 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ የተወለደው በእናቱ ወ/ሮ አድማስወርቅ ጥላሁንና በአቶ ዘውዴ በሱፈቃድ መካከል የነበረው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ መሆኑ ያልተካደ በመሆኑ የተጠሪ አባት አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ መሆናቸውን ህጉ ግምት የያዘበት ጉዳይ ነው፡፡

ተጠሪ በህግ ግምት የአቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅ መሆኑን ከማስረዳቱም በላይ አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ባለቤታቸውን ሊጠይቁ ለእረፍት በመጡበት ጊዜ የተረገዘ መሆኑን የአቶ ዘውዴ በሱፈቃድ የቅርብ ዘመዶች በምስክርነት በማቅረብ አስረድተዋል፡፡ ይኸ በመሆኑ ተጠሪ የአቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅ አለመሆኑን ማስረዳት የሚቻለው በቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 144 መሠረት ሳይሆን በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 167 መሠረት የመካድ ክስ በማቅረብና በቤተሠብ ህጉ አንቀፅ 168 እስከ አንቀፅ 173 ከተዘረዘሩት አንደኛውን ለማስረዳት የሚችል በቂ ማስረጃ በማቅረብ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚችለው አባት ነህ ተብሎ በህግ ግምት የተሰጠው እሱ የሞተ እንደሆነ ተወላጆቹ እና ሌሎች ዘመዶቹ በቅደም ተከተል እንደሆነ የቤተሰብ ህጉ ደንግጓል፡፡ አንደኛ አመልካች ዘውዴ እሱባለው ሚስትና የሁለተኛ፣ ሶስተኛና አራተኛ አመልካቾች እናት ብትሆንም በዚህ ጉዳይ ተጠሪ ላይ የመካድ ክስ የማቅረብ መብትና ችሎታ የላትም፡፡ ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት መቃወሚያና መቃወሚያቸውን ለማስረዳት ያቀረቡት ማስረጃ ታዓማኒነት የሌለው መሆኑና የተጠሪ ማስረጃ ሚዛን የሚደፋ መሆኑ ፍሬጉዳይ የመመዘን ስልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተስማምተውበታል፡፡ ሚች አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ አደረጉት የተባለው ኑዛዜም ተጠሪ የሚች ልጅ ላለመሆኑ ብቃት ያለው ማስረጃ ተደርጎ እንዲወሰድ የሚያስገድድ ህግ የሌለ በመሆኑ በዚህ በኩል የበታች ፍርድ ቤቶች የህግ ስህተት ፈፅመዋል የሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአጠቃላይ የአመልካቾች ተጠሪ የሚች ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅ አይደለም የሚለውን ክርክራቸውን የቤተሰብ ህጉ በሚደነግገው መሠረት በበቂ ሁኔታ አላስረዱም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ህጉን መሠረት ያደረገና ስህተት የሌለበት ሆኖ ስላገኘነው በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት አፅንተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. አመልካቾችና ተጠሪ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ/ 41857

ጥቅምት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አሕመድ ሑሴን - ጠበቃ ማርቆስ ወ/ሰንበት ቀረበ

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ የኔዓለም ተመስገን - ጠበቃ ደምሰው ዘገየ ቀረበ

2. ወ/ሮ የኔነሽ ሙሉጌታ - ቀረበች

3. ወ/ሮ አስቴር ሙሉጌታ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የውርስ ሃብት ክፍፍልን መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ አንደኛ ተጠሪ ናት፡፡ ክስ የመሠረተችው በአሁኑ አመልካች፣ በሁለተኛ እና በሦስተኛ ተጠሪዎች ላይ ነው፡፡ በክስዋም ሞግዚት የሆነችለት የኟላአሸት ሙሉጌታ የተባለውን ልጅ የውርስ መብት ለማስከበር ክሱን እንደመሠረተች ገልጻ ያለሞግዚት አድራጊዋ ስምምነት ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ያደረጉት የቤት ሺያጭ ውል እንዲፈርስ እና የቤቱ 1/3ኛ ለሞግዚት አድራጊዋ እንዲሰጥ ይወሰንላት ዘንድ ጠይቃለች፡፡

ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስ የቤቱ ግማሽ የሌላ ሰው መሆኑን በአንድ በኩል ሲገልጹ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ቀሪውን (የቤቱን ግማሽ) ለሦስቱ ተከፋፍሎ ከሣሽ ሞግዚት የሆነችለት ልጅ ድርሻውን 1/3ኛ ሊወስድ ይችላል ብለዋል፡፡ አመልካች ግን ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚል መቃወሚያ ከማቅረቡም በላይ፤ ቤቱን የገዛው ስመሃብቱ ለሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ከዞረ በኂላ እንደሆነና ከውሉ በኂላም ስመሃብቱ ለሱ መዛወሩን በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡ ክሱን ያስተናገደው ፍ/ቤትም የሁሉን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኂላ፣ በአመልካች፣ በሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ፈርሶአል፡፡ የቤቱ ግማሽ ከተቻለ በአይነት፣ ካልተቻለ ተሽጦ 1/3ኛ ለከሣሽ ሞግዚት አድራጊ ይሰጥ በማለት ወስኖአል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ውሉ ይፈርሳል የሚለውን የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ሲያፀና ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች በቤት ሺያጭ ውል ስም የወሰዱት ብር 100,000(መቶ ሺህ ብር) ግን ከነወለዱ ለአመልካች ይመልሱ በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ህዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የቤት ሺያጭ ውሉ እንዲፈርስ መደረጉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡

ከሥር ጀምሮ በተደረገው ክርክር እንደተመለከተው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት አንደኛ ተጠሪ ሞግዚት ለሆነችለት ልጅ እና ለሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች በውርስ የተሰጠ ሃብት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ

ውርሱ ከመከፋፈሉ በፊት ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ለአመልካች ሸጠውታል፡፡ የአንደኛ ተጠሪ ክርክር የተመሠረተውም የ3ቱም የጋራ የሆነው ንብረት ለመሸጥ የሁሉም የጋራ ባለሃብቶች ስምምነት ሊኖር ይገባል በሚለው ላይ ነው፡፡ በእርግጥም የጋራ የሆነውን ንብረት ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ የጋራ ባለንብረቶቹ ሁሉ ስምምነት አስፈላጊ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁ 1266 የተደነገገ ሲሆን፣ የውርስ ሃብትም አካፋፈሉ እስኪፈጸም ድረስ በወራሾቹ መካከል ውርሱ ሳይነጣጠል እንደሚቆይ በፍ/ብ/ሕግ ቁ 1060(1) ተመልክቶአል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ቤቱን ለአመልካች የሸጡት ስመሃብቱን በራሳቸው ካዛወሩ በኋላ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የሺያጭ ውሉ ከመደረጉ ወይም ቤቱን ለአመልካች ከማስተላለፋቸው በፊት ከሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል የባለቤትነት የምስክር ወረቀት በስማቸው አግኝተው ነበር ማለት ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁ 1195(1) እንደተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት በተሰጠ ጊዜ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ባለሃብት ሆኖ ይቆጠራል፡፡ እንግዲህ በያዝነው ጉዳይ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠውን ሁኔታ ከሕጉ ጋር አገናዝበን ስንመለከተው ቤቱ ያልተከፋፈለ የውርስ ሃብት መሆኑ ቀርቶ የሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች የግል ሃብት እንደሆነ እንደሚቆጠር ነው መገንዘብ የሚቻለው፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ አመልካች ቤቱን የገዛው የሽያጮቹን የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት በማየት ሲሆን፣ ይህን በመከተልም ቤቱ በራሱ ስም አዙሮ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ያገኘበት በመሆኑ በአመልካቹ እና በሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል የሚፈርስበት በሕግ የሚደገፍ ምክንያት የለም፡፡

ሌላው ቀጥለን የተመለከትነው አንደኛ ተጠሪ ሞግዚት የሆነችለት ልጅ ድርሻ እንዴት ይታያል? የሚለው ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሉ መፍረስ በመስማማቱ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች በቤት ሽያጭ ስም የተቀበሉት ገንዘብ ለአመልካች እንዲመልሱ ወስኖአል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አንደኛ ተጠሪ ሞግዚት የሆነችለት ልጅም ከሌሎቹ ወራሾች ጋር በመሆን ከቤቱ ድርሻውን ሊያገኝ ስለሚችል ችግር አይኖርም፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት እምነት ግን ውሉ ሊፈርስ ስለማይገባ ቤቱ በወራሾቹ መካከል ይከፋፈል የሚል አካሄድ አይኖርም፡፡ ወራሾቹ ሊከፋፈሉ የሚችሉት ከቤቱ ሽያጭ የተገኘውን ገንዘብ ነው፡፡ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ቤቱን የእነሱ ሃብት ብቻ እንደሆነ አድርገው ቢሸጡትም፤ በመጨረሻ የታመነው ግን የ3ቱም ወራሾች ሃብት መሆኑ ስለሆነ ከዚህ ሃብት የተገኘው የሺያጭ ገንዘብም የ3ቱ ወራሾች ነው ማለት ነው፡፡ በመሆኑም አንደኛ ተጠሪ ሞግዚት የሆነችለት ልጅ የተለየ ሥነ-ሥርዓት መከተል ሳያስፈልገው ከቤቱ ሽያጭ ከተገኘው ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ድርሻውን 1/3ኛ (አንድ ሦስተኛ) የማግኘት መብት አለው፡፡ በዚህ መሠረትም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 07153 ግንቦት 28 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 57214 ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. በአመልካች እና በሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል አይፈርስም ብለናል፡፡
3. አንደኛ ተጠሪ ሞግዚት የሆነችለት ልጅ ከቤቱ ሽያጭ ከተገኘው ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ድርሻውን 1/3 (አንድ ሦስተኛ) ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ይስጡት ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡
5. በዚህ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሠረት ይፈጸም ዘንድ ለሥር ፍ/ቤቶች ይጻፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 42682

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካቾች፡-** 1. ወ/ሮ ፋንታነሽ ሲሳይ ሙላቴ ቀረቡ

2. አለሙ ደምሴ

3. ወ/ሪት ትእግስት ደምሴ

**ተጠሪ፡-** ሞላ ደምሴ ቀረበ ጠበቃ ፋንታ አየለ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ልጅነትን ለማረጋገጥ በቀረበው ጥያቄ ላይ ተመስርቶ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ቀደም ሲል ለፍ/ቤት ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የሟች ደምሴ ፀጋዬ ልጅ መሆኑ ተረጋግጦ ተወስኖ ነበር፡፡ አመልካቾች ክርክሩ ውስጥ የገቡት ውሳኔውን በመቃወም እንዲሻርላቸው በመጠየቃቸው ነው፡፡ ተቃውሞአቸውም ተጠሪ የሟች ልጅ አይደለም የሚል ስለነበር፤ መቃወሚያው የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪን በማስቀረብ የግራ ቀኝ ወገኖቹን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም በተጠሪ በኩል የቀረበው የሰው እና የሰነድ ማስረጃ በእርግጥም የሟች ልጅ እንደሆነ አረጋግጦአል፡፡ ተቃዋሚዎች ይህን ማስረጃ ማስተባበል አልቻሉም በማለት የቀድሞው ውሳኔውን አፅንቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኋላ ተጠሪ የሟች ልጅ ነው በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካቾች ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተፈጽሞአል የሚሉትን ስህተት በመግለጽ ውሳኔው ይሻርላቸው ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው ተጠሪ የሟች ልጅ ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 143 አንፃር ሲታይ አግባብነት ያለው ነው ወይስ የለውም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የተሰማው የግራቀኝ ወገኖች ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራቀኝ ወገኖችን ያከራከረው የልጅነት ጥያቄ በተመለከተ ማስረጃዎችን ሰምቶአል፡፡ በሰማው ማስረጃም ሟች (አባት ነው የተባለው ሰው) ተጠሪን እንደልጁ በማድረግ ሲንከባከብ እንደነበር፣ ትምህርት ቤት ወስዶ እንዳስመዘገበው፣ ከቤተሰቦቹ ጋር በመቀላቀል ያኖረው እንደነበር ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ አመልክቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቾች በተጠሪ በኩል የተሰማውን ማስረጃ ሊያስተባብሉ እንዳልቻሉ በትችቱ ገልጾአል፡፡ በመጨረሻም በማስረጃ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ (አዋጅ ቁ 213/92) አንቀጽ 143(ሠ) መሠረት አባትነትን ለማረጋገጥ በቂ ምክንያት እንደሆነ በመገንዘቡ ተጠሪ የሟች ልጅ ነው በማለት እንደወሰነ ተገንዝበናል፡፡ አመልካቾችም ቢሆኑ እየተከራከሩ ያሉት የሥር ፍ/ቤት አረጋግጫለሁ ያለውን ፍሬ ነገር አላረጋገጠም በማለት

ሳይሆን፣ ተጠሪ ተወልጃለሁ የሚለው ከጋብቻ ውጪ በተፈጸመ የግብረስጋ ግንኙነት በመሆኑ ይህንኑ ግንኙነት በማያጠራጥር ሁኔታ ማስረዳት ሲገባው አላስረዳም በማለት እንደሆነ ከአጠቃላይ የክርክራቸው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 143 "በፍርድ ስለሚነገር አባትነት" በተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይዞአል፡፡ እነዚህም ከንኡስ አንቀጽ(ሀ) እስከ (ሠ) ድረስ ያሉት ሲሆኑ፣ አመልካቾች በመከራከሪያነት ያነሱት ነጥብ በንኡስ አንቀጽ (መ) በተመለከተው ድንጋጌ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የልጁ እናትና አባት የተባለው ሰው በሕግ የታወቀ ግንኙነት ባይኖራቸውም፤ በሕግ በተመለከተው የእርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በግብረሥጋ ግንኙነት አብረው የኖሩ መሆናቸው ከተረጋገጠ አባትነትን በፍርድ ውሳኔ ሊታወቅ እንደሚችል ስለሚያመለክት እንደሌሎቹ ድንጋጌዎች አንደኛው አባትነትን በፍርድ ውሳኔ የማወቂያ ዘዴ (ሁኔታ) ነው፡፡ ይህ ማለት ግን በዚህ ድንጋጌ የተመለከተው ሁኔታ ባለመረጋገጡ ብቻ አባትነትን በፍርድ ውሳኔ ማወቅ አይቻልም ማለት አይደለም፡፡ በተጠቀሰው አንቀጽ 143 መሠረት አባትነትን በፍርድ ውሳኔ ማወቅ የሚቻለው ከንኡስ አንቀጽ (ሀ) እስከ (ሠ) ካሉት ድንጋጌዎች ውስጥ በአንዱ የተመለተው ሁኔታ ሲሟላ ነው፡፡ በመሆኑም ቀጣይነት የግብረሥጋ ግንኙነት ስለመኖሩ ተጠሪ በማስረጃ አላረጋገጠም የሚለው የአመልካቾች ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ስናጠቃልለው የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪን የሟች ልጅ በማለት በሰጡት ውሳኔ የተፈጸመ የሕግ ስህተት የለም ለማለት ችለናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

4. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 27622 ጥቅምት 1 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 63272 ህዳር 4 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348(1) መሠረት አፅንተናል፡፡
5. ተጠሪ የሟች ልጅ ነው መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
6. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 42766

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** *መንበረፀሀይ ታደሰ*

*ሐጎስ ወልዱ*

*ሂሩት መለሠ*

*ታፈሰ ይርጋ*

*አልማው ወሌ*

**አመልካቾች፡-** እነ ወ/ት ሠናይት ኃ/ማርያም - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ አበበች ወርቁ - አልቀረቡም

*መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡*

## ፍ ር ድ

*ይህ ጉዳይ በአመልካቾች አባት እና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ መፈረስን ተከትሎ የንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት የውርስ አጣሪ ሰይሞ አጣሪውም ጉዳዩን ከተመለከተ በኋላ ለሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን የቤ.ቁ 084 ጨምሮ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው በማለት ሪፖርቱን ለፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም ይህንኑ ሪፖርት ተቀብሎ ማጽደቁን ተገንዝቦአል፡፡*

*ከዚህ በኋላም የአሁን አመልካቾች የቤ.ቁ 084 የሆነው ቤት የሟች አባታችን የግል ንብረት ሆኖ ሳለ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ በውርስ አጣሪ የተደረሰበትን ሪፖርት የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተቀብሎ ሪፖርቱን ማጽናቱ በአግባቡ አይደለም በማለት የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የውርስ አጣሪው ቤቱ የጋራ ነው ወደሚል ድምዳሜ የደረሰው የጋብቻ ውሉን መሠረት በማድረግ ሲሆን ነገር ግን ውሉ የጋራ ያደረገው የቤቱን ገቢ እንጂ ቤቱን እንዳልሆነ ከውሉ በግልጽ መረዳት ይቻላል ካለ በኋላ የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ይሄው ቤት የአመልካቾች አባት የግል ሀብት ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱን መዝገቡ ያስረዳል፡፡*

*የአሁን ተጠሪም በከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይግባኝ ባይና የመ/ሰጭዎች አባት ሲጋቡ የቤ.ቁ 084 አስቀድሞ በሟች ተሰርቶ የነበረና ሁለት ክፍል ቤት ብቻ የነበረ ሲሆን ነገር ግን በጋብቻ ላይ እያሉ ቤቱን በተደጋጋሚ ማደሳቸው ይህ ቤት እንዳይሸጥ በማሰብም ሌላ ቤት ሸጠው ለዕዳ መክፈያነት በማዋል ቤቱ ከመሸጥ ስለማዳናቸው ቤቱም በፊት ከነበረው ሁለት ክፍል ላይ ተጨማሪ 9 ክፍል ሰርቪስ ቤቶችን በጋራ ስለመስራታቸውና አስቀድሞ ቤቱ የሚገኝበት ይዞታ 300 ሜ.ካሬ ብቻ የነበረ ሲሆን ነገር ግን በተጨማሪ ግንባታ ሲደረግ ይዞታውም ወደ 578 ካ.ሜትር ከፍ ስለማለቱ በክርክሩ የተረጋገጠ ስለሆነ በዚህ ሁኔታ ቤቱ የመ/ሰጪዎች አባት የግል ንብረት ነው መባሉ በአግባቡ አይደለም በማለት በመሻር የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው ሲል ውሳኔ ሠጥቷል፡፡*

*የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለሰበር ሊቀርብ ይገባል ብሎ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡*

ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ ክርክር ያስነሳው ቤት የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው? ወይንስ የባል የግል ንብረት? የሚለው ነው፡፡

ከዚሁ ጭብጥ አኳያም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው እንደሚቀሩ በተሻሻለ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 57 ላይ ተመልክቷል፡፡ የአመልካቾች አባትና ተጠሪ ጋብቻቸውን በፈጸሙ ጊዜ የቤ.ቁ 084 በሟች የአመልካቾች አባት ስም ተመዝግቦ ሁለት ክፍል ቤት ብቻ እንደነበር የተረጋገጠ ሲሆን ይህ ፍሬ ነገርም ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ ሆኖም ግን ግራ ቀኙ ሚያዝያ 13 ቀን 1966 ዓ.ም ያደረጉት የጋብቻ ውል ክርክር የተነሳበትን ቤትም ሆነ ሌሎች በባል ስም ተመዝግበው የሚገኙ ንብረቶችን የጋራ ለማድረግ እንደተስማሙ ከውሉ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ እንደተመለከተው ባልና ሚስቱ ጋብቻቸው ጸንቶ በቆየበት ጊዜ ቤቱን በተደጋጋሚ ማደሳቸው፣ በንግድ ምክንያት የመጣና በጋራ የሚፈለግባቸውን የግብር ክፍያ በተመለከተም ይሄው ቤት እንዳይሸጥ በማሰብ ሌላ ንብረት ሸጠው የግብር ዕዳውን በመክፈል ቤቱን ማቆየታቸውና ቀድሞ የነበረውንም ይዞታ በማስፋፋት ሌላ ተጨማሪ 9/ዘጠኝ/ ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ስለመስራታቸው የተረጋገጠ እንደመሆኑ መጠን ይህም ቀድሞውንም ቢሆን በጋብቻ ውሉ ቤቱን የጋራ ለማድረግ የነበራቸውን ሃሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡

ስለሆነም ግራ ቀኙ ባደረጉት የጋብቻ ውል አከራካሪው ቤት የጋራ እንዲሆን የተስማሙ ከመሆኑም ሌላ ጋብቻው ጸንቶ በቆየ ጊዜም የቤቱ አገልግሎት በመሠረታዊነት የተለወጠ ስለሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ቤቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 31335 ታህሳስ 27 ቀን 2001 ዓ.ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ስለሆነ ጸንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 42648

ታህሣሥ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዘነበች በያን - ተወካይ አለምነሽ ከበደ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ት ብርቅነሽ ከበደ - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ ልጅነት ማረጋገጥን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁኑዋ ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ አባታቸው የ፺ አለቃ ከበደ በያን እና እናታቸው ወ/ሮ ብርሃኔ ኃ/ማሪያም ተጋብተው ሲኖሩ በ1964 ዓ.ም የተወለዱ በመሆኑና አባታቸው ፺ አለቃ ከበደ በያን ከዚህ አለም በሞት ስለተለዩ የሟቹ ልጅ መሆናቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ቀርበው ሟች የ፺ አለቃ ከበደ በያን እና ወ/ሮ ብርሃኔ ኃ/ማርያም ልጅ ያልወለዱና ተጠሪ የወ/ሮ ብርሃኔ የክርስትና ልጅ መሆናቸውን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም በግራ ቀኙ የቀረቡትን ምስክሮች ከሰማ በኋላ በተሻሻለው ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 156 መሰረት የሟች የ፺ አለቃ ከበደ በያን ልጅ ናቸው ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው የ፺ አለቃ ከበደ በያን እና ወ/ሮ ብርሃኔ ኃ/ማርያም በጋብቻቸው ዘመን ልጅ ያልወለዱና ወ/ሮ ብርሃኔም መሐን የነበሩ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን በሚገባ ሳያጣራ ተጠሪ የሟች ልጅ ናቸው ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚል ነው፡፡ ችሎቱም ተጠሪ የሟች ልጅ ናቸው ተብሎ የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ የፁሁፍ ክርክር አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

በስር ፍ/ቤት አቤቱታ የቀረበው ተጠሪ የሟች የ፺ አለቃ ከበደ በያን ልጅ ስለመሆናቸው እንዲረጋገጥ ነው፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ልጅነትን ማስረዳት የሚቻለው የልደት ምስክር ወረቀት በማቅረብ ወይም የልደት ምስክር ወረቀት የሌለ እንደሆነ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት እንደሆነ ከፍ ሲል የተጠቀሰው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 154 እና 155 ያመለክታሉ፡፡ ከመዝገቡ ሂደት ለመረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ ልጅነታቸውን ለማስረዳት የሞከሩት የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ነው፡፡ አንድ ሰው የልጅነት ሁኔታ አለው የሚባለው በማህበረሰቡ ዘንድ የእርሱ ልጅ ነው ተብሎ ሲገመት መሆኑን ከአንቀጽ 156 መረዳት ይቻላል፡፡ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ማስረዳት ከተቻለ ፍ/ቤት ልጅ ሲል የሕግ ግምት ሊወስድ የሚችል መሆኑ አንቀጽ 157/1/ ያመለክታል፡፡ ከአንቀፁ መረዳት እንደሚቻለው የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ የመጨረሻ ማስረጃ (conclusive evidence) ሳይሆን የሕግ ግምት ብቻ ነው፡፡ ግምቱም ቢሆን አስገዳጅነት ያለው የሕግ ግምት አይደለም፡፡ ግምቱን የሚቃወም ወገን ማስረጃ በማቅረብ ግምቱን ማፍረስ እንደሚችል ንኡስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ ግልባጭ እንደተረዳነው ሟች የተጠሪ ልጅ ለመሆናቸው የሰው ምስክሮች ያቀረቡ ሲሆን አመልካችም ቢሆኑ ተጠሪ ልጅ አለመሆናቸውን ለማስረዳት ተቃራኒ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡ ነገር ግን የተጠሪ ምስክሮች ተጠሪ ሟች እና ወ/ሮ ብርሃኔ ባልና ሚስት በነበሩበት ጊዜ የተወለዱና የአካባቢውም ህብረተሰብ ተጠሪን የሟች ልጅ አድርጐ የሚገምት መሆኑን ሲያስረዱ የአመልካች ምስክሮች ይህንን የሕግ ግምት ማፍረስ አልተቻላቸውም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ተጠሪ የልጅነት ሁኔታ መኖርን ስላረጋገጡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 156 መሰረት የ፺ አለቃ ከበደ በያን ልጅ ናቸው ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለው ለማለት አልተቻለም፡፡

# ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 12503 ግንቦት 04 ቀን 2000 ዓ.ም ሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 68578 ጥቅምት 13 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ፀንቷል፡
2. ተጠሪ የ፺ አለቃ ከበደ በያን ልጅ ናቸው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 44612

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዘውዴ ወ/ጊዮርጊስ - ጠበቃ ፈጠነ ከበደ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ት ኤልሳቤጥ ኪዳኔ - ቀረበች

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ ናቸው፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም፤ወላጅ እናቴ ወ/ሮ ቻይና ከበደ ከሟች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ ጋር ከጋብቻ ውጪ ባደረጉት ነዋሪ የሆነ ግንኙነት በ1971 ዓ.ም የተወለድኩ፣እኔ በተፀነስኩበት ጊዜ ሟችና እናቴ በአንድ ግቢ፤ በአንድ ቤት ውስጥ ይኖሩ የነበረ ሲሆን ሟች በሕይወት እያሉ በወር ብር 200.00(ሁለት መቶ) በወላጅ እናቴ አማካኝነት ቀለብ ይከፍሉ ነበር፣ስለዚህ ከሟች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ መወለዴ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 125/1/ መሰረት ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኗ አመልካችም በጣልቃ ገብነት ወደ ክርክሩ ገብተው ተጠሪ አባትነት እንዲታወቅ ያቀረቡት ክስ የተሟላ ስላልሆነና የተጠሪ እናት ወ/ሮ ቻይና ከበደ ከሟች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ ጋር በሕግ የታወቀ ግንኙነት እንደነበራቸው ያስወሰኑበትን ማስረጃ ስላላቀረቡ አቤቱታቸው የክስ ምክንያት የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ተጠሪ መቼ ቀንና ወር እንደተወለዱ ስላልጠቀሱ፣ሟች ከተጠሪ እናት ጋር ለአንድም ጊዜ አብረው ኖረው ስለማያውቁ፣ሟች ከተጠሪ እናት በየትኛው ግቢ መቼ እንደኖሩ ስላልተገለፀና ለተጠሪ እናት በወር ሁለት መቶ ብር ቀለብ መክፈል አባት ለልጁ በሕግ ማድረግ የሚገባውን እንክብካቤ መመዘኛዎችን ስለማያሟላና ቀለብም ቆርጠውላቸው ስለማያውቁ፣የተጠሪ ምስክሮች በምን ጭብጥ ላይ ቃላቸውን እንደሚሰጡ በአቤቱታቸው ስላልጠቀሰ፣እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ በሟችና በተጠሪ መካከል የአባትነት እና የልጅት ግንኙነት ሁኔታ ስላልነበረ አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተጠሪ እንደክሳቸው አቀራረብ ሟች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌና እናታቸው ቻይና ከበደ ተጠሪ የተወለዱበትንና የተፀነሱበትን ጊዜ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 125/1/ እና 106/2/ ድንጋጌዎች መሰረት አላስረዱም፣የምስክሮች ቃልም እርስ በራሱ የሚጋጭ ነው በማለት የተጠየቀውን ዳኝነት ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በምስክሮች ቃል ተከሰተ የተባለው ልዩነት ጊዜን ብቻ የሚመለከት መሆኑን ይህ ልዩነት ከአጠቃላይ የምስክሮች ቃል ይዘት ጋር ተዛምዶ ሊታይ እንደሚገባ በመጥቀስ በተጠሪ ምስክሮች ቃል ፍሬነገር ላይ ቅራኔ ሳይኖርና ምስክርነቱ የተሰጠበት ጊዜ እርዝማኔ ግምት ውስጥ መግባት እንደአለበት በመግለጽ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በመሻር የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 106/1/ እና 125/1/"ን" ጠቅሶ ተጠሪ የሟች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ ልጅ ናት ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኗ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን

ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ መጋቢት 21 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት 4(አራት) ገጽ የሰበር አቤቱታ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች በሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ትእዛዝ ተሰጥቶ ተጠሪ ቀርበው ሐምሌ 16 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ 4/አራት/ ገጽ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ የሟች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ ልጅ ናት ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የተጠሪ ክስ መሰረት ያደረገው ሟች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ እና ወ/ሮ ቻይና ከበደ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አንድ ላይ ሲኖሩ ተፀንሰው የተወለዱ መሆኑንና ሟች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ ለተጠሪ በወር ብር 200.00(ሁለት መቶ ብር) ቀለብ ይሰጡ የነበረ መሆኑን ሆኖ ይህንኑ ለማስረዳትም የሰው ምስክሮችን አቅርበው ያሰሙ መሆኑን ነው፡፡ ጉዳዩን በተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የተመዘገበው የተጠሪ ምስክሮችን ቃል ይዘት፡-1ኛ ምስክር የአመልካች እናት ሲሆኑ ከሟች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ ጋር ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ዓመት በቤታቸው ውስጥ አብረው ሲኖሩ ተጠሪን ሦስት ወር እርጉዝ ሆነው ሟች ቤት ተከራይተው ከቤታቸው እንደአስወጡ፣በወር ብር 200.00 ይረዷቸው እንደነበርና የቤት ኪራይም ይከፍሉላቸው የነበረ መሆኑን፣ገንዘቡን ሕይወታቸው እስከአለፈ ጊዜ ድረስ መስጠታቸውን፣በሟች ቤት በኪራይ በሱማሌ ጦርነት ጊዜ ከውጪ ዜጋ ጋር ይኖሩ የነበረ መሆኑንና ሟች ልጅ ውለጂልኝ፣ቤት ተከራይቼ አስቀምጥሻለሁ ያሏቸው መሆኑን፣ተጠሪን ዓመተምህረቱን በማያስታውሱት በየካቲት ወር የውጪ ዜጋው ከሄደ ከሁለት ዓመታት በኋላ ከሟች መውለዳቸውንና የባልና ሚስት ፊርማ ግን ያልነበራቸው መሆኑን መመስከራቸውን፣2ኛ ምስክር በበኩላቸው ወ/ሮ ቻይና ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1980 ዓ.ም ድረስ በሰገነት ሆቴል ውስጥ ከፊታውራሪ ኪዳኔ ጋር ሲወጡ ሲገቡ አያለሁ፣ልጅ ግን አልወለዱም በማለት መመስከራቸውን፣3ኛ ምስክር ደግሞ ፊታውራሪ ኪዳኔ እና ወ/ሮ ቻይና በ1970 ዓ.ም ሰገነት ሆቴል ውስጥ አብረው ይኖሩ እንደነበረ፣ወ/ሮ ቻይና ከበደ ወሩን በማያስታውሱት በ1970 ዓ.ም የሦስት ወር ቅሪት ነኝ ብለው የነገሯቸው መሆኑን፣ሟችና ወ/ሮ ቻይና ከበደ እንደ ባልና ሚስት መኖራቸውን እንደሚያውቁ፣በ1970 ዓ.ም መጨረሻ ወደ አዲስ አበባ በመሄዳቸው ልጅ መውለዱን ግን አላውቅም በማለት መመስከራቸውንና 4ኛ ምስክርም በ1973 ዓ.ም ወ/ሮ ቻይና ቤት ተከራይተው ይኖሩ ነበር፣ሟች በሕይወት እስካሉ ድረስ ለረጅም ጊዜ ለተጠሪ ቀለብ እያሉ በየወሩ ሲሰጡ የነበረ መሆኑን እንደሚያውቁ በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሣይ መሆኑን ነው፡፡

በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አባትነት የሚታወቅባቸው መንገዶች፣ በእናትየዋና በአንድ ወንድ መካከል በሕግ የታወቀ ግንኙነት መኖሩን በማረጋገጥ፣አባትየው ልጁን ልጄ ነው ሲል በመቀበሉ ምክንያት ወይም በፍርድ በሚሰጥ ውሣኔ እንዲታወቅ ሲደረግ የሚሉት ሦስት መንገዶች ናቸው፡፡

አባትነት በሕግ ግምት የሚታወቅበት መንገድ በተዘዋዋሪ የጋብቻ መኖሩን ወይም ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን በማስረዳት የሚረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘትና አቀራረፃቸው ወንድየውና ሴትየዋ በሕግ በታወቀው ግንኙነት መኖራቸውና መኖር የጀመሩበት ጊዜ ከግምት ሊገባና በተገቢው መንገድ ሊረጋገጥ እንደሚገባው ያስገነዝባሉ፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 126 መሰረት ልጅ በሚፀነስበት ወይም በሚወለድበት ጊዜ በልጅ እናትና በአንድ ወንድ መካከል በሕግ የታወቀ ግንኙነት መኖሩ ከተረጋገጠ ወንድየው የልጁ አባት ነው የሚል የሕግ ግምት እንደሚወሰድ ተመልክቷል፡፡ በዚህ የሕጉ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው በልጁ እናትና በወንድየው መካከል በሕግ የታወቀ ግንኙነት እንዳለ ወይም የተወለደው በሕግ የታወቀው ግንኙነት ፀንቶ ባለበት መሆኑን ማሣየት የግድ የሚል መሆኑን ነው፡፡ በቤተሰብ ሕጉ "በሕግ የታወቀ ግንኙነት" የሚባሉ ግንኙነቶች ጋብቻ አንዱ ስለመሆኑ

አንቀጽ 1/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች የሚያሣዩ ሲሆን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 35/2/ ድንጋጌ ይዘትም ይህንኑ ያስረዳል፡፡ ሌላው በሕግ የታወቀ ግንኙነት የሚባለው ጋብቻ ሣይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ስለመሆኑም የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 98 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡት ነው፡፡ በመሆኑም የሕግ ግምት ተጠቃሚ የሚሆነው ልጅ በጋብቻ ወይም ጋብቻ ሣይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ በሕጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የተጸነሰ ወይም የተወለደ ልጅ ነው፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 128/1/ አንድ ልጅ ጋብቻው ከተፈጸመ ከ180 ቀናት በኂላ ወይም ጋብቻው በፈረሰ በ300 ቀናት ውስጥ የተወለደ እንደሆነ ልጁ በጋብቻው ውስጥ እንደተፀነሰ ንኡስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ለዚሁ ተቃራኒ የሆነ ማስረጃ ተቀባይነት እንደማይኖረው አስገዳጅነት ባለው መልኩ አስቀምጧል፡፡ እንዲሁም የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 130/2/ ድንጋጌ አንቀጽ 128 ድንጋጌ ሥር የተመለከተው ሕጋዊ ግምት በጋብቻ ተሳስረው በሚገኙ ተጋቢዎች ብቻ ሳይሆን ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩ ወንድና ሴት ላይም ተፈፃሚ መሆናቸውን ያስገነዝባል፡፡

እንግዲህ ሕጉ እነዚህን ሁኔታዎች ካስቀመጠ በጉዳዩ ላይ የሚቀርበው ማስረጃም በተገቢው መንገድ በጥንዶች መካከል የነበረውን ግንኙነት ዓይቱንና የጽንሱ ጊዜ እንዲሁም የልደት ጊዜው ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ ምስክሮች ቃል የተጠሪ እናትና ሟች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ የነበራቸውን የግንኙነት ዓይነት በተመለከተ የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩ እንደነበርና ቤተሰቦቻቸውም ሆነ ማህበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው ይገምቷቸው እንደነበር የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ የተጠሪ እናትና ሟች አብረው ይኖሩ ነበር የተባለውን ጊዜ እና ተጠሪ ተወለዱ የተባለውን ጊዜ በተመለከተ ልዩነት ባለበት ሁኔታ መመስከራቸውን ከመዝገቡ ግልባጭ ተመልክተናል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይኸው ፍሬ ነገር ስለመኖሩ ግንዛቤ ለተጠሪ ምስክሮች ቃል ክብደት ሰጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ ይኸው የፍርድ ቤቱ አካሄድ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 128፣130፣106 እና 125 ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች አፈፃፀም ተግባራዊነቱን ሊያሣይ የሚችል ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ እናትና በሟች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሉ መካከል በህጉ አግባብ የተፈጸመ ጋብቻ ሣይኖር እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ለመኖሩ ተጠሪ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 125/1/፣128፣130 እና 106/2/ አንፃር ያላስረዱና ያቀረቧቸው ምስክሮች ቃልም እርስ በእራሱ የሚጋጭ መሆኑን ገልጾ የደረሰበትን ድምዳሜ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሻረው ሕጋዊ በሆነ ምክንያት ሆኖ አልተገኘም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተፈጸመውን ስህተት ማረም ሲገባው ውሣኔውን ማጽናቱ ባግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም መሰረት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 03729 ኅዳር 09 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 44026 መጋቢት 08 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 15572 የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪ የሟች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ ልጅ አይደሉም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 38533

ህዳር 08 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- እነ ወ/ሮ ጽጌ ወልደመስቀል (6 ሰዎች) ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ስዩም ክፍሌ ቀረቡ

*መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡*

**ፍ ር ድ**

በዚህ የሰበር መዝገብ የቀረበው ክርክር በውርስ ህጉ ውስጥ የተመለከቱትን ይርጋ ድንጋጌዎችን አተረጓጎም እና አፈፃፀማቸውን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ጥቅምት 22 ቀን 1997 ዓ.ም አሻሽለው በአሁኑ አመልካቾች ላይ ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ተጠሪና አመልካቾች የኮሎኔል ክፍሌ ደስታ ወራሾች ለመሆናቸው በአውራጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1009/80 ህዳር 11 ቀን 1980 ዓ.ም ማረጋገጣቸውን፣ የአውራሻቸው ንብረት የሆነ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11 ቁጥሩ 228 የሆነ ቤት ከአመልካቾች ጋር በእኩልነት በመካፈል የደረሳቸው እንዳላቸው፣ ቤቱን አመልካቾች ተጠሪን አስወጥተው በመኖሪያነት እና እያከራዩ በመጠቀም ላይ እንደሚገኙ፣ የቤቱ ግምት ድርሻቸውም ብር 33,547.90 (ሰላሳ ሶስት ሺህ አምስት መቶ አርባ ሰባት ብር ከዘጠና ሳንቲም)፣ የኪራይ ደግሞ ብር 8118.75(ስምንት ሺህ አንድ መቶ አስራ ስምንት ብር ከሰባ አምስት ሳንቲም) እንደሚሆን ገልፀው አመልካቾች ገንዘቡን እንዲከፍሏቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾችም በተከሳሽነታቸው ቀርበው ክሱ የቀረበው አውራሻቸውን ከሞቱበት ከመስከረም 28 ቀን 1980 ዓ.ም በኋላ ታህሳስ 24 ቀን 1992 ዓ.ም በመሆኑ እና ይህንንም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000(1) ስር የተመለከተው የሶስት ዓመት የይርጋ ጊዜ ገደብ የሚያግደው ነው፣ የኪራይ ገንዘብ ጥያቄም ከዘጠኝ ዓመትና ከሰባት ወር በኋላ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(መ) መሰረት እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን አንስተው የተከራከሩ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ተገቢነት አሏቸው ያሏቸውን ነጥቦችን በማንሳት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ አመልካቾች ብር 7422.50 (ሰባት ሺህ አራት መቶ ሀያ ሁለት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) እንዲከፍሉ፣ ቤቱን በተመለከተም 1/2ኛው ለአንደኛ አመልካች ከተሰጣቸው በኋላ ሌላው ቀሪውን 1/2ኛው ከተቻለ በአይነት፣ ካልተቻለ በስምምነት ወይም በሐራጅ ከተሸጠ በኋላ 1/6ኛው ለተጠሪ እንዲሰጥ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይገባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይርጋን በተመለከተ የቀረበው ቅሬታ፤ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ጥያቄ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ እንጂ የወራሽነት ጥያቄ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000/1/ መሠረት እንደማይታገድ፣ የኪራይ ገንዘብ ጥያቄም የተከራይና አከራይ ግንኙነት የሌለ በመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2024/መ/ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ የአመልካቾችን የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ ካደረገ በኋላ ቤቱን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ያስቀመጠውን ክፍፍል በማሻሻል ተገቢ ነው ያለውን የክፍፍል መንገድ በመጥቀስ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይርጋንና የቤቱን ክፍፍል አስመልክቶ የተሰጠውን ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ ሰኔ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው

ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000/1/ ሆኖ እያለ የይርጋ ክርክሩ መታለፉና ቤቱን በተመለከተ የተሰጠው የክፍፍል ጥያቄም የአንደኛዋን አመልካች ግማሽ ባለድርሻነት አለማገናዘቡ ተገቢነት የሌለው ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ቀርበው ጥቅምት 4 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የመልሳቸው ይዘትም የይርጋ ክርክሩ የታለፈው ጥያቄው የውርስ ንብረት ክፍፍል በመሆኑ መሆኑንና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ ድንጋጌ ተፈፃሚነቱ የወራሽነት ጥያቄን በሚመለከት ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካቾች ህዳር 1 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነ ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ሲባል ከተያዘው የይርጋ ክርክር የመታለፉ አግባብነት አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የሚች ወራሽነታቸውን ከአመልካቾች ጋር በአንድነት ህዳር 11 ቀን 1980 ዓ.ም በፍርድ ቤት ማስወሰናቸውን፣ አሁን እየተከራከሩ ያሉት የውርስ ንብረት ድርሻቸውን አመልካቾች እንዲያካፍሏቸው መሆኑን ነው፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000 የወራሽነት ጥያቄ የማቅረቢያ የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 996 እስከ 1002 ድረስ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 999 ስር በተመለከተው መሠረት የሚቀርበው የወራሽነት ጥያቄ (Petition hereditists) በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 996 እና ተከታዬቹ ቁጥሮች ከተገለፀው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የወራሽነት ጥያቄ አንድ ወራሽ በሌላ በወራሽነት የውርስ ሐብት በያዘ ሰው ላይ ክስ ሲያቀርብ ተፈፃሚነት ባላቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች ስር በተመለከቱት ደንቦች መሰረት የሚገደብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የሚች ኮሎኔል ክፍሌ ደስታ ወራሽነታቸውን ህዳር 11 ቀን 1980 ዓ.ም ከሌሎች ወራሾች ጋር በመሆን በፍርድ ቤት ውሳኔ አረጋግጠው የክፍፍሉ ጥያቄ በቀረበበት ቤት ውስጥ ከአመልካቾች ጋር ይኖሩ የነበረ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም የምንገነዘበው የሚቹ ወራሾች ተለይተው መታወቃቸውን ነው፡፡ የተጠሪ ጥያቄ ደግሞ የውርስ ክፍያ ነው፡፡ የውርስ ክፍያ ደግሞ ራሱን የቻለ የውርስ ህግ ሆኖ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1060 እስከ 1113 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ስር የተሸፈነ ጉዳይ ነው፡፡ የውርስ ክፍያ ጊዜን በተመለከተ የፍ/ብ/ሕጉ በአንቀጽ 1062 ስር የደነገገ ሲሆን የድንጋጌው ይዘትም ውርሱ በተጣራ ጊዜ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን እያንዳንዱ የጋራ ወራሾች ውርሱን እንክፋፈል ብለው ለመጠየቅ እንደሚችሉ መደንገጉን የሚያሳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1060 ድንጋጌ ስር ደግሞ የውርስ አከፋፈል እስካልተፈፀመ ድረስ ውርሱ በወራሾች መካከል ሳይነጣጠል እንደሚቆይ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የሚች ወራሽነታቸውን በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ አረጋግጠው ከቆዩ በኋላ የውርስ ንብረቱን የክፍፍል ጥያቄ ማቅረባቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ እና /2/ ስር በተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ የሚታገድ ሳይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1062 ድንጋጌ መሠረት በማናቸውም ጊዜ የሚቀርብ በመሆኑ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የፈፀመው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለ ለማለት አልተቻለም፡፡

ሌላው አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት በቤቱ ላይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የክፍፍል ሥነ-ሥርዓቱን በተመለከተ ነው፡፡ የውርስ አከፋፈል አሰራርን በተመለከተ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1082 እስከ 1096 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት መፈፀም ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1083 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ በዚህም መሠረት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ሲታይ በህጉ የተመለከተውን የውርስ አከፋፈል አሰራርንና በቤተሰብ ህጉም የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን ያገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር የአንደኛ አመልካችን መብትም ሆነ የሌሎችን አመልካቾችን መብት ያጣበበ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ አመልካቾች ለተጠሪ የቤቱን ግምት ከፍለው ቤቱን በአይነት ለማስቀረት ከፈለጉም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1060/2/ የጋራ ወራሾች የሆኑ ሰዎች ባልተከፋፈሉት የውርስ ንብረቶች ላይ ያላቸው መብት ስለ የጋራ ባለሐብትነት፣ ስለ ሪምና ስለ ሌሎች ግዙፍ መብቶች በሚለው የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ በተነገሩት ድንጋጌዎች መሠረት ይወሰናል በማለት ስለሚደነግግ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት የቤቱን የገቢያ ዋጋ ለተጠሪ በመስጠት

የቅድሚያ ግዥና መብት (Right of Recovery) ጥያቄ ከሚያነሱ በስተቀር ከወዲሁ ተጠሪ ቤቱን በሐራጅ እንዲሸጥ መጠየቅ አይችሉም በማለት ሊቃወሙ የሚችሉበት ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካቾች ቅሬታም ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም፤ ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ ውሳኔ ያሳረፈው ፍርድ ቤት የውርስ ህግ ድንጋጌዎችና አፈፃፀም ላይ የፈፀመው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስላልተገኘ ውሳኔው ሊፀና የሚገባ ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00668 ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 61968 ሚያዚያ 22 ቀን 2000 ዓ.ም ተሻሽሎ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ሥ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

የሰ/መ/ቁ 42569

ታህሳስ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** 1. ዳግማዊ ታዲዮስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ

ወ/ሮ ፍሬህይወት ታመነ

2. ናትናኤል ታዲዮስ

} ጠበቃ ፋንታሁን አባተ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የሃና ታዲዮስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ

ወ/ሮ ቤተልሄም ግርማ - ጠበቃ አልታዬ ወ/አማኑኤል - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ልጅነት ይታወቅልኝ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪ ሞግዚትና አስተዳዳሪ መጋቢት 13 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ሕፃን ሐናን ከአቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ የወለድኳት ስለሆነ ሕፃን ሐና የአቶ ታዲዮስ ልጅ መሆኗ በፍርድ ውሳኔ ይታወቅልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀው ፍርድ ቤቱም የአሁኑ አመልካቾች በሌሉበት የተጠሪን ምስክሮችን በመስማት የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 143(መ)"ን" መሰረት በማድረግ ሕጻን ሐና የአቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ ልጅ ናት በማለት ግንቦት 22 ቀን 1997 ዓ.ም ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካቾች ውሳኔው መብታችንን የሚነካ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 መሰረት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ለመቃወሚያው መሰረት ያደረጓቸው ነጥቦችም ለውሳኔ መሰረት የሆነው የልደት ምስክር ወረቀት የወጣው አቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ ህዳር 06 ቀን 1997 ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ጥር 18 ቀን 1997 ዓ.ም ነው፣ የጥምቀት ምስክር ወረቀቱም አቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ ያልፈረሙበት ነው፣ የተሰሙት ምስክሮችም ለውሳኔው መሰረት የሆነው ድንጋጌ የሚጠይቀውን መመዘኛ በሚገባ አላስረዱም የሚሉ ናቸው፡፡ የአሁኗ ተጠሪም በአመልካቾች መቃወሚያ ላይ መልስ ሲሠጡ በጉዳዩ ላይ የቀረቡት የጽሑፍ ማስረጃዎች የወጡበት ሁኔታ በአሰራር ደረጃ የተለመደ በመሆኑ ማስረጃዎች በሕግ ፊት ተቀባይነት ያላቸው መሆኑንና ሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅም ሕፃን ሐናን እንደአባት ሆነው ሲንከባከቧት የነበረ መሆኑ በምስክሮች ባግባቡ መመስከሩን ገልፀው መቃወሚያው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ሕፃን ሐና የሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅ ልጅ ስለመሆኗ ልጅነት በፍርድ ከሚታወቅባቸው መንገዶች መካከል በአንዱ አልተረጋገጠም በማለት ቀደም ሲል የሠጠውን ውሳኔ ሠርዞታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ እና የተጠሪ ምስክሮችን በድጋሚ ከተሰሙ በኋላ ሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅ ከሕፃን ሐና ወላጅ እናት ጋር ቀጣይነት ባለው ግንኙነት ውስጥ እንደነበሩ፣ ሕፃኗን እንደ አባት በመሆን ያሳድጓት እንደነበር መረጋገጡን እና የልደት ምስክር ወረቀትም ማስረጃውን በሠጠው አካል እስካልተሠረዘ ድረስ ተቀባይነት እንዳለው በመግለፅ ሟቹ የአቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ የህፃኗ አባት መሆናቸው በልደት ምስክር ወረቀትና በምስክሮች ቃል ተረጋግጧል

በማለት በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 51348 ሰኔ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የተሠጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ ጥር 06 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቀርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የልደት ምስክር ወረቀቱ አቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ ከሞቱ በኋላ የወጣ መሆኑ እየታወቀ እና የተጠሪ ምስክሮች ቃልም የሕፃኗ እናት እና አባት የተባለው ሰው በሕግ በተመለከተው የእርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በግብረ ስጋ ግንኙነት አብረው የነበሩ ስለመሆኑ ሕጉ በሚጠይቀው መመዘኛ የመሰከሩ ስለመሆኑ የማያረጋግጥ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ በሕጉ የተቀመጠውን ጥብቅ መመዘኛ በማለፍ ሟች የሕፃን ሐና አባት ናቸው ብሎ የወሰነው ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ሕፃን ሐና የሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅ ልጅ ናት በሚል የተሠጠው የልጅነት ምስክር ወረቀት ሟች ከሞቱ በኋላ የተሠጠ ነው እየተባለ የስር ፍርድ ቤት ይህንን የልጅነት ምስክር ወረቀት ብቻ መሰረት አድርጎ ሟች የሕፃኗ አባት ናቸው በማለት የሠጠው ውሳኔ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ሐምሌ 08 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ ተገቢነት ያለው መሆኑን ያሳያሉ ያሏቸውን ምክንያቶችን በመዘርዘር መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካቾች ጠበቃም ነሐሴ 20 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ አንድ ገፅ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባዋል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪው የልደት ምስክር ወረቀት ለተጠሪ የተሠጠው አቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ ሕዳር 06 ቀን 1997 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ጥር 18 ቀን 1997 ዓ.ም መሆኑን፣ ይህንኑ የልደት ምስክር ወረቀት የሠጠው አካልም ሥልጣን ያለው ሆኖ ማስረጃውን ያልሰረዘው መሆኑን፣ ተጠሪ ከዚህ የሰነድ ማስረጃ በተጨማሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ማስረጃ የሰው ምስክሮችን የሚጨምር መሆኑን የስር ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሠጠው የሰነድ እና የሰው ምስክሮች ቃል በመመዘን መሆኑን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜም ሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅ የህፃን ሐና አባት መሆናቸው በልደት ምስክር ወረቀትና በምስክሮች ቃል ተረጋግጧል የሚል ስለመሆኑም የውሳኔው ግልባጭ በግልፅ የሚያሳይ መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡ ልጅነት ደግሞ በቀዳሚነት በልጅነት የምስክር ወረቀት የሚረጋገጥ ሲሆን የልጅነት ምስክር ወረቀት ከሌለ ደግሞ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በማሳየት እንደሚረጋገጥ፣ የልጅነት ሁኔታ የሌለ ከሆነ ሲሆንም ተወላጅነትን በምስክሮች ወይም ማናቸውንም ዓይነት ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት እንደሚቻል የተሻሻለው የቤተሰብ ሕጉ እንደቅደም ተከተሉ በአንቀፅ 156፣ 168፣ 158፣ እና 169 ስር ደንግጓል፡፡ አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት ደግሞ የልደት ምስክር ወረቀት ለተጠሪ የተሠጠበት ጊዜ ሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅ ከሞቱ በኋላ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የልደት ምስክር ወረቀት አባት ነው የተባለው ሰው ከሞተ በኋላ የተሠጠ ሆኖ ሲገኝ ዋጋ የለውም የሚል የሕግ ድንጋጌ የሌለ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ማስረጃው በተገቢው አካል እስካልተሰረዘ ድረስ ዋጋ አለው በማለት ከተጠሪ የሰው ምስክሮች ቃል ጋር አዛምዶ በመመዘን ክብደት መስጠቱ በማስረጃ አቀባበል ላይ የተፈፀመ ስህተት ስለመኖሩ የሚያሳይ አይደለም፡፡ ይልቁንም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሲታይ መሰረት ያደረገው ማስረጃ ምዘናን ነው፡፡ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ደግሞ የሰበር ችሎት ስልጣንና ኃላፊነት አለመሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 80(3/ሀ) እና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 እና 22 ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ሊፀና የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 57322 ጥቅምት 10 ቀን 2001 ዓ.ም በተሠጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር ታህሳስ 01 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ሕፃን ሐና የሚች ታዲዮስ ሐረገወርቅ ልጅ ናት ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ 47487

ታህሳስ 27 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሀይለራጉኤል ደበላ - ጠበቃ ገመቹ ሮሮ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሪት አለምፀሀይ ፈለገ
2. አቶ አቦነህ ፈለገ
} ጠበቃ ባርናባስ ደስታ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ጥር 13 ቀን 1999 ዓ.ም በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ የአመልካች አባት የነበሩት ሟች አቶ ደበላ ልቡ ከወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል ጋር ጋብቻ ከማድረጋቸው በፊት የነበሯቸውንና ቁጥራቸው 1056/1057 የሆኑት የግል ቤቶች መስከረም 19 ቀን 1956 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ወ/ሮ ክብነሽ በሕይወት እስከአሉ ድረስ እንዲኖሩ እና እንዲጠቀሙበት ከሞቱ በኂላ ወደ ወራሾች እንዲተላለፍ በማለት መናዘዛቸውን፣ ኑዛዜውም በፍ/ቤት መፅደቁም፣ ኑዛዜው ወ/ሮ ክብነሽ ቤቱን ከፈለጉ እንዲሸጡ፣ እንዲለውጡ የሚል ቢሆንም በውርስ እንዲያስተላልፉ የሚያዝ ሆኖ እያለ ለዘመዶቻቸው ማውረሳቸውን ገልፀው ተጠሪዎች ያላግባብ የያዙትን ቤት ለቀው እንዲያስረክቧቸው፣ ተጠሪዎች ለተጠቀሙበት የቤት ኪራይ አመልካች የመጠየቅ መብታቸው ተጠብቆ እንዲወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎችም በተከሳሽነት ቀርበው በሠጡት መልስ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ በሟች አቶ ደበላ ልቡ ኑዛዜ መሰረት ንብረቱን ወደራሳቸው በማዞር የግል ንብረት በማድረግ ሲጠቀሙበት የቆዩ በመሆኑና ክሱም ኑዛዜው ከተፈፀመ በኂላ የቀረበ በመሆኑ እንዲሁም ኑዛዜውን ለመቃወም የሚቀርብ ክስን ስርዓት ተከትሎ ያልቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚሉ ነጥቦችን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስተው የተከራከሩ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ሟች አቶ ደበላ ባደረጉት ኑዛዜ ወ/ሮ ክብነሽ ቤቱን ለመሸጥ፣ ለመለወጥ እንዲችሉ ስልጣን የሚሠጥ በመሆኑ ወ/ሮ ክብነሽ ንብረቱን ለሌላ የማስተላለፍ መብት አላቸው ንብረቱንም በስማቸው አዙረው ሲጠቀሙበት ቆይተው ግንቦት 27 ቀን 1996 ዓ.ም በውልና ማስረጃ በተደረገ ኑዛዜ ለተጠሪዎች የሰጧቸው በመሆኑ የአመልካች ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጀ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የተጠሪዎችን ክርክር ውድቅ አድርጎ ሟች አቶ ደበላ ልቡ መስከረም 19 ቀን 1956 ዓ.ም አደረጉ የተባለው ኑዛዜ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል በኑዛዜ ንብረቱን ለማስተላለፍ ሥልጣን የሚሠጥ አይደለም፣ የሟች ደበላ ልቡ ኑዛዜ ከወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል ሞት በኂላ ተፈፃሚነት አለው በሚል ምክንያት ተጠሪዎች አከራካሪውን ቤት ለአመልካች እንዲያስረክቡ የቤት ኪራይ በተመለከተ ከቤቱ ጋር ክስ መቅረብ የነበረበት ስለሆነ የአመልካች ወደፊት የመክሰስ መብት ሊጠበቅ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪዎች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ከአከራካሪው ኑዛዜ ይዘት ጋር በማገናዘብ መርምሮ በኑዛዜው ላይ ሟች አቶ ደበላ ልቡ ወ/ሮ ክብነሽ ሕይወቷ እስካለ ድረስ በከፊል ወይም በሙሉ ለመሸጥ በፈለገች ጊዜ ልትሸጥና ልትለውጥ ትችላለች፣ ለመሸጥ

በፈለገች ጊዜ ወራሾቿ ወይም ወራሾቹ እርሷ ፈቅዳ ካልሰጠቻቸው ሊቃወሟት አይችሉም በሚል ያስቀመጡ ስለሆነና ይህ የተናዛዡ ሀሳብ የሚያስገነዝበው ደግሞ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ካልፈቀዱ በቀር ቤቱን ለፈለጉት ሰው ቢሰጡ ከኑዛዜው መልዕክት ውጪ እንዳደረጉ የሚያስቆጥር አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 13 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ሟች አቶ ደበላ ልቡ ባደረጉት ኑዛዜ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል ንብረቱን ለመሸጥ፣ ለመለወጥ ትችላለች ተብሎ የተቀመጠው ሐረግ በኑዛዜ ለሌላ ሰው መሥጠትን ያጠቃልላል ተብሎ የተተረጎመው ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ንብረቱን ለራሳቸው ጥቅም ብቻ ለመሸጥ፣ ለመለወጥ ይችላሉ የሚል ግልፅ የሆነ ቃል እንጂ ለሌላ ሰው ጥቅም ንብረቱን እንዲለውጡ ወይም እንዲሸጡ የሚል መልዕክት የሌለው ግልፅ ቃል ሆኖ እያለ ይህንኑ ግልፅ ቃል በሚጻረር መልኩ መተርጎሙ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ሟች አቶ ደበላ ልቡ ያደረጉት ኑዛዜ ወ/ሮ ክብነሽ ንብረቱን ሊሸጡ፣ ሊለውጡ እንጂ እርሳቸው በኑዛዜ እንዲያስተላልፉ የሚያስችላቸው እንደሆነ ተደርጎ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መስከረም 26 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪው ንብረት የሟች አቶ ደበላ ልቡ የግል ንብረት መሆኑን ተጠሪዎች አለመካዳቸውን፣ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል የሟች አቶ ደበላ ልቡ ሚስት የነበሩ መሆኑን፣ አቶ ደበላ ልቡ ለወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል መስከረም 19 ቀን 1956 ዓ.ም የተደረገ ኑዛዜ የተውላቸው መሆኑን፣ ይህንኑ ኑዛዜም በከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1553/59፣ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ በመ/ቁጥር 70/62 ማስፀደቃቸውን፣ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል ግንቦት 27 ቀን 1996 ዓ.ም ውል እና ማስረጃ ክፍል ባደረጉት ኑዛዜ ደግሞ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት ለሁለተኛ ተጠሪ፣ ለወ/ት ትዕግስት ፈለገ፣ ለወ/ት ኩላገር ፈለገ፣ ለወ/ት ወለላ ፈለገ፣ ለወ/ት ሙላቷ ፈለገ እና ለሕፃን ዮሴፍ እንዳሳ ፈለገ የተናዘዙላቸው መሆኑን ነው፡፡ አከራካሪው ነጥብ ሟች አቶ ደበላ ልቡ በተውት ኑዛዜ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል ንብረቱን ከፍጻሜ ሕይወታቸው በኂላ በኑዛዜ ለሌላ ሰው የማስተላለፍ መብት/ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል ወይስ አልተሰጣቸውም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ለጉዳዩ እልባት መስጠት ይቻል ዘንድም ሟች አቶ ደበላ ልቡ መስከረም 19 ቀን 1956 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ቃል አግባብነት ያለውን ክፍል ተመልክተናል፡፡ ይኸው የኑዛዜ ክፍል *"የሰጠኂትን ቤት ከነቦታው ሕይወቷ እስካለ ድረስ በክፊል ወይም በሙሉ ለመሸጥ በፈለገች ጊዜ ልትሸጥ ልትለውጥ ትችላለች፣ ለመሸጥ በፈለገች ጊዜ ወራሾቿ ወይም ወራሾቹ እርሷ ፈቅዳ ካልሰጠቻቸው ሊቃወሟት አይችሉም፣ ..... ከዚህ በላይ እንደተጻፈው ቃል የሰጠኂትን ሀብትና ንብረት ለውጣ እራሷ የምትጦርበት ሲሆን ከርሷ የተረፈ ቢኖር ግን ውርሱ ለልጇ አርያና ለልጅ ልጇ ለኃይለራጉኤል መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከቀሪው ሀብቴ ጋር አንድ ላይ ተደባልቆ ከኔ በተወለዱት ማለት ከሙሉነሽ ላይ ለወለድኂቸው ልጆች ብቻ ከክብነሽ የማደን ልጆቿ ጋር እንደየድርሻቸው ሊከፋፈሉ ይችላሉ ....."* በሚል የተቀመጠ ነው፡፡

በመሰረቱ ኑዛዜ ሊተረጎም የሚገባው ቃላቶቹ እና መልእክቱ ግልፅ ሳይሆን ሲቀር ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ኑዛዜው ግልፅ ቃላቶችንና መልዕክትን የያዘ ከሆነ ትርጓሜ መስጠት አያስፈልግም፡፡ ይህንን መሰረታዊ መርህን መከተል ያለብን መሆኑን ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 910(2) ድንጋጌ በግልፅ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም የኑዛዜው ቃል መተርጎም ያለበት ስለኑዛዜው መልእክት ጥርጣሬ በሚፈጥርበት ጊዜ አሻሚ ወይም ግልፅ ያልሆነ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ይህን ደንብ ተፈጻሚ የሚሆንበትን መንገድም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 910(1)፣ 911፣ 925 እና ሌሎች

ድንጋጌዎች ያሳዩናል፡፡ ስለሆነም የኑዛዜው ቃላት ግልፅ የሆኑ እንደሆነ የተናዛዡ እውነተኛ፣ ትክክለኛ ፈቃድ የትኛው ነው ብሎ ትርጓሜ መስጠትና ከኑዛዜው ቃል መራቅ የማይፈቀድ ስለመሆኑ ከላይ የተጠቀሱት የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የሟች አቶ ደበላ ልቡ ኑዛዜ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል በሕይወት እስካሉ ድረስ ለመሸጥ፣ ለመለወጥ የሚያስችላቸው እንጂ ከራሳቸው ጥቅም ውጪ ለሌላ ሰው በኑዛዜ እንዲያስተላልፉ የሚያስችላቸው አለመሆኑን ከላይ የተገለፀው የኑዛዜ ክፍል ያሳያል፡፡ በመሆኑም ይኸው የኑዛዜ ክፍል የሟች ፍላጎትና መልዕክት ግልፅ የሚያደርገው ሆኖ እያለ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የኑዛዜውን አንድን ክፍል ብቻ ነጥሎ ትርጉም የሠጠው ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 910(1) እና (2) ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን የኑዛዜ አተረጓጎም መርህን ባላገናዘበ መልኩ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 60988 ጥር 29 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 44232 ሚያዚያ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15647 ጥቅምት 22 ቀን 2000 ዓ.ም የተሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 41893

*ታህሣሥ 21 ቀን 2002 ዓ.ም*

***ዳኞች፡-*** *መንበረፀሐይ ታደሰ*

*ሐጐስ ወልዱ*

*ሒሩት መለሰ*

*ታፈሰ ይርጋ*

*አልማው ወሌ*

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዮዲት ኃይሉ የህፃን ሄኖክ ዳንኤል ሞግዚትና አሳዳጊ ቀረበች፡፡

***ተጠሪዎች፡-*** 1. ወ/ሪት ገነት አረጋይ
2. ወ/ሮ አዜብ አረጋይ
3. ወ/ሮ ሰብለ አረጋይ
} ጠበቃ ታምራት ኪዳነ ማሪያም - ቀረበ

*መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡*

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍልን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረችው አመልካች ስትሆን፣ፍ/ቤቱ ቀደም ሲል በሰጠው ትእዛዝ መሰረት በውርስ አጣሪ ተጣርቶ የቀረበውን የውርስ ክፍፍል የውሳኔ ሐሳብ በመቃወም ተከራክራለች የውርስ አጣሪው ባቀረበው የውሣኔ ሐሳብ ላይ ባቀረበችው የጽሑፍ አስተያየት በወረዳ 23 ቀበሌ 10 ውስጥ የሚገኘው ቁጥር 1220 የሆነው ቤት ከሟች እማሆይ ምጽላል ተድላ ለወ/ሮ የሺንርኤ በስጦታ የተላለፈ ነው፡፡ ወ/ሮ የሺንርኤ የህፃን ሄኖክ አባትን (ዳንኤል አረጋይን) ጨምሮ አራት ወራሾች አሉዋቸው፡፡ በመሆኑም የቤቱ ¼ኛ ድርሻ የህፃን ሄኖክ አባት ነው፡፡ አጣሪው የወ/ሮ የሺንርኤ ወራሾች ስምንት(8) እንደሆኑ አድርጐ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም፡፡ የእማሆይ ምጽላል ተድላ 8(ስምንት) ልጆች በማከል ውርሱ እንዲከፋፈል በማለት የውሳኔ ሐሳብ ማቅረቡም ትክክል አይደለም የሚሉትንና ሌሎች ነጥቦችንም በማከል እንደተከራከረች በመዝገቡ ተመልክቶአል፡፡

በወቅቱ ተከሣሾች የነበሩት ተጠሪዎችም በበኩላቸው ባቀረቡት አስተያየት እማሆይ ምጽላል ተድላ ቤቱን ለወ/ሮ የሺንርኤ የሰጡት በሕይወት እስካሉ ድረስ እንዲጠቀሙበት ብቻ ነው፡፡ ወ/ሮ የሺንርኤ ከሞቱ በኂላ ሐብቱ የሟች እማሆይ ምጽላል ተድላ ስለሚሆን የእማሆይ ምጽላል ተድላ ወራሾች ለሆንነው ለስምንታችን ይከፋፈላል፡፡ ከስምንቱ የእማሆይ ምጽላል ተድላ ልጆች ውስጥ ሟች ወ/ሮ የሺንርኤ አንድዋ ስለመሆኑ የሚደርሳቸው ከቤቱ 1/8ኛ ነው፡፡ ይህ 1/8ኛ ደግሞ ለስምንቱ ልጆቻቸው (ለወ/የሺንርኤ ልጆች) ይከፋፈላል፡፡ ከእነዚህ ልጆች ውስጥ የህፃን ሄኖክ አባት አንዱ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ህፃን ሄኖክ የሚወርሰው የአባቱን ድርሻ ስለሆነ ሊያገኝ የሚችለው ከቤቱ 1/56ኛ ነው በማለት የውርስ አጣሪው ያቀረበው አማራጭ ሃሳብ እንደግፋለን በማለት ክርክራቸውን አሰምተዋል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ የተጠሪዎችን ክርክር እንዳለ በመቀበል የህፃን ሄኖክ ዳንኤል ድርሻ 1/56ኛ ነው በማለት ወስኖአል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች *ታህሣሥ* 7 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው እማሆይ ምጽላል ተድላ መጋቢት 14 ቀን 1964 ዓ.ም ላደረጉት ስጦታ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ትርጓሜ አግባብነት

ለመመርመር ነው። በዚህ መሰረትም ግራ ቀኝ ወገኖች በዚህ ረገድ ያሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል።

እንደምንመለከተው ለቀረበው ክርክር አወሳሰን በዋንኛነት መሰረት የሆነው እማሆይ ምጽላል ተድላ ለልጃቸው ለወ/ሮ የሺ.ንርኤ ያደረጉት የስጦታ ውል ነው። የስጦታ ውሉ እማሆይ ምጽላል አከራካሪውን ቤት በወ/ሮ የሺ. መሰጠታቸውን ያመለክታል። ይህ አከራካሪ አልሆነም። አከራካሪ የሆነው በስጦታው ውሉ ወ/ሮ የሺ. ያገኙት መብት የባለሃብትነት ነው ወይስ የመጠቀም ብቻ? የሚለው ነው። የሥር ፍ/ቤቶች "…. እስከ እድሜ ልኳ ድረስ ማንም ሰው እንዳይጠይቃት ሰጥቻታለሁ።" የሚለውን ሐረግ ነጥለው በመያዝ ወ/ሮ የሺ. በስጦታ ውሉ ያገኙት መብት ከባለሃብትነት በመለስ ያለው ነው የሚል ትርጓሜ ሰጥተዋል። በበኩላችን እንዳየነው ውሉን በትክክል መተርጐም የሚቻለው አንድዋን ሐረግ ለይቶ በውጣት ሳይሆን፣አጠቃላይ ይዘቱን በማየት እንደሆነ ነው መገንዘብ የቻልነው። እማሆይ ምጽላል በስጦታ ውሉ የገለጹት ቤቱ የተሰራው በወ/ሮ የሺ.ንርኤ ቦታ ላይ መሆኑን፣ስመ ሐብቱ በእማሆይ ምጽላል ቢመዘገብም፤የሰሩት ግን ወ/ሮ የሺ.ንርኤ እንደሆኑ ለወደፊቱ (የስጦታ ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ) ወ/ሮ የሺ.ንርኤ የቦታውን ካርታ በስማቸው አስነስተው እስከ እድሜ ልካቸው ድረስ ማንም ሰው ሳይጠይቃቸው የተሰጣቸው መሆኑን፣በአጠቃላይ እማሆይ ምጽላል ቤታቸውን ለልጃቸው (ለወ/ሮ የሺ.ንርኤ) የሰጡዋቸው መሆኑን ነው። እነዚህ በስጦታ ውሉ የተመለከቱት ፍሬ ነገሮች ተያይዘው ሲታዩ በትክክል የሚያረጋግጡት እማሆይ ምጽላል ቤታቸውን ለልጃቸው ያለምንም ገደብ ለመስጠት አስበው መነሳታቸው እና ይህን ሐሳባቸውም በውሉ በቂ በሆነ ሁኔታ መግለፃቸውን ነው። ወ/ሮ የሺ.ንርኤ የቦታውን ካርታ በስማቸው አስነስተው እንዲይዙ ተፈቀደላቸው ማለት ቤቱ በሃብትነት ተሰጥቶአቸዋል ከማለት ውጪ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ የለም በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች በስጦታ ውሉ የሰጡት ትርጓሜ በእርግጥም በውሉ የተገለጸውን የስጦታ አድራጊዋ ሐሳብና ፍላጐት መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም።

የስጦታ ውሉ ከፍ ሲል በተመለተው ሁኔታ የሚተረጐም እስከ ሆነ ድረስ ቤቱ የወ/ሮ የሺ.ንርኤ ሐብት ሆኖአል ማለት በመሆኑ የውርስ ማጣራቱ ሂደትም የኘው የወ/ሮ የሺ.ንርኤ ውርስ የሚመለከት ነው የሚሆነው። ውርሱን እንዲያጣራ የተሾመው ውርስ አጣሪ የወ/ሮ የሺ.ንርኤ ልጆች 8(ስምንት) እንደሆኑ በማረጋገጥ ንብረቱ ለ8ቱ በማካፈል አመልካች ሞግዚት የሆነችለት ህፃን ሄኖክ ዳንኤል ድርሻ 1/8ኛ እንደሆነ በመግለጽ በአንድ በኩል ሲያቀርብ በሌላ በኩል ደግሞ የእማሆይ ምጽላል 8 ልጆችም የውርሱ ተካፋይ እንደሆኑ በመቁጠር የህፃን ሄኖክ ድርሻ 1/56ኛ ነው የሚል ሁለተኛ አማራጭ አቅርቦአል። በግልጽ እንደሚታየው የሁለተኛው አማራጭ መነሻ ቤቱ የእማሆይ ምጽላል ሐብት ነው የሚለው ነው። ይህ የሆነው ግን የስጦታ ውሉን በተሳሳተ ሁኔታ በመተርጐም በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም። በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሁለተኛውን አማራጭ በመቀበል የውርስ ክፍፍሉ እንዲከናወን መወሰኑ ትክክል አይደለም። በሌላ በኩል ግን የወ/ሮ የሺ.ንርኤ ልጆች (ወራሾች) 8 (ስምንት) መሆናቸው በውርስ አጣሪው የተረጋገጠ በመሆኑ ውርሱ የሚከፋፈለው ለስምንቱ ወራሾች እንጂ አመልካች እንደምትለው ለህፃን ሄኖክ አባት እና ለሦስቱ ተጠሪዎች ብቻ አይደለም። በዚህ ስሌትም የውርስ አጣሪው ባቀረበው ሪፖርት አንደኛው አማራጭ መሰረት የህፃን ሄኖክ ዳንኤል ድርሻ ከቤቱ 1/8ኛ (አንድ ስምንተኛ) ይሆናል። ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች ለስጦታ ውሉ የሰጡት ትርጓሚ የተሳሳተ በመሆኑ ታርሞ የውርስ ክፍፍሉ መደረግ ያለበት ቤቱ የሟች ወ/ሮ የሺ.ንርኤ ሐብት እንደሆነ በመቁጠር ነው ብለናል።

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04749 የካቲት 14 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 54613 ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች ሞግዚትና አስተዳዳሪ የሆነችለት የህፃን ሄኖክ ዳንኤል ድርሻ የቤቱ 1/8ኛ (አንድ ስምንተኛ) ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡ ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 47957

ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡-1. አቶ ተፈሪ ሐጎስ

2. አቶ ዛፉወርቅ ሐጎስ — ወኪል አንደኛ አመልካች - ቀረቡ

3. ወ/ሮ ፃጌሃና ሐጎስ

ተጠሪ፡- አቶ ተስፋይ ገ/እግዚአብሔር - ጠ/መድህን መሐሪ - ቀረቡ

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የውርስ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካwች ለምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት መቃወሚያ የእህታቸው ልጅ አቶ ሣምሶን ተስፋይ ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን የሚቹ ወራሾች ተጠሪ ብቻ ሣይሆኑ አመልካwችም መሆናቸውን ተጠሪ ግን ለብቻቸው ውርስ አጣርተው በፍ/ቤት ማፀደቃቸውን ገልፀው ይኸው ሪፖርትና ሪፖርቱን መሠረት ተደርጎ ለተጠሪ የተሰጣቸው የወራሽነት ምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ ጠይቀዋል፡፡ በተጨማሪም በሟች ስም የተመዘገበው ቤት ከእናት ወገን የመጣ በመሆኑ ሊወርሱ የሚገባቸው አመልካwች ብቻ መሆናቸው የሟች ገንዘብን በተመለከተ ከተጠሪ ጋር እኩል ሊካፈሉ እንደሚገባና በዚሁ መሠረት የወራሽነት ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ለቀረበው መቃወሚያ በሰጡት መልስ ክርክር የተነሣበት ቤት የተሰራበትን ቦታ ወ/ሮ አመዘነች ከማዘጋጃ ቤት ተመርተው ለልጃቸው ለወ/ሮ አበበች ሐጎስ በስጦታ ሰጥተዋቸው ወ/ሮ አበበች ቤት እንደሰሩበት አመልካwች ቦታው የእናታችን ነው በሚል ክስ አቅርበው ተጠሪ ልጃቸውን ወክለው ተከራክረው ቦታው የወ/ሮ አበበች ነው ተብሎ መወሰኑን ቦታው በምሪት የተገኘ እንጂ በውርስ የተላለፈ ርስት ባለመሆኑ የቤተሰብ ንብረት ነው ሊባል እንደማይቻል ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ርስት የሚለው ቃል መሬት የግለሰብ እያለ መሸጥ መለወጥ በሚቻልበት ጊዜ የመጣ ሆኖ በአንድ ወገን ዘር ሐረግ የመጣ ቅርስ መሠረት በማድረግ ነው በተያዘው ጉዳይ የሟች እናት ቦታውን በስጦታ ካገኙ በኂላ ንብረት ያስፈሩበት ስለሆነ የአንድ ወገን ዘር ሐረግ ነው ሊባል አይችልም፣ የሟች የአቶ ሳምሶን ተስፋይ ብቸኛ ወራሽ ተጠሪ ብቻ ናቸው የሚቹ እናት ሟችን ሣይወርሱ ስለሞቱ አመልካwች እህታቸውን ተክተው ሊወርሱ አይችሉም በማለት የአመልካwች ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካwች ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤትና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጎባቸዋል፡፡ የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካwች በአቤቱታቸው ወ/ሮ አመዘነች ለሟች እናት በስጦታ የሰጡት ቤት የነበረበት ቦታ ነው ስለሆነ ከእናት ወገን የተገኘ ንብረት ለእናት ወገን ሊሰጥ ይገባል፣ ቤቱን የሰሩት የሟች እናት ናቸው ቢባል እንኳን እህታቸውን ተክተው ሊወርሱ ስለሚችሉ ውርሱ ለተጠሪ ብቻ መተላለፉ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ችሎቱም የሟች ገንዘብ በሙሉ ተጠሪ እንዲወርሱ እና ከእናት ወገን የመጣ የማይንቀሣቀስ ንብረት /ቤት/ ለሟች አባት ይገባል በሚል የሰጠው ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክራቸውን አቅርቧል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪ የልጃቸውን ውርስ አጣርተው በፍ/ቤት በማፀደቃቸው አመልካwች ተቀዋሚ ሆነው ቀርበዋል፡፡ አመልካwች መቃወሚያ ያቀረቡት የሟች አቶ ሳምሶን ተስፋይ እናት የአመልካwች እህት በመሆናቸው የሟችን ውርስ እህታቸውን በመተካት የመውረስ መብት ያላቸው መሆኑን ምክንያት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ስለ ተተኪ ወራሽነት በፍ/ሕጉ ውስጥ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 842/3/ ስር እንደተመለከተው የሟች ልጆች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ሲሆኑ ልጆች ቀድመው ከሞቱና ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ ትተው ከሆነ ተወላጆቹ ወላጆቻቸውን ተክተው ሟችን እንደሚወርሱ ያመለክታል፡፡ ሟች ልጆች የሌሉት ከሆነ እናትና አባት ሁለተኛ ደረጃ ወራሾች እንደሚሆኑና አባት ወይም እናት ቀድመው ከሞቱም የእነሱን ፋንታ ልጆቻቸው ወይም ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆች እነሱን ተክተው እንደሚወርሱ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 843/ 844/2 ተመልክቷል፡፡ በአባት ወይም በእናት በኩል ወደታች የሚቆጠር ከሌለ ውርሱ በሙሉ ለሌላው መስመር ላለ ወራሽ እንደሚተላለፍ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 844/3 ያመለክታል፡፡ ከፍ ሲሉ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የተተኪ ወራሽነት የተፈፃሚነት ወሰን ወደታች በሚቆጠሩ ተወላጆች እንጂ ወደ ጎን በሚቆጠር ዝምድና እንዳልሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካwች የሟች እናት ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆች ሣይሆኑ ወደጎን የሚቆጠሩ ዘመዶች ወይም እህቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ከጅምሩም ቢሆን የሟችን እናት ተክተው ወራሽ ለመሆን የሚያስችላቸው መብት አልነበራቸውም፡፡ የሟች እናት ትተው የሄዱት ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆች ስለሌላቸው ውርሱ ሊተላለፍ የሚችለው ለሌላኛው መስመር ወራሽ በዚህ ጉዳይ ለሟች ወላጅ አባት ነው፡፡ በመሆኑም አመልካwች እህታቸውን ተክተው መውረስ ስለማይችሉ ቀድሞውንም ቢሆን ተቃውሞ ለማቅረብ የሚያስችላቸው መብት አልነበራቸውም፡፡ በዚህም ምክንያት የሟች እናት የተረከቡት ባዶ ቦታ ሣይሆን ቤት የተሰራበት ቦታ ነው የሚለው ክርክርም ሆነ የሟችን ገንዘብ ለመካፈል ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች የሟች አቶ ሳምሶን ተስፋይ ውርስ በሙሉ ለተጠሪ ሊተላለፍ ይገባል በማለት በሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የምዕራባዊ ዞን ማዕከላዊ ፍ/ቤት የመዝገብ ቁጥር ባልተጠቀሰ ጥር 21 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 7370 መጋቢት 11 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 30799 ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸው ይቻሉ

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 42346

የካቲት 9 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- 1. አቶ ፍስሐ መንግስቱ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ አበባ አርአያ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ አለምነሽ ፍስሐ - ቀረቡ ከጠ/ሰለሞን ተፈራ ጋር

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው የስጦታ ውልን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት አመልካቾች ሲሆኑ በክሳቸውም ልጃቸው ተጠሪ እንዲጦሯቸውና እንዲንከባከቧቸው ግዴታ በማስገባት በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 03/04 ክልል ውስጥ ቁጥር 1561 የሆነ ቤታቸውን በስጦታ የሰጧቸው ሲሆን የተጣለባቸውን ግዴታ ስላልተወጡ የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ በመልሳቸው የስጦታ ይፍረስልን ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው፣ቤቱ በስሜ ተዛውሯል፣በመሐከላችን ምንም አይነት የስጋ ዝምድና የለም፣የገባሁት ግዴታም የለም በነፃ ፈቃዳቸው ያደረጉት ውል ስለሆነ ሊፈረስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተጠሪ በውሉ ላይ አመልካቾችን ለመጦርና ለመቀለብ የገቡት ግዴታ ስለሌለ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካቾች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ተጠሪዎችን ሳይጠራ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች በቅሬታቸው ላይ ለተጠሪ ስጦታ የሰጡት ተጠሪዋ አመልካቾችን ለመጦርና ለመንከባከብ እንዲሁ ሌላ ቤት ገዝታ ለመስጠት ግዴታ በመግባቷና ይህንን ግዴታ ባለመወጣቷ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ብለዋል፡፡ ችሎቱም ተጠሪዋ አመልካቾችን ለመንከባከብና ለመጦር ግዴታ ስላልገቡ ውሉ ሊፈረስ አይገባም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አኳያ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካቾች ለስር ፍ/ቤት ክስ ያቀረቡት የስጦታ ውል እንዲፈርስላቸው ነው፡፡ ውሉ እንዲፈርስ የጠየቁበት ምክንያት ተጠሪ አመልካቾችን ለመንከባከብና ለመጦር የገቡትን ግዴታ ባለመወጣታቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ተጠሪ ስጦታ የተሰጣቸው መሆኑን አምነው ነገር ግን በውሉ ላይ የገቡት ምንም አይነት ግዴታ እንደሌለ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የአመልካቾችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ተጠሪ አመልካቾችን ለመንከባከብና ለመጦር ግዴታ አልገቡም በሚል ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ችሎት ተጠሪ በስጦታ ውሉ ላይ አመልካቾችን ለመርዳት ግዴታ የገቡ መሆኑን እና የስጦታ ውሉ ሊፈርስ የሚገባበት የሕግ ምክንያት መኖር አለመኖሩን መመርመር ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ለዚህ ይረዳው ዘንድ አመልካቾች ለተጠሪ ስጦታ ያደረጉበትን ውል ተመልክቷል፡፡ ጥር 12 ቀን 1991 ዓ.ም የተደረገው የስጦታ ውል በከፊል

***"ስጦታ ሰጪዎች ባልና ሚስት ስንሆን በአ/አበባ ከተማ በወረዳ 12 ቀበሌ 11 የቤት ቁጥር አዲስ የካርታ ቁጥር 37655 የሆነውን ቤታችን ለወለድናት ልጃችን ወደፊትም ለምትጦረንና ለምትንከባከበን ጧሪ ቀባሪያችን ለሆነችው ልጃችን በፈለገችው አይነት እንድትጠቀምበት ይህንን ከላይ የተጠቀሰውን ቤታችንን በፍ/ሕ/ቁ. 2427 መሰረት በስጦታ የሰጠናት መሆናችንን በፊርማችን እናረጋግጣለን፡፡" የሚል ነው፡፡***

ከዚህም የስጦታ ውል ይዘት "… ወደፊትም ለምትጦረንና ለምትንከባከበን ጧሪ ቀባሪያችን…" የሚለው ሐረግ አመልካቾች ለተጠሪዋ ስጦታ ያደረጉበት ምክንያት ተጠሪዋ ወደፊት እንድትንከባከባቸው እና እንድትጦራቸው መሆኑን ማየት የሚቻል ነው፡፡ በእርግጥ በኑዛዜው ላይ ተጠሪዋ አመልካቾችን የመንከባከብና የመጦር ግዴታ ገብታለች በሚል ግልጽ አማርኛ አልተቀመጠም፡፡ ነገር ግን ውል ሲተረጐም የቅንነትና የመተማመን ግንኙነትን መሰረት በማድረግና በቅን ልቦና ሊሆን እንደሚገባው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1732 መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ አመልካቾች ቤታቸውን ለተጠሪ ሲሰጡ ወደፊት ከልጃቸው እርዳታና እንክብካቤ የሚያገኙ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ለመሆኑ የውሉ ይዘት ያሳያል፡፡ በእርግጥ ተጠሪ ከአመልካቾች ጋር ምንም አይነት የስጋ ዝምድና የለኝም በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም በስጦታ ውሉ ላይ አመልካቾች የተጠሪ ወላጆች መሆናቸው ተጠቅሶ የተቀመጠውን ተጠሪዋም አምነው ስጦታውን መቀበላቸውን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ለተጠሪ ቤታቸውን የሰጡት ተጠሪ ልጃቸው በመሆናቸውና ወደፊትም እንድትንከባከባቸውና እንድትረዳቸው ግዴታ በማስገባት መሆኑን ችሎቱ ተገንዝቧል፡፡

እንግዲህ ተጠሪ አመልካቾችን ለመርዳትና ለመንከባከብ ግዴታ ገብተዋል ከተባለ ይህንን ግዴታቸውን ተወጥተዋል ወይ? የሚለው በመቀጠል ሊታይ ይገባል፡፡፡ አመልካቾች ተጠሪ ይህንን ግዴታ አልተወጡም በማለት ሲከራከሩ ተጠሪ ግዴታ አልገባሁም ከማለት በቀር አመልካቾችን እየረዱና እየተንከባከቡ ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ለዚህም ለሰበር ችሎት በሰጡት መልስ የሚከራከሩት አመልካቾች የጡረታ አበልና በኮንትራት እየተቀጠሩ ገቢ የሚያገኙና እርዳታ የማያሻቸው መሆኑን እንጂ በውሉ መሰረት ግዴታቸውን ስለመወጣታቸው በማስተባበል ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ በግልጽ ክዶ ካልተከራከረ ወይም በመሸሽ መልስ ከሰጠ ክሱን እንዳመነ እንደሚቆጠር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 235/2/ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በውሉ የተመለከተውን ግዴታቸውን ስላለመወጣቸው በአመልካቾች የተነገረውን በግልጽ ክደው ስላልተከራከሩ እዳመኑ ሊቆጠር ይገባል፡፡

ስጦታ ገደብ ያለበት ወይም ግዴታ የተጣለበት ሊሆን እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2452/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ ስጦታ ሰጪውም ተቀባዩ ግዴታውን ባለመፈፀሙ ምክንያት ስጦታው እንዲፈርስለት ለመጠየቅ እንደሚችል የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2464/1/ ያስገነዝባል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ተጠሪ አመልካቾች ለመርዳትና ለመንከባከብ ግዴታ የገቡ በመሆኑና ግዴታቸው ባለመወጣታቸው አመልካቾች ውሉ እንዲፈረስ ለመጠየቅ መብት አላቸው፡፡ ተጠሪ የአመልካቾች የስጦታ ይፍረስልን ጥያቄ በይርጋ ይታገደል በማለት ተከራክረዋል፡፡ በእርግጥ በመንፈስ መጫን የተደረገ ስጦታ ስጦታው ከተደረገ ጊዜ አንስቶ በሁለት አመት ውስጥ ለዳኞች ካልቀረበ ዋጋ እንደሌለው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2441/1/ ያመለክታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ውሉን ሲያደርጉ የመንፈስ መጫን ነበር በማለት ይግለፁ እንጂ ስጦታው እንዲፈርስ በዋናነት የጠየቁት ተጠሪ በውሉ መሰረት ግዴታቸውን እልተወጡም በሚል በመሆኑ ይህ የይርጋ ድንጋጌ አግባብነት የለውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪዋ በስጦታ ውሉ ላይ የተመለከተውን ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ውሉ ሊፈርስ ይገባል፡፡ የውል መፍረስ ውጤቱም ተዋዋዮች ወደነበሩበት ቦታ መመለስ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 ስር ስለተመለከተ አመልካቾችና ተጠሪም በዚሁም መሰረት ውሉ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ ሊመለሱ ይገባል፡፡ በአጠቃላይ ውሉ እንዲፈርስ ሊወሰን ሲገባ የስር ፍ/ቤቶች ስጦታው ሊፈርስ አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24359 መስከረም 8 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 72830 ኅዳር 5 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በስጦታ ውሉ ላይ የተመለከተውን ግዴታቸውን ስላልተወጡ ስጦታው ፈራሽ ነው ብለናል፡፡
3. የስጦታ ውሉ በመፍረሱ ምክንያት ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ሊመለሱ ስለሚገባ ተጠሪ ከአመልካቾች በስጦታ ያገኙትን ቤት ለአመልካቾች መልሰው ያስረክቡ ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 44101

የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሒሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ሚስስ ፍራንሱዊስ ፖስተር - ጠበቃ ፈቃዱ ሞላ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡- 1. ሚ/ር ዱክማን ቬኖ

2. ሚ/ስ ባርቦት ለቲቲያ } በሌሉበት የሚታይ ነው

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉዲፈቻ ስምምነት የሚፈርስበትን የሕግ አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክር የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ብርሃነ ሕይወት የሕጻናት እና ቤተሰብ መርጃ ድርጅት የተባለው ባሁኑ ተጠሪዎች ላይ በመሰረተው ክሰ መነሻ ነው፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለውም የአሁኑ ተጠሪዎች ሕፃን ቱሉን በጉዲፈቻ ለመውሰድ በመጠየቃቸው የአሁኑ አመልካች በኃላፊነት የሚመሩት ድርጅት ሕፃኑን በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከነበረው ብርሃነ ሕይወት የሕፃናትና ቤተሰብ መርጃ ድርጅት ተቀብሎ የፍርድ ቤት ስርዓቱን በማከናወን ላይ እያለ ተጠሪዎች ሕጻኑን የመውሰድ ሃሳባቸውን በመቀየራቸው የጉዲፈቻ ስምምነት እንዳይጸድቅ ከውሳኔ በፊት ግልጽ ደብዳቤ በመጻፍ ቢያሳውቁም ይህ ደብዳቤ በወቅቱ ለፍርድ ቤቱ ባለመድረሱ የጉዲፈቻ ስምምነቱ መጽደቁን ለተጠሪዎች ፍርድ ቤቱ የወሰነ ስለመሆኑ የነገራቸው ቢሆንም ሕጻኑን ላለመውሰድ በወሰዱት ውሣኔ በመጽናታቸው ሕፃን ቱሉ የአሁኑ አመልካች በሚያስተዳድሩት ድርጅት ጊዜያዊ ማቆያ ውስጥ ለመቆየት በመገደዱ ማቆያው ለወደፊት የጉዲፈቻ ወላጅ የሆኑትን የአሁኑን ተጠሪዎች ድርጊት የሕፃኑን የወደፊት ሕይወት እና እድገት በከፍተኛ ሁኔታ የሚያሰጋ በመሆኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ መሠረት እንዲሰረዝ ለፍርድ ቤቱ ጥያቄ ማቅረቡን፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪዎች አድራጎት የሕፃኑን ሕይወት በአደጋ ላይ የሚጥል ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት ሳይቀበለው መቅረቱን ነው፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የካቲት 27 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በይግባኝ በነበረው የክርክሩ ሂደት የተጠሪዎች ወኪል ቀርበው የጉዲፈቻ ውሉ ቢፈርስ ተቋውሞ የለኝም እያሉ ፍርድ ቤቱ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐ ለተጠሪዎች በጋዜጣ ጥሪ ቢደረግላቸውም የቃል ክርክሩ በሚሰማበት ወቅት ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጎአል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ግልባጭ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምሮታል፡፡

የጉዲፈቻ ስምምነት ከፀደቀ በኋላ በማናቸውም ምክንያት ሊፈርስ የማይችል ስለመሆኑ በፀንሰ ሃሳብ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 195(1) የሚያሳይ ቢሆንም የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት የጉዲፈቻ ስምምነት የሚፈርስባቸውን ምክንያቶችን ደንግጓል። የዚህ ድንጋጌ መንፈስ ሲታይም በጉዲፈቻ አድራጊው ልጁን በዓለም አቀፍ የሕጻናት እና ሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን በሚፃረርና የልጁን ጥቅምና ደህንነት በሚጎዳ አኳኋን መያዙን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የጉዲፈቻ ስምምነቱ እንዲቀጥል ማድረግ የሚያስገኘው ፋይዳ ባለመኖሩ ጉዳዩን በሚመለከተው ማንኛውም አመልካች ጠያቂነት መሰረዝ እንደሚቻል ታመኖበት ድንጋጌው መቀመጡን የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ ሐተታ ምክንያት ያስገነዝባል።

ሕጉ ጉዲፈቻ በሚወሰዱት ልጆች ላይ በተጨባጭ እና በተግባር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ማገናዘብ የሚጠበቅበት በመሆኑ የድንጋጌው መካተት የሕፃናትን ጥቅምና ደህንነት ከመጠበቅ አኳያ ጠቀሜታው የጎላ ስለመሆኑም የሚታመን ነው። ድንጋጌው በአተረጓጉም ላይ ጥንቃቄ ካልተደረገ የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲሰረዝ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው በልጁ አኗኗርና አያያዝ እንዲሁም በወደፊት ሕይወቱ ላይ በተጨባጭ የደረሰ ጉዳት ወይም ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳት ስለመኖሩ ማረጋገጥ በሚቻልበት ጊዜ ይሆናል ፍርድ ቤቱም የስምምነቱ መሰረዝ የሚያስገኘው ጠቀሜታ በሚገባ ማጤንና መመዘን የሚጠበቅበት ስለመሆኑ የሕግ መንፈስና ይዘት ያሳያል

በመሠረቱ ጉዲፈቻ በሕግ ጥበቃ የሚያስፈልገው በዋናነት የልጁን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል ነው። የሕፃናትና ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል የተለያዩ ስምምነቶች በዓለምና በአህጉር ደረጃ ተፈርመው በስራ ላይ /እየተተገበሩ/ ይገኛሉ። ከስምምነቶች ውስጥም የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽንና የአፍሪካ ሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር ተጠቃሾች ናቸው። ሐገራችን ኢትዮጵያም የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽንን ህዳር 29 ቀን 1984 ዓ.ም የአፍሪካ ሕጻናት መብቶችና ደህንነት ቻርተርን ደግሞ እ.ኤ.አ. ኦክቶበር 02 ቀን 2002 አጽድቃለች። ከእነዚህም በተጨማሪ የሕጻናትን መብትንና ደህንነትን በሚመለከት የፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ እና ሌሎች ሕጐች በስራ ላይ ይገኛሉ። በዓለም አቀፍም በአህጉርም ሆነ በአገር ደረጃ ያሉት እነዚህ ሕጐች መሠታዊ መርሆዎችን ይዘዋል። በእነዚህ ሕጐች ከተካተቱት መሠረታዊ መርሆዎች አንዱ ሕጻናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ለሕጻናት ጥቅምና ደህንነት (The Best interest of the child) ቅድሚያ መስጠት የሚለው መርህ ይገኝበታል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን የዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የአገሪቱ የሕግ አካል መሆናቸውን በአንቀጽ 9(4) ስር ከመደንገጉና በሕገ-መንግሥቱ በስፋት ሽፋን የተሰጣቸው መሠረታዊ የመብቶችና የነጻነቶች ድንጋጌዎች ሀገሪቱን ከተቀበለቻቸውና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት ስምምነቶች ወይም ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ መተርጐም ያለበት ስለመሆኑ ከማስቀመጡም በተጨማሪ የሕጻናትን ልዩ ችግር ከግምት ውስጥ ያስገቡ ንዑስ ድንጋጌዎች የያዘ አንቀጽ 36 ደንግጓል። የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ ሁሉ የመንግስታዊ ወይም የበጐ አድራጐት ተቋማት እንዲሁም ፍርድ ቤቶችንና አስተዳደር ባለስልጣናት ወይም የሕግ አውጪው አካላት የሕጻናትን ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ ያለበት ስለመሆኑ አስገዳጅነት ባለው መልኩ ደንግጓል። ይህንኑ የሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌ ለማስፈፀም የወጡ ፖሊሲዎች ወይም ሕጐችም መንፈሳቸው ሲታይ ለሕፃናት መብትና ደህንነት በተገቢው ሁኔታ የማስከበር ዓላማን ግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ ናቸው ተብሎ ይታሰባል።

ጉዲፈቻ ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች ተብለው በሕገ-መንግሥቱ ከተጠቀሱት ነገሮች አንዱ መሆኑ የሚያከራክር ነጥብ ካለመሆኑም በላይ ሕገ- መንግሥቱ በአንቀጽ 36(5) ስር መንግሥት ለእጓለማውታን ልዩ ጥበቃ እንደሚያደርግላቸው በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ስርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሰርቱ እንደሚያበረታታ በግልጽ አስቀምጧል። ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው የጉዲፈቻ ጉዳይ ከሕገ-መንግሥቱ ከተቀመጠው መርህ ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸው የሕፃናት መብት ኮንቬንሽን እንዲሁም ከተሻሻለው የፌዴራሉ ቤተሰብ ሕግና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ሰነዶች ይዘትና መንፈስ በጥንቃቄ መታየት ያለበት መሆኑን ነው። ይህ ችሎት አግባብነት ያላቸውን ሕጐች በመመርመርም የሕፃናት መብትና ጥቅም ለማስከበር በቀደምትነት ሊታይ የሚገባው መርህ የሕፃናት ጥቅምና

ደህንነት (the best interest of the child) ስለመሆኑ በመ/ቁጥር 23632፣35710 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት አስገዳጅነት ያለውን ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ሕጐች ይዘታቸው ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ሕፃን ቱሉ ከተጠሪዎች ጋር የተደረገለት የጉዲፈቻ ውል እንዲፈርስ ጥያቄ ያቀረቡት ተጠሪዎች ሕፃኑን ላለመውሰድ በመግለጻቸውና በውሳኔያቸውም በመጽናታቸው ሕፃን ቱሉ አመልካች በሚያስተዳድሩት ጊዜያዊ ማቆያ ውስጥ ለመቆየት ግድ ያለ መሆኑን ማቆያውም ለሕፃኑ ሕይወቱ የሚያስፈልጉትን ነገሮችን ያሟላ ባለመሆኑና ለሌላ ወላጅ ለመስጠት ባለመቻሉ በሕፃኑ የወደፊት እድገት የተጠሪዎች አድራጐት ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች ሕፃን ቱሉን ላለመውሰድ በወሰዱት ውሳኔ መጽናታቸውን አረጋጋጠው የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበሉት የቀሩት ተጠሪዎች ሕፃኑን ካለመውሰድ የወሰኑት ውሳኔ ሕፃኑ አላስደሰተንም፣ ህጻኑን ለመውሰድ ፍላጐት አላሰደሩም፣ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 195(2) ስር የተመለከቱት ምክንያቶች አልተሟሉም በሚል ምክንያት ሆኖ በሌላ ምክንያት የተደገፈ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ነው፡፡

ከፍ ብለን እንደተመለከትነው በጉዲፈቻ አድራጊው ልጁን በዓለም አቀፍ የሕፃናት እና ሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን በሚፃረርና የልጁን ጥቅምና ደህንነት በሚጐዳ አኳኋን መያዙን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የጉዲፈቻ ስምምነቱ እንዲቀጥል ማድረግ የሚያስገኘው ፋይዳ ባለመኖሩ ጉዳዩን በሚመለከተው ማንኛውም አመልካች ጠያቂነት መሰረዝ እንደሚቻል በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 195 እና 196 ተደንግጓል፡፡ አንቀጽ 195(2) በተለይ ሲታይም ጉዲፈቻ አድራጊው በጉዲፈቻ የተቀበለውን ልጅ እንደልጅ ከማሳደግ ፋንታ በባርነት ወይም በባርነት በሚመስል ሁኔታ ወይም ከግብረ ገብ ውጪ በሆኑ ተግባሮች እንዲሰማራ በማድረግ መጠቀሚያ ያደረገው እንደሆነ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የልጁን የወደፊት ሕይወት ክፉኛ በሚጎዳ አኳኋን የያዘው መሆኑን (ሰረዝ የተጨመረ) የተረዳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ለመሰረዝ እንደሚችል አስቀምጧል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ሕጻን ቱሉ ያለበት ሁኔታ ሲታይ እና ተጠሪዎች ሕፃኑን ለመውሰድ ፍቃደኛ ለመሆን ያለመቻላቸው እንዲሁም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር የተጠሪዎች ወኪል ቀርበው "ልጁን አንደማንወስድ የጉዲፈቻ ውሉ ከመጽደቁ በፊት የገለጽን በመሆኑ ልጁን ለመውሰድ አንገደድም የጉዲፈቻ ስምምነቱ ቢፈርስ አንቃወምም" በማለት መከራከራቸው ሲታይ በሕፃኑ የወደፊት ሕይወት ችግር አያስከትልም ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የቀረበውን ክርክር ከሕጉ መንፈስ ጋር ባግባቡ ሳያገናዝቡ የጉዲፈቻ ስምምነት ሊፈርስ አይገባም በማለት መወሰናቸው የሕፃኑን እድገት የሚጐዳ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፌርድ ቤት በመ/ቁጥር 111497 ሕዳር 05 ቀን 2001 እና ታህሳስ 04 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 75193 የካቲት 12 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ሕፃን ቱሉን ለመውሰድ የካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም ያደጉት እና መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በፍርድ ቤት የፀደቀ የጉዲፈቻ ስምምነት ውል ፈራሽ ነው ብለናል፡፡ ይህንኑ አውቀው ተገቢውን እንዲፈጽሙ ለስር ፍርድ ቤቶች ይፃፍ፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

የሰ/መ/ቁ 46527

የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሃይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

አለማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ገነት በቀለ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ትዕግስት አሰፋ - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

ለክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በአድአ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች በሁለት ግለሰቦች ላይ በመሰረቱት ክስ ተከሳሾች ሞግዚት ለሆኑላቸው ልጃቸው በውርስ ከአባታቸው ሊተላለፍላቸው የሚገባውን ቤት ስለያዙ እንዲመልሱላቸው ጠይቀው ፍ/ቤቱ ተከሳሾቹ ቤቱን እንዲመልሱ ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሰረት መቃወሚያ በማቅረብ ቤቱን ከስር ተከሳሾች ገዝተው የባለቤትነት ስሙ በስማቸው ያዛወሩ በመሆኑ ውሳኔው እንዲሰረዝላቸው አመልክተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ሁሉንም ወገኖች አስቀርቦ ክርክራቸውን ከሰማ በኋላ ቀደም ሲል የተሰጠው ውሳኔ የሚሰረዝበት ምክንያት የለም በማለት ተጠሪን መቃወሚያ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪ በምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ተጠሪን ቤቱን ያገኙት በህጋዊ መንገድ ገዝተው በመሆኑ ሊያስረክቡ አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቀጥሎም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡም ቅሬታቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን ቅሬታው በአጭሩ ተጠሪ ቤቱን የገዙት መብት ከሌላቸው ሰዎች በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ ሊሻር ይገባል የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አመልካች ክስ ያቀረቡት ከአባታቸው በውርስ ሊተላለፍላቸው የሚገባውን ንብረት ለመረከብ ሲሆን ክስ የመሰረቱት ወራሽ ነን በሚሉ ግለሰቦች ላይ ነው፡፡ ከመዝገቡ የስር ተከሳሾች ክርክር የተነሳበትን ቤት የባለቤትነት ስም በስማቸው በማዛወር በ1993 ዓ.ም ቤቱን ለተጠሪ መሸጣቸውን ተረድተናል፡፡ የስር ተከሳሾች ቤቱን በሚሸጡበት ወቅት የባለቤትነት ምስክር ወረቀት በስማቸው አግኝተው የቤቱ ባለቤት ሆነዋል፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195 የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የባለሃብትነት ምስክር ወረቀት በተሰጠ ጊዜ ምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀሰው ንብረት ባለንብረት ሆኖ እንደሚቆጠር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሽያጩ በተከናወነበት ጊዜ ቤቱ የሻጮቹ የግል ንብረት ሲሆን ተጠሪም ቤቱን የገዙት የሻጮቹን የባለቤትነት ምስክር ወረቀት በማየት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የቤቱም ሽያጭ ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት መደረጉንና ስሙም ወደ ገዢዋ መዛወሩን መገንዘብ ችለናል፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪ ቤቱን በገዙበት ወቅት ቤቱ በሻጮች ስም የነበረ በመሆኑ ሽያጩን ህጉ በሚጠይቀው የአፃፃፍ ስርዓት መሰረት ማከናወናቸው ተጠሪዋ ቤቱን የገዙት በቅን ልቦና መሆኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ምናልባት አመልካች በንብረቱ ላይ ድርሻ አለን የሚሉ ከሆነ ስር ተከሳሾችን ከሚጠይቁ በቀር ተጠሪ በህጋዊ መንገድ የገዙትን ቤት እንዲያስረክቡ የሚደረግበት የህግ አግባብ ስለሌለ ውሳኔው መሰረታዊ ህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ማለት አልተቻለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 15094 መጋቢት 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 65463 ጥር 8 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 74733 መጋቢት 09 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 47378

የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ኂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ ዓለማየሁ ከተማ - ጠበቃ ኃይለማሪያም ኢትቻ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- 1. ወ/ሮ ላቀች አይተንፍሱ - ቀረቡ

2. አቶ ደምሴ ወርቅአፈሰኩ - ወራሾች ቀረቡ

3. ወ/ሮ እቴነሽ ኃ/ስላሴ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የጋራ ውርስ ሃብት ሽያጭ ውል ይፍረስ ጥያቄን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች እና በወ/ሮ አበበች ጫካ ላይ ሕዳር 27 ቀን 1999 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው አጠራር ወረዳ 13 ቀበሌ 21 በአሁኑ አጠራር የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07 ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 266/2/ የሆነውን ቤትና ይዞታ ከእናታቸው ከወ/ሮ ጥሩነሽ ወልደየስ ከወ/ሮ አበበች ጫካ ጋር በውርስ የተላለፈላቸው መሆኑን፣ቤቱ ለሰባት ወራሾች ለማከፋፈል አመቺ ካለመሆኑ በላይ ከእናታቸው መታሰቢያነት እንዲሆንና ወራሾችንም በቤቱ ላይ ለመገናኘት ይችሉ ዘንድ ከሚሸጥ ይልቅ ቤት ያልነበራት ወ/ሮ አበበች ቤቱ ውስጥ እንድትኖርበትና ማንኛውም ወራሽ በቤቱ መኖር ከፈለገ መኖር እንደሚችል በቤተ ዘመድ ጉባኤ ውሳኔ መስጠቱን፣ይህ ሆኖ እያለ ወ/ሮ አበበች ጫካ የሟች ወ/ሮ ጥሩነሽ ወልደየስ ብቸኛ ወራሽ በማስመሰል የወራሽነት ማስረጃ አውጥተው ቤቱን በስሟ ካዛወረች በኋላ ቤቱን ለአሁኑ አመልካች በብር 450,000(አራት መቶ አምሳ ሺህ ብር) በመሸጥ ስመ ሐብቱ ሁሉ በገዥው ስም እንዲዛወር ማድረጓን በመግለጽ በውርስ ንብረታችን ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል እንዲፈርስ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ለክሱ በሰጡት መልስ፡- የሽያጭ ውል ይፍረስልን ጥያቄ በይርጋ የታገደ መሆኑን፣ሽያጩን በሕጉ አግባብ ያደረጉት በመሆኑ ሊፈርስ እንደማይገባ ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ቤቱ የውርስ ሃብት መሆኑን በማረጋገጥ እና ቤቱ የተሸጠው ከሁሉ ወራሾች ፈቃድ ውጪ በመሆኑ ሽያጩ በሕግ ፊት ሊፀና የሚችልበት ምክንያት አለመኖሩን በመግለጽ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ፣አመልካች የሽያጭ ገንዘቡን ብር 270,000(ሁለት መቶ ሰባ ሺህ ብር) ከወ/ሮ አበበች ወልደየስ እንዲቀበሉ፣ቤቱን አመልካች ለወራሾች እንዲመልሱ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሐምሌ 07 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት አመልካች እጃቸው ውስጥ ያስገቡት ሕጋዊ በሆነ መንገድ መሆኑ በግልጽ ተረጋግጦ እያለ ሽያጩ ፈራሽ ነው መባሉ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን

የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በስር አንደኛ ተከሳሽ በነበሩት በወ/ሮ አበበች ወልደየስ ስም ተመዝግቦ የሚታወቀውን አከራካሪውን ቤት ውል ማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት በመቅረብ አመልካች መግዛታቸው ተረጋግጦ እያለ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ አንደኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ጥቅምት 11 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ፣የሁለተኛ ተጠሪ ወራሾች ደግሞ ታህሣሥ 27 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ አምስት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የመልሳቸው ይዘትም ባጭሩ፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የጋራ ውርስ ንብረት ላይ በተጭበረበረ መንገድ በውልና ማስረጃ የተደረገ የሽያጭ ውል ሕጋዊ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት ስለሌለ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃም በተጠሪዎች መልስ ላይ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀችን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪው ቤት ተጠሪዎች ከወ/ሮ አበበች ጫካ ጋር ከሟች ወ/ሮ ጥሩነሽ ወልደየስ በውርስ የተላለፈላቸው መሆኑን፣ይህንን ቤት በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበሩት ወ/ሮ አበበች ጫካ ሲያስተዳድሩትና ሲጠቀሙት ቆይተው የቤቱን ስመ ሐብት ወደ ራሳቸው በማዞር ለአሁኑ አመልካች በውልና ማስረጃ ፊት በተደረገ የሽያጭ ውል በብር 450,000(አራት መቶ ሃምሳ ሺህ) መሸጣቸውን፣ከዚህም በኋላ አመልካች የስመ ሃብቱን ወደ ራሳቸው አዙረው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች መሆናቸውን ነው፡፡ የተጠሪዎች ክርክር መሰረቱም የወራሾች የጋራ የሆነው ንብረት የሁሉም የጋራ ባሃብቶች ስምምነት ሊኖር ሲገባ ወ/ሮ አበበች ጫካ በተጭበረበረ መንገድ ወራሽነት አሳውጀው እና የቤቱን ስመ-ሃብት በማዞር መሸጣቸውን ሽያጩን ሕጋዊ አያደርገውም በሚል ምክንያት ስለመሆኑም ተገንዝበናል፡፡ እኛም በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ከሕጉ ጋር በሚከተለው መልኩ በማዛመድ ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ የውርስ ሃብት አከፋፈሉ እስኪፈፀም ድረስ በወራሾቹ መካከል ሳይነጣጠል እንደሚቆይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1060/1/ ስር የተመለከተ ሲሆን የጋራ የሆነውን ንብረት ለመሸጥ፣ለማስተላለፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ የጋራ ባለሃብቶቹ ሁሉ ስምምነት አስፈላጊ ስለመሆኑ ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1266 ድንጋጌ ያሳያል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የስር አንደኛ ተከሳሽ የነበሩት ወ/ሮ አበበች ጫካ አከራካሪውን ቤት የሸጡት የተጠሪዎችን ስምምነት አግኝተው ባይሆንም የቤቱን ስመ-ሐብት ከሽያጩ በፊት ከተገቢው የአስተዳደር አካል ከአገኙ በኋላ ሲሆን ሽያጩም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 ድንጋጌ መሰረት ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የምስክር ወረቅት ሲሰጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት ሆኖ ሊቆጠር እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይህን ማስረጃ የያዘ ሰው ደግሞ ሃብቱን በሕጉ አግባብ ከሸጠ ተግባሩ ሕገ ወጥ የሚባልበት ምክንያት የለውም፡፡ አንድ ሰው በሕግ ጥበቃ የተደረገለትን መብት በሕጋዊ መንገዶች ለሌላ ለማስተላለፍ መብት አለውና፡፡ በስር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበሩት ወ/ሮ አበበች ጫካ አከራካሪውን ቤት በስማቸው የባለሃብትነት ምስክር ወረቀት መያዛቸው ንብረቱ የግል ሃብት እንደሆነ የሚያስቆጥር ሲሆን ይህን ማስረጃ በመመልከት ንብረቱን ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት የሚገዛ ሰው ሽያጩን ያከናወነው ከሕግ ውጪ ነው ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በቤቱ ላይ ሕጋዊ መብት የሌለው ሰው ሽያጩን አከናውኖ ሲገኝም ትክክለኛው ባለሃብት ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጐ የገዛውን ገዥ ሳይሆን ሻጩን ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 997፣እና 2882 እስከ 2884 ድረስ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መንፈስ እና ይዘት የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ በአጠቃላይ አመልካች አከራካሪውን ቤት የገዙት በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ ከያዙት ግለሰብ ሆኖ ሽያጩንም ያከናወኑት ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት በመሆኑ ውሉ የሚፈርስበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪዎች በቤቱ ላይ የጋራ ወራሽነት መብት ያላቸው መሆኑ የተረጋገጠ

ሲሆን ያላቸው መፍትሄ የሽያጩን ዋጋ ከስር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ ከነበሩት  ከወ/ሮ አበበች ጫካ መቀበል ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33368 ግንቦት 10 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 81698 ሰኔ 19 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በአከራካሪው ቤት ላይ የተደረገው ሽያጭ ውል ሊፈረስ አይገባም፣አመልካች ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ብለናል፡፡

3. ተጠሪዎች በቤቱ ላይ ባላቸው ድርሻ መሰረት የሽያጩን ገንዘብ ከወ/ሮ አበበች ጫካ በሌላ ክስ የመቀበል መብታቸውን ይህ ውሣኔ አያስቀርም ብለናል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 42482

የካቲት 3 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃነ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** አቶ ፍሬዘውድ ተካ ጉጂ - ቀረቡ

ወ/ሮ ትርሲት ተካ ጉጂ - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** አቶ ሰለሞን ኃ/ማሪያም - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የውርስ ንብረት የሚመለከት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ ነበር፡፡ የክሱ ምክንያትም ከአያታቸው በኑዛዜ የተላለፈላቸውን የቤት ቁ. 1133 በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ቀበሌ 03 ክልል የሚገኝ ቤት ተጠሪ አላአግባብ ይዞ እየተጠቀመ በመሆኑ እንዲለቅ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ ተጠሪም በሰጠው መልስ አመልካቾች በኑዛዜ ተሰጠን የሚሉት ቤት የተናዛዧ ባለመሆኑ ለመክሰስ መብት የላቸውም እንዲሁም ቤቱን ከያዘበት ጊዜ አንስቶ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ክስ ያልቀረበ በመሆኑ በይርጋ ሊታገድ ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ በፍሬ ነገር ረገድም ቤቱን የሰሩት የእሱ አባት እና እናት መሆናቸውን እና ቤቱ በስጦታ ለእህቱ የተሰጠ ስለመሆኑ እሱም እህቱ በሰጠችው ውክልና ይዞ እየተጠቀመ መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ አመልክቷል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ፍርድ አመልካቾች ክስ ያቀረቡበት የቤት ቁ. 1133 የሟች ወ/ሮ ጌጤ ሸኔ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም በማለት አመልካቾች በተጠቀሰው ቤት ላይ ባለመብት ስለመሆናቸው አላረጋገጡም በሚል ክስ ለማቅረብ የላቸውም ሲል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ እና 244/2/መ በመመርኮዝ ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤት ፍርድን አጽንቷል፡፡ የአመልካቾች ጠበቃ ታህሣሥ 20/2001 ዓ.ም ጽፎ ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሟች ወ/ሮ ጌጤ ሸኔ ጥቅምት 24/1989 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በመ/ቁ. 265 ላይ መቃወሚያ ቀርቦ ተቀባይነት ሳያገኝ ኑዛዜው በፍርድ ቤት የፀደቀ ስለሆነ ይህንን ወደ ጐን በመተው የባለቤትነት ማስረጃ አልቀረበም በሚል የሥር ፍ/ቤት ክሱን ወድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲሻር እና እንደክሳቸው እንዲወሰን የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የአመልካቾች የኑዛዜ ወራሽነት በመ/ቁ. 265 ተረጋግጦ እያለ እና ቀደም ሲል የቀረበው መቃመሚያ ውድቅ ተደርጐ አመልካቾች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው ተብሎ ከተወሰነ በኂላ ይህንኑ ቤት ለማስለቀቅ ያቀረቡት ክስ ውድቅ መደረጉ በግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ ተጠሪ መስከረም 15/2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ሲታይ ኑዛዜ ለማጽደቅ የቀረበው አቤቱታ ላይ ተከራካሪ የነበሩት ተጠሪ እና ወ/ሮ ጉዶ ጉጂ የነበሩ መሆኑንና ኑዛዜው መጽደቁ

በሐብቱ ላይ የሚቀርበውን ክርክር የሚያግድ ሊሆን እንደማይችል በማለት የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ እንዲፀና አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን መልስ እና የመልስ መልስ ከመረመረ በኋላ ታህሣሥ 22/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ቤቱ ያለበትን ይዞታ እና ቤቱ በማን እንደተሰራ ግራ ቀኙን በቃል በማነጋገር ጉዳዩን በማጣራት ግንዛቤ አግኝቷል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር እና የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን በዚሁም መዝገቡን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ምላሽ የሚሻው ነጥብ ኑዛዜ በፍ/ቤት በመጽደቁ አመልካቾች በንብረቱ ላይ ባለመብት መሆናቸውን ማረጋገጫ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ ኑዛዜ ሕጉ ያስቀመጠውን ሥርአት እና መስፈርቶች አሟልቶ ከተገኘ በራሱ በሕግ ረገድ ውጤት የሚሰጠው ሰነድ እንጂ በፍርድ ቤት ቀርቦ ማፀደቅ አስፈላጊ እንዳልሆነ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 17058 በተሰጠ ውሳኔ የተሰጠ የሕግ ትርጉም መረዳት ይቻላል ከዚህም አልፎ ኑዛዜው በፍ/ቤት ቀርቦ መጽደቅ ሌሎች ባለመብቶች ክርክር ወይም መቃመሚያ እንዳያቀርቡ ሊገድባቸው እንደማይችል በዚሁ ተጠቃሽ መዝገብ ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡

ከዚህ አንፃር አመልካቾች በመ/ቁ. 265 ኑዛዜ ለፍ/ቤት ማፀደቃቸው በራሱ በኑዛዜ በተሰጠው ቤት ላይ ባለሐብት ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ብቸኛ ማስረጃ አይደለም፡፡ ከዚህም ሌላ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ቤት የተናዛዢ ስለመሆኑም በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1195 በተደነገገው መሰረት ከአስተዳደር ክፍል የተሰጠ ማረጋገጫ አልቀረበም ይልቁንም ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ ለመረዳት እንደተቻለው የቤት ቁ. 1133 የሟች ወ/ሮ ጌጤ ሸኔ ስለመሆኑ ለማጣራት ሥር ፍ/ቤት ከክፍሉ አስተዳደር ማህደር አስቀርቦ እንደተመለከተ እና ቤቱ የሟች ስለመሆኑ አስረጅ ሰነድ እንዳልቀረበ ተገልጿል፡፡

ይህ በሆነበት ሁኔታ ደግሞ ኑዛዜ አጸድቀናል በሚል ምክንያት ብቻ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት ማጣቱ የሕግ ስህተት ነው ሊባል የሚቻልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካቾችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የሰጡት ምክንያትና ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል ለማለት ስላልተቻለ ባለበት ሁኔታ አጽንተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 09779 የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 64033 የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 45819

የካቲት 12 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** አቶ ካሳ ፋንታ - ጠበቃ ታደሰ መርእድ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ እስካዳር ግጨው - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የልጅ ቀለብን በተመለከተ ለአከፋፈሉ ዋስትና ይሆን ዘንድ የአመልካች የግል መኪና ቀለብ ጠያቂዎቹ አስራ ስምንት ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ እንዳይሸጥ፣እንዳይለወጥ ተከብሮ እንዲቆይ የሚል ትእዛዝ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በመጽናቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ተብሎ የቀረበውን አቤቱታ የሚመለከት ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ግንቦት 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ትእዛዝ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ቀርበው ታህሳስ 28 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው ጥር 17 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ይህ ችሎት ግራ ቀኙን በቃል ሰምቷል፡፡ ጉዳዩንም አቤቱታው ከቀረበበት ትእዛዝ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች የቀለብ ጥያቄው የሚመለከታቸው መሆኑን ሳይክዱ የግል ንብረታቸው የሆነው ሕፃናቱ አስራ ስምንት ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ ሊከበር አይገባም የሚሉት ለሌላ እዳ አከፋፈል መኪናውን ለመሸጥ ካሰቡ ችግር የሚፈጥር ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይህ ችሎትም መኪናው ላይ የተላለፈው እግድ እንዲነሳላቸው ከፈለጉ ጥሬ ገንዘቡን ሙሉ በሙሉ በአደራ ሊያስቀምጡ የሚችሉበት መንገድ ካለ በችሎት የአመልካችን ጠበቃ ጠይቆ ከሶስት እስከ አራት ወራት ድረስ ያለውን የቀለብ ገንዘብ ካልሆነ ሕፃናቱ እስከ አስራ ስምንት ዓመት ድረስ ሊከፈላቸው የሚችለውን የቀለብ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ በአደራ ሊያስቀምጡ የማይችሉ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህም በላይ ለሁለቱ ህፃናት በአሁኑ ጊዜ የተቆረጠው የቀለብ ገንዘብ ብር 450.00(አራት መቶ___ሃምሳ) ሲሆን ይህ ገንዘብ ሕፃናቱ አካለ መጠን እኪሞላቸው ድረስ ይህ የገንዘብ መጠን ብቻ ለቀለብ ይበቃል ተብሎ ሊታሰብ የማይችል መሆኑን ከነባራዊው ዓለም እውነታ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የአመልካች የግል ንብረት ለህፃናቱ የቀለብ ጥያቄ አከፋፈል ዋስትና ይሆን ዘንድ መከበሩ ስለቀለብ የተደነገጉትን የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎችንና በሕገ መንግስቱ የተመለከተቱትን የህፃናቱን መብት የሚያስከበር ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 45202

መጋቢት 08 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ ድንቁ ወርዶፋ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሪት ኤደን ድንቁ ወርዶፋ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የብድር እዳን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች እና የአመልካች ባለቤት በሆኑት በወ/ሮ ፀጋዬ ተክሌ ላይ ሐምሌ 23 ቀን 1999 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪ በአረብ አገር ሰርተው ከሚያገኙት ደመወዝ ለአመልካችና ለባለቤታቸው ገንዘብ በሐዋላ ልከው ወላጅ እናታቸው ገንዘቡን ተቀብለው ለሚፈልጉት ጉዳይ ማዋላቸውን ገልፀው ክሱን ያስነሳውን ገንዘብ ብር 70,500.00(ሰባ ሺህ አምስት መቶ ብር) ከነሕጋዊ ወለድ እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ ከተጠሪ ላይ የተበደሩት ገንዘብ የሌለ መሆኑን፣ለማስረጃነት በቀረበው ሰነድ ላይም ያልፈረሙ በመሆኑ የሚከሰሱበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ሲሉ ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩትና የአመልካች ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ፀጋዬ ተክሌ ደግሞ የተጠሪን ክስ በማመን መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ የአመልካችን መከራከሪያ ነጥቦችን ውድቅ አድርጐ አመልካች እና ወ/ሮ ፀጋዬ ተክሌን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለክሱ ምክንያት የሆነው ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ ክሱ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ እና ተገቢው ማጣራት ከተደረገ በኋላ በዚህ ፍርድ ቤትም የአመልካች ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ፀጋዬ ተክሌ ቀርበው ገንዘቡን ከተጠሪ ወስደው ለጋራ ጥቅማቸው ማዋላቸውን በድጋሚ በማረጋገጣቸው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ሚያዝያ 14 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም አመልካች እዳውን ከወ/ሮ ፀጋዬ ተክሌ(ከባለቤታቸው) ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪ የካቲት 12 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ተገቢነት በመግለጽ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል ሲሉ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት የመልስ መልስ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ወ/ሮ ፀጋዬ ተክሌ በትዳር ፀንተው በነበሩበት ወቅት ተጠሪ ገንዘብ ያደበሯቸው ስለመሆኑ መረጋገጡን፣በዚህም ወቅት አከራካሪውን ብርድ አመልካች በሰነዱ ላይ ባይፈርሙም ባለቤታቸው የሆኑት ወ/ሮ ፀጋዬ ተክሌ መፈረማቸውንና ገንዘቡን ለጋራ ጥቅም ያዋሉ መሆኑን ነው፡፡

ብድሩ አመልካች ሳይፈርሙበት በትዳር ወቅት ወ/ሮ ፀጋዬ ተክሌ ወስደው በጋራ ጥቅም የዋለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በእርግጥ ከብር 500.00(አምስት መቶ) በላይ የሆነ ብድር ለማበደር ወይም ለመበደር የሁለቱም ተጋቢዎች ስምምነት ማስፈለጉ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 68/መ/ ስር የተመለከተ ሲሆን ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢም ውሉ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ በማቅረብ ውሉ እንዲፈርስ ማድረግ የሚችል መሆኑን የቤተሰብ ሕጉ ደንግጐ እናገኘዋለን፡፡ የሕጉ መንፈስ ውሉ የአንደኛው ተጋቢ ስምምነት ሳይኖር በመደረጉ ብቻ ከጅምሩ ውጤት አልባ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የማይወስድ ነው፡፡ ይልቁንም ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ በሕጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ውሉ እንዲፈርስ እስካላደረገው ድረስ ውሉ ውጤት ይኖረዋል፡፡ በተያዘው ጉዳይም አመልካች ሳያውቁ የተደረገ ነው ቢባል እንኳ ብድሩ ለጋራ ጥቅም የዋለ መሆኑ እና ፣ውሉን እንዲፈርስ ያላደረጉት መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

ብድሩ በትዳር ወቅት የተወሰደ ከሆነ ደግሞ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ ሕግ ግምት የሚወስድበት ሲሆን ለትዳር ጥቅም አለመዋሉን የማስረዳት ሸክም ያለባቸው አመልካች እንጂ ሌላ ወገን ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የብድር እዳው የጋራ ነው ሲሉ የሰጡትን ውሳኔ ከቤተሰብ ሕጉ መንፈስ አንፃር ሲታይ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት በአብላጫ ድምጽ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የልዩነት ሐሳብ

ስሜ በተ/ቁ. 2 የተመለከተው ዳኛ አበላጫው ድምጽ ከሰጠው ውሳኔ በሚከተለው ምክንያት በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

ተጠሪ ክስ የመሰረቱት ገንዘብ አባታቸው ለሆኑት አመልካችና ለስር 2ኛ ተከሳሽ ለሆኑት እናታቸው በሃዋላ ልከውላቸው ገንዘቡን እናታቸው ተቀብለው ለሚፈልጉት ስላዋሉት ገንዘቡን ባልና ሚስቱ እንዲከፍሏቸው ነው፡፡ ለዚህም ማስረጃ ይሆናቸው ዘንድ ያቀረቡት ሰነድ በርእሱ መተማመኛ የሚል ሲሆን በይዘቱ ሲታይ ግን የስር 2ኛ ተከሳሽ ከተጠሪ ብር 35,000 ለትዳራቸው ጥቅም ሲሉ የተበደሩ መሆኑን በማረጋገጥ የፈረሙበት ነው፡፡ ምንም እንኳን ተጠሪ ለአመልካችና ለባለቤታቸው ገንዘቡን የሰጡት በብድር ይሁን በአደራ በግልጽ ባይናገሩም ከሰነዱ በግራ ቀኙ መሃከል ነበረ ሊባል የሚችለው የብድር ስምምነት ነው፡፡ በመሆኑም ለውሳኔው አሰጣጥ ሊያዝ የሚችለው ጭብጥ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የብድር ስምምነት አለ? ወይስ የለም? የሚለው ነው፡፡

ብድር ከውል አይነቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ውል ማለት ንብረታቸውን የሚመለከቱ ግዴታዎችን ለማቋቋም ወይም ለመለወጥ ወይም ለማስቀረት ባላቸው ተወዳዳሪ ግንኙነት በሁለት ወይም በብዙ ሰዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 1675 ሲያመለክት በህግ ፊት የሚፀና ውል ለማቋቋም በተዋዋዮች መሃከል ጉድለት የሌለው ስምምነት መኖር አስፈላጊ እንደሆነ ከፍ/ሕ/ቁ 1678/ሀ/ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም በሁለት ተዋዋዮች መሃከል ውል አለ ለማለት የተዋዋዮቹ ስምምነት መኖሩ መሰረታዊ ነገር ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስናመራ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል ውል መኖሩን ለማስረዳት የቀረበው ሰነድ 2ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ሆነው ብድሩን የወሰዱ ስለመሆኑ ይጥቀስ እንጂ አመልካች በውሉ ላይ አልፈረሙም፡፡ በፁሁፍ ውል ላይ ተዋዋዮች ስምምነታቸውን የሚገለፁት ሰነድ ላይ ፊርማቸውን ወይም የጣት አሻራቸውን በማስፈር በመሆኑ አመልካች የብድር ውሉ ላይ ግዴታ ለማቋቋም ስምምነታቸውን ሰጥተዋል ማለት አይቻልም፡፡ ብድር የተሰጠው ከብር 500.00 በላይ በመሆኑ ስምምነት መፈፀሙን ማስረዳት የሚቻለው በጽሁፍ ወይም በፍ/ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም በመሐላ ብቻ እንደሆነ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2472/1/ ያመለክታል፡፡ ውል በፁሁፍ እንዲደረግ ህጉ በሚያዝበት ግዜ ደግሞ የጽሁፍ የአፃፃፍ ስርአት ሊከተል እንደሚገባ ከፍ/ሕ/ቁ. 1720/1/ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በፁሁፍ ውል ተዋዋዩን ለማስገደድ እንዲችል በውሉ ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ሁሉ ሊፈረሙ እንደሚገባ የፍ/ሕ/ቁ. 1727/1/ ያመለክታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች በብድሩ ውል ግዴታ ያለባቸው ለመሆኑ ተስማምተው አልፈረሙም፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ ደግሞ አመልካችን ወክለው የብድር ውል ለመፈረም የተሰጣቸው የውክልና ስልጣን ስለመኖሩ የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ ስለሆነም 2ኛ ተከሳሽ እኔና አመልካች ሆነን ብድሩን ወስደናል በማለት አረጋገጠው መፈረማቸው ብቻ አመልካችን ለማስገደድ የሚችል የሕግ መሰረት የለውም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ብድር አለመውሰዳቸውን ክደው የተከራከሩና በመሓላ ቃልም ቢሆን ያመኑት ነገር ስለሌለ በተጠሪና በአመልካች መሃከል የብርድ ስምምነት አለ ማለት አይቻልም፡፡

የስር ፍ/ቤቶች አመልካች ለብድሩ ሃላፊ ናቸው ወደሚለው መደምደሚያ የደረሱት ገንዘቡ ለጋራ ጥቅም ውሏል በማለት የቤተሰብ ህጉን አንቀጽ 71ን በመጥቀስ መሆኑን ከመዝገቡ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመጀመሪያ ክሱ ተጠሪ ለአመልካች ገንዘብ በማበደራቸው ገንዘቡን እንዲመልሱ እስከሆነ ድረስ ሊያዝ የሚገባው ጭብጥ ብድር አለ? ወይስ የለም? የሚለው እንጂ ገንዘቡ ለጋራ ጥቅም ውሏል አልዋለም የሚል ሊሆን አይገባም ይህ ጭብጥ ደግሞ ሊወሰን የሚገባው የብድር ውልና ስለወጪዎች በጠቅላላው ከሚናገሩት የሕግ ድንጋጌዎች አኳያ ነው፡፡ የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 70/2/ እና 71 ስንመለከትም ለትዳር ጥቅም እንደተደረገ የሚቆጠር እዳ ከተጋቢዎቹ የጋራ ሃብት ወይም ከባል ወይም ከሚስት የግል ሃብት ሊከፈል እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌም ግን ምናልባት የተጋቢዎቹ አንደኛው በግሉ ብድር ወይም ሌላ እዳ ውስጥ ቢገባም ገንዘቡ ለጋራ ጥቅም እስከዋለ ድረስ እዳው ከተጋቢዎቹ የጋራ ወይም የአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረትም ሊከፈል የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ነው ይህ ድንጋጌም በአፈፃፀም ግዜ ችግር እንዳያመጣ የተቀመጠ ድንጋጌ ስለመሆኑ ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ሃተታ ምክንያት መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የስር 2ኛ ተጠሪ የተበደሩት እዳ ለጋራ ጥቅም ከዋለ እዳው ከአመልካችም የግል ንብረት ሊከፈል የሚችይል በቀር አመልካች የወሰዱት ብድር ሳይኖር በስር 2ኛ ተከሳሽ ብቻ የተወሰደው ብድር አመልካችም እንደወሰዱት ብድር ተቆጥሮ ሃላፊ ናቸው መባሉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ውሳኔው ሊሻር ይገባል በማለት አብላጫው ድምጽ ከሰጠው ውሳኔ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 45370

መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** 1. አቶ ዳንኤል አበበ

2. አቶ ኤርሚያስ ቦጋለ - ጠበቃ አቶ ሽፈታው ከበደ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ ሙሉ ወልደየስ - አልቀረቡም

2. አቶ አብዱልአዚዝ ሠኢድ - ጠበቃ ሀሰን ሁሴን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ሐሰተኛ የወራሽነት ማስረጃ መሰረት ተደርጎ የተከናወነ የውርስ ሃብት ሽያጭ ውል ይፍረስልን ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የሐረሪ ክልል ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካቾች በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም አሻሽለው በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም የአመልካቾች አውራሽ ወ/ሮ ታደለች ወ/ገብርኤል በጥር 21 ቀን 1987 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን፣ የሟች ሕጋዊ ወራሾች አመልካቾች እና በክስ ውስጥ ያልገቡ ሁለት ወራሾች መኖራቸውን፣ አንደኛ ተጠሪ ከሟች ወ/ሮ ታደለች ወ/ገብርኤል ጋር ምንም አይነት ለወራሽነት የሚያበቃ ዝምድና ሳይኖራቸው፣ በአንድ በኩል በ1968 ዓ.ም ስጦታ አድርገውልኛል የሚል ሰነድ ለፍርድ አቅርበው ተቀባይነት ሲያጡ ከሟች ጋር የአንድ እናት ልጆች፤ እህትማማቾች ናቸው፣ ሌላ ወራሽ የላቸውም በማለት በሐሰት የሚመሰክሩ ምስክሮችን አዘጋጅተው በፍርድ ቤት የወራሽነት ማስረጃ ማግኘታቸውን፣ ይህንኑ ማስረጃ ይዘውም የሟች ወ/ሮ ታደለች ንብረት የሆነውን ቤት ለሁለተኛ ተጠሪ መሸጣቸውን፣ የአንደኛ ተጠሪ ወራሽነት ማስረጃም ሐሰተኛ መሆኑን ዘርዝረው አንደኛ ተጠሪ ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል እንዲፈርስላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎችም ለክሱ በሰጡት መልስ የቤቱ ስመ ሐብት በአንደኛ ተጠሪ ስም የሚታወቅ በመሆኑ አመለካቾች ክስ ለመመስረት መብት (ጥቅም) የሌላቸው መሆኑን፣ የሽያጭ ውል ይፍረስልን ጥያቄ በይርጋ የታገደ መሆኑን፣ ሽያጩን በሕጉ አግባብ ያደረጉት በመሆኑ ሊፈርስ እንደማይገባ ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ቤቱ ስመ ንብረቱ የሚታወቀው በአንደኛ ተጠሪ መሆኑን፣ ንብረቱን አንደኛ ተጠሪ ወደ እጃቸው ያስገቡትም በአደራ ሊጠብቁ ተብሎ ስለመሆኑ አመልካቾች ገልፀው መከራከራቸውን፣ አንደኛ ተጠሪ የሟች ወ/ሮ ታደለች ወ/ገብርኤል ወራሽ መሆናቸውን የሚያሳይ የወራሽነት ማስረጃ ይዘው ባሉበት ጊዜ የቤት ሽያጩን ስልጣን ባለው አካል ፊት ቀርበው ያደረጉ ቢሆንም የወራሽነት ማስረጃው ሐሰተኛ መሆኑ መረጋገጡን በመግለፅ አመልካቾች አንደኛ ተጠሪን ከሚጠይቁ በስተቀር የቤት ሽያጭ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካቾች ሚያዚያ 12 ቀን 2001 ዓ.ም በተጻፈ ሦስት ገጽ አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ተጠሪዎች የሽያጭ ውሉ የፈፀሙት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ መሆኑ በግልፅ ተረጋግጦ እያለ ሽያጩ ሊፈርስ አይገባም መባሉ ያላገባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ የሽያጩ ውል ሊፈርስ አይገባም መባሉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ አንደኛ ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ በጠበቃቸው አማካኝነት ነሐሴ 18 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ አምስት ገጽ ማመልከቻ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው መስከረም 15 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሶስት ገፅ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪውን ቤት አንደኛ ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ በመያዝና ስመ ሃብቱን በማዞር ለሁለተኛ ተጠሪ ስልጣን ባለው አካል ፊት ቀርበው የሸጡ መሆኑን፣ በውሉ ላይም ለገዥ መድህን ስለመሆናቸው በመግለፅ ግዴታ የገቡ መሆኑን፣ አንደኛ ተጠሪ የያዙት የወራሽነት ማስረጃ ከሽያጩ በኂላ ሐሰተኛ መሆኑ መረጋገጡን፣ የተሸጠው ቤትም የአመልካቾች አውራሽ የሆኑት የወ/ሮ ታደለች ወ/ገብርኤል መሆኑ መረጋገጡን፣ ከሽያጩ በኂላ ሁለተኛ ተጠሪ የስመ ሃብቱን ወደ ራሳቸው አዙረው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች መሆናቸውን ነው፡፡ የአመልካቾች ክርክር መሰረቱም የአውራሻቸው የግል ንብረት የሆነውን ምንም መብት የሌላት አንደኛ ተጠሪ በተጭበረበረ መንገድ ወራሽነት አሳውጀው እና የቤቱን ስመ ሃብት በማዞር መሸጣቸው ሽያጩን ሕጋዊ አያደርገውም በሚል ምክንያት ስለመሆኑም ተገንዝበናል፡፡ እኛም በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ከሕጉ ጋር በሚከተለው መልኩ በማዛመድ ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው አንድ ንብረት ለሌላ ሰው በሕጋዊ መንገድ ሊያስተላልፍ የሚችለው በንብረቱ ላይ መብት ሲኖረው መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ በጥበቃ የማይደረግለት ወይም የሌለ መብት ወደ ሰው ሊተላለፍ አይችልም፡፡ ይህ ተቀባይነት ያለው የሕግ መርሕ ነው፡፡ የሌላ ሰው ንብረት ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ ሕጋዊ የሆነ ስልጣን ሊኖር ይገባል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አንደኛ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት የሸጡት የአመልካቾችን ወይም የአውራሻቸውን ሕጋዊ ስምምነት ወይም ወራሽነት አግኝተው ባይሆንም የሚች ወራሽ መሆናቸውን በፍርድ ቤት አረጋግጠው፣ የቤቱን ስመ ሃብት ከሽያጩ በፊት ከተገቢው የአስተዳደር አካል ከአገኙ በኂላ ሲሆን ሽያጩም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ መሰረት ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተደደር ክፍል የምስክር ወረቀት ሲሠጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ባለሃብት ሆኖ ሊቆጠር እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይህን ማስረጃ የያዘ ሰው ደግሞ ሃብቱን በሕጉ አግባብ ከሸጠ ተግባሩ ሕገ ወጥ የሚባልበት ምክንያት የለውም፡፡ አንድ ሰው በሕግ ጥበቃ የተደረገለትን መብት በሕጋዊ መንገዶች በሌላ ለማስተላለፍ መብት አለውና፡፡ በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበሩት የአሁኗ አንደኛ ተጠሪ ወ/ሮ ሙሉ ወልደየስ አከራካሪውን ቤት በስማቸው የባለሃብትነት ምስክር ወረቀት መያዛቸው ንብረቱ የግል ሃብት እንደሆነ የሚያሰቆጥር ሲሆን ይህን ማስረጃ በመመልከት ንብረቱን ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት የሚገዛ ሰው ሽያጩን ያከናወነው ከሕግ ውጪ ነው ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በቤቱ ላይ ሕጋዊ መብት የሌለው ሰው በውሉ ለገዥው መድህን ለመሆን ግዴታ ገብቶ ሽያጩን አከናውኖ ሲገኝም ትክክለኛው ባለሃብት ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጎ የገዛውን ገዥ ሳይሆን ሻጩን ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2882 እስከ 2884 ድረስ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 997 ድንጋጌ መንፈስ እና ይዘት የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ በአጠቃላይ ሁለተኛ ተጠሪ

አከራካሪውን ቤት የገዙት በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ ከያዙት ግለሰብ ሁኖ ሽያጩንም ያከናወኑት ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት በመሆኑ ውሉ የሚፈርስበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ አመልካቾች በቤቱ ላይ የወራሽነት መብት ያላቸው መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ያላቸው መፍትሔ የሽያጩን ዋጋ ከስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ ከነበሩት ከወ/ሮ ሙሉ ወልደየስ መቀበል ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሠጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአከራካሪው ቤት ላይ የተደረገው ሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም፣ ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ብለናል፡፡
3. አመልካቾች የቤቱን ሽያጭን ገንዘብ ብር 60000.00 (ስልሳ ሺህ) ከወ/ሮ ሙሉ ወልደየስ እንዲቀበሉ ብለናል፡፡ በዚሁ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈፅም ለስር ፍርድ ቤት ግልባጩ ይድረሰው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 42691

መጋቢት 22 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ አደፍርስ በቀለ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ይቁም በቀለ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በስጦታ የተገኘ ቤት ልረከብ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ ጥር 21 ቀን 1999 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15 (በቀድሞው አጠራር ወረዳ 28 ቀበሌ 15) ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቁጥር 321 የሆነውን ቤት ከሟች ወ/ሮ አለሚቱ በላይነህ በስጦታ የተላለፈላቸው መሆኑን፣አመልካች ወንድማቸው በመሆኑ በጊዜው ሲቸግራቸው ቤቱን እንዲጠቀሙበት ተጠሪ ፈቅደውላቸው ይዘው ሲጠቀሙት ከቆዩ በኋላ ቤቱን እንዲለቁላቸው ሲጠየቁ አመልካች ፈቃኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውን ገልፀው አመልካች ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ለክሱ በሰጡት መልስ፤ተጠሪ ያቀረቡት የስጦታ ማስረጃ አለመኖሩን፣ግብር መክፈል የቤት ባለቤት እንደማያደርግ እና ተጠሪ ክስ ለመመስረት የሚያስችላቸው መብት የሌላቸው መሆኑ፣የቤቱ ግምትም የተጋነነ መሆኑን፣በቤቱ ውስጥ ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ መኖር የጀመሩ በመሆኑ ጉዳዩ በይርጋ እንደሚታገድ፣ቤቱ የወ/ሮ አለሚቱ በላይነህ ሆኖ አመልካችም የወ/ሮ አለሚቱ በላይነህ ወራሽ በመሆናቸው ቤቱን ሊለቁ እንደማይገባ ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመመረመረ በኋላ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ተጠሪ በስጦታ ውል መሰረት ያገኙት በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ጥር 04 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- በስር ፍርድ ቤት የተነሳው የይርጋ ክርክር የታለፈው ያላግባብ ነው፣የቤቱ ባለቤት መሆኔን የሚያሳይ ማስረጃ ስላለኝ ይቅረብልኝ የሚል ጥያቄ የታለፈው ያላግባብ ነው በማለት ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም አመልካች ያነሱት የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ የተደረገው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ሰኔ 24 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ አመልካችም ሐምሌ 16 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ አንድ ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ ችሎት ግራ ቀኙን ታህሣሥ 20 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በቃል አከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪው ቤት የሟች ወ/ሮ አለሚቱ በላይነህ መሆኑን፣ተጠሪ ቤቱን አግኝቼአለሁ የሚሉት ሐምሌ 26 ቀን 1972 ዓ.ም በተደረገው ስጦታ ሆኖ ስጦታው አግባብነት ባላቸው አካላት የተቀመጠ እና የተመዘገበ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ማረጋገጡን፣የቤቱ ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ አለሚቱ በላይነህ ከዚህ አለም በሞት እስከተለዩበት ጥር 11 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ በአከራካሪው ቤት ውስጥ ይኖሩበት እንደነበር፣አመልካች በቤቱ ውስጥ ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ አስካሁን ድረስ መኖራቸውን፣የቤቱ ስመ ሃብት ከሟች ወደ አመልካችም ሆነ ተጠሪ ያልተዛወረ መሆኑን ነው፡፡

ተጠሪ ለክርክሩ መሰረት ያደረጉት የስጦታ ውል ሐምሌ 26 ቀን 1972 ዓ.ም የተደረገ ሆኖ ክሱ እስከተመሰረተበት ጊዜ ድረስ ለአፈፃፀም ያልቀረበ መሆኑን ክርክሩ በግልጽ ያሳያል፡፡ ስጦታ በምን ያህል ጊዜ መፈፀም አለበት የሚለውን ጥያቄ በዚህ ረገድ የተመለከቱት ልዩ ድንጋጌዎች በግልጽ ያስቀመጡት የጊዜ ገደብ የለም፡፡ ይሁን እንጂ የስጦታ ውል ድንጋጌዎች በዚህ ረገድ ያስቀመጡት የጊዜ ገደብ የለም ተብሎ የስጦታ ውል ይፈፀም ጥያቄ በማናቸውም ጊዜ ሊቀርብ ይችላል ሊባል አይችልም፡፡ በሕጉ በግልጽ ካልተቀመጠ በስተቀር ማንኛቸውም ግዴታ ሊፈፀም የሚገባበት የጊዜ ገደብ ሊኖር ይገባል፡፡ የስጦታ ውልን የሚገዙ ድንጋጌዎች ግልጽ የሆነ ጊዜ ገደብ ባያስቀምጡም ስጦታ ውል እንደመሆኑ መጠን ሊፈፀም የሚገባው በአስር አመት የጊዜ ገደብ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1676/1/ እና 1845 ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ ተጠሪ የስጦታ ውሉ ሐምሌ 26 ቀን 1972 ዓ.ም ተደርጐልኛል እያሉ ስጦታ አድራጊያቸው በሕይወት እያሉ አከራካሪውን ቤት በስጦታ ውሉ መሰረት እንዲፈጸምላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የለም፡፡ የስጦታ ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከተመሰረተበት ጊዜ እስከ ጥር 21 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ደግሞ በሕጉ የተመለከተው የአስር አመት ጊዜ ገደብ አልፏል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የይርጋ ክርክር ውድቅ ያደረጉት ያላግባብ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 34508 ሐምሌ 02 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 69852 ግንቦት 06 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ስጦታውን መሰረት አድርገው የአቀረቡት የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄ በይርጋ የታገደ ነው፣አመልካች ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 44237

መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ሙሉሸዋ ቦጋለ - በራሳቸውን እና ወኪል ለሆኑላቸው

1. አቶ ሳሙኤል ቦጋለ
2. ወ/ሪት መሰረት ቦጋለ
3. አቶ ኤርሚያስ ቦጋለ

} ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ መስፍን ቦጋለ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ የሰበር መዝገብ የቀረበው ክርክር በውርስ ሕጉ ውስጥ የተመለከቱትን ይርጋ ድንጋጌዎችን አተረጓጐም እና አፈፃፀማቸውን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካቾች መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም በአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ፤የአመልካቾች ወላጆች የሆኑት አቶ ቦጋለ ባሩዴ ሰኔ 06 ቀን 1989 ዓ.ም ፣እና ወ/ሮ ኢትዮጵያ ናዴ ደግሞ መስከረም 17 ቀን 1997 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ወራሽነታቸውን ማረጋገጣቸውን፣ሟቾች በሕይወት እያሉ ያፈሩትን ንብረት የአሁኑ ተጠሪ እንዲያካፍሏቸው ቢጥይቋቸውም ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው ለብቻቸው ይዘው እየተጠቀሙ እንደሚገኙ ገልፀው የውርስ ሃብቱን የሚያጣራ የውርስ አጣሪ በፍርድ ቤት እንዲሾምቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ የአመልካቾች የውርስ ይጣራልን ጥያቄ አውራሾቻቸው በሞት ከተለዩ በኂላ ከሦስት አመታት በኂላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ውድቅ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር የአመልካቾች የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ አውራሾቻቸው ከሞቱ በአንድ ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም፣ሆኖም አመልካቾች የውርስ ንብረቱን በተመለከተ ገምተው ክስ ማቅረብ ይችላሉ የሚል ምክንያት በመስጠት የአመልካቾችን አቤቱታ (ጥያቄ) ውድቅ አድርጉል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ ይኸው ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ይርጋን አስመልክቶ የያዘውን ምክንያት በመቀየር የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ በሦስት አመት ያልቀረበ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ምክንያቱን ለውጦ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካቾች መጋቢት 07 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አመልካቾች ወራሽነታቸውን በጊዜው አረጋግጠው የውርስ ንብረት ይጣራልኝ የሚለውን ጥያቄ ማቅረባቸውንና

ተጠሪም የሰጠው መልስ አመልካቾች ለቤቱ ጥበቃ የወጣውን ሂሳብ ለተጠሪ ከፍለው ውርሱ ቢጣራ ተቃውሞ የለኝም የሚል ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በይርጋ የታገደ ነው በማለት መወሰናቸው ያላግባብ ነው ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ቀርበው የካቲት 12 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የመልሳቸው ይዘትም ጉዳዩ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ስለሆነ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካቾች የውርስ ይጣራልን ጥያቄ በሦስት ዓመት ይርጋ የታገደ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው አከራካሪውን ንብረት ሟች ወ/ሮ ኢትዮጵያ ናዴ እስከእለተ ሞታቸው ድረስ ይዘው ሲጠቀሙት የነበረ መሆኑ፣ወ/ሮ ኢትዮጵያ ናዴ መስከረም 17 ቀን 1997 ዓ.ም መሞታቸውን፣አመልካቾች የወ/ሮ ኢትዮጵያ ናዴ መጀመሪያ ደረጃ ወራሽነታቸውን በመ/ቁ. 612/98 የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም፣ተጠሪ በበኩላቸው የወ/ሮ ኢትዮጵያ ናዴ መጀመሪያ ደረጃ ወራሽነታቸውን በመ/ቁጥር 56/98 ታህሣሥ 25 ቀን 1998 ዓ.ም ማረጋገጣቸውን፣አሁን እየተከራከሩ ያሉት የውርስ ንብረት ድርሻቸውን አመልካቾች እንዲያካፍሏቸው መሆኑን ነው፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁ .1000 የወራሽነት ጥያቄ የማቅረቢያ የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996 እስከ 1002 ድረስ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 999 ስር በተመለከተው መሰረት የሚቀርበው የወራሽነት ጥያቄ(petition hereditists) በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች ከተገለፀው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የወራሽነት ጥያቄ አንድ ወራሽ በሌላ በወራሽነት የውርስ ሐብት በያዘ ሰው ላይ ክስ ሲያቀርብ ተፈፃሚነት ባላቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች ስር በተመለከቱት ደንቦች መሰረት የሚገደብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የሟች ወ/ሮ ኢትዮጵያ ናዴ ወራሽነታቸውን ታሕሣሥ 25 ቀን 1998 ዓ.ም ብቻቸውን፣አመልካቾች ደግሞ የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም በመሆን በፍርድ ቤት ውሳኔ አረጋግጠዋል፣የክፍፍሉ ጥያቄ በቀረበበት ንብረት ደግሞ በሟች ወ/ሮ ኢትዮጵያ ናዴ ተይዞ የቆየ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም የምንገነዘበው የሟቿ ወራሾች በሕጉ በተመለከተው ጊዜ ገደብ ውስጥ ተለይተው መታወቃቸውን ነው፡፡ የአመልካቾች ጥያቄ ደግሞ የውርስ ክፍያ ነው፡፡ የውርስ ክፍያ ደግሞ ራሱን የቻለ የውርስ ሕግ ሆኖ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1060 እስከ 1113 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ስር የተሸፈነ ጉዳይ ነው፡፡ የውርስ ክፍያ ጊዜን በተመለከተ የፍ/ብ/ሕጉ በአንቀጽ 1062 ስር የደነገገ ሲሆን የድንጋጌው ይዘትም ውርሱ በተጣራ ጊዜ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን እያንዳንዱ የጋራ ወራሾች ውርሱን እንክፋፈል ብለው ለመጠየቅ እንደሚችሉ መደንገጉን የሚያሳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1060 ድንጋጌ ስር ደግሞ የውርስ አከፋፈል እስካልተፈፀመ ድረስ ውርሱ በወራሾች መካከል ሳይነጣጠል እንደሚቆይ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አመልካቾች የሟች ወራሽነታቸውን በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ አረጋግጠው ከቆዩ በኂላ የውርስ ንብረቱን የክፍፍል ጥያቄ ማቅረባቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ .1000/1/ እና /2/ ስር በተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ የሚታገድ ሳይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1062 ድንጋጌ መሰረት በማናቸውም ጊዜ የሚቀርብ በመሆኑ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የያዙት ምክንያትም ሆነ የደረሱበት መደምደሚያ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57313 በሐምሌ 30 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጠቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 71948 ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም ምክንያቱ ተለውጦ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ የውርስ ክፍፍል በመሆኑ በይርጋ ሊታገድ አይገባም ብለናል፡፡
3. የአመልካቾችን የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄያቸውን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተገቢውን እንዲያሟሉ አድርጐ እንዲያስተናግደው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 46490

መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** እነ ወ/ሮ ቦጋለች ደባልቄ(4 ሰዎች) - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ መሰረት በለጠ - አልቀረቡም

## ፍ ር ድ

አመልካቾች ለአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ የስር ሁለተኛ ተከሳሽ ከነበሩት ግለሰብ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል እንዲፈርስ ያቀረቡት ክስ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ ውሉ እንዲፈርስ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ይግባኝ ሰሚው የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔውን ስለሻረውና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለውም በማለቱ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

አመልካቾች በአዋሳ ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተጠሪዋ ከአቶ ፍሬው ለማ ጋር በጋብቻ በነበሩበት ጊዜ ቤት መስራታቸውንና ሁለት ልጆችም መውለዳቸውን ገልፀው አቶ ፍሬው ለማ ከዚህ አለም በሞት ሲለዩ ግን ተጠሪዋ የጋራ ንብረት የሆነውን ቤት በስማቸው አዛውረው ለስር ሁለተኛ ተከሳሽ ስለሸጡና ይህም የህፃናቱን መብት ስለሚጐዳ የሽያጩ ውል እንዲፈርስ ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም የሽያጩ ውል በሕጉ አግባብ የተከናወነ በመሆኑ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ተጠሪ በቤቱ ላይ ያላቸው ድርሻ ግማሽ ሲሆን ቀሪው ድርሻ ለህፃናቱ ከአባታቸው የተላለፈላቸው በመሆኑ የህፃናቱን ድርሻ አጠቃለው ቤቱን መሸጣቸው የህፃናቱን መብት የሚጐዳ በመሆኑ የሽያጩ ውል ሊፈርስ ይገባል ማለት በተጠሪ ስም ተሰጥቶ የነበረው የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰረዝና በሟች ስም ተመዝግቦ ቤቱ የተጠሪና የህፃናቱ የጋራ ሃብት ሆኖ እንዲቆይ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ሁለቱን ወገኖች አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለውም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጓል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የተሰጠው ውሳኔ ከህፃናት መብትና ከሞግዚት ሥልጣን ወሰን አኳያ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው አመልካቾች የሚጠይቁት ተጠሪ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት የሆነውን ቤት በመሸጣቸው ውሉ እንዲፈርስላቸው ነው፡፡ ውሉ ሊፈርስ ይገባል የሚሉትንም ቤቱ የተጠሪ የግል ሃብት ሳይሆን የተጠሪና የሕፃናቱ የጋራ ሃብት በመሆኑ የህፃናቱን ድርሻ አጠቃለው መሸጣቸው የህፃናቱን መብት ይጐዳል

በማለት ነው፡፡ አካለ መጠን ያላደረሰ ልጅ የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ስልጣን የሚሰጠው ለልጁ እናትና አባት ሲሆን ከወላጆቹ አንደኛው የሞተ ከሆነ ይህንን ስልጣን ይዞ የሚቆየው በህይወት ያለው ወላጅ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ የልጆቹ አሳዳሪና ሞግዚት ሆነዋል፡፡ የልጆቹ አስተዳዳሪና ሞግዚት በመሆናቸውም የልጆቹን መኖሪያ፣ጤና አጠባበቅ፣አስተዳደግ፣ትምህርት ማህበራዊ ግንኙነቱን በተመለከተ እንዲማሩና እንዲሁም ንብረትን በተመለከተ እንዲያስተዳድሩ ህጉ ለተጠሪ ሥልጣን ሰጥቷቸዋል፡፡ በመሆኑም ለልጆቹ መልካም አስተዳደግ ይረዳ ዘንድ የልጆቹን ሃብት እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው የመወሰን ስልጣን ስላላቸው የልጆቹን ግማሽ ድርሻ በተመለከተ ለልጆቹ መልካም አስተዳደግ አስፈላጊ ከሆነ ድርሻቸውን መሸጣቸው ብቻውን የልጆቹን መብት ይነካል ለማለት የሚያስችል አይሆንም፡፡ በእርግጥ በተሻሻለው የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 292 ስር ሞግዚቱ እንዲሸጥ በግልጽ የተፈቀደለት የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ ንብረቶችን፣አክስዮኖችንና የገንዘብ ሰነዶችን ነው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በመለከተ በህጉ መሸጥ የሚቻል መሆን አለመሆኑ በግልጽ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡ ከፍ ሲል የተጠቀሰው ድንጋጌ ሞግዚቱ ሊሸጥ የሚችለውን የንብረት አይነቶች በግልጽ ለይቶ ማስቀመጡ ከዚህ ውጭ ያሉትን ንብረቶች እንዳይሸጥ መከልከሉን ያሳያል የሚባል ቢሆን እንኳን ሞግዚቱ የሕግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ለፈፀማቸው ድርጊቶች ወኪል የሆነ ሰው ከተሰጠው ስልጣን በላይ በሚሰራበት ጊዜ አግባብነት ያላቸው የውክልና ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ የክልሉ ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 321 ያመለክታል፡፡ ውክልናን በሚመለከቱ የፍ/ህጉ ድንጋጌዎች ስንመለከት ደግሞ ወኪሉ የስልጣን ወሰኑን በማለፍ በስራ ጊዜ ሿሚው ተግባሩን ለማጽደቅ ወይም ለማፍረስ የሚችል ቢሆንም እንኳን ተወካዩ በውክልና ከተሰጠው ስልጣን ውጭ በማለፍ ሰርቶ የተገኘ ስራ በቅን ልቦና የሰራው ከሆነ ወካዩ ስራውን ለማጽደቅ የሚገደድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2207/1/ ያመለክታል፡፡ ተጠሪም ቤቱን የሸጡት ለልጆቻቸ4ው መልካም አስተዳደግ በተለይ ለትምህርታቸው ስለሚጠቅም ያለባቸውን የሞግዚትነት ስልጣን በአግባቡ ለመወጣት እንደሆነ ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች ግን ተጠሪዋ ሌላ ባል ስላገቡ ንብረቱን አዲስ ከመሰረቱት ጋብቻ ንብረት ጋር ይቀላቅላሉ ከማለት ባለፈ አመልካች በልጆቹ አስተዳደግና አጠባበቅ ላይ ጉዳት አድርሰዋል ወይም ንብረታቸውን ያለአግባብ አባክነዋል በማለት በማስረጃ የተደገፈ ተጨባጭ ክርክር አላቀረቡም፡፡ በእርግጥ ተጠሪ ሞግዚት በመሆናቸው ብቻ የልጆቹን ሃብት እንደፈለጉ ማባከን ስልጣን የላቸውም፡፡ አመልካቾችም ማስረዳት ያለባቸው ተጠሪ ቤቱን መሸጣቸውን ብቻ ሳይሆን ቤቱ በመሸጡ ምክንያት በልጆቹ ላይ የደረሰው ጉዳት ጭርም ነው፡፡ ለልጆቹ መልካም አስተዳደግ አስከሆነ ድረስ ተጠሪ የራሳቸውንና የልጆቻቸውን የጋራ ሃብት የሆነውን የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጣቸው በራሱ የሽያጩ ውል ለማፍረስ የሚያስችል በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቱ የተሸጠው የልጆቹ መልካም አስተዳደግ መሆን አለመሆኑን ሳይመረምር ተጠሪ የራሳቸውንና የልጆቻቸው የጋራ ንብረት የሆነውን ቤት መሸጣቸውን ብቻ በምክንያትነት በመውሰድ የሽያጩ ውል ሊፈረስ ይገባል በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔውን መሻሩ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23385 ጥር 1 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 26392 መጋቢት 29 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 51295

መጋቢት 06 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሒሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ ዮሐንስ ጡእማይ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ ምህረት ገብሩ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ባልና ሚስት በትዳር ወቅት እያሉ አንደኛው ተጋቢ ከሌላው ተጋቢ እውቅና ውጪ ብድር ተበድሮ ሲገኝ ብድር የጋራ የሚሆንበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክር የተጀመረው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በውቅሮ በደደቢት ጣቢያ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የአመልካች የካቲት 01 ቀን 2000 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም ባጭሩ፡- ከተጠሪ ጋር የነበረኝ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ የጋራ ንብረት ክፍፍልም በፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፈፀምልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ ጋብቻው በፍቺ በፍርድ ቤት ቢፈርስ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን፣በጋራ ንብረት ክፍፍልም ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመመረመረ በኋላ በአመልካችና በተጠሪ በፈፀሙት የጋብቻ ውል መሰረት እኩል በእኩል እንዲካፈሉ፣በጋብቻ ወቅት የተወለዱት ሦስት ልጆች ከተጠሪ ጋር እንዲያድጉ ሆኖ ቀለብን በተመለከተ ግን ለእያንደንዳቸው በወር ብር 70.00(ሰባ ብር) አመልካች እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም ተጨማሪ አመልካች ለአሁኑ ክርክር መሰረት የሆነው ማረት ከተባለ ድርጅትና ከዳሽን ባንክ የተወሰነውን የብድር እዳ በተመለከተ ተጠሪና አመልካች በጋራ የከፈሉት ተቀንሶ ቀሪውን በጋራ እንዲከፍሉት፣እዳው ከተቀነሰ በኋላ የንብረት ክፍፍልም እንዲፈፀም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለውቅሮ ወረዳ ፍርድ ቤት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ከዚህ በኋላም ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ሰበር ሰሚው ችሎት የንብረት ክፍፍልን በሚመለከት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ሲያፀና በስር ፍርድ ቤቶች የጋራ ነው ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ ግን አመልካች የተበደሩትን ብር በሚመለከት ተጠሪን ሳያሳየው የተበደሩት፣የተበደሩትም ብር በጋራ ጥቅም መዋሉን ያላስረዱ እና እንዲሁም የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ቤት የሆነውን አመልካች ከዳሽን ባንክ ለተበደሩት ብድር አስፍፈል ለዋስትና ሲያስይዙ የተጠሪን ፈቃድ አልጠየቀም የሚሉትን ምክንያቶች በመያዝ አመልካች ከዳሽን ባንክ የተበደሩትን ብር 65,000.00(ስልሳ ስምንት ሽህ ብር) የአመልካች የግል እዳ ነው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ታህሣሥ 19 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ የክልሉ ሰበር ችሎት በሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት በተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ ብድሩ መኖሩን አውቀው ከስምንት ወራት ያህል እዳውን ከአመልካች ጋር ሲመልሱ የነበሩ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ እና አመልካች ነጋዴ በመሆናቸው የተጠሪን ፈቃድ ሳይጠይቁ ብድር መበደርና የጋራ ንብረትን በዋስትና ማስያዝ የሚችሉ መሆኑን ሕጉ የሚፈቅድ ሆኖ እያለ የተጠሪ ፈቃድ ያልተጠየቀበት እና እዳው ለትዳር ጥቅም የዋለ መሆኑ አልተረጋገጠም ተብሎ እዳው ተጠሪን አይመለከታቸውም መባሉ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በአንድ በኩል የአመልካች በንግድ ስራ ከመሰማራታቸውና በሌላ በኩል ደግሞ የባንክ ብድሩ የተወሰደው ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ከመሆኑ አንፃር ብድሩ ለጋራ ጥቅም አልዋለም ተብሎ ተጠሪ ከእዳው ነፃ እንዲሆኑ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጉአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ በትዳር ፀንተው በነበሩበት ወቅት አመልካች በንግድ ስራ ተሰማርተው የነበሩ መሆኑን፣በዚህም ወቅት አከራካሪውን ብድር ተጠሪን ሳያሳውቁ የማይንቀሳቀስ የጋራ ንብረት በዋስትና አስይዘው መውሰዳቸውን፣ከትዳር ላይ እያሉም የተወሰነውን የብድሩን ገንዘብ መመለሳቸውን ነው፡፡

አመልካች በንግድ ስራ የተሰማሩ ነጋዴ ከሆኑ ብድሩን በሚበደሩበት ወቅት የተጠሪን ፈቃድ ማግኘት ነበረባቸው ሊባሉ የማይችሉ መሆኑን የንግድ ሕግ ቁጥር 16 ድንጋጌን ይዘትና መንፈስ በምንመለከትበት ጊዜ የምንረዳው ነጥብ ነው፡፡ ተጠሪ እዳው መኖሩን ያውቁ የነበረ ስለመሆኑም በወቅቱ የብድሩን ገንዘብ በጋራ መመለሳቸው የሚያረጋግጠው ነገር ነው፡፡ በመሆኑም ብድሩ አመልካች ነጋዴ ሆነው በትዳር ወቅት ወስደው በጋራ ሲከፈል የነበረ በመሆኑ የተጠሪ ፈቃድ የለበትም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በእርግጥ የባልና ሚስት የጋራ ሐብት የሆነ አንድ የማይነቀሳቀስ ንብረት ሐብትነትን ወይም ሌላ መብት ለ3ኛ ሰው ለማስተላለፍ የሁለቱም ተጋቢዎች ስምምነት ማስፈለጉ በቤተሰብ ሕጉ የተመለከተ ሲሆን ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢም ውሉ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ውሉ እንዲፈርስ ማድረግ የሚችል መሆኑን የቤተሰብ ሕጉ ደንግጐ እናገኘዋለን፡፡ የሕጉ መንፈስ ውሉ የአንደኛው ተጋቢ ስምምነት ሳይኖር በመደረጉ ብቻ ከጅምሩ ውጤት አልባ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የማይወስድ ነው፡፡ ይልቁንም ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ በሕጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ውሉ እንዲፈርስ እስካላደረገው ድረስ ውሉ ውጤት ይኖርዋል፡፡ በተያዘው ጉዳይም አመልካች ነጋዴ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ብድሩን ተጠሪ እያወቁ ለተወሰነ ጊዜ አብሮ ሲከፍሉ የነበረ፣ውሉን እንዲፈርስ ያላደረጉት መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

ብድሩ በትዳር ወቅት የተወሰደ ከሆነ ደግሞ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ ሕግ ግምት የሚወስድበት ሲሆን ለትዳር ጥቅም አለመዋሉን የማስረዳት ሸክም ያለባቸው ተጠሪ እንጂ አመልካች ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ስለሆነም የትግራይ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የበታች ፍርድ ቤቱ የብድር እዳው የጋራ ነው ሲሉ የሰጡትን ውሳኔ መሻሩ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ባግባቡ ከንግድ ሕጉ እና ከቤተሰብ ሕጉ መንፈስ ሳያገናዝብ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 30245 ጥቅምት 26 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ከዳሽን ባንክ እና ከማረት ማህበር የወሰዱት ብድር የጋራ እዳ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 49851

ሚያዝያ 4 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ታሪኳ አበበ የህፃን ሮቤል ንጉሤ ሞግዚት

**ተጠሪ**፡- የለም

መዝገቡን መርምርን የሚከተለውን ፍርድ ስጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ጥቅምት 16 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች የህፃን ሮቤል ንጉሤ ሞላ አያት የነበሩት ወ/ሮ ተስፋነሽ አምባነሽ ደስታ መስከረም 27 ቀን 2001 ዓ.ም ውልና ማስረጃ ቀርበው ሁለት ምስክሮች ባሉበትና በውልና ማስረጃ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ፊት በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01 የቤት ቁጥር 872 የሆነውን መኖሪያ ቤትና ሌሎች ንብረቶች በሙሉ በኑዛዜ መስጠታቸውን በመናዘዝ ህፃን ሮቤል ንጉሤ የኑዛዜ ወራሻቸው መሆኑን በማረጋገጥ ፈርመውበት ምስክሮችም ፈርመውበትና ባለሥልጣኑም ይህንን አረጋግጦ ኑዛዜውን መዝግቦ አንድ ኮፒ አስቀምጧል፡፡ አንድ ኮፒ በኑዛዜ ተጠቃሚ ተሰጥቷል ስለዚህ ህፃን ሮቤል ንጉሤ የሟች ወ/ሮ ተስፋነሽ አምባዬ ወራሽ መሆኑ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ሁለት ምስክሮች በማስቀረብ ሰምቷል፡፡ ሟች ውልና ማስረጃ ኑዛዜ ማድረጋቸውን መስክሯል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የኑዛዜ ሰነዱንና የምስክር ቃል ከመረመረ በኋላ ኑዛዜው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 የተደነገገውን ፎርም አላሟላም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የውልና ማስረጃ ባለሥልጣን በምስክርነት ስሙ ያልተጠቀሰና ያልተፈረመ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 የተደነገገውን መስፈርት አያሟላም፡፡ አመልካች ሟች ወ/ሮ ተስፋነሽ አምባዬ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስትር የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ መስከረም 27 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር 044/7/2001 ኑዛዜ ያደረጉ መሆናቸው በክፍሉ ባለሥልጣን ተረጋግጦና ተፈርሞ የተሰጠን ማስረጃ አለ፡፡ ኑዛዜው ውል ክፍል ውስጥ በሥራ ቀን ሁለት ምስክሮች ባሉበት የተደረገና ሟችና ምስክሮች የፈረሙበትና በውል ክፍል የሚመለከተው ባለሥልጣን ባለበት የተደረገ መሆኑ የተረጋገጠ ሆኖ እያለ ለፍትሐሔር ሕግ ቁጥር 882 የተዛባ የሕግ ትርጉም በመስጠት ኑዛዜው ዋጋ የለውም ተብሎ መወሰኑ የሟችን የኑዛዜ ቃል ዋጋ የሚያሣጣና የህፃኑን መብት ሚጐዳ

በመሆኑ የሕግ ትርጉም ስህተቱ በሰበር ታርሞ ኑዛዜው ዋጋ አለው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል በሥርም ሆነ በሰበር ደረጃ ተከራካሪ የሆነ ተጠሪ የለም፡፡

አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ፍርድ ቤቶቹ የሰጡት ውሣኔና አመልካች ያቀረበችው የሰበር አቤቱታ ይዘት ከላይ የተገለፀው ሲሆን መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ሟች ወ/ሮ ተስፋነሽ አምባነሽ መስከረም 27 ቀን 2001 ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ቀርበው ያደረጉት ኑዛዜ በሁለት ምስክሮች እና በውልና ማስረጃ ሰራተኛ ፊት የተደረገና ወዲያውኑ ሟችና ምስክሮች የፈረሙበትና የውልና ማስረጃ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ትክክለኛነትን በማረጋገጥ በጽ/ቤቱ ማህተም በማተምና በፊርማው በማረጋገጥ ያደረጉት መሆኑን በሥር ከቀረበው ክርክር ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህንን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 ድንጋጌ አንፃር መመዘን ያስፈልጋል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 "በግልጽ የሚደረገው ኑዛዜ ከምስክሮቹ መካከል አንዱ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሆኖ ኑዛዜውም የተደረገው ይህ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ሥራቸውን በሚያካሄድበት ክፍል ውስጥ የሆነ እንደሆነ ለኑዛዜው ዋጋ ለማግኘት ሁለት ምስክሮች ብቻ በቂ ናቸው"

የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ይህ ድንጋጌ ውል አዋዋይ ባለሥልጣኑ ስሙ በምስክርነት መገለጽ ያለበት መሆኑን እንደሚያስገድድ ኑዛዜው የተደረገው በውል አዋዋይ ባለሥልጣን ፊት ቢሆንም ባለሥልጣኑ በምስክሮች ስም ዝርዝር ስሙ ካልተገለፀ የሕጉን ፎርም ኑዛዜው አያሟላም ኑዛዜው ህጋዊ ውጤት አይኖረውም የሚል ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ይህ አተረጓጎም የህጉን መንስፈና አላማ የሚያሣካ ውጤታማ አተረጓጎም አይደለም፡፡ በቀረበው የኑዛዜ ማስረጃ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ያለው ባለሥልጣን ፊት የተደረገ፣ኑዛዜው ከተነበበ በኂላ ሁለቱ ምስክሮችና ሟች እንደፈረሙበት ይህ ሁሉ ተግባር በፊቱ ሲከናወን ጠቅላላ ሂደቱን የተከታተለው ውል ለማዋዋል ሥልጣን ያለው ባለሥልጣን ሂደቱ በአግባቡ የተፈፀመ መሆኑን በፊርማው በማረጋገጥና ማህተም በመምታትና ቁጥር በመስጠት አንድ ኮፒ ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በማስቀረት ቀሪውን ለሟች እንደሰጠ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ይህ መስፈርት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 የተደነገገውን ፎርም የሚያሟላና ህጉ ኑዛዜው የሟች እርግጠኛ የመጨረሻ ቃል መሆኑን ለማረጋገጥ የደነገገውን መስፈርት የሚያሟላ ነው፡፡ ስለዚህ አጠቃላይ ኑዛዜው የተደረገው ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው ባለሥልጣን ፊት መደረጉን በማረጋገጥ በመሥሪያ ቤቱ ማህተምና ፊርማ የተረጋገጠ ከሆነ የባለሥልጣኑ ስም በምስክሮች ፊት ስም ዝርዝር ውስጥ መጠቀሱ የግድ አስፈላጊ አይደለም፡፡ የባለሥልጣኑ ስም መገለጽ የሚያስፈልገው ከእሱ ውጭ ሌላ አንድ ምስክር ብቻ ከኖረ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ውል አዋዋይ ባለሥልጣኑ ውጭ ሌሎች ሁለት ምስክሮች ያሉ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 የሰጠው ትርጉም የሕጉን መንፈስና አጠቃላይ ግብ መሰረት ያላደረገና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ሟች ወ/ሮ ተስፋነሽ አምባዬ ደስታ መስከረም 27 ቀን 2001 ዓ.ም በህፃን ሮቤል ንጉሤ ሞላ ያደረጉት ኑዛዜ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 የተደነገገውን መስፈርት የሚያሟላና ሕጋዊ ውጤት ያለው ኑዛዜ ነው ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 43069

ሚያዝያ 6 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ አማረ ረታ - ወ/መላኩ ረታ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሰለሞን ካሣዬ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የኑዛዜ ወራሽ እና ያለኑዛዜ ወራሽ የሟች ንብረት ይካፈሉ ሲል የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ትርጉም ስሕተት የተፈፀመበት ነው ሲል አመልካች አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የአሁን አመልካች ሟች አቶ ካሣዬ ክፈተው ግንቦት 23 ቀን 1992 ዓ.ም ያደረጉትን የኑዛዜ ስጦታ መሠረት በማድረግ በአቃቂ ክ/ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኝ መኖሪያ ቤት ይዞ ያለ ሲሆን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት የሟች ወራሽ መሆናቸውን ጠቅሰው አመልካች ቤቱን እንዲለቅላቸው ዳኝነት ጠይቀው ነበር፡፡ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ሟች ተወላጅ እያላቸው ከውርስ የነቀሉ ስለመሆኑም በቂ ምክንያት ሳይሰጡ ያላቸውን ንብረት ለአመልካች በኑዛዜ ማስተላለፋቸውን ጠቅሶ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 939/3/ መሠረት በኑዛዜ ወራሽ እና ያለኑዛዜ ወራሾች ንብረቱን እኩል ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቀርቦለት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ አፅንቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል በማለት ታህሳስ 9/2001 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የሰበር አቤቱታው ይዘት ባጭሩ ለአመልካች በኑዛዜ የተሰጠው የሟች ጠቅላላ ንብረት ሳይሆን አንድ መኖሪያ ቤት ብቻ ነው በሚል የሥር ፍ/ቤት የጠቅላላ የውርስ ስጦታ ነው በሚል የፍ/ብ/ህግ ቁ 939/3/ ያለአግባብ ትርጉም ሰጥቷል በማለት እንዲታረም ጠይቋል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ በሟች የተሰጠውን ኑዛዜ የሥር ፍ/ቤቶች በማለፍ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁ. 939 እና 852 መሠረት መወሰናቸው በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ ተጠሪም ነሐሴ 15 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት መልስ ያለኑዛዜ ወራሾች በሕጉ አግባብ ከውርስ ያልተነቀሉ ስለመሆኑና ሟችም ከተጠቀሰው ቤት ሌላ ንብረት የሌላቸው መሆኑን ጠቅሶ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቋል፡፡

እኛም ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር መሠረት አድርገን ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው አመልካች በኑዛዜ የተሰጠውን ቤት ለብቻው ለመውሰድ የሚከራከር ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የሟች ያለኑዛዜ ወራሽ መሆኑን ጠቅሶ ከኑዛዜው ተጠቃሚ ጋር በሥር ፍ/ቤት በተወሰነው አግባብ ለመካፈል እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

በዚህ ፍ/ቤት ውሳኔ የሚያሻው ጉዳይ ሟች ለአመልካች ያደረጉት የኑዛዜ ስጦታ የጠቅላላ ውርስ(ስጦታ) ወይንስ ተለይቶ የታወቀ ንብረት ስጦታ ተብሎ ሊወሰድ ይገባል የሚለው መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች አንድ መኖሪያ ቤት ብቻ ነው በኑዛዜ የተሰጠኝ ሲል ተጠሪ ደግሞ ሟች ከዚህ ቤት ሌላ ንብረትም የላቸውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ይህንን መሠረታዊ ጉዳይ ለመፍታት የኑዛዜ ሰነዱን አጠቃላይ ይዘት ማየት ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ሟች ካሣዬ ክፈተው ግንቦት 23 ቀን 1992 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ እንደሚያመለክተው የወለዷቸው ልጆች እንዳልጠየቋቸው ጠቅሰው ያላቸውን ቤት ከነጣሪያው ከነግድግዳው ከነአፈሩ ለክርስትና ልጃቸው ለአማረ ረታ የተናዘዙ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ቤት ውስጥ ያለ እቃ የኔነው ያለችውን ሚስት እንድትወስድ እንዲሁም በመንግሥት ተወርሷል የተባለ አንድ ክፍል ቤት ለሚስት ወ/ሮ እናት መንግሥቱ መስጠታቸውን ነው፡፡ ሚስት በሕይወት እስካለች ተጠቅማ በኋላ ለአቶ አማረ ረታ እንድታስረክብ የሚል ሀሳብ ተጨምሮ ይገኛል፡፡

እንግዲህ ከዚህ የኑዛዜ ሰነድ ይዘት መረዳት የሚቻለው ሟች አለኝ ያሉትን ንብረት ጠቅሰው የተናዘዙ ስለመሆኑ ነው፡፡ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 911(1) እንደተደነገገው የሟች ተወላጆች እንዳያገኙ በማሰብ ያለውን ንብረት አጠቃሎ ለኑዛዜ ተጠቃሚ ስጦታ ያደረገ መሆኑ ሲታይ ሟች ያለውን ንብረት አጠቃላይ ያስተላለፈ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ መልክ ያለውን ንብረት ዘርዝሮ ጠቅላላ በኑዛዜ ስጦታ ያስተላለፈ እንደሆነ ደግሞ ኑዛዜው ጠቅላላ ኑዛዜ ሊባል እንደሚችል ከፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 912(1) መረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም አመልካች የጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚ ነው በሚል በሥር ፍ/ቤት የተደረሰው ድምዳሜ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት አለው ሊባል የሚችልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡

አመልካች የሟች ተወላጅ (ያለኑዛዜ ወራሽ) አለመሆኑ አላከራከረም፡፡ አመልካች በጠቅላላ ኑዛዜ የሟች ሀብት በስጦታ የተላለፈለት መሆኑ ከተረጋገጠ በሌላ በኩል ሟች ተወላጆቹን (ያለኑዛዜ) ወራሾችን ከውርስ የነቀለበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ መሆኑ ሲገናዘብ በዚህ ንብረት ላይ በኑዛዜ ወራሽ እና ያለ ኑዛዜ ወራሾች መካከል የሚኖረው መብት ምን ሊሆን ይገባል የሚለው ጥያቄ አስመልክቶ የሥር ፍ/ቤቶች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 939/3/ መሠረት መወሰናቸው ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ወደዚህ ድምዳሜ ለመድረስ የሚቻለው በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 915/1/ የተመለከተው ሁኔታ ተሟልቶ ሲገኝ እንደሆነ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አመልካች በኑዛዜ ጠቅላላ ስጦታ የተሰጠው ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ያለኑዛዜ የመጀመሪያ ደረጃ የሟች ወራሽ ነው፡፡ ይህ ከተሟላ ስለክፍፍሉ ሥርዓት የሚወሰነው ደግሞ መርሁ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 939/3/ ይሆናል፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ይህንኑ የህጉን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ተከትሎ የሰጡት ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሊያሰኝ የሚያስችል ምክንያት የለውም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ባለበት ሊፀና ይገባል ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 09965 ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 68488 የሰጠው ፍርድ ፀንቷል፡፡

ግራቀኙ በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገው ክርክር የየራሳቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 52691

ሚያዝያ 22 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ኂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አብዱራሂም አህመድ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** 1. ቤተዛታ ችልድረንስ ሆም አሶሴሽን

2. ሚስተር ማይክል አለን ዳቮልት

3. ሚስ ዴቪስ አን ኸርናዴዝ

} ጠ/ስለሺ ዘዮሐንስ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** የለም

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የጉዲፈቻ ውል ይፍረስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ አመልካቾች ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በጉዲፈቻ የተወሰደው ልጅ ከውሳኔ በኋላ ሲመረመር የአእምሮ እድገት ዝግመት ያለበት መሆኑ ስለተረጋገጠ የጉዲፈቻ አድራጊዎቹ በዚህ ምክንያት ልጁን ሊቀበሉ ስላልቻሉ ውሳኔው ይሰረዝልን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን አይቶ የጉዲፈቻ ውል በመርህ ደረጃ ሊፈርስ እንደማይችል በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 195/1/ ስር የተቀመጠ ሲሆን በንኡስ አንቀጽ 2 ስር ደግሞ የጉዲፈቻ ውል ሊፈርስ የሚችልበት ልዩ ሁኔታ መስፈሩን፣በዚህ መሰረት ውሉ ሊፈርስ የሚችለው የጉዲፈቻ ውል ተቀባዩ የጉዲፈቻ ልጅን እንደልጁ በማሳደግ ፋንታ የልጁን የወደፊት ህይወት በሚጐዳ አኳኋን ሲይዘው እንደሆነ፣በተያዘው ጉዳይ ግን ውል እንዲፈረስ የቀረበው ምክንያት ውሉን ለማፍረስ የሚያስችል አለመሆኑን ተችቶ ጥያቄውን ውድቅ አድርጐታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካቾች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች በቅሬታቸው ጉዲፈቻ የተደረገው ልጅ በሽታ ያለበት መሆኑ የተረጋገጠው ስምምነቱ ከፀደቀ በኋላ ስለሆነና ጉዲፈቻ አድራጊዎቹ የዚህ አይነት ችግር መኖሩን ቢያውቁ ህፃኑን መረከብ እንደማይችሉ፣ልጁን እንዲረከቡ ቢገደዱ የልጁን ጤንነት የሚጠይቀውን ወጪ ለማውጣት አቅማቸው የማይፈቅድ በመሆኑ የልጁ የወደፊት ህይወት ባያሌው የሚጐዳ መሆኑን ገልፀው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የቤተሰብ ሕጉን አንቀጽ 195/2/ በአግባቡ ያላገናዘቡ ስለሆነ ውሉ እንዲፈርስ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 36/1/ ስር ከተደነገገው የህፃናትን ጥቅም ማስጠበቅ (best interest of the child) መርህ አኳያ ተገቢነቱን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርገናል፡፡ መዝገቡንም እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 195/1/ በመርህ ደረጃ የጉዲፈቻ ውል ሊፈርስ እንደማይችል ያስቀምጥና በንኡስ ቁጥር 2 ስር ደግሞ ውሉ ሊፈርስ የሚችልባቸውን ልዩ ሁኔታዎች ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት ውሉ እንዲፈርስ የሚደረገው ጉዳፈቻ አድራጊው በጉዲፈቻ የተቀበለውን ልጅ እንደ ልጁ በማሳደግ ፋንታ በባርነት ወይም ባርነት በሚመስል ሁኔታ ወይም ከግብረ-ገብ ውጪ በሆኑ ተግባሮች እንዲሰማሩ በማድረግ መጠቀሚያ ያደረገው እንደሆነ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የልጁን የወደፊት ሕይወት ክፉኛ በሚጐዳ አኳኋን የያዘው መሆኑን የተረዳን እንደሆነ ነው፡፡ በመሆኑም ውሉ በተለይ "በማንኛውም ሌላ መንገድ የልጁን የወደፊት ሕይወት ክፉኛ በሚጐዳው አኳኋን የያዘው" የሚለው ትርጉም የሚያስፈልገው ሲሆን ይህ ችሎት ድንጋጌው እንዴት መተርጐም እንዳለበት በመ/ቁ. 44101 ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በዚህም መሰረትም ይህ ድንጋጌ የተቀመጠውም ጉዲፈቻ አድራጊው ልጅን በዓለም አቀፍ የሕፃናት እና ሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን በሚፃረርና የልጁን ጥቅምና ደህንነት በሚጐዳ አኳኋን መያዙን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የጉዲፈቻ ውሉ እንዲቀጥል ማድረጉ የሚያስገኘው ፋይዳ ባለመኖሩ ጉዳዩ በሚመለከተው ማንኛውም አመልካች ጠያቂነት መሰረዝ እንዲችል ታምኖበት መሆኑን የተሻሻው የቤተሰብ ሕግ ሃተታዘምክንያት ማመልከቱን፣ጉዲፈቻ እንዲደረግና የሕግ ጥበቃ እንዲደረግለት ያስፈለገው በዋናነት የሕፃኑን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል እንደሆነ፣የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትም ሆነ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው አለም ዓቀፍ ስምምነቶች ህፃናትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ለሕፃናት ጥቅም ደህንነት (best interest of the child) ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ መሆኑ በመርህ ደረጃ ማስቀመጣቸውን፣በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 36/5/ ስር መንግስት ለእጓለማውታን ልዩ ጥበቃ እንደሚያደርግላቸው፣በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ስርአት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋማች እንዲመሰረቱ እንደሚያበረታታ መደንገጉን፣ከፍ ሲል የተመለቱት ድንጋጌዎች ሁሉ የጉዲፈቻ ጉዳይ በጥንቃቄ መታየት ያለበት መሆኑንና በድንጋጌ አተረጓጉም ላይ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ፣በዚህም መሰረት የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲሰረዝ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው በልጁ አኗኗርና አያያዝ እንዲሁም ወደፊት ሕይወቱ ላይ በተጨባጭ የደረሰ ጉዳት በመኖሩ ብቻ ሳይሆን ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳት ስለመኖሩም ማርጋገጥ ሲቻል እንደሆነ የሕግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች የጉዲፈቻ ስምምነቱ እንዲሰረዝ ጥያቄ ያቀረቡት ስምምነቱ ከተደረገና በፍ/ቤት ከፀደቀ በኂላ ልጁ ሲመረመር የአእምሮ እድገት ዝግመት ያለበት መሆኑ በሃኪም በመረጋገጡ ነው፡፡ አመልካቾች በአቤቱታቸው በጉዲፈቻ ለመቀበል የሚችሉት ጤነኛ ልጅ መሆኑና በጉዲፈቻ የተቀበሉት ልጅ ካለበት የጤና ችግር አኳያ ለአስተዳደጉና ለጤንነቱ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ወጪዎችን ለመሸፈን የገንዘብ አቅም የሌላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከዚህም የአመልካቾች አቤቱታ መረዳት የሚቻለው ጉዲፈቻ አድራጊዎቹ በጉዲፈቻ የተቀበሉት ልጅ ካለበት የአእምሮ ዝግመት ችግር አኳያ ልዩ እንክብካቤ እና አያያዝ እንዲሁም ክትትል የሚያስፈልገው ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ የጉዲፈቻ አድራጊዎቹ አቅም ያላቸው ለመሆኑና ወጪውንም ለማውጣት ፈቅደው ስምምነቱን ያደረጉ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ በተቃራኒው ጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ልጁን እንዲወስዱ ቢገደዱ በልጁ የወደፊት ሕይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊደርስ እንደሚችል እየገለፁ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ደግሞ ጉዲፈቻ እንዲደረግ የሚፈቅደውና የሕግ ጥበቃ የሚደረግለት ዋነኛ አላማ የህፃናቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ነው፡፡ የጉዲፈቻ ውሉ እንዲቀጥል ማድረጉ የሕፃኑን የወደፊት ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑ ከወዲሁ ከተረጋገጠ ውሉ ሊሰረዝ ይገባል፡፡ ሕጉም ውሉ እንዲፈርስ የሚፈቅደው ወደፊት ልጁ ላይ በተጨባጭ ጉዳት መድረሱ ሲረጋገጥ ብቻ አይደለም፡፡ ጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ልጁን ወስደው ለማሳደግ የማይችሉ መሆኑንና እንዲወስዱ ቢገደዱ እንኳን ወደፊት ህይወቱ ላይ ከፍተኛ ችግር እንደሚከተል መግለፃቸው ሲታይ ውሉ እንዲቀጥል ማድረጉ የልጁን ጥቅም ከማስጠበቅ ይልቅ ህይወቱን አደጋ ላይ መጣል መሆኑን መገንዘብ ስለሚቻል ውሉ አይፈርስም ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ከፍ ሲል የተመለከቱት የሕግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 136357 ግንቦት 3 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 82881 ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ፀንቷል፡፡

2. ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ህፃን ፊጠነን በጉዲፈቻ ልጅነት ለመቀበል ታህሣሥ 28 ቀን 2001 ዓ.ም ያደረጉትና በፍ/ቤት መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም የፀደቀው የጉዲፈቻ ውል ተሰርዟል፡፡ ይህንኑ አውቆ ተገቢውን እንዲፈጽም የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 53279

ሰኔ 08 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ትዕግስት ግርማ የእነ አቤል ወርቁ ሞግዚት - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ኤፍሬም መንግስቱ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኑዛዜ ወራሽነት ይረጋገጥልኝን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክር የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ የስር አቤቱታ ይዘት ሲታይም መስከረም 14 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ ሆኖ ሟች ወ/ሮ ውዴ ሙሉጌታ መስከረም 18 ቀን 1995 ዓ.ም ኑዛዜ ለምዕራፍ ሰለሞን ያደረጉት ስለሆነ ልጅቱ የሟች ኑዛዜ ወራሽ መሆኗና የእኔም ሞግዚትነት ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጠኝ የሚል ነው፡፡ ምስክሮቻቸውን አቅርበውም እንደአቤቱታቸው ይዘት አስመስክረዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኗ አመልካች በተቃዋሚነት ቀርበው ሟች ወ/ሮ ውዴ ሙሉጌታ የአሁኗ አመልካች ሞግዚት የሆኑላቸው እናት መሆናቸውን አድርገውታል የተባለው ኑዛዜም ሟች ማንበብና መፃፍ የሚችሉ በብዕር መፈረም የሚችሉ ሆነው እያለ በጣት የተፈረመ መሆኑ ሐሰተኛ መሆኑን እንደሚያሳይ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የሟች አለመሆኑን ሟች በጣም ታመው መናገርና መንቀሳቀስ የማይችሉ በመሆኑ ከመሞታቸው አንድ ቀን በፊት አድርገውታል የተባለው ኑዛዜ የሟች ሊሆን እንደማይችል ኑዛዜው በሕጉ መሠረት ስለመነበቡም የሚገልፀው ነገር ስለሌለ መሆኑን ገልፀው ኑዛዜ ፈራሽ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የሟች መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለባቸው ተጠሪ ሲሆኑ ሟች በጣታቸው የፈረሟቸውን ሌሎች ተመሳሳይ ፊርማዎችን አቅርበው በባለሙያ ሊረጋገጥ አልተቻለም በተጨማሪም ሟች በብዕር ይፈርሙ እንደነበርና ኑዛዜውንም ያደረጉት ከመመታቸው በፊት አንድ ቀን ሲቀራቸው ነው የሚሉትን ምክንያትቶችን በመያዝ ኑዛዜው ሟች ያደረጉት ነው ለማለት አስቸጋሪ ነው ብሎ ኑዛዜው ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ኑዛዜው ትክክል አይደለም የሚለው ወገን ይህንኑ ማስረዳት ግዴታ አለበት የአሁኗ አመልካች ግን ይህንኑ አልተወጡም የሚል ምክንያት በመያዝ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮ ኑዛዜው ህጋዊ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር ሰሚ

ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ፀንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 22 ቀን 2002ዓ.ም በፃፉት ሶስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ በኑዛዜው ላይ የሰፈረው ፊርማ የሟች ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም የኑዛዜው ተጠቃሚ የሆነ ሰው ሆኖ እያለ ይህው ታልፎ ኑዛዜው ሕጋዊ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም አከራካሪው የጣት አሻራ የሟች /የተናዛዥ/ መሆኑን በተመለከተ የማስረዳት ሸክሙ ላይ ያለውን ክርክር ለማየት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ቀርበው ሰኔ 07 ቀን 2002ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ በመንቀፍና በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ተገቢነት በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ቢሆንም በኑዛዜው ላይ የጣት ፊርማ ማስቀመጣቸውን ነው፡፡

በመሰረቱ የኑዛዜውን ቃልና ይዘት አስመልክቶ ማን ማስረዳት እንዳለበትና ምን አይነት ማስረጃዎች ማቅረብ እንደሚገባው በውርስ ሕግ ውስጥ ልዩ ድንጋጌዎች ተቀምጠው እናገኛለን፡፡ በዚህም መሠረት አንድ የኑዛዜ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ሟች በሕይወት ዘመኑ ለእሱ ጥቅም ያደረገው ኑዛዜ መኖሩንና የኑዛዜው ቃልና ይዘትምን እንደሆነ የማስረዳት ሸክም ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 896 በግልጽ ያሳያል ይህ ድንጋጌ በግልጽ የሚያሳየው በኑዛዜው ሰነድ ላይ የሰፈረው ቃል እና ኑዛዜ መኖሩን ማስረዳት ያለበት የኑዛዜው ተጠቃሚ ነኝ የሚለው ሰው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የሟች የኑዛዜ ወራሽ እና ተጠቃሚ ነኝ የሚል ሰው ሟች በህግ ፊት ውጤት ያለውን ኑዛዜ የፈፀመ መሆኑን የኑዛዜውን ቃልና ይዘት እንደዚሁም እሱ እራሱ በሟች ኑዛዜ መሠረት ተጠቃሚ መሆኑን የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ ህጉ ለምን አይነት ኑዛዜ ምን አይነት ማስረጃ መቅረብ እንዳለበትም በግልጽ ማስቀመጡ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 897 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ሞግዚት የሆኑላቸው ልጆች የሟች ወራሾች ሲሆኑ ተጠሪ ሞግዚት ለሆኑላት ልጅ የተደረገው ኑዛዜ የተቃወሙት ሟች በብዕር የሚፈርሙ እንጂ በጣት አሻራ የሚፈርሙ አይደሉም በማለት ነው፡፡ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ተጠሪ ሞግዚት የሆኑላት ልጅ የኑዛዜው ተጠቃሚና የኑዛዜው ወራሽ ነኝ የምትል በመሆኑ ሟች የጣት አሻራ በሌሎች ጉዳዩች ይፈርሙ የነበረ ስለመሆኑ እንዲያስረዱ ትዕዛዝ ሰጥቶ ይህንኑ ሊፈጽሙ ባለመቻላቸው ኑዛዜው አይፀናም ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ችሎት በሰጡት መልስም የጣት አሻራው የተፈረመው በአራት ሽማግሌዎች ፊት ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የጣት አሻራው የሟች ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም የአመልካች ነው ከሚሉ በስተቀር ሟች በሌሎች ጉዳዮች በጣት አሻራ ይፈርሙ የነበረ መሆኑን ወይም ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሆነው እያለ በጣት አሻራ ሊፈርሙ የቻሉበትን አሳማኝ ምክንያት በስር ፍ/ቤት ያረጋገጡ መሆኑን ገልፀው አልተከራከሩም፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ባቀረቧቸው ማስረጃዎች ሟች በብዕር ሲፈርሙ የነበሩ ማንበብና መፃፍ ይችሉ የነበሩ መሆኑን በሚገባ ያስረዱ ስለመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ በግልጽ ያሳያል፡፡ እንግዲህ አመልካች ሟች በብዕር መፈረም ይችሉ የነበሩ መሆኑን ከማስረዳት እና በኑዛዜው ሰነድ ላይ የሰፈረው የጣት አሻራ የሟች አይደለም በማለት መከራከር ብቻ በቂ ሲሆን ይህንኑ የማስተባበል ግዴታ ያለባቸው የኑዛዜው ተጠቃሚ የሆኑት ተጠሪ ሞግዚት የሆኑላት ልጅ ነች፡፡ ተጠሪ ደግሞ የኑዛዜ ተጠቃሚ የሆኑትን ልጅ ወክለው ባቀረቡት ክርክር በኑዛዜው ሰነድ ላይ ያለውን የጣት ፊርማ የሟች ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 896 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ በሚያስገነዝበው ሁኔታ አላስረዱም፡፡ በመሆኑም የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሻረውም ሆነ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምጽ ያፀናው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 896 ድንጋጌ መንፈስ ውጭ በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 03848 ሰጥቶ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 07225 ጥር 07 ቀን 2002ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 350/97 ጥቅምት 08 ቀን 1999ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

የሰ/መ/ቁ. 50901

ሰኔ 10 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐ□ስ □ል□

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

□ሊ መሐመ□

***አመልካች፡-*** □/ሮ □ል□ ኃይሌ ጠ/መስፍን አድሴ - ቀረቡ

***ተ□ሪዎች፡-*** □ነ ወ/ሮ ትዕግሥት ደበሌ /3 ሰዎች/ - አልቀረቡም

*መዝገቡን መርምረን ተከ□□ን ፍርድ ሰጥተናል፡፡*

**□ ር □**

*በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የውርስ ንብረት ክፍፍል የሚመለከት ነው፡፡ ሥር ፍ/ቤት ተጠሪዎች ከሳሽ አመልካች ተከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ የሚች አባ□ቸው ሀብት ነው ያሉትን የቤት ቁጥር 190/02 የሆነውን ቤት ከሶስት ክፍል ሰርቪስ ጋር ግምቱ ብር 70,000 /ሰባ ሺህ/፣ ሁለት የልብት ስፌት መኪና □ምቱ ብር 4,000 /አራት ሺህ/ እና ሌሎች የቤት እቃዎች በድምሩ ብር 83,190.00 /ሰማንያ ሶስት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ብር/ ግምት ያለው ንብረት ግማሽ ድርሻ አመልካች እንድታካፍላቸው እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቀዋል አመልካች ሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት መልስ ተጠቃሹ ቤት የልብስ ስፌት መኪና እና ቴሌቪዥን ሟች ታህሣሥ 25 ቀን 1998 ዓ.ም ባደረገው ኑዛዜ አመልካች በሕይወት □ስካለች እንድትጠቀም ከ□□ም በኃላ ከሁለቱ ለተወለደችው ለአየለች ደበሌ እንዲሰጥ የተናዘዘ ስለመሆኑ ገልፀው ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡*

*የወረዳው ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ሟች ታህሣሥ 25 ቀን 1998 ዓ.ም አድርጓል የተባለው ኑዛዜ የተከሣሾችን /ተጠሪዎችን/ ጥቅም የሚጐዳ እና እነሱ በሌሉበት የተደረገ መሆኑን ጠቅሶ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 872 ምርኩዝ በማድረግ ኑዛዜው ቀሪ ሆኖ ንብረቶቹ □ንዲከፋፈሉ ወስኗል፡፡*

*ይግባኝ የቀረበለት የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ኑዛዜው የወራሾችን የመውረስ መብት የተከለከለበት ምክንያት የማይገልፅ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤት ኑዛዜው እንዲፈርስ መወሰኑ በአግባቡ ነው ሲል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አፅንቷል፡፡*

*□ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎትም የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ የሕግ ስሕተት የለውም ሲል አቤቱታውን ውድቅ አድርጓል፡፡*

*ለዚህ ሰበር የቀረበው አቤቱታ በዚህ ላይ ነው፡፡*

*□ህሣሥ 1 ቀን 2002 ዓ.ም ተፅፎ የቀረበው አቤቱ□ ባ□ ሩ ተጠሪዎች ንብረት ለመካፈል እንጂ ኑዛዜ ለማስፈረስ ክስ ሳያቀርቡ የሥር ፍ/ቤቶች ከተጠየቀው ዳኝነት ውጪ ስለመወሰናቸው ተጠሪዎች የውርስ ንብረት ይጣራ ጥያቄ ሳያቀርቡ ንብረት መጠየቃቸው አለአግባብ ስለመሆኑ ኑዛዜው በፍርድ ቤቶቹ እንዲፈርስ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 875 መንፈስ የወጣ ስለመሆኑ እና ንብረቶቹ በአግባቡ ሳይጣሩ □ማሽ እንዲካፈል መወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት ወሣኔው እንዲሻር አመልክተዋል፡፡*

*ይህ ሰበር ችሎትም ኑዛዜው ዋጋ አልባ ነው ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተጠሪዎችን አስቀርቧል፡፡ ተጠሪዎችም የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ቀርበው ክርክራቸውን አሰምተዋል በክርክራቸውም ኑዛዜው የተደረገላቸው መሆኑን ያወቁት በክስ ሂደት ስለመሆኑ ለእነሱ ተሰጠ የተባለው ቤት በመንግሥት የተወረሰ በእጃቸው የሌለ ስለመሆኑ እና ብር 200(ሁለት መቶ) ብቻ ለእያንዳቸው ተከፍሎ ንብረቱ ለአንደኛዋ ልጃቸው ብቻ እንዲሆን መደረጉ አለአግባብ መብታቸውን የሚጐዳ ስለመሆኑ ዘርዝረው የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፀና አመልክተዋል፡፡*

*□ኛም □□ራ ቀኙን ክርክር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል በዚህ ችሎት እልባት የሚያሻው ጉዳይ ኑዛዜው ዋጋ አልባ ነው ሲሉ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ስለመሆኑ ኑዛዜው በሕግ አግባብ የተደረገ ነው ከተባለ ሕጋዊ ወጤቱ ምን ሊሆን ይገባል የሚል እና ተያያዥ ነጥቦችን እንደሚከተለው አንድ በአንድ ተመልክተናል፡፡*

*የአመልካች ባለቤት እና የተጠሪዎች ወላጅ አባት የሆኑት ሟች አቶ ደበሌ ሮቤ ታህሣሥ 25 ቀን 1998 ዓ.ም ያደረጉት ግልፅ ኑዛዜ በተናዛዡ እና በምስክሮች ፊት የተደረገ እና የተፈረመ ስለመሆኑ እና በውልና የክብር መዝገብ አገልግሎት ጽ/ቤት የተረጋገጠ ስለመሆኑ ሰነዱ ያመለክታል፡፡ ግልፅ ኑዛዜ ማሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881 የተደነገገውን መስፈርት ያሟላ ስለመሆኑ ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ካለው የኑዛዜ ሰነድ መረዳት ችለናል፡፡*

*ስለሆነም የወረዳው ፍ/ቤት ኑዛዜው ሲደረግ ተጠሪዎች በቦታው አልነበሩም በሚልና ከፍተኛው ፍ/ቤት ኑዛዜው ወራሾች ባሉበት ስለመነበቡ አልተገለፀም በሚል ሰነዱ በሕግ የተመለከተውን ፎርማሊቲ አላሟላም ከሚል መደምደሚያ መድረሳቸው በሕጉ ያልተመለከተን መስፈርት መሠረት ያደረጉ ስለሆነ ድምዳሜው ስህተት ነው እንላለን፡፡*

*የኑዛዜው ሰነድ በፎርማሊቲ ረገድ ጉድለት የለበትም፡፡*

*የኑዛዜው ሰነድ በፎርማሊቲ ረገድ ጉድለት የሌለበት ነው ከተባለ በይዘት ረገድ ያለውን ውጤት እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡*

*ከኑዛዜው ይዘት መረዳት የሚቻለው ሟች ከአመልካች ጋር ካፈሯቸው ንብረቶች ውስጥ በሣጉሬ ከተማ ቀበሌ 02 የሚገኝ የቤት ቁጥር 120/02 የሆነውን መኖሪያ ቤት እና የቤት ቁሳቁስ ድርሻቸውን አመልካች እስከ ሕልፈተ ሕይወቷ እንድትጠቀም በኃላም ለልጃቸው ለወ/ሮ አየለች ደበሌ ሮቢ የግል ንብረት እንዲሆን በሚል ወስኗል፡፡ እንዲሁም ወ/ሮ አየለች ደበሌ ለሌሎቹ ወራሾች /ተጠሪዎችን ጨምሮ አምስት የሚች ተወላጆች/ ለሆኑት ለእያንዳንዳቸው ብር 200 /ሁለት መቶ/ እንድትሰጥ በኑዘዜው አዟል፡፡ ከዚህም ሌላ በሳጉሬ ከተማ የሚገኝ በመንግስት በአዋጅ የተወረሰ ቤት የሚከፈለውን አበል አመልካች እንድትጠቀም ሆኖ ቤቱ የሚመለስ ከሆነ ተጠሪዎች እንዲካፋፈሉት 14 ኢንች ቴሌቪዥን እና የልብስ ስፌት መኪና በገንዘቧ የገዛቸው ወ/ሮ አየለች ደበሌ መሆኗን ገልፆ የግል ንብረት እንዲሆን ተናዟል፡፡*

*ከዚህ ሰነድ ባጠቃላይ መረዳት የሚቻለው በእጃቸው ያለውን ቤት እና በመንግሥት ተወርሶ አበል የሚከፈልበትን ቤት አበሉን አመልካች እስከ ሕልፈተ ሕይወቷ እንድትጠቀም ተናዛዡ መፍቀዱን ከዚያ በ□ላ በ□□ ያለው ቤትና የቤት ቁሳቁስ የልብስ ስፌት መኪና እና ቴሌቪዥን የወ/ሮ አየለች ደበሌ የግል ንብረት እንዲሆን ሌሎቹ ወራሾች ደግሞ ሁለት መቶ ብር እና በመንግስት እጅ ያለ ቤት ሲመለስ እንዲከፋፈሉ የሚል ማድረጋቸው ነው፡፡*

*□ንግዲህ በዚህ የኑዛዜ ሰነድ ላይ የተጠቀሱት የኑዛዜው ተጠቃሚዎች ከአመልካች በስተቀር ሌሎቹ የሟች ተወላጆች መሆናቸው ግራቀኙን አላከራከረም፡፡*

አመልካች እስከ ሕይወት እንድትጠቀም የሚል በመሆኑ ንብረቱን በማከፋፈል ረገድ ኑዛዜው የተለየ ጥቅም አላስጣትም ተወላጆቹ መካከል ግን ክፍፍል ያደረገ ስለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ መታየት ያለበት ጉዳይ ለተወላጆቹ የተሰጠ ኑዛዜ በሕጉ ምን ውጤት አለው የሚለው ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ሟቹ በኑዛዜው ለተወላጆቹ የንብረት ክፍፍል አድርጓል፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 913 እንደተደነገገው የተናዛዡ ተቃራኒ ሃሳብ በግልፅ አልተመለከተም አንድን የውርስ ሀብት ለተወላጅ መስጠቱ የክፍያ ደንብ እንጂ የኑዛዜ ስጦታ ተብሎ እንደማይቆጠር ተመልክቷል፡፡ ይህም ማለት ሟቹ በኑዛዜው ንብረቶቹን ለወራሾቹም መደላደል እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡ ነገር ግን በድልድል አፈፃፀም ላይ ሌላኛው ተወላጅ ወራሽ መብት ከሩብ የበለጠ ጉዳት የሚደርስበት እንደሆነ □ስፌታ አከፋፈል እንዲቀር ለመጠየቅ እንደሚችል የፍ/ብ/ሕ ቁጥር 1123/1/ ይደነግጋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ሟች ታህሣሥ 25/1998 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ በሳጉሬ ከተማ ቀበሌ 02 ቁጥር 120/02 የሆነውን ቤት ባለሀብትነት መብት ለወ/ሮ አየለች ደበሌ ብቻ እንዲሆን ተናዟል፡፡ ለተቀሩት ተወላጆች ብር 200.00(ሁለት መቶ) እንዲከፈላቸው እና በመንግሥት እጅ ያለ ቤት የሚመለስ ከሆነ ብቻ እንዲከፋፈሉ አድርገዋል፡፡

ስለሆነም ኑዛዜውን መሠረት አድርጎ ክፍፍሉ በተወላጆች መካከል ሲደረግ ከሩብ ያላነሰ ጉዳት □□ርስባቸዋል የሚያሰኝ ሆኖ ሲገኝ በኑዛዜው መሠረት እንዳይፈጸም ተጠሪዎች መቃወም የሚችሉ ከሚሆን በስተቀር ከወዲሁ ኑዛዜው የተጠሪዎችን መብት የሚጎዳ ነው በሚል የሥር ፍ/ቤት ኑዛዜውን ሙሉ በሙሉ ማፍረሱ ተገቢ አይደለም፡፡

ስለዚህ በወራሾች መካከል በተደረገ የውርስ ንብረት ክፍፍል አፈፃፀም ላይ በገንዘብ ወይም በአይነት ማስተካከል የሚቻል በሆነ ጊዜ ኑዛዜውን በተናዣዥ ሀሳብና ፈቃድ መሠረት ማስፈጸም እንደሚገባም የፍ/ብ/ሕ ድንጋጌ ቁጥር 910 ያመለክ□ል፡፡

በተመሳሳይ ጉዳይላይም ይርጋ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 18394 ውሣኔ ሲሰጥ ስለአፈፃፀሙ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ስለሆነም በተወላጆች መካከል በኑዛዜው መሠረት ክፍፍል ሲደረግ ለተጠሪዎች ከአንድ አራተኛ /ሩብ/ በታች የሚደርሳቸው ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚቻለው የውርስ ንብረት ማጣራት ከተደረገ በኃላ እንደሆነ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች ገምተው ከቀረቡት የንብረት ዓይነት እና □□ ላ□ ተ□ቢ□ ማ□ሪ□ ስላልተ□ረ□ የድርሻቸውን መጠን በግልፅ ለመለየት አስቸጋሪ ሆኗል፡፡

በሌላ በኩል ከፍ ሲል እንደተመለከተው የቤት ቁጥር 120/02 እና የቤት ቁሳቁስ አመልካች በሕይወት □ስካለች ጊዜ ድረስ እንድትጠቀም ሟቹ በግልፅ በኑዛዜው ስለተወሰነ ይህም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 920 መሠረት መፈጸም ያለበት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪዎችም ሆኑ ሌሎች ተወላጆች ይህንን ንብረት ለመከፋፈል ጥያቄ ማቅረብ የሚችሉት ከአመልካች እልፈተ ሕይወት በኃላ ነው፡፡ አልያም ከአመልካች ጋር በሚደረግ ስምምነት ብቻ ይሆናል፡፡

ባጠቃላይ የአመልካች በኑዛዜው የተጠበቀላትን የመጠቀም መብት በሚጐዳ ሁኔታ የሥር ፍ/ቤቶች የኑዛዜውን መንፈስ እና የተናዛዡን ፍላጐት ባላገናዘብ ሁኔታ ኑዛዜው ፈራሽ ነው ንብረቶቹን ይከፋፈሉ በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

<u>***ው ሣ ኔ***</u>

1. የዲገሎ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 07255 የሰጠው ውሣኔ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 19592 የሰጠው ውሣኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 88384 የሰጠው ትዕዛ□ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሎ ተከታዩ ተወስኗል፡፡
2. አመልካች በሟች በተደረገለት ኑዛዜ መሠረት በሰጉሬ ከተማ ቀበሌ 02 በሚገኝ ቤት ቁጥር 120/02 እና የቤት ቁሳቁስ እንዲሁም በመንግሥት የተወረሰውን ቤት አበል እስከ ሕይወቷ ፍፃሜ የመጠቀም መብት አላት ብለናል፡፡
3. ተጠሪዎች እና ሌሎች የሟቹ ተወላጆች የሟችን ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ማቅረብ የሚችሉት ከአመልካች ሕልፈተ ሕይወት በኃላ ነው ብለናል፡፡

4. በዚህ ፍ/ቤት የተደረገውን ክርክር ወጪና ኪሣራ □ራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም.አ

የሰ/መ/ቁ. 46613

ሰኔ 24 ቀን 2002 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ኑኑ ሽህሞሎ - ቀረበ ጠ/ሰለሞን ታደሰ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ አሰገድች ጫኔ - ጠ/መስፍን ጌታቸው ቀረቡ፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካችና አቶ አለም ባሕታ በሚከራከሩበት ጉዳይ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት ታግዶ እንዲቆይ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ እግዱ እንዲነሳላቸው አመልክተዋል፡፡ በማመልከቻቸውም ከሥር ተከሣሽ ጋር ባልና ሚስት እንዳልሆኑና ተከሣሹ የተጠሪን ፈቃድ ሳያገኙ የቤቱን ካርታ አስይዘው በመበደራቸው ቤቱ የታገደ በመሆኑ እግዱ እንዲያነሳላቸው ፍ/ቤቱን ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለቀረበው አቤቱታ በሰጡት መልስ ተጠሪና የስር ተከሣሽ እንደ ባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ የተፈራ ንብረት በመሆኑ የጋራ ንብረት ስለሆነ እግዱ ሊነሳ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በሁለቱ መሃከል እንደ ደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ስላለ እና ንብረቱም በግንኙነቱ ውስጥ የተፈራ ስለሆነ እግድ እንዲነሳ የቀረበውን ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ በተሻሻለው ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 106/3/ መሠረት በሁለት ሰዎች መሃከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖርን ሁኔታ የሚረጋጠው በግንኙነቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ጠያቂነት ብቻ እንጂ በሌላ ሶስተኛ ወገን ጥያቄ አይደለም፣ ቤቱን በሥር ተከሣሽ ስም ባለመሆኑና የመያዣ ውሉም ስላልተመዘገበ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር በቤቱ ላይ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ የቀረበውን ይግባኝ ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው ከጋብቻ ውጪ እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ስለመኖሩ ማስረዳት የሚችል በግንኙቱ ውስጥ ያሉት ብቻ ናቸው መባሉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለዋል፡፡ ችሎቱም ይህንኑ ነጥብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ማመልከቻ ከሥር ተከሣሽ ጋር ከጓደኝነት የዘለለ ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን ገልፀው ተከሣሹ ያለ እሳቸው ፈቃድ ካርታቸውን አስይዞ በመበደሩ ምክንያት ቤታቸው መታገዱ አግባብ አለመሆኑን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው በስር ተከሣሽና በተጠሪ መሃከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ መኖሩን ተከራክረዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ማስረዳት የሚችሉት በግንኙቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ብቻ ናቸው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ የተሻሻለው ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 98፣ 99 እና 106 በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መሃከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ አለ የሚባለው መቼ እንደሆነና የግንኙነቱ መኖር በምን አይነት መንገድ ማስረዳት እንደሚቻል ከሚያመለክቱ በቀር ግንኙነት ስለመኖሩ ለማስረዳት መጠየቅ የሚችሉት በግንኙቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ብቻ እንዲሆኑ ገድቦ ያስቀመጠው ነገር የለም፡፡ በአንቀጽ 106/3/ ግንኙነት መኖሩን "አንደኛው ወገን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ" በማለት የተቀመጠው በግንኙቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች መሃከል የሚነሳውን ክርክር ታሳቢ በማድረግ እንጂ ሌላ 3ኛ ወገን ግንኙነቱን ማስረዳት እንዳይችል ለመከልከል አይደለም፡፡ በመሆኑም የግንኙነቱ መኖር አለመኖር በሶስተኛ ወገኖች መብት ላይ የሚያስከትለው ውጤት ካለ ይኸው ሶስተኛ ወገን ግንኙነቱን ከማስረዳት የሚከለክለው የሕግ መሠረት ስለሌለ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት መኖሩን ማስረዳት የሚችሉት በግንኙነቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ብቻ ናቸው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ማመልከቻ ያቀረቡት ንብረቴ ነው በሚሉት ቤት ላይ የተሰጠው እግድ እንዲነሳቸው ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 መሠረት በተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ቅሬታ የተሰማው ወይም ያለአግባብ ነው የሚለው ወገን ለፍ/ቤት ጥያቄ ሲያቀርብ ፍ/ቤቱ በቂ ምክንያት መኖሩን ያመነ ከሆነ የሰጠውን የእግድ ትዕዛዝ ማሻሻል፣ ማንሣት ወይም ጨርሶ መሰረዝ ይችላል፡፡ ተጠሪ እግዱ ይነሳልኝ የሚሉት ቤቱ የግል ንብረቴ ነው በማለት ነው፡፡ አመልካች በበኩላቸው በተጠሪና በሥር ከሣሽ መሃከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ያለና ንብረቱም የተፈራው በዚህ ግንኙነት ውስጥ በመሆኑ የተጠሪ ጥያቄ ውድቅ እንዲሆን አመልክተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም በዚህ ጉዳይ በዋናነት ሊያስተናግድ የሚገባው የእግድ ትዕዛዝ ሊነሳ ይገባል? አይገባም? የሚለው ቢሆንም ከዚህ አልፎ በተጠሪና በሥር ተከሣሽ መሃከል በሕግ የታወቀ ግንኙነት መኖር አለመኖሩ እንዲሁም የንብረቱን ባለቤት አስመልክቶ ውሣኔ አሳርፏል፡፡ ከመዝገቡም መረዳት እንደሚቻለው እነዚህ ጉዳዮች በዋና ጭብጥነት ተይዘው በመደበኛ የሙግት ስርዓት ተገቢው ክርክርና ማስረጃ ቀርቦባቸው የተወሰኑ አይደሉም፡፡ የተሰሙት ምስክሮች የሰጡት ምስክርነትም ቢሆን የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 106 የሚያስቀምጠውን ሁኔታ የሚያሟላ መሆን አለመሆኑ ሳይመዘን እንዲሁም ቤቱ የተሰራው መቼ እንደሆነ ሳይረጋገጥ የተሰጠው ውሣኔ የተጠሪን መብት በእጅጉ የሚጎዳ መሆኑን መረዳት ችለናል፡፡ ፍ/ቤቱ እግድ የተሰጠበት ንብረት የተጠሪ የግል ንብረት ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ያልቀረበለት ከሆነ የተጠሪን የእግድ ይነሳልኝ ጥያቄ ውድቅ ማድረግ እንጂ በጭፍጫፊ ጉዳይ መደበኛ ክርክርና ማስረጃ ሳይቀርብና ጉዳዩ በአግባቡ ሳይመረመር ተጠሪ ከሥር ተከሣሽ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና የንብረት ባለቤትነት መብት በማረጋገጥ የሰጠው ውሣኔ የሙግት ስርዓትን ያልተከተለና ስነ ሥርዓታዊ ግድፈት የተፈፀመበት ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን ምንም እንኳን ተጠሪ በንብረቱ ላይ ያላቸውን መብት በሌላ መንገድ የማረጋገጥ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በሥር ፍ/ቤት ዕግድ የተሰጠበት ንብረት የተጠሪ የግል ሃብት መሆን አለመሆኑ በበቂ ሁኔታ ስላልተረጋገጠ በንብረቱ ላይ የተሰጠው እግድ እንዳይነሳ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 69894 ታህሣሥ 25 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 43288 መጋቢት 25 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08135 ሐምሌ 7 ቀን 2000 ዓ.ም. በሰጠው ብይን በተጠሪና በሥር ተከሣሽ መሃከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ አለ እንዲሁም የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት ቤት በዚህ ግንኙት መሃል የተፈራ ነው በማለት የሰጠው ትችት ውድቅ ተደርጓል፡፡ የእግድ ትዕዛዙ ሊነሳ አይገባም ሲል የሰጠውን ብይን ግን ፀንቷል፡፡

ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. *51866*

ሐምሌ *02* ቀን *2002* ዓ.ም

***ዳኞች፣*** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

***አመልካች፣*** ወ/ሮ ደጅይጥኑ አለማየሁ - ቀረቡ

***ተጠሪ፣*** ወ/ሮ አዛለች ደበብ - ጠበቃ ደርበው ተመስገን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ***ፍ ር ድ***

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የጋብቻ ማስረጃን መስጠት በመቃወም የተጀመረ ነው፡፡ የጉዳዩ አጀማመር ለተጠሪ የተሰጠ የጋብቻ ማስረጃ አለአግባብ ነው፤ ሊሰረዝ ይገባል በማለት አመልካች መቃወሚያ በማቅረባቸው የአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቀደም ሲል ለተጠሪ የሰጠው ማስረጃ በመሰረዝ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ለአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ አመልካች ያቀረቡት መቃወሚያ በተጠሪ እና በሟች መካከል ጋብቻ መኖሩን አምነው ጋብቻው ፈርሷል የሚል መከራከሪያ ያቀረቡ ስለሆነ ጋብቻው ፈርሷል? አልፈረሰም? የሚለውን ማጣራት ይገባው ነበር ካለ በኃላ በዚህ ምክንያት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን ሽሯል፡፡ አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት በዚሁ ላይ ሲሆን ይዘቱም በተጠሪ እና በሟች ጫኔ በዛብህ መካከል ጋብቻ አልነበረም አለ ከተባለም በሕይወት እያሉ ተፋትተው የተለያዩ በመሆኑ ይህ ሳይጣራ የተሰጠው ውሣኔ አለአግባብ ነው ሲሉ እንዲሻር ጠይቀዋል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩን መርምሮ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጋብቻ ፈርሷል ወይስ አልፈረሰም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በራሱ ሳያጣራ ወይም በሥር ፍ/ቤት ተጣርቶ እንዲወሰን ሳያደርግ በደፈናው የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል የተጠሪ ጠበቃ ሚያዚያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ

አቅርበዋል በይዘቱም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለውም ተብሎ እንዲፀና ያመለከቱበት ነው፡፡

እኛም የክርክሩን አመጣጥ አስመልክቶ በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመረ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ከሥር መዝገብ መረዳት የተቻለው አመልካች ለተጠሪ የተሰጠው የጋብቻ ማስረጃ እንዲሰረዝ አቤቱታ ሲያቀርቡ በተጠሪ እና በሟች መካከል የነበረው ጋብቻ ቀድሞ ፈርሷል በሚል መነሻ ምክንያት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት በሟች እና በተጠሪ መካከል ጋብቻ ነበር ወይስ አልነበረም? ጋብቻ ነበር ከተባለ ቀድሞ በፍቺ የፈረሰ ወይንስ በሟች ሞት ምክንያት? የሚሉት ነጥቦች በአግባቡ ሳያጣራ የተወሰነ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም በውሣኔው በግልፅ እንዳመለከተው በተጠሪ እና በሟች መካከል የነበረው ጋብቻ ፈርሷል? ወይስ አልፈረሰም? የሚለው ነጥብ ያልተጣራ መሆኑ ሲረዳ ይህ ነጥብ እንዲጣራ ማድረግ አሊያም ሥር ፍ/ቤት ጉዳዩ እንዲጣራ ማድረግ ይገባው ነበር ይህ ሳይጣራ በደፈናው የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር ብቻ ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት አግኝቷል ለማለት አያስችልም ምክንያቱም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በተመለከተ በግልፅ በመቀበል ወይም ባለመቀበል የተሰጠ ውሣኔ ባለመኖሩ ነው፡፡ ስለሆነም የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ የሙግት አመራር እና ጭብጥ አያያዝ ስህተት ያለው መሆኑን ከተረዳ ማረም ሲገባው ማለፉ እና የአመልካችን ጥያቄ ግልፅ ዳኝነት ያልሰጠበት ከመሆኑም አንፃር በክርክሩ አመራር ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የአ/አ ከተማ ፍርድ ቤቶች ሰበር ችሎትም ይህንን ማረም ሲገባው ማለፉ ተገቢ አይደለም፡፡

ስለሆነም ይኸው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ በመ/ቁ 1234/99 በ3/01/02 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10849 በ9/03/02 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የአ.አ ከተማ ፍ/ቤቶች ሰበር ችሎት በመ/ቁ 12433 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በሟች እና በተጠሪ መካከል ጋብቻ ነበር በአመልካች ስላልተካደ፤ ጋብቻ ነበር ከተባለስ ጋብቻው በፍቺ ፈርሷል? አልፈረሰም? የሚለው የአመልካች መቃወሚያ ነጥቦች ላይ ግራቀኙን አከራክሮ የመሰለውን ውሣኔ እንዲሰጥ ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መዝገቡን ለአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ እንዲመለስ አዝዘናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ም.አ

የሰ/መ/ቁ. *51893*

*ሐምሌ 8 ቀን 2002 ዓ.ም*

***ዳኞች፣*** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

***አመልካች፣*** እንዳልካቸው ዘለቀ ጠ/ቴዎድሮስ ተስፋዬ ቀረቡ

***ተጠሪ፣*** ወ/ሮ ብዙዓለም መንግሥቱ ጠ/ዩሴፍ ደስታ ቀረቡ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ነው፡፡ በአመልካች እና በተጠሪ መሃከል የነበረው ጋብቻ ከፈረሰ በኃላ ተጠሪ የጋራ ንብረት ለመካፈል የንብረት ዝርዝር አቅርበዋል፡፡ ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር ውስጥም ለክርክር ምክንያት ሆነው ቤት የጋራ በመሆኑ አመልካች እንዲያካፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው የኮንዶሚኒየም ቤት እጣ የተመዘገቡት ከጋብቻ በፊት መሆኑንና ሐምሌ 4 ቀን 1999 ዓ.ም ከአ/አ ከተማ አስተዳደር የኮ/ቀ/ክ/ከ/ የቤት ማስተላለፊያ ጽ/ቤት ጋር የቤት ሽያጭ ውል የፈረሙ አመልካች ብቻ እንጂ ተጠሪ አለመፈረማቸውን ገንዘቡንም አመልካች ከመ/ቤት ካገኙት ብድር እና ወደፊትም ከደሞዛቸው የሚከፈል በመሆኑ ቤቱ አመልካች የግል ንብረት ሊባል እንደማይችል ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ግራቀኙ ጋብቻ የመሠረቱት ሚያዚያ 22 ቀን 1998 ዓ.ም ሲሆን ፍቺ የተፈፀመው መስከረም 30 ቀን 2000 ዓ.ም ነው አከራካሪ የሆነው ኮንዶሚኒየም ቤት እጣ የወጣውና ሽያጭ ውሉ ከአ/አ መስተዳድር ጋር የተፈረመው በጋብቻ ወቅት ሐምሌ 4 ቀን 1999 ዓ.ም በመሆኑ ቤቱ የጋራ ንብረት ነው በሚል ከተቻለ በአይነት ካልተቻለ በሃራጅ ተሸጦ እንዲካፈሉ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው የይግባኝ ቅሬታቸው ተሰርዞባቸዋል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው የኮንዶሚኒየም ቤት ምዝገባ የተከናወነው ከጋብቻ በፊት በመሆኑ የቤቱ ግዥ የተፈፀመው አመልካች ከአ/አበባ መስተዳድር የኮ/ቀ/ክ/ከ የቤት ማስተዳደር መምሪያ ጋር በፈረሙት ውል መሆኑ የቅድሚያ ክፍያ የተከፈለው ከአመልካች ደሞዝ በተወሰደ ብድር መሆኑ ለቀሪው ክፍያ ከባንክ ጋር የብድር ውል የፈረሙት አመልካች ብቻ በመሆናቸው እንዲሁም የቤቱ ርክክብ በጋብቻ ጊዜም ሆነ በፍቺ ወቅት ያልተፈፀመ በመሆኑ ቤቱ የአመልካች የግል ሃብት ነው በማለት ስር ፍ/ቤት ቤቱን አስመልክቶ የሰጠው ውሣኔ እንዲሻርላቸው ጠይቀዋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም ምንም እንኳን የኮንደሚኒየሙ እጣ በጋብቻ ወቅት የወጣ ቢሆንም አመልካች ምዝገባ ያደረጉት ከጋብቻ በፊት መሆኑና ከባንክ የተወሰደው ብድር ጋብቻው ከፈረሰ በኃላ ከአመልካች የሚከፈል ከመሆኑ አንፃር ተጠሪ ያላቸው መብት ምንድነው? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ግራቀኙ ቀርበው የቃል ክርክራቸው ተሰምቷል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የግራቀኙ የጋራ ንብረት ነው ወይስ የአመልካች የግል ንብረት ነው የሚለው ነው ስለ ባልና ሚስት የጋራ ንብረት የሚደነግገው የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 62 በንዑስ ቁጥር ሁለት ስር በጋብቻ ወቅት በግብይት የተገኙ ንብረቶች የጋራ ንብረቶች እንደሆኑ ተመልክቷል በተያዘው ጉዳይ አከራካሪውን ቤት አመልካች የተመዘገቡት ከጋብቻ በፊት ስለመሆኑና ዕጣው የደረሰው ግን የሁለቱ ጋብቻ ፀንቶ በነበረበት ወቅት ስለመሆኑ ክርክር አላስነሳም ይህም ብቻ ሳይሆን አመልካች ከአ/አበባ አስተዳደር የቤት ማስተዳደር መምሪያ ጋር የቤቱን የሽያጭ ውል ያደረጉት ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ነው፡፡ አመልካች ለኮንዶሚንየሙ ቤት የተመዘገቡት ከጋብቻ በፊት ቢሆንም የቤቱ ባለቤት የሚያደርጋቸውን የሽያጭ ውል ያደረጉት ግን በጋብቻ ወቅት በመሆኑ ቤቱ በግብይት ተገኘ ሊባል የሚችለው የሁለቱ ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ወቅት ነው አመልካች ውሉን ለብቻቸው መፈረማቸው ብቻውን ቤቱን የግል ንብረታቸው አያደርገውም የሽያጩን ውል ለብቻቸው ማድረጋቸው ቀርቶ በጋብቻ ወቅት የተገኘው ቤት በስማቸው መመዝገቡ እንኳን ንብረቱን የግል ንብረት እንደማያደርገው የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 63/1/ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የሽያጩን ውል አመልካች ብቻ መፈረማቸው ቤቱ የአመልካች የግል ንብረት ነው አያሰኘውም ሌላው አመልካች ቤቱ የግል ሊሆን ይገባል በማለት የሚከራከሩት ለቤቱ የቅድሚያ ክፍያ የተከፈለው ከአመልካች ደመወዝ በብደር የተገኘ ገንዘብ መሆኑ እንዲሁም ቀሪውን ዕዳ ለመክፈል አመልካች ለብቻቸው ከባንክ ብድር መውሰዳቸውን ነው ይሁን እንጂ አመልካች ለቤቱ ግዥ ከደሞዛቸውም ሆነ ከባንክ ለወሰዱት ብድር ተጠሪም የጋራ ባለእዳ ከሚሆኑ በቀር ንብረቱን የአመልካች የግል ንብረት አያደርገውም በአጠቃላይ ምንም እንኳን አመልካች ለቤቱ የተመዘገቡት ከጋብቻ በፊት ቢሆንም እጣው የወጣው በጋብቻ ጊዜ ስለመሆኑና የቤቱ ባለቤት የሚያደርጋቸው የሽያጭ ውልም የተፈረመው በጋብቻ ውስጥ በመሆኑ ቤቱ የግል ነው መባሉ ከተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 62/2/ አኳያ ሲታይ ተገቢ በመሆኑ ቤቱን ከተቻለ በአይነት እንዲካፈሉ ካልተቻለ አንፋ ለሌላኛው የቤቱን ግምት ከፍሎ እንዲያስቀር በዚህም ካልተስማሙ ቤቱ በሃራጅ ተሽጦ የሚገኘውን ገንዘብ ግራቀኙ እንዲካፈሉ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ማለት አይቻልም፡፡

በሌላ በኩል ግን ግራቀኙ ክርክር የቤቱን ዋጋ ለመክፈል ብድር ስለመወሰዱና ወደፊትም የቤቱ ቀሪ እዳ መከፈል ያለበት መሆኑን መረዳት ችለናል ተጠሪ የቤቱ የጋራ ባለሃብት ናቸው የተባለ በመሆኑ ቤቱ ለተገዛበት የብድር ገንዘብ እንዲሁም ቀሪ ክፍያም ካለ የጋራ ባለእዳ ሊሆኑ ይገባል በመሆኑም ለቤቱ መግዣ አመልካች ከደሞዛቸውም ሆነ ከባንክ ለወሰዱት እዳ እንዲሁም የቤቱ ቀሪ ክፍያ ካለም ግራቀኙ ለእዳው በጋራ ሃላፊ ሊሆኑ ስለሚገባ የስር ፍ/ቤት ይህን በተመለከተ ሳይወሰን ማለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 57488 የካቲት 29 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 80996 የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡

2. አከራካሪው የኮንደሚኒየም ቤት የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ እንዲካፈሉ መወሰኑ ተገቢ ቢሆንም ቤቱን ለመግዛት አመልካች የወሰዱት ብድር እና እንዲሁም ከቤቱ ለሚፈለገው ቀሪ እዳ አመልካችና ተጠሪ በጋራ ባለእዳ ናቸው ብለናል፡፡ በመሆኑንም የሚፈለገውን እዳ ግማሽ ተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፣፣

3. ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም.አ

የሰ/መ/ቁ 50836

ሐምሌ 13 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ቅድስት ተካ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ የኔነሽ ተካ - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የወራሽነት ማስረጃን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በሟች ወ/ሮ መሠረት በሪ መጋቢት 7 ቀን 1995 ዓ.ም ኑዛዜ መሠረት የኑዛዜ ወራሽነታቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ኑዛዜውን በማጽደቅ አመልካች የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት አመልካች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሰረዝ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ በመቃወሚያቸውም ኑዛዜው በህጉ የተመለከተውን መስፈርት አያሟላም ሟች ኑዛዜው ያደረጉበት የራሳቸው ባልሆነ ንብረት ላይ ነው የሟች ኑዛዜ ተጠሪን ነቅሏል ንብረቱም በተጠሪ የተሰራ ነው የሚሉ ክርክሮችን አንስተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የተጠሪን መከራከሪያዎች በሙሉ ውድቅ በማድረግ ቀደም ሲል የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞባቸዋል፡፡ በመቀጠልም ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ

አቅርበው ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ የወራሽነት ምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ማመልከቻ ሲቀርብ ፍ/ቤቱ ወራሽነትንና የውርስ ሃብቱን ድርሻ በማረጋገጥ ማስረጃ መስጠት ስላለበት በቅድሚያ የውርስ ሃብት ሊጣራ ይገባል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የውርስ ሃብት ተጣርቶ ባልቀረበበት ሁኔታ የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወራሾች የውርስ ሃብት አጣርተው ሲቀርቡ መሆኑን የማንቀሳቀስ መብታቸው ተጠብቆ ውሳኔውን ሽሮታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ዋነኛ ቅሬታ በግራ ቀኙ መሃከል ያለው ክርክር ሟች ወ/ሮ መሠረት በሪ ያደጉት ኑዛዜ ሊፀና ይገባል አይገባም? የሚል ሆኖ ሳለ ተከራካሪዎቹ ያላነሱትን ክርክር መሠረት አድርጐ ውሳኔ መስጠቱ የህግ ስህተት ስለሆነ መታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ ክርክር ኑዛዜው ይሰረዝልኝ የሚል ሆኖ ሳለ በቅድሚያ የውርስ ሃብት እንዲጣራ የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪም ቀርበው በፁሁፍ በሰጡት መልስ ፍ/ቤት የሚሰጠው ማስረጃ ወራሽነትን የማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን የሚደርሰው የውርስ ሃብት ድርሻም የሚያረጋግጥ መሆን ስላለበት ህጉ በአግባቡ ተተርጉሟል በማለት ውሳኔው እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

በስር ፍ/ቤት አመልካች የኑዛዜ ወራሽነታቸው ተረጋግጦ የወራሽነት ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው አመልክተው ፍ/ቤቱ በዚሁ መሠረት አመልካች ኑዛዜ ወራሽ መሆናቸው ተገልጾ ማስረጃ ሰጧቸዋል፡፡ ተጠሪ ኑዛዜው በህጉ የተመለከተውን የአፃፃፍ መስፈርት ስላላሟላ ሟች ኑዛዜውን ያደረጉት የራሳቸው ሃብት ባልሆነ ንብረት ስለሆነና እንዲሁም ኑዛዜው ተጠሪን የነቀለ በመሆኑ አመልካች የኑዛዜው ወራሽ ሊባሉ አይችሉም በሚል መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት ፍ/ቤት መቃወሚያውን መርምሮ ተጠሪ ያቀረቡት መከራከሪያዎች ተቀባይነት የላቸውም ሲል የቀድሞውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግን የወራሽነት ምስክር ወረቀት የሚሰጠው ወራሽነትን በማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን የወራሹን የውርስ ሃብት ድርሻም በማረጋገጥ ስለሆነ በቅድሚያ የውርስ ሃብት ሊጣራ ይገባል በማለት አመልካች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ ሽሯል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1)(ሸ) መሠረት የወራሽነት ምስክር ወረቀት የመስጠት ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህም መሠረት ለአመልካች የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ ወይም ምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸዋል፡፡ የተሰጠው የወራሽነት ምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ ጥያቄ ሲቀርብም ፍ/ቤቶች በቂ ምክንያት ሲኖር የሰጡትን ምስክር ወረቀት ሊሰርዙ እንደሚችሉ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 998(1) ስር የተመለከተ ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪ ተቃውሞ ያቀረቡት አመልካች የውርስ ተጠቃሚ የሆኑበት ኑዛዜ ህጋዊነት ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቶቹ ሊመረምሩ የሚገባው የአመልካችን የውርሱ ተጠቃሚ ያደረጋቸው ኑዛዜ በህግ ፊት ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑን ነው፡፡ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግን ኑዛዜው በህግ ፊት ተቀባይነት አለው የለውም የሚለውን መመርመር ሲገባው በግራ ቀኙ ክርክር ያልተነሳበትን ነጥብ መሠረት አድርጐ በቅድሚያ የውርስ ማጣራት ሳይደረግ የወራሽነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊሰጥ አይገባም ብሏል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ በኑዛዜ ለአመልካች የተሰጠውን ንብረት አመልካች ሊወስዱ አይገባም የሚሉ ሲሆን በንብረት ክፍፍል ጊዜ ተቃውሞ ከሚያቀርቡ በቀር የውርስ ሃብቱ ባለመጣራቱ ብቻ የአመልካች የኑዛዜ ወራሽነት ሊሰረዝ የሚችልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ኑዛዜው ፈራሽ ሊሆን የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት መኖር አለመኖሩን በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ሲገባው በግራ ቀኙ ክርክር ያልተነሳውን የውርስ ሃብት ማጣራት ጉዳይ አንስቶ ውሳኔውን መሻሩ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

## **ው ሳ ኔ**

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 08219 መስከረም 22 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡

2. ችሎቱ የስር ፍ/ቤቶች የኑዛዜው ህጋዊነት አስመልክቶ የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ በመመርመር ተገቢ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ጉዳዩን መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 44561

ሐምሌ 28 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ገነት በላይ ጠበቃ - ኮሎኔል መላኩ ካሣዬ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ፌኔት ተክሉ - ሞግዚት ነጋ ቦንገር በሌሉበት ይታያል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት መጋቢት

10 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የአቶ ተክሉ ነጋ ውርስ እንዲጣራ ለውርስ አጣሪ መርቷል፡፡ የውርስ አጣሪው የሟች አቶ ተክሉ ነጋ ወራሾች ህፃን ኬሩዝ ተክሉና ህፃን ፌኔት ተክሉ መሆናቸውንና የውርሱ ንብረት ክፍል የሚሆነውን ጥሬ ገንዘብና ያክሲዮን ድርሻ በመዘርዘር የውሣኔ ሐሳብ አቅርቧል፡፡ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ለአሁን አመልካች ለሥር ተጠሪ ከፔፕሲ ኮላ ዓለም አቀፍ መስሪያ ቤት የተከፈላቸው መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠው 166,449.97 የአሜሪካን ዶላር/አንድ መቶ ስልሣ ስድስት ሺ አራት መቶ አርባ ዘጠኝ ከዘጠና ሰባት ሣንቲም/ የአሜሪካን ዶላር ለአመልካች ጥቅም የተገባ የኢንሹራንስ ፖሊስ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባለመኖሩ የውርስ ሃብት ነው በማለት የውርስ አጣሪው ያቀረበው ሃሳብ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተቀብሎ አጽድቆታል፡፡ የውርስ አጣሪው ከላይ መጠኑ የተገለፀው የአሜሪካን ዶላር አመልካች እንዲካፍሉ ያቀረበውን የውሣኔ ሐሳብ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በማጽደቁ ተጠሪ ይህንን በመቃወም ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዋ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የይግባኝ ማመልከቻ ሟች አቶ ተክሉ ነጋ ከፔፕሲ ኮላ ዓለም አቀፍ ተጠሪ ጽ/ቤት ለአፍሪካ አህጉር ሥራ አስኪያጅ በሆኑበት ጊዜ የሕይወት ኢንሹራንስ የገባው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 07/01/98 (ከታህሣሥ 19 ቀን 1990 ዓ.ም) እስከ አውሮፓውያን አቆጣጠር 05/21/2001 (ከግንቦት 13 ቀን 1993 ዓ.ም) ነው በዚህ ጊዜ 166,449.97(አንድ መቶ ስልሳ ስድስት ሺህ አራት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር ከዘጠና ሰባት ሣንቲም) የአሜሪካን ዶላር ለአሁን አመልካች (መልስ ሰጭ መክፈሉ ተረጋግጧል)፡፡ ይህ ገንዘብ የውርስ ንብረት ክፍል ሆኖ በወራሾች መካከል ብቻ ሊከፋፈል ሲገባው የሥር መልስ ሰጭ የአሁን አመልካች የሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ ሣይሆኑ የገንዘቡ ተጠቃሚ እንደሆኑ መደረጉ ተገቢ አይደለም የሚል ይግባኝ አቅርበዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች በበኩላቸው ለከፍተኛው ፍ/ቤት መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ባቀረቡት መስቀለኛ ይግባኝ ሟች አሜሪካዊና የሕይወት ኢንሹራንስ የገባው በአሜሪካን አገር በሚገኝ ኩባንያ ኢንሹራንስ ከፋዩም የአሜሪካን ኩባንያ በሆነበት ሁኔታ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ የወሰነው የሥረ ነገር ሥልጣን ሳይኖረው ነው በማለት አመልክተዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ተጠሪዋ ላቀረቡት ይግባኝ የሰጡትን መልስና የአሁን ተጠሪዎች ለአመልካች የመስቀለኛ ይግባኝ የሰጡትን መልስ ከተቀበለና ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ የዓለም አቀፍ የግለሰብ ሕግ ጥያቄ ስላልተነሣ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አለው፡፡ የአሁን አመልካች የኢንሹራንስ ክፍያው ለሟች አሰሪ መስሪያ ቤት የከፈላቸው መሆኑን እንጂ የሕይወት ኢንሹራንስ ለእሳቸው ጥቅም የተደረገ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህንን ለማጣራት የኢንሹራንስ ውሉ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቶ ውሉ ተፈልጐ እንዳልተገኘ መሥሪያ ቤቱ ጥር 22 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አመልካች የሕይወት ኢንሹራንስ ውል የተለየ ተጠቃሚ መሆናቸውን የኢንሹራንስ ውሉ በማቅረብ ያላስረዱ ስለሆነ የሕይወት ኢንሹራንሱ የሟች የውርስ ንብረት ክፍል በመሆን ለሟች ልጆችና ወራሾች ብቻ የሚተላለፍ ነው በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/ መሰረት በማድረግ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከኢንሹራንስ ገንዘቡ ግማሹን ትውሰድ በማለት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የሌለበት መሆኑን በመግለጽ ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች መጋቢት 10 ቀን 2001 ዓ.ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ጉዳዩን ማየትና መወሰን የሚችለው በአሜሪካን ግዛት ውስጥ ያለ የስረ ነገር ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት መሆን ሲገባው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን አለኝ በማለት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 በመተርጐም ረገድ የከፍተኛው ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሰርቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ በሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ የሚሆኑ ባል ወይም ሚስት መብት ሙሉ በሙሉ በሚያሣጣና የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡን ወደ

ሟች ወራሾች ሙሉ በሙሉ ለማስተላለፍ በሚችል መንገድ መተርጐም የለበትም፡፡ አመልካች የኢንሹራንስ ገንዘብ ተከፍሏቸዋል፡፡ የህይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ ባይሆኑ ኖሮ አይከፈላቸውም ነበር ስለዚህ በህይወት ኢንሹራንስ ልዩ ተጠቃሚ ስለመሆናቸው አላስረዱም ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ/ ድንጋጌዎች ከግምት ውስጥ ሣያስገቡ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ ሞግዚታቸው የተሻረ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ስለሆነም ተጠሪዋ ፌኔት ተክሉ በሚል ስም በጋዜጣ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቶ በጋዜጣ ጥሪ የተደገላቸው ቢሆንም ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ከሥር የክርክር አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት አመልካች ሟች ከገባው የሕይወት ኢንሹራንስ የምታገኘው ድርሻ የላትም የሕይወት ኢንሹራንስ ክፍያው የሟች ውርስ ንብረት ክፍል ስለሆነ የሕይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡን የሟች ልጆችና ወራሾች ብቻ ይካፈሉ በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ትርጉምና የተፈፃሚነት ወሰን መሰረት በማድረግ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ነጥቦች በዝርዝር መመርመር የሚያስፈልገው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ የተያዘው ጭብጥ እልባት ለመስጠት በመጀመሪያ አመልካች የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡን በተመለከተ የዳኝነት ሥልጣን የላቸውም? የሟች አሰሪ መሥሪያ ቤት የኢንሹራንስ ገንዘቡን ለእኔ መክፈሉ የሕይወት ኢንሹራንስ ውሉ ልዩ ተጠቃሚ መሆኔን ያስረዳል በማለት ያቀረቧቸውን ክርክሮች ተገቢነት ማየት ያስፈልጋል፡፡

1. አመልካች ሟች የህይወት ኢንሹራንስ ክፍያ 166,449.97(አንድ መቶ ስልሳ ስድስት ሺህ አራት መቶ አርባ ዘጠኝ ከዘጠና ሰባት ሣንቲም) ዶላር የተከፈላቸው መሆኑን በመግለጽ የኢንሹራንስ ውሉ የተገባው ከኢትዮጵያ ውጭ በመሆኑ የኢንሹራንስ ገንዘቡን የሚከፍለው የኢንሹራንስ ኩባንያ በውጭ አገር ያለ በመሆኑ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን የላቸውም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ ክርክር የተነሣው አመልካችና የሟች ወራሾች ማግኘት የሚገባቸውን የኢንሹራንስ ገንዘብ የኢንሹራንስ ኩባንያው ስላልከፈላቸው በኢንሹራንስ ኩባንያውና በአመልካችና የሟች ልጆች መካከል አይደለም፡፡ የሟች አሰሪ መሥሪያ ቤት የኢንሹራንስ ገንዘቡን ከፍሏል፡፡ የመድን ሽፋን የሰጠው የኢንሹራንስ ኩባንያም በውሉ መሰረት ግዴታና ኃላፊነቱን ተወጥቷል፡፡ አከራካሪው ጉዳይ የሕይወት ኢንሹራንስ የመድን ሽፋን የሰጠው ድርጅት በሟች መሥሪያ ቤት በኩል የከፈለው የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ ላይ መብት ያለው ማን ነው? የሚለው ነው፡፡ አመልካችም ሆኑ ተጠሪ በዜግነት ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሟች ውርስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 944 ድንጋጌ መሰረት የተጣራው በኢትዮጵያ ሕግ በኢትዮጵያ ግዛት ክልል ውስጥ ነው፡፡

የውርስ ማጣራት አንደኛው ተግባር የሟች ወራሾች እነማን እንደሆኑ መለየት የሟች ውርስ ሐብት ክፍል የሚሆነውንና የሟችን እዳ አጣርቶ መለየትና መወሰን የሚያጠቃልል ነው፡፡ በውርስ ማጣራት ሒደት አመልካች የተቀበሉት 166,447.97(አንድ መቶ ስልሳ ስድስት ሺህ አራት መቶ አርባ ዘጠኝ ከዘጠና ሰባት ሣንቲም) የአሜሪካን ዶላር የውርስ ንብረት ክፍል ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጥያቄ አከራካሪ ጭብጥ ሲሆን ጥያቄው በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ለመወሰን የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው በመሆኑ አመልካች ጉዳዩን ለማየትና ለመወሰን የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የላቸውም በማለት ያቀረቡት ክርክር በመዝገቡ የተያዘው ክርክሩ በአመልካችና የሟች ወራሾች በሆኑ ሁለት ኢትዮጵያውያን መካከል መሆኑን፣የክርክሩም መሰረታዊ ጉዳይ በሟች አሰሪ መስሪያ ቤት በኩል የተከፈለው ወደ አገር ውስጥ የተላከው የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ የሟች ውርስ ንብረት ክፍል ነው ወይስ አይደለም? የሚልና በውጭ አገር የሚገኙ የሕግ ወይም የተፈጥሮ ሰዎች በክርክሩ ተካፋይ የማይሆኑበት መሆኑን ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

2. ሁለተኛው ምላሽ ማግኘት ያለበት ነጥብ አመልካች የህይወት ኢንሹራንስ ክፍያው ለእኔ ተከፍሎኛል፡፡ ይህም የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ ልዩ ተጠቃሚ መሆኔን የሚያስረዳ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተገቢነው ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡ አመልካች የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ የተለዩ ተጠቃሚ

መሆናቸውን የሚያስረዳ ማስረጃ በተለይም አመልካችን የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ በማድረግ ሟች የመድን ዋስትና ከሰጠው የመድን ድርጅት ጋር የገባውን ውል እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ውሉን ሊያቀርቡ አለመቻላቸው በሥር ፍርድ ቤትና በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ለአንድ ለተለየ ተጠቃሚ የሚደረግ የህይወት ኢንሹራንስ ውል በዝርዝር የሚይዛቸው ጉዳዮችን የንግድ ሕግ አንቀጽ 195 በዝርዝር ይደነግጋል፡፡ አመልካች የኢንሹራንስ ፖሊሲው ልዩ ተጠቃሚ ነኝ ካሉ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 195 እና 701/1/ የተደነገጉትን ዝርዝር ጉዳዮች የሚያሥረዳ የኢንሹራንስ ውልና ፖሊሲ በማቅረብ የማስረዳት ግዴታ አለባቸው፡፡ አመልካች ይህንን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነታቸውን ያልተወጡ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በመደበውና ተቀብሎ ሪፖርቱን ባፀደቀው የውርስ አጣሪና በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡

አመልካች የሟች ልጆች ሞግዚትና የሟች ሚስት በመሆናቸው ምክንያት ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት በሟች መኖሪያ ቤት በኩል የኢንሹራንስ ገንዘቡ ተከፍሏቸዋል፡፡ የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡ አመልካች መክፈሉ ብቻውን አመልካች በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ መሆናቸውን አያስረዳም ከሚል መደምደሚያ ላይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የደረሰው ሟች የህይወት መድን ሽፋን ከሰጠው የኢንሹራንስ ኩባንያ ጋር ያደረገው የኢንሹራንስ ውል እንዲላከለት ትእዛዝ ሰጥቶ የህይወት ኢንሹራንስ የውል ሰነዱ ተፈልጎ ሊገኝ አለመቻሉ የሟች አሰሪ መሥሪያ ቤት ከገለጹለት በኋላ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ መሆናቸው የተገለፀ መሆኑን አግባብነት ያለው ማስረጃ በማቅረብ አላስረዱም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት እና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ የሰጡት የህይወት ኢንሹራንስ ውሉን ለማስቀረብና ፍሬ ጉዳዩን ለማጣራት ተገቢውን ጥረት ካደረጉ በኋላ በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን ማስረጃ በመመዘን በመሆኑ አመልካች የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ መሆኔን አስረድቻለሁ በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተገቢነት የሌለውና የሰበር ችሎት በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 80 ንኡስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ሟች የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 1 እና በንግድ ሕግ ቁጥር 695 በተደነገገው መሰረት የህይወት ኢንሹራንስ ውሉን ያደረገው ለአመልካች ወይም ለልጆቹ ህፃን ኬራዝ ተክሉና ህፃን ፌኔት ተክሉ ልዩ ጥቅም ያደረገ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ የህይወት መድን ውል በመድን ውል በተጠቃሚነት ለተገለፀው ሰው ወይም ሰዎች ወይም ኢንሹራንስ ከገባው ሰው መብት ላላቸውና ስማቸው በተጠቃሚነት ላልተገለፁ ሰዎች ሊደረግ እንደሚችል ከንግድ ሕግ ቁጥር 692 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሟች በገባው የሕይወት ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ የሚሆነውን ሰው በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 1 የገለፀ በሆነ ጊዜ የኢንሹራንስ ውሉ መሰረት ገንዘብ ለማን ይከፈላል የሚለው ጥያቄ በዚህ መዝገብ አከራካሪ ጭብጥ ሆኖ አልቀረበም፡፡ በያዝነው ጉዳይ ሟች ያደረገው የኢንሹራንስ ውል ለአመልካች ወይም ለልጆቹ ልዩ ጥቅም የተደረገ መሆኑን የማይገልጽና ለተለየ ተጠቃሚ ያልተደረገ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የደረሱበት መደምደሚያ ተገቢነት ያለው ቢሆንም ሟች ባደረገው የህይወት ኢንሹራንስ ውል በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረት የኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ ወይም ተጠቃሚዎች ያልገለፀ በሆነ ጊዜ በህይወት ኢንሹራንስ ውል መሰረት በሚከፈለው ገንዘብ ላይ መብት የሚኖራቸው እነማን ናቸው? ጉዳዩስ የትኛውን የሕግ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ይወስናል የሚለውን ሰፊ የሕግ ክርክር ያስነሳ ጭብጥ አስመልክቶ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔና የደረሱበት መደምደሚያ በዝርዝር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. ሟች የተዋዋለው የህይወት ኢንሹራንስ ውል የኢንሹራንስ ውሉን ተጠቃሚ የማይገልጽ በሆነ ጊዜ የኢንሹራንስ ገንዘቡ ይገባናል ብሎ ለመጠየቅ የሚያስችሉ ሶስት የሕግ ድንጋጌዎች ያሉ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕጉንና የንግድ ሕጉን ድንጋጌዎች በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡ የሕይወት ኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ ባልተገለጸበት ጊዜ የሟች ወራሾች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 እና የንግድ ሕግ ቁጥር 705 ድንጋጌዎችን በመጥቀስና መሰረት በማድረግ የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡ ሙሉ በሙሉ እንዲሰጣቸው ጥያቄ የሚያቀርቡ መሆኑን የተጠሪ ሞግዚት በዚህ መዝገብ ያቀረቡትን ክርክርና የድንጋጌዎቹን ይዘት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ሟች

ያደረገው የህይወት የኢንሹራንስ ውል የተለየ ተጠቃሚ ባልገለፀ ጊዜ ወይም የህይወት ኢንሹራንስ ውሉን ለወራሾቹ ጥቅም ያደረገው መሆኑን በኢንሹራንስ ውሉ ባልገለፀ ጊዜ የሟች ባል ወይም ሚስትና የኢንሹራንስ ውሉ ሲፈረም የተወለደው ልጅ የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡ እንዲሰጣቸው የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ/ እና /ለ/ በመጥቀስ የሚጠይቁና የሚከራከሩ መሆኑን አመልካች ከሥር ጀምሮ ያቀረቡትን ክርክርና የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ይዘት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም በዚህ መዝገብ አመልካችና ተጠሪ የከተከራከሩበትን ጭብጥና ውሣኔ ለመስጠት ከላይ የተጠቀሱትን የሕግ ድንጋጌዎች ይዘት መሰረታዊ ግብና ዓላማ በተናጠል ማየትና የሕግ ድንጋጌዎች በአንድ ላይ ለማስፈፀም በሚሞክርበት ጊዜ የሚያጋጥሙ ችግሮችንና ችግሮቹን ለመፍታት ለሕግ ድንጋጌዎቹ ሊሰጣቸው የሚገባውን ትርጉም በዝርዝር ማየትና ውሣኔ ላይ መድረስ የሚጠይቅ ጉዳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን የሕግ ድንጌጋዎች፣ ይዘት መንፈስና ዓላማና በአንድ ላይ ተፈፃሚ በማይደረጉበት ጊዜ የሚያጋጥመን ተጨባጭ ነባራዊ ችግር በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

ሀ. የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ይዘትና መሰረታዊ ባህሪ ለመረዳት በኢትዮጵያ የውርስ ሥርአት ከሟች ወደ ወራሾች የሚተላለፈው መብትና ግዴታ በተመለከተ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን ጠቅላላ መርህ ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡ በርካታ አገሮች ለምሣሌ ሩሲያ ከሟች ወደ ወራሾቹ በውርስ ሊተላለፉ የሚችሉ ንብረቶችና መብቶች በዝርዝር ያስቀምጣሉ፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826/2/ የሟች ውርስ ክፍል ሆነው ለወራሾቹ ሊተላለፉ የሚችሉ ንብረቶችና መብቶች ምንምን እንደሆኑ ከመዘርዘር ይልቅ በሟች መሞት የሚያቋርጡ የሟች መብቶችና ግዴታዎች ለሟች ወራሾችና የኑዛዜ ባለስጦታዎች የሚተላለፉ መሆኑን በመርህነት የሚደነግግ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም ማለት በሟች መሞት ምክንያት ቀሪ የሚሆኑና ሟች በግሉ ብቻ ሊሰራባቸው የሚችሉ መብቶችና ሟች በግሉ ብቻ እንዲፈጽማቸው የሚገደድባቸው ግዴታዎች ውጭ ያሉ በሟች መሞት ምክንያት የማይቋረጡ መብትና ግዴታዎች ለሟች ወራሾች የሚተላለፉ መሆኑ በአጠቃላይ መርህነት ተደንግጓል፡፡

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 828 በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ጠቅላላ መርህ ለየት ባለ ሁኔታ ሕግ አውጭው የደነገጋቸው ልዩ የሕግ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 "በውርስ ውስጥ የሚገኘው ስለሕይወት ኢንሹራንስ ውል" በሚል እርስ ንኡስ አንቀጽ 1 "ሟች ተጠቃሚውን ያልወሰነ እንደሆነ ወይም ኢንሹራንሱ ለሟች ወራሾች ጥቅም የተደረገ እንደሆነ ሟች በፈረመው ስለ ህይወት ኢንሹራንስ ውል አፈፃፀም የሚከፈሉ ገንዘቦች የውርስ ንብረት ክፍል ይሆናሉ" በማለት የሚደነግግ ሲሆን ንኡስ አንቀጽ 2 "ተቃራኒ ሁኔታ ሲኖር የውርስ ክፍል አይሆንም" በማለት ይደነግጋል፡፡

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ድንጋጌ በሞት ጊዜ እንዲከፈል የተደረገ የህይወት ኢንሹራንስ ውል መሰረት የሚከፈል የኢንሹራንስ ገንዘብ በሟች መሞት ምክንያት የማይቋረጥ ይልቁንም ገንዘቡ የሚጠየቀው ኢንሹራንስ ገቢው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ መሆኑን በመገንዘብ ሕግ አውጭው በሞት ጊዜ የሚከፈል የህይወት ኢንሹራንስ ውል በንግድ ሕግ ቁጥር 695 እና በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሰረት የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ ወይም ተጠቃሚዎች የተደረገ በሆነ ጊዜ የኢንሹራንስ ገንዘቡ የውርስ ንብረት ክፍል እንደማይሆንና ወራሾቹ ድርሻ አለን ብለው የመብት ጥያቄ ሊያነሱ የማይችሉ መሆናቸውን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 2 በግልጽ የሚደነግግ ሲሆን፣የሕይወት ኢንሹራንስ ውል ተከፋይ የሆነ ገንዘብ የሟች የውርስ ሐብት ክፍል የሚሆነው በመጀመሪያው ሟች "ለወራሾቹ" በሚል መንገድ ኢንሹራንስ ውሉ በተጠቃሚነት የገለፀ ከሆነ መሆኑን ሁለተኛው ሟች የኢንሹራንስ ተጠቃሚ ማን እንደሆነ ሣይገልጽ በቀረ ጊዜ እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ ድንጋጌው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 ንኡስ አንቀጽ 1 ከተደነገገው ጠቅላላ መርህ በተለየ ሁኔታ በህይወት ኢንሹራንስ ውል መሰረት የሚከፈል ገንዘብ በምን ሁኔታ የሟች የውርስ ሐብት ክፍል እንደማይሆንና የሟች ወራሾች የመብት ጥያቄ እንደማያነሱ የሚደነግግ ነው፡፡

ለ/ የንግድ ሕግ ቁጥር 705

የንግድ ሕግ ቁጥር 705 የህይወት ኢንሹራንስ ክፍያ የሟች የውርስ ክፍል ስለሚሆንባቸውን ሁኔታዎች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገጉትን ሁኔታዎች የሚያሰፋ ነው፡፡ ድንጋጌው የሕይወት ኢንሹራንስ ውሉ ለተለየ ተጠቃሚ የተደረገ መሆኑን በማይገልጽበት ጊዜ ብቻ ሣይሆን ሟች የኢንሹራንስን ውሉ ተጠቃሚ ነው ብሎ የገለፀውን ሰው በንግድ ሕግ ቁጥር 703 መሰረት በመሻር ሌላ ተጠቃሚ ያልገለፀ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ወይም ተጠቃሚው ፈቃዱን ሣይገልጽ በመሞቱ ምክንያት ውድቅ በሆነ ጊዜ የኢንሹራንስ ገንዘቡ የሟች የውርስ ንብረት ክፍል እንደሚሆንና ለሟች ወራሾች እንደሚተላለፍ የሚገልጽ ነው፡፡ የንግድ ሕግ ቁጥር 705 "ተጠቃሚው ሣይለይ የተደረገ ኢንሹራንስ" በሚል ርእስ "ተጠቃሚው ተለይቶ ያልታወቀ እንደሆነ ወይም ተሽሮ እንደሆነ ወይም በሕይወት የሌለ በመሆኑ ውድቅ የሆነ እንደሆነ ስለሞት የተደረገው የኢንሹራንስ ዋናው ገንዘብ የሚከፈለው ኢንሹራንሱን ለተዋዋለው ሰው ውርስ ነው" በማለት በግልጽ ይደነግጋል፡፡

ከዚህ በላይ የተደነገጉት የሕግ ድንጋጌዎች የተጠሪ ሞግዚት ሟች ባደረገው የሕይወት ኢንሹራንስ ውል መሰረት አመልካች የተቀበሉት ገንዘብ የሟች ውርስ ክፍል በመሆኑ ለሟች ወራሾች ብቻ ሊከፋፈል ይገባል በማለት የሚያቀርቡትን ክርክር የሚደግፍና የሟች ወራሾች የኢንሹራንስ ተጠቃሚው በኢንሹራንስ ውሉ ተለይቶ ባልተገለፀበት ጊዜ የሚኖራቸውን ሰፊ መብት የሚደነግጉና የሟችን ባል ወይም ሚስት በኢንሹራንስ ገንዘቡ መብት የሌለው መሆኑን የሚያሣዩ ናቸው፡፡

ሐ. የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2

የንግድ ሕግ ቁጥር 701 "ለሞት በሆነ ኢንሹራንስ ተጠቃሚ የሆነ ሰው" በሚል ርእስ ሥር በንኡስ አንቀጽ 2 "ስማቸው በውሉ ላይ ተለይቶ ባይጠቀስም /ሀ/ ጋብቻው የተደረገው የኢንሹራንስ ውሉ ከተፈረመ በኂላ ቢሆን እንኳን የኢንሹራንስ ውል የፈረመው ባል ወይም ሚስት /ለ/ የኢንሹራንስ ውል ሲፈርም የተወለዱት የኢንሹራንስ ውል ፈራሚ ልጆች ተለይተው የታወቁ ተጠቃሚዎች ተብለው ይቆጠራሉ" በማለት ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ ሟች የኢንሹራንስ ውሉን ተጠቃሚ ሣይገልጽ የኢንሹራንስ ውል ባደረገ ጊዜ ከኢንሹራንስ ውሉ ከመፈረሙ በፊት ወይም በኂላ ኢንሹራንስ ውል የተዋዋለው ሰው ጋር በጋብቻ የተሣሰሩ ሚስት ወይም ባልና የኢንሹራንስ ውሉ ሲፈረም ተወልደው የነበሩ ልጆቹ የኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ የሚሆኑ መሆናቸውን የሚደነግግ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የኢንሹራንስ ውል ፈራሚው ባል ወይም ሚስት የሟች ወራሽ ባይሆኑም ተጠቃሚው ተለይቶ ያልተገለፀበት የህይወት ኢንሹራንስ ውል የሕግ ተጠቃሚና ባለመብት እንደሚሆኑና የሟች አንደኛ ደረጃ ወራሾች ከሚሆኑት ከሟች ልጆች መካከል የኢንሹራንስ ውሉ ሲፈረም የተወለዱት የኢንሹራንስ ውሉ የሕግ ተጠቃሚ እንደሚሆኑና የኢንሹራንስ ውሉ ከተፈረመ በኂላ የተወለዱት በዚህ ድንጋጌ መሰረት የተጠቃሚነት መብት የሌላቸው መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 እና የንግድ ሕግ ቁጥር 705 ድንጋጌዎችና የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች እንዲሁ እንዳሉ በአንድ ላይ ተፈፃሚ ለማድረግ በምክር የተለያየ ውጤት የሚያስከትሉ መሆኑን በአመልካችና በተጠሪ መካከል በዚህ መዝገብ የተደረገው ክርክርና ፍርድ ቤቶቹ በየደረጃው የሰጡት ውሣኔ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሟች የሕይወት ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ ሣይገልጽ የገባው የህይወት መድን ገንዘብ የይገባኛል ጥያቄን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 እና የንግድ ሕግ ቁጥር 705 ድንጋጌ ብቻ መሰረት በማድረግ የወሰነው ከፍተኛ ፍ/ቤት የኢንሹራንስ ገንዘቡ ለሟች ወራሾች (ልጆች ብቻ) ይከፋፈል በማለት የወሰነውን ሲሆን በተቃራኒው ጭብጡን የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ብቻ የሚወስን አመልካችና የኢንሹራንስ ውሉ ሲፈረም የተወለደችውን የሟች ልጅ ብቻ የኢንሹራንስ ተጠቃሚ እንደሆኑ የሚወሰንበት ሁኔታ እንደሚኖር ከላይ ይዞታቸውንና ዓላማቸውን በዝርዝር ያየናቸውን ድንጋጌዎች ያላቸውን ልዩነትና የሚያስከተሉት ህጋዊ ውጤት በመመርመር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

4. በዚህ መዝገብ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን እነዚህ ተቃራኒ ይዘትና በተግባራዊ አፈፃፀምም የተለያየ ውጤት የሚያስከትሉ የሕግ ድንጋጌዎች ማለትም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 የንግድ ሕግ ቁጥር 705 እና የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች በምን መንገድ ቢተረጐሙ ሕግ አውጭው

ያሰበውን ግብና ዓላማ ለማሣካትና ሁሉም ድንጋጌዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ ተፈፃሚ ለማድረግ ይቻላል? የሚለውን ጥያቄ በቅድሚያ መመለስ ያስፈልጋል፡፡

በሁለት የሕግ ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና በአንድ ላይ ሲፈፀሙ የሚያስከትሉትን ተቃራኒ ውጤት ለማስቀረት ፍርድ ቤቶች የተለያዩ የሕግ አተረጓጎም መርሆችን በመጠቀም የሕግ ትርጉም በመስጠት ችግሩን የሚያቃልሉ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ከላይ በተገለፁት ድንጋጌዎች በመካከል ያለውን መሰረታዊ ቅራኔ ለመፍታት ሌሎች ድንጋጌዎችን ለማስታረቅ ዘወትር የምንከተላቸው የሕግ አተረጓጎም ዘዴዎች (ጥበቦች) አገልግሎት የሌላቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ፍርድ ቤቶች የዚህ አይነት ችግር ሲያጋጥም የሚከተሉት የሕግ አተረጓጎም ጥበብ አንደኛው ከሁለቱ ሕጐች ማንኛው ቀድሞ እንደታወጀ ማንኛው በኋላ እንደታወጀ በመመርመር በኋላ የወጣው ሕግ ቀድሞ በወጣው ሕግ የተደነገገውን ድንጋጌ እንዳሻሻለው ወይም እንደሻረው ይቆጠራል የሚለውን የሕግ አተረጓጎም ዘዴ በመከተል በኋላ የታወጀውን ሕግ ተፈፃሚ በማድረግ ችግሩን ያቃልላሉ፡፡ በያዝነው ጉዳይ የፍትሐብሔር ሕጉም ሆነ የንግድ ሕጉ በአንድ ቀን ማለትም ሚያዝያ 27 ቀን 1952 ዓ.ም የታወጀ መሆኑን በመግቢያቸው የተገለፀ በመሆኑ ይኸ የአተረጓጎም ዘዴ ከላይ በገለጽናቸው የሕግ ድንጌዎች መካከል ያለውን ልዩነት ለመፍታት የሚያስችለን ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሁለት የሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና በውጤት በአንድ ጉዳይ ልዩነት የሚያስከትል ሲሆን ፍርድ ቤቶች የሚከተሉት ሌላው የሕግ አተረጓጎም ዘዴ ስለ ልዩ ሁኔታ የተደነገገው ድንጋጌ በጠቅላላ የሕግ ድንጋጌዎች ላይ የበላይነትና ተፈፃሚነት ይኖረዋል የሚለው ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 826 ንኡስ አንቀጽ 2 ለተደነገገው መሰረታዊ ጠቅላላ መርህ በልዩ ሁኔታ የተደነገገ ልዩ ድንጋጌ ሲሆን የሕይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ የሟች የውርስ ክፍል የሚሆንባቸውንና የማይሆንባቸውን ልዩ ሁኔታዎች የሚደነግግ ነው፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ የንግድ ሕግ ቁጥር 705 ተጠቃሚው ሣይለይ የተደረገ ኢንሹራንስ የሚመለከት ደንቦችን የያዘ ልዩ ድንጋጌ ሲሆን የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎችም በሞት ጊዜ የሚከፈልና ተጠቃሚው ያልተገለፀበት የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ በልዩ ሁኔታ ባል ወይም ሚስት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን የሚደነግግ ልዩ ድንጋጌ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች አንደኛውን ጠቅላላ የሕግ ድንጋጌ ሌላውን ልዩ የሕግ ድንጋጌ ነው ብሎ ለመፈረጅ የማይቻልና ልዩ የሕግ ድንጋጌ በጠቅላላ የሕግ ድንጋጌ ላይ የበላይነትና ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡ የሚለውን የሕግ አተረጓጎም መርህ ለመከተል የሚያስቸግር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በእኛ በኩል በድንጋጌዎቹ መካከል ያለውን ልዩነት ለመፍታት ሕግ አውጭ እያንዳንዱን የሕግ ድንጋጌ የደነገገው በነባራዊ ህይወት ውስጥ ተፈፃሚ እንደሆነና አንድ ማህበራዊ ችግር እንዲፈታ አስቦ ነው፡፡ ስለዚህ ለአንደኛው የሕግ ድንጋጌ የሚሰጠው የሕግ ትርጉም ሌላውን ድንጋጌ ሙሉ በሙሉ ውጤት አልባ በማያደርግ መንገድና ሁሉም ድንጋጌዎች ውጤታማ የሚሆኑበትን የሕግ አተረጓጎም መከተል አለበት የሚለውን የሕግ አተረጓጎም መርህ ጠቃሚና አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህ አተረጓጎም መሰረት ተጠቃሚው በኢንሹራንስ ውሉ ባልተገለፀበት ጊዜ የሟች ባል ወይም ሚስት የኢንሹራንሱን ገንዘብ ከሟች ወራሾች ጋር የሚካፈሉበትን ልዩ ሁኔታ በመከተል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 የንግድ ሕግ ቁጥር 705 እና የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ/ ድንጋጌዎች በማጣጣም የሟች ወራሾችም ሆኑ የሟች ባል ወይም ሚስት በሕግ የተሰጣቸውን መብት ሙሉ በሙሉ ሣያጡ የኢንሹራንሱ ገንዘብ እንዲካፈሉ በማድረግ ሁሉም የሕግ ድንጋጌዎች ውጤታማ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው ማድረግ የተሻለው የሕግ አተረጓጎም መንገድ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ስለሆነም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 እና በንግድ ሕግ ቁጥር 705 ተጠቃሚው ተለይቶ ባልተገለፁበት የህይወት ኢንሹራንስ ውል መሰረት በሚከፈል የኢንሹራንስ ገንዘብ የመካፈል መብት ያላቸው የሟች ወራሾችና የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሰረት የኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ የመሆን መብት ያላቸው የሟች ሚስት ወይም ባል የኢንሹራንስ ገንዘቡን የመጠየቅ በሕግ እንደ ልዩ ተጠቃሚ የሚቆጠር መብት ያላቸው በመሆኑ አንድ ላይ የኢንሹራንስ ገንዘቡ ተጠቃሚና ተካፋይ ሊሆኑ ይገባል ብለናል፡፡

5. የሟች ወራሾችና የሟች ባልና ሚስት ተጠቃሚው ተለይቶ ያልተገለፁበት የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ የጋራ ተጠቃሚ በሚሆኑበት መንገድ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 የንግድ ሕግ ቁጥር 705 እና

የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ/ መተርጉም ያለባቸው መሆኑ መደምደሚያ ላይ ከተደረሰ በኂላ የሚነሣው ሌላው ጥያቄ የሟች ወራሾችና የሟች ባል ወይም ሚስት የኢንሹራንስ ገንዘቡን በምን ሁኔታ ሊካፈሉ ይገባል የሚለው ነጥብ ነው፡፡ በእኛ በኩል አሁን ባለው የሕግ ሥርአት ሚስት ባሏን ባል ሚስቱን ያለኑዛዜ ለመውረስ የማይፈቀድላቸው መሆኑ ግምት ውስጥ በማስገባት የህይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚውን ሣይገልጽ የተዋዋለው ሟች በኢንሹራንስ ውሉ መሰረት ወቅታዊ ክፍያ ከባለንብረት የተከፈለ መሆኑ ካልተረጋገጠ የባልና ሚስት የጋራ ገቢ ከሆነው ገንዘብ (ደሞዝ) እየቀነሰ ሲከፍል የቆየ ነው የሚል ግምት የመያዝ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የኢንሹራንስ ገንዘቡን ግማሽ የሟች ባል ወይም ሚስት እንዲወስዱ ማድረግና የኢንሹራንስ ገንዘቡን ግማሽ የሟች ወራሾች ተካፍለው በመውሰድ የሟች የውርስ ሐብት ክፍል በማድረግ በውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት የሚደርሳቸውን ድርሻ የሚካፈሉበትን ሁኔታ መከተል ከሌሎች አማራጮች የተሻለና ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 የንግድ ሕግ ቁጥር 705 እና በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ/ ሕግ አውጭው ሲደነግግ የነበረውን ሐሳብና ግብ ለማሣካት የሚያስችል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም የአመልካችና የተጠሪ ክርክርም ከላይ በዝርዝር ያስቀመጥነውን የሕግ አተረጓጉም በመከተል መፍታት ሲገባቸው የከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ለአመልካች በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ/ የተረጋገጠላትን መብት ሙሉ በሙሉ ዋጋ በሚያሣጣ ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 በመተርጉም የኢንሹራንስ ገንዘቡ የሟች የውርስ ክፍል ስለሆነ አመልካች መብት የላትም፡፡ የኢንሹራንስ ገንዘቡን የሟች ልጆችና ወራሾች ብቻ እኩል ይካፈሉ በማለት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ- ሥርአት ሕግ ቁጥር 348/1/መሰረት በማሻሻል አመልካች ከሟች ልጆችና ወራሾች ጋር የኢንሹራንስ ገንዘቡ ተጠቃሚ የመሆን መብት አላት በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ በሆነው 166,449.97(አንድ መቶ ስልሣ ስድስት ሺ አራት መቶ አርባ ዘጠኝ ) የአሜሪካን ዶላር ከጠዘና ሰባት ሳንቲም በተመለከተ የሟች ሚስት የሆኑት አመልካችና የሟች ልጆች ወራሽ የሆኑት ሕፃን ኬሩዝ ተክሉና ህፃን ፌኔት ተክሉ በሕግ ጥበቃ የተሰጠው መብትና ጥቅም አላቸው ብለናል፡፡
3. አመልካች የኢንሹራንስ ገንዘቡን ግማሹን ብር 83,224(ሰሚኒያ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሃያ አራት) የአሜሪካን ዶላር ይውሰዱ ብለናል፡፡
4. የሟች ልጆች ወራሾች የሆኑት ህፃን ኬሩዝ ተክሉና ህፃን ፌኔት ተክሉ(ተጠሪ) ቀሪውን 83,224(ሰማኒያ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሃያ አራት) የአሜሪካን ዶላር እኩል ይካፈሉ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 44025

ሐምሌ 22 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች**፡- 1. ወ/ሪት ፀሃይ ሃይሌ - ቀረበች

2. ወ/ሪት ጤናዬ ሃይሌ - ቀረበች

3. ወ/ሪት ኤልሳቤጥ ሃይሌ - አልቀረበችም

4. መስፍን ሃይሌ - አልቀረቡም፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ፈልቃ ቤኛ - ጠበቃ ሙላት ፈለቀ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 65587 ጥር 15 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ክርክሩ በአሁኖቹ አመልካቾች ከሣሽነት የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካቾች ተጠሪን የከሰሱት ከአባታችን ልናገኝ የሚገባውን የውርስ ድርሻ ይዛ እየተጠቀመች ስለሆነ ውርስ አጣሪ ተሾሞ ድርሻችን እንዲለይ ይታዘዝልን በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ለክሱ በሰጠችው ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበች ሲሆን፣ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን በመቀበል ክሱን ውድቅ አድርጐአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቾች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረባቸው ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካቾች የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚሉበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካቾች የቀረበው የውርስ ይጣራልን ክስ /ጥያቄ/ በይርጋ ቀሪ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ የአመልካቾች አባት ሚስት ናት፡፡ የአመልካቾች አባት እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ አመልካቾች በዚሁ የአባታቸው እና የተጠሪ የጋራ ነው የተባለው ቤት ውስጥ በአባታቸው እና በተጠሪ ሲያድጉ ቆይተዋል፡፡ አባታቸው ከሞቱም በኋላም ተጠሪ እንደእናት በመሆን ስታሳድጋቸው እንደቆየች እና ንብረቱንም በጋራ ይዘው ሲያስተዳድሩት እንደነበር አመልካቾች በክርክራቸው ገልጸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት እንዲለይ እና የአባታቸውን ድርሻ በወራሽነታቸው ማግኘት ይችሉ ዘንድ ክስ የመሰረቱት ተጠሪ እነሱ ባላወቁት ምክንያት ከቤት ወጥታ በመሄድ ዘመዶቼናቸው ከምትላቸው ሰዎች ጋር በመቀመጥዋ እንደሆነ በሰበር አቤቱታቸው ላይ በግልጽ በማመልከት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪም ለሰበር አቤቱታው በጽሑፍ መልስ የሰጠች ሲሆን በአመልካቾች ክርክር በግልጽ በተነሱት ነጥቦች ላይ ምንም ማለት አልቻለችም፡፡ በዚህ ረገድ የመረጠችው በዝምታ ማለፍ ነው፡፡ በእርግጥ ከዚህ በፊት በሰበር ችሎቱ የተሰጡትን ውሳኔዎች በመጥቀስ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ትክክል ነው እንዲባልላት ተከራክራለች፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ችሎቱ ከጠበቃው ላቀረበው ጥያቄ ከተሰጠው ምላሽ ተጠሪዎች በፍሬ ነገር ረገድ ያነሱት ክርክር ትክክል እንደሆነ ለማረጋጥ ችለናል፡፡ የተጠሪ ጠበቃ ለቀረበለት ጥያቄ በሰጠው መልስ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ንብረቱ/ቤቱ/ በአመልካቾች ይዞታ ሥር እንደሆነ አረጋግጦአል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካቾች የውርስ ድርሻ የጠየቁበት ንብረት ሁለቱም ወገኖች ይዘውት በጋራ ሲያስተዳድሩት የነበረ በመጨረሻም (ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ) በአመልካቾች ይዞታ ሥር ያለ ነው፡፡ አመልካቾች ወደ ክስ ያመሩትም ንብረቱ በዚህ ደረጃ ላይ እንዳለ ተጣርቶ የአባታቸው ድርሻ እንዲታወቅና ወራሽነታቸው ለእነሱ እንዲሆን እንዲወሰንላቸው እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ እውነታው ይህ ከሆነ ደግሞ ንብረቱ በተጠሪ እጅ (ተይዞ) እንደቆየ በማድረግ የተጠሪን የይርጋ መቃወሚያ ተቀባይነት ይኖረዋል የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪ የሰበር ችሎቱ በሰበር መ/ቁ. 24675 እና 28317 የሰጣቸውን ውሳኔዎች በመጥቀስ ያቀረበችው ክርክርም እንዳየነው ውሳኔዎቹ የተሰጡት በዚህ መዝገብ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር የተለየ በሆነ ፍሬ ነገር ላይ በመመስረት በመሆኑ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካቾች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል፡፡ በማለት የወሰኑት በፍትሐብሔር ሕጉ የተቀመጠውን የይርጋ ድንጋጌ እና የይርጋ መሰረተ ሃሳብ እንዲሁም የክርክሩን ፍሬ ነገር እግንዛቤ ውስጥ ባለማስገባት በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 108209 የካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 65587 ጥር 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩ በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግና ወደ ጉዳዩ ሥረ-ነገር በመግባት ግራ ቀኝ ወገኖችን በማከራከር ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሰረት ይመለስለት ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 47622

ሐምሌ 30 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ትእግስት ነጋሽ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ መንበረስላሴ ተኸሌ ለሁሉም - ጠ/ፈቃዱ ሞላ ቀረቡ

2. አቶ ሃብታሙ ነጋሽ

3. አቶ አሰፋ ነጋሽ

4. ወ/ት መሳይ ነጋሽ

5. አቶ ደሳለኝ ነጋሽ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የውርስ ሃብት ለመካፈል የቀረበን ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የሟች አባታቸው አቶ ነጋሽ ደሳለኝ ወራሽ መሆናቸው ገልጸው የሟችና የአንደኛ ተጠሪ የጋራ ሃብት የሆነ ቤት ከነሰርቪሱና ሌሎች ንብረቶችን አንደኛ ተጠሪ ስለያዙ ውርስ እንዲጣራ አመልክተው ተጠሪዋ የአመልካችን ልጅነት ሳይክዱ ሟች በሰጡት ኑዛዜ አመልካች እንዲያገኙ ከተናዘዙት ብር 5,000(አምስት ሺህ) ውጪ ሊጠይቁ አይችሉም ብለው የተቃወሙ ሲሆን ሟች በቤቱና በሰርቪሱ እንዲሁም በቤት ቁሳቁስ ላይ ያላቸውን ድርሻ አንደኛ ተጠሪ በስማቸው አዛውረው እንዲጠቀሙና እሳቸው ስለሞቱ ንብረቱ በሙሉ ለቀሪዎቹ ተጠሪዎች እንዲተላለፍ ተናዘዋል፡፡ ሟች ለአመልካች ብር 5,000(አምስት ሺህ) ከመስጠት በቀር እንደሌሎቹ ልጆች አላካፈሉኝም፡፡ ከኑዛዜው ነቅለውኛል፡፡ በመሆኑም ኑዛዜው ሊፈረስ ይገባል በማለት አመልክተዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ ጥያቄው ከ3 ወር በኋላ የቀረበ በመሆኑ ይርጋ ያግደዋል፣ ኑዛዜው ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ነው፣አመልካች ብር 5,000(አምስት ሺህ) ስለተሰጣቸው ከውርስ አልተነቀሉም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆንላቸው ጠይቀዋል፡፡ ቀሪዎቹም ተጠሪዎች ወደክርክሩ ጣልቃ ገብተው ባቀረቡት ክርክር ጥያቄው በይርጋ ቀሪ ነው፣ድርሻ አንሶኛል ለምትለው ድርሻዋን ለማወቅ የውርስ አጣሪ ስለተሾመ የአጣሪውን ሪፖርት መጠበቅ ግድ ይላል፣ውርስ የመጣራቱ ሂደት እስኪጠናቀቅ መዝገቡ ተዘግቶ ይቆይ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ተመልክቶ የይርጋ መቃወሚያው ውድቅ ካደረገ በኋላ ኑዛዜው ለአመልካች በግልጽ 5,000(አምስት ሺህ) ይከፈላት ስለሚል ለመፈፀም የሚቻል ነው፣በኑዛዜው ስጦታ ስለተደረገላቸው ተነቅያለሁ ማለት አይችሉም፣ሟች ለወራሾቻቸው በፈለጉት መጠን ሃብታቸውን በኑዛዜ ማከፋፈል ይችላሉ፣ስለሆነም ኑዛዜው የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጐ አመልካች ለአንደኛ ተጠሪ ብር 5,000(አምስት ሺህ) የጠበቃ አበል እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ጠበቃ አበል እንዲከፍሉ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ብቻ ለመመርመር ሲያስቀርብ ኑዛዜውን በተመለከተ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበውን ይግባኝ ግን ውድቅ አድርጐታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው፣በኑዛዜው የተመለከተው ድርሻ ማነሱን፣ገንዘቡ ከየትኛው ሃብት ላይ እንደሚከፈልና ማን እንደሚከፍል ስለማያመለክት ለመፈፀም የሚቻል እንዳልሆነ፣ ያለምንም ህጋዊ ምክንያት ከኑዛዜ የተነቀሉ መሆኑን ገልጸው ኑዛዜ እንዲፈረስ ያቀረቡት ክስ ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም፣በማለት ውሳኔ እንዲሻርላቸው ጠይቀዋል፡፡ ችሎቱም ይህን የአመልካች አቤቱታ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪዎችም በሰጡት የፁሁፍ መልስ፤ሟች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 920 በሚፈቅደው መሰረት የጋራ ሃብት ድርሻቸውን አንደኛ ተጠሪ በሕይወት እያሉ ወራሾች እንዳይካፈሉ አግደዋል፣ከ2-5 ያሉት ተጠሪዎች ከአንደኛ ተጠሪ የተወለዱ በመሆኑ ተጠሪዋ በህይወት እያሉ እንደማይጠይቁ በመገመት ለአመልካች ብር 5,000(አምስት ሺህ) ሰጥተዋል፣በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የሕግ ስህተት ስለሌለው ውሳኔው እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ሟች አባታቸው በተውት ኑዛዜ ለልጆቻቸው ያደረጉት ክፍፍል ከማነሱም በላይ ያለምንም ምክንያት ከውርስ የነቀሏቸው በመሆኑ ኑዛዜው እንዲሻርላቸው ነው፡፡ ከውርስ ተነቅያለሁ የሚለውን በተመለከተ በኑዛዜው አመልካች ብር 5,000(አምስት ሺህ) የተሰጣቸው መሆኑን አመልካችም አልካዱም፡፡ ክርክራቸው አነስተኛ ድርሻ ማግኘታቸው ከውርስ ሃብት እንደተነቀሉ የሚያስቆጥር መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን ከውርስ መነቀል ማለት ደግሞ ከውርስ ሃብቱ ምንም አይነት ድርሻ አለማግኘት እንጂ አነስተኛ ድርሻ ማግኘት ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ሟች የውርስ ሃብት ክፍፍል ሲያደርጉ ለአመልካች ከሚገባቸው በላይ አሳንሰው ሰጥተዋቸዋል የሚል ክርክር ያቀርባሉ፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.913 የኑዛዜ ቃል የተናገዙን ተቃራኒ ሃሳብ የሚገልጽ ካልሆነ በቀር በውርስ ሃብት አንድ ድርሻን ወይም አንድ ንብረትን ሟቹ ለወራሾቹ መስጠቱ ተራ የሆነ የክፍያ

ደንብ እንጂ እንደ ኑዛዜ ስጦታ እንማይቆጠር ያመለክታል፡፡ ይህ ድንጋጌ በኑዛዜ የኑዛዜ ስጦታ (legacy) እንዲሁም የክፍያ ደንብ (rule of partition) ማድረግ እንደሚቻል የሚናገር ነው፡፡ በመርህ ደረጃ አንድ ሰው ከውርስ ሃብት መካከል አንድን ንብረት ለወራሾቹ መስጠቱ የኑዛዜ ስጦታ አያስኘውም፡፡ ይልቁንም ይህ አይነት ኑዛዜ ሕጉ የሚቀበለው እንደ አንድ የክፍያ ደንብ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ወራሽ ለወራሹ አንድን ሃብት ሲናዘዝ የኑዛዜው አፈፃፀም የስጦታ(legacy) አፈፃፀምን በመከተል ሳይሆን የክፍያ ደንብን (partition) በመከተል የሚከናወን ነው፡፡ የክፍያ ደንብ የሚከናወነውም ከአንቀጽ 1117 ጀምሮ ባሉት ድንጋጌዎች ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ይህ የሰበር ችሎት በመ/ቁ. 18394 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ አመልካች የሟች ልጅ በመሆናቸውም ለእርሳቸው የተሰጠው ብር 5,000(አምስት ሺ.ህ) ከፍ ሲል በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት የክፍያ ደንብ ነው፡፡ ምንም እንኳን ሟች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1017 መሰረት ውርስ ሃብታቸውን በሚፈልጉት መልክ መደልደል ቢችሉም ድልድል ሲያደርጉ ግን አንድ ተወላጅ ከሚደርሰው ከሩብ የበለጠ ጉዳት ደርሶበት ከሆነ ክፍፍሉ እንዲቀር ጥያቄ ማቅረብ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1123/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ቢሆን ሟች ሃብታቸውን በሙሉ አንደኛ ተጠሪ በሕይወት እስካሉ እንዲጠቀሙበትና ከእሳቸው ህይወተ-ህልፈት በኋላ ግን ሃብቱ በሙሉ ለሌሎች ልጆች እንዲሰጥ ተናዘዋል፡፡ ለአመልካች እንዲሰጣቸው የተናዘዙት ብር 5,000(አምስት ሺ.ህ) ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የሟቹ ድርሻ ንብረታቸው ተጣርቶ አመልካች ሊደርሳቸው ከሚገባው ከሩብ የበለጠ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ አለመሆኑ ሊረጋገጥ ይገባ ነበር፡፡ ከ2 እስከ 5 ያሉት ተጠሪዎችም ቢሆኑ በስር ፍ/ቤት የአመልካች ድርሻ እንዲታወቅ ውርሱ ሊጣራ እንደሚገባ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት ግን አመልካች የደረሰባቸው ጉዳት ምን ያህል መሆኑን ሳያጣራ አመልካች ብር 5,000(አምስት ሺ.ህ) የተሰጣቸው በመሆኑ ከኑዛዜ አልተነቀሉም በሚል ብቻ ጥያቄውን ውድቅ አድርጐታል፡፡ ምንም እንኳን አመልካች ከውርስ ተነቅያለሁ የሚል ክርክር ቢኖራቸውም በተጨማሪ ግን በክፍፍሉ ድርሻቸው ያለአግባብ ማነሱንና ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን የሚያሳይ ይዘት ያለው ክርክር አቅርበዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት አመልካች አልተነቀሉም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ ቢሆንም የአመልካችን የክፍያ ደንብ ጥያቄ ሳይመረምር አልፎታል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት አመልካች ክፍያውን በተመለከተ ያቀረቡት ጥያቄ ሳይመረምር ማለፉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ተከታዩ ውስኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 145134 ሰኔ 5 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 82145 ሐምሌ 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የሟች የአቶ ነጋሽ ደሳለኝ የውርስ ሃብት እንዲጣራ አድርጐ አመልካች የደረሰባቸውን ጉዳት ካረጋገጠ በኋላ የኑዛዜውን ውጤት አስመልክቶ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 45587

ሐምሌ 29 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሓጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** እነ ወ/ሮ አተረፈች ዘውዴ - ወኪል ዶ/ር ደረጀ አሻጋሪ - ቀረቡ

ስለ ሁለተኛ አመልካች ጠበቃ ወኪል እስራኤል ተክሌ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ዘውዱ ወሰኔ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ሳይናዘዝ የሞተ ሰው ውርስ ተጠቃሚዎችን በሚመለከት በሕጉ ያለውን ቅደም ተከተልና አፈፃፀሙን የሚመለከቱትን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎችን ትርጉም የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ የሟች ወ/ሮ አያልነሽ ዘውዴ ወራሽ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ መያዛቸውንና የሟቿ ንብረቶች በተጠሪዎች መያዛቸውን ገልጸው ውርስ እንዲያጣራላቸው የውርስ አጣሪ በፍርድ ቤት እንዲሾምላቸው ህዳር 24 ቀን 2001 ዓ.ም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾችም በስር ፍርድ ቤት ቀርበው ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃውን ያገኙት የሟች እህትና ወንድም መኖራቸውን በመደበቅ በመሆኑ የወራሽነት ማስረጃው ተቀባይነት የለውም በማለት የተጠሪ የውርስ አጣሪ ይሾምልኝ ጥያቄ ወድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዮን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለተው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙ ከሟች ጋር ያላቸውን የዝምድና ደረጃ በማጣራት ተጠሪ የሟች እናት እህት ልጅ ስለሆኑ ሟችን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 842 እና ተከታዮቹ መሠረት ሊወርሱ ይችላሉ ወደ ሚለው ድምዳሜ በመድረስ የሟች ወ/ሮ አያልነሽ ዘውዴ የውርስ ሐብት እንዲጣራ በማለት አዟል፡፡ በዚህ ፍርድ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ አመልካቾች ተጠሪ ያገኙትን የወራሽነት ማስረጃ ሳያስርዙ የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄን መቃወም እንደማይችሉ ገልፆ ውርስ አጣሪው በፍርድ ቤት እንዲሾም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው በማለት የይግባኝ ባዩችን ቅሬታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሚያዝያ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቀርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 843 እና 844(3) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካቾች የሟች ወንድምና እህት ተጠሪ ደግሞ የሟች እናት እህት ልጅ ስለሆኑ ውርሱ ሊጣራ ይገባል ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ የጽሁፍ መልሳቸው እንዲያቀርቡ በችሎት ተነግሯቸው ከሄዱ በኋላ በተሰጣቸው ቀነ ቀጠሮ ሳያቀርቡ በመቅረታቸው በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ የሟች እናት እህት ልጅ በመሆን የሟች ወንድም እና ልጅ እያሉ ሟችን ሊወርሱ ? ይችላሉ? ወይስ አይችሉም? የሚለው ጭብጥ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የሟች ወራሽነታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ከተገቢው ፍርድ ቤት ካገኙ በኋላ የሟች ውርስ ንብረት እንዲጣራላቸው ለስር ፍርድ ቤት አቤቱታ ሲያቀርቡ አመልካቾች የሟች እህትና ወንድም እያሉ ተጠሪ ሊወርሱ አይችሉም በማለት የውርስ ማጣራት ሂደት እንዳይጀመር ተቃውሞ ማንሳታቸውን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ተቃውሞ ሳይቀበለው የቀረው ተጠሪ የሟች እናት እህት ልጅ ስለሆነ በተተኪነት ወራሽ ሊሆኑ ይችላሉ በሚል ምክንያት ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ ተመልክቷል፡፡

በመሰረቱ በውርስ ህጋችን ውስጥ ያሉት ደንቦች ሳይናዘዝ የሞተ ሰው ወራሾች በቀጥታ ከሟች ውርስ ተካፋይ ሊሆኑ የሚችሉ የሟች የስጋ ዘመዶች እና እነዚህ ወገኖች ከሌሉ እነዚህን ወገኖች በመተካት የሚወርሱ ወገኖች በሚል በሁለት መንገዶች ከፍለው ያስቀምጣሉ፡፡ በሌላ አገላለጽ የሟች የስጋ ዘመዶች በሟች ውርስ ሊካፈሉ የሚችሉት በቀጥታ ወራሽነት ወይም በተተኪነት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 842 ተከታዩቹ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ሕጉ የሟችን ወራሾች ቅደም ተከተል አስቀምጧል፡፡ የሟቹ የመጀመሪያ ወራሽ የሟች ልጆች እንደሆኑ ሕጉ በአንቀጽ 842 ስር በግልጽ ያስቀመጠ ሲሆን የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ከሌለ የሟች ንብረት ለሁለተኛ ደረጃ ዘመዶች እንደሚተላለፍ እነዚህ ሁለተኛ ደረጃ ዘመዶች የሚባሉበትም የሟች እናትና አባት

መሆናቸውን የሟች አባትና እናት ሟችን ቀድሞ ከሞቱ የእነርሱ ተወላጆች ማለትም የሟች ወንድምና እህት ወይም የወንድሞቹና የእህቶቹ ተወላጆች እናትና አባቱን በመተካት በሟች ውርስ እንደሚካፈሉ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 843 እና 844 ድንጋጌዎች ይዘት የሚያሳየን ጉዳይ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 844(3) ድንጋጌ ከሟች እናት እና አባት በአንዱ መስመር ወራሽ ቢታጣ የሟች ውርስ ወደ ሌላው መስመር በሙሉ ሊተላለፍ እንደሚችል ደንግጓል፡፡ ከእነዚህ የሕጉ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ተተኪ ወራሽነት የተፈጻሚነት ወሰን ወደታች በሚቆጠሩ ተወላጆች እንጂ ወደ ጎን በሚቆጠር ዝምድና ትስስር አለመሆኑን ነው፡፡ ይህ ችሎትም የድንጋጌዎቹ አፈፃፀም በዚህ መልኩ ስለመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 47957 በቀረበው ተመሣሣይ የህግ ክርክር ከአዋጅ ቁጥር 454/97 በየትኛውም እርከን የሚገኘውን ፍርድ ቤት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካቾች የሟች ወ/ሮ አያልነሽ ዘውዴ እህቶች ናቸው ሟች ሌሎች እህትና ወንድሞች ያላቸው መሆኑንም ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ የሟች እናት እህት ልጅ መሆናቸውን በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጅ ሳይሆኑ የሟች እናት እህት የሆኑት (የሟች አክስት) ልጅ ሲሆኑ የተጠሪ እናት ወደ ጐን የሚቆጠሩ የሟች የስጋ ዘመድ ናቸው፡፡ በዚህ አግባብ የሚቀርብ የወራሽነት ጥያቄ ምላሽ የሚያገኘው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 843 እና 844 ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ ሟች ወ/ሮ አያልነሽ ዘውዴ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ (ልጅ) የሌላቸው ሲሆን እነዚህ ወገኖች አለመኖራቸው ከተረጋገጠ የሟችን ውርስ ሊወስዱ የሚገባቸው የሟች እናት እና አባት ሲሆኑ በውርሱ የሚካፈሉት በሁለተኛ ደረጃ ወራሽነት ነው፡፡ የሟች እናት እና አባት በሕይወት አለመኖራቸው የተረጋገጠ ሲሆን እነዚህ ወገኖች ሳይኖሩ ሲቀሩ በሟች ውርስ ሊካፈሉ የሚገባቸው የሟች እህትና ወንድሞች ናቸው፡፡ የሟች እህትና ወንድሞች ሟችን የሚወርሱት ደግሞ ወላጆቻቸውን ተክተው ነው፡፡ የሟች እናት ወደታች የሚቆጠር ሌላ ልጅ አልተዉም፡፡ ለሟች እህትና ወንድም ያሉት በአባት መስመር ብቻ ስለመሆኑ ተጠቅሷል፡፡ እንዲህ ሲሆን የሟች ውርስ ተጠቃልሎ የሚሄደው በአባታቸው ልጆች በኩል እንጂ ሟችን ወደ ጎን በሚቆጠሩ የአሁኑ ተጠሪ እናት ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 843 እና 844 ድንጋጌዎችን አፈጻጸም በሚገባ ሳይለይ በደፈናው ተጠሪ ተተክተው ሟች ወ/ሮ አያልነሽን መውርስ ይችላሉ በማለት የደረሰበት ድምዳሜ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ወራሽ ሊሆን የማይችል ሰው ደግሞ የሟች ውርስ ንብረት ይጣራልኝ የሚልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከመነሻውም የሟች ውርስ እንዲጣራላቸው ይዘው የቀረቡት ማስረጃ ሕጋዊ ባለመሆኑ የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታውን ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም አልነበራቸውም ለማለት የሚያስችል ነው፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተጠሪ የያዙት የወራሽነት ማስረጃ በማስረጃነቱ በማንኛውም የክርክር ደረጃ ተቃውሞ የሚቀርብበት ሆኖ እያለ ማስረጃው ባልተሰረዘበት ሁኔታ አመልካቾች የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ሊከራከሩ አይችሉም ሲል የአመልካቾችን ይግባኝ ሳይቀበል ማለፉና የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆ5ኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 132791 ጥር 21 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 77713 መጋቢት 21 ቀን 2001 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ የሟች ወ/ሮ አያልነሽ ዘውዴ እናት እህት ልጅ በመሆናቸውና ሟች ደግሞ እህትና ወንድም ያላቸው በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 843 እና 844 መሠረት ተተኪ ወራሽ ሊሆኑ አይችሉም የሟች ውርስ ይጣራልኝ በማለት አቤቱታ ለማቅረብም መብትና ጥቅም የላቸውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፀ/መ

የሰ/መ/ቁ.42546

ሀምሌ 28 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ተስፋልደት ኪዳኔ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ ዘሀቡ ይመር

2. አቶ ፀጋዬ ኪዳኔ የሶስቱም

3. አቶ ገብረህይወት ኪዳኔ

(ተጠሪዎች 1–3) ጠበቃ አቶ ዘመነ ፍቅሬ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>**ፍ ር ድ**</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የአመልካችና የተጠሪዎች የክርክር መነሻ አቶ ኪዳኔ ንዎቱ በህይወት በነበሩበት ጊዜ አድርገውታል የተባለውን ኑዛዜ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ተጠሪዎች ሟች ኪዳኔ ንዎቱ ጥር 30 ቀን 1984 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ አለ በማለት ለቀድሞው ልደታ አውራጃ ፍርድ ቤት በማቅረብ ሚያዝያ 24 ቀን 1984 ዓ.ም አስወስነዋል፡፡

የአሁን አመልካች ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሟች አድርገውታል የተባለው ኑዛዜ ስለ ግልፅ ኑዛዜ አደራረግ የተደነገገውን መሥፈርት የማያሟላ ሟች ካሏቸው ወራሾች ልጁና ወራሹ የሆንኩትን እኔን አመልካችን የረሣና የእኔን መብትና ጥቅም የሚጎዳና በዝምታ የሚነቅል ትክክለኛ የሟች ኑዛዜ ሣይሆን የሀሰት ሰነድ በመሆኑ ከዚህ በፊት የልደታ አውራጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 631/84 ሚያዝያ 24 ቀን 1984 ዓ.ም ኑዛዜው ህጋዊ መሆኑን በማረጋገጥ የሰጠው ውሣኔ ይሰርዝልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሟች ጥር 30 ቀን 1984 ዓ.ም አደረጉት የተባለው ኑዛዜ ራሳቸው የፃፉት ወይም እርሳቸው እየተናገሩ ሌላ ሰው የፃፈው መሆኑን አይገልፅም፡፡ ኑዛዜው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 ንዑስ አንቀፅ 2 ፎርማሊቲ የማያሟላ ስለሆነ ፈራሽ ነው በማለት የአውራጃው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሰርዟል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ኑዛዜው "እኛም ከላይ በስም የተገለፅነው አቶ ኪዴኔ ንዎቱ ክፍሌ ሀብትና ንብረታቸውን ለ…. በኑዛዜ ሲሰጡ አይተንና ሰምተን ፈርመናል" የሚል ሀረግ ያለው መሆኑን በመግለፅ ኑዛዜ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 የተደነገገውን መሥፈርት ያሟላል በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ የህግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የሌለበት መሆኑን በመግለፅ ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ- ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ጥር 5 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች የኑዛዜ ተጠቃሚና ወራሽ መሆናቸውን ለማስረዳት ያቀረቡት ኑዛዜ ትክክለኛ ሰነድ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች በኑዛዜው ላይ በምስክርነት የተገለፁትን ሰዎች በፍርድ ቤት በማስረጃነት ያላቀረቡት ኑዛዜው በሀሰት የተዘጋጀ መሆኑን ያሣያል፡፡ ኑዛዜው ህጋዊ ነው ቢባል እንኳን ሟች ያለምንም ምክንያት እኔን ከውርሱ የሚነቅል ኑዛዜ በማድረግና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 938 መሠረት ከውርስ የነቀለበትን ምክንያት ስላልገለፀና ኑዛዜው የሟች ወራሽ የሆንኩት የረሣና ጉዳት ያደረሰብኝ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1123 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ፈራሽ ሊሆን ይገባል በማለት ያቀረብነው ክርክር አላግባብ የታለፈብኝ በመሆኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው 1984 ዓ.ም በፍርድ ቤት ታይቶ ህጋዊነቱ የተረጋገጠውን ኑዛዜ አመልካች ኗሪነታቸው በውጭ አገር ነው በማለት ኑዛዜውን በሌለንበት ለማስፈረስ ያደረጉትን ጥረት ዘርዝረን ያቀረብነውን ይግባኝ የከፍተኛው ፍረድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ ኑዛዜው የህጉን ፎርም ያሟላ ነው አመልካች የሚያቀርቡት ክርክር የህግ መሠረት የለውም የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1123 በመጥቀስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የፅሑፍ የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ሟች አቶ ኪዳኔ ንዎቱ ጥር 30 ቀን 1984 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በተጠሪዎች የሚያስገኘውን መብትና በአመልካች የወራሽነት መብት ላይ የሚኖረው ውጤት ምንድን ነው? የሚለውን ጭብጥ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር ማገናዘብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. አመልካች ሟች አቶ ኪዳኔ ንዎቱ ያደረጉት ግልፅ ኑዛዜ በሀሰት የተዘጋጀ ነው፡፡ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 881 ፎርማሊቲ አያሟላም በማለት ያቀረቡት ክርክር ማስረጃ የመመዘንና ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች የአመልካችንና የተጠሪን ማስረጃዎችና የኑዛዜ ሰነዱን በመመርመር ኑዛዜው ህጋዊ ፎርማሊቲዎችን

የሚሉና የሟች ያደረጉት ትክክለኛ ኑዛዜ መሆኑን በማረጋገጥ ውሣኔ ሰጥተውበታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር የቀረበውም የኑዛዜውን ትክክለኛነትና ህጋዊ መስፈርት ያሟላ መሆኑን በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ሣይሆን ኑዛዜው የሚያስከትለውን ውጤት አግባብነት ካላቸው የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ውሣኔ ለመስጠት ነው፡፡ ስለሆነም በማለት በሰበር የሚያቀርበው ክርክር ህጋዊ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

2. ሟች ጥር 30 ቀን 1984 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ትክክለኛና የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 881 ድንጋጌዎች መስፈርት የሚያሟላ ሰነድ ነው፡፡ ሆኖም ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በባህሪው የተለያዩ የህግ ጥያቄዎችን የሚያስነሣ ይዘት ያለውና የሟች ኑዛዜ በህግ ረገድ የሚያስከትለው ውጤት ምንድን ነው? የሟች ኑዛዜ ተፈፃሚነትስ በምን መንገድ መሆን አለበት የሚሉትን ጥያቄዎች የሚያስነሣ ነው፡፡

ሟች ጥር 30 ቀን 1984 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ መሠረታዊ ይዘት ሲታይ "እኔ አቶ ኪዳኔ ንዋቱ ክፍል በአዲስ አበባ ከፍተኛ 24 ቀበሌ 13 የቤት ቁጥር 1370 ነዋሪ የሆንኩ በሰው ልጅ ላይ በመኖር መሞትም ስላለ ሐብትና ንብረቴን በሙሉ ለግል ቤቴ ወ/ሮ ዘሀቡ ይመር ቸኮልና ልጆች 1/ አቶ ፀጋይ ኪዳኔ ንዎቱ 2/ አቶ ገብረህይወት ኪዳኔ ንዎቱ በእኔ ስም ያለውን ሀብትና ንብረቴን በሙሉ ለልጆችና ለባለቤቴ የሰጠኋቸው በመሆኔ በትክክል አእምሮዬ አስቤ የተናዘዝኩ ስለሆነ ከእነዚህ ሌላ በእኔ ንብረት ተጠቃሚ እንደሆኑ ያልፈቀድኩና ሐብትና ንብረቴም ወራሾች መሆናቸውን አረጋግጨ ተናዝዣለሁ የሚል ነው፡፡

ይኸ የሟች ኑዛዜ መሠረታዊ ዓላማው የሟች ንብረት ወራሾች በኑዛዜው ውስጥ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪዎች ብቻ መሆናቸውን ማረጋገጥ መሆኑን በኑዛዜው ውስጥ "ከእነዚህ ሌላ በእኔ ንብረት ተጠቃሚ እንደሆኑ ያልፈቀድኩና የሐብትና ንብረቴ ወራሾች መሆናቸውን አረጋግጨ ተናዝዣለሁ፡፡ በማለት ካደረጉት የኑዛዜው ማደማደሚያ ሀረግ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሟች በኑዛዜው የንብረታቸው ጠቅላላ ወራሾች ተጠሪዎች ብቻ እንደሆኑ ሀሳብና ፍላጎት የነበራቸው መሆኑንና በኑዛዜው ውስጥ ስማቸው ያልተገለፁ ሌሎች የሟች የህግ ወራሾች በውርሣቸው ተካፋይ እንዳይሆኑ እንደሚፈልጉ ከእነዚህ ሌላ በእኔ ንብረት ተጠቃሚ እንደሆኑ ያልፈቀዱ መሆኑን በመግለፅ ኑዛዜ ትተው አልፈዋል፡፡

አመልካች የሟች አቶ ኪዳኔ ንዎቱ ልጅና ወራሽ መሆናቸውን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መጋቢት 26 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በማስረጃነት አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች ይኸንን የአመልካች በፍርድ የተረጋገጠ ወራሽነት የሚያስቀርና ፍርዱ የተሰረዘ ወይም የተሻረ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ከሰጡት ውሣኔ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይኸም ሟች ጥር 30 ቀን 1984 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 842 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የሟች ልጅና አንደኛ ደረጃ ወራሽ መሆናቸው በፍርድ በተረጋገጠው በአመልካች የወራሽነት መብትና ከሟች ውርስ ንብረት ድርሻቸው እንዲሰጣቸው በሚያቀርቡት ጥያቄ ላይ ምን ህጋዊ ውጤት ያስከትላል? የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ሟች በኑዛዜው ስማቸው ከተጠቀሱት ውጭ ያሉ ወራሾች በውርሳቸው እንዲካፈሉ ያልፈቀዱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይኸም ሟች በስም ሣይጠቅሱ ከተጠሪዎች ውጭ ያሉ ያለ ኑዛዜ ወራሾች በሙሉ በውርሳቸው እንዳይካተት ግልፅ በሆነ ቃል በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 937 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ መሠረት ለመንቀል ኑዛዜ ያደረጉ መሆናቸውን ያስረዳል፡፡ ሟች ከተጠሪዎቹ ውጭ ያለ ኑዛዜ ወራሽ ነኝ ብሎ በውርሱ ተካፋይ ለመሆን የሚመጣ ማንኛውም ወራሽ ከውርሣቸው እንዲሣተፍ ፈቃድ የሌላቸው መሆኑን በመግለፅ አመልካችን በቀጥታ ስማቸውን በመጥቀስ ሣይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ከውርስ ለመንቀል ኑዛዜ አድርገዋል፡፡ ሆኖም ሟች አመልካችና ሌላ ያለ ኑዛዜ ወራሽ ነኝ ብሎ የሚመጣ ሰው በውርሣቸው ተካፋይ እንዳይሆን በመግለፅ ያደረጉት ኑዛዜ አመልካች በሟች ውርስ በወራሽነት እንዳይሣተፉ የማድረግ ህጋዊ ውጤት የለውም፡፡ ምክንያቱም አመልካች የሟች ልጅና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ናቸው፡፡ ማንኛውም ሰው ከውርስ ለመንቀል የደረሰበትን ምክንያት በኑዛዜው ውስጥ ካልገለፀ በቀር ልጁን ወይም ወደታች የሚቆጠር ተወላጁን ከውርስ ለመንቀል ያደረገው ኑዛዜ የማይፀናና ህጋዊ ውጤት እንደማይኖር የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 938 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ የሚደነግግ በመሆኑ ነው፡፡

ሟች ጥር 30 ቀን 1984 ዓ.ም ባደረጉት ግልፅ ኑዛዜ ውስጥ ስሙ ያልተገለፀ ወራሻቸው በውርሳቸው እንዲሳተፉ ፈቃድ የሌላቸው መሆኑን የገለፁ ቢሆንም በኑዛዜው ስማቸው ከተገለፁት ሁለት ልጆቻቸው ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪ ውጭ ያሉ ወራሾቻቸውን ለምን በውርሳቸው ተካፋይ እንደሆኑ እንዳልፈለጉና ከውርስ በኑዛዜ

እንዲነቀሉ በኑዛዜው ውስጥ የሰጡት ምክንያት የለም፡፡ አመልካች የሟች ልጅና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 842 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ በመሆኑ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሟች ምክንያቱን ሣይገልፅ ከውርስ ለመንቀል ያደረጉት ኑዛዜ የማይፀና መሆኑ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 938 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ የተደነገገ በመሆኑ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ አመልካች በሟች ውርስ በመሣተፍ ድርሻውን ከመጠየቅ የሚገድበው አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ያደረጉት ኑዛዜ አመልካች በሟች ውርስ በወራሽነት እንዳይሣተፍ የማድረግና ከውርሱ የመነቀል ውጤት የሚያስከትል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. ሟች ያደረጉት ኑዛዜ የአመልካችን ከውርስ መነቀል ህጋዊ ውጤት ካላስከተለ ያሟች ሚስትና የኑዛዜ ተጠቃሚ ለሆኑት አንደኛ አመልካች የሚያስገኘው መብት ምንድን ነው? የሚለው ነጥብ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው ነው፡፡ ሟች አንደኛ ተጠሪ ከልጆቻቸው ከሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች ጋር በመሆኑ የጠቅላላ ሀብትና ንብረት ወራሽ መሆናቸውን በኑዛዜአቸው ገልፀው ሟች አንደኛ ተጠሪ ካላቸው ሀብት ውስጥ አንድ የተለየ ንብረት እንደወሰዱ ሣይሆን ከሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች ጋር በመሆኑ ያላቸው ሀብት በጠቅላላ ወራሽ እንደሆኑ የተናዘዙ በመሆኑ አንደኛ ተጠሪ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 912 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረት የሟች ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ ናቸው፡፡

የሟች ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ የሆነ ሰው በኑዛዜው ውስጥ ሟች ተቃራኒ ውጤት ያለው መሆኑን ካልገለፀ በስተቀር የሟች ያለኑዛዜ ወራሽ እንደሆነ እንደሚቆጠር በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 915 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ሟች አንደኛ ተጠሪ በሁለተኛ እና ሶስተኛ ተጠሪዎች ጋር የጠቅላላ የንብረታቸው ወራሽ መሆናቸውን ከመግለፅ ውጭ ሌላ የገለፁት ሁኔታ የሌለ በመሆኑ አንደኛ ተጠሪ እንደ ሟች ያለኑዛዜ ወራሽ (አንድ ልጅ) ተቆጥረው በውርሱ የመካፈል መብት ይኖራቸዋል፡፡ ስለሆነም ሟች ጥር 30 ቀን 1984 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ሚስታቸው የሆኑት አንደኛ ተጠሪ እንደሟች አንድ ወራሽ ተቆጥረው በውርሱ የመሣተፍ ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

4. የመጨረሻውና እልባት ሊያገኝ የሚገባው ሟች ለሁለተኛ እና ሶስተኛ ተጠሪ ያደረጉት ኑዛዜ ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው የሚለው ነው፡፡ ሟች በኑዛዜአቸው ሁለተኛ ተጠሪና ሶስተኛ ተጠሪ ልጆቻቸው መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ሟች ያደረገው ኑዛዜ ከአለው የውርስ ንብረት አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ የትኛውን መውሰድ እንዳለባቸው የሚዘረዝር አይደለም፡፡ ኑዛዜው አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር በመሆን የጠቅላላ ሀብትና ንብረቱ ወራሽ መሆናቸውን የሚገልፅ ነው፡፡ ስለሆነም የሟችን ሁለተኛ እና ሶስተኛ ተጠሪ ያደረገው ኑዛዜ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 913 በሚደነግገው መሠረት የተደረገ የክፍያ ደንብ ነው ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡

በሌላ በኩል ኑዛዜው ሁለተኛ ተጠሪና ሶስተኛ ተጠሪ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር በመሆን የሟች ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን ከሚገልፅ በስተቀር እያንዳንዳቸው ከውርሱ ንብረት ስለሚደርሳቸው ድርሻ የማይዘረዝር በመሆኑ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2017 መሠረት የተደረገ የሀብት ክፍፍል ነው ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኑዛዜው ሟች ልጃቸውና አንደኛ ደረጃ ወራሻቸው የሆነውን አመልካች በውርሱ እንዳይካፈል ለመንቀል አስበው ያደረጉትና አመልካችን ለመንቀል የተናገሩት ቃል በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 938 ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀውን መስፈርት የማያሟላ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የሌለው በመሆኑ ሟች ለሁለተኛ እና ሶስተኛ ተጠሪዎች ያደረጉት ኑዛዜ ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች ልጆቻቸውና ወራሾቻቸው መሆናቸውን ከማረጋገጥ ውጭ የተለየ ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ ሟች ጥር 30 ቀን 1984 ያደረጉት ኑዛዜ ህጋዊ ውጤት ስንመረምረው ኑዛዜው አመልካች ከውርስ የሚነቀል የሚያስከትል አይደለም፡፡ አንደኛ ተጠሪ እንደ ሟች አንድ ወራሽ ተቆጥረው በሟች ውርስ እንዲሳተፉ የሚያስችልና ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች የሟች ልጆችና ወራሾች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ህጋዊና ፎርሙን ያሟላ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ኑዛዜው አመልካችና በተጠሪዎች መብት ላይ የሚያስከትለው ህጋዊ ውጤት ምን እንደሆነ ሣይዘረዝሩ ማለፋቸው ተገቢ ሆኖ ባለማግኘታችን ውሣኔአቸውን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት አሻሽለናል፡፡ በዚህ መሠረት አንደኛ ተጠሪና የሟች ሚስት እንደ አንድ የሟች ልጅና ወራሽ ተቆጥረው የሟችን ውርስ ከልጆቻቸው

ጋር የመካፈል መብት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም የሟችን የውርስ ሀብት አመልካች ሁለተኛ ተጠሪ ሶስተኛ ተጠሪና አንደኛ ተጠሪ እኩል ድርሻ የማግኘት መብት አላቸው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የሟች ኑዛዜ በከፊል ህጋዊ ውጤት የሌለው በመሆኑ የሟች የውርስ ንብረት አመልካች ሁለተኛ ተጠሪ ሶስተኛ ተጠሪና አንደኛ ተጠሪ በወራሽነት ተሣትፈው በእኩል ድርሻ ያገኛሉ በማለት ወስነናል፡፡
   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

# ውል

የሰ/መ/ቁ. 44800

ጥቅምት 05 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ አብዱራዛቅ ሐሚድ - ጠ/አስቻለው አሻግሬ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ መንበረ አድማሱ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የመያዣ ውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ነው፡፡ አመልካች ለፌ/መ/ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ሐሚድና ቤተሰቡ የግብርና ውጤቶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከተጠሪ ላይ ለወሰደው ብድር አመልካች በአ/አበባ ከተማ ወረዳ 23 ቀበሌ 12 ውስጥ የሚገኘውን ቤት በመያዣ ያስመዘገቡ ሲሆን አቶ ሐሚድ ይስሐቅ የተባሉ ግለሰብም 2 ቤቶች በመያዣ ሰጥተዋል፡፡ ተበዳሪው ብድሩን አጠናቆ ባለመክፈሉ ባንኩ በመያዣ የያዛቸውን

ቤቶች በሃራጅ ለመሸጥ በመንቀሳቀሱ ባንኩ የአቶ ሐሚድ ይስሐቅ ቤቶችን በሐራጅ ሸጦ እዳውን በሙሉ ከፍሎ አጠናቋል፡፡ እዳው ተከፍሎ ስለተጠናቀቀ በመያዣ የሰጠሁት ቤት ካርታ እንዲመልስልኝ ብጠይቀው ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ የመያዣው ውሉ ከተፈረመ 10 አመት ያለፈው በመሆኑ ቀሪ ሆኗል፡፡ ስለዚህ ባንኩ ቤቴን በሐራጅ ለመሸጥ የጀመረውን እንቅስቃሴ እንዲያቆም የያዘውን ካርታ እንዲመልስ፣ ያልተከፈለ እዳ ካለ የሂሳብ መግለጫ እንዲያቀርብና ቀሪውን ገንዘብ ከፍዬ ቤቴ ከመያዣነት እንዲለቀቅልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተበዳሪው የወሰደው ብድር ተከፍሎ ያልተጠናቀቀ በመሆኑና በፍ/ብ/ህ/ቁ 3058(1) የተመለከተው የ10 አመት ጊዜ ከማለፉ በፊት በመያዣ ንብረቱ ላይ እንቅስቃሴ የጀመረ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቶባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ዋነኛ አቤቱታ የመያዣው ውል ከተመዘገበ 10 አመት ስላለፈው በፍ/ብ/ህ/ቁ 3058(1) መሰረት መያዣው ቀሪ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም ይህንኑ የአመልካችን ቅሬታ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረግ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካች ሐሚድና ቤተሰቡ የግብርና ውጤቶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለወሰደው ብድር ቤታቸውን በመያዣ ሰጥተዋል፡፡ የመያዣ ውሉም የተመዘገበው በ1987 ዓ.ም መሆኑን እንዲሁም ተበዳሪው ድርጅት ብድሩን መክፈል ባለመቻሉ ተጠሪ ለአመልካች ጥቅምት 24 ቀን 1992 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ መስጠቱን አመልካች አልካዱም፡፡ አመልካች መያዣው ቀሪ ነው በማለት የሚከራከሩት የፍ/ብ/ሕ/ቁ 3058(1)"ን" በመጥቀስ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ድንጋጌ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ አመልካች የጠቀሱት ይህ ድንጋጌም እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

***የማይንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን አንስቶ እስከ አስር ዓመት ድረስ ነው፡፡***

በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ የመያዣ ውል ውጤት የሚኖረው መያዣው ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ እስከ 10 አመት ድረስ ነው፡፡ በመሆኑም በመያዣ ውሉ ምክንያት በሚገኙ ማናቸውም መብቶች መገልገል የሚቻለው ይኸው የተወሰነው ጊዜ ከማለፉ በፊት ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህ የጊዜ ዘመን ሊራዘም የሚችለው 10 ዓመቱ ከማለፉ በፊት ውሉ እንዲታደስ አዲስ ምዝገባ ተከናውኖ ከሆነ ብቻ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 3058(2) እንገነዘባለን፡፡ በመሰረቱ ይህ ህግ አመልካች እንደሚሉት የይርጋ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ይርጋ ማለት በህግ ተለይቶ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በኋላ በአንድ ጉዳይ ክስ ለማቅረብ የሚከለከልበት የህግ ፅንሰ-ሃሳብ ነው፡፡ በመሆኑም ይርጋ አንድ ሰው በጉዳዩ ላይ መብት ያለው ቢሆንም እንኳን ይህንን መብቱን ለመጠየቅ የማይችልበትን ገደብ የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ክልከላም ተፈፃሚ የሚሆነው ክስ ከቀረበ በኋላ ተከሳሹ የይርጋ መቃወሚያ አንስቶ የተከራከረ ከሆነ ነው፡፡ ከሳሽ ክስ የማቅረብ መብቱ በይርጋ ቀሪ ከሆነ በኋላ ክስ አቅርቦ ተከሳሽ ክሱ በይርጋ ቀሪ መሆኑን በመግለፅ ካልተቃወመ ክሱ ተቀባይነት አግኝቶ መታየት ይቀጥላል፡፡ የጊዜ ገደቡ በማለፉ ብቻ ፍ/ቤት የይርጋውን በራሱ አነሳሽነት አንስቶ ክሱን ውድቅ ሊያደርግ አይችልም፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 3058(1) የሚያስቀምጠው የይርጋን ጽንሰ-ሐሳብ አይደለም፡፡ የተጠቀሰው አንቀፅ የሚናገረው በህጉ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ማለፍ የመያዣው ውሉን ቀሪ (lapse) የሚያደርገውና ከዚሁ ጊዜ በኋላ መያዣ ውሉ ተጠቃሚ የሆነው ሰው በመያዣው ላይ ያለው መብት የሚያበቃበትን ሁኔታ ነው፡፡ የመያዣ ውሉ ከተመዘገበ በኋላ 10 ዓመት ሆኖት እንደሆነና እንዲታደስ ካልተጠየቀ ጠያቂ ባይኖርም አቃቤ መዝገቡ መያዣውን እራሱ ሊሰርዘው እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1632(2) ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም መያዣ ሰጪው 10 አመት በማለፉ መያዣው እንዲሰረዝ ጥያቄ ባያቀርብም መዝጋቢው አካል ራሱ ምዝገባውን ሰርዞ መያዣውን ቀሪ ሊያደርገው ይገባል፡፡

በሌላ በኩል መያዣው ነሐሴ 17 ቀን 1987 ዓ.ም የተመዘገበ ቢሆን በመያዣ የተያዘው ቤት አመልካች ክስ እስከመሰረቱበት ህዳር 12 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ አለመሸጡን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካችም ይህንኑ ጊዜ መሰረት አድርገው ነው መያዣው ቀሪ ነው ሲሉ የሚከራከሩት፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መያዣው ከተመዘገበ በኋላ ተበዳሪው እዳውን ባለመክፈሉ 10 አመቱ ሳያልፍ ጥቅምት 24 ቀን 1992 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ለአመልካች በመስጠቱ መያዣው ቀሪ አልሆነም ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካች የተባለው ማስጠንቀቂያ የደረሳቸው መሆኑን አልካዱም፡፡ ክርክራቸው ማስጠንቀቂያ በመስጠት የይርጋ ጊዜን ማቋረጥ የሚቻለው ለዋና እዳ እንጂ ለማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ አይደለም የሚል ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው በፍ/ብ/ህ/ቁ 3058 ስር የተቀመጠው የጊዜ ገደብ የይርጋ ጊዜ ገደብ ባለመሆኑ ስለይርጋ ማቋረጫ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል ግን ባለገንዘቡ የመያዣ ውሉ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ 10 ዓመት ከማለፉ በፊት በመብቱ መገልገል

ጀምሯል ሊባል የሚችለው መቼ ነው? የሚለው ሊታይ ይገባል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት ለሰጠው ብድር መያዣ የያዘ ባንክ ብድሩ ካልተከፈለው የ30 ቀናት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ንብረቱን ለመሸጥና የባለቤትነት ስሙን ለገዢ ለማስተላለፍ እንደሚችል በቁጥር 3 ስር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ባንኮች የመያዣ መብታቸውን መገልገል የሚጀምሩት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ለመሆኑ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ቢሆን ተጠሪ ለአመልካች ጥቅምት 24 ቀን 1992 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ በመስጠት በመብቱ መገልገል ጀምሯል፡፡ መያዣው ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠር ደግሞ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው 10 ዓመት ሳያልፍ ነው፡፡ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ ቤቱን ሳይሸጥ የ10 ዓመቱ ጊዜ አልፎ ሊሆን ይችላል፡፡ የቤቱ ሽያጭ ሳይጠናቀቅ 10 አመቱ ማለፉ ብቻውን ግን መያዣውን ቀሪ አያደርገውም፡፡ ሊታይ የሚገባው ተጠሪ በመብቱ መገልገል የጀመረበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ ደግሞ መያዣው ቀሪ የሚሆንበት የህግ መሰረት የለም፡፡ በዚህም ምክንያት የስር ፍ/ቤቶች የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለው ለማለት አልተቻለም፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 78317 ታህሳስ 09 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 64469 ጥር 05 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. ውሳኔው ስለፀና ይህ ችሎት ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ትዕዛዙ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 42897

ኅዳር 10 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ አየለ ሐብተየስ - ጠ/ውብሸት ክብሩ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ሚ/ር ኖቼራ ጃካርሎ
2. ሚ/ር ኖቼራ ፍሪንኮ } ጠ/ሻምበል ተሾመ ደምሴ ቀረቡ

## <u>ፍ ር ድ</u>

ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው አመልካች ለፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ ከተጠሪዎች ለፎቶ ቤትነት ለ10 አመት የተከራዩትን ቤት መብራት

ውሐ በመቁረጥ የፎቶ ቤት ስራው ሙሉ በሙሉ እንዲቋረጥ ስላደረጉ መብራቱን ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ላሉት 76 ቀናት የተቋረጠ ጥቅም ብር 64,752(ስልሳ አራት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ሁለት) ተጠሪዎች እንዲከፍሉና መስመሩን እንዲቀጥሉ ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎችም ቀርበው አመልካች የተከራዩት ቤቱን እንጂ ውሐና መብራቱን አይደለም፣የኤሌትሪክ ቆጣሪው የሚገኘው የሕብረት ባንክ የተከራየው ህንፃ ውስጥ ነው፣ለስራ እንዲያመቸው ባንኩ የኤሌክትሪኩንና የውሐውን መስመር ለግሉ እንድናደርግ ስለጠየቀ ተገቢ ማስጠንቀቂያ ለአመልካች በመስጠት መስመሩ መቋረጡ በሕግም ሆነ በሞራል የሚያስነቅፍ ስላይደለ የተቋረጠ ገቢ ልንከፍል አይገባም፣ክፈሉ እንኳን ከአገር ውስጥ ገቢ በሚቀርብ ማስረጃ ሊወሰን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የመብራት መስመሩ በኪራይ ስምምነት ውስጥ ስላልተካተተ እና ህብረት ባንክ በሚጠቀምበት ህንፃ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ የመብራት መስመሩ ይቀጠልልኝ ሊሉ አይችሉም፡፡ ነገር ግን ተጠሪዎች አመልካች ሌላ የሃይል አቅርቦት አማራጭ ለመፈለግ የሚያስችል ቢያንስ የ1 ወር ጊዜ መስጠት ሲገባቸው ከቅን ልቦናና ከልማዳዊ አሰራር ውጪ የሆነ ተግባር በመፈፀማቸው የ1 ወር ትርፍ የመተካት ሐላፊነት ስላለባቸው በርትእ ብር 4000(አራት ሺህ) እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅረበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪዎች ቤቱን ያከራዩት ለፎቶ ቤት ንግድ ስራ በመሆኑና ከፎቶ ማንሳት፣ማጠብና ተያያዥነት ያላቸው ሥራዎች በአሌትሪክ ሃይል አማካኝነት የሚሰሩ እንደመሆኑ መስመሩን ማቋረጣቸው አይነተኛ የውል መጣስ ተግባር ስለሆነ ለተቋረጠ ገቢ ብር 64,572(ስልሳ አራት ሺህ አምስት መቶ ሰባ ሁለት) ኪለፈሉ ይገባ፣የተቋረጠውን መስመር መልሰው ይቀጥሉ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔን ሽሮ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ችሎቱም አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

በዚህ ጉዳይ ሊታይ የሚገባቸው ጭብጦች ተጠሪዎች የኤሌትሪክ መስመሩን መቁረጣቸው የውል መጣስ ተግባር መሆን አለመሆኑ ነው ከተባለ ተጠሪዎች በውሉ መሰረት ሊፈጽሙና በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ሊከፍሉ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ አለመሆኑ ናቸው፡፡ ተጠሪዎች ለአመልካች ቤት ማከራየታቸውን ሳይክዱ የሚከራከሩት ያከራዩት ቤቱን ብቻ እንጂ የኤሌትሪክ መስመር አለመሆኑ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ቤቱን ከመከራየት ጋር በኤሌትሪክ መስመሩ የመጠቀም መብት አግኝተዋል አላገኙም የሚለውን ከግራ ቀኙ ስምምነት እና አግባብ ካለው ሕግ አኳያ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የተጠሪዎችን ንብረት አመልካች በቅን ልቦና ከሌሎች ሰዎች ላይ ተከራይተው ፍጹም ፎቶ የሚል ድርጅት ከፍተው የሚጠቀሙበት በመሆኑና በቤቱ ላይ ላወጡት ወጪ ማካካሻ ይሆን ዘንድ ለ10 አመት ያለምንም ክፍያ እንዲጠቀሙበት ግራ ቀኙ ተስማምተዋል፡፡ በዚህ ስምምነት ላይ በግልጽ አመልካች የኤሌትሪክ መስመር ስለመከራየታቸው የተመለከተ ነገር የለም የፌ/መ/ደረጃ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች የተከራዩት ቤቱን ብቻ እንጂ የመብራት መስመር አይደለም ያሉትም በስምምነቱ ላይ የኤሌትሪክ መስመር ስለመከራየታቸው በግልጽ ባለመመልከቱ ነው፡፡ ነገር ግን ከስምምነቱ አመልካች ቤቱን የሚጠቀሙት ለፎቶግራፍ ማንሳት፣ማጠብና ማተም ስራ መሆኑን ተጠሪዎች ለአመልካች ቤቱን ሲያከራዩ ሚያውቁት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ አንድ ውል ደግሞ ሊተረጐም የሚገባው በተዋዋዮች መሃከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነትና የመተማመን ግንኙት መሰረት በማድረግና ጉዳዮቹ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ሥርአት በመከተል በቅን ልቦና ሊሆን እንሚገባው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1732/1/ ያመለክታል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ተጠሪዎች ቤቱን ለአመልካች ሲያከራዩ አመልካች ቤቱን ለምን አገልግሎት እንደሚጠቀሙበት ያውቁ የነበረ በመሆኑና የአመልካችም ስራ ያለኤሌትሪክ መስራት የማይቻል መሆኑን ሊገነዘቡ የሚችሉ ሆኖ ሳለ ቤቱን ብቻ እንጂ ኤሌትሪኩን እንዲጠቀሙ አልተስማማንም የሚለው የተጠሪዎች ክርክር የቅን ልቦና ተቃራኒ የሆነ ነው፡፡ በተጨማሪ ውል ሲተረጐም ተዋዋዮች ውላቸውን ከማድረጋቸው በፊት ወይም በኋላ የነበሩበት ሁኔታ ሊመዘን እንደሚገባ የፍ/ሕ/ቁ. 1734/2/ ያመለክታል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ተጠሪዎች አመልካች ቤቱን ብቻ እንጂ ኤሌትሪክ መስመሩን አብረው አልተከራዩም ይበሉ እንጂ ስምምነት ካደረጉበት ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ መስመሩን እስካቋረጡበት ጊዜ ድረስ አመልካች በኤሌክትሪኩ መስመር ሲጠቀሙ መቆየታቸው ግራ ቀኙ ስምምነት ባደረጉ ጊዜ ሃሳባቸው ምን እንደነበረ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ለአንድ ቤት የሚዘረጋው አንድ የኤሌትሪክ መስመር ከመሆኑ አኳያ ተጠሪዎች ቤቱን ሲያከራዩ ተከራይ በዚሁ የኤሌትሪክ መስመር የመጠቀም መብት ሊኖረው ይገባል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.

1355 ስር እንደተመለከተውም በአንድ ቤት ክፊል ላይ ብቻ የመኖር መብት ያለው ሰው ለጋራ አገልግሎት በተቋቋሙት ነገሮች ለመጠቀም መብት ያለው መሆኑን ያመለከታል፡፡ የኤሌትሪክ መስመርም ለአጠቃላይ ቤቱ እንዲያገለግል የሚዘረጋ በመሆኑ አመልካች ለተከራዩት ቤት በኤሌትሪክ መስመሩ የመጠቀም መብት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ከክርክሩ እንደተገነዘብነው ተጠሪዎች መስመሩን ያቋረጡት የመብራት ቆጣሪው ህብረት ባንክ በተከራየው የሕንፃው ክፍል ውስጥ የሚገኝ በመሆኑና ለስራ እንዲያመቸው መስመሩን ብቻውን እንዲጠቀምበት በመጠየቁ ነው፡፡ ነገር ግን አከራዩ ክፊል ህንፃውን ካከራየ በኋላ ሌሎች የህንፃውን ክፍሎች ሲያከራይ የመጀመሪያውን ተከራይ ጥቅም መጠበቅ እንዳለበት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2947 ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ለህብረት ባንክ ክፊል ህንፃውን ሲያከራዩ አመልካችን በመብት እና ጥቅም በሚጐዳ መልኩ ሊሆን አይገባም፡፡

የአመልካች ጥያቄ ወድቅ የተደረገበት ሌላኛው ነጥብ አመልካች ቤቱን እንዲገለገሉበት የተሰጣቸው በነፃ በመሆኑ ውሉ ለተጠሪዎች ግዴታን ብቻ የጣለ በመሆኑ ሊተረጐም የሚገባው ተጠሪዎችን በሚጠቅም መልኩ ነው በሚል ነው፡፡ ነገር ግን ምንም እንኳን አመልካች ቤቱን ያለምንም ክፍያ እንዲገለገሉበት የተስማሙ ቢሆንም ለዚህ ስምምነት ምክንያት የሆነው ግን አመልካቾች በቤቱ ላይ ከፍተኛ ወጪ ያወጡበት በመሆኑ ሳወጡት ወጪ ማካካሻ እንዲሆን ነው፡፡ ስለሆነው የተደረገው ውል አመልካች ቀደም ሲል ያወጡት ወጪ ከኪራዩ ገንዘብ ጋር እንዲጣጣ ታሳቢ ተደርጐ የተደረገ እንጂ ተጠሪዎች ምንም አይነት ጥቅም ያላስገኘ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ውሉም ፈጽሞ ጥቅም ለማስገኘት እንዳልተደረገ ውል ተቆጥሮ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1739 መሰረት ግዴታው በቀላል አኳኋን ሊተረጐም ይገባል መባሉ አግባብ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም አመልካች ቤቱን ብቻ እንጂ የኤሌትሪኩን መስመር አልተከራዩም የሚለው የተጠሪዎች ክርክር ከፍ ሲል በተዘረዘሩት ምክንያቶች ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች የአምስት ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት የኤሌትሪክ መስመሩን መቁረጣቸው መሰረታዊ የውል መጣስ ተግባር መሆኑን ተረድተናል፡፡

ተጠሪዎች የውል መጣስ ተግባር ፈጽመዋል ከተባለ ቀጥለን ይህ ድርጊት ስለሚያስከትለው ሃላፊነት እንመለከታለን፡፡ ውል ያልተፈፀመለት ሰው ውሉ እንዲፈፀምለት ወይም ውሉ እንዲፈርስለት ሊጠይቅ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1771/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች እንደ ውሉ እንዲፈፀምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎችም የውል መጣስ ተግባር አለመፈፀማቸውን እንጂ እንደውሉ መፈጸም የማይገደዱበትን ሌላ ምክንያት ያልገለፁ ስለሆነ የኤሌትሪክ መስመሩን ሊቀጥሉ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተዋዋይ ወገን ግዴታውን ባልፈጸመ ጊዜ ውሉን በግዴታ እንዲፈጽም ከመደረጉም በተጨማሪ ለደረሰው ጉዳት ካሳ እንዲከፈል እንደሚገደድ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1790/1/ ገልጿል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ኤሌትሪክ መስመር በመቆረጡ ምክንያት ስራ ስላቆሙ የብር 64,572(ስልሳ አራት ሺህ አምስት መቶ ሰባ ሁለት) ኪሳራ የደረሰባቸው መሆኑን ገልፀዋል ሲገልፁ ተጠሪዎች በበኩላቸው የአመልካች የንግድ ፈቃድ ተሰርዞ የነበረ በመሆኑ ኪሳራ ሊከፍሉ እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪዎች ሊያረጋግጡ የሚገባቸው  አመልካች ያልሰሩና ገቢ ያላገኙ መሆኑን እንጂ የአመልካች ንግድ ፈቃድ መሰረዙን አይደለም፡፡ አመልካች ስራ ሰርተው ገቢ ያገኙ የነበረ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ያለ ንግድ ፈቃድ መስራታቸው በሚመለከተው ክፍል ተገቢው እርምጃ ሊያስወስድባቸው የሚችል ከሚሆን በቀር ተጠሪዎችን ኪሳራ ከመክፈል ነፃ የሚያደርጋቸው አይሆንም፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ከአመልካች ጋር ተመሳሳይ ስራ የሚሰራ ድርጅት የሚያገኘውን ገቢ አስመልክቶ የላከውን መረጃና በአመልካች ድርጅት ውስጥ የሚሰሩትን ሰራተኞች ስለ አመልካች ገቢ በምስክርነት ሰምቶ አመልካችን በክሱ ላይ የተመለከተውን ገቢ ያጡ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የተረጋገጠውን ኪሳራ ተጠሪዎች የመክፈል ሃላፊነት አለባቸው፡፡ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ከተሰረዘ የንግድ ፈቃድ ኪሳራ እንዲከፈል ማድረግ ሕገ ወጥነትን ማበረታታት ነው ከማለት ውጪ አመልካች የተቋረጠባቸው ገቢ ሰላለመኖሩ ያጣራው ነገር እንደሌለ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች የ5 ቀናት ማስጠንቀቂያ ብቻ ሰጥተው መስመሩን በማቋረጣቸው በአመልካች ላይ ለደረሰው ኪሳራ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን የኪሳራ ገንዘብ ተገቢ ነው ማለቱ አመልካች የተቋረጠባቸው ገቢ የነበረ መሆኑን መቀበሉን ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ  ተጠሪዎች አመልካች የተከራዩትን ቤት የኤሌትሪክ መስመር መቁረጣቸው የውል መጣስ ተግባር አይደለም በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 15812 መጋቢት 21 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24407 ጥቅምት 27 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 47038 ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪዎች የቆረጡትን የኤሌትሪክ መስመር ሊቀጥሉ ይገባል፡፡ መስመሩን በመቁረጣቸው በአመልካች ላይ የደረሰውን ኪሳራ ብር 64,572 (ስልሳ አራት ሺህ አምስት መቶ ሰባ ሁለት) የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ይክፈሉ ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

    መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 40947

ህዳር 15 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሃይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** አቶ መዝገቡ መድህኔ - ጠ/ሐጎስ ደበሱ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የአ.አ ከተማ አስተዳደር - ነ/ፈጅ አትርሣው ወልዴ ቀረቡ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች ተጠሪ ላወጣው ጨረታ ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ብር 20,000(ሃያ ሺህ) ሊመለስ አይገባም ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች በፌ/መ/ደረጃ

ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ባወጣው የጨረታ ብር 2,000,000(ሁለት ሚሊዮን) የሚያወጡ 32 አይነት እቃዎች ለማቅረብ የተወዳደሩ ቢሆንም ያሸነፉት በሁለት አይነት እቃዎች ብቻ በመሆኑ ውል እንዲሞሉ የቀረበላቸውን ጥያቄ ባለመቀበላቸው ተጠሪ ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ አልመልስም በማለቱ ገንዘቡን እንዲመልስላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ለክሱ በሰጠው መልስ አመልካች ባሸነፉባቸው ሁለት አይነት እቃዎች ውል እስካልፈረሙ ድረስ ገንዘቡ ሊመለስላቸው እንደማይገባ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም አመልካች በዋስትና ሰነዱ ላይ የተመለከተውን ግዴታ እስካልተወጡ ድረስ ገንዘቡ ሊመለስላቸው አይገባም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው የነበረ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቶባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በመባሉም ግራ ቀኙ ቀርበው የቃል ክርክራቸው ተሰምቷል፡፡ መዝገቡም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ተጠሪ ባወጣው የጨረታ ማስታወቂያ አመልካች 32 አይነት እቃዎች ለማቅረብ ተወዳድረው ለጨረታ ማስከበሪያም የእነዚህ እቃዎች ዋጋ አንድ በመቶ ማስያዛቸውን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ አመልካች የተወዳደሩበት የጠቅላላ ንብረቶቹ ዋጋ ብር 2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን) ስለሆነ የተያዘው ገንዘብ ብር 20,000(ሃያ ሺህ) ስለመሆኑና አመልካች ከተወዳደሩበት 32 አይነት እቃዎች ውስጥ ያሸነፉት በሁለት እቃዎች ብቻ ለመሆኑ ግራ ቀኙ አልተካካዱም፡፡ አከራካሪው ጉዳይ አመልካች ላሸነፉበት ሁለት እቃዎች ውል አለመፈረማቸው ያስያዙት ብር 20,000(ሃያ ሺህ) እንዳይመለስላቸው ይከለክላል ወይስ አይከለክልም? የሚለው ነው፡፡

የጨረታ ማስከበሪያ ማለት አንድ ተጫራች ጨረታውን ቢያሸንፍ ውል የሚፈፅም ለመሆኑ ዋስትና እንዲሆን የሚያዝ ገንዘብ ነው፡፡ ለውል መፈፀም ዋስትና ሲባል የሚያዝ ገንዘብ እንደመሆኑም መጠን የጨረታው አሸናፊ ባሸነፈው መሰረት ውል ካልፈረመ የጨረታው ማስከበሪያ ይያዝበታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ብር 2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን) ለሚያወጡ 32 ዓይነት እቃዎች ተጫርተዋል፡፡ ለጨረታ ማስከበሪያም የተጫረቱባቸውን ጠቅላላ እቃዎች ዋጋ አንድ በመቶ ብር 20,000 (ሃያ ሺህ) አስይዘዋል፡፡ ከክርክሩ ሂደትም አመልካች ከተወዳደሩባቸው እቃዎች ውስጥ ያሸነፉት በሁለቱ እቃዎች ብቻ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ተጠይቀውም ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ያልሆኑት እነዚህን ሁለት እቃዎች በተመለከተ ነው፡፡ አመልካች 20,000(ሃያ ሺህ) ብር የጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙት ጠቅላላ ለተጫረቱበት እቃዎች በመሆኑ ጠቅላላው የጨረታ ገንዘብ ሊያዝ የሚገባው አመልካች በተወዳደሩባቸው እቃዎች በሙሉ አሸናፊ ቢሆኑና በዚሁ መሰረት ውል አልፈርምም ቢሉ ነበር፡፡ አመልካች ያሸነፉት ግን በሁለት እቃዎች በመሆኑ ለነዚህ እቃዎች ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የጨረታው ማስከበሪያ ሊያዝ የሚገባው አሸናፊ በሆኑባቸው እቃዎች ዋጋ መጠን የተያዘው ገንዘብ እንጂ አመልካች ለ32 አይነት እቃዎች ላስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ በጠቅላላ ሊሆን አይገባም ባላሸነፉባቸው ዕቃዎች ቀድሞውንም ውል ለመዋዋል ስለማይችሉ ለነዚህ እቃዎች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ ውል አልፈፀሙም ተብሎ ሊያዝባቸው የሚገባበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ላሸነፉት ሁለት አይነት እቃዎች ውል አልፈረሙም በሚል ለ32 አይነት እቃዎች ያስያዙት ብር 20,000(ሃያ ሺህ) በሙሉ ሊያዝ ይገባል በሚል የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01619 ጥቅምት 25 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 43929 ሐምሌ 15 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለ32 ዓይነት እቃዎች ካስያዙት ብር 20,000(ሃያ ሺህ) ሊያዝባቸው የሚገባው ጨረታ ያሸነፉባቸው ሁለት እቃዎች ዋጋ አንድ በመቶ ብቻ ስለሆነ ይኸው ገንዘብ ተቀንሶ ቀሪው ገንዘብ እንዲመለስላቸው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 43825

ታህሣሥ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- የህፃን ኮከቤ ተፈሪ ሞግዚትና አስተዳዳሪ ፀሐይ በየነ ቀረበ

**ተጠሪ**፡- 1. አቶ አያሌው ካሳዬ - አልቀረቡም

2. አቶ ጣእመ ካሳዬ - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካች በሞግዚታቸው አማካኝነት ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በክሳቸው የአመልካች እናት ንብረት ለማስተዳደር እንጂ ለመሸጥ ስልጣን ሳይኖራቸው ለአመልካች ከአባታቸው በውርስ የሚተላለፍላቸውን ቤት ለአንደኛ ተጠሪ የሸጡ በመሆኑና ሁለተኛ ተጠሪም ወኪል ነኝ በማለት ቤቱን ይዘው ስለሚገኙ የሽያጩ ውል ፈርሶ ወደነበርበት እንዲመልሱ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ ክሱ ለተጠሪዎች ደርሷቸው በሰጡት መልስ ከሳሽ ክሱን ለማቅረብ መብት የላቸውም ክሱም በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም አመልካች ክስ ለማቅረብ መብት የላቸውም የሚለውን መቃወሚያ ውድቅ ካደረገ በኋላ በአመልካች እናትና በአንደኛ ተጠሪ መሐከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል በፁሁፍና ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው ሰው ወይም በፍርድ ቤት ፊት ያልተከናወነ በመሆኑ ረቂቅ እንጂ በህግ ፊት የሚፀና ውል ስላልሆነ ውል በሌለበት ሁኔታ የውል ይፍረስልን ጥያቄ ሊቀርብ አይችልም፣የይርጋ መቃወሚያም ሊቀርብበት አይችልም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የስር ውሳኔን አጽቶታል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎት የውል አፃፃፍ ፎርም አለመከተል በተዋዋይ ወገን ወይም በማናቸውም ያገባኛል ባይ ውል እንዲፈርስ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ የሚታይ ነው ወይስ ፍ/ቤቱ በእራሱ አነሳሽነት ሊያየው ይችላል? የሚለውን የሕግ ነጥብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡ መርምሯል፡፡

አመልካች በሞግዚታቸው አማካኝነት ያቀረቡት ክስ በአመልካች እናትና በአንደኛ ተጠሪ መሐከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስና ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ነው፡፡ ተጠሪዎችም ቢሆኑ ይህ ውል ስለመደረጉ አምነው ሌሎች ክርክሮችን አቅርበዋል፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤት የቤት ሽያጩ ውል በፁሁፍና ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ወይም ፍ/ቤቱ ያልተደረገ በመሆኑ ክርክር ሊቀርብበት የሚችል ውል የለም በማለት ወስኗል፡፡ በእርግጥ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን ለማስተላለፍ የሚደረግ ውል በፁሁፍና ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ወይም በፍ/ቤት ካልተደረገ ውጤት የሌለው መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 ስር ተመልክቷል፡፡ ይህን በሕጉ የተመለከተው የአፃፃፍ ስርአትን አለመከተል የሚያስከተለው ውጤት ምን እንደሆነ ደግሞ በዚሁ ሕግ ቁጥር 1808/2/ ስር ተቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት የአፃፃፍ ስርአት ያላሟላ ውል የሚፈርሰው ከተዋዋዮቹ በአንዱ ወይም ማናቸውም ጥቅም ያለው ሰው ሲጠየቅ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ይህም አንድ የአፃፃፍ ስርአትን ያላሟላ ውል በሕጉ በተመለከቱት ሰዎች እንዲፈርስር ጥያቄ አስካልቀረበበት ድረስ ከጅምሩ ፈራሽ ነው ሊባል እንደማይችል ያስገነዝበናል፡፡ ውሉ የአፃፃፍ ስርአትን ባለመከተሉ ምክንያት እንዲፈርስ ጥያቄ እስካልቀረበ ፍ/ቤቱ በራሱ አነሳሽነት የአፃፃፍ ስርዓቱን ምክንያት በማድረግ ውሉን ከጅምሩ ውድቅ ሊያደርግ የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በዚህም ምክንያት የስር ፍ/ቤት በውሉ የአፃፃፍ ስርአትን ባለመከተሉ ምንም አይነት ክርክር ሊቀርብበት አይችልም በሚል የደረሰበት መደምደሚያ የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘውም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 14336 በሐምሌ 27 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 59734 ኀዳር 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የመልካችን እና የተጠሪዎችን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 29181

ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ልየው ቸኮል

2. አቶ ሚሊዮን መንግስቱ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በብድር የተሠጠን ገንዘብ የመክፈያ ጊዜ ጋር በተያያዘ ዕዳው እንደተከፈለ ሊቆጠር የሚችልበትን የሕግ አግባብና ትርጉም የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ባቀረበው አቤቱታ የአሁኑ አንደኛ ተጠሪ ለንግድ ስራቸው ማስፋፊያ የሚውል ታህሳስ 11 ቀን 1987 ዓ.ም በተፃፈ የብድር ውል ብር 10,000.00(አስር ሺ.ህ ብር) የተበደሩ መሆኑን፣ ዋናውን ብድርና ልዩ ልዩ ወጪዎችን ጨምረው በዓመት 14% /አስራ አራት በመቶ/ ወለድ እየታሰበ ከታህሳስ 11 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ በየወሩ ብር 900.00(ዘጠኝ መቶ) እየከፈሉ ሳያቋርጡ እስከ ታህሳስ 10 ቀን 1988 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ከፍለው ለማጠናቀቅ መስማማታቸውን፣ ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ አንደኛ ተጠሪ ለተበደረው ለዚሁ የገንዘብ መጠን የአንድነትና የነጠላ ዋስ በመሆን መፈረማቸውን በመግለፅ ዋናውን ብድር ብር 10,000.00(አስር ሺ.ህ) እስከ ሐምሌ 24 ቀን 1992 ዓ.ም ድረስ የታሰበ ወለድ ብር 13,783.64(አስራ ሦስት ሺ.ህ ሠባት መቶ ሰማንያ ሦስት ብር ከስድሳ አራት ሣንቲም) እና ለኢንሹራንስ የተከፈለ ብር 1,813.80(አንድ ሺ.ህ ስምንት መቶ አስራ ሦስት ብር ከሰማኒያ ሣንቲም) ስለመሆኑ በመዘርዘር በድምሩ ብር 25,097.54(ሃያ አምስት ሺ.ህ ዘጠና ሰባት ብር ከሃምሳ አራት ሣንቲም) ያልተከፈለ ዕዳ የመቀጫ ወለድ 3% ጨምሮ በድምሩ 17% ወለድ እየታሰበ ተጠሪዎች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አንደኛ ተጠሪ ቀርበው የቀረበባቸውን ክስ በመቃወም ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፣ መክፈል ያልቻልኩት በደረሰብኝ ኪሳራ ስለሆነ ለመክፈል የማልችል ስለሆነ ባንኩ ተገንዝቦ ከአስር ዓመት በላይ ስለቆየ ክሱ ውድቅ ነው የሚሉትን ክርክሮች አንስተው ተከራክረዋል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ በበኩላቸው ባንኩ በተበዳሪው ላይ ክስ መስርቶ ሀብቱን ሣያጣራ በዋሱ ላይ ክስ መመስረቱ ያላግባብ መሆኑን፣ ባንኩ በአዋጅ በተሠጠው ሥልጣን መጠቀም ሲገባው ክስ መመስረቱም ከአዋጁ ዓላማ ውጪ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሁኖ በነፃ ልሰናበት ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ከመረመረ በኂላ አመልካች ለአንደኛ ተጠሪ የሠጠው ብድር ክፍያ መጠናቀቅ የነበረበት በውላቸው መሠረት እስከ ታህሳስ 10 ቀን 1988 ዓ.ም ነው፣ አመልካች በዚህ ጊዜ ውስጥ አልጠየቀም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) መሠረት አበዳሪው የተወሠነ ጊዜ ተበጅቶለት በዓመት ወይም ከዓመት በፊት የሚከፈለውን የገንዘብ ዕዳ ሣይጠይቅ እስከ ሁለት ዓመት ጊዜ ከቆየና ከሁለት ዓመት ጊዜ በኂላ ከጠየቀ ገንዘቡ በተበዳሪው እንደተከፈለ ወይም ዕዳው ምህረት እንደተደረገለት ሕግ ግምት ይወስዳል፣ ፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በሠ/መ/ቁጥር 17068 በሰጠው ውሣኔ ላይ በሕግ ግምት የሚሸፈን የፍሬ ነገር ክርክር ተከሳሽ ፍሬ ነገሩን ካደ አልካደ ፍርድ ቤቶች የሕግ ግምቱን ተፈፃሚ ማድረግ አለባቸው የሚል አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሠጥቷል የሚል ምክንያት በመያዝ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም፣ ገንዘቡ በጊዜ ማለፍ እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው የተጠሪዎች ግዴታ ቀሪ ሆኗል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሠርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ የካቲት 22 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት 3(ሦስት) ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የሥር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ መሠረት ያደረገው ድንጋጌ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 ስር የተመለከተውን ያላገናዘበ የሰበር ችሎት ለፍ/ህ/ቁጥር 2024 የሰጠው ትርጉምም አምኖ ለሚከራከር ተከራካሪ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን በመጥቀስ ውሣኔው መሠታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ ተሽሮ ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት በቀረበባቸው ክስ መሠረት በብድር ዕዳ የሚፈለግባቸውን ብር 25097.54(ሃያ አምስት ሺህ ዘጠና ሰባት ብር ከሃምሳ አራት ሣንቲም) ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ 17% (አስራ ሰባት በመቶ) ወለድ እየታሰበ ከክርክሩ ወጪና ኪሣራ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ የሠበር ሠሚ ችሎትም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) መሰረት እንደተከፈለ ይቆጠራል በሚል ውድቅ እንዲሆን የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሠበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡

ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ሁለተኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው ያልቀረቡ ሲሆን አንደኛ ተጠሪ ቀርበው ሰኔ 28 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የፍ/ብ/ህ/ቀጥር 2024(ረ) ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መሆኑን፣ የሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 17068 የሠጠው የሕግ ትርጉም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መሆኑን ዕዳው አለመከፈሉን አምነው የተከራከሩት ሁኔታ አለመኖሩን ገልፀው የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት የተከራከሩ ስለመሆኑ የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅም ሐምሌ 25 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሠረት ውሳኔ እንዲሠጥ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የቀረበውን ክርክር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባዋል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪዎች ያበደረውን ብድርና ወለድ እንደተከፈለው ይቆጠራል በማለት ፍርድ ለመስጠት መሰረት ያደረጉት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተውን የሕግ ግምት በመሆኑ በዚህ አንቀፅ የተጠቀሰው የሕግ ግምት ለባንኮች የሚሰራ መሆን አለመሆኑ ይሰራል የሚባል ቢሆን አመልካች በምስክር፣ በሰነድና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ማስረጃዎች ግምቱን ለማስተባበል ይችላል ወይስ አይችልም? የሚሉት ነጥቦች መፈታት ያለባቸው ጭብጦች ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት በቅድሚያ የሕግ ግምት ምንነት ባሕርያት በጠቅላላውና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌን ይዘትና ባህሪን በትኩረት ማየትና መመርመር ያስፈልጋል፡፡

የሕግ ግምት የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ስንመለከተው ሕግ አውጪውን ለግምት መነሻ ከሚሆኑ የተወሰኑ ፍሬ ጉዳዮች በመነሳት አንድ ድርጊት ተፈፅሟል ወይም አልተፈፀመም ብሎ የሚደርስበትን መደምደሚያ በሕግ

የሚደነግጋቸውን ሁኔታዎች የሚያመላክት ነው፡፡ የሕግ ግምቶች ዳኞች አንድን ፍሬ ጉዳይ የተፈፀመ ወይም ያልተፈፀመ መሆኑን በማስረጃ በማረጋገጥ ረገድ የሚገጥማቸውን ክፍተት በመሙላትና የማስረዳት ሸክም ያለበትን ወገን ጫናውን በማቃለል በኩል የላቀ ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑ ይታመናል፡፡ ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይም የሕግ (የህሊና) ግምት ዓይነተኛ ዓላማ የማስረዳት ሸክም ያለበትን ወገን ጫና የማቃለል፣ ውሳኔ ሠጪ አካልንም ተገቢና ግልፅ ሆኖ የሚታይ የጠራ ማስረጃ ካላገኘ ወደ ውሳኔ በአፋጣኝ እና በቀላሉ እንዲደርስ ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሠጥ መሆኑ ይታመናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ ወደሆነው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ስንመጣ ይህ ድንጋጌ በጠቅላላው ሲታይ በሕግ የሕሊና ግምት የሚሸፈን የፍሬ ነገር ነጥብን (Legal Presumptions) የሚመለከት ሲሆን ዓይነቱም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 እና 2026 ድንጋጌዎቹ ጋር ተዛምዶ ሲታይ ውስን የሆነ የማስተባበያ ማስረጃ የሚቀርብበት የሕግ የህሊና ግምት ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 የተለያዩ የክፍያ አይነቶች የሚዘረዝር ሆኖ ድንጋጌው በጠቅላላው ሲታይ ግን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎች (እዳዎች) በዚሁ የሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ሳይጠየቁ የቀሩ እንደሆነ ክፍያውን(እዳውን) የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ወገን የተባለውን ክፍያ (እዳ) እንደተከፈለ የሕግ ግምት እንደሚወሰድበት ያስገነዝባል፡፡

ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ፣ አግባብነትና ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌ በተጠቀሰው ቁጥር በፊደል(ረ) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ሲሆን ሙሉ ይዘቱም በሚከተለው መልኩ የተቀመጠው ነው፡፡

<u>**ቁ 2024 በሁለት አመት የተወሰነ ጊዜ**</u>

እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ የሚቆጠረው

(ረ) በብድር ለተሰጠ የገንዘብ ወለድና በጠቅላላውም የዓመት ጊዜ ተወስኖለት በየዓመቱ ወይም ከዚህ ባነሰ የጊዜ ውሳኔ ውስጥ ሊከፈል የሚገባው ዕዳ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዘኛው ቅጂም፡-

<u>Art.2024 presumption of payment after two years</u>

The following debts shall be deemed to have been paid where two years have elapsed since they fell due:

(f) interest on loans and generally any sum payable annually or at shorter periodical intervals. በሚል ተቀምጧል፡፡ ከላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ይዘት አቀራረፅ እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የድንጋጌው መጀመሪያ ፓራግራፍ የመክፈያ ጊዜያቸው ከደረሰ ጊዜ አንስቶ ሁለት አመት ያለፋቸው እዳዎች(ክፍያዎች) እንደተከፈሉ ይቆጠራሉ የሚል ሲሆን በተከታይ የተዘረዘሩት ንዑስ ድንጋጌዎች ደግሞ የሕግ ግምት የሚወሰድባቸውን የክፍያ (እዳ) ዓይነቶችን የሚዘረዝር ነው፡፡ በድንጋጌው ፊደል(ረ) ስር የተመለከተው ሲታይ በብድር የተሠጠ ወይም ለማናቸውም የአከፋፈል ሁኔታ በየአመቱ ወይም ከአመት ባነሰ ጊዜ እየተከፈለ እንዲያልቅ ጊዜ ተቆርጦለት የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ እዳው ከበሰለበት ወይም በየተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ገንዘብ ከሆነ ደግሞ ገንዘቡ ተከፍሎ ማለቅ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ያለፈ እንደሆነ በእነዚህ ክፍያዎች (እዳዎች) ላይ ሊጠየቅ የሚችለው የወለድ ክፍያ እንደተከፈለ የሕግ ግምት የሚወሰድ መሆኑን ያሳያል፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው ይህ ድንጋጌ አስገዳጅ የሆነ የሕግ ግምት መሆኑ የመጀመሪያው ባህሪው ሲሆን ማናቸውም የተፈጥሮም ሆነ የሕግ ሰው(ባንክና ሌሎች አበዳሪ ተቋማት) የገንዘብ ብድር ካበደረ በኋላ ብድሩ ተከፍሎ የሚያልቅበትን የጊዜ ገደብ ካበቃ ከሁለት ዓመት በኋላ የብድሩ <u>የወለድ ይከፈለኝ ጥያቄ</u> በሕግ እንደተከፈለ የሚገመት መሆኑን የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተው የሕግ ግምት ለዳኞች የሕሊና ሚዛን እድል የማይሰጥ ዳኞች የነገሩን ሁኔታ በማየት ሲፈልጉ የሚጠቀሙበት፣ ከነገሩ

ሁኔታ አንፃር አስፈላጊ ሆኖ ካላገኙት የሚተውት ፈቃጅ የሆነ የሕግ ግምት አይደለም፡፡ በአንጻሩ ይኸው ድንጋጌ የሚሸፍነው ጉዳይ ባጋጠማቸው ጊዜ ዳኞች ያለምርጫ ሊከተሉትና ሊፈፅሙት የሚገባ አስገዳጅ የሕግ ግምት ነው፡፡

በዚህ ድንጋጌ ስር የሰፈረው የሕግ ግምት ሁሉንም አይነት ዕዳዎች በአጠቃላይ የሚያስቀምጥ በመሆኑ ባንኮች በሚሠጧቸው ብድሮችም ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን ጭምር የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ይኸው አንቀፅ ባንኮች ለሚያቀርቡት ክስ አግባብነት የለውም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ሌላው ነጥብ ይኸው የሕግ ግምት የሚመለከተው ወለዱን ብቻ ነው ወይስ ዋናውን ዕዳ ያጠቃልላል የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ድንጋጌውን በመጠቀስ ወለዱ ብቻ ሳይሆን ዋናውን ዕዳ ጭምር ሁለት ዓመት ካለፈው እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ባንክ ይህ ትክክለኛ ትርጉም አይደለም በማለት ይከራከራል፡፡

በዚህ ረገድ የቀረበውን ቅሬታ ለመፍታት የድንጋጌውን አቀራረፅ እና መንፈስ በጥንቃቄ መመርመር ይስፈልጋል፡፡ አከራካሪ የሆነው የሕግ አንቀፅ <u>በብድር ለተሠጠ የገንዘብ ወለድና</u> በጠቅላላውም የዓመት ጊዜ ተወስኖለት በየዓመቱ ወይም ከዚህ ባነሰ የጊዜ ውሳኔ ውስጥ ሊከፈል የሚገባው ዕዳ የሆነ እንደሆነ …(ሰረዝ የተጨመረ) በማለት የሚደነግግ ነው፡፡ ከዚሁ የሕግ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው የድንጋጌው የመጀመሪያው ክፍል በብድር የተሠጠ የገንዘብ ወለድን በልዩ ሁኔታ ጠቅሶ በሁለት ዓመቱ የሕግ ግምት ውስጥ እንደሚካተት ያስቀምጣል፡፡ ሕግ አውጪው በዚሁ አንቀፅ የሰፈረው የሕግ ግምት ዋናውንም ዕዳ እንደያጠቃልል ቢፈልግ ኖሮ ወለዱን ለይቶ ያስቀምጣል ተብሎ አይገመትም፡፡ ስለዚህ በድንጋጌው የመጨረሻ ክፍል የሚገኘውና **"ሊከፈል የሚገባው ዕዳ"** የሚለው ሐረግ ብድርን ለመመልከት የገባ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ድንጋጌው ወለዱንና ዋናውን ዕዳ ለይቶ በሕግ ግምት የሚሸፍነው ወለዱ ብቻ እንደሚሆን አድርጊ እያለ በመጀመሪያው ደረጃ ፍርድ ቤት ዋናው ዕዳ ጭምር ሁለት ዓመት ካለፈው በሕግ ግምት እንደተከፈለ ይቆጠራል ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ ትክክል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተደነገገው የሕግ ግምት በማስረጃ ቀሪ ሊሆን የሚችለው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 ድንጋጌ ስር በተመለከቱት መንገዶች ነው፡፡ ሆኖም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ስር የተቀመጠውን የሕግ ግምት ለማፍረስ የሚያስፈልጉት ማስረጃዎች በጣም ውስንና በሕግ በግልጽ የተደነገጉ መሆናቸውን ማየትና በጥብቅ ሥርዓት እና በውስን የማስረጃ ዓይነቶች ብቻ ሊስተባበል የሚችል የሕግ ግምት መሆኑን መገንዘብ የግድ ይላል፡፡ በዚህም መሰረት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተደነገገው የሕግ ግምት ቀሪ ሊሆን የሚችለው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 ስር እንደተመለከተው ባለዕዳው በፁሑፍ ዕዳውን ያመነ እንደሆነ በሕግ የተደነገገው የጊዜ ውሳኔ ሳይደርስ ባለገንዘቡ ገንዘቡን እንዲከፍለው ባለዕዳውን ከፍርድ ቤት አስጠርቶ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህም በላይ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026 ድንጋጌ ሲታይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተው በሕግ የተሸፈነ የፍሬ ነገር የህሊና ግምት ከመሓላ ቃል በስተቀር በሌላ ማስረጃ ሊፈርስ እንደማይችል ደንግጓል፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተው የሕግ ግምት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 ስር በተመለከቱት ሁለት ዓይነት ማስረጃዎች ቀሪ የሚሆን ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026 ንዑስ ቁጥር ሁለትና ሦስት ድንጋጌዎች መሰረት ደግሞ በመሓላ ቃል ካልሆነ በቀር በሌላ አይነት ማስረጃ ሊስተባበል የማይችል ማስረጃ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026(1) ድንጋጌ በግልፅ ያስቀመጠው ጉዳይ ነው፡፡ ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተውን የሕግ ግምት ለማስተባበል ያለው ዕድል ውስንና ጠባብ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ እንግዲህ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 አስገዳጅ የሆነ እና በውስን መንገዶች ብቻ ሊስተባበል የሚችል የሕግ ግምት መሆኑ ሁለት ግልፅና የተለዩ ባሕርያት ያሉት ድንጋጌ መሆኑን ከላይ ከገለፅናቸው ህጋዊ ምክንያቶች መገንዘብ የምንችለው ነጥብ ነው፡፡

በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌ ስር የተደነገገውን የሕግ ግምት ባንኮች ለማስተባበል የሚችሉት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2025 እና 2026 ድንጋጌ ስር በተመለከቱት ማስረጃዎች ብቻ ነው ወይስ የሰው ምስክር የሰነድና ሌሎች ማስረጃዎችን በማቅረብ የሕግ ግምቱን ማፍረስና ማስተባበል ይችላሉ? በሌላ አገላለፅ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026 ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ መሰረት ባንኮች ያበደሩትን ብድርና ወለድ

ያልተከፈላቸው መሆኑን ለማስረዳት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ላይ ተፈፃሚነት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ለጥያቄው ተገቢውን ምላሽ ለማግኘት ይቻል ዘንድም ባንኮችና ሌሎች ገንዘብ አበዳሪ ተቋማት ገንዘብ ያበደሩ መሆኑን ያበደሩት ገንዘብ ያልተከፈላቸው መሆኑን ለማስረዳት ሊያቀርቡ ስለሚገባው የማስረጃ አይነት እንደዚሁም በተመሳሳይ ሁኔታ የባንክና የሌሎች ገንዘብ አበዳሪ ተቋማት ደንበኞች ገንዘብ ያለመበደራቸውን ወይም ብድር መክፈላቸውን ለማስረዳት ሊያቀርቡ ስለሚገባው የማስረጃ አይነት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473 ንዑስ አንቀፅ ሁለት የተደነገገውን ማየትና ማገናዘብን ያስፈልጋል፡፡

በመሰረቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472(1) በብድር የተሰጠ ገንዘብ ከአምስት መቶ የኢትዮጵያ ብር በላይ ሲሆን የብድሩን ውል በፁሑፍ ወይም በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም መሓላ ካልሆነ በቀር ለማስረዳት የማይቻል መሆኑን በአስገዳጅ ኃይለ ቃል የደነገገ ሲሆን የተጠቀሰው ድንጋጌ ንዑሰ ቁጥር ሁለት ደግሞ በንዑስ ቁጥር አንድ ከተመለከተው ልዩ የሰነድ ማስረጃ በስተቀር ለብድር ውል ማናቸውም ሌላ ማስረጃ ለማቅረብ የማይቻል መሆኑን ደንግጓል፡፡

ሆኖም በባንክ፣ በአበዳሪ ተቋማት እና በደንበኞቻቸው መካከል ያለውንና የሚኖረውን የጠበቀ እምነትና ግንኙት፣ ባንኮችና አበዳሪ ተቋማት የዕለት ተዕለት የሥራ ተግባራቸው ብድር በመስጠትና ተከፋይ የብድር ገንዘብ በመሰብሰብ ቀልጣፋ የፋይናንስና የንግድ ግንኙነት እንዲኖር በማድረግ በኩል ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው መሆኑን በማገናዘብ ሕግ አውጪው ባንኮችና ሌሎች አበዳሪ ተቋማት ደንበኞቻቸው ገንዘብ የተበደሩና የተበደሩትን ገንዘብ ያልከፈሉ መሆኑን ለማስረዳት በተመሳሳይ ሁኔታ የባንክ ተበዳሪ ብድር ያልወሰደ ወይም የወሰደውን ብድር የከፈለ መሆኑን ለማስረዳት በሰው ምስክር እና በሕሊና ግምት ለማስረዳት የሚችሉ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473(2) ስር ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472 ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ ሲነበብ በባለባንኮችና በደንበኞቻቸው መካከል ስላለ ግንኙነት ሊቀርብ የሚችለውን ማስረጃ አይነት በተመለከተ አመላካች የሕግ ድንጋጌ በመሆኑ ባንኮችም ሆነ ተበዳሪዎች የሰነድ የሰው ማስረጃ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችን በማቅረብ ለማስረዳት የሚችሉ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473 ንዑስ ቁጥር ሦስት ድንጋጌ በተለየ ሲታይም በባለባንኮችና በደንበኞቻቸው መካከል ስላሉ ግንኙነቶች የብድርን ውል ወይም የተበደረውን ገንዘብ መልሶ መክፈልን በምስክሮች ወይም በአእምሮ ግምት ለማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ መደንገጉ ከላይ የተመለከተውን ምክንያት የሚያጠናክር ነው፡፡

የባንክ ደንበኞች የተበደሩትን የብድር ወለድ የከፈሉ መሆኑን በሕሊና ግምት ለማስረዳት ከሚችልባቸው ሁኔታዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌ ስር የተመለከተው የሕግ ግምት አንደኛው ሲሆን ይህ ከሆነ አበዳሪው ባንክ ደንበኛው በህሊና ግምት ከፍዬዋለሁ በማለት ያቀረበበትን ክርክር ለማስተባበልና የብድሩ ወለዱ ያልተከፈለው መሆኑን ለማስረዳት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473(2) ስር በተደነገገው መሰረት የሰው ምስክር፣ የህሊና ግምት፣ የሰነድና ሌሎች ማስረጀዎችን በማቅረብ ግምቱን ማስተባበል የሚችል በመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026 ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ ለባንኮችና ለደንበኞቻቸው መብት ልዩ ጥበቃ የሚያደርገውን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473 ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌን ዋጋ በሚያሳጣ መልኩ ሊተረጎምና ተፈፃሚ ሊሆን አይገባም፡፡ በመሰረቱ የብድር አገልግሎት መስጠት፤ ከተሰጠውም ብድር በማትረፍ የተሻለ አገልግሎት መስጠት የባንክ እና አበዳሪ የፋይናንስ ተቋማት ዋና ተግባር ብቻ ሳይሆን ለእነዚህ ተቋማት ሕልውና መሰረት ሲሆን ተበዳሪዎች ብድሩን ለማንኛውም የኢኮኖሚ መስክ ለማዋል የሚችሉት ይኸው የአበዳሪ ገንዘብ ተቋማት ህልውና ሲጠበቅ ነው፡፡ ይህ ሊሳካ የሚችለው ደግሞ ህግ አውጭው ለእነዚህ ተቋማት ያደረገውን ልዩ ጥበቃ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በሕጉ ሊፈፀም የሚችል ውጤት የሚሠጥ ትርጉም በመስጠት መሆኑን አምነንበታል፡፡ ስለሆነም በእነዚህ ሕጋዊ ምክንያቶች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026(1) ስር የተመለከተው ድንጋጌ በባንኮች፣ በሌሎች አበዳሪ ተቋማት እና በደንበኞቻቸው መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተፈፃሚነት የሌለው የሕግ ድንጋጌ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም ባንኮች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር በተመለከተው የሕግ ግምት የሚገዙ ቢሆንም ለደንበኞቻቸው ያበደሩት የብድር ወለድ ያልተከፈለ መሆኑን የሰው ምስክር፣ የሰነድና ሌላ ማስረጃ በማቅረብ ይህን

የሕግ ግምት ለማስተባበል የሚችሉበት የፍርድ ሂደት መኖር ይገባዋል፡፡ በዚህ መሰረት በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የብድሩ ወለዱ ያልተከፈለው መሆኑን ለማስረዳት እድሉን ሳይሠጡ፣ ያቀረባቸውንም ማስረጃዎችን ሳይመረምሩና ሳይመዝኑ ውሳኔ መስጠታቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473(2) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ መንፈስና ዓላማውን ባላገናዘበ መልኩ ሆኖ ስለአገኘነው ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

በስር ፍርድ ቤት በዋና ተበዳሪነት የተከሰሱት የአሁኑ አንደኛ ተጠሪ ከስር ጀምሮ ያቀረቡትን ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ስር የሰፈረው የሕግ ግምት እና አመልካች ካቀረባቸው ማስረጃዎች አንፃር ነገር ስንመለከተው በአመልካች የተጠየቀው እዳ ያልተከፈለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም አንደኛ ተጠሪ የሕግ ግምት ተጠቃሚ ቢሆኑም አመልካች ይህንን የሕግ ግምት ሊያፈርስ የሚችል በቂ ማስረጃ ያቀረበ በመሆኑ በክርክሩ ሂደት በተረጋገጠው መሰረት አንደኛ ተጠሪ ዕዳውን የማይከፈሉበትን ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ የሁለተኛ ተጠሪ ክርክር ሲታይም አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ክስ መስርቶ ሃብት ሳያጣራና በህጉ በተሠጠው ስልጣን መሰረት መብቱን ሳያስከብር ዋሱ ላይ ክስ መመስረት አይችልም በማለት የሚከራከሩ የነበረ መሆኑንና በዚህ ችሎትም ካለመቅረባቸውም በላይ የአንደኛ ተጠሪ ክርክር የሚጠቅማቸው አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ የገቡት የዋስትና ዓይነት የአንድነትና የነጠላ እንደመሆኑ መጠን አመልካች ተጠሪን ከዋናው ተበዳሪ ጋር በአንድ ላይ መክሰሱ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1933(1) ድንጋጌ አንፃር ህጋዊ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረትም የተሠጠውን ሥልጣን ባንክ የሚጠቀመው መያዣ በአስያዡ ተበዳሪዎች ላይ ሆኖ በእነዚህ ተበዳሪዎችም ቢሆን ባንክ በአዋጁ የተሠጠውን ሥልጣን በመተው ፍርድ ቤት ክስ ከመመስረት የሚከለክልበት ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ሕጎቹ ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ ተጠሪም በገቡት ግዴታ አይነትና በክርክሩ ሂደት በተረጋገጠው መሰረት ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ገንዘብ ለአመልካች የማይከፍሉበትን ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 09312 ሚያዝያ 26 ቀን 1998 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 02227 ሕዳር 27 ቀን 1999 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት በቀረበባቸው ክስ መሰረት በብድር ዕዳ የሚፈለግባቸውን ብር 25097.54(ሃያ አምስት ሺህ ዘጠና ሰባት ብር ከሃምሳ አራት ሳንቲም) ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ 17%(አስራ ሰባት በመቶ) እየታሰበ በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች እንዲከፍሉ በማለት ወስነናል፡፡

3. አመልካች ለዳኝነት ያወጣውን ወጪ ደረሰኝ በመስከረው መሰረት ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች እንዲከፍሉ ብለናል፡፡

4. በክርክሩ የወጡትን ሌሎች ወጪዎችና ኪሳራዎችን የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

የዚህ መዝገብ ውሳኔ ግልባጭ በመ/ቁጥር 26363፣ 32196፣ 32199፣ 32202፣ 32203፣ 32205፣ 33222፣ 33282፣ 34329 እና 35605 ጋር ይያያዝ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 35758

ታህሣሥ 20 ቀን 2002

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መሰሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ገብረመድኅን አየናቸው } ቀረቡ፡፡
2. እንግዳ አየናቸው

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ሰብስቤ ኃይሌ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በብድር የተሰጠን ገንዘብ የመክፈያ ጊዜ ጋር በተያያዘ ዕዳው እንደተከፈለ ሊቆጠር የሚችልበትን የሕግ አግባብና ትርጉም የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ መጋቢት 16 ቀን 1997 ዓ.ም. በፃፉት አቤቱታ የአሁኑ አመልካቾች ጥር 24 ቀን 1990 በተፃፈ የብድር ውል ብር 32,000.00 /ሠላሣ ሁለት ሺህ ብር/ የተበደሩ መሆኑን፣ ብድሩን በየሣምንቱ ብር 250.00 እየከፈሉ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1992 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ከፍለው ለማጠናቀቅ መስማማታቸውን፣ ተበዳሪዎች በጋራ በጠቅላላው ብር 9090 /ዘጠኝ ሺህ ዘጠና ብር/ የመለሱላቸው ሰለመሆኑ በመዘርዘር ቀሪውን ብር 22,910.00 /ሃያ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስር ብር/ ከነወለዱ አመልካቾች እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎችም ቀርበው የቀረበባቸውን ክስ በመቃወም ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፣ ፊርመን የወሰድነው ገንዘብ የለም፣ አበዳሪው ፊርማችንን የሚያውቁ በመሆናቸው እራሳቸው ውሉን አዘጋጅተውና ገንዘቡን በመሰላቸው ሞልተው ያቀረቡት ሠነድ ነው፣ የቀረበው የብድር ውሉ ሠነድ ትክክል ነው ቢባል እንኳ ውሉ በተፈፀመበት ጊዜ ለዕለት የምንመገበው ያጣን ችግረኞች ስለነበርን ይህንኑ አጋጣሚ ተጠቅመው ጥቂት ገንዘብ አበድረው በ70% /ሰባ በመቶ/ አስበው ካበደሩን ገንዘብ ጋር ደምረው ያስፈረሙን ሕገ-ወጥ የአራጣ ብድር ውል በመሆኑ ፈራሽ ነው የሚሉትን ክርክሮች አንስተው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በብድር ውሉ ላይ አለ የተባለውን ፊርማ በፌዴራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርመራ እንዲከናወን ከአደረገ በኋላ ጉዳዩን በመመርመር ውሉ ላይ ያለው ፊርማ የተበዳሪዎች መሆኑ ተረጋግጧል፣ ውሉ ሕገ-ወጥ ሊባል የሚችልበት ምክንያት የለም በማለት የተጠሪዎችን መከራከሪያ ውድቅ ከአደረገ በኋላ ለክሱ ኃላፊ በማድረግ በክሱ የተጠቀሰውን ብር 22,910.00 /ሃያ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስር ብር/ ክሱ ከቀረበበት ቀን አንስቶ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም

ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሠርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካቾች የካቲት 17 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፉት 3 /ሦስት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የሥር ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/"ን" ድንጋጌ መሠረት ተደርጎ የቀረበውን ክርክር ውድቅ ማድረጉ ያላግባብ መሆኑን፣ ውሣኔውም ለዚሁ ድንጋጌ ሰበር ችሎቱ በመ/ቁጥር 17068፣ 14047 እና 15493 የሰጠውን ትርጉም ያላገናዘበ መሆኑን በመጥቀስ ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሽሮ አመልካቾች በተጠሪ በብድር ዕዳ የሚፈለግባቸው ገንዘብ የለም ተብሎ ከክርክሩ ወጪና ኪሣራ ጋር ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት በፍ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ መሠረት ያቀረቡት ክርክር የመታፉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ሐምሌ 24 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፉት ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ- የፍ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ በሥር ፍርድ ቤትም ያልተነሳ መሆኑን፣ አመልካቾች ዕዳው ያልተከፈለ መሆኑን ስለአመኑ ክርክራቸው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልፀው የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት የተከራከሩ ስለመሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካቾች ጥቅምት 04 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ የመልስ መልስ ማመልከቻ የፍ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/"ን" መሠረት ያደረገ ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያነሱ መሆኑን በመጥቀስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሠረት ውሣኔ ይሠጥልን ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በተጠሪ እና በአመልካቾች መካከል የብድር ውሉ የተፃፈው ጥር 24 ቀን 1990 ዓ.ም. ሆኖ የብድሩ አመላለስም በየሣምንቱ ብር 250.00 /ሁለት መቶ ሃምሣ ብር/ እየተከፈለ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1992 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ሊጠናቀቅ መስማማታቸውን፣ የአሁኑ ተጠሪ የብድር ገንዘቡን አመልካቾች አልመለሱም፤ ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት በፍርድ ቤት ክስ የመሠረቱት መጋቢት 16 ቀን 1997 ዓ.ም. መሆኑ እና አመልካቾች ስለ ውሉ ህጋዊ አለመሆን በውሉ ላይ ያለው ፊርማ የእነሱ አለመሆኑና ውሉም አራጣ ሊባል የሚችል መሆኑን በመጥቀስ ኃላፊነት የለብንም በማለት መከራከራቸውን ነው፡፡ በዚህ ችሎት አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት የስር ፍርድ ቤት የብድር እዳው ክፍያ ጥያቄ በሁለት ዓመት የጊዜ ማለፍ እንደተከፈለ ሊቆጠር ይገባል በማለት ያቀረብነውን ክርክር ያለፈው ያላግባብ ነው በሚል ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ ይህ የአመልካቾች ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ በዚህ ችሎት መከራከሪያ ሊሆን አይችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ በሕግ የሚሸፈን የፍሬ ነገር ክርክርን በተከራካሪ ወገኖች ባይነሳም ፍርድ ቤቱ በራሱ ሊያነሳው የሚችለው ጉዳይ በመሆኑና ይህም ስለመሆኑ ይህ ችሎት ከዚህ በፊት በሰ/መ/ቁጥር 17068 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም የሰጡበት በመሆኑ አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት ማንሣት አለማንሳታቸው ሊያስከትል የሚችለው የስነ-ሥርዓት ግድፈት ስለሌለው ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር የምንቀበለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በዚህ ጉዳይ ዋናውና የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ነጥብ፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ድንጋጌ አግባብነቱ ለዋናው የብድር ገንዘብ ነው? ወይስ ለብድሩ ገንዘብ ወለድ ብቻ? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ይቻል ዘንድ ስለ የሕሊና ግምት ምንነትና ዓይነቶች እንዲሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ድንጋጌን ይዘት፣ አቀራረጹንና መንፈሱን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

በመሠረቱ የሕሊና ግምት /Presumption/ ሲባል ቀደም ብሎ በነገሮች መካከል የነበራቸውን የግንኙት ልምድ መሠረት በማድረግ /Experience of previous connections/ ከታመኑ ወይም በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ

ነገሮች በመነሳት በአንፃሩ ሌላ አዲስ ፍሬ ነገር መከሰትን ወይም እውነትን በአእምሮ መቀበል /inference/ ማለት ስለመሆኑ በዚህ ረገድ የተፃፉት የሕግ ምሁራን ጽሁፎች ያሳያሉ፡፡ የዚህ ጽንሰ ሀሳብ ውጤትም አንድን አከራካሪ የሆነ ፍሬ ነገር መኖር አለመኖር በማስረጃ ማረጋገጥ ሳያስፈልግ እንዳለ መቀበል ስለመሆኑም ያሰምሩበታል፡፡ ይሁን እንጂ የሕሊና ግምት ዓይነቶች የተለያዩ ስለሆኑ ውጤታቸውን ፍርድ ቤት የሚቀበልበት መንገድም የተለያየ ነው፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይም የሕግ የሕሊና ግምት ዓይነተኛ ዓላማ የማስረዳት ሸክም ያለበትን ወገን ጫና የሚያቃልል ውሣኔ ሰጪ አካልንም ተገቢና ግልጽ ሆኖ የሚታይ የጠራ ማስረጃ ካላገኙ ወደ ውሣኔ በአፋጣኝ እና በቀላሉ እንዲደርስ ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሠጥ መሆኑ ይታመናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ ወደሆነው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ስንመጣ ይህ ድንጋጌ በጠቅላላው ሲታይ በሕግ የሕሊና ግምት የሚሸፈን የፍሬ ነገር ነጥብን /Legal presumptions/ የሚመለከት ሲሆን ዓይነቱም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 እና 2026 ድንጋጌዎች ጋር ተዛምዶ ሲታይ ውስን የሆነ የማስተባበያ ማስረጃ የሚቀርብበት /not freely rebuttable/ የሕግ የሕሊና ግምት ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 የተለያዩ የክፍያ ዓይነቶች የሚዘረዝር ሆኖ ድንጋጌው በጠቅላላው ሲታይ ግን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎች /እዳዎች/ በዚሁ የሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሳይጠይቁ የቀሩ እንደሆነ ክፍያውን /እዳውን/ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ወገን የተባለውን ክፍያ /እዳ/ እንዲከፈለ የሕግ ግምት እንዲወሰድበት ያስገነዝባል፡፡

ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነትና ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ በተጠቀሰው ቁጥር በፊደል /ረ/ ስር የተመለከተው ድንጋጌ ሲሆን ሙሉ ይዘቱም በሚከተለው መልኩ የተቀመጠው ነው፡፡

<u>**ቁ 2024 በሁለት ዓመት የተወሰነ ጊዜ**</u>

እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ የሚቆጠረው፡፡

/ረ/ በብድር ለተሰጠ፣ የገንዘብ ወለድና በጠቅላላውም የዓመት ጊዜ ተወስኖለት በየዓመቱ ወይም ከዚህ ባነሰ የጊዜ ውሣኔ ውስጥ ሊከፈል የሚገባው ዕዳ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዝኛው ቅጂም፡-

Art. 2024 presumption of payment after two years

The following debts shall be deemed to have been paid where two years have elapsed since they fell due:

/f/ Interest on loans and generally any sum payable annually or at shorter periodical intervals. በሚል ተቀምጧል፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ይዘት አቀራረጽ እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የድንጋጌው መጀመሪያ ፓራግራፍ የመክፈያ ጊዜያቸው ከደረሰ ጊዜ አንስቶ ሁለት ዓመት ያለፋቸው እዳዎች /ክፍያዎች/ እንደተከፈሉ ይቆጠራሉ የሚል ሲሆን በተከታታይ የተዘረዘሩት ንዑስ ድንጋጌዎች ደግሞ የሕግ ግምት የሚወሰድባቸውን የክፍያ /እዳ/ ዓይነቶችን የሚዘረዝር ነው፡፡ በድንጋጌው ፊደል /ረ/ ስር የተመለከተው ሲታይ በብድር የተሰጠ ወይም ለማናቸውም የአከፋፈል ሁኔታ በየአመቱ ወይም ከዓመት ባነሰ ጊዜ እየተከፈለ እንዲያልቅ ጊዜ ተቆርጦለት የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ እዳው ከበሰለበት ወይም በየተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ገንዘብ ከሆነ ደግሞ ገንዘቡ ተከፍሎ ማለቅ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ያለፈ እንደሆነ በእነዚህ ክፍያዎች /እዳዎች/ ላይ ሊጠየቅ የሚችለው የወለድ ክፍያ እንደተከፈለ የሕግ ግምት የሚወሰድ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም የሚያስገነዝበው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ስር የተመለከተው ድንጋጌው ተፈፃሚነት የሚኖረው በብድር ለተሰጠ ገንዘብ ወለድ ላይ መሆኑንና ዋናውን የብድር ገንዘብ የማይጨምር መሆኑ ነው፡፡ ምክንያቱም ድንጋጌው ዋናውን የብድር ገንዘብ የሚጨምር ቢሆን ኖሮ ሕግ አውጪው የብድርን ገንዘብንና ወለድ በማለት ያስቀምጠው ነበር እንጂ ለብቻው

ነጥሎ የብድር ገንዘብ ወለድን በማለት አይጽፌውም ነበር፡፡ ብድር ዋናው ዓላማ ሰዎች ዘርፈ ብዙ የሆኑ የግልና ማኀበራዊ ችግሮቻቸውን ማቋቋሚያ መንገድ ሆኖ ለኑሮ ድኀነትንና መድኀን መሆን ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ሕጉም የዚህ ዓይነት ዓላማ ያለውን የሰዎች ሕጋዊ ግንኙነት መጠበቅ አለበት፡፡ ሕግ ሲተጎምም ሊፈፀም የሚችል ውጤት እንዲኖረው በማድረግ ስለመሆኑም ጠቅላላ የሕግ አተረጓጎም ደንቦች የግድ የሚሉት ነው፡፡ በመሆኑም ከብድር አስፈላጊነትም ሆነ ከሕግ አተረጓጎም ደንብ አንፃር ሲታይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ሥር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነቱ በብድር ለተሰጠ የገንዘብ ወለድ እንጂ ለዋናው የብድር ገንዘብ አለመሆኑን ከድንጋጌው ይዘት፣ አቀራረጽና መንፈስ የምንገነዘበው ነጥብ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ክስ ሲመሰርቱ ዳኝነት የጠየቁት ዋናውን የብድር ገንዘብ ሲሆን አመልካቾች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት የሚከራከሩት ይህንኑ ዋናውን የብድሩ ገንዘብ ነው፡፡ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የብድር ውል ስምምነት የብድር ገንዘቡ በብድሩ ወቅት ወለድ የሚታሰብበት ስለመሆኑ አይገለጽም፡፡ ተጠሪ ዳኝነት ሲጠይቁ ወለድ እንዲታሰብላቸው የገለጹትም ከክሱ በኋላ ያለውን ሕጋዊ ወለድ ነው፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ መሠረት በሁለት ዓመት ጊዜ ማለፍ እንደተከፈለ ሊቆጠር እና በፍ/ቤቱ የሕግ ግምት የሚወሰድበት የብድር ወለድ በተያዘው ጉዳይ የለም፡፡ አመልካቾች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም አመልካቾች ብር 22,910 /ሃያ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስር ብር/ ለተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክስ ከቀረበበት ቀን አንስቶ ከሚታሰብ ዘጠኝ በመቶ /9%/ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03288 ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 59093 ታህሣሥ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 45422

ጥር 13 ቀን 2002 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መሰሠ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ ፈታሂ ባየህ
2. ወ/ሮ ጽጌ ባየህ
3. ወ/ሮ ተዘራ ባየህ
4. ፍሬሕይወት ባየህ
5. አቶ ዘውገ ባየህ
6. ሰብለሥላሴ ባየህ
7. ወ/ሮ ማስረጃ ባየህ

በራሣቸውና በሌሎች ወኪሎቻቸው አቶ ፈታሂ ባየህ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች**፡- 1. ወ/ሮ አስራት ባየህ - ከክርክሩ ውጪ ሁነዋል፡፡
2. ዲያቆን ገ/ሕይወት ንጋቱ
3. ቀኝ ጌታ ልሳነወርቅ

ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ቤት ይለቀቅልን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካቾች ግንቦት 02 ቀን 1998 ዓ.ም. አሻሽለው በፃፉት እና በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ በመሠረቱት የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- አመልካቾች እና አንደኛዋ ተጠሪ ከሟች ወላጆቻቸው ከአዛዥ ባየሕ ገ/ኢየሱስና ከእናታቸው ከወ/ሮ ደብሪቱ ኃ/ጊዮርጊት በውርስ የተላለፈላቸው በአዲስ አበባ ከተማ፣ በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15/16/17 ወስጥ የሚገኙ በአባታቸው ስም ተመዝግበው የሚታወቁትን፣ ቁጥራቸው 922፣ 738፣ 739 እና 740 የሆኑ ቤቶች እንዳላቸው፣ የቤቶቹን ስመ ሃብት አንደኛ ተጠሪ በራሳቸው ስም በማድረግ ቁጥራቸው 739 እና 740 የሆኑትን ቤቶች ከሁለተኛ እና ለሦስተኛ ተጠሪዎች በወለድ አግድ በማስያዝ ብድር ተበድረው ለግላቸው እንደሚጠቀሙበትና በስምምነት ክፍፍል እንዲደረግ ሲጠየቁ ፈቃደኛ ሆነው ባለመገኘታቸው የውርስ አጣሪ ተሹሞ ውርሱ እንዲጣራ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች በማመላከት ፍርድ ቤቱ የውርስ አጣሪ በመሾም ውርሱ ከተጣራ በኂላ ሪፖርቱ ለፍርድ ቤቱ ጥር 14 ቀን 1998 ዓ.ም. ተልኮ የካቲት 09 ቀን 1998 ዓ.ም. ፍርድ ቤቱ የመዘገበው መሆኑን፣ በዚህ የውርስ አጣሪው ሪፖርት አጠቃላይ የውርስ ሃብት ግምት እና የወራሾች ድርሻ እንዲሁም የተጠቀሙበት ሀብት መጠን ተለይቶ መቀመጡን፣ አንደኛ ተጠሪ ያላግባብ ቤቱቹን ሕጋዊ ባልሆነ የወለድ አግድ ውል ለሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ያሰያዙ መሆኑንና በወለድ አግድ ውል ቤቶቹን የያዙት ተጠሪዎችም አስያዢ መብት ሳይኖራት እያወቁ የያዙት መሆኑን ዘርዝረው ቁጥራቸው 739 እና 740 የሆኑ ቤቶችን ተጠሪዎች እንዲያስረክቡ፣ አጠቃላይ የውርስ ሃብት የሆኑ ንብረቶች ከእነ ይዞታቸው

በአውራሽ አባታቸው ስም የነበረው የባለቤትነት ማረጋገጫ ስም በአመልካቾች ስም እንዲዛወር ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቀቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ፣ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በአዋጅ ተወርሷል ተብሎ የቀበሌው መስተዳደር አከራይቶ ቆይቶ እያለ አንደኛ ተጠሪ ከአዋጅ ውጪ ያላግባብ፣ የተወረሰ /የተወሰደ/ ነው በማለት በፍርድ ቤት ከሰው በፍርድ ኃይል አስለቅቀው በመረከብ በፍ/ቤት ውሣኔ ባለመብት ሆነው፣ የቤት ባለቤትነት ደብተርና ካርታም በስማቸው አረጋግጠው፣ ይዞታቸው በመሆኑ፣ መጋቢት 01 ቀን 1994 ዓ.ም. በተፃፈ የውል ሰነድ ብር 10,000.00 /አስር ሺህ/ ተቀብለው ቁጥሩ 739 የሆነውን ቤት እስከ መጋቢት 1999 ዓ.ም. ድረስ የሚቆይ ወለድ አግድ ውል፤ ለአምስት ዓመት በማስያዝ የተዋዋሉ መሆኑን፣ ቤቱም ተረክበው ይዘው እንደሚገኙና አንደኛ ተጠሪ የተበደሩትን ገንዘብ ሲመልሱ ቤቱን እንደነበረ ሊያስረክቧቸው መዋዋላቸውን፣ አመልካቾች በስምምነት ድርሻቸውን ይዘው እየተጠቀሙ የሚገኙ በመሆኑና በቤቱ ላይ አንደኛ ተጠሪ በሕጉ አግባብ ባለመብት ከሆኑ በኋላ ያቋቋሙት የወለድ አግድ ውል ሕጋዊ መሆኑን እንዲሁም አንደኛ ተጠሪ ቤቱን በብዙ ድካምና ወጪ አስመልሰው መያዛቸውን እያወቁና እየተረዱ መብት ሳይኖራቸው ቤቱን አስይዘዋል ማለታቸው በሕግ ተቀባይነት የሌለው ነው በሚል ተከራክረዋል፡፡ አንደኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸው የጽሁፍ መልስ መስጠት መብት የታፈባቸው ሲሆን ሦስተኛ ተጠሪ በቃል ክርክር ወቅት ቀርበው ቁጥሩ 740 የሆነ ቤት በወለድ አግድ ውል ለሰባት ዓመታት እንደያዙ፣ የውሉ ዘመንም እስከ ጥር 2007 ዓ.ም. መሆኑን ገልፀው ጊዜው ሳያልቅ ቤቱን የሚያስረክቡበት ምክንያት እንደሌለ ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ በቤት ቁጥር 739 የተቋቋመው የወለድ አግድ ውሉ የውል ዘመኑ ማብቃቱን በመግለጽ አንደኛ ተጠሪ የተቀበሉትን ብር 10,000.00(አስር ሺህ) ለሁለተኛ ተጠሪ መልሰው ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካቾች እና ለአንደኛ ተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል ቤቱንም አመልካቾችና አንደኛ ተጠሪ እኩል ሊካፈሉት ይገባል ሲል የወሰነ ሲሆን የቤት ቁጥር 740 የሆነውን በተመለከተ ደግሞ የወለድ አገድ ውሉ እስከ ጥር 2007 ዓ.ም. ድረስ የሚቆይ በመሆኑ ሦስተኛ ተጠሪ ቤቱን ሊያስረክቡ እንደማይገባ፣ የውሉ ዘመን ሲያልቅ በውሉ የተገለፀውን ገንዘብ አንደኛ ተጠሪ ለሦስተኛ ተጠሪ መልሰው ሦስተኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካቾችና ለአንደኛ ተጠሪ እንዲያስረክቡና ቤቱንም ሊከፋፈሉት እንደሚገባ፣ እንዲሁም በቤት ቁጥር 739 እና 740 እስኪከፋፈሉ ድረስ በአመልካቾችና በአንደኛ ተጠሪ ስም የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርና ካርታ በጋራ ሊያወጡበት ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወምና ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካቾች ሚያዝያ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. በፃፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አንደኛ ተጠሪ በአከራካሪው ቤቱ ላይ ሙሉ መብት የሌላቸው ሆኖ እያለ እና የወለድ አግድ ውሉም በሕጉ አግባብ ያልተመዘገበ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የውርስ ንብረቱ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች እንደያዙት እንዲቆዩ የተደረገው እና ውሉ ሕጋዊ ነው መባሉ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የወለድ አግድ ውሉ ሕጋዊ ነው መባሉ ባግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ኀዳር 10 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት ሦስት ገጽ የመልስ ማመልከቻ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ነጥብ በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳ ስለመሆኑ እና ውሉ ሕጋዊ ነው የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ከክርክሩ ውጪ እንዲሆኑ ተደርጎአል፡፡ አመልካቾች ታህሣሥ 08 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት ሁለት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤቶች ያቀረቡት ክስ ይዘት ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ቤቶች በውርስ ያገኟቸው መሆኑን፣ በእነዚህ ቤቶች ላይ አመልካቾችና አንደኛ ተጠሪ ያላቸው ድርሻ በውርስ አጣሪ ተለይቶ መታወቁንና ቤቶቹን ለማካፈል አንደኛ ተጠሪ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን እንዲሁም ሕጋዊ ባልሆነ የወለድ አግድ ውል ለሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ቤቶቹን አንደኛ ተጠሪ አስተላልፈው እንደሚገኙ ገልፀው ቤቶቹን እንዲያስረክቧቸውና የቤቶቹ ስመ ሃብት ወደ ወራሾች እንዲዞር ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ መሆኑን ነው፡፡ የአሁኑ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ደግሞ የወለድ አግድ ውሉ በሕጉ አግባብ የተደረገ ስለሆነ ቤቶቹን ልናስረክብ አይገባም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ከዚህ የግራ ቀኙ ክርክር መገንዘብ የሚቻለው አመልካቾች በግልጽ እየተቃወሙ ያሉት የወለድ አግድ ውሉ በሁለት ምክንያቶች ሕጋዊ አይደለም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ይኸውም አንዱ ውሉ የተደረገው በንብረቱ ላይ ሙሉ መብት በሌላቸው አንደኛ ተጠሪ በመሆኑ ሕጋዊ አይደለም የሚል ሲሆን ሌላው ተደረገ የተባለው የወለድ አግድ ውልም ቢሆን ስልጣን ባለው አካል ፊት የልተደረገና ያልተመዘገበ ስለሆነ ሊፀና የሚገባው አይደለም የሚል ነው፡፡ እንግዲህ የአመልካቾች ክርክር ቤቱ ያላግባብ ተይዞብናል የሚል ስለመሆኑ በቀላሉ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች የአመልካቾች ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1810 ያላገናዘበ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር የአመልካቾችን የስር ክርክር ይዘቱን ባግባቡ መሠረት ያላደረገ ስለሆነ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ይልቁንም የወለድ አግድ ውሉ ስልጣን ባለው አካል ፊት ያልተደረገና ንብረቱ በሚገኝበት መዝገብ ያልተመዘገበ ስለመሆኑ ተጠሪዎች በማመን የሚከራከሩ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ የወለድ አግድ ውሉ ስልጣን ባለው አካል ፊት ያልተደረገና ያልተመዘገበ ከሆነ ውጤቱ ምንድነው? የሚለውን በዚህ ረገድ የተደነገጉትን የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች በማየት ምላሽ ማግኘት የሚችለው ነጥብ ነው፡፡

በመሠረቱ የወለድ አግድ ውል የሚቋቋመው የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣን መቋቋም የሚመለከቱት ድንጋጌዎችን በመከተል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3118 ድንጋጌ ያጣቅሳል፡፡ በዚህ አግባብ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3045 እና 3052 ሲሆኑ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚደረግ የመያዣ ውል በጽሁፍ መሆን እንዳለበትና የማይንቀሳቀስ ንብረት በሚገኝበት መዝገብ መመዝገብ እንዳለበት የስገነዝባሉ፡፡ ይህን ያላሟላ የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውል የሕግ ውጤት አይኖረውም፡፡ በመሆኑም የወለድ አግድ ውል በሕጉ ጥበቃ የሚደረግው በሕጉ አግባብ ተቋቁሞ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን በዚሁ መንገድ የተደረገ የወለድ አግድ ውለ የለም፡፡ ስለሆነም ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች አበድረናል የሚሉትን ገንዘብ ከሚመለከተው ሰው በሕጉ አግባብ ከሚጠይቁ በስተቀር ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ቤቶች የሚይዙበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም የወለድ አግድ ውል የተባለው በሕጉ አግባብ የተቋቋመ መሆን አለመሆኑን ከሕጉ ጋር ሳያገናዝቡት ቤቶቹን ተጠሪዎች ሊለቁ አይገባም በማለት የሰጡት ውሣኔ አመልካቾችን በውርስ የተላለፈላቸውን የባለቤትነት መብትን ያጣበበ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10218 ጥቅምት 01 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 62724 የካቲት 27 ቀን 2001 ዓ.ም. የፀናው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ከአንደኛ ተጠሪ ጋር አድርገናል፡፡ የሚሉት የወለድ አግድ ውል ፈራሽ ነው ብለናል፡፡
3. ሁለተኛ ተጠሪ የቤት ቁጥር 739፣ ሦስተኛ ተጠሪ ደግሞ የቤት ቁጥር 740 ለአመልካቾች ሊያስረክቡ ይገባል፡፡
4. አመልካቾች እና አንደኛ ተጠሪ በቤቶቹ ላይ በጋራ ያላቸውን መብትና ጥቅም በሥር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ እንደተጠበቀ ነው ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ 48967

ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሳዲቅ ሐሰን - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - ነገረ ፈጅ

አቶ ጌታነህ ቸሬ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ለውጭ አገር የተደወለ የስልክ አገልግሎት ክፍያ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ከታህሳስ ወር 2003 ዓ.ም እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር መስከረም 2004 ዓ.ም ድረስ የተጠቀመበትን ብር 19,793.52(አስራ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ሦስት ብር ከሃምሳ ሁለት ሣንቲም) እና የስልክ ቀፎ ዋጋ ብር 249.55(ሁለት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ አምስት ሣንቲም) በድምሩ ብር 20,043.07 (ሀያ ሺ አርባ ሶስት ብር ከሰባት ሣንቲም) የስልክ አገልግሎት ክፍያና የቀፎ ዋጋ እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካች በበኩሉ የተጋነነ ሒሳብና ያልደወሉበት የውጭ አገር የስልክ ሒሳብ የተጠየቁና ይኸም በኮንፒዩተር ስህተት የመጣ መሆኑን በመግለፅ ጉዳዩ እንዲመረመር ለአመልካች መሥሪያ ቤት ያመለከቱ መሆኑንና በዚህ መሠረት የታህሣሥ ወር ክፍያ ተመርምሮ ከብር 891.25(ስምንት መቶ ዘጠና አንድ ብር ከሃያ አምስት ሣንቲም) ወደ ብር 92.26 (ዘጠና ሁለት ብር ከሃያ ስድስት ሣንቲም) ዝቅ ያለ መሆኑን ገልፀው ሒሳቡ ሣይመረመር በዓለም ላይ ወደ ሌላ አገር USSR ደውለሀል ተብዬ መከሰሴ ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ የታህሣሥ ወር በአማካኝ ክፍያ እንዲፈፅሙ ስለተደረገ እንጅ ተመርምሮ ስህተት በመሆኑ ሒሳቡ አልተቀነሰም የተገለገሉበትን ስልክ ዋጋ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ አመልካች በክሱ የተገለፀውን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኙ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የጠየቅሁት የስልክ ግልጋሎት ክፍያ በኮንፒዩተር ስህተት ምክንያት ተጋንኖ የተጠየቀ ነው፡፡ ይኸ እንዲመረመርልኝ ያቀረብኩት አቤቱታ በመቀበል እንዲመረመር ሣይደረግ ተጠሪ የጠየቀውን ሂሳብ እንድከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ያቀረብነው ክስ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ ከአመልካች ላይ የጠየቀው የስልክ ግልጋሎት ዋጋ የተጋነነ በኮምፒዩተር ስህተት የመጣ ነው የሚለውን የአመልካች አቤቱታ መሠረት በማድረግ ጉዳዩ በባለሙያ ሣይመረመር ተጠሪ የጠየቀውን ሂሳብ በሙሉ አመልካች እንዲከፍሉ መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የስልክ መስመሩ ተገልጋይና የስልክ ቀፎው ባለይዞታ መሆኑ በእሱ ስልክ ቁጥር ወደ ውጭ አገርም ሆነ በአገር ውስጥ የተደረገው የስልክ ግንኙነት በእሱ የተፈፀመ ነው የሚል ግምት የሚያሣድር ነው፡፡ ሆኖም አመልካች የተጠየቀው የስልክ ግልጋሎት ዋጋ ከወትሮው የተለየና የተጋነነ መሆኑን አመልካች እስከ አዲስ አበባ ዋናው መሥሪያ ቤት ድረስ ያመለከተ መሆኑንና እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር የታህሳስ ወር 2003 ብር 891.25(ስምንት መቶ ዘጠና አንድ ብር ከሃያ አምስት ሣንቲም) ተጠይቀው የነበረውን 92.26 /ዘጠና ሁለት ብር ከሀያ ስድስት ሣንቲም/ እንዲከፍል መደረጉን አመልካችና ተጠሪ አልተካካዱም፡፡ አመልካችና ተጠሪ የተለያዩበት ዋናው ነጥብ አመልካች ኮንፒዩተሩ ተመርምሮ ስህተት ሆኖ በመገኘቱ በፊት የተጠየቅሁት ገንዘብ ተቀንሶ ከፍያለሁ ሲል ተጠሪ በበኩሉ በአቨሬጅ ወጥቶና በዚያ መሠረት ተሰልቶ ነው እንዲከፍል የተደረገው በማለት ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ የሚካካዱበት ምክንያት ቢሆንም እንደ አውሮፓሮውያን አቆጣጠር ከታህሳስ ወር 2003 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪ ከአመልካች የሚጠይቀው የስልክ ግልጋሎት ክፍያ አመልካች በደንበኝነት በቆዩበት ጊዜ ይከፍሉት ከነበረው አቬሬጅ ክፍያ በየወሩ ስምንት እጥፍ ብልጫ ያለውና የተጋነነ በመሆኑ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይኸንንም ሁኔታ በመቃወም አመልካች እንዲመረምርላቸው ጥያቄ ያቀረቡ መሆኑን ከበታች ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

አመልካች የተገለገለበትን የስልክ ግልጋሎት ዋጋ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሲሆን በተነፃፃሪው ተጠሪ የአመልካች የስልክ መስመር ከአመልካች ውጭ ሌላ ሰው እንዳይገለገልበት ተገቢውን ጥበቃና ጥንቃቄ የማድረግና አመልካች ላገኘው ግልጋሎት የአገልግሎት ዋጋ የመጠየቅ መብት አለው፡፡ ተጠሪ ደንበኞቹ የተጠየቁት የአገልግሎት ክፍያ ትክክለኛነት በሚጠይቁበት ወቅት የማስመርመሪያ ገንዘብ ከፍለው እንዲመረመር የሚያደርግ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ያላቸው የውል ግኑኝነትና በውል አፈፃፀም የሚነሡ ችግሮች በመጀመሪያ ተጠሪ በልምድ ባዳበረው አሠራር መሠረት መታየትና መጣራት ያለበት ነው፡፡ ይኸም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሊኖር የሚገባው ግኑኝነት ቅንነትንና መተማመንና በጉዳዩ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ሥርዓት በመከተል ሊፈታ የሚገባው በመሆኑ ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1732 ድንጋጌ ለመገንዘብ ስለሚቻልና ተጠሪ ደንበኞቹ የተጠየቁት የአገልግሎት ክፍያ የተጋነነ ነው ወይም ጥሪ ያላደረግሁበትን የውጭ አገር ስልክ አገልግሎት ዋጋ እንድከፍል ተጠይቄአለሁ በሚሉበት ወቅት ደንበኞቹ የተወሰኑ ሁኔታዎችን በማሟላት የሚመረመርበት በልምድ የዳበረ አሠራር ያለው በመሆኑ ተጠሪ እ.ኤ.አ በታህሳስ ወር 2003 የተጠየቀው ሂሳብ የተጋነነ መሆኑን አቤቱታ ሲያቀርብ ተገቢው ምርመራ ማድረግ ሲገባው ምርመራ አለማድረጉና እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከጥር ወር 2003 እስከ መስከረም 2004 ድረስ ያለው ሒሳብም ሣይመረመር አመልካች እንዲከፍሉ መጠየቁና የበታች ፍርድ ቤቶችም በጉዳዩ ተገቢው ምርመራ ተደርጎ ዕውነታው ሣይረጋገጥ ተጠሪ የጠየቀውን ገንዘብ አመልካች ሙሉ በሙሉ እንድከፍል መወሰናቸው አመልካችን ግዴታና ኃላፊነትና በልምድ የዳበረውን የተጠሪን አሠራር ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለማስመርመር የሚገባውን ግዴታና ኃላፊነት እንዲወጣ በማድረግና የአመልካች መስመር እንዲመረመር በማድረግ በሚቀርብለት ውጤት መሠረት ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ 46052

ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሃይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ - ጠበቃ ውብሸት ሥ/ጊዮርጊስ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የቦንጋ ማዘጋጃ ቤት ከፋ ዞን ዐ/ህግ - ነ/ፈጅ ደበበ ወንድሙ ቀረቡ

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በከፋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለፍ/ቤቱ ባቀረበው ክስ አመልካች ዘመናዊ ሆስፒታል ለመገንባት ቦታ ጠይቀው 1,931 ካ.ሜ ቦታው ተሰጥቷቸው ግንባታውን ስላቋረጡ ውሉ ተሰርዞ ግንባታው በራሳቸው ወጪ አፍርሰው ቦታውን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ እንዲሁም ከ1996 ዓ.ም - 1999 ዓ.ም የቦታና የቤት ግብር ብር 52,782.35(ሃምሳ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሰማንያ ሁለት ሺህ ብር ከሰላሳ አምስት ሳንቲም) እንዲከፍሉ በማለት ጠይቋል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካቀረቡ በኋላ ለዋናው ጉዳይ በሰጡት መልስ ግንባታው የተቋረጠው በፕሮጀክቱ ሳይት ላይ ተጠሪ የኮንቴነር ሱቆች በማቆሙና ይህም የግንባታ እቃዎች በመኪና ተጭነው እንዳይገቡና እንዳይራገፍ እንቅፋት በመሆናቸው በተጨማሪም የግንባታ እቃ ዋጋ በመናሩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን፣ ለሆስፒታል አገልግሎት ለሚውል ጅምር ቤት ፕሮጀክቱ ሳይጠናቀቅ የቦታና የቤት ግብር ሊከፈል የማይገባ መሆኑንና በግራ ቀኙ መሃከል ውል ባለመኖሩ ክሱ ውድቅ እንዲደረግላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ክርክሩን መርምሮ አመልካች ሳይት ፕላኑ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ግብር የመክፈል ሃላፊነት አለባቸው፣ የግንባታ ዕቃዎች ወደ ግቢው በመኪና ተጭኖ እንዳይገባ ያገደው ነገር የለም፣ ግራ ቀኙን የሚገዛ ህጋዊ ውጤት ያለው ውል አለ፣ ከዲዛይኑ አኳያ ከግማሽ በላይ የተከናወነ በመሆኑ ውሉ ተሰርዞ ለጅምር ግንባታው ግምቱን ተጠሪ ለአመልካች ከፍሎ ግንባታውን ከነይዞታው ይረከብ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ግራ ቀኙ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የሁለቱን ወገኖች ክርክር ተመልክቶ አመልካች የቦታና የቤት ግብር ሊከፍሉ አይገባም፣ ግንባታው የተቋረጠው በአመልካች ድክመት ወይም ጥፋት ሳይሆን ተጠሪ ባቆማቸው የኮንቴነር ሱቆች ችግር ምክንያት ለመሆኑ የፍ/ቤት ዳኛው ቦታው ድረስ በመሄድ አረጋግጠዋል፣ የግንባታ ዕቃዎች እጥረት ለግንባታው መቋረጥ አስተዋፅኦ አድርጓል፣ ተጠሪ ያቀረበው የይዞታ ማረጋገጫ ም/ወረቀት አመልካች የሆስፒታል ግንባታ በሚመለከት የፀና ውል መኖሩን አያስረዳም፣ ውል አለ ቢባል እንኳን በውሉ መሰረት እንዳይፈፀም አስተዋፅኦ ያደረገው ተጠሪ ስለሆነ ውሉ ሊሰረዝ የሚችልበት ሁኔታ የለም አለ ቢባል እንኳን ግንባታው ከ55% በላይ ስለተገነባ ወደነበሩበት መመለስ አስቸጋሪ ይሆናል በማለት ለግንባታው እንቅፋት የሆኑት ኮንቴነሮች ተጠሪ እንዲያነሳና ግንባታው ይቀጥል፣ አመልካች የቦታና ቤት ግብር አይከፍሉም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሳኔ በማሻሻል አመልካች የቤትና ቦታ ግብር ሊከፍሉ ይገባል፣ አመልካች ቀሪ ግንባታውን ሊያጠናቅቁ የሚገባበት ጊዜ ተጠሪ ወስኖ እንዲያሳውቃቸው፣ ተጠሪ በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታውን ማጠናቀቅ ካልቻሉ ውሉ ተሰርዞ ተጠሪ ቦታውንና ግንባታውን ባለበት ሁኔታ የመረከብ መብቱ ተጠብቋል፣ ለግንባታ ስራው እንቅፋት የሆኑት ኮንቴነር ሱቆች ተጠሪ በየደረጃው በመለየት እንዲያፈርስ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው ግንባታውን ያላጠናቀቁት በእርሳቸው ጥፋት ሳይሆን በፕሮጀክቱ ሳይት ዙሪያ ህገ-ወጥ የኮንቴነር ሱቆች እንዲለጠፉና

የግንባታው ግብዓቶች ለመጫንና ለማራገፍ ባለመቻሉ መሆኑን፣ ተጠሪ እነዚህን ኮንቴነሮች በማንሳት ግንባታው እንዲቀጥል የማድረግ ኃላፊነቱን አለመወጣቱን፣ ግንባታው መጠናቀቅ የሚገባበትን የጊዜ ገደብ ተጠሪ ወስኖ እንዲያስታውቅ መደረጉ የህግ መሰረት እንደሌለው የቦታና የቤት ግብር ሊከፈል የሚገባው ግንባታው ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ስራ ላይ በዋለ ቤት በመሆኑ ግብር ሊከፍሉ እንደማይገባ ለፕሮጀክቱ ግንባታ ከፍተኛ መጠን ያለው መዋለ ንዋይና የሰው ሃይል ስለፈሰሰበት የተፈጠረው መሰናክል ተወግዶ ግንባታውን ተጠሪ እንዲረከብ መወሰኑ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎት ግንባታው የሚጠናቀቅበትን የጊዜ ገደብ ተጠሪ ወስኖ ለአመልካች እንዲያሳውቅ እና አመልካች ለቦታና ቤት ግብር እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ቀርበው የቃል ክርክራቸው ተሰምቷል፡፡ ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ ከተገቢው ህግ አኳያ መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንዳየነው አመልካች ሆስፒታል ለመገንባት ቦታ የተረከቡ ቢሆንም ግንባታውን አለማጠናቀቃቸው ያልተካደ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ተጠሪም ይህንን መሰረት አድርጎ ነው ውሉ እንዲፈርስ የጠየቀው፡፡ አመልካች በበኩላቸው ግንባታውን ያላጠናቀቁት በግዴለሽነት ሳይሆን በፕሮጀክት ሳይቱ ላይ ተጠሪ የኮንቴነር ሱቆች በማቆሙና ይህም የግንባታ እቃ ለማስገባትና ለማራገፍ እንቅፋት በመሆኑና በሃገሪቱ የግንባታ እቃም ዋጋ በከፍተኛ መጠን በመናሩ በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡ ከመዝገቡ ላይ አመልካች ቦታውን ሚያዚያ 1993 ዓ.ም ተረክበው እስከ 1996 አጋማሽ ድረስ ግንባታውን ያከናውኑ እንደነበር ተገንዝበናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በፕሮጀክት ሳይቱ ላይ የኮንቴነር ሱቆች የቆሙት በ1997 መጨረሻ ወይም በ1998 መጀመሪያ ላይ ለመሆኑ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ማረጋገጡን ከውሳኔ ግልባጩ ተመልክተናል፡፡ ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠው የዳኝነት ስልጣን አንፃር ይህ ችሎት በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ትክክል ነው አይደለም የሚለውን ሳይመረምር እንዳለ የሚቀበለው ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች ለግንባታው ስራ እንቅፋት ሆኑብኝ በማለት የሚጠቅሷቸው የኮንቴነር ሱቆች በሳይቱ አካባቢ የቆሙት አመልካች የግንባታ ስራውን ካቋረጡ እጅግ ዘግይቶ ነው፡፡ በመሆኑም ግንባታው በተጠሪ አስተዋፅኦ መቋረጡን በማንሳት ያቀረቡት ክርክር ፍ/ቤቱ ውድቅ በማድረጉ የሰራው የህግ ስህተት አለ ለማለት አይቻልም፡፡ በሌላ በኩል የክልሉ ደንብ ቁጥር 41/97 አንቀፅ 8(3) የግንባታ ቦታ የተረከበ አስገንቢ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ሥራውን መጀመር እንዳለበት እና እስከ ሁለት አመት ማጠናቀቅ እንዳለበት ያስጠነቅቃል፡፡ ትልልቅ ግንባታዎችን በተመለከተ ግን ውል ሰጪውን አካል በማስፈቀድ ጊዜውን ማራዘም እንደሚቻል ይፈቅዳል፡፡ ከፍ ሲል እንዳየነው አመልካች ቦታውን የተረከቡት ሚያዚያ 1993 ዓ.ም ነው፡፡ ነገር ግን ግንባታውን እስካሁን አላጠናቀቁም፡፡ እንደውም ከ1996 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ ግንባታው ተቋርጧል፡፡ ቀደም ብሎ እንደተመለከትነው ግንባታው የተቋረጠው በኮንቴነር ሱቆቹ ምክንያት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ለግንባታው መቋረጥ ሌላው የሰጡት ምክንያት የግንባታ ዕቃዎች ዋጋ መናርን ነው፡፡ በእርግጥ በአገሪቷ ውስጥ የግንባታ ዕቃ ዋጋ መናር ተከስቶ እንደነበር የስር ፍ/ቤቶች ተቀብለውታል፡፡ ነገር ግን በዚህ ችግር ምክንያት ግንባታው የሚዘገይ ከሆነ ከፍ ሲል በተጠቀሰው ደንብ መሰረት ውል ሰጪው አካል ጊዜውን እንዲያራዝም መጠየቅና ማራዘም በተገባቸው ነበር፡፡ ይህንን ስለማድረጋቸው ግን ማስረጃ አለመቅረቡን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ በመሆኑም በህጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ እንዲራዘም ሳይጠይቁና በዚሁ ጊዜ ውስጥ ግንባታውን ሳያጠናቅቁ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ከዚህ ሌላ አመልካች ተጠሪ ግንባታው ሊጠናቀቅ የሚገባበት ጊዜ ወስኖ እንዲያሳውቅ መወሰኑ የህግ መሰረት የለውም በማለት ይከራከሩ እንጂ በክልሉ ደንብ መሰረት በደንቡ ግንባታ ለማጠናቀቅ የተቀመጠው ጊዜ እንዲረዝም ፈቃድ የሚሰጠው ውል ሰጪው አካል እንደመሆኑ መጠን የጊዜውንም እርዝመት እራሱ እንደሚወስን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚሁ መሰረት ተጠሪ አመልካች ግንባታውን ማጠናቀቅ የሚገባቸውን ጊዜ ወስኖ እንዲያሳውቃቸው መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው ማለት አልተቻለም፡፡

በመጨረሻም አመልካች ለጅምርና ጥቅም ላይ ላልዋለ ቤት የቦታና የቤት ግብር እንድከፍል የተሰጠው ውሳኔ የህግ ድጋፍ የለውም ይበሉ እንጂ በክልሉ አዋጅ ቁጥር 51/1994 እና በደንብ ቁጥር 41/1997 የከተማ ባለይዞታ የሆነ ማንኛውም ሰው ግንባታ ቢጨርስም ባይጨርስም የአገልግሎት ተጠቃሚ በመሆኑ ብቻ የተጠቀሱት ግብሮች እንደሚከፍል ይደነግጋል፡፡ አመልካች በተቃራኒው ለጅምር ቤት የቤትና የቦታ ግብር እንዳይከፈል የሚከለክል ህግ ስለመኖሩ የጠቀሱት ነገር የለም፡፡ በመሆኑም በዚህም በኩል የተሰጠው ውሳኔ የህግ

ስህተት ተፈፅሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡ በአጠቃላይ በፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 39394 የካቲት 25 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. ይህ ችሎት ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ 46394

የካቲት 11 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ስንቁ መስፍን - ጠበቃ ካሣሁን አሰፋ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ጅፋር አባገሮ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የኪራይ ውልን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ መጋቢት 11 ቀን 2000 ዓ.ም በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም በቀድሞ ወረዳ 02 ቀበሌ 09 ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 026/3 የሆነ የተጠሪን ቤት ከአመልካች ጋር መጋቢት 01 ቀን 1998 ዓ.ም በተጻፈ የኪራይ ውል በወር ብር 629.00(ስድስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ብር) ተጠሪ ሊከፍሉና ከአከራይ ፈቃድ ውጪ ግንባታ ላያከናውኑ ግዴታ ገብተው (በመግባት) ውል ማድረጋቸውን ሆኖም አመልካች በውሉ ላይ የገቡትን ግዴታ በመጣስ የተጠሪን የጽሑፍ ፈቃድን ሳያገኙ የቀድሞውን ማቴሪያል በመቀየር ሸክላ አልብሰው እንደተገኙና እንዲሁም የጭስ ቤቱን ጣሪያ ከፍታ ጨምረው መስራታቸውን ዘርዝሮ ውሉ ተቋርጦ ቤቱን እንዲያስረክቡ እስኪያስረክቡ፣ ድረስ የሚኖረውን ኪራይም እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሠጡት መልስ በቤቱ የንግድ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን ፅዳቱ እንዲጠበቅለት በማሰብ ተጠሪን በተደጋጋሚ እንዲያስጠግንና እንዲያድስ ጠይቀው በተገቢው ጊዜ ተገቢው ምላሽ ስላልተሠጣቸው በሆቴሉ ስራ አስፈላጊ የሆነ ስራ መስራታቸውንና ይህንም ስራ በቀበሌ አስተዳደሩ አግባብነት ያለው መሆኑ መረጋገጡን ገልፀው ግንባታው የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ በቂ ምክንያት አይደለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር የኪራይ ውሉ ተቋርጦ አመልካች ቤቱን ሊያስረክቡ ይገባል እስኪያስረክቡ ድረስ ያለውን ኪራይም ሊከፍሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሰኔ 02 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ሦስት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች በቤቱ ላይ አድርገዋል የተባለው ተግባር/ሥራ/ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን የኪራይ ውል ለማቋረጥ የሚያበቃ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል ተብሎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ሕዳር 09 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ከሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያቋቋመው የኪራይ ውሉ እንዲቋረጥ ዳኝነት የጠየቀው አመልካች በኪራይ ውሉ የገቡትን ግዴታ በመጣስ ያለተጠሪ ፈቃድ ግንባታ አከናውነዋል በሚል መሆኑን አመልካች ግንባታውን ማከናወናቸውን ሳይክዱ የተከናወነው ግንባታ ቤቱ ለሆቴል ስራ አገልግሎት የሚውል በመሆኑ ለስራው አስፈላጊ መሆኑን ይህም በቀበሌው ጽ/ቤትም ታይቶ ተገቢነቱ መረጋገጡን ማስረዳታቸውን ነው፡፡ እንግዲህ በኪራይ ውሉ ላይ አመልካች በቤቱ ላይ የሚያከናውኑትን ግንባታ ለተጠሪ በቅድሚያ የማሳወቅ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ አከራካሪ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ አከራካሪው ለኪራይ ውሉ መቋረጥ ምክንያት የሚሆነው ምን አይነት ግንባታ ነው? የሚለው ነው፡፡ በተጠሪና በአመልካች መካከል የተደረገው የኪራይ ውል ማንኛውም ግንባታ የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ ምክንያት ስለመሆኑ እንደሚያሳይ ተጠሪ ገልፆ አለመከራከሩን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ እንዲህ ከሆነ ጉዳዩ በጠቅላላ የውል ሕግ ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱትን ስለውሎች አተረጓጎም ደንቦችንና ኪራይን በተመለከተ የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ እልባት ሊሰጠው የሚገባው ነው፡፡ በዚህም መሰረት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1732 ድንጋጌ ሲታይ በተዋዋዮች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነትንና የመተማመንን ግንኙነት መሰረት በማድረግና በጉዳዮቹ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ስርዓት በመከተል ውሎች በቅን ልቦና ሊተረጎሙ እንደሚገባ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2953 ተከራዩ ሊያደርሳቸው የሚገባውን የተከራያቸውን ቤቶች በራሱ ኪሳራ ለማደስ የሚገደድ ስለመሆኑ ሲደነግግ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2954 የማደስ ትርጉምን አስቀምጧል፡፡ ይኸውም ተከራዩ ቤቶችን ማደስ ይገባዋል የተባሉትን(የሚባለውን) በኪራዩ ውል ተከራዩ ይፈጽማቸዋል ተብሎ የተወሰኑትን ስለመሆኑ ተቃራኒ የሚሆን ስምምነት ከሌለ በቀር ቤቶችን የማደስ ስራዎች ተብለው የሚቆጠሩት ደግሞ መዝጊያዎችን ወይም መስኮቶችን፣ የቤት ወለሎችን ወይም ንጣፎችን፣ የውሃ መቅጃ መዘውሮችንና የውሃ መስደጃዎችን ለማደስ አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮችን እንደሆነ እንደዚሁም በተከራየው ቤት ለመጠቀም አስፈላጊ የሆኑትን ቤቶችን የማፅዳትና በደንብ የመያዝ ስራዎች ቤቱን እንደማደስ ያሉ ተግባሮች ስለመሆናቸው ይደነግጋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ያከናወኗቸው የግንባታ ስራዎች በቤቱ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ያመጡ ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ ሲሆን በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠው ግንባታው ለሆቴሉ ስራ አስፈላጊ ይልቁንም በሆቴሉ ተነስቶ ለነበረው የእሳት አደጋ ተገቢውን ጥንቃቄ ለማድረግ የሚያስችል ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም አመልካች ያከናወኑት የግንባታ ስራ የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ ምክንያት ሊሆን የማይችል በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሉን በኪራይ ውሉ ላይ የተመለከተውን "ግንባታ" የሚለውን ቃል ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1732፣ 2953 እና 2954 ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ ማገናዘብ ሲገባቸው ውሉ ሊቋረጥ ይገባል ሲሉ የሠጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 105945 ሰኔ 20 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 69864 መጋቢት 28 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በቤቱ ላይ አድርገዋል የተባለው ተግባር/ሥራ/ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን የኪራይ ውል ለማቋረጥ የሚያበቃ አይደለም ብለናል፡፡ የኪራይ ውሉ በሌላ ሕጋዊ ምክንያት እስካልተቋረጠ ድረስ አመልካች ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 45559

የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ አ/ማ - ነ/ፈጅ አስቴር በቀለ ቀረበች

**ተጠሪዎች**፡- 1. የአቶ ኃይሉ ፈይሳ - ወራሾች በሌሉበት

2. ወ/ሮ ብርቄ ዘለቀ - በሌሉበት

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሥር ፍ/ቤት የወለድ ስሌት እስከቀረበበት ቀን የተጠየቀውን ዳኝነት አልፎ ውሳኔ ከተሰጠበት በማለት የሰጠው ውሳኔ ግራ ቀኙ ያደረጉትን ውል ባለማገናዘብ የተሰጠ በመሆኑ እንዲታረም የሚል ነው፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይ አመልካች ለተጠሪዎች የሰጠው የብድር ገንዘብ በከፊል ሳይከፈል የቀረ ስለመሆኑ ቀሪውን ገንዘብ ከልዩ ልዩ ወጪዎች ጋር እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት በመጠየቁ ነው፡፡ የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ብር 370,295.81 ውሳኔ ከተሰጠበት ነሐሴ 15/1999 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 10.5% ወለድ፣ለዳኝነት የተከፈለውን ብር 9,150.09 እና ወጪዎች በቁርጥ ብር 200.00 ብር ጋር በአንድነት እና በነጠላ እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ወለዱ መታሰብ ያለበት ክስ ከቀረበበት ግንቦት 22 ቀን 1999 ዓ.ም መሆን ይገባዋል ሲል የሥር ፍ/ቤት ሥህተት እንዲታረም ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው አቤቱታ በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው የብድር ውል እዳው ተከፍሎ እስከ ድረስ ያለማቋረጥ ከነወለዱ ለመክፈል መስማማታቸው ጠቅሶ የሥር ፍ/ቤት ወለዱን ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን እንዲታሰብ በማድረጉ አመልካች በልዩነት ብር 8,841.45(ስምንት ሺህ ስምንት መቶ አርባ አንድ ብር ከአርባ አምስት ሣንቲም) እንዳያገኝ አድርጓል በሚል ይኸው እንዲታረም አመልክቷል፡፡

ሰበር ሰሚው ችሎትም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በሥር ፍ/ቤት የታለፈው በአግባቡ ስለመሆን አለመሆን ለመመረመር ተጠሪዎች እንዲቀርቡ አዟል፡፡ ተጠሪዎች በጋዜጣ ጥሪ ተደርጐላቸው ስላልቀረቡ ክርክሩ በሌሉበት ተሰምቷል፡፡

የአመልካችን አቤቱታ ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች የዋናው ገንዘብ ወለድ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ እንዲታሰብ ዳኝነት ጠይቆ ሳለ የሥር ፍ/ቤት ያለፈው የተለየ ምክንያት ያለው ስለመሆኑ በውሳኔው ያልጠቀሰ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

በመሰረቱ የገንዘብ ብድር ውል በግራ ቀኙ መካከል ሲደረግ ወለዱን ጨምሮ ለመክፈል ስምምነት የተደረገ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ ተጠሪዎችም በሥር ፍ/ቤት የተጠየቀውን ገንዘብ ወለድ የማይከፍሉበት ምክንያት ስለመኖሩ አላስረዱም፡፡ ይህ ሁኔታ በሌለበት የሥር ፍ/ቤት ወለዱ መታሰብ ያለበት ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ነው ሲል የደረሰበት ድምዳሜ ከግራ ቀኙ ውል እና በተጠሪዎችም ባልቀረበ ክርክር መነሻ በመሆኑ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ ግራ ቀኙ ባደረጉት የገንዘብ ብድር ውል ተጠሪዎች ከነወለዱ ሳያቋርጡ ለመክፈል ግዴታ የገቡ በመሆኑ ስለውሎች በተደነገገው ፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1731 እና 2478 መሰረት ወለድንም ጭምር የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡ ወለዱንም ጭምር ከጅምሩም መክፈል ያለባቸው ስለመሆኑ በውለታቸው የተመለከተ መሆኑ ከታወቀ አመልካች ቅጣት 3% ጭምር ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ እንዲታሰብ የጠየቀውን ዳኝነት የሥር ፍ/ቤት ማለፉ ያላግባብ በመሆኑ እና በዚህ ረገድ የግራ ቀኙን ስምምነት ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለዚህም ወለድን አስመልክቶ አመልካች እስካቀረበበት ከግንቦት 22 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ 10.5% ወለድ እንዲታሰብ መወሰን ሲገባው ውሳኔ ከተሰጠት ቀን ማለትም ነሐሴ 15 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ እንዲታሰብ በመወሰኑ በልዩነት አመልካችን ብር 8,841.45(ስምንት ሺህ ስምንት መቶ አርባ አንድ ብር ከአርባ አምስት ሣንቲም) ማሳጣቱ ስህተት በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ረገድ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02175 የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03481 የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት በከፊል ተሻሽሏል፡፡

2. ተጠሪዎች ያልከፈሉትን ቀሪ የብድር ገንዘብ ወለድ ማለትም ሥር ፍ/ቤት ክስ ከቀረበበት ከግንቦት 22/1999 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 15 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ያለውን ብር 8,841.45 (ስምንት ሺህ ስምንት መቶ አርባ አንድ ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም) በሥር ፍ/ቤት ከተወሰነው ገንዘብ ጋር በአንድነት እና በነጠላ እንዲከፍሉ ወስነናል፡፡

3. በዚህ ችሎት በተሻሻለው ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም ለሥር ፍ/ቤት ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 47800

የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሃይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ እመቤት ደርበው - የቀረበ የለም ከጠ/ሃይሉ አግዘው ጋር ቀረቡ

**መ/ሰጪ፡-** አቶ ታደለ ሰዳማ - የቀረበ የለም ከተባለ በኋላ ጠ/ሰመረ አሰፋ ቀረቡ

በዚህ መዝገብ የቀረበልንን ጉዳይ ተመልክተን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ እንደቻልነው አሁን በቀረበልን ጉዳይ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች ጣልቃ ገብ በመሆን በሆሳእና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበውት የነበረው የውል ይፍረስልኝ ማመልከቻ ነው፡፡ አመልካችዋ ውል ይፍረስልኝ በማለት ጥያቄ ያቀረቡት ያለእርሳቸው ፈቃድ ባለቤታቸው የጋራ ንብረት የሆነውን ድርጅት ለአሁኑ መልስ ሰጭ ሸጦአል በማለት ነው፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት በውሉ አፈፃፀም መሟላት የሚገባቸው የፎርም ቅድመ ሁኔታዎች እንደነበሩ ካረጋገጠ በኋላ ከውሉ መፈፀም በኋላ የተፈጠሩ ሌሎች በርካታ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ በማስገባት ተዋዋዮች ወደ ነበሩበት ይመለሱ ሊባል አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጠ፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቢያቀርቡም ይግባኝ የቀረበለት የሐድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን አጽንቷል፡፡ ይግባኝ ፍ/ቤቱ ውሳኔው ሲያፀና ከውሉ መፈፀም በኋላ ድርጅቱን የገዛው የአሁን መልስ ሰጪ በርካታ ንብረት ሲያሰፍሩበት አመልካች በአጠገቡ ስለሚኖሩ ያውቁ እንደነበርም አትቷል፡፡ ከክርክሩ ሂደት አሁን አከራካሪ የሆነው ሽያጭ የተፈፀመው በ1992 ዓ.ም ሲሆን ጣልቃ ገብ ይፍረስልኝ ብለው የጣልቃ ገብነት ጥያቄ ያቀረቡት የአሁኑ መልስ ሰጪ ስም ይዛወርልኝ በማለት ሐምሌ 11 ቀን 1997 ባቀረቡት ማመልከቻ መሰረት በተመሰረተው ክስ ነው፡፡

ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው የሰበር ማመልከቻ እንዲፈርስ ጥያቄ የቀረበበት የወፍጮ የሽያጭ ውል ሕጉ የሚጠይቀውን የሁለቱም ተጋቢዎች ፈቃድና የምዝገባ ፎርማሊቲ አለማሟላቱ ከተረጋገጠ ሌላ ምክንያት በማቅረብ ተዋዋዮቹ ወደነበሩበት ሊመለሱ አይገባም መባሉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን የሚያመለክት ነው የሚል ነው፡፡

መልስ ሰጪ በጽሑፍ ባቀረቡት መልስ የፎርማሊቲ ጥያቄውንም ሆነ የፈቃድ ጉዳዮችን ከውሉ በኋላ ከተደረገው ኢንቨስትመንት ጋር በማነፃፀር ውሉ አይፈርስም ተብሎ መወሰኑ አግባብ ነው ስለዚህ ውሣኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

እኛም ውሉ ከተፈፀመ በኋላ በተገዛው ንብረት ላይ የተደረገውን ለውጥ ግምት ውስጥ በማስገባት ውሉ እንዲፀና መወሰኑ አግባብ መሆን አለመሆኑን አግባብነት ካላቸው የሕጉ ድንጋጌዎችና ይህ ፍርድ ቤት ቀደም ብሎ ከሰጣቸው የሕግ ትርጉም ውሣኔዎች ጋር በማያያዝ ተመልክተናል፡፡ በመሰረቱ የፈቃድ ወይም የፎርም ጉድለት ያለበት ውል ሕጉ መብት በሚሰጠው ሰው የይፍረስልኝ ጥያቄ ሲቀርብበት ፈራሽ እንደሚሆን በመርህ ደረጃ በሕጉ በግልጽ የሰፈረ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ውሉ በሚፈፀምበት ወቅት ጉድለት የነበረበት መሆኑ ከተረጋገጠ ውሉ እንዲፈርስና ባለጉዳዮች ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ማዘዝ ከፍርድ ቤት የሚጠበቅና ሕጉም የሚያዘው መርህ

ነው፡፡ /የፍትሐብሔር ሕግ ቁ.1815 ይመለከታል/ ሆኖም ይህ ተዋዋዮችን ወደነበሩበት የመመለስ መርህ ተፈፃሚ ማድረግ የማይቻል ከሆነ ወይም ለአንደኛው ተዋዋይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ ውሉን ለመፈፀም የተከናወኑ ተግባራት ፀንተው እንደሚቆዩ የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1817 በግልጽ ደንግጐታል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ውሉ ሲመሰረት ጉድለት የነበረበት መሆኑን ቢያረጋግጥም ውሉን ማፍረስ የማይቻል ወይም ለአንደኛው ወይም ለሁሉም ወገን ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን በሂደት ከተረዳ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት ሊመለሱ አይገባም በማለት ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህ ትርጉም ይህ የሰበር ችሎት በሌሎች በርካታ ጉዳዮችም የተከተለው ነው፡፡

አሁን በቀረበልን ጉዳይም ፍ/ቤቱ የተከተለው ይህን መርህ ነው፡፡ ውሉ ሲመሰረት ጉድለት እንደነበረበት አረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል ውሉ በ1992 ዓ.ም ከተፈፀመ በኂላ በመልስ ሰጪ በኩል ተጨማሪ ንብረት የታከለበት መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ አስገብቷል፡፡ አመልካችም በሰበር አቤቱታቸው ጭምር በተሸጠው ንብረት ላይ ተጨማሪ ግንባታ የተካሄደበት መሆኑን አይክዱም፡፡ ሁኔታው ይህ ከሆነ ደግሞ ፍ/ቤቶች የውሉ መፍረስ የሚያስከትለው ጉዳት በዝርዝር ገልጸው ውሉን ከማፍረስ ይልቅ ፀንቶ እንዲቆይ ማዘዛቸው የሕጉን አንቀጽ 1817/1/ መንፈስና ግልጽ ቃል የተከተለ እንጂ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተሰራበት ውሳኔ ሰጡ ለማለት የሚያበቃ ሆኖ አላገኘነውም በመሆኑም በዚህ ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊፀና የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በደ/ብ/ብ/ሕ/መ በሃዲያ ዞን የሆሳእና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 0024/98 እና የሐድያ ዞን በመ/ቁ. 04688 የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ የራሳቸውን ወጪ ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 40336

መጋቢት 22 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ወንድወሰን ጥሩነህ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- የወ/ሮ አሰገደች ካሣሁን ወራሽ ሄኖክ ሣሙኤል - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኪራይ ቤትን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጥቅምት 08 ቀን 2000 ዓ.ም በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በቀድሞው አጠራር በወረዳ 21 ቀበሌ 01 (ባሁኑ አጠራር በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15) ቁጥር 288/45 የሆነውን ቤት ከሳሽ የሚያስተዳድረው ቤት አካል የሆነውን ቤት ተጠሪ ክሱ በስር ፍርድ ቤት እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ይዘው እየተጠቀሙ መሆኑን፣ቤቱን እንዲያስረክቡ ሲጠየቁም ለማስረከብ ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውን ገልጾ ቤቱን እንዲያስረክቡ፣ቤቱን እስኪያስረክቡ ያለውን ኪራይ እና በዚህ ክስ ምክንያት የወጣውን ወጪና ኪሳራ እንዲከፍሉ እንዲወሰንለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ለክሱ በሰጠው መልስ አውራሼ ቤቱን ተከራይታ ስትኖርበት የነበረ ሲሆን ኪራዩን ባግባቡ እየከፈልኩ የምኖርበት ነው፣አመልካች ቤቱን ልቀቅ ሲል ያቀረበው ምክንያትም የለም፣የሰጠኝ ተለዋጭ ቤትም የለም፣ስለሆነም ተወልጄ ያደግሁበት ቤት እንድለቅ የቀረበው ክስ አግባብ ስላለሆነ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር በአመልካችና በተጠሪ መካከል የአከራይ ተከራይ ግንኙነት መጀመሩን፣ አመልካች ይህ ሆኖ እያለ ተጠሪን ቤቱን ልቀቅ የሚልበትን ምክንያት ሳይገልጽ ቤቱን እንዲለቅለት ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አግባብነት እንደሌለው በምክንያትነት በመያዝ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት የሚያስረክብበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ነሐሴ 28 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ በመጠየቁ ውሉ ሊቋረጥ የተፈለገበት ምክንያት አልተገለፀም በሚል አይቋረጥም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪ ቀርበው የጽሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ነገረፈጅም የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊመረመር ይገባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪው ቤት ባለቤትነቱ የመንግስት ሆኖ የሚያስተዳድረው የአሁኑ አመልካች መሆኑን፣ቤቱን በተከራይነት የአሁኑ ተጠሪ ወላጅ እናት የሆኑት ሟች ወ/ሮ አሰገደች ካሳሁን ይዘው ሲጠቀሙት የቆዩ መሆኑን፣ተጠሪም በቤቱ በቤተሰብነት የኖሩበት ከመሆኑም በላይ አውራሻቸው ሲሞቱ ኪራዩን እየከፈሉ መጠቀም መቀጠላቸውን፣አመልካች ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ቤቱን እንዲያስረክቡ ጥያቄ ቢያቀርብም ተጠሪ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ክስ ሊመሰርት የቻለ መሆኑን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት እነዚህን ፍሬ ነገሮች አረጋግጦ የአመልካችን ክስ ውድቅ ሊያደርግ የቻለው አመልካች ቤቱን ተጠሪ እንዲለቅ ጥያቄ ሲያቀርብ ቤቱን ተጠሪ የሚለቁበትን ምክንያት አልገለፀም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ተጠሪ አውራሽ ከዚህ አለም በሞት ከተለዩ በኋላ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጊዜው ያልተቆረጠለት የኪራይ ውል በመካከላቸው መመስረቱንም ከክርክር ሂደት መገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ጥያቄ የዚህ አይነት የኪራይ ውል የሚቋረጠበት አግባብ እንዴት ነው? የሚለው ነው፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2966/1/ ሲታይ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውልን አከራዩ ተከራዩን ወይም ተከራዩ አከራዩን በማስታወቅ ሊያልቅ እንደሚችል ደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በአከራዩም ሆነ በተከራዩ ላይ በሕጉ በተጣለው ግዴታ ማስታወቂያ መስጠት ሲሆን የዚሁ ድንጋጌ ንኡስ ቁጥር ሁለት ደግሞ ውሉ አለቀ የሚባለው በኪራዩ ውል ወይም በሕጉም መሰረት ተከታዩ የኪራይ ዘመን ዋጋ በሚከፈልበት ቀን ወይም የኪራዩ ውል ስለማለቅ ማስታወቁን ባይሰጥ ኑሮ ኪራዩ ሊከፈልበት ይገባው በነበረበት ቀን ስለመሆኑ ደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ የምንገነዘበው ነጥብ ተከራይ እና አከራይ የኪራይ ውልን ማስታወቂያ በመስጠት ለማቋረጥ የሚችሉ መሆኑን እንጂ ውሉ የሚቋረጥበትን ምክንያት ጭምር የመግለጽ ግዴታ ያለባቸው አለመሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ የሚፈልግበትን ምክንያት ጭምር መግለጽ ይኖርበታል በማለት ክሱን ወድቅ ያደረጉት በሕጉ አግባብ ያልተጣለበትን ግዴታ በመጨመር ሁኖ ስለተገኘ ውሳኔው ከላይ የተጠቀሰውን ድንጋጌ መንፈስ ያላገናዘበ፣የአመልካችን የመንግስት ቤቶችን የማስተዳደር ስልጣን ያጣበበ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 69842 ጥቅምት 02 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 62626 ሰኔ 04 ቀን 2000 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በቀድሞው አጠራር በወረዳ 21 ቀበሌ 01 (ባሁኑ አጠራር በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15) ቁጥር 288/45 የሆነውን ቤት ለአመልካች እንዲያስረክቡ፣ቤቱን እስኪያስረክቡ ያለውን ኪራይ እንዲከፍሉ ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 43381

መጋቢት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ፎዚያ ሁሴን

**ተጠሪ፡-** አቶ ውብሸት ተ/ወልድ

## ፍ ር ድ

ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካችና በሌላ ግለሰብ ላይ በመሰረቱት ክስ በወረዳ 17 ቀበሌ 24 ክልል ውስጥ ቁጥር 050 የሆነው ቤት በወር 500.00(አምስት መቶ ብር) ለአመልካች አከራይተው የነበረ ቢሆንም አመልካች ያልከፈሉት የቤት ኪራይ መኖሩን፣ የኪራይ ውሉ ዘመን ካበቃ በኋላም አመልካች ቤቱን ያለአግባብ ይዘው ስለተጠቀሙ እንዲሁም ቤቱን ለስር ሁለተኛ ተከሳሽ በማስተላለፍ ሁለቱም ያለአግባብ ስለበለፀጉ አመልካች ያልከፈሉት የኪራይ ገንዘብ ብር 26,000(ሃያ ስድስት ሺህ) እንዲከፍሉ እንዲሁም ሁለቱም ተከሳሶች በቤቱ ያለአግባብ በመበልፀጋቸው ኪሳራ እንዲከፍሉ እና ቤቱን እንዲያስረክቧቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ቤቱ በመንገድ ስራ ምክንያት በመፍረሱ የቤቱን መመለስ አስመልክቶ በቀረበው ጥያቄ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ የለም በማለትና አመልካችን በተመለከተ የቀረቡትን ሌሎች የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ አመልካች ከተጠሪ ላይ ቤት ተከራይተው የውሉ ዘመን ሲያበቃ ቤቱን መመለስ ሲገባቸው ይዘው ያለአግባብ በመበልፀጋቸው ብር 26,000(ሃያ ስድስት ሺህ) ኪሳራ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ሁለቱን ወገኖች ሰምቶ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሆኖ ቅሬታው በአጭሩ የቤቱ ባለንብረት ነን በማለት ከአመልካች ኪራይ ሲቀበል የነበረው ቀበሌ ጣልቃ እንዲገባ ጠይቄ መከልከሉ አግባብ ስላልሆነ፣ ውሉ ፀንቶ ከሚቆይበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ድረስ 10 አመት ስለሚያልፍ ክሱ በይርጋ ቀሪ በመሆኑ፣ አላግባብ መበልፀግን መሰረት በማድረግ ክስ ለማቅረብ የንብረቱ ባለቤት መሆን ስለሚያስፈልግ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊሻር ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎት አመልካች ከቤቱ ባለንብረት ጋር የኪራይ ውል በማድረግ ኪራይ ሲከፍሉ የነበረ በመሆኑ በዛው ጉዳይ አላግባብ መበልፀግ በሚል ገንዘብ እንዲከፍሉ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪም ክርክራቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥና አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ አኳያ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት ባለንብረት ቀበሌው መሆኑ፣ ቤቱን በቅድሚያ ከቀበሌው የተከራዩት ተጠሪ መሆናቸው፣ አመልካች ቤቱን መጀመሪያ የተከራዩት ከተጠሪ ላይ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ስለመሆኑ ተረድተናል፡፡ ከዚህ በኋላ ግን ቀበሌው ከተጠሪ ጋር የነበረውን የኪራይ ውል ሰርዞ ቤቱን ለአመልካች ማከራየቱን ተጠሪ ክደው ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ በሌላ ሰው ድካም ወይም የሌላ ሰው ሃብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አላግባብ ጥቅም ባገኘበት መጠንና ባደረሰው ጉዳት መጠን ለባለሃብቱ ወይም ጉልበቱ ለደከመው ሰው ኪሳራ ሊከፍል እንደሚገደድ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2162 ይናገራል፡፡ በመሆኑም

በዚህ ድንጋጌ መሰረት ኪሳራ የሚጠይቀው ሰው የንብረቱ ባለሃብት መሆኑን ማረጋገጥና ተከሳሹ በንብረቱ ያለበቂ ምክንያት መገልገሉን ማስረዳት አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የቀበሌው መሆኑ አልተካደም፡፡ ተጠሪም በአንድ ወቅት ቤቱን የተከራዩ ግለሰብ እንጂ ባለሃብት አይደሉም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የቤቱ ባለሃብት የሆነው ቀበሌው ከተጠሪ ጋር ያደረገውን የቤት ኪራይ ውል አቋርጦ ከአመልካች ጋር ከነሐሴ 1988 ዓ.ም ጀምሮ የኪራይ ውል አድርጓል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የቤቱ ላይ የነበራቸው የተከራይነት መብትም ቢሆን አክትሟል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላም ተጠሪ በቤቱ ላይ ያገኙት የተከራይነት መብት ስለመኖሩ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ በተጨማሪም አመልካች በቤቱ ሲገለገሉ የቆዩት ከቤቱ ባለቤት ከሆነው ቀበሌ ተከራይተው በመሆኑ በቤቱ ያለበቂ ምክንያት ተገልግለዋል ለማለት አይቻልም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች በቤቱ ያለበቂ ምክንያት ያለአግባብ መገልገል በልጽገዋል በማለት ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ከፍ ሲል በተገለጹት ምክንያቶች ተቀባይነት የለውም፡፡ የስር ፍ/ቤትም ተጠሪው በአንድ ወቅት ቤቱን ከቀበሌ ተከራይተው ለአመልካች ማከራየታቸውን ብቻ በመመልከት አመልካች ያለአግባብ በልፅገዋል ሲል ብር 26,000(ሃያ ስድስት ሺህ) እንዲከፍሉ የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 48820 ህዳር 6 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 52062 ህዳር 5 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች አለአግባብ በልፅገዋል ሊባል ስለማይችል ብር 26,000(ሃያ ስድስት ሺህ) ለተጠሪ ሊከፍሉ አይገባም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 43992

መጋቢት 6 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሃይ ታደሰ

ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** 1. አቶ ይልማ አንበሴ

2. ወ/ሮ አስቴር ሃይሌ

3. አቶ ብሩክ ይልማ

4. አቶ ትእዛዙ አንበሴ

ጠ/ካሣሁን አሠፋ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ እመቤት መንገሻ

2. ወ/ሮ ቤተልሔም ግርማ

3. አቶ ብሩክ ግርማ

4. አቶ ሱራፌል ግርማ

5. አቶ በቃ ግርማ

አልቀረቡም

## ፍ ር ድ

አመልካቾች በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ሆቴላቸውን ተከራይተው የኪራዩ ዘመን ሲያበቃ ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ተከሰው በፍርድ ሆቴሉን ስለመለሱ ከውል ውጪ ሆቴሉን ይዘው ለተገለገሉበት ጊዜ የኪራይ ገንዘብና ያላግባብ ለበለፀጉበት በበለፀጉበት መጠን እንዲከፍሉ ክስ አቅርበው ፍ/ቤቱ ከ2-4 ያሉትን አመልካቾች ከክሱ ነፃ በማድረግ አንደኛ አመልካች ከውል ውጪ በሆቴሉ ለ86 ወራት በመገልገል ያለአግባብ የበለፀጉበትን ብር 602,000.00(ስድስት መቶ ሁለት ሺህ) ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ በመወሰኑና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ውሳኔ በማጽናቱ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

ተጠሪዎች በክሳቸው ዝርዝር አመልካቾች ሆቴሉን የውሉ ዘመን ካበቃ በኋላ ሆቴሉን ያለአግባብ ይዘው በመገልገላቸው ኪሳራ ከፍለው ሆቴሉን እንዲለቁ ስለተወሰነባቸው ከኅዳር 2 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ ሆቴሉን ለተጠሪዎች እስካስረከቡበት ታህሳስ 26 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ የድርጅቱን ኪራይና ወለድ፣መብት ሳይኖራቸው ይዘው ባይጠቀሙ ኖሮ ተጠሪዎች ሊያገኙ ይችሉ የነበረውን ጥቅምና ወለድ እንዲሁም ከ1995-1996 ዓ.ም ያገኙትን ትርፍ በአጠቃላይ ብር 2,102,261.35(ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ስልሳ አንድ ብር ከሠላሣ አምስት ሣንቲም) እንዲከፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች ለስር ፍ/ቤት በሰጡት መልስ ከ2-4 ያሉት አመልካቾች ላይ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሰረት ውድቅ ነው፣ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2143 መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው፣ድርጅቱን የያዝነው በመንግስት መመሪያ መሰረት ከኪ.ቤ.አ.ድ ተከራይተን ስለሆነ አላግባብ በልጽጋችኋል ልንባል አይገባም፣ከ2-4 ያሉት

አመልካቾች በድርጅቱ ስለመስራታችን የቀረበ ማስረጃ የለም፣ተጠሪዎች አጥተዋል ሊባል የሚችለው ኪራይ ብቻ በመሆኑ የታጣ ገቢ ሊጠይቁ አይችሉም፣ከውል ውጪ ደረሰ በሚሉት ጉዳት ወለድ መጠየቅ አይችሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በአመልካቾች የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ ካደረገ በኋላ ከ2-4 ያሉት አመልካቾች ድርጅቱን ይዘው ተገልግለዋል ማለት አይቻልም ተብሎ በመ/ቁ. 11597 ስለተወሰነና ስለመገልገላቸው ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ከክሱ ነፃ ናቸው፣አንደኛ አመልካች ግን በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ በፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የሆቴል ድርጅቱን ያለአግባብ ይዘው በመቆየታቸው ተጠሪዎች ላይ ለሚደረሰው ጉዳት ሃላፊ ስለሆኑ ኪሳራ ሊከፍሉ ይገደዳሉ ስለተባለ ሃላፊ ናቸው በማለት ከኀዳር 1989 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 27 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ የ86 ወር ብር 602,000.00(ስድስት መቶ ሁለት ሺህ ብር) ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካቾች ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2143 በይርጋ ሊታገድ ይገባል፣አንደኛ ተጠሪ ድርጅቱን የተገለገልኩት በመንግስት መመሪያ ከኪ.ቤ.አ.ድ ጋር ባደረኩት የኪራይ ውል በመሆኑ ያለበቂ ምክንያት እንደተገለገልኩ ተደርጎ ያለአግባብ በልጽገሃል ልባል አይገባም፣ተጠሪዎች ቀደም ሲል ሲከሱ ድርጅቱ እስኪለቀቅላቸው ድረስ ኪራይ መጠየቅ ሲችሉ ነጥለው ባቀረቡት ክስ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 መሰረት ድጋሚ ክስ ሊያቀርብ አይችሉም፣ የሰራሁት ከ2-4 ካሉት አመልካቾች ጋር ኃ/የተ/የግ/ማህበር ማቋቋም በመሆኑ ብቻዬን ሃላፊ ልባል አይገባም፣ለኪ.ቤ.አ.ድ በወር ብር 4,767.00(አራት ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ ሰባት) ስከፍል ስለነበር ይኸው ገንዘብ ሊቀነስ ይገባል፣ወለድ ልከፍል አይገባም፣ሊከፈል ይገባል ከተባለም ያለአግባብ መበልጸጌ በፍ/ቤት ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ ሊሆን ይገባል፣ከ2-4 የተጠቀሱት አመልካቾች ወጪና ኪሳራ ሊታሰብላቸው ይገባል በማለት ስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲሻርላቸው ጠይቀዋል፡፡ ይህ ችሎት አመልካቾች ያቀረቧቸው ቅሬታዎች ለሰበር ችሎት ቀርበው እንዲታዩ በማዘዙ ተጠሪዎች ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት ካቀረቡት ቅሬታ አኳያ ይህ ችሎት ምላሽ ሊሰጣቸው ይገባል ብሎ ያመነባቸው፣

1. ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል? አይገባም?
2. ክሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216/4/ መሰረት በድጋሚ ሊቀርብ አይችልም? ይችላል?
3. አንደኛ አመልካች ብቻቸውን ለክሱ ሃላፊ ናቸው? አይደሉም?
4. ሃላፊ ናቸው ከተባለ መጠኑን አስመልክቶ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት አለበት? የለበትም?
5. አንደኛ ተጠሪ ወለድ ሊከፍሉ ይገባል? አይገባም?
6. ከ2-4 ያሉት አመልካቾች ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው አለመወሰኑ መሰረታዊ ሕግ ስህተት ነው? አይደለም? የሚሉት ናቸው፡፡ ችሎቱም እያንዳንዱን ጭብጥ በየተራ ተመልክቷል፡፡

### 1. <u>ይርጋ በተመለከተ</u>

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት አንደኛ ተጠሪ ከውልና ከሕግ ውጪ የተጠሪዎችን የሆቴል ድርጅት ይዘው በመገልገል ያለአግባብ በመበልፀጋቸው ኪሳራ ከፍለው ድርጅቱን ለቀው እንዲያስረክቡ ስለተወሰነባቸው የፍ/ቤቱ ውሳኔ ካረፈበት ዘመን ጀምሮ ድርጅቱን እስካስረከቡበት ጊዜ ድረስ ያለአግባብ በድርጅቱ በለፀጉበት መጠን እንዲከፍሉ ነው፡፡ አንደኛ አመልካች ክሱ የቀረበው ነሐሴ 16 ቀን 1996 ዓ.ም ስለሆነ ከነሐሴ 16 ቀን 1994 ዓ.ም በፊት ያለው በፍ/ሕ/ቁ. 2143 መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2143 ሳይሆን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677/1/ እና 1845 ነው በማለት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡ ችሎቱም ጉዳዩን እንደመረመረው አግባብነት ያለው የትኛው የሕግ ድንጋጌ ነው የሚለው እንዳለ ሆኖ አንደኛ አመልካች እንደሚሉት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2143 ነው ቢባል እንኳን ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ ተጠሪዎች ቀደም ሲል በነበረው ክርክር አንደኛ አመልካች ድርጅቱን የውሉ ዘመን ካበቃ በኋላ ድርጅቱን ያለአግባብ በመያዛቸው ድርጅቱን እንዲለቁና ኪሳራ እንዲከፍሉ ጥቅምት 22 ቀን 1989 ዓ.ም ያቀረቡት ክስ በፍ/ቤት ክርክር ሲደረግበት ቆይቶ በመጨረሻ በጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ያገኘው ሚያዝያ 21

ቀን 1995 ዓ.ም ነው፡፡ ከዚህ በኋላ በዚህ መዝገብ የቀረበውን ጉዳይ አስመልክቶ ተጠሪዎች ክስ ያቀረቡት ነሐሴ 16 ቀን 1996 ዓ.ም ነው፡፡ ይርጋ ከሚቋረጥባቸው ምክንያቶች አንደኛው ባለገንዘቡ መብቱ እንዲታወቅለት በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ለባለእዳው አስታውቆ የተገኘ እንደሆነ መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1851/ለ/ ስር የተመለከተ በመሆኑ ተጠሪዎች መብታቸውን ለማረጋገጥ ያቀረቡት ክስ ይርጋውን ስለሚያቋርጠውና በዚህ መዝገብ በቀረበው ጉዳይ ላይ ክስ የቀረበው የቀድሞው ክስ የመጨረሻ ውሳኔ ካገኘ በኋላ ሁለት አመት ሳይሞላው በመሆኑ አንደኛ አመልካች ይርጋውን በተመለከተ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

2. <u>ክሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216/4/ መሰረት ድጋሚ ሊቀርብ አይገባም የተባለው በተመለከተ</u>

ተጠሪዎች ቀደም ሲል ባቀረቡት ክስ አንደኛ አመልካች የኪራይ ዘመኑ ካበቃ በኋላ የሆቴል ድርጅቱን ይዘው ስለተገለገሉ ክስ እስከቀረበበት ግዜ ድረስ ያለውን ኪራዩን ከፍለው እንዲወጡና ክስ ከተመሰረተ በኋላ ላለው ጊዜ የመክሰስ መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም አንደኛ አመልካች ያለአግባብ የሆቴል ድርጅቱን ስለያዙ ክስ እስከተመሰረተበት ጊዜ ድረስ ያለውን ኪሳራ ሲወስን ከክሱ በኋላ ላለው ጊዜ በሕጉ መሰረት የመክሰስ መብታቸውን ጠብቆላቸዋል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216/2/3/ መሰረት ከሳሽ ክሱን ለማቅረብ ምክንያት የሆኑትን ሁሉ አጠቃሎ ማቅረብ እንዳለበትና ክስ ለማቅረብ ሲችል ሆነ ብሎ ቀንሶ ባስቀረው ንብረት ላይ ድጋሚ ክስ ለማቅረብ የማይቻል መሆኑን አጠቃላይ መርህ ያስቀምጣል፡፡ ይሁን እንጂ ፍ/ቤትን በማስፈቀድ ሊጠየቅ ይገባው ከነበረው ውስጥ ቀንሶ ማስቀረት እንደሚቻልና በከፊል በቀረው መብት ላይም ድጋሚ ክስ ማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ ንኡስ ቁጥር 4 ልዩ ሁኔታን አስቀምጧል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ተጠሪዎች ከክሱ በኋላ ላለው ጊዜ የመክሰስ መብታቸውን ፍ/ቤቱ የጠበቀላቸው በመሆኑ ቀደም ሲል ሊከሱ ሲገባ ቀንሰው ስላስቀሩ በድጋሚ ሊከሱ አይገባም የሚለው የአንደኛው አመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

3. <u>አንደኛ አመልካች ለደረሰው ጉዳት ሃላፊ ናቸው አይደሉም? የሚለውን በተመለከተ</u>

ቀደም ሲል ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ አንደኛ አመልካች የተጠሪዎች ሃብት መሆኑን እያወቁ በውል ወይም በሕግ ሆቴሉ ላይ ያገኙት መብት ሳይኖር ከተጠሪዎች ፈቃድ ውጪ በእምቢተኝነት ይዘው በመቆየታቸው ተጠሪዎች ራሳቸው ሰርተው እንዲጠቀሙበት ወይም ለአንደኛ አመልካች ባከራዩት መንገድ ለሌላ ሰው አከራይተው የኪራይ ገቢ እንዳያገኙበት በማድረግ ጉዳት በማድረሳቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2027/2/ እና 2028 መሰረት በሃላፊነት ሊጠየቁ የሚገባ ከመሆኑም በላይ በፍ/ሕ/ቁ. 2162 መሰረት ኪሳራ ሊከፍሉ ይገደዳሉ በማለት አንደኛ አመልካች ብቻቸውን ሃላፊነት ያለባቸው መሆኑን የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም የአንደኛ አመልካች ሃላፊነት ቀደም ሲል ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ በመሆኑ ብቻቸውን ኪሳራ የመክፈል ሃላፊነት አለባቸው፡፡

4. <u>የኪሳራውን መጠን በተመለከተ</u>

ይህን ነጥብ አስመልክቶ አንደኛ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ቤቱን መንግስት ባወጣው መመሪያ መሰረት ከኪ.ቤ.አ.ድ ከታህሣሥ 1 ቀን 1988 ዓ.ም ጀምሮ ተከራይተው ለድርጅቱ በወር ብር 4,767.00(አራት ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ ሰባት) ሲከፍሉ ስለነበር የስር ፍ/ቤት ይህንኑ ገንዘብ ሊቀነስ ይገባ ነበር የሚል ነው፡፡ አንደኛ አመልካች የሆቴል ድርጅቱን ያለበቂ ምክንያት ይዘው በመገልገላቸው አላግባብ በበለፀጉበት መጠን ሃላፊ መሆናቸው ተወስኗል፡፡ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሲሰጥ የኪሳራው መጠን ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበትና ተጠሪዎች ያጡት ጥቅም በኪራይ መጠን ልክ ታስቦ መሆን እንዳለበት የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት አስቀድሞ መወሰኑን ከግምት በማስገባት ተጠሪዎች የሚገባቸው ድርጅታቸው ከውል ወይም ከህግ ውጪ በአንደኛ አመልካች በመያዙ ምክንያት እነሱ ባጡት ልክና አመልካቹ ራሳቸውን ባበለፀጉበት መጠን ሲሆን ይህም የድርጅቱ የኪራይ መጠን ነው በማለት በወር ብር 7,000.00(ሰባት ሺ.ህ) ታስቦ የ86 ወር ብር 602,000(ስድስት መቶ ሁለት ሺ.ህ) ወስኗል፡፡ በሌላ ሰው የስራ ድካም ወይም የሌላ ሰው ሃብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አላግባብ ጥቅም ባገኘበት መጠንና ለባለሃብቱ ወይም ጉልበቱ ለደከመው ሰው አድራጉቱ ባደረሰው ጉዳት መጠን ለባለሃብቱ ወይም ጉልበቱ ለደከመው ሰው ኪሳራ መክፈል እንደሚገደድ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2162 ስር ተመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች ላይ የደረሰው የጉዳት መጠን በድርጅቱ ኪራይ መጠን እንደሆነ ቀደም ሲል የፌ/ጠቅላይ

ፍ/ቤት ሆነ በዚህ ጉዳይ ፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ወስነዋል፡፡ ነገር ግን አንደኛ አመልካች ለታህሣሥ 1 ቀን 1988 ዓ.ም ጀምረው ከኪ.ቤ.አ.ድ ጋር ባደረጉ የኪራይ ውል ለድርጅቱ ብር 4,767.00 ኪራይ ይከፍሉ እንደነበር የገለፁትን ተጠሪዎች ክደው አልተከራከሩም፡፡ በመሆኑም አንደኛ አመልካች አላግባብ በለፀጉ ሊባል የሚችለው ከድርጅቱ የኪራይ መጠን ላይ ለኪ.ቤ.አ.ድ ሲከፍሉ የነበሩ ኪራይ ተቀንሶ በልዩነት በሚገኘው የገንዘብ መጠን ነው፡፡ 1ኛ አመልካች በአንድ በኩል ለኪ.ቤ.አ.ድ ኪራይ ሲከፍሉ ቆይተው በድጋሚ ለተጠሪዎች ገንዘቡን ይክፈሉ ማለት አለአግባብ ከበለጸጉበት ገንዘብ በላይ እንዲከፍሉ ማድረግ በመሆኑ ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች የተመለከቱት የኪሳራ አከፋፈል ደንብን የሚጥስ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች አንደኛ አመልካች ያለአግባብ ከበለጸጉበት በላይ እንዲከፍሉ መወሰናቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## 5. <u>ወለድን በተመለከተ</u>

አንደኛ አመልካች ያለአግባብ በልጽገዋል ተብሎ ለቀረበ ክስ ወለድ ሊከፈል እንደማይገባና ይገባል የሚባል ቢሆን እንኳን ሊከፈል የሚገባ ያለአግባብ መበልፀጋቸው በፍርድ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ተከራክረዋል፡፡ አንደኛ አመልካች የተጠሪዎች የሆቴል ድርጅት ከሕግና ከውል ውጪ ይዘው በመገልገል ያለአግባብ መበልፀጋቸው በመረጋገጡ ኪሳራ እንዲከፍሉ ተወስኖባቸዋል፡፡ በመሆኑም ገንዘቡን ከፍለው እስኪያጠናቅቁ ድረስ ወለድ የማይከፍሉበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በሌላ በኩል እኚሁ ተጠሪ አላግባብ መበልፀጋቸው የተረጋገጠው በዚህ መዝገብ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን ቀደም ሲል የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሚያዝያ 21 ቀን 1995 ዓ.ም ውሳኔ ሲሰጥ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች አንደኛ አመልካች በዚህ ጉዳይ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ገንዘቡን እንዲከፍሉ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለውም፡፡

## 6. <u>ወጪና ኪሣራን በተመለከተ</u>

በስር ፍ/ቤት ከሁለት እስከ አራት ያሉት አመልካቾች ከክሱ በነፃ በመሰናበታቸው በጉዳዩ ረቺ መሆናቸውን ተገንዝበናል፡፡ ነገር ግን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.462 ስር እንደተመለከተው ፍ/ቤቱ በክስ ምክንያት የሚከፈለውን ወጪና ኪሳራ በተመለከተ ሊከፈል የሚገባው መሆን አለመሆኑን፣ማን እንደሚከፍልና ምን ያሕል እንደሚከፈል ፣ከምን ሃብት ላይ እንደሚከፈል በአጠቃላይ ትክክል መስሎ በሚገመተው ሁኔታ ትእዛዝ መስጠት የሚያስችለው ሰፊ ስልጣን አለው፡፡ በመሆኑም የክርክሩን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማካተት ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ እንዲቻቻሉ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ለማለት አላስቻለንም፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33915 ሰኔ 28 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 31943 ጥር 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አንደኛ አመልካች የተጠሪዎችን የሆቴል ድርጅት ያለአግባብ ይዘው የበለፀጉበትን መጠን በወር ብር 7000(ሰባት ሺህ) በመሆኑና ከዚህ ገንዘብ ውስጥ አንደኛ አመልካች ለኪ.ቤ.አ.ድ ሲከፍሉ የነበረው ብር 4,767.00 (አራት ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ ሰባት) ሊቀነስ ስለሚገባ አንደኛ ተጠሪ የ86 ወራት በወር ብር 2,233.00(ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ሶስት) ታስቦ በጠቅላላው ብር 192,038(አንድ መቶ ዘጠና ሁለት ሺ ሰላሳ ስምንት) ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪዎች ይክፈሉ፡፡
3. ቀሪው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ፀንቷል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. በተሻሻለው ውሳኔ መሰረት መፈፀም ይቻል ዘንድ ይህ ችሎት ሚያዝያ 13 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 43636

መጋቢት 22 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አልማዝ ተሰማ - ጠ/ደሣለኝ ደምሴ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ በየነ ወ/ሚካኤል
2. ወ/ሮ ፅጌ ተሾመ } የቀረበ የለም

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ውል ይፈፀምልኝ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ ተጠሪዎች ቤት ሸጠውላቸው አብዛኛውን ገንዘብ የተቀበሉ መሆኑን ገልፀው ቀሪውን ክፍያ ተቀብለው ቤቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ቤቱን እንዲያስረክቧቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎችም ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ አመልካች እንዲፈፀምላቸው የሚጠይቁት ውል ከተደረገ 10 አመት ያለፈው በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የመ/ደረጃ መቃወሚያና ሌሎች ክርክሮች አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ውሉ የተደረገው የካቲት 18 ቀን 1985 ዓ.ም ሲሆን ክስ የቀረበው ደግሞ ከ14 ዓመት በኋላ ሐምሌ 6 ቀን 1999 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበው የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው ተጠሪዎች ቀሪ ገንዘብ አልተከፈለንም በማለት በአመልካች ላይ ክስ አቅርበው ውሉ አይፈርስም ተብሎ ህዳር 15 ቀን 1993 ዓ.ም ውሳኔ ስለተሰጠ ይርጋው ይቋረጣል፣ ውሉ ሊፈርስ ይገባል? አይገባም? የሚለው ክርክር ውጤት ሳያገኝ ውል ሊፈፀም ይገባል? አይገባም? የሚል ክርክር ሊቀርብ ስለማይገባ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ ለክርክር ምክንያት የሆነው የሽያጭ ውል ይፈርሳል አይፈርስም? በሚለው ነጥብ ላይ በፍ/ቤት ሲከራከሩ የቆዩ መሆኑ ከተረጋገጠ የአመልካች የንብረት ልረከብ ጥያቄ በይርጋ ሊታገድ ይገባል የሚለውን ዳኝነት አግባብነት ለማየት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ተጠሪዎችም ቀርበው የቃል ክርክራቸው ተሰምቷል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘ ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ክስ የመሰረቱት ከተጠሪዎች ጋር ባደረጉት የሽያጭ ውል መሰረት ተጠሪዎች ቤቱን እንዲያስረክቧቸው ነው፡፡ በሌላ አነጋገር አመልካች እየጠየቁ ያሉት ውል እንዲፈፀምላቸው ነው፡፡ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በቀር ውሉ እንዲፈፀም ወይም ካለመፈፀሙ የተነሳ ስለሚደርስ ጉዳት ወይም ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት በአስር አመት ይርጋ እንደሚቀር ፍ/ብ/ህ/ቁ 1845 ይናገራል፡፡ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት መቃወሚያ አመልካች የውል ይፈፀምልኝ ጥያቄ ያቀረቡት ውሉ ከተደረገ ከ10 አመታት በኋላ በመሆኑ ጥያቄው በይርጋ ሊታገድ ይገባል በሚል ነው፡፡ ከስር ፍ/ቤት መዝገብ እንደተረዳነውም በግራ ቀኙ መሃከል የሽያጭ ውል የተደረገው የካቲት 18 ቀን 1985 ዓ.ም ሲሆን ክሱ የቀረበው ግን ሐምሌ 6 ቀን 1999 ዓ.ም ከ14 አመት በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም ከፍ ሲል በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል የሚለው መከራከሪያ አግባብነት አለው፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች ምንም እንኳን ውሉ ከተደረገ 10 አመት ያለፈው ቢሆን ተጠሪዎች

ውሉ እንዲፈርስላቸው ክስ መስርተው ክርክር ሲደረግ ቆይቶ ውሉ አይፈርስም በሚል የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠው ህዳር 15 ቀን 1993 ዓ.ም በመሆኑ ይርጋውን ያቋርጠዋል እንዲሁም ውል ይፈርሳል አይፈርስም የሚለው ጭብጥ ክርክር ላይ እያለ ይኸው ውል ሊፈፀም ይገባል የሚል ክርክር እንዳይቀርብ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 8 ይከለክላል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ቢኖርም ይህ የይርጋ ጊዜ ግን በተለያዩ ምክንያቶች ሊቋረጥ እንደሚችል የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851 ያስቀምጣል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ይርጋ ከሚቋረጥበት ምክንያት አንዱ ባለገንዘቡ መብቱ እንዲታወቅለት በፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ ለባለእዳው አሳውቆ የተገኘ እንደሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች የሚከራከሩት ውል እንዲፈርስ ክስ አቅርበው የነበሩት ተጠሪዎች እንጂ አመልካች ባለመሆናቸው ይርጋው ሊቋረጥላቸው አይችልም በማለት ነው፡፡ ከመዝገቡም እንደተረዳነው በእርግጥም ቀደም ሲል ውሉ እንዲፈርስ ክስ አቅርበው የነበሩ ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በቀረበውም ክስ ፍ/ቤቱ የያዘው የሽያጩ ውል ሊፈርስ ይገባል አይገባም የሚለውን ጭብጥ ግን ውሉ ሊፈፀም ይገባል አይገባም ከሚለው ጭብጥ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው፡፡ ምክንያቱም ውሉ ሊፈርስ ይገባል ከተባለ ውጤቱ ግራ ቀኙ ውሉን ለመፈፀም የሰሯቸው ስራዎች ሁሉ ቀሪ ሆነው ወደነበሩበት መመለስ ሲሆን ውሉ የማይፈርስ ከሆነ ደግሞ ውሉ እንዲፈፀም ለሚጠይቀው ወገን የውሉን መፈፀም እንዲጠይቅ መብት የሚሰጠው በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም የውሉን አፈፃፀም በተመለከተ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ክርክር ይርጋውን የሚያቋርጠው ነው፡፡ በአጠቃላይ ግራ ቀኙ በውሉ መፍረስ አለመፍረስ ክርክር ላይ በነበሩበት ወቅት አመልካች ውል እንዲፈፀምላቸው ክስ ስላላቀረቡ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 6841 መጋቢት 9 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 66753 ህዳር 29 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን አይገባም ብለናል፡፡ በመሆኑም በፍሬ ጉዳዩ ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 46947

መጋቢት 07 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- አቶ ዘበነ ኃ/ማሪያም - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- 1. ወ/ሮ አባይነሽ ለገሰ

2. ወ/ሮ አስካለ ወ/ሐዋሪያት } ቀረቡ

3. ወ/ሮ ጽጌ ተሰማ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የኪራይ ገንዘብን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ሲሆኑ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካች ከተጠሪዎች አንድ ክፍል የፀጉር ቤት ሱቅ በወር ብር 155.00(አንድ መቶ ሃምሳ አምስት ብር) ለመክፈል ተስማምተው፣ተከራይተው ከሐምሌ 1999 ዓ.ም እስከ ሕዳር 2001 ዓ.ም ድረስ ያለውን ውዝፍ የቤት ኪራይ እዳ ያልከፈሉ መሆኑን በመግለጽ በገቡት የኪራይ ውል ግዴታ መሰረት እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ በማንሳት የተከራከሩት የኪራይ ውል ከተጠሪዎች ጋር ማድረጋቸውን ሳይክዱ ውሉ የተደረገው ተጠሪዎች በፀጉር ቤቱ ላይ መብት ሳይኖራቸው በማጭበርበር በመሆኑ አዲስ የኪራይ ውል ከሕጋዊ ባለቤት (ፌድባር ከተባለ የገብረሰናይ ድርጅት) ጋር አድረገው ኪራዩን ለዚሁ ህጋዊ ባለቤት ለሆነው ማህበር በደረሰኝ እየከፈሉ ሱቁን የሚሰሩበት መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት ክርክሩን ከመረመረ በኂላ አመልካች የኪራይ ውሉን ከሱቁ ህጋዊ ባለቤት ጋር አድርጌአለሁ በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው፣ህጋዊ ነው የተባለ ድርጅትም ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጐ አለመከራከሩ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመጥቀስ የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጐ ለኪራይ ገንዘቡ ኃላፊ በማድረግ ብር 2,870.00(ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ብር) ለተጠሪዎች እንዲከፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ ከዚያም አመልካች በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት በሰበር አቤቱታ ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 22 ቀን 2001 ዓ.ም በዓፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱት በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪዎች በሱቁ ላይ ሕጋዊ መብት ሳይኖራቸውና የኪራይ ገንዘቡን አመልካች በአዲስ ኪራይ ውል መሰረት ለሕጋዊ አከራይ የኪራይ ገንዘቡን ከፍለው ባለበት ሁኔታ ተጠሪዎች ቀደም ሲል የኪራይ ውል አድርገዋል ተብሎ የኪራይ ገንዘቡን አመልካች በድጋሚ እንዲከፍሉ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፣አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ተጠሪዎች ያከራዩኝ የእነርሱ ያልሆነ ቤት ነው እኔ ከቤቱ ትክክለኛ ባለንብረት ጋር የቤት ኪራይ ውል ተዋውዬ ለቤቱ ባለቤት ኪራይ ከፍያለሁ በማለት ካቀረቡት ክርክርና ማስረጃ ታልፎ ለተጠሪዎች የቤት ኪራይ ይክፈሉ መባሉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪዎች ቀርበው ታሕሳስ 21 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎችንና አመልካች የኪራይ ውል ማድረጋቸውን፣አመልካች ለተወሰነ ጊዜ የኪራይ ገንዘቡን ለተጠሪዎች ከከፈሉ በኂላ ማቋረጣቸውን፣አመልካች የኪራይ ገንዘቡን ለተጠሪዎች አልከፍልም በማለት የሚከራከሩት የሱቁ ሕጋዊ ባለቤት አይደሉም፣ምንም መብት የላቸውም በማለት ስለመሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች ቤቱን ሬድባር ከተባለ የግብረሰናይ ድርጅት ያገኙት መሆኑን ጠቅሰው መከራከራቸውን ተገንዝበናል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው በአመልካች በኩል የቀረቡት ማስረጃዎች ተቀባይነት የማያገኙበትን ምክንያት በመግለጽ ነው፡፡ እንዲሁም አመልካች የኪራይ ገንዘቡን ከፍዬአለሁ የሚሉት ድርጅት ወደ ክርክሩ እንዲገባ አለመጠየቁም ተገቢነት የለውም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ከዚህ በስር ፍርድ ቤት ከተደረገው ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም ከስር ፍርድ ቤት የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት በግልጽ መገንዘብ የተቻለው ውሳኔው የተሰጠው በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን የኪራይ ውል መሰረት አድርጐ መሆኑን ሲሆን የኪራይ ውሉ በሕጉ አግባብ ውድቅ ባልተደረገበት ሁኔታ አመልካች የተጠሪዎችን የባለቤትነት መብት መሰረት በማድረግ በኪራይ ውሉ አልገደድም የሚሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በሕጉ አግባብ የተቋቋመ ውል በሕጉ አግባብ እስካልፈረሰ ድረስ በተዋዋይ ወገኖች መካከል አስገዳጅነት አለውና፡፡ በመሆኑም የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ የኪራይ ውሉን መሰረት ያደረገ መሆኑ ተረጋግጦ አመልካች በገቡት ግዴታ ውዝፍ ኪራዩን እንዲከፍሏቸው መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

- ይህ ችሎት ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሰጥቶት የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ.45545

መጋቢት 22 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሰ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሸዋዬ ኑርዬ - ጠበቃ አቶ አበራ ማሬ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ምንአዩ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ አቶ አበራ ታደሰ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ አመልካች ስላቀረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርበው ሰኔ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ የእጅ በእጅ ሽያጭ ውል ብር 120,540.00(አንድ መቶ ሀያ ሺ አምስት መቶ አርባ ብር) ዋጋ ያለው የቢሮ ዕቃ ከተጠሪ(ተከሳሽ) ለመግዛት በመስማማት ብሩን ወዲያውኑ የከፈሉ መሆኑንና ተጠሪ ግን የገዛሁትን የቢሮ ዕቃ ወዲያውኑ አላስረከበኝም፡፡ ተጠሪ ዕቃውን ስላላስረከበኝ ከሃምሌ 1998 ጀምሮ ውሉን ማፍረሴን ለተከሳሽ አሳውቄአለሁ፡፡ ተጠሪ ገንዘቡን ሊመልስልኝ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ገንዘቡን ከነወለዱ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ ከከሳሽ (አመልካች) ጋር ያደረግሁት ውል የለም፡፡ ከሳሽ ያቀረቡት የእጅ በእጅ ሽያጭ የክፍያ ደረሰኝ ሰነድ ዕቃውን ሰነዱን የያዘው ሰው የተረከበበትን ቀን የሚገልፅ ስለሆነ ሰነዱ ዕቃውን ስለመረከባቸው በቂ አስረጅ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሁለት ጭብጦችን መስርቷል፡፡ የመጀመሪያው በተጠሪና አመልካች መካከል የእጅ በእጅ ሽያጭ ተፈፅሟል ወይስ አልተፈፀመም? የሚል ሲሆን ሁለተኛው አመልካች ዕቃውን ተረክበዋል ወይስ አልተረከቡም? የሚሉ ናቸው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪና በአመልካች መካከል የእጅ በእጅ ሽያጭ የተፈፀመ መሆኑን በቂ ማስረጃ አልቀረበም፣ የሽየጭ ውል አለ ቢባል እንኳን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278(1) አመልካች ክፍያ ሲፈፅም ዕቃውን የሚረከብ መሆኑ ስለተደነገገና ይህንን በምስክር ማስተባበል ስለማይቻል ከሳሽ(አመልካች) ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት የሽያጭ ውል የለም በማለት የወሰነው እኔ ባቀረብኩት ሰነድ ስም አልተጠቀሰም በማለት ነው፡፡ ሆኖም እኔ ያቀረብኩት ክፍያ የፈፀምኩበት ደረሰኝ ነው፡፡ የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በፅሑፍ እንዲደረግ ህግ አያስገድድም፡፡ እኔ ደረሰኙን ይዤ መገኘቴ ከተጠሪ ጋር የዕቃ ግዥ የፈፀምኩ መሆኑን የሚያስረዳ ደጋፊ ማስረጃ ነው፡፡ ተጠሪ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278

ዕቃውን አላስረከበኝም፡፡ ተጠሪ የሸጠውን ዕቃ የሚያስረክብበት የራሱ ሥርዓት ያለው ሲሆን በዚያ ሥርዓት መሠረት ዕቃውን ስለማስረከቡ አላስረዳም፡፡ በእኔ በኩል ተጠሪ የገዛሁትን ዕቃ ለማስረከብ የቆጠርኳቸውን ምስክሮች ለማስረዳት ያቀረብኩትን ጥያቄ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278 እና ፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2006 የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ውሉ እንዲፈርስና ወደ ነበርንበት እንድንመለስ አለመወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የያዙት ደረሰኝ ተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለበት ደረሰኝ እንጅ የሽያጭ ውል መኖሩን የሚያስረዳ አይደለም፡፡ ፍርድ ቤቱ ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278(1) የሰጠው ትርጉም ስህተት የለበትም፡፡ ድርጅታችን በመጋዘን የሌለን ዕቃ እና ወዲያውኑ የማናስረክበውን ዕቃ ዋጋ የመቀበል ልምድ የለውም፡፡ አመልካች ውሉ እንዲፈርስ ከሀያ ስምንት ቀናት በኋላ መሆኑ ውሉን አጠራጣሪ ያደርገዋል የሚል ክርክር አቀርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከመዝገቡ ለመረዳት እንደቻልነው አመልካች የቢሮ ዕቃ ከተጠሪ የገዙ መሆኑን የዕቃውን ዋጋ ገቢ ያደረጉ መሆኑንና ዕቃውን ከተጠሪ ተረክበው ያልወሰዱ መሆኑን ለማስረዳት የፅሑፍ (የሰነድ) ማስረጃና የሰው ምስክሮች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የእጅ በእጅ ሽያጭ ውል በማለት ውሣኔ የሰጠው ተጠሪ ለአመልካች የቢሮ ዕቃ የሸጠ መሆኑን ለሽያጭ ውል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2266 በተሰጠው ትርጉም መሠረት አመልካች ለማስረዳት ያቀረቧቸውን ሁሉንም ማስረጃዎች በመመርመርና በመመዘን ሣይሆን አመልካች በሰነዱ ማስረጃነት ያቀረቡትን የዕቃ ዋጋ የተከፈለበትና የተጠሪ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሰበሰበ መሆኑን የሚያረጋግጠውን ከአመልካች እጅ የሚገኘውን ደረሰኝ ብቻ በመመርመር ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የቢሮ ዕቃ ሽያጭ ውል አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ የወሰነው ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን በአመልካች በኩል የቀረቡ ማስረጃዎችን በመስማትና በመመርመር አለመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የዳኝነት አካሄድ ሥርዓት ጉድለት የፈፀመ መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡት ደረሰኝ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278(1) የተሸጠውን ዕቃ ማስረከብ ከዋጋው መክፈል ጋር አንድ ላይ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ አመልካች ገንዘብ በተቀበለበት ጊዜ ዕቃዎቹን መረከቡን ደረሰኙ ያስረዳል ሌላ ማስረጃ መሰማት አይቻልም በማለት የሰጠው የሕግ ትርጉም ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ “በውሉ የተነገረ ተቃራኒ ነገር ከሌለ በቀር የተሸጠውን ማስረከብ ከዋጋው መክፈል ጋር በአንድ ጊዜ መሆን አለበት” የሚል ነው ይህ ድንጋጌ በሻጭ ላይ ግዴታ የሚጥል ድንጋጌ ነው፡፡ የእጅ በእጅ ሽያጭ በሆነ ጊዜ የዕቃው ዋጋ ሲከፈል የተገዛውን ንብረት ወዲያውኑ ለገዥ የማስረከብ ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 2 ሻጭ ዕቃውን ለገዥ ሣያስረክብ ሊቆይ የሚችልበትን ልዩ ሁኔታ ይደነግጋል፡፡

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 1 በተደነገገው መሠረት ገዥ ገንዘቡን ከከፈለ ከግማሽ ሠዓት በኋላ ከሶስት ሠዓት በኋላ ወይም በማግስቱ ለመረከብ ተስማምቶ የነበረ መሆኑን በማናቸውም አይነት ማስረጃ ሊያስረዳ የሚችል ስለመሆኑ “በውሉ የተነገረ ተቃራኒ ቃል ከሌለ በቀር” ከሚለው የድንጋጌው ሐረግ ለመረዳት እንችላለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ገዥ የዕቃውን ዋጋ ሙሉ በሙሉ የከፈለ ቢሆንም ሻጭ ዕቃውን ወዲያውኑ በማስረከብ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 1 የተጣለበትን ግዴታና ኃላፊነት ያልተወጣ መሆኑን ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳትን መብቱን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ የሚገደብ አይደለም፡፡ ከላይ የተገለፁትን ሁኔታዎች በማስረጃ በማረጋገጥ ገዥ የዕቃውን ዋጋ ለሻጭ ከፍሎ ዕቃውን ያልተረከበ መሆኑን በማስረዳት ሻጭ ዕቃውን እንዲያስረክበው ወይም የሽያጭ ውሉ ፈርሶ ገንዘቡን እንዲመልስለት መጠየቅ የሚችል መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ የማይገደብ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ የዕቃውን ዋጋ ከፍዬ ዕቃውን አለመረከቤን በማስረጃ

ላረጋግጥ በማለት ያቀረበውን ጥያቄ ለህጉ ድንጋጌ የተሣሣተ ትርጉም በመስጠት ዕቃውን አለመረከብህን በማስረጃ ለማረጋገጥ አትችልም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍርድ ቤት ከላይ የተገለፀው የዳኝነት አካሄድ ግድፈትና የህግ አተረጓጎም ስህተት ያለበትን ውሣኔ ሣያርም ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ከተጠሪ ጋር የቢሮ ዕቃዎች ለማግዛት ውል የተዋዋለ መሆኑን፣ አመልካች ለዕቃዎቹ ክፍያ የፈፀመ መሆኑን ወይም አለመሆኑንና አመልካች ዕቃዎቹን ተረክቦ የወሰደ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በአመልካችና በተጠሪ በኩል የሚቀርቡለትን አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመስማትና በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 47971

ሚያዝያ 05 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ጅቦ፣ ቱና - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ብርቂ ኢርክታ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ዋስትናን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኗ አመልካች እና በሌሎች ሁለት ግለሰሶች በስር ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ አመልካች ሁለት ግለሰቦች (አቶ ፌደሳ ሽኑ እና አቶ ዘውዱ ሽመልስ) የተጠሪን መኖሪያ ቤት ሰብረው ገብተው ስምንት ላደና ገብስ ሰርቀዋል ተብለው በተጠረጠሩበት ጉዳይ በአካባቢ ሽማገሌዎች እና በአከባቢው ቡድን ፊት ቀርበው ፌደሳ ሽኑ ልጃቸው ስለሆነ፣ ዘውዱ ሽመልስ ባለቤታቸው ስለሆነ በተጠረጠሩበት ጉዳይ ሌባ እንዳልሆኑ ቦኩ ላይ ቀርበው ካልማሉ የተጠቁትን የእህል ግምት ገንዘብ እከፍላለሁ በማለት የዋስትና ግዴታ በግዴታዋ መሰረት የተጠረጠሩትን ሰዎች በቦኩ አቅርባ ካለማስማሏ በተጨማሪ ሰዎቹን ሸሽገው የእህሉን ግምት ሳያስከፍሉ የቀሩ መሆኑን ገልፀው የእህሉን ግምት እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኗ አመልካችም የገቡት ግዴታ አለመኖሩን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር የአሁኗን አመልካች ለክሱ ኃላፊ በማድረግ የእህሉን ግምት ብር 686.00(ስድስት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር) እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለወረዳው ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 01 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ከጉዳዩ ለማስረጃነት በቀረበው ሰነድ ላይ የተገለፀው የአመልካች ግዴታ ተጠርጣሪዎቹን ለማቅረብ ሆኖ እያለ ለተጠረጠሩበት እህል ግምት ክፍያ ትፈፅሚያለሽ መባሉ ከዋስትና ሕግ ድንጋጌዎች መንፈስ ውጪ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አቤቱታቸውም ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች የገቡት የዋስትና ግዴታ አለ ወይስ የለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡

በመሰረቱ ዋስትና በሕጉ ጥበቃ የሚያገኘው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1922 ድንጋጌ ስር የተመለከተውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ዋስትና ግልፅ መሆን ያለበት ከመሆኑም በላይ ከተደረገው ውል ወሰን ለማለፍ የማይችል እና ለግዴታው ዋስ የሆነበት የገንዘቡ ልክ በዋስትናው ውል መገለፅ አለበት፡፡ ዋስትና ይህን ፎርማሊቲ ከማሟላቱም በተጨማሪ ለዋስትናው መሰረት የሆነው ዋናው ጉዳይም ሕጋዊ መሆን አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ፈረሙ በተባሉት ሰነድ የዋስትና ገንዘቡ በግልፅ ተገልጾ የተቀመጠ ካለመሆኑም በላይ ለግዴታው መሰረት ነው የተባለው ዋናው ጉዳይም ተጠርጣሪዎች በሕግ አስገዳጅነት በሌለው ሁኔታ ቦኩ ሂደው እንዲምሉ የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሕጉ አግባብ ጥበቃ የሚደረግለት የዋስትና ግዴታ አለ ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በጀርማ ኮርጴሳ ቀ/ገ/ማ/ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 050/2001 መጋቢት 02 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በኤልፋታ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 09144 ሰኔ 02 ቀን 2001 ዓ.ም፣ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 86060 ሐምሌ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 48358

ሚያዝያ 07 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ብርሃነ ገብረ ሐይሉ - ጠበቃ ሐጐስ ደበሱ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አንሲዮን ኮንትር ላፋም - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በቤት ኪራይ የሚከፈለውን የተርን ኦቨር ታክስ ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በመሰረቱት ክስ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 በቁጥር 459 የተመዘገበና የአመልካች ንብረት የሆነውን ቤት ሰኔ 26 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ የቤት ኪራይ ውል በኪራይ ይዞ ለሦስት አመታት በቢሮነት እና በማከማቻነት መገልገሉን፣ በዚህም መሰረት የቤት ኪራይ በድምሩ ብር 612,000.00(ስድስት መቶ አስራ ሁለት ሺህ) መከፈሉን፣ ለማከማቻነትና ለመሳሰለ አገልግሎት በኪራይ ለተያዘ ቤት በሚከፈል የቤት ኪራይ ላይ በመቶ አስር(10) የሆነ የተርን ኦቨር ታክስ በአገልግሎት ተጠቃሚ የሆነው ተከራይ እንዲከፍል፣ አከራዩም ታክሱን ከቤቱ ኪራይ ጋር ከተከራዩ ላይ እየሰበሰበ ሥልጣን ላለው ግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ገቢ እንዲያደርግ የውክልና ስልጣን እንደሰጠውና ግዴታ የሚጥልበት መሆኑን፣ በኪራይ ውሉም ተከራይ ከታክሱ ነፃ እንዳልሆነ ታክሱ ከቤት ኪራይ ገቢ ጋር ስላልተከፈለ አመልካች በህጉ መሰረት ለታክሱ ክፍያ በቅድሚያ ተጠያቂ ሆነው ላንድ አመት በተከፈለ የቤት ኪራይ ገቢ ብር 204,000.00(ሁለት መቶ አራት ሺህ ብር) ላይ የታሰበ ተርን ኦቨር ታክስ ብር 20,400.00(ሃያ ሺህ አራት መቶ ብር) ለግብር ሰብሳቢ አካል መክፈላቸውን፣ ለተጨማሪ የሁለት ዓመት ጊዜ በተከፈለ የቤት ኪራይ ክፍያ ብር 408000.00(አራት መቶ ስምንት ሺህ ብር) ላይ የሚታሰብ የተርን ኦቨር ታክስ ብር 48000.00(አርባ ስምንት ሺህ ብር) እንዲከፈል፣ እንዲሁም የታክስ እዳው ብር 61,000.00(ስልሳ አንድ ሺህ ብር) በሕግ በተወሰነው የመክፈያ ጊዜ ውስጥ ባለመከፈሉ ምክንያት መቀጫ ተጨምሮበት እንዲከፈል የአዋጁ ድንጋጌ እንደሚያስገድድ፣ ለጠበቃ ብር 11,000.00(አስራ አንድ ሺህ ብር) የተርን ኦቨር ታክስ ለመክፈል ግዴታ መግባታቸውን ገልጸው ተጠሪ በድምሩ ብር 61,200.00(ስልሳ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር) እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ለክሱ በሰጠው መልስ የቤት ኪራይ መኖሩን ሳይክድ ሕጉ ተከራይ ታክሱን እንዲከፍል የሚያስገድድ ነው ቢባል እንኳ በውሉ አንቀጽ 6 ስር በመንግስት ባለስልጣናት የሚጣለው ማንኛውም ቀረጥ አከራይ እንዲከፍል በማያሻማ መልኩ የተቀመጠ በመሆኑ ተፈፃሚነት ያለው ውሉ መሆኑን፣ ታክሱ በወቅቱ ባለመከፈሉ ለሚጣለው መቀጮ ግዴታ ያለበት አከራይ መሆኑን በመግለፅ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር አመልካች ብር 20,400.00(ሃያ ሺህ አራት መቶ ብር) ለግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት መክፈላቸው ስለተረጋገጠና ተከራይም የተርን ኦቨር ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን በመግለፅ ይህንኑ ገንዘብ ተጠሪ ለአመልካች ከዳኝነት ገንዘቡ እና ከጠበቃ አበል ከሆነው ብር 2040.00(ሁለት ሺህ አርባ) እንዲሁም ከቴምብር ቀረጥ ጋር እንዲከፍላቸው፣ ብር 61,200.00(ስልሳ አንድ ሺህ ሁለት መቶ) ግን አመልካች ለታክስ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት መክፈላቸውን ሳያረጋግጡ ተከራዩን(ተጠሪን) ሊጠይቁ አይችሉም በማለት ውድቅ አድርጎባቸዋል፡፡ ተጠሪ ብር 61,200.00 ሊከፍሉ አይገባም በተባለው የውሳኔ ክፍል አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ

ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የውሳኔ ክፍል ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ነሐሴ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ተርን ኦቨር ታክሱን አመልካች ከፍለው ካጠናቀቁ በኋላ ነው መጠየቅ የሚችሉት በሚል የተሠጠውን ውሳኔ ክፍል አግባብነቱን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልሳቸውን በፁሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪው የአመልካችን ቤት በኪራይ ይዞ በቢሮነትና በማከማቻነት እንደተገለገለበት እንዲሁም ቤቱ ለተጠቀሰው አገልግሎት በመዋሉ ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 308/1995 መሰረት ለአመልካች ለተከፈላቸው የቤት ኪራይ ገቢ ላይ ከመቶ አስር (10%) የሚከፈል ተርን ኦቨር ታክስ የሚከፈልበት ስለመሆኑ በተጠሪ ማስተባበያ ማስረጃ ያልቀረበበት ከመሆኑም በላይ በስር ፍርድ ቤትም የተረጋገጠ ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለታክሱ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን አምኖ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ያልተቀበለው አመልካች ብር 40,800.00 (አርባ ሺህ ስምንት መቶ ብር) ለታክስ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት መክፈላቸው አልተረጋገጠም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 308/1995 አንቀፅ 2(3፣ 5፣ 7፣ 8፣ 9 እና 12) እና 6 ድንጋጌዎች መሰረት ታክሱን ለአስከፋይ ባለሥልጣን ገቢ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡ ይህንን በሕጉ የተጣለባቸውን ግዴታ ለመወጣት ደግሞ ታክሱን ለታክስ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት ገቢ ከማድረጋቸው በፊት ከአገልግሎት ገዥው ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ ክፍያ መጠየቅ የሚከለክላቸው ምክንያት የለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ታክሱን ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ ሲያደርጉ ነው መጠየቅ የሚችሉት በማለት ያስቀመጠው ምክንያት በሕጉ ያልተመለከተ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በሕጉ የተጣለባቸውን ግዴታ ለመወጣት ተጠሪን ክፍያ እንዲፈፅሙ መጠየቃቸው ተቀባይነት የማያገኝበት አጥጋቢና ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 133650 ጥር 08 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 77649 ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች ብር 40,800.00(አርባ ሺህ ስምንት መቶ ብር) እንዲከፍል ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጡትን ሌሎች ወጪዎችን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 44691

ሚያዝያ 8 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ ሽባባው ወሌ - ጠበቃ ጌታቸው ውብሸት ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ሙሉጌታ ዓባይ - ጠበቃ አቶ እንዳልካቸው ይላቅ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርበው ተጠሪ ብር 7000(ሰባት ሺህ ብር) እስከ ግንቦት 30 ቀን 1991 ዓ.ም ሊመልስ ብድር ወስዶ ያልከፈለኝ ስለሆነ ሊከፍለኝ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ ከነ ወለዱ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ የአመልካች ጥያቄ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 መሰረት ሁለት ዓመት ያለፈው በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል፡፡ አክሲዮን ማህበር ለማቋቋም ውል ተዋውለን ብር 8000(ስምንት ሺህ ብር) ስለወሰደ እንዲቻቻልልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ የብድር ገንዘቡ ሊከፈል ከሚገባው ከሁለት ዓመት በላይ የቆየ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 መሰረት እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 የሰጠው ትርጉም የተሣሣተ መሆኑን በመተንተን የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሯል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 የሰጠው ትርጉም ስህተት መሆኑን በመግለጽ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024/ረ/ ጊዜ ተወስኖለት በየወቅቱ ለሚከፈል ገንዘብ እንጂ በአንድ ጊዜ ለሚከፈል ወለድ የሚያገለግል አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ እዳውን አልካደም የመቻቻል ጥያቄም ያቀረበ መሆኑ በመልሱ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የታመነ የብድር እዳ እንደከፈለ ይገመታል ተብሎ መወሰኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2025 ድንጋጌ የሚጥስ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው፡፡ በሁለት ዓመት ያልተከፈለ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024/ረ/ ቀሪ ይሆናል በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ብድሩን አለመክፈሉን በማመን የመቻቻል ጥያቄ እንዳቀረበ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ አንድ ሰው ብድሩን አለመክፈሉን አምኖ በሚከራከርበት ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024/ረ/ ተፈፃሚነት የሚኖረው አይደለም፡፡ ይኸም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2025/ሀ/ ድንጋጌ ለመገንዘብ

ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሳሽ በክሱ የገለፀውን ፍሬ ጉዳይ ተከሳሽ በከፊል ወይም በሙሉ ካመነ በእምነቱም መሰረት ውሣኔ ሊሰጥ እንደሚችል የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 242/፪/ በግልጽ የሚደነግግ በመሆኑ ተጠሪ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/፪/ ድንጋጌ እንደ ይርጋ ድንጋጌ በመቁጠር ብድሩን አለመክፈሉን ገልፆ መልስ ሰጥቶ ለሁለት ዓመት ስላልጠየቀ ልከፍል አይገባኝም በማለት ያቀረበው ክርክር የሕግ ድጋፍ የሌለው ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024/፪/ በዋናው ብድር ሣይሆን ለብድር የሚከፈለን ወለድን የሚመለከት ድንጋጌ መሆኑ የሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 35758 ታህሣሥ 20 ቀን 2002 ዓ.ም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ አመልካችና ተጠሪ ወለድ የሚከፈልበት የብድር ውል የሌላቸው በመሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024/፪/ በእነርሱ መካከል ያለውን የብድር ግንኙነት የሚመለከት አይደለም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ባይ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ከአመልካች የተበደረውን ብር 7000(ሰባት ሺህ) በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ክስ ከቀረበበት ሰኔ 13 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ለአመልካች ይክፈል ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 48094

ግንቦት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** እነ ሙና እንድሪስ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን አመልካቾች በተጠሪና በሥር አንደኛ ተከሳሽ ላይ ባቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 6 ቀበሌ 13 ክልል ቁጥር 563 የሆነው ቤት ለከሳሾችና ለአንደኛ ተከሳሽ ከወላጆቻችን በውርስ የተላለፈልን ንብረት ሲሆን አቶ ጅላል አብዱልመናን የተባሉ ግለሰብ ከሁለተኛ ተከሳሽ ላይ ገንዘብ ሲበደሩ አንደኛ ተከሳሽ አካለመጠን ባላደረሱት ወራሾች ላይ የተሰጠውን የሞግዚትነት ሥልጣን መሠረት አድርጎ የጋራ የውርስ ንብረት የሆነውን ቤት በመያዣነት ሠጥቷል፡፡ በአንደኛ ተከሳሽ የተፈጸመው ተግባር ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/300 እና 1266 አኳያ ሕገ-ወጥ ስለሆነ ሐምሌ 7 ቀን 1987 ዓ.ም እና ጥቅምት 16 ቀን 1987 ዓ.ም የፈረመው የመያዣ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ እንዲወሰንና የቤቱንም ካርታ ሁለተኛ ተከሳሽ እንዲመልስ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሾች ክስና ማስረጃ ለተከሳሾች ደርሶ መልስ እንዲሰጡ ታዞ አንደኛ ተከሳሽ ተጠርቶ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ሁለተኛ ተከሳሽ/የአሁን ተጠሪ/ ቀርቦ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት በመያዣነት መያዙን አምኖ ይህንን ለማድረግ የቻለው አንደኛ ተከሳሽ በቤተዘመድ ጉባኤ ዓማካይነት በ24/1/87 ዓ.ም የሞግዚትነት ሥልጣን ተሰጥቶት ፍ/ቤትም ቀርቦ በመፅደቁ ምክንያት እንደሆነና የተሰጠውም የሞግዚትነት ሥልጣን ሞግዚት በሆነላቸው ሰዎች ስም የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት በዋስትና ለመስጠት እንደሚችል በሰነዱ ላይ ስለተመለከተ በመሆኑ ለአንደኛ ተከሳሽ በተሰጠው የሞግዚትነት ሥልጣን ላይ ተመስርቶ የመያዣ ውሉ መፈረሙ በአግባቡ ስለሆነ የመያዣ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት ተከላክሏል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም የመያዣ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይንስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ መስርቶ ጉዳዩን ከመረመረ በኂላ የቤተዘመድ ጉባኤ አንደኛ ተከሳሽን ሞግዚት አድርጎ የሾመው በ18/10/81 ዓ.ም ሲሆን ጥቅምት 11 ቀን 1987 ዓ.ም የሞግዚትነት ሥልጣኑ ፍ/ቤት ቀርቦ ፀድቋል፡፡ በሞግዚትነት ማፅደቅ ውሳኔውም ላይ ከከሳሾች መካከል አንደኛ እና ሁለተኛ ከሳሾች ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ የወጡ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ሞግዚት በሆነላቸው ስም የተመዘገበ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ ወይም ዋስትና ለመስጠት የተፈቀደለት ቢሆንም የመያዣ ውሉን በተፈራረሙ ጊዜ አንደኛ እና ሁለተኛ ከሳሾች ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ ወጥተው የነበረ ስለሆነ ያለ እነሱ ስምምነት የመያዣ ውሉን መፈራረሙ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1266"ን" የሚጻረር ነው፡፡

በመሆኑም በወረዳ 6 ቀበሌ 13 ክልል የቤ.ቁ 563 ተመዝግቦ የሚገኘው የከሳሾችና የአንደኛ ተከሳሽ የጋራ የውርስ ሀብት ሆኖ እያለ አንደኛ እና ሁለተኛ ከሳሾች ስምምነታቸውን ሳይሰጡ በአንደኛ ተከሳሽ በኩል ከሁለተኛ ተከሳሽ ጋር የመያዣ ውል የተፈጸመው የሕጉን ድንጋጌ ባልተከተለ ሁኔታ ስለሆነ ጥቅምት 1987 ዓ.ም እና ሐምሌ 1987 ዓ.ም የተደረገ የመያዣ ውል ፈራሽ ነው በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

የሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የአሁን አመልካች በውሳኔው ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ አንድ ውል እንዲፈርስ ተዋዋይ ወገን ያልሆኑ ሦስተኛ ወገኖች አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1808(2) እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ ውሉ የማይረጋበት ምክንያት ከቀረበት ጊዜ አንስቶ ከ2 ዓመት በኋላ የውል ይሰረዝልኝ ክስ ሊቀርብ እንደማይችል ጉዳቱ የደረሰበት ሰው አካለመጠን የደረሰ ሰው ከሆነ ክሱን ማቅረብ የሚገባው ውሉ በተደረገ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1810(1) ላይ ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከተራ ቁጥር 1-3 የተጠቀሱት መ/ሰጭዎች ውሉ ሲደረግ ለአቅመ አዳም የደረሱ መሆናቸው ከ4ኛ-7ኛ የተጠቀሱትም መ/ሰጭዎች ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ለአካለመጠን የደረሱ መሆናቸው በመ/ሰጭዎች ያልተካደ በመሆኑ የውል ይሰረዝልኝ ክሱ 2 ዓመት ያለፈው መሆኑን ፍ/ቤቱ ተገንዝቧል፡፡ ስለሆነም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1810(1) መሠረት የውሉ ይሰረዝልኝ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

የሥር ከሳሾች/የአሁን አመልካቾች/ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ የአመልካቾች የውል ይፍረስልኝ ክስ በ2 ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መወሰኑ ለሰበር ቀርቦ መጣራት የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ ይህ ችሎት አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጐ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችንም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አንድ ውል በሚመሰረትበት ጊዜ የችሎታ ወይንም የፈቃድ ጉድለት ያለበት ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ችሎታ አልነበረኝም ወይንም ፈቃዴን በአግባቡ አልሰጠሁም በሚለው ተዋዋይ ወገን ብቻ ጠያቂነት ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል እንደዚሁም ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ለሕግ ወይንም ለሞራል ተቃራኒ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜና የውሉ አጻጻፍ ሥርዓትም ባልተጠበቀ ወቅት ከተዋዋይ ወገኖች መካከል ወይንም በውሉ ጥቅም አለኝ በሚል 3ኛ ወገን ዓማካይነት የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ሲቀርብ ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1808(1) እና (2) ላይ ተመልክቷል፡፡

የውል ይፍረስልኝ ክስ ማቅረቢያ ጊዜውን በተመለከተም ውሉ የማይረጋበት ምክንያት ከቀረበት ጊዜ አንስቶ በ2 ዓመት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ሊታገድ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1810 ላይ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ውሉ ሊፈርስ ይገባል ተብሎ ውሳኔ የተሰጠው የጋራ ባለንብረቶች የሆኑት አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች ፈቃዳቸውን አልሰጡም በሚል ምክንያት ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1810 ላይ የተመለከተው የ2 ዓመት ይርጋ ጊዜ ተፈጻሚነቱ ውሉ የማይረጋበት ምክንያት ቀሪ በሚሆንበት ጊዜ ሲሆን ይህም የሚመለከተው ከአንደኛው ተዋዋይ ወገን ችሎታ ወይንም ፈቃድ ጉድለት ጋር የተያያዘ በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡ ውሉ ከችሎታ ወይንም ከፈቃድ ጋር በተያያዘ ጉድለት አለበት በሚባልበት ጊዜ ይህንኑ መሠረት አድርጎ ክስ የሚያቀርበው ወገን በ2 ዓመት ክሱን ካላቀረበ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1810 መሠረት በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ ውሉ እንዲፈርስላቸው የጠየቁት አንደኛ እና ሁለተኛ አመልካቾች ለውሉ መፍረስ በምክንያትነት የጠቀሱት የጋራ የሆነውን የውርስ ሀብት ለመሸጥም ሆነ በመያዣ ለመስጠት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1266 መሠረት የጋራ ባለሀብቶች ስምምነት አስፈላጊ ሆኖ ሳለ የሥር አንደኛ ተከሳሽ ያለ እኛ ስምምነት የጋራ የውርስ ሀብት የሆነውን ቤት ለሁለተኛ ተከሳሽ/ለአሁን ተጠሪ/ በመያዣነት የሰጠ ስለሆነ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት ነው፡፡ አንደኛ እና ሁለተኛ አመልካቾች ተዋዋይ ወገን ካልሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1808(1) መሠረት ውሉ የችሎታ ወይንም የፈቃድ ጉድለት ያለበት ስለሆነ ሊፈርስ ይገባል በማለት ሊጠይቁ የማይችሉ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1810 ላይ የተመለከተው የ2 ዓመት ይርጋ ጊዜ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት አይኖረውም፡፡

በሌላ በኩልም በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 318 ላይ የተቀመጠውን የይርጋ ጊዜ በተመለከተም አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ በሞግዚቱ ላይ የሚያቀርበውን ክስ አስመልክቶ ተፈጻሚ የሚሆን ሲሆን በዚህ ጉዳይ ግን ውሉ ፈራሽ ነው የተባለው ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ ወጥተዋል በተባሉት አንደኛ እና ሁለተኛ አመልካቾችን አስመልክቶ ስለሆነ ድንጋጌው ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡

እንግዲህ ተጠሪ ያነሳው የይርጋ ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1810 እና በቤተሰብ ሕጉ የሚሸፈን ባይሆንም የጋራ የሆነን ንብረት ለማስተላለፍ ወይንም በዋስትና ለመስጠት የሁሉንም የጋራ ባለንብረቶች ስምምነት ማግኘት እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1266 ላይ የተመለከተ ሲሆን ነገር ግን የጋራ ባለንብረት ከሆኑት መካከል አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች በመያዣ ውሉ ስምምነታቸውን ያልሰጡ ስለሆነ ይህም ውሉ ሕግን የሚጻረር መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ አንድ ውል ሕግን የሚቃረን ነው በሚባልበት ጊዜ እንዲፈርስ ጥያቄ መቅረብ ያለበት በ10 ዓመት ጊዜ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1845 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካቾች ክሱን ቀረቡት ደግሞ በሕጉ ላይ የተቀመጠው የ10 ዓመት ጊዜ ከማለፉ በፊት ስለሆነ አቤቱታቸው በይርጋ የታገደ አይደለም፡፡

ሲጠቃለልም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካቾች ክስ በ2(ሁለት) ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል ያለው ለጉዳዩ አግባብነት በሌለው ድንጋጌ ላይ ተመስርቶ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 65139 በ1/9/2000 ዓ.ም የአመልካቾች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 46909 ሐምሌ 28 2001 ዓ.ም ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348(1) መሠረት ሽረነዋል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በፍሬ ጉዳይ ረገድ ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ መርምሮ የበኩሉን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 49453

ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** አቶ ተፈሪ ማሞ - በሌሉበት

## ፍ ር ድ

ተጠሪ የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ የነበሩ ሲሆን የኤም.ኤስ.ሲ. ትምህርት እንዲከታተሉ ከአመልካች ጋር ባደረጉት ውል አመልካች በትምህርት በሚቆዩበት ጊዜ ደመወዝ፣ የት/ቤት ክፍያ፣ ለምርምር ማካሄጃ የሚፈልጉትን ሊከፍልና ተጠሪ ደግሞ በትምህርት ለቆዩባቸው እያንዳንዱ ወር የሁለት ወራት አገልግሎት ለመስጠት ግዴታ ገብተው ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ በግዴታቸው መሰረት ግልጋሎት ስላልሰጡ በውሉ መሰረት እንዲፈፅሙ ወይም አመልካች ያወጣውን ወጪ ብር 326,092.57 ከነወለዱ እንዲከፍሉ በማለት አመልካች ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ለክሱ መልስ እንዲሰጡ ተጠርተው ስላልቀረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤትም አመልካችና ተጠሪ መጋቢት 19 ቀን 1994 ዓ.ም ባደረጉት ውል አመልካች ለ24 ወራት ደሞዝ እየከፈለ ተጠሪን ለማስተማርና ተጠሪ ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲመለሱ በአመልካች መ/ቤት ለመስራት ግዴታ መግባታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ተጠሪ በውሉ መሰረት እንዲፈፅሙ ማድረጉ የግል ነፃነታቸውን የሚጋፋ በመሆኑ፣ ግራ ቀኙ ባደረጉት ውል ላይ ተጠሪ ግዴታቸውን ባይፈፅሙ አመልካች ያወጣውን ገንዘብ ለመመለስ ግዴታ ስላልገቡና አመልካችም ውል እንዲፈርስ ስላልጠየቀ ገንዘቡን እንዲከፍሉ የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው የነበረ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታው፤ ተጠሪ ወደውና ፈቅደው የፈረሙት ውል የግል ነፃነታቸውን ይነካል የሚል እምነት የለንም፣ በውሉ መሰረት ቢፈፅሙ የግል ነፃነታቸውን ይነካል የሚባል ቢሆን እንኳን ውሉ በአመልካች በኩል ተፈፅሞ ያበቃ በመሆኑና ተጠሪ ግዴታቸውን ስላልተወጡ ውሉ የሚፈርስበት ሁኔታ አይኖርም፣ ውሉን መፈፀም ግዴታቸውን የሚነካ ከሆነ ግዴታቸውን በአይነት ወይም በገንዘብ የመመለስ የውልም ሆነ የህግ ግዴታ አለባቸው በማለት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻር ጠይቋል፡፡ ይህ ችሎትም አመልካች ለተጠሪ ትምህርት ያወጣቸው ወጪዎች ሳይከፈል የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪ እንዲቀርቡ ተጠርተው ስላልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

አመልካች ክስ የመሰረተው ከተጠሪ ጋር ባደረጉት ውል መሰረት አመልካች ግዴታውን ከፈፀመ በኋላ ተጠሪ ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው በውሉ መሰረት እንዲፈፅሙ ካልሆነ የከፈላቸውን ደሞዝና የትምህርት ቤት ወጪዎች እንዲተኩለት ነው፡፡ ተጠሪ አልፈፀሙም የተባለው ትምህርታቸውን ሲጨርሱ ተመልሰው በአመልካች መ/ቤት ግልጋሎት የመስጠት ግዴታቸውን ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው አመልካች አንደኛው የዳኝነት ጥያቄ ተጠሪ በውሉ በገቡት ግዴታ መሰረት በመ/ቤቱ ውስጥ አገልግሎት እንዲሰጡ ነው፡፡ ነገር ግን የስር ፍ/ቤት

እንዳለው ተጠሪ በግድ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረጉ የግል ነፃነታቸውን የሚነካ በመሆኑና እንዲህ ባለ ጊዜ ደግሞ ውሉ በግድ እንዲፈፀም ማድረግ የተከለከለ በመሆኑ (የፍ/ብ/ህ/ቁ 1776 ይመለከቷል) ውሉ በግድ እንዲፈፀም የቀረበው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

በአማራጭ የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ስንመለከት ተጠሪ በውሉ መሰረት ለመፈፀም ካልፈቀዱ ተጠሪ በትምህርት ላይ በቆዩበት ወቅት አመልካች ለተጠሪ የከፈለው ደሞዝና የትምህርት ቤት ወጪዎች እንዲተካለት የሚጠይቅ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ይህን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በግራ ቀኙ በተደረገው ውል ተጠሪ ግልጋሎት ባይሰጡ አመልካች ያወጣውን ወጪ ለመተካት ግልፅ ግዴታ አልገቡም በማለት ነው፡፡ ግራ ቀኙ ካደረጉት ውል አመልካች ተጠሪ በትምህርት በሚቆዩበት ጊዜ ደሞዛቸውንና ሌሎች ከትምህርቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ወጪዎች ለመሸፈን ተጠሪ ደግሞ ትምህርታቸውን ጨርሰው ሲመለሱ አመልካች ድርጅት ውስጥ ለማገልገል ግዴታ መግባታቸውን የስር ፍ/ቤት  አረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ትምህርታቸውን ተምረው የጨረሱ በመሆኑ አመልካች ግዴታውን ፈፅሟል፡፡ ተጠሪ ግን በእርሳቸው በኩል የሚፈለገውን ግዴታ አልፈፀሙም፡፡ ተዋዋይ  ወገን የውሉን ግዴታ ያልፈፀመ ከሆነ ሌላው ወገን ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰበት ጉዳት ካለ የጉዳት ኪሳራ እንዲከፈለው ለመጠየቅ እንደሚችል ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1771(2) እና 1790(1) መረዳት ይቻላል፡፡ ይህን ነጥብ በተመለከተ ይህ የሰበር ችሎት በመ/ቁ 29169፣ 29170 እና በሌሎችም መዝገቦች ላይ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪ በውሉ መሰረት ባለመፈፀማቸው ኪሳራ እንዲከፈለው መጠየቁ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ኪሳራ ሊከፈለው ይገባል የሚባል ከሆነ የኪሳራው መጠን ምን ያህል ሊሆን ይገባል የሚለው በቀጣይነት ሊታይ ይገባዋል፡፡ ተዋዋይ ወገን ግዴታውን ሳይፈፅም ቀርቶ በሌላው ወገን ላይ ጉዳት ደርሶ ከሆነ የኪሳራው ልክ ከውል ውጪ ስለሚደርስ ኃላፊነት በሚመለከተው ድንጋጌዎች መሰረት ሊወሰን እንደሚገባ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1790(2) ያመለክታል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች ሊካስ የሚገባው ከደረሰበት ጉዳት ጋር ተመዛዛኝ የሆነ ኪሳራ እንደሆነ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 2090(1) እና 2091 መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪ በትምህርት ላይ እያሉ ምን ያህል ደመወዝ እንደከፈላቸው እንዲሁም ከትምህርቱ ጋር ተያያዥነት ላላቸው ጉዳዮች ምን ያህል ወጪ እንዳወጣ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ነገር ስለመኖሩ መዝገቡ አያሳይም፡፡ የኪሳራውን ልክ ለመወሰን ደግሞ እነዚህ ነገሮች ሊረጋገጡ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት ተጠሪ ትምህርቱን ከተከታተሉ በኋላ በራሳቸው በኩል ያለውን የውል ግዴታ ባለመፈፀማቸው አመልካች ላይ ለደረሰው ጉዳት ኪሳራ ሊከፍሉ ሲገባ ወጪውን ለመተካት በውሉ ላይ በግልፅ አልተስማሙም በሚል ጥያቄው ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 34503 ህዳር 08 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 75952 ሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በትምህርት ላይ በቆዩበት ጊዜ አመልካች ያወጣውን ወጪ ተጠሪ የመክፈል ግዴታ አለባቸው ብለናል፡፡
3. አመልካች ተጠሪ በትምህርት ላይ በቆዩበት ጊዜ ያወጣውን ወጪ ለማስረዳት ያቀረበውን ማስረጃ መሰረት አድርጎ በማጣራት የኪሳራውን መጠን እንዲወስን ጉዳዩን ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ያወጣውን ወጪ አመልካች ራሱ ይቻል፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 49326

ሰኔ 28 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ እታፈራሁ ኃ/ማርያም - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** 1. መምህር በቀለ ታችበሌ
2. መምህር አዜብ ታደሰ } የቀረበ የለም

**ፍ ር ድ**

ገዳዩ ተጠሪዎች የሸጡላቸው ቤት በሚገኝበት ቦታ ላይ ተጨማሪ ግንባታ ያከናወኑ ቢሆንም ተጠሪዎቹ ስም ስላላዛወሩላቸው ለቤቱ መግዣ የከፈሉት ገንዘብ እንዲመለስላቸውና በተጨማሪ ለሰሩት ቤት ግምቱ እንዲከፈላቸው ጠይቀው ፍ/ቤቱ ተጠሪዎች የሽያጩን ገንዘብ እንዲከፍሉ ሲወስን አመልካች ተጨማሪ ሰራሁ ያሉትን ቤት ግምት ክፍያ ውድቅ በማድረግ በሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተጠሪዎች በድሬደዋ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ ካላቸው ይዞታ ላይ ቀንሰው ከሸጡላቸው እና ብር 29,000(ሃያ ዘጠኝ ሺህ) ከከፈሏቸው በኋላም ስመ-ርስቱን ለማዛወር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የወሰዱትን ገንዘብ እንዲመልሱ በይዞታው ላይ ብር 80,000(ሰማኒያ ሺህ) የሚያወጣ ቪላ ቤት ስለሰሩ ይህንኑ ገንዘብ እንዲመልሱላቸውና በአደራ ያስቀመጡት እቃ ዋጋ እንዲከፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው የሽያጭ ውል ማድረጋቸውን ሳይክዱ ስመ-ርስቱን ለማዛወር ፈቀደኛ ስለሆኑ የሽያጩን ገንዘብ የሚመለሱበት ምክንያት የሌለ መሆኑንና አመልካች በረቂቅ የሽያጭ ውሉ ካልተስማሙ የሰሩትን ቤት አፍርሰው ከሚሄዱ በቀር የቤቱን ግምት የሚከፍሉበት ምክንያት የሌለ መሆኑን በተጨማሪም በአደራ የተረከቡት ንብረት አለመኖሩን በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የቤት ሽያጭ ውሉ ህጉ በሚጠይቀው መሰረት በውል አዋዋይ ፊት ወይም በዳኛ ፊት ስላልተደረገ ረቂቅ ቢሆንም ይህንን መነሻ በማድረግ አመልካች ብር 29,000(ሃያ ዘጠኝ ሺህ) ለተጠሪዎች ስለከፈሉ ተጠሪዎች ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍሉ በቦታው ላይ አመልካች ሰራሁ የሚሉትን ቤት ስለከፈሉ ተጠሪዎች ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍሉ በቦታው ላይ አመልካች ሰራሁ የሚሉትን ቤት በተመለከተ ምንም እንኳን በቦታው ላይ አመልካች ቤት መስራታቸውን ተጠሪዎች ያልካዱ ቢሆንም አመልካች የገለፁትን ያህል ገንዘብ ለማውጣታቸው ያቀረቡት ማስረጃ ስለሌለ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም አመልካች ለተጠሪዎች በአደራ የሰጡት ንብረት ስለመኖሩ በማስረጃ ስላላስረዱ በዚህ ረገድ የቀረበው ክስም ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቶባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው አመልካች በይዞታው ላይ ቤት ስለመስራታቸው ተጠሪዎች ስላመኑ ግንባታው በባለሙያ ተገምቶ እንዲቀርብ ማድረግ ወይም ቢያንስ ተጠሪዎች ያወጣል ያሉትን ግምት እንኳን እንዲከፈል ማድረግ ሲችል መታለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ችሎቱም ተጠሪዎች አመልካች ለቤት መስሪያ ያወጣችውን የተወሰነውን እንከፍላለን እያሉ የስር ፍ/ቤት ጥያቄውን ውድቅ የማድረጉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኝ ቀርበው የቃል ክርክራቸው ተሰምቷል፡፡ ተጠሪዎች አመልካች ቤት መስራታቸውን ሳይክዱ በመጠኑ ላይ ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ክስ የመሰረቱት ከተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ሊፈፀም ባለመቻሉ በሽያጩ ውል ምክንያት የከፈሉት ገንዘብ እንዲሁም ቤቱን ገዝቸዋለሁ በሚል ሃሳብ በይዞታው ላይ የሰሩት ተጨማሪ ቤት ግምት እንዲከፈላቸው ነው፡፡ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስ በሽያጩ ውል መሰረት ለመፈፀም ፈቃደኛ በመሆናቸው ገንዘቡን ሊመልሱ እንደማይገባ ገልፀዋል፡፡ ምንም እንኳን አመልካች ክስ ሲመሰርቱ ውሉ ይፍረስልን በሚል በግልፅ ያስቀመጡት ነገር ባይኖርም የክሱ ይዘት ሲታይ ውሉ ፈርሶ ወደነበርንበት እንድመለስ የሚል ጥያቄ ያዘለ ነው፡፡ ተጠሪዎችም የሚከራከሩት በውሉ መሰረት ለመፈፀም ፈቃደኛ በመሆናቸው ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ለክርክር ምክንያት የሆነው የሽያጭ ውል ህጉ የሚጠይቀውን የአፃፃፍ ፎርምን የተከተለ አለመሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ በህጉ የተመለከተውን የአፃፃፍ ፎርም አለመከተልም ውሉን ለማፍረስ በቂ ምክንያት እንደሚሆን በፍ/ብ/ህ/ቁ 1808(2) መገንዘብ ይቻላል፡፡ ውሉ መፍረሱ የሚያስከትለው ውጤትም ተዋዋዮቹን በተቻለ መጠን ውለታው ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ መመለስ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት በውሳኔ ላይ አመልካች የውል ይፍረስልኝ ክስ አላቀረቡም በማለት ቢተችም ከፍ ሲል እንደተመለከተው የአመልካች ክስ ይዘት ይኸው ሲሆን ፍ/ቤቱም ቢሆን ውሉ የህጉን መስፈርት ያላሟላ በመሆኑ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ሊመለሱ እንደሚገባ ተቀብሏል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪዎች በሽያጩ ውል ምክንያት የወሰዱትን ገንዘብ እንዲመልሱ ወስኗል፡፡ ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት የሚመለሱት ተጠሪዎች የሽያጩን ገንዘብ እንዲከፍሉና አመልካች ቤቱን እንዲያስረክቡ በማድረግ ብቻ አይደለም፡፡ አመልካች ተጨማሪ ቤት ሰርቻለሁ በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎችም አመልካች ቤት መስራታቸውን አልካዱም፡፡ ክርክራቸው ሊከፍሉ በሚገባቸው የቤት ግምት መጠን ላይ ነው፡፡ ተጠሪዎች ፍ/ብ/ህ/ቁ 1179 እና 1180 መሰረት አመልካች በይዞታው ላይ ለገነቡት ቤት ሊከፍሉ የሚገባው የቤቱን ግምት ¼ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ እነዚህ የህጉ ድንጋጌዎች ባለይዞታ ሳይቃወም በይዞታው ላይ የተሰራውን ግንባታ ለማስለቀቅ ስለሚችልበት ሁኔታ የሚናገሩ ናቸው፡፡ አመልካች ግን ግንባታውን የሰሩት በዚህ አይነት ሁኔታ ሳይሆን በግራ ቀኙ በተደረገው የሽያጭ ውል መሰረት ቤቱን ገዝቻለሁ፣ የቤቱ ባለቤት ሆኛለሁ በሚል እምነት ነው፡፡ ምንም እንኳን ውሉ በህግ የተደነገገውን የአፃፃፍ ስርዓት ባለመከተሉ ፈራሽ ቢሆንም ውሉ በመፍረሱ ወይም በመሰረዙ ምክንያት ንብረት የመመለስ ግዴታ ያለበት ሰው ንብረቱን ለውጦ ወይም በዚሁ ላይ ወጪ አውጥቶ ከሆነ ባወጣው ወጪ መጠን ሊጠይቅ እንደሚገባ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1818 ያመለክታል፡፡ ስለሆነም አመልካች ቤቱን እንዲለቁ ሲደረግ ተጠሪዎች ሊከፍሉ የሚገባው አመልካች በይዞታው ላይ የሰሩት ቤት የሚያወጣውን ዋጋ በሙሉ እንጂ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1179 እና 1180 መሰረት አይደለም፡፡ ተጠሪዎች በዚህ የሰበር ችሎት አመልካች ቤቱን ያለ ግንባታ ፈቃድ የሰሩት በመሆኑ የቤቱን ግምት ልንከፍል አይገባም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ይህ ክርክር በስር ፍ/ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል የስር ፍ/ቤት አመልካች ቤት ለመስራታቸው በተጠሪዎችም መታመኑን ተቀብሏል፡፡ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ቤቱን ለመስራት ብር 80,000(ሰማኒያ ሺህ) ለመውጣቱ አመልካች ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ ነገር ግን ቤት መስራቱ እስካልተካደ ድረስ የቤቱን ዋጋ ግምት ለማወቅ ምትክ ዳኛ ሊሾም የሚችል መሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 132 ስር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤት ግምቱ በባለሙያ ተገምቶ እንዲቀርብ ማድረግ ሲችል አመልካች አላስረዱም በሚል ብቻ ማለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 25476 መጋቢት 9 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 04566 ሐምሌ 11 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የሰሩትን ቤት ዋጋ ግምት ተጠሪዎች የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡ የስር ፍ/ቤት ቤቱን በባለሙያ አስገምቶ ግምቱን ካጣራ በኋላ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ.42700

ሀምሌ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት

- ነ/ፈጅ አቶ መላኩ መኮንን ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ወ/ሮ መርከቧ ሽጉጤ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ የህግ ትርጉም ስህተት ያለበት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች በአጭር ሥርዓት እንዲታይለት ባቀረበው ማመልከቻ ከተጠሪ ጋር እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 1978 ዓ.ም የትራንዚት አገልግሎት የሰጠና የደንበኝነት ውል ያለው መሆኑን ገልፆ አመልካችና ተጠሪ ሂሳብ ተሣሥበው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 1978 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2004 በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1970 ዓ.ም እስከ ሰኔ 23 ቀን 1996 ዓ.ም አመልካች ለተጠሪ ለሰጠው አገልግሎት ያልተከፈለ ብር 7,955,271.42(ሰባት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሣ አምስት ሺ ሁለት መቶ ሰባ አንድ ብር ከአርባ ሁለት ሣንቲም) ያለ መሆኑን በማረጋገጥ ተጠሪ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 23-09-99 እና ግንቦት 28 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፉ ሰነዶችን ፈርሟል፡፡ ስለዚህ ገንዘቡን እንዲከፍል በማለት ክስ አቅርቧል ተጠሪ በይርጋ ጊዜ ያለውን ዕዳ አመልካች በአጭር ሥርዓት ታይቶ እንዲወሰንለት የጠየቀ በመሆኑ መከላከያ እንዲያቀርብ ይፈቀድልኝ በማለት ጠይቋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበው ብቁ መከላከያ አይደለም በማለት ውድቅ አድርጎ ተጠሪ አመልካች በክሱ የጠየቀውን ገንዘብ እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካች አስራስድስት ዓመት ካለፈ በኋላ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈለው የጠየቁ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ አመልካች ለሰበር ባቀረበው አቤቱታ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሣኔ የሰጠው የህግ ትርጉም በተከራካሪ ያልቀረበና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1846 ድንጋጌ ያላገናዘበ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ የረዥም ጊዜ ደንበኞች ቢሆንም በየወቅቱ ሂሳባቸው እያጣሩ የሚዘጉ አልነበረም፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የከፈለው የአገልግሎት ዋጋና ያልከፈለው ሂሳብ ተጣርቶ የታወቀው እንደ ኤ.አ 23-9-99 በጋራ ሒሳቡን በማስታረቅ በተሠራው ሥራ ነው፡፡ አመልካች ክፍያውን ለመጠየቅ የሚችለው ሒሳቡ ተጣርቶ የሁለቱ ወገኖች ሂሳብ ለማስታረቅ ሥራ ከተሠራና ሒሳቡ ከተለየ በኋላ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አገልግሎት የተሰጠበትን ዓመት መነሻ በማድረግ ይርጋው አልፏል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በይግባኝ ችሎት አተረጓጎም የአስር ዓመት ይርጋ ያላለፈበትን እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 23-9-89 እስከ 23-9-99 ያለውን ሒሳብ አላግባብ በይርጋ ይቋረጣል በማለት መወሰኑ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ የይርጋ ጊዜው መታሰብ ያለበት አመልካች አገልግሎቱን ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ መሆን አለበት፡፡ አመልካች የትራንዚት ሥራውን ጨርሶ ንብረቱን ለተጠሪ ካስረከበበት ወይም በውሉ በእሱ በኩል ያለውን ግዴታ ከተወጣበት ቀን ጀምሮ ሒሳቡን ከመጠየቅ የሚከለክለው ነገር የለም፡፡ የይርጋ መከራከሪያ ክሱን ለመከላከል ጠቃሚ ነጥብ መሆን አንስተን የከፍተኛ ፍርድ ቤትን ጠይቀናል ስለዚህ በተከራካሪዎች ያልተነሣ ነጥብ ይግባኝ ሰሚው በጭብጥነት በመያዝ የሰጠው ውሣኔ የለም፡፡ ስለዚህ የአመልካች ማስረጃዎች አመልካች ክፍያ የጠየቀው ክስ ካለፈ በኋላ መሆኑን የሚያስረዱ በመሆኑ የሰበር አቤቱታው የህግ መሠረት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በፅሑፍ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የአመልካች ክስ የይርጋ የጊዜ ገደብ ያለፈበት በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ የይርጋ የጊዜ ገደቡ መቆጠር ያለበት ከመቼ ጀምሮ ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስና በሁለተኛ ደረጃ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን ክስ ሙሉ በሙሉ በይርጋ ቀሪ ነው ብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆኑን መመርመር ያስፈልጋል፡፡

1. የይርጋው ጊዜ መቆጠር ያለበት ከመቼ ጀምሮ ነው የሚለውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረንን ሂሳብ በጋራ አስልተን ሐሳባችንን ያስታረቅነው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 23-9-1999 ዓ.ም በመሆኑና ሒሳቡ ከመስማማቱ በፊት የአገልግሎት ዋጋ መጠየቅ ስለማንችል ይርጋው ጊዜ መስላት ያለበት እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 23-9-1999 ጀምሮ መሆን አለበት በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1846"ን" በመጥቀስ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የትራንዚት ሥራ ሰርቶ ዕቃውን ካስረከበበት ቀን ጀምሮ ሒሳቡን መጠየቅ ስለሚችልና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1846 ይህንንም የሚደነግግ በመሆኑ ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው አመልካች አገልግሎቱን ከሰጡት ዕቃውን ካስረከበበት ጊዜ ጀምሮ መሆን አለበት በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1846 ድንጋጌ የየራሳቸውን ትርጉም በመስጠት ነው፡፡ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1846 "የይርጋው መነሻ ጊዜ" በሚል ርዕስ "የይርጋው ቀን መቆጠር የሚጀምረው ግዴታን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ወይም ውሉ የሚሰጠው መብት ከሚሠራበት ቀን ጀምሮ ነው" በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚህን ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ አመልካችና ተጠሪ ካላቸው ግንኙነት አንፃር ስንመለከተው አመልካች ተጠሪ ከውጭ አገር የሚያስገባቸውን ዕቃዎች አስፈላጊ የሆኑ የወደብና የጉምሩክ ፎርማሊቲዎች በማሟላት ዕቃውን ለተጠሪ እንዲረከብ የማድረግ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑና ተጠሪ አመልካች ለሰጠው የትራንዚት ግልጋሎት ዋጋ የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ግራቀኙ አልተካካዱም፡፡ አመልካች አስፈላጊ የሆኑ የወደብ አስተዳደራዊ ፎርማሊቲዎችና የጉምሩክ ፎርማሊቲዎች በማሟላት አንድ ዕቃ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ለሰጠው አገልግሎት ወዲያውኑ ተጠሪ ክፍያ እንዲፈፅምለት የመጠየቅና ተጠሪ እንቢተኛ ቢሆን በፍርድ ከስሶ የአገልግሎት ዋጋውን ከመቀበል የሚያግደው ነገር የለም፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የትራንዚት የአገልግሎት ዋጋ የሚከፍለው በየወቅቱ የነበራቸው ሒሳብ በጋራ ተሰርቶ የአመልካችና የተጠሪ ሒሳብ መስማሚያ ሰነድ ሲቀርብ ስለመሆኑ አመልካችና ተጠሪ የተስማሙበት ልዩ የውል ስምምነት ያላቸው ስለመሆኑ አመልካች ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የዚህ አይነት ግልፅ የውል ስምምነት ከሌለ አመልካች የተጠሪን ዕቃ ለማስገባት አስፈላጊ የሆኑ የትራንዚት አገልግሎት ሰጥቶ ዕቃው ወደ አገር ውስጥ ካስገባና ተጠሪ እንዲረከብ ካደረገበት ቀን ጀምሮ ክፍያ የመጠየቅ መብት አለው፡፡ ተጠሪ ለሰጠው አገልግሎት ክፍያ የመጠየቅ መብቱን አገልግሎቱን ከሰጠ በኋላ በሚቀጥለው ቀን እንዳይሠራበት የሚከለክለው ግልፅ የሆነ የውል ቃል ወይም የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ለተጠሪ ለሰጠው እያንዳንዱ የትራንዚት አገልግሎት አገልግሎቱን ከሰጠበት ቀን ጀምሮ የአገልግሎት ክፍያ ተጠሪ እንዲከፍል መጠየቅ የሚቻልና በመብቱ ሊሠራበት የሚቻል በመሆኑ አመልካች የአገልግሎት ክፍያ ለመጠየቅ የሚችለው ሂሳቡ በጋራ ተሰርቶ ከታረቀበት ቀን ጀምሮ ነው ተብሎ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1846 ይተርጎምልኝ በማለት ያቀረበው ክርክር የፍትሐብሔር

ሕግ ቁጥር 1846 ድንጋጌ ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና የህግ ድጋፍ የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም የአስር ዓመቱ የይርጋ የጊዜ ገደብ መቆጠር ያለበት አመልካች ለተጠሪ የትራንዚት አገልግሎቱን ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ መሆን ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. አመልካች ተጠሪ ለሰጠው የትራንዚት አገልግሎት ክፍያ እንዲፈፅምለት የጠየቀው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 1978 ዓ.ም እስከ ጁን 30 ቀን 2004 ያለውን ሒሳብ ነው፡፡ ይህም የሚያሣየው አመልካች በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ1970 ዓ.ም እስከ ሰኔ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ በሰጠው አገልግሎት ክፍያ ተጠሪ እንዲከፍለው የጠየቀ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች ለተጠሪ የሰጠው የትራንዚት አገልግሎት ክፍያ እንዲከፍለው መጠየቅ የሚቻለው አገልግሎቱ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በአስር ዓመት ውስጥ መሆን ያለበት መሆኑ ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1845 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር የይርጋው ጊዜ ሲቆጠር አመልካች በክሱ ከጠየቀው የአገልግሎት ክፍያ ውስጥ አስር ዓመት ካለፈባቸው በኋላ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ህዳር 12 ቀን 2000 ክስ የቀረበባቸው እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር 1970 ዓ.ም እስከ ህዳር 11 ቀን 1990 ዓ.ም ለሰጠው አገልግሎት የጠየቀው ሒሳብ ነው፡፡ አመልካች በአጭር ሥነ- ሥርዓት ክስ ያቀረበው ህዳር 12 ቀን 2000 ዓ.ም መሆኑን የከፍተኛው ፍርድ ቤት በውሣኔው ገልጿል፡፡ ስለሆነም ከህዳር 12 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ተጠሪ ክፍያ እንዲፈፅምለት ያቀረበው ክስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 የተደነገገው የአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ገደብ አላለፈበትም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ከህዳር 12 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ለሰጠው አገልግሎት ተጠሪ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል በመጠየቅ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ በከፊል ትክክል ሲሆን በከፊል መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላገኘነው በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት በማሻሻል ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ህዳር 11 ቀን 1990 ዓ.ም ለሰጠው የትራንዚት አገልግሎት ተጠሪ ክፍያ እንዲፈፅም በፍርድ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ክስ በአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ገደብ ይታገዳል ብለናል፡፡
3. አመልካች በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከህዳር 12 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ለሰጠው የትራንዚት አገልግሎት ተጠሪ ክፍያ እንዲፈፅም በፍርድ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም ብለናል፡፡
4. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር አመልካች ከህዳር 12 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ለሰጠው የትራንዚት አገልግሎት ተጠሪ ሊከፍለኝ ይገባል የሚለውን የአገልግሎት ክፍያ ለይቶ እንዲያቀርብ በማድረግና የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሠረት መልሰንለታል ይፃፍ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ
   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 46019

ሐምሌ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የአቶ ደሳለው ፋንታ ወራሾች - እነ ሙሉጌታ ደሳለው ጠበቃ ግሩም አየለ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አየለ ደበላ - ጠበቃ ኤሊያስ ተ/ብርሃን ቀረቡ

መዝገቡን መረምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በእቁብ ገንዘብ የመክፈያ ጊዜ ጋር በተያያዘ እዳው እንደተከፈለ ሊቆጠር የሚችልበትን የሕግ አግባብና ትርጉም የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ የካቲት 08 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ የአሁኑ አመልካቾች አውራሽ በተጠሪ የሚሰበሰበው እቁብ በአባልነት ተመዝግበው ዋስ ቆጥረው ብር 650,000.00(ስድስት መቶ ሃምሳ ሺህ) መውሰዳቸውን፣ተከሳሽ በተመዘገቡበት እጣ እቁብ ከተጀመረበት ከሕዳር 03 ቀን 1992 ዓ.ም ድረስ እስከ ጥቅምት 02 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ 28 ክፍያዎችን ከከፈሉ በኂላ ኀዳር 7 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ እስከ እቁቡ ማለቂያ እለት ድረስ መክፈል የሚገባቸውን 29 ክፍያዎችን ሳይከፍሉ መቅረታቸው በመግለጽ ተከሳሽ ከእቁቡ የሚደርሳቸውን ገንዘብ ከወሰዱ በኂላ መክፈል ሲገባቸው ያልከፈሉትንና ባለመክፈላቸው በእቁቡ ስምምነት መሰረት ሊከፈል የሚገደዱበትን በቀን የሚታሰብ ተጭማሪ ክፍያ በድምር የሆነውን ብር 342,600.00 (ሦስት መቶ አርባ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ) ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች ቀርበው በሰጡት መከላከያ መልስ የተጠሪ ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ስር በተመለከተው የክፍያ ግምት መሰረት ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከተመለከተ በኂላ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ድንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ የከሳሽን ክስ ውድቅ አድርጓአል፡፡ ከዚህም በኂላ ተጠሪ ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ ለእቁብ ገንዘብ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮ ጉዳዩን ለስር ፍ/ቤት መልሶለታል፡፡ ጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ያሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ግንቦት 14 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤቶች የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/"ን" ተደርጉ የቀረበውን ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው ያላግባብ መሆኑን፣ድንጋጌው ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677/1/ ድንጋጌ አንፃር ሲታይ ለእቁብ ገንዘብ አግባብነት ያለው መሆኑን በመዘርዘር ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጐላቸው ቀርበው ጥር 25 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024/ረ/ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣የአመልካቾች አውራሽ የእቁብ ገንዘቡን ያልተከፈሉ በመሆኑ ክርክራቸው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልፀው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት የተከራከሩ ስለመሆኑ የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካቾች ጠበቃ የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በተጠሪ እና በአመልካቾች አውራሽ መካከል ያለው ግንኙነት የእቁብ ገንዘብን የሚመለከት መሆኑን፣የአመልካቾች አውራሽ ተጠሪ በሚሰበስቡት እቁብ ውስጥ አባል ሆነው እጣው ደርሷቸው ገንዘቡን በመውሰድ 28 እጣዎችን ከከፈሉ በኋላ 29 እጣዎች ሲቀሩ መክፈላቸውን ማቋረጣቸውን ገልጸው ተጠሪ ክስ መመስረታቸውን፣የእቁቡን ገንዘብ የሚከፈልበት ጊዜም የተቆረጠ መሆኑን ነው፡፡ በዚህ ችሎት አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የእቁብ እዳው ክፍያ ጥያቄ በሁለት አመት ጊዜ ማለፍ እንደተከፈለ ሊቆጠር ይገባል ማለት ያቀረብነውን ክርክር ያለፈው ያላግባብ ነው በሚል ነው፡፡

ዋናውና የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ጉዳይ፡- የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ድንጋጌ ለእቁብ ገንዘብ እግባብነት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይቻል ዘንድ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ድንጋጌን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 በጠቅላላው ሲታይ በሕግ የሕሊና ግምት የሚሸፈን የፍሬ ነገር ነጥብን (legal presumptions) የሚመለከት ሲሆን ዓይነቱም ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2025 እና 2026 ድንጋጌዎች ጋር ተዛምዶ ሲታይ ውስን የሆነ የማስተባበያ ማስረጃ የሚቀርብበት (not freely rebuttable or rebuttable but in limited way) የሕግ የሕሊና ግምት ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር የተለያዩ የክፍያ አይነቶች የሚዘረዝር ሆኖ 2024 በጠቅላላው ሲታይ ግን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎች(እዳዎች) በዚሁ የሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሳይጠየቁ የቀሩ እንደሆኑ ክፍያውን (እዳዎች) የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ወገን የተባለውን ክፍያ (እዳ) እንደከፈለ የሕግ ግምት እንደሚወስድበት ያስገነዝባል፡፡ ድንጋጌው እቁብን ለይቶ አላስቀመጠም፡፡

ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነትና ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ ተብሎ በአመልካቾች የሚጠቀሰውን በስር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ተቀባይነት ያገኘው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 ድንጋጌ በፊደል/ረ/ ስር የተመለከተው ሲሆን ሙሉ ይዘቱም በሚከተለው መልኩ የተቀመጠው ነው፡፡

<u>ቁ. 2024 በሁለት አመት የተወሰነ ጊዜ</u>

እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ የሚቆጠረው፡-

/ረ/ በብድር ለተሰጠ፣ የገንዘብ ወለድና በጠቅላላውም የዓመት ጊዜ ተወስኖለት በየዓመቱ ወይም ከዚህ ባነሰ የጊዜ ውሳኔ ውስጥ ሊከፈል የሚገባው እዳ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዝኛው ቅጂም፡-

<u>Art.2024 presumption of payment after two years</u>

The following debts shall be deemed to have been paid where two years have elapsed since they fell due:

(f) interest on loans and generally any sum payable annually or at shorter periodical interval. በሚል ተቀምጧል፡፡ ከላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ይዘትና እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የድንጋጌው መጀመሪያ ፓራግራፍ የመክፈያ ጊዜያቸው ከደረሰ ጊዜ አንስቶ ሁለት አመት ያለፋቸው እዳዎች(ክፍያዎች) እንደተከፈሉ

ይቆጠራሉ የሚል ሲሆን በተከታይ የተዘረዘሩት ንኡስ ድንጋጌዎች ደግሞ የሚወሰንባቸውን የክፍያ (እዳ) ዓይነቶችን የሚዘረዝር ነው፡፡ በድንጋጌው ፊደል/ረ/ ስር የተመለከተው ሲታይ በብድር የተሰጠ ወይም ለማናቸውም የአከፋፈል ሁኔታ በየአመቱ ወይም ከአመት ባነሰ ጊዜ እየተከፈለ እንዲያልቅ ጊዜ ተቆርጦለት የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ እዳው ከበሰለበት ወይም በየተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ገንዘብ ከሆነ ደግሞ ገንዘቡ ተከፍሎ ማለቅ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ያለፈ እንደሆነ በእነዚህ ክፍያዎች (እዳዎች) ላይ ሊጠየቅ የሚችለው የወለድ ክፍያ እንደተከፈለ የሕግ ግምት የሚወሰድ መሆኑን ያሳያል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ስር የተመለከተው ድንጋጌው ተፈፃሚነት የሚኖረው <u>በብድር ለተሰጠ ገንዘብ ወለድ</u> ላይ ሲሆን ዋናውን የብድር ገንዘብ <u>የማይጨምር</u> መሆኑን የድንጋጌው ይዘትና አቀራረጽ ያስገነዝባል፡፡ ምክንያቱም ድንጋጌው ዋናውን የብድር ገንዘብ የሚጨምር ቢሆን ኖሮ የብድር ገንዘብንና ወለድ በማለት ያስቀምጠው ነበር እንጂ ለብቻው ነጥሎ የብድር ገንዘብ ወለድን በማለት አይጽፈውም ነበር፡፡ ይህ ስለመሆኑም ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 29181 እና የሰ/መ/ቁ. 35758 በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም እቁብ ከመሰረቱ ብድር አይደለም፤የብድር ባህርይም የለውም፡፡ እቁብ ሰዎች ባላቸው አቅም መሰረት ገንዘብ ለማጠራቀም የሚጠቀሙበት ማህበራዊ እሴት ነው፡፡ እቁብ ዋናው ዓላማ አባላቱ የቁጠባ ባህል እዲኖራቸው የሚያደርግ ነው፡፡ በመሆኑም የእቁብ አባል ለሌላው አባል እንደ ተበዳሪ ወይም አንዱ ለሌላው ከወዲሁ ባለገንዘብ ነው ሊባል የሚችልበት የስምምነት አይነት አይደለም፡፡ ምናልባት አባሉ እጣው ደርሶት ከተጠቀመ በኋላ ቀሪውን እጣ ካልከፈለ እንደማንኛውም ደንበኛ እቁቡን ካልከፈለው አባል ላይ ግዴታ የሚጥል ነው የሚል ክርክር ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ይህም ጉዳይ ተቀባይነት የሚኖረው በጠቅላላው ሕጉ የተመለከቱትን ይርጋ ደንቦችን መሰረት አድርጐ ሲቀርብ ሊሆን ይገባል፡፡ የአመልካቾች ጠበቃ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ለጉዳዩ አግባብነት ይኖረዋል በማለት የሚራከሩት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677/1/ ድንጋጌን በማጣቀስ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የጠቅላላ ውል ድንጋጌዎች በአንድ ጉዳይ ተፈፃሚ እንዲሆኑ የሚደረገው ከጉዳዩ ተፈፃሚነት ያላቸው መሆኑ በቅድሚያ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ስር የተመለከቱት ጉዳዮች ተለይተው በተቀመጡበት ሁኔታ ለእቁብ ተፈፃሚ የሚሆንበት የሕግ አተረጓጐም ደንብ የለም፡፡ ሕጉም እቁብ የሚቋቋምበትን ዓላማ የመጠበቅ ሐሳብ ያለው ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ሕግ ሲተረጐምም ሊፈፀም የሚችል ውጤት እንዲኖረው በማድረግ ስለመሆኑም ጠቅላላ የሕግ አተረጓጐም ደንቦች የግድ የሚሉት ነው፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነቱ በብድር ለተሰጠ የገንዘብ ወለድ እንጂ ለዋናው የብድር ገንዘብ አለመሆኑን ከድንጋጌው ይዘትና አቀራረጽ የምንገነዘበው ነጥብ በመሆኑ ለእቁብ ገንዘብ ተፈፃሚ የሚሆንበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ በዚህም ምክንያት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በማለት መወሰናቸው ሕጋዊ እንጂ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተናል፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 64158 በሕዳር 01 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጠቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 42252 የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የእቁብ ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ በይርጋ ደንብ የሚገዛ እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ስር የተመለከተው የሕሊና ግምት የሚሸፈን አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 49900

ሀምሌ 19 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሓጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** 1. ወ/ሮ ሐመልማል ዓለሙ - ከጠበቃ ይነሡ በላይ ጋር ቀረቡ

2. አቶ ዓለሙ አበረቱኝ ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** ወ/ሮ ሀረገወይን ዘለቀ ከጠበቃ አቶ አብይ ደግፌ ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት መስከረም 20 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካቾች ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩን መነሻ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርበው ያለ ፍላጐቴ በተንኮልና በማስገደድ ለአንደኛ አመልካች/አንደኛ ተከሳሽ/ ሚያዝያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም የስጦታ ውል እንድፈፅም ያደረገችኝ በመሆኑ የስጦታ ውሉ እንዲፈርስና አንደኛ ተከሳሽ/ አመልካች/ ምንም አይነት ግንባታ እንዳታከናውን ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካችና በሥር በተከሳሽነት ቀርበው

አመልካች ወደውና ፈቅደው በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ቀርበው ባደረጉት የሥጦታ ውል መሠረት አንደኛ አመልካች ቤት ገንብተው እየኖሩበት የሚገኙ መሆኑን ገልፀው የተጠሪ ጥያቄ ውድቅ እንዲደረግላቸው ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል ያቀረቡት ምስክሮች ሁለተኛው አመልካች ተጠሪ ለአንደኛ አመልካች የስጦታ ውል እንዲፈርሙላት ብቻና ማስፈራራት ይፈፅሙ ነበር ስጦታው ከመደረጉ በፊት ሁለተኛ አመልካችና ተጠሪ ስጦታው መደረግ አለበት የለበትም በሚል ምክንያት ይጨቃጨቁ ነበር በማለት የመሰከሩ መሆኑን መዝግቦ በተጠሪ ሚያዝያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም የተደረገው የስጦታ ውል በማሣሣትና በተንኮል የተደረገና ስህተት ያለበት ስለሆነ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2442/3/ መሠረት የስጦታ ውሉ ፈርሷል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

መስከረም 20 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካቾች አንደኛ አመልካች ብር 600.000 /ስድስት መቶ ሺ ብር/ ያላነሠ ወጭ በማውጣት ተጠሪ ከሁለተኛው አመልካች ጋር በመሆን ከነበራቸው ሰፊ ግቢ ከፋፍለው 261 ካ.ሜ ቦታ ላይ የነበረ ጅምር ቤት በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ቀርበው በሰጧቸው ላይ ትልቅ ቤት ገንብተዋል፡፡ ተጠሪ የስጦታ ውሉን በፈረሙበት ጊዜ መገደድም ሆነ ማታለል ያልተደረገባቸው መሆኑን የተጠሪ ምስክሮች ለፍርድ ቤት አስረድተው እያለ፣ ከህጉ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ሁኔታ የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው የስጦታ ውሉን ሲፈርሙ ተጠሪ በሁለተኛ አመልካች ስለመገደዳቸው የንስሀ አባታቸው መሥክረዋል፡፡ የሁለተኛው አመልካች አድራጎት ባልና ሚስት የጋራ ሀብታቸውን በማስተዳደር በኩል እኩል መብት ያላቸው መሆኑን የሚደነግገውን ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ፣ የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ሰፊ ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካቾች በቃል ክርክር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ለአንደኛ አመልካች ያደረጉት የጅምር ቤት ስጦታ ውል ይፈርሣል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ በዝርዝር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ተጠሪ የህጉን መስፈርት የሚያሟላ የውል ማፍረሻ ምክንያት ያላቸው መሆኑን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል ወይስ አልተወጡም የሚለውን ነጥብ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአንደኛ አመልካች ያደረጉት የስጦታ ውል እንዲፈርስ የወሰነው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2442 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ በመጥቀስ ነው፡፡ በእርግጥ የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች የቀጥታ ንባብ የስጦታ ሰጭው ወራሾች ሰጭው በህይወት ሣለ ስጦታው እንዲፈርስ ያቀረበውን ክስ ለመቀጠል ስለሚችሉበት ሁኔታ የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡ ሆኖም የድንጋጌውን መሠረታዊ ግብ እና አላማ መሠረት በማድረግ ስናገናዝበው ስጦታ ሰጭው በስህተት ወይም በተንኰል የተደረገ ስጦታ እንዲፈርስለት ክስ የማቅረብ መብት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2442 ድንጋጌ በተያዘው ጉዳይ

በቀጥታም ባይሆን በትርጉም ግንኙነት ያለው ቢሆንም የስጦታ ውል ለማፍረስ የሚያስችል " ስህተት" ምን አይነት ስህተት ነው; የስጦታ ውል በተንኮል ተደርጓል ተብሎ የሚፈርሰው ምን ሁኔታዎችን ሲሟላ ነው; የሚሉትን መሠረታዊ ሁኔታዎች የሚደነግግ ባለመሆኑ እነዚህን ነጥቦች ለመረዳት ስለ ጠቅላላ ውል የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ማገናዘብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአንደኛ አመልካች ያደረጉት የጅምር ቤት ስጦታ እንዲፈርስ የወሰነው የስጦታ ውሉ በስህተት የተደረገ መሆኑን በመግለፅ ነው፡፡

አንድ ውል በመዋዋል የደረሰው ስህተት የውል ማፍረሻ የሚሆነው ተዋዋዬቹ አስፈላጊ አቋም ነው ሲሉ በሚቀበሉበት አኳኋን ላይ የተደረገ ስህተት ሲሆንና ውሉ ሲፈፀም በአኳኋኑ በቅን ልቦና አስፈላጊ አቋም በሚሆነው ላይ መሆኑ ሲገመት እንደሆነ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1698 ተደንግጓል፡፡ አንድ ውል በስህተት ምክንያት የሚፈርሰው በተለይ በውሉ ዓይነት ላይ ስህተቱ የደረሰ እንደሆነ ወይም አንደኛው ተዋዋይ ወገን በሰጠው ቃል ስለመሣሣቱ የሚያቀርበው መከራከሪያ ከፍ ያለ አስረጅነት የሚያገኝ ሲሆን እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1699 ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ሚያዝያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ለአንደኛ አመልካች በሰነዶችና ውል ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው ያደረጉት ውል የስጦታ ውል መሆኑን ሣያውቁ በስህተት ያደረጉት ስለመሆኑ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በምስክርነት ቀርበው የሰጡት ቃል እንኳን አያረጋግጥም፡፡ ተጠሪ ለአንደኛ አመልካች የጅምር የቤት ስጦታ እንዲያደርጉ በተደጋጋሚ በሽማግሌዎች ሁለተኛ አመልካች እንዳስጠየቋቸው የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ ተጠሪ የስጦታ ውል ያደረጉ መሆኑን አውቀውና ተገንዝበው ያደረጉትና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1698 እና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1699 ድንጋጌዎች በተደነገገው መሠረት ውሉን

ለማፍረስ የሚያስችል ስህተት የፈፀሙ መሆኑን በማስረጃ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነታቸውን ያልተወጡ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በማስቀረብ ተጠሪና ሌሎች ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል በመመርመር ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ውል በማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ቀርበው የሚያደርጉትን የስጦታ ውል መሆኑንና ስጦታ ተቀባይ አንደኛ አመልካች መሆናቸውን ሙሉ ግንዛቤ ይዘውና በስጦታ የሚሰጡት ጅምር የመኖሪያ ቤት መሆኑን ተረድተው ያደረጉት የስጦታ ውል ለማፍረስ የሚያስችል መሠረታዊ የሆነ ስህተት የፈፀሙ መሆኑን በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1698 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1699 መሠረት ሣያስረዱ

የበታች ፍርድ ቤቶች የስጦታ ውሉ የተፈፀመው በስህተት ስለሆነ ፈራሽ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ የህግ መሠረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአንደኛ አመልካች ያደረጉት የጅምር የመኖሪያ ቤት ስጦታ እንዲፈርስ ሲወስን የጠቀሰው ሌላው ምክንያት የስጦታ ውሉ በተንኮል የተደረገ ነው የሚል ነው፡፡
አንድ ውል በተንኮል የተደረገ ውል ነው በሚል ምክንያት ፈራሽ የሚሆነው ከተዋዋዬቹ አንደኛው ወገን ውሉ እንዲያደርግ ያደረገው በሁለተኛው ተዋዋይ ላይ ተንኮል ባይደርስበት ኖሮ ውል የማያደርግ የነበረ መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1704 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የስጦታ ውል ከአንደኛ አመልካች ጋር እንዲያደርጉ በሽማግሌ የተጠየቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪን ለማስፈረም እውነታውን የመደበቅ ወይም ተጠሪ ዕውነታውን እንዳይረዱ የሚያደርጉ የተንኮል ተግባራት በአንደኛ አመልካች በኩል ስለ መፈፀሙ ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት አቅርበው ያሰሟቸው ምስክሮችም ሆኑ ተጠሪ የሰጡት የምስክርነት ቃል አላስረዱም፡፡ ተጠሪ በአንደኛ አመልካች በፈፀሙት የተንኮል ተግባር ምክንያት በሰነዶችና ውል ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው የስጦታ ውል የፈረሙ ስለመሆኑ የማስረጃነት በማስረዳት የማስረዳት ሽክማቸውን ባልተወጡበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2442 ንዑስ አንቀጽ 3"ን" በመጥቀስ ውሉ በተንኮል የተደረገ ስለሆነ ፈራሽ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ የስጦታ ውል እንዲፈርስላቸው የጠየቁት ተጠሪ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1704 ድንጋጌ መሠረት በተንኮል ውል የተዋዋሉ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የሌለ መሆኑን ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው መደምደሚያ የስጦታ ውሉ መፍረሻ ምክንያት አድርጎ ባይገልፀውም፤ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤትና በሰበር የሚከራከሩት የስጦታ ውሉን የፈረምኩት ባለቤቴ /ሁለተኛው አመልካች/ በፈፀመብኝ ዛቻና ማስፈራራት ምክንያት ነው በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ቀርበው የሰጡት ውሉን በሰነዶችና ውል ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው የፈረሙት ሁለተኛ አመልካች የስጦታ ውሉን ካልፈረምሽ ከዚህ ቤት መኖር አትችይም እያለ ስለአስፈራራኝና ስለዛተብኝ ነው በማለት የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ተጠሪ ውሉን እንዲፈርም የማስገደድና የማስፈራራትና የዛቻ ተግባራትን ተፈፅሞብኛል የሚሉት በስጦታ ተቀባይዋ አንደኛ አመልካች ሳይሆን ከተጠሪ ጋር በስጦታ ሰጪነት ያፈረሙት በሁለተኛ አመልካች ነው፡፡
ሁለተኛ አመልካች የስጦታ ውሉ ተጠቃሚና ስጦታ ተቀባይ ባይሆኑም ተጠሪ የስጦታ ውሉን እንዲፈፅሙ የማስገደድ ተግባር መፈፀማቸው ከተረጋገጠ

የውሉ ማፍረሻ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1707 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም በውሉ በስጦታ ሰጪነት ከተጠሪ ጋር ፈራሚ የነበሩት ሁለተኛ አመልካች ተጠሪ ውሉን እንዲፈርሙ የማስገደድ ተግባር ፈፅመዋል ወይስ ወይም አልፈፀሙም? የሚለው ነጥብ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1706 ድንጋጌዎች አንፃር መመዘን ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አንድ ውል በሀይል ሥራ ወይም በመገደድ የተፈፀመ ነው ተብሎ የሚፈርሰው፤ ተዋዋዩን ራሱን ወይም ወላጆቹን ወይም ተወላጆቹን ወይም ባልን ወይም ሚስትን ከባድና የማይቀር አደጋ በህይወቱ፣ በአካሉ፣ በክብሩ ወይም በንብረቱ እንደሚመጣበት ያሳመነው ሲሆንና ተዋዋዩን ሥጋት ላይ የጣለው ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይችላል፡፡

በህጉ መስፈርት በተዋዋዩ ላይ የሚደርሰው አደጋ ከባድ የማይቀር ነው የሚል እምነት የሚያሣድርና ለስጋት የሚዳርግ መሆኑን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት ውሉ በመገደድ የፈፀምኩት ስለሆነ ሊፈርስልኝ ይገባል በማለት የሚጠይቀው ወገን ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የስጦታ ውሉን የፈረምኩት ሁለተኛ አመልካች ውሉን ካልፈረምሽ እዚህ ቤት እትኖሪም በማለት ስላስፈራራንና ስለዛተብኝ ነው የሚል ምስክርነት ቃል የሰጡ ሲሆን ሌሎችም ምስክሮች ተጠሪ ሁለተኛ አመልካችና ፈፅመውብኛል እያሉ የነገሯቸው መሆኑን የሚመሰክሩ ናቸው፡፡ ሆኖም ዝቅተኛ አደጋ የሚያስከትል መድረሱን እርግጠኛ ያልሆነ ዛቻና ማስፈራራት ተደርጎብኛል በሚል ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ እንደማይቻልና የሀይል ተግባሩ በህይወቱ ወይም በአካሉ

ወይም በንብረቱ ላይ ከባድና የማይቀር አደጋ እንደሚደርስበት የሚያሣምን መሆን እንዳለበት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1706 የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪ በሰነዶችና ውል ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ ለአንደኛ አመልካች የስጦታ ውል ያደረግሁት ሁለተኛው አመልካች ውሉን ካልፈረምሽ እዚች ቤት አትኖሪያትም ብሎ ስለዛተብኝና ስላስፈራራኝ ነው በማለት የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ ተጠሪ ያቀረቡት ጥያቄ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1707 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1706 ድንጋጌ መሠረት ያላደረገና ተቀባይነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ሚያዝያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም በሰነዶችና ውል ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው በውል አዋዋይ ባለሥልጣን ፊት ፈርመው ለአንደኛ አመልካች የጅምር የመኖሪያ ቤት ስጦታ ውል ያደረጉት በፍትሐብሔር ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት በመሣሣት፣ በተንኮል ወይም በመገደዳቸው መሆኑን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነታቸውን አልተወጡም፡፡ ተጠሪ በውል አዋዋይ ፊት የተደረገ ውል ጉድለት ያለበትና የሚፈርስበት በቂ ህጋዊ ምክንያት ያለ መሆኑን በማስረጃ ሣያስረዱና ሣያረጋግጡ የበታች ፍርድ ቤቶች አንድ ውል በስህተት የተደረገ ነው፣ በተንኮል የተፈፀመ ወይም በመገደድ የተፈፀመ ነው ተብሎ የሚፈርሰውም ምን ምን ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ እንደሆነ ከላይ በዘረዘርናቸው የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች የተቀመጠውን መሥፈርት ሣያገናዝቡ የስጦታ ውል በስህተትና በተንኮል የተፈፀመ ስለሆነ እንዲፈርስ በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

ተጠሪ እና ሁለተኛ አመልካች ለአንደኛ አመልካች ሚያዝያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ያደረጉት ጅምር የመኖሪያ ቤት ስጦታ ውል ህጋዊ አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት ያለው ውል ነው ብለናል፡፡

በዚህ ፍርድ ቤት አመልካቾችና ተጠሪ ያወጡትን ውጭ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፍ/ዘ

# አፈፃፀም

የሰ/መ/ቁ. 43888

መጋቢት 23 ቀን 2002ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ፀሐይ ወንድም - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1/ አቶ አያለው መለስ - አልቀረቡም

2/ ወ/ት ፍሬህይወት - ተመስገን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዮን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የውሳኔ አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍልን መነሻ ያደረገ ሲሆን ግራ ቀኙ በአይነት ለመከፋፈል ከስምምነት ለመድረስ አለመቻላቸውን ጠቅሶ በጨረታ ተሸጦ ውጤቱ እንዲቀርብ ሲል የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአፈፃፀም መዝገብ የሰጠውን ትዕዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች በማጽናታቸው አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አመልካች የካቲት 26 ቀን 2001ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የውርስ ሐብቱን ስመሐብት ወደ ስማቸው ለማዞር ያቀረቡትን አቤቱታ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳይሰጥበት ማለፉ እና የቤቱ ዋጋ በባለሙያ ወይም በሽማግሌ ሳይገመት ቤቱ በወር በሚያስገኘው የኪራይ ገቢ መነሻ በጨረታ እንዲሸጥ መደረጉ መብታቸውን እንደሚጎዳ ጠቅሰው ንብረቱን በስምምነት ለመሸጥ ወይም ለማከራየት እንዲችሉ እንዲወሰን አመልክተዋል፡፡

ይህ ችሎትም አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ የስር ፍ/ቤት አፈፃፀሙን የሰራው በተከራከሪ ወገኖች ፈቃድ እና በውሳኔው መሠረት መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪዎችን አስቀርቧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ጥር 25 ቀን 2002ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት መልስ በውሳኔው መሠረት ቤቱን ማስረከቡን ገልጿል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ጥር 3 ቀን 2002ዓ.ም በጽሑፍ በሰጡት መልስ ከአመልካች ጋር ወራሽ መሆናቸውን ጠቅሰው ቤቱን በአይነት ለመከፋፈል አመቺ አለመሆኑን አመልካች እያወቁ ቤቱን ይዞ አፈፃፀሙን ማጓተት ተገቢ አለመሆኑን ጠቅሰው ቤቱ በጨረታ ተሸጦ ገንዘቡን እንዲካፈሉ እንዲወሰን አመልክተዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በዚህ ፍ/ቤት ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በዚህ ፍ/ቤት ምላሽ የሚያሻው ነጥብ ግራ ቀኙ ንብረቱን በስምምነት ለመከፋፈል ያልቻሉ እንደሆነ የጨረታው ሽያጭ መነሻ ዋጋ ተብሎ የተወሰደውን አግባብነት እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከከፍተኛው ፍ/ቤት ትዕዛዝ መረዳት እንደተቻለው የጨረታ መነሻ ዋጋ ተብሎ የተጠቀሰው ብር 16,527.29(አስራ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ሰባት ከሃያ ዘጠኝ ሣንቲም) ቤቱን የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ማከፋፈያ የተከራየበት ግምት መሆኑ ነው፡፡ ይህ ገንዘብ የቤቱ የአመት የኪራይ ዋጋ ስለመሆኑ አመልካች በአቤቱታቸው ገልፀዋል፡፡ ተጠሪዎች ይህ ሐሰት ነው አላሉም፡፡ ይህ ፍሬ ነገር ሲታይ ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ ሲወሰን የቤቱ ዋጋ ተብሎ ሊወሰድ የሚገባው የኪራይ ዋጋ ማለት እንዳልሆነ መረዳት የሚያዳግት አይደለም፡፡ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት ግን የኪራይን ዋጋ ለቤቱ ሽያጭ የጨረታ መነሻ ዋጋ አድርጎ ወስዶታል፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1083 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የውርስ ንብረት ግምት አፈፃፀም ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የንብረቱ ግምት በወራሾች ስምምነት ሊወሰን የሚችል ሲሆን ከስምምነት ካልደረሱ እነሱ በመረጧቸው የሽምግልና ዳኞች አሊያም ፍ/ቤቱ በሚመርጣቸው የሽምግልና ዳኞች ሊገመት እንደሚችል ተጠቅሷል፡፡ ይህም ካልተቻለ በፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1084 መሠረት በባለሙያ እንዲገመት ማድረግ ይገባል፡፡

ይህ ግምት የሚከናወነው የንብረቱን ይዞታ እና የገቢያ ዋጋ ለማመልከት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ፍ/ቤቱ የንብረቱ ግምት ነው ብሎ የኪራይ ዋጋ ግራ ቀኙ የተስማሙበት ነው በማለት ለሽያጭ መነሻ ዋጋ ግምት አድርጎ መውሰድ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም በዚህ ገረድ ፍ/ቤቱ የሰጠው ትዕዛዝ የግራ ቀኙን መብት የሚያጣብብ ከመሆኑ አንፃር እንዲሁም በሕጉ ከተመለከተው አግባብ ውጪ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ስለሆነም ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የምሥራቅ ጎጃም ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 25564 የሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ እና የአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁ 01020 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት የውርስ ንብረት ዋጋ በግራ ቀኙ ስምምነት አሊያም በባለሙያ ተገምቶ እንዲቀርብ በማድረግ የሐራጅ ሽያጭ እንዲደረግና በውጤቱም መሠረት እንዲያስፈጽም መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት ለምሥራቅ ጎጃም ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲመለስ አዝዘናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ውጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

የሰ/መ/ቁ. 39837

ግንቦት 03 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሰመንጉስ አሰፋ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** መ/ርት ምህረት ክበበው - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በጋብቻ ወቅት በግል ለመጣ እዳ ለአፈፃፀም የሚውለውን ንብረት የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በይርጋለም ከተማ የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት የአፈፃፀም ማመልከቻ ነው፡፡ የአፈፃፀም ማመልከቻ ይዘቱም ባጭሩ፡- አመልካች የአሁኑ ተጠሪ ባለቤት በነበሩት በአቶ ፀጋዬ ከበደ ላይ የብድር ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ አቅርበው በዋናው ጉዳይ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ አቶ ፀጋዬ ከበደ የብድር ገንዘቡን ለአሁኑ አመልካች እንዲከፈላቸው የተወሰነ መሆኑን ገልፀው አፈፃፀሙ በተጠሪ ደሞዝ እንዲቀጥልላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት አፈፃፀሙ ቀጥሎ ተጠሪ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጐ ከተጠሪ ደመወዝ 1/3ኛ እየተቆጠረ ለአፈፃፀሙ እንዲውል የሚል የፍርድ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኋላም ተጠሪ እዳውን የማያውቁት መሆኑን ገልፀው በሌሉበት የተሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ እንዲነሳላቸው አመልክተው የስር ፍርድ ቤት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ እዳው የመጣው በተጠሪ ባለቤት በነበሩት ግለሰብ የግል ጉዳይ በመሆኑ በተጠሪ ደመወዝ አፈፃፀሙ ሊቀጥል የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለውም የሚለውን ምክንያት በመያዝ የስር ፍርድ ቤትን

ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ይህ ውሳኔ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚውም ሆነ ሰበር ሰሚው ችሎት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሳኔ ባለመስማማት ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 07 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመወሰኑ ተጠሪ ቀርበው መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ አንድ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ

መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ያስፈረዱት ፍርድ በተጠሪ ደመወዝ ላይ እየተቆጠረ ሊፈፀም አይገባም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ዋናውን ፍርድ ያስፈረዱት በተጠሪ ባለቤት በነበሩት አቶ ፀጋዬ ከበደ ሲሆን እዳውም በግል የመጣ መሆኑ በፍርድ መረጋገጡን ነው፡፡ እንዲሁም አቶ ፀጋዬ ከበደ የግል ንብረት የሌላቸው ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡

በመሰረቱ አንድ ተጋቢ በግሉ ያመጣው እዳ ከሌላኛው ተጋቢ የጋራ ንብረት እንዲከፈል የሚደረገው እዳውን ያመጣው ተጋቢ በግሉ መክፈል ያልቻለ መሆኑ ሲረጋገጥ እና እዳው የመጣው በጋብቻ ወቅት ሆኖ ተጋቢዎቹ እዳው በሚከፈልበት ወቅት የፀና ጋብቻ ውስጥ ያሉ ከሆነ ስለመሆኑ ለውሳኔው መሰረት ከሆነው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግም ሆነ ከተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ (አዋጅ ቁጥር 213/92) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ እዳው በአቶ ፀጋዬ ከበደ በግል የመጣ እና ለቤተሰቡ የጋራ ጥቅም ያልዋለ መሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ በላይ ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ነጥብ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪ ከአቶ ፀጋዬ ጋር እዳው ሲወሰድ ጋብቻ መስርተው ነበር ተብሎ ለጋራ ጥቅም ሳልዋለውና በግልጽ አቶ ፀጋዬ ለግል ጉዳይ ብለው ለተበደሩት ገንዘብ የተጠሪ ደመወዝ የሚቆረጥበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች በአቶ ፀጋዬ የግል ንብረት ላይ አፈፃፀሙን ከሚቀጥሉ በስተቀር በተጠሪ ደመወዝ ላይ አፈፃፀሙን እንዲቀጥሉ የሚደረግበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ በሥነ-ሥርአትም ሆነ በመሰረታዊ ሕግ ረገድ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 08543 ታህሣሥ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመ/ቁ. 21205 ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም፣በሰበር ችሎቱ በመ/ቁጥር 22419 ሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 46143

ሐምሌ 2 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ድልበኔ ራሕመቶ

**ተጠሪዎች፡-** 1. የባህር ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት - ነ/ፈጅ መላኩ መኮንን

2. የአቶ መሐመድ ዑስማን ወራሾች - ሙሣማ መሐመድ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአፈጻጸም ጊዜ የተነሳን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አንደኛ አመልካች የፍርድ ባለመብት ሲሆን የሁለተኛ ተጠሪዎች አውራሽ አቶ መሐመድ ዑስማን ደግሞ የፍርድ ባለዕዳ ነው፡፡ አመልካች ክርክሩ ውስጥ የገባችው የፍርድ ባለመብቱ የአፈጻጸም ትዕዛዝ (በሐራጅ ይሸጥ) ያሰጠበት ቤት የፍርድ ባለዕዳ ንብረት አይደለም፡፡ ቀደም ሲል ኑርሑሴን በርሄ የተባለው ሰው ንብረት የነበረ፤ በኋላም ከዚህ ሰው ወራሾች (እነ ዘይኑ ኑርሑሴን) ላይ የገዛሁት ነው፡፡ በንብረቱ ላይ የተሰጠው የሐራጅ ትዕዛዝ እና እግድ ይነሳልኝ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.418 መሠረት በማለት መቃወሚያ በማቅረብዋ ነው፡፡ መቃወሚያው የቀረበለት ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ የአመልካችን መቃወሚያ በመቀበል የሐራጁ ሽያጭ ቀሪ ሆኖ ቤቱ ለአመልካች ይለቀቅ በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንደኛ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም አመልካች ቤቱን ገዝቻለሁ በማለት ውል ከማቅረብዋ ውጪ ስመሃብቱን በስምዋ አላዛወረችም፡፡ ባለቤት ናት ለማለት የሚያስችል ማስረጃ የላትም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም ብሎአል፡፡ በዚህ መሠረትም በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በውል መገዛት እየታወቀ በስምሽ አልተመዘገበም በሚል ምክንያት መቃወሚያዬ ውድቅ መደረጉ አግባብ አይደለም የሚለውን የአመልካች አቤቱታ ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ክርክሩ በአፈጻጸም ደረጃ ያለን ጉዳይ የሚመለከት ስለመሆኑ ከላይ ተገልጾአል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ቤቱን በአፈጻጸም እንዲያዝለት የጠየቀው የፍርድ ባለዕዳው የአቶ መሐመድ ዑስማን (የሁለተኛ ተጠሪዎች አውራሽ) ንብረት ነው በማለት ነው፡፡ አመልካች ቤቱን ገዛሁት የምትለው ደግሞ ከፍርድ ባለዕዳው ላይ ሳይሆን፣ አቶ ኑርሁሴን በርሄ ከተባለው ሰው ወራሾች ላይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ያቀረበችው መቃወሚያ አንደኛ ተጠሪ ከአቀረበው ክርክር አንፃር ከመታየቱ በፊት በእርግጥ ቤቱ የፍርድ ባለዕዳው ንብረት ለመሆኑስ ተረጋግጦአል ወይ? የሚለውን ነጥብ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በዚህ ረገድ አንድም ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ ሲከራከር የቆየው አመልካች የሽያጭ ውል ከማቅረብ አልፋ የቤቱን ስመሃብት በስምዋ አላዛወረችም በሚለው ነጥብ ላይ ብቻ በመመስረት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ይህን የክርክር አቅጣጫ ተከትለው ነው የወሰኑት፡፡ በበኩላችን እንደምናየው ግን ለሽያጭ የቀረበው /አንደኛ ተጠሪ በአፈጻጸም ያስያዘው/ ቤት በእርግጥም የፍርድ ባለዕዳው ንብረት ለመሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ይህ ከተረጋገጠ በኋላም ነው በአመልካች እና በአንደኛ ተጠሪ መካከል ያለውን ክርክር ማየት የሚገባው፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው አመልካች ቤቱን የገዛችው ከፍርድ ባለ ዕዳ ላይ እንዳልሆነ አላከራከረም፡፡ አንደኛ ተጠሪም ቤቱ የፍርድ ባለዕዳ ንብረት ለመሆኑ ወይም የአቶ ኑርሁሴን በርሄ ንብረት ላለመሆኑ በማስረጃ ሊያስረዳ ቀርቶ በክርክር ደረጃ እንኳን ምንም ያለው ነገር የለም፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክርም የአንደኛ ተጠሪ ነገረ-ፈጅ ተጠይቆ የሰጠው መልስም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ በሁለተኛ ተጠሪነት የቀረቡት የሥር የፍርድ ባለዕዳ ወራሾችም ቤቱ የእነሱ እንዳልሆነ በመግለጽ መልስ ሰጥተዋል፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ስናየው ቤቱ አንደኛ ተጠሪ በሁለ ተኛ ተጠሪ ባስፈረደው ገንዘብ ምክንያት በአፈጻጸም የሚያዝበት የሕግ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 68424 የካቲት 5 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 44935 ሚያዝያ 19 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ የሆነው በአፈጻጸም ሊያዝ አይችልም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

# ወንጀል

የሰ/መ/ቁ. 48850

ታህሣሥ 8 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መሰለ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** 1. አቶ ታረቀኝ ገ/ጊዮርጊስ

2. ካሌብ ጌጣጌጥ ኃ/የተ/የግ/ማህበር } ጠበቃ ፊሊጶስ አይናለም ቀረቡ

3. አቶ ለአከ ፍስሐ

**ተጠሪ፡-** የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - ነ/ፈጂ ሌንሳ ዳንኤል

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ጋር በተያያዘ የቀረበ የወንጀል ክስ ሲሆን ተጠሪ በአመልካቾችና በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ ላይ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረበው የወንጀል ክስ አንደኛ እና ሁለተኛ ተከሳሾች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/1/ እና እንደተሻሻለው አንቀጽ 22/1/ እና 50/ለ//1/ የተመለከተውን በመተላለፍ ሦስተኛ ተከሳሽ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34/1/ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 እና እንደተሻሻለው አንቀጽ 22/1/ እና አንቀጽ 50/ለ/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ አራተኛ ተከሳሽም የተጨማሪ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 55 እና እንደተሻሻለው አንቀጽ 22/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ መጋቢት 26 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ 5፡45 ሰዓት ላይ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ በካሌብ ጌጣጌጥ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ተከሳሾች ቀርበው ክሱን እንዲረዱት ከተደረገ በኂላ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ክሱን እንደማይቃወሙ ገልጸው ድርጊቱን አልፈጸምንም ጥፋተኞችም አይደለንም በማለት ክደው ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የዓ/ሕግ ማስረጃን ሰምቶ ተከሳሾች በክሱ ላይ በተጠቀሰው ጊዜና ሥፍራ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ በካሌብ ጌጣጌጥ ኃ/የተ/የ/ማህበር ድርጅት ውስጥ የአንገት ሐብል ሽያጭ ስለማከናወናቸው የተረጋገጠ ስለሆነ ይከላከሉ በማለት ብይን ሰጥቶ ተከሶሾች መከላከያ ማስረጃቸውን አሰምተዋል፡፡ ከዚያም ተከሳሾች የወንጀሉን

ድርጊት ስለመፈጸማቸው በአቃቤ ሕግ ማስረጃ ተረጋግጦባቸው በመከላከያ ማስረጃቸው ማስተባበል እንዳልቻሉ ፍ/ቤቱ ዘርዝሮ የመከላከያ ምስክሮቻቸውን ቃል ውድቅ ከአደረገ በኋላ ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ ናቸው ካለ በኋላ አንደኛ እና አራተኛ ተከሳሾች እያንዳንዳቸው በአንድ ዓመት እሥራትና በብር 10ሺህ የገንዘብ መቀጫ እንዲቀጡ ሦስተኛ ተከሳሽም በብር 60 ሺህ የገንዘብ መቀጫ እንዲቀጣ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ ግን በተከሰሰበት ወንጀል ኃላፊነት የለበትም በማለት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 149/2/ መሰረት በነፃ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡

ከ1-3 የተጠቀሱት ተከሳሾች የአሁን አመልካቾች በውሳኔው ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በሚል ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካቾች ጥፋተኛ ተብለው የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጐ ግራ ቀኙ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን በአመልካቾች ላይ የተሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ ከሕጉ አኳያ አግባብነቱ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ እንደተቻለው አመልካቾች ፈጽመዋል ተብለው የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት ለማስረዳት አቃቤ ሕግ ሁለት ምስክሮች በፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት አቅርቦ ያሰማ ሲሆን እነዚህም ምስክሮች የሰጡት ቃል ተጠቃሎ ሲታይ መጋቢት 26 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ 5፡45 ሰአት ሲሆን ወደ አንደኛ አመልካች የጌጣጌጥና ወርቅ መሻጫ ድርጅት ሄደን ባለ 18 ካራት የወርቅ የአንገት ሐብል ጠይቀን 5.9 ግራም ወርቅ በብር 2100 ተስማምተን ሐብሉን ከገዛን በኋላ የድርጅቱ የሽያጭ ሰራተኛ የነበረውን ሦስተኛ አመልካችን የቫት ደረሰኝ እንዲሰጠን ስንጠይቀው የቢዝነስ ካርድ ሰጠን ከዚያም ማንነታችንና የመጣንበትን ስንገልጽለት ስልክ በመደወል ደረሰኝ እንዲመጣለት ጠይቆ አንደኛ ተከሳሽ የቫት ደረሰኙን ይዘው ወደ ሱቁ መጥተዋል የሚል ነው፡፡

ማንኛውም በተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ድርጅት የሚያካሂደውን ማንኛውንም ሽያጭ ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ካከናወነ ድርጊቱ ሕገወጥ እንደሆነና እንደሚያስቀጣም የተጨማሪ እሴት ታክስን ባሻሻለው አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 50/ለ/ /1/ ላይ ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም ማንኛውም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ የተመዘገበ ድርጅት ታክስ የሚከፈልበትን ሽያጭ ያከናወነ ሰው ደረሰኝ ለገዢው ወዲያውኑ መስጠት እንዳለበት በዚሁ በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 22/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም የሁለተኛ አመልካች የካሌብ ጌጣጌጥ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሽያጭ ሰራተኛ የሆኑት ሦስተኛ አመልካች ከፍ ብሎ በተጠቀሱት የአዋጁ ድንጋጌዎች መሰረት የወርቅ ሽያጩን ካከናወኑ በኋላ ደረሰኝ ለገዢዎች ወዲያውኑ መስጠት ሲገባቸው ደረሰኙን ወደያውኑ ሳይሰጡ መቅረታቸው በአቃቤ ሕግ ማስረጃ ተረጋግጦባቸው በመከላከያ ማስረጃ ያላስተባበሉ በመሆኑ ጥፋተኛ መባላቸው የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩልም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል (Body corporate) በወንጀል ተጠያቂ ለመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/3/ መሰረት ወንጀል የመፈጸም ሐሳብ(criminal intention) ግዑዝ ከመሆኑ አኳያ እንዲሟላ የሚጠበቅ ሳይሆን ኃላፊነቱ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1/ ላይ እንደተመለከተው ከድርጅቱ ኃላፊዎች ወይንም ከሰራተኞቹ አንዱ የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ ባለመወጣት የድርጅቱን ጥቅም ሕገወጥ በሆነ መንገድ ለማራመድ ተንቀሳቅሰው በሚገኙበት ጊዜ ሊመነጭ ይችላል፡፡ በሁለተኛ አመልካች ድርጅትም የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ በመወጣት ረገድ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው አኳኋን የድርጅቱ ሰራተኛ በሆኑት ሦስተኛ አመልካች ዓማካኝነት የተፈጸመ እንደመሆኑ መጠን በወንጀል ሕግ ቁጥር 34/1/ እና በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/1/ መሰረት ድርጅቱ ጥፋተኛ መባሉ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘም የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆነ ድርጅት አዋጁን በመተላለፍ ጥፋት ፈጽሞ በሚገኝ ጊዜ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በድርጅቱ የተፈጸመውን ጥፋት እንደፈጸመ ተቆጥሮ በአዋጁ የተጣለው ቅጣት ተፈፃሚ እንደሚሆንበት በዚሁ አንቀጽ 56/1/ ሥር የተመለከተ ሲሆን ሥራ አስኪያጁ ከኃላፊነት ነፃ የሚሆነው በንኡስ አንቀጽ /3/ ላይ እንደተመለከተው ጥፋቱ የተፈጸመው ግለሰቡ ሳያውቅ ወይም ሳይስማማበት ሲቀር እንደዚሁም ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያሳይ ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የጥፋቱን መፈጸም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብሎ የሚገመቱ ጥንቃቄዎችን ተገቢውን ትጋትና የአሰራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ወስዶ የተገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

ሆኖም ግን ከጉዳዩ መገንዘብ እንደተቻለው አንደኛ አመልካች እንደ ድርጅቱ ሥራ አስኪያጅነታቸው አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ ሽያጭ በሚከናወንበት ጊዜ ገዢዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ወዲያውኑ እንዲያገኙ የሚያስችል የአሰራር ሥርአት መዘርጋት ሲገባቸው ይህንን በሕግ የተጣለባቸውን ግዴታ ባለማክበር የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኙ ሽያጩ ከተከናወነበት ሱቅ ወደ ሌላ ሱቅ ሁልጊዜ እየተወሰደ የኦዲት ሥራ እንዲሰራ መደረጉ ኦዲት ተደርጐ እስከሚመጣም ሱቁ ያለደረሰኝ እንዲቆይ ግድ ስለሚያደርገው የኦዲት ሥራው በዚያው ሱቅ ደረሰኙ ሳይወሰድ እንዲከናወን ማድረግ ከአንድ ጠንቃቃ ሥራ አስኪያጅ የሚጠበቅ ተግባር እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኙ ወደ ሌላ ሱቅ እንዲሄድ ማድረግ ከውጤት አኳያ ያለደረሰኝ ሽያጭ ለማካሄድ እንደመወሰን የሚቆጠርና የማያመች አሰራርን በመከተል ሕጉ የታለመለትና ዓላማና ግብ እንዳያገኝ የሚያበቃ ነው፡፡

በመሆኑም አንደኛ አመልካች እንደ ሥራ አስኪያጅነታቸው በሕግ የተጣለበባቸውን ግዴታ በመከተል ተገቢውን ጥንቃቄ ያላደረጉና ይልቁንም የዘረጉት የአሰራር ሥርአት ያለደረሰኝ የሚደረገውን ግብይት አውቀውና ፈቅደው እንደሚከናወን ከክርክሩና ከማስረጃው መገንዘብ የተቻለው ስለሆነ በአንደኛ አመልካችም ላይ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡

ሲጠቃለልም አመልካቾች በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆነው መገኘታቸው በሕጉ አግባብ ከመሆኑም በላይ በቅጣቱም ላይ ከአመልካቾች ቅሬታ አኳያ የሕግ ስህተት የተፈጸመ ሆኖ አላገኘውም፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 144166 በ12/9/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 80867 ነሐሴ 18 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 45927

ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የኦሮሚያ ክልል ዓቃቤ ሕግ - ዮሴፍ ሐጎስ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** መሠረት መኮንን - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ ሕዳር 13 ቀን 2000 ዓ.ም. በመሠረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበበት ክስ በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ/ ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ ሟች ሲያኔ ታሬሳን ተከሣሽን ባለማግባትዋ ምክንያት ቂም ይዞ ሲሳይ በተባለው ሆቴል ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም. አብሯት አድሮ በንጋታው ጥቅምት 27 ቀን 2000 ዓ.ም. በጩቤ ሆዷንና ግራ እግሯን ወግቶ በግፍ ስለገደለ በፈፀመው ከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ሊጠየቅ ይገባል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በሥር ፍርድ ቤት ቀርቦ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል በክሱ ተቃውሞ የሌለው መሆኑን በመግለጽ የወንጀል ድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ ግን ስለመፈፀሙ አምኖ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ ዓቃቤ ሕግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም ተጠሪ እንዲከላከል አድርጎ የመከላከያ ማስረጃዎችን ሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ የተጠሪ መከላከያ ማስረጃዎችን የዓቃቤ ሕጉን ማስረጃዎችን ማስተባበል ያልቻሉ መሆኑን በመግለጽ የመከላከያ ምስክሮችን ቃል ውድቅ ከአደረገ በኋላ ተጠሪን ለሰው ግድያ ወንጀሉ ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል ካለ በኋላ ድርጊቱ ሊሸፈን የሚችለው በዓቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበው አንቀጽ ሥር ሳይሆን በወ/መ/ሕ/ቁጥር 540 ሥር ነው በማለት በዚሁ አንቀጽ ሥር ጥፋተኛ አድርጎ የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ የቅጣቱን መጠን 14 /አስራ አራት ዓመት/ በማድረግ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታውን ደግሞ ለሰበር ችሎቱ ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካቾች ግንቦት 07 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ድርጊቱ ቅድመ ዝግጅት ተደርጎበት በቂም በቀል የተፈፀመ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ፤ ተራ ሰው ግድያ ወንጀል በሚያስጠይቅበት ድንጋጌ ሥር ይወድቃል መባሉ ያላግባብ ስለሆነ የጥፋተኝነት ውሣኔው በወ/መ/ሕ/ቁጥር 539/1/ሀ/ ሥር ተሰጥቶ ተመጣጣኝ ቅጣት ሊጣል ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በማስረጃ የተረጋገጠው ፍሬ ነገር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ/ ሥር የተመለተውን ከባድ የግድያ ወንጀል ያቋቁማል አያቋቁምም? የሚለውንና የዚሁ ተከታይ የሆነውን ቅጣት መጠን ለማየት ሲባል በሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ መስከረም 15 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ 2 ገጽ የሰበር አቤቱታ መልሱን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ሟችን በቂም ተነሳስቶ በጩቤ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቿን በመውጋት ለሕልፈት ዳርጓል በሚል አመልካች ክስ መስርቶ የድርጊቱን መፈፀም ተጠሪ ሳይክድ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለቱ ዓቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን የሰነድና የሰው ምስክሮችን አቅርቦ ማስማቱን ነው፡፡ በዓቃቤ ሕግ የሰው ምስክሮች ቃል የተነገረው ፍሬ ነገር ሲታይም በነቀምቴ ቴሌኮሙኒኬሽን አካባቢ፣ ሲሳይ ማሞ ሆቴል ፊት ለፊት ቁመው መኪና ሲጠበቁ ከቆዩ በኋላ በመኪናው ሥር ቁመው ባሉበት ሁኔታ ተጠሪ ሟችን ይሄት ጩሃ እያዩአቸው ጉድኗን በጩቤ ወግቶ ከጣላት በኋላ ጨምሮ ሁለት ጊዜ ደግሞ ጭኗን /እግሯን/ ወግቶ ወጣሉን ከዚህም በኋላ የተጠሪን እጅ ምስክሮች በመምታት ጩቤውን በማስጣል ተጠሪን ፖሊስ መያዙን እንዲሁም ሟችን ሆስፒታል ወስደዋት በእለቱ ከጠዋቱ አራት ሰዓት ላይ መሞቷን መመስከራቸውን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ተጠሪ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 35 መሠረት ለወረዳው ፍርድ ቤት በሰጠው ቃል ሲሆን ይዘቱም ሲታይ ሟች ጓደኛዬ /ፍቅረኛዬ/ ሆና ለሦስት ዓመት በየወሩ ብር ሦስት መቶ እየረዳት በነቀምቴ መምራን ኮሌጅ ሲያስተምራት ቆይቶ በሽምግልና ሲያስጠይቃት እምቢ ስላለችው ገንዘቡን እመልስለታለሁ፣ አልፈልገውም ብላ ስለተናገረች ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም. ሲሳይ ማሞ ሆቴል አብረው አድረው ጥቅምት 27 ቀን 2000 ዓ.ም. ጠዋት ላይ በጩቤ ሟችን ወግቶ የገደላት መሆኑን ቃሉን በነፃ ፈቃዱ መስጠቱን የሚያስረዳ ነው፡፡ ሌላው በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ከነቀምቴ ሆስፒታል የተሰጠ የሕክምና ማስረጃ ሲሆን ይዘቱም በሟች አካል ላይ በሦስት በተለያዩ ክፍሎች የተለያየ መጠን ያላቸው ቁስሎች የነበሩ ስለመሆኑና በዚሁ ምክንያትም መሞቷን የሚያሳይ ነው፡፡ እንግዲህ በአቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡት ማስረጃዎች ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ ከላይ የተመለከተው ስለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶችም ያረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን በተጠሪ መከላከያ ማስረጃም ይኸው ፍሬ ጉዳይ የተስተባበለ ወይም ሌሎች ሁኔታዎች ባሉበት የተፈፀመ ስለመሆኑ የተነገረ ነገር የሌለ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪን ጥፋተኛ ሲያደርግ በዓቃቤ ሕግ በኩል የተጠቀሰውን አንቀጽ ዝቅ ወደአለ አንቀጽ መቀየሩ ባግባቡ ነውን? የሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚያስፈልገው ነው፡፡

በመሠረቱ የሰው ግድያ ወንጀል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ/ መሠረት ድርጊት ፈፃሚውን ሊያስጠይቅ የሚችለው ድርጊቱ ሆነ ተብሎ አስቀድሞ በማሰብና በመዘጋጀት ሲፈፀም ወይም በአንቀጽ 84 ወይም 86 ሥር የተመለከቱት አክባጅ ሁኔታዎች በተገኙበት ሁኔታ የወንጀል አድራጊው በተለይ ጨካኝ፣ ነውረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን ሲያመለክቱ ስለመሆኑ ተጠቃሹ ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በድንጋጌው ሥር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች በየራሳቸው መቆም የሚችሉ ነጥቦች ስለመሆናቸው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ሟችን የገደለው ፍቅረኛው ሆና ትምህርት በራሱ ወጪ ሲያስተምራት ቆይቶ አላገባህም፣ ገንዘብህን እመልስልሃለሁ ስላለችው በዚህ መልሷ ቂም ይዞ ቆይቶ እንዲሁም ወንጀሉ ከመፈፀሙ በፊትም አንድ ቀን ቀደም ብለው አብረው በሆቴል ውስጥ አድረው ከወጡ በኋላ በጩቤ ደጋግሞ በመውጋት ለሕልፈት የዳረጋት ስለመሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ፍሬ ነገሮች ተጠሪ የግድያ ወንጀሉን አስቦበትና ቀድሞ ተዘጋጅቶበት በጭካኔ ወይም በአደገኛነት የፈፀመው ስለመሆኑ ያሳያሉ ከሚባሉ በስተቀር

በአለታዊ ፀብ እና አለመግባባት ምክንያት የፈፀመው ድርጊት ነው ለማለት የሚያስችሉ አይደሉም። በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በዓቃቤ ሕጉ ማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ከሕጉ ጋር ማገናዘብ ሲገባቸው ያለ ምክንያት በተጠሪ ላይ ተጠቅሶ የቀረበውን ድንጋጌ መቀየራቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል። በዚህም መሠረት ተጠሪ ለፈፀመው የሰው ግድያ ወንጀል ሊጠየቅ የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539/1/ሀ/ ሥር እንጂ በአንቀጽ 540 ሥር ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በተጠሪ ላይ የሰጡትን የጥፋተኛነት ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2/ለ/2/ መሠረት ለውጠን ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539/1ሀ/ ሥር ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል።

ተጠሪ ሊቀጣ የሚገባው በዚህ ፍርድ ቤት ጥፋተኛ በተባለበት ድንጋጌ ሥር በተመለከተው ቅጣት አንፃር ነው። ቅጣት የሚወሰነው ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 82፣ ሥር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው። ይህ ችሎትም እነዚህ ሁኔታዎችን ተመልክቷል፤ አመዛዝኗልም። ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈፀሙ በዝርዝር ማመኑ፣ ሪኮርድ ያልቀረበበት መሆኑም መልካም የነበረ መሆኑን እንደሚያሳይ የሚያስገነዝብ ነው። እነዚህ ነጥቦች ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 82/1/ሀ/ እና /ሠ/ መሠረት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ሲሆኑ መጠኑም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 179/ለ/ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል። ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪን ተጠያቂ ያደረጉበት ድንጋጌ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሠረት ያላደረገና በምክንያትም ያልተደገፈ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሲሆን የተጠሪን አድራጎት በከባድ የሰው መግደል ወንጀል የሚሸፈንና የቅጣት መጠኑንም ከፍ ብሎ መወሰን ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል።

## ው ሣ ኔ

1. በአመልካቾች ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኛነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2/ለ/2/ መሠረት ተሻሽሏል።
2. ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539/ሀ/ ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፈ ጥፋተኛ ነው ብለናል።
3. ተጠሪ በጉዳዩ የታሰረው የሚታሰብለት ሆኖ ሊቀጣ የሚገባው በ20 /ሃያ/ ዓመት ጽኑ እስራት ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195/2/ለ2/ መሠረት አሻሽለን ወስነናል።
4. ውሣኔው የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለማ/ቤት ይፃፍ።
   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 45572

የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዘነበች ሽብሩ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌ/ዐ/ህግ - ፈቃዱ አብዲሣ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የዐ/ህግ ምስክሮች ተሟልተው ባለመቅረባቸው መዝገቡ ለጊዜው ሲዘጋ ያለውን ውጤት የሚመለከት ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ተጠሪ ያቀረበውን የወንጀል ክስ በሚያስተናግድበት ጊዜ በጉዳዩ ላይ የተቆጠሩት ምስክሮች ተሟልተው ባለመቀረባቸው የዐ/ህግ ክስ ምስክሮቹ ተሟልተው ሲቀርቡ ይቀጥል ዘንድ ትዕዛዝ ሠጥቶ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ የስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ ቅር በመሠኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሠጡትን ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡ ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ጥር 20 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሠምቷል፡፡ እኛም ጉዳዩን ከስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ ይዘትና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካች ላይ ተጠሪ የመሠረተው ክስ ለጊዜው የተዘጋው የዐ/ህግ ምስክሮች ሲሟሉ ዐ/ህግ ክሱን የማንቀሳቀስ መብት ተጠብቆለት መሆኑን ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃ አጥብቀው የሚከራከሩት ይህ የስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ ገደብ የለሽ ሆኖ አመልካች በስጋት ውስጥ እንደኖሩ የሚያደርግ ነው በሚል ነው፡፡ ሆኖም የስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ በጉዳዩ በህጉ የተመለከተውን የይርጋ ጊዜ ተግባራዊ አይሆንም የሚል አንድምታ የሌለው በመሆኑ የአመልካች ጠበቃ ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ አፅንተነዋል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 43501

መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች**፡- 1. ረዳት ሣጅን ሺጋ ተካ ሞላ
2. ኮን/ል ሐብታሙ ዝናቡ ወንድሙ
3. ኮን/ል ሐብታሙ መኮንን ኩምሣ

ከማ/ቤት ቀርበዋል ዋ/ኢ/ር ደጀኔ ወንድሜነህ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኦሮሚያ ክልል ዓ/ሕግ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች በተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት በማጽናታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ነው፡፡

አመልካቾች የተከሰሱት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ለ/ እና 540 የተመለተውን በመተላለፍ በቀን 09/05/99 ዓ.ም ከቀኑ 5፡00 ሰዓት ላይ በሻክሶ ወረዳ ቀንጢቻ ቀበሌ በታንታለም ፋብሪካ አጠገብ ሰው በመሞቱ ምክንያት ተሰብስቦ ካለው ሕዝብ ውስጥ አንደኛው ተጠሪ ሟች ጴጥሮስ ቦሩን ጉኑ ላይ መትቶ በመግደሉ፣ሁለተኛው ተጠሪ ሟች በዴሳ ሚጣ ከለቻን መትቶ በመግደሉ ሦስተኛው ተጠሪ ሟች በቀለ ጂሎና ዱከሌ ደረስ ላይ ተኩሶ በመግደሉ እንዲሁም ሁለተኛ ክስ በሦስተኛው ተጠሪ ላይ የወንጀል ሕግ ቁጥር 27/1/ እና 540 በመተላለፍ በአንደኛው ክስ በተገለፀው ቦታና እና ቀን በብዛት ቆመው ባሉት ህዝብ ላይ ደግኖ ተኩሶ ተበዳይ ጂሎ ጡኔን እግሩን፣ዲጉ ገናሌን፣እያሱ ደደቻን ግራ እጅ እና ዋጩሎ ሙደን በጥይት መትቷቸው የግድያ ሙከራ ወንጀል ፈጽሟል በሚል የጉጂ ዞን ዓ/ሕግ ክስ መስርቶባቸዋል፡፡

አመልካቾች ጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርበው ወንጀል አለመፈፀማቸውን ክደው ተከራክረዋል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኂላ በተከሰሱበት የወንጀል አንቀጽ ጥፋተኛ ናቸው ካለ በኂላ አንደኛ እና ሁለተኛ አመልካቾች በ15 (አስራ አምስት ዓመት) ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሦስተኛው አመልካች በአንቀጽ 540 በሁለት ድርጊት ጥፋተኛ ነው በሚል በሃያ ዓመት (20) ጽኑ እስራት እንዲቀጣ

ፈርዷል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ስሕተት የለውም በሚል አጽንተዋል፡፡

አመልካቾች በፌ/ፖ/ክ/ሕግ አገልግሎት ነ/ፈጅ በኩል ሚያዝያ 5 ቀን 2001 ዓ.ም የተሻሻለ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ችግሩ በተፈጠረበት ቦታ ቁጥራቸው ከ300 በላይ የሚሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ክላሽ ጠመንጃ፣ጦርና ገጀራ በመያዝ ቃንጥቻ የሚገኘውን የታንታለም ማምረቻ ፋብሪካን ለመዝረፍ ሲንቀሳቀሱ በተፈጠረ ግጭት ከሕዝቡ በተተኮሰ ጥይት የፖሊስ አባላትም የቆሰሉ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ አመልካቾችን ጥፋተኛ ማድረጉ የግራ ቀኙን ማስረጃ በአግባቡ ሳያገናዝብ ነው በሚል የሥር ፍ/ቤት ፍርድ ተሽሮ አመልካቾች በነፃ እንዲሰናበቱ አመልክቷል፡፡

የሰበር ችሎትም አመልካቾች ድርጊቱን ፈጽሟል ቢባል እንኳ ጥፋተኛ የመባላቸውን አግባብነት ከወንጀል ሕጉ መርህ እና ድንጋጌዎች አንፃር ለመመርመር ሲል ዓ/ሕግ መልስ እንዲሰጥ አዟል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ዓ/ሕግ በ28/12/2001 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካቾች የተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት ስለመፈጸማቸው ከጥርጣሬ ውጪ የተመሰከረባቸው ስለሆነ በሥር ፍ/ቤት የተወሰነው የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ እንዲፀና በማለት አመልክቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር እና የሥር መዝገብ ውሳኔ ይዘት ከመረመረ በኋላ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ምላሽ የሚያሻው የሕግ ጥያቄ ሆኖ ያገኘው አመልካቾች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወ/ሕ/ድንጋጌ አንቀጽ 540 ወይንስ 541 የሚለውን ነው፡፡ ይህንኑ ለመፍታት የጉዳዩን አፈፃፀም እና መነሻ ሁኔታዎች በአጭሩ መመለከት ተገቢ ነው፡፡

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት የተቻለው ፍሬ ነገር ወንጀሉ ተፈፀመ ከተባለበት ቀን አስቀድሞ ሌሊቱን በታንታለም ፋብሪካ አጠገብ አንድ ሰው ተገድሎ የነበረ ስለመሆኑ፣ይህንንም መነሻ በማድረግ የአካባቢው ሕዝብ እዚያው ፋብሪካ አጠገብ የተሰበሰበ ስለመሆኑ፣የተሰበሰበው ሕዝብ ክላሽ፣ገጀራና ጦር ይዞ የነበረ ስለመሆኑ እና የታንታለም ፋብሪካ ሰራተኞችም ወደ ሥራ እንዳይገቡ እንዳይወጡ በዚሁ በተሰበሰበው ሕዝብ ሁከት የተፈጠረ ስለመሆኑ ነው፡፡ የአሁን አመልካቾች እና ሌሎች ባልደረቦቻቸው ወደ ቦታው የተንቀሳቀሱት ይህንኑ የፋብሪካው ሥራ መስተጓጐልና ሌላ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል እንዲቻል ስለመሆኑም በምስክሮች ተነግሯል፡፡

አመልካቾች እና ባልደረቦቻቸው በቦታው ሲደርሱ እነሱን በያዘው መኪና እና አባሎቻቸው ላይም ጉዳት የደረሰ ስለመሆኑም ተመስክሯል፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች የተከሰሱበትን ወንጀል ስለመፈጸማቸውም በሥር ፍ/ቤት በቀረቡት ማስረጃዎች የተመሰከረ ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ እንግዲህ አጠቃላይ  የወንጀሉ አፈፃፀም ሁኔታ ይህንን የሚመስል ሲሆን አመልካቾች ወንጀሉን አልፈጸምንም በማለት እዚህም ፍ/ቤት ዘንድ አጥብቀው የተከራከሩ ቢሆንም ስለወንጀሉ አፈፃፀም እና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን የሚታይ ባለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር እንዳለ በመቀበል በሕግ ረገድ የሚኖረውን ውጤት ብቻ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካቾች የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት የፈፀሙት በታንታለም ፋብሪካ ላይ የተቃጣን አደጋ ለመከላከል እንደሆነ ከፍ ሲል የተመለከተው ፍሬ ነገር እና ከወንጀሉ አፈፃፀም ከባቢያዊ ሁኔታ መረዳት ይቻላል፡፡

ድርጊቱ ወንጀል ነው ቢባልም በሕግ በተመለከተ ልዩ ሁኔታ በሕግ በተፈቀዱ ድርጊቶች የማያስቀጡት እና ይቅርታ የሚያሰጡ ሁኔታዎች በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተመለከተውን ድንጋጌ ከተያዘው ጉዳይ ጋር ማየት ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ለተያዘው ጉዳይ ቀጥታና አግባብነት ያለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 78"ን" እንመለከታለን፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሰረት የራሱን ወይም የሌላውን ሰው መብት ሕገወጥ ከሆነ ጥቃት ወይም በቅርብ ከሚደርስ ሕገ-ወጥ ጥቃት ለማዳን ጥቃቱ እንዳይደርስ ለማድረግ ሌላ መንገድ ሳይኖር ከሁኔታው መጠን

ባለማለፍ የተፈፀመ ድርጊት አያስቀጣም ተብሎ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ተከሳሹ ከቅጣት ነፃ የሚሆነው ሕገ-ወጥ ጥቃት በራሱ ወይም በሌላው ሰው መብት ላይ የተሰነዘረ ወይም በእርግጠኛነት ሊደርስ የሚችል ጥቃት ስለመኖሩ፣ይህንንም ለማስወገድ ወይም ለመከላከል ሌላ አማራጭ የሌለው ስለመሆኑ እና የወሰደው የመከላከል ወይም ጥቃቱን የማስወገድ እርምጃ ከተሰነዘረው ጥቃት ጋር ተመጣጣኝ ኃይል የተጠቀመ መሆኑን ማስረዳት ሲችል ብቻ ነው፡፡ ይህንኑ የሕጉን መንፈስ እና ይዘት መሰረት አድረገን የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት በአመልካቾች በኩል የቀረበው ፍሬ ነገር በታንታለም ፋብሪካ አካባቢ የተሰበሰበው ሕዝብ የፋብሪካውን ሥራ ስለማወኩ፣ ሕዝቡም የተለያዩ መሣሪያዎችን ያየዘ ስለመሆኑ፣ አመልካቾች ፀጥታ ለማስከበር ያደረጉትን ጥረት በፀጥታው ሃይል አባላት እና ንብረት ላይ ጥቃት የተሰነዘረ ስለመሆኑ እና በፋብሪካውም ላይ አደጋ ሊሰነዘር የተቃጣ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህ ፍሬ ነገር የሚያስገነዝበን በፋብሪካውም ሆነ በፀጥታ አስከባሪዎች ላይ የተቃጣ ሕገ-ወጥ ጥቃት ስለመኖሩ ነው ይህንን ጥቃት ለማስወገድ አመልካቾች ተኩሰው ሰው መግደላቸው እና ማቁሰላቸው ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን ተከትሎ የሚነሳው ጥያቄ አመልካቾች የተሰነዘረውን ጥቃት ለማስወገድ ሌላ አማራጭ ያልነበራቸው ስለመሆኑ እና የወሰዱት አማራጭም ተመጣጣኝ ስለመሆኑ አስረድተዋል ወይ? የሚለው ነው፡፡ በዚህ ረገድ አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ያስረዱት ፍሬ ነገር የለም፡፡ አመልካቾች ሕገ-ወጥ ጥቃትን ለማስወገድ እርምጃ ስለመውሰዳቸው የተመለከተ ቢሆንም እርምጃው ሌላውን አማራጭ ያሟጠጠ ስለመሆኑ እና ተመጣጣኝ ስለመሆኑ ለማስረዳት ያልቻሉ ስለሆነ በወ/ሕ አንቀጽ 78 የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘት አሟልተዋል ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለዚህም ድርጊታቸው ሕገወጥ ጥቃትን ለማስወገድ ነው የሚያስብል መነሻ ቢኖረውም የፈፀሙት የነፍስ ግድያ ወንጀል በሕጉ ከተመለከተው መጠን በማሳለፍ መሆኑን መገንዘብ ችለናል፡፡

ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ የተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ደግሞ ከቅጣት ነፃ የማያደርግ ስለመሆኑ የወ/ሕ ድንጋጌ ቁጥር 79/1/ ያመለክታል፡፡ ይልቁንም ይህ አድራጎት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ስለመሆኑ ይህ ድንጋጌ ቁጥር 79/1/ ይገልፃል፡፡ ይህንን መሰረታዊ ጉዳይ ከተረዳን የአመልካቾች ድርጊት ጥፋተኛ ሊያሰኝ የሚገባው በየትኛው የወ/ሕጉ ድንጋጌ ነው? የሚለውን መሰረታዊ ጭብጥ ወደ ማየት ስንመለስ የአመልካቾች ድርጊት ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን ማሳለፍ መሆኑ መሰረት በማድረግ የወ/ሕጉ ልዩ ክፍል በዚህ ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆን ድንጋጌ እንዳለው እንረዳለን፡፡ ይኸውም በወ/ሕጉ አንቀጽ 541/ሀ/ ሥር ከተመለከቱት የድንጋጌው ማቋቋም ምክንያቶች አንዱ ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ የተፈፀመ የነፍስ ግድያ ወንጀል እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው የወ/ሕጉ አንቀጽ 79/1/ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አድርጐ በገለፀው አኳኋን አንቀጽ 541/ሀ/ ሁለተኛው ሐረግ ደግሞ ወንጀሉን ለማቋቋም እንደሚችል ደንግጓል፡፡

እንዲህ ያለ ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ ደግሞ በወ/ሕጉ አንቀጽ 82/2/ እንደተደነገገው ድርጊቱን ለማቋቋም የተደነገገው ልዩ ክፍል ተፈፃሚነት ይኖርዋል፡፡ ይህንን ለማለት የወ/ሕጉን ድንጋጌ ቁጥር 82/2/ እና 84/2/ ይዘት እና አቀራረጽ አገናዝቦ መመልከት ተገቢ ነው፡፡

ስለሆነም አመልካቾች የፈፀሙት የወንጀል ድርጊት የወ/ሕጉን አንቀጽ 540 የሚያቋቁም ነው በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ የድርጊቱን አፈፃፀም ከባቢያዊ ሁኔታ እና ምክንያት በአግባቡ ባለማገናዘብ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆኑን መረዳት ችለናል፡፡

ስለሆነም አመልካቾች የፈፀመት የወንጀል ድርጊት ሊደርስ ይችል የነበረን ሕገ-ወጥ ጥቃት ለማስወገድ እና ለመከላከል መሆኑን ነገር ግን አፈፃፀማቸው ሲታይ ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ በመሆኑ የወ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 541/ሀ/ ያቋቁማል ብለናል፡፡

ስለዚህም በአንደኛው ክስ አንደኛ፣ሁለተኛ እና ሦስተኛ አመልካቾችን በወ/ሕ ቁጥር 32/1/ (ሀ)ና(ለ) እና 540 ሥር እንዲሁም በሁለተኛው ክስ ሦስተኛ አመልካችን በወ/ሕግ ቁጥር 27/1/ እና 540 ሥር ጥፋተኛ መባላቸው አግባብ ሆኖ ስላላገኘው ሕጉን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113/2/ መሰረት ለውጠን በአንደኛው ክስ ሦስቱም አመልካቾች በወ/ሕግ ቁጥር 32/1/ (ሀ)ና(ለ) እና 541/ሀ/ ሥር እንዲሁም በሁለተኛው ክስ ሦስተኛ አመልካች በወ/ሕግ ቁጥር 27/1/ እና 541/ሀ/ ሥር ጥፋተኞች ናቸው ብለናል፡፡

ቅጣትን በተመለከተ አመልካቾች በዚህ ፍ/ቤት ጥፋተኛ የተባሉበት አንቀጽ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እንደሚያስቀጣ ድንጋጌው ያመለክታል፡፡ በመሰረቱ ቀላል እስራት በመደቡ የሚጣለው ከአሥር ቀን እስከ ሦስት ዓመት የሚደርስ ስለመሆኑ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 106/1/ ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ቀላል እስራት ቅጣት ከዚህ መደብ ጣሪያ ከፍ ብሎ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችለው በዚሁ አንቀጽ ሥር የተመለከቱት ምክንያቶች ወይም ሁኔታዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ ስለመሆኑም ተደንግጓል፡፡ ይህንኑ በማገናዘብ አመልካቾች ላይ ሊፈፀም የሚገባውን ቅጣት እንደሚከተለው ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02204 ታህሣሥ 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ፣የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 60135 መጋቢት 19/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 64351 ነሐሴ 20/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሰረት አሻሽለናል፡፡
2. በዚሁ መሰረት በአንደኛው ክስ አንደኛ፣ሁለተኛ፣እና ሦስተኛ አመልካቾች በወ/ሕግ አንቀጽ 32/1/ (ሀ)ና(ለ) እና 541/ሀ/ ድንጋጌ በሁለተኛው ክስ ሦስተኛ አመልካች በወ/ሕግ አንቀጽ 27/1/ እና 541/ሀ/ ድንጋጌ በመተላለፍ ጥፋተኞች ናቸው ብለን ወስነናል፡፡
3. አንደኛ እና ሁለተኛ አመልካቾች በዚህ ጉዳይ እጃቸው ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በሦስት(3)ዓመት ቀላል እስራት እንዲቀጡ ብለናል፡፡ ሦስተኛው አመልካች በሁለት ቀላል ወንጀል ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በአምስት (5) ዓመት ቀላል እስራት እንዲቀጣ ብለናል፡፡
4. የጥፋተኛነት አንቀጽ እና ቅጣቱ የተሻሻለ መሆኑን እንዲያውቅ የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ግልባጭ ለጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡ ይፃፍ፡፡
5. ማረሚያ ቤቱ በዚህ ችሎት በተሻሻለው ቅጣት መሰረት እንዲያስፈጽም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
6. የጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገብ ቁጥር 02204 በመጣበት ሁኔታ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 44235

መጋቢት 28 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ቄስ ጌታቸው ተሾመ

**ተጠሪ**፡- ዓቃቤ ሕግ

## ፍ ር ድ

አመልካች በስር ፍርድ ቤት በቀረበባቸው ሁለት የወንጀል ክሶች ጥፋተኛ ተብለው በሁለት አመትና በ300.00 ብር እንዲቀጡ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት አለበት በሚል ይህን የሰበር አቤቱታ ሊያቀርቡ ችለዋል፡፡

በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቃቤ ሕግ ባቀረበባቸው አንደኛ ክስ የወንጀል ሕግ ቁጥር 543/1/"ን" በመተላለፍ የካቲት 29 ቀን 2000 ዓ.ም ከቀኑ 5 ሰዓት ድርጊቱ ሞትን ሊያስከትል እንደሚችል ማሰብ ሲገባው ባለመጠንቀቅ የቡዳ መድሃኒት ነው ብሎ ቅጠላቅጠል አጨሶ በማጠንና ማረሻ አግሎ ከፊቷ ላይ በመተኮስ ሟችን የገደለ በመሆኑ በቸልተኛነት ሰው መግደል ወንጀል ተከሷል፣እንዲሁም በሁለተኛ ክስ ጉጂነቱ ጉዳቱ በተረጋገጠ ልማዳዊ ድርጊት የቡዳ መድሃኒት ነው ብሎ ቅጠላ ቅጠል አጨሶ በማጠን ማረሻ አግሎ ፊትዋን በተመተኮስ ለሞት ያበቃት በመሆኑ በልማዳዊ ድርጊት ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሷል በማለት ክስ መስርቶባቸዋል፡፡ አመልካች ድርጊቱን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለታቸው አቃቤ ሕግ ሶስት የሰው ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ፍ/ቤቱም የአቃቤ ሕግ ምስክሮች እንደክስ አቀራረቡ አስረድተዋል በማለት አመልካች ክሱን እንዲከላከሉ በማለቱ አመልካች ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት እለት ሟች ቤት ያልነበሩ ስለመሆናቸው ይመሰክሩልናል ያሏቸውን ሁለት ምስክሮች አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የአመልካች ምስክሮች ቃል እርስ በእርሱ የሚጋጭና የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ያሰረዱትን ለማስተባበል ያልቻለ ነው በማለት በሁለቱም ክሶች አመልካችን ጥፋተኛ በማለት በአንደኛው ክስ ሁለት አመት ቀላል እስራት በሁለተኛው ክስ 300.00(ሶስት መቶ ብር) እዲቀጡ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ይግባኙ ተቀባይነት ያላገኘ ሲሆን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታም አቅርበው ችሎቱ በአብላጫ ድምጽ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን አመልካች በቅሬታቸው ጥፋቱን ለመፈፀማቸው ከጥርጣሬ በላይ የተረጋገጠባቸው መሆኑን፣ሟች ቀድሞውኑ ታማ ስለነበር ለሞቷ ምክንያት የሆነው የያዛት ህመም መሆኑን፣ባትታመም ኖሮ ቅጠሉ ወይም ማረሻው ጉዳት ያደርስ እንደሆነ እንጂ ለሞት የማያበቃት

መሆኑን፣ቅጠሉ ሰው ገዳይ ለመሆኑ በህክምና አለመረጋገጡን እንዲሁ በተደራራቢ ክስ መከሰሳቸው አግባብ አለመሆኑን በመዘርዝር የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔው እንዲሻር ይህ የሚታለፍ ከሆነ ደግሞ በወ/ሕ/ቁ. 567 ብቻ ተጠያቂ እንዲሆኑ ጠይቀዋል፡፡ ይህ ችሎት አመልካች በወ/ሕ/ቁ. 543 እና 567 መሰረት መከሰሳቸው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አመልካች የተከሰሱት በቸልተኛነት ሰው ገድለዋል እንዲሁም በልማዳዊ ድርጊት ጉዳት አድርሰዋል በማለት በሁለት የወንጀል ድርጊቶች ነው፡፡ አመልካችም በሁለት ተደራራቢ ወንጀሎች ልጠየቅ አይገባም በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪም በቃል ክርክር ወቅት አመልካች በተደራራቢ ወንጀሎት መከሰሳቸው አግባብ አልነበረም በማለት ገልጿል፡፡ ችሎቱም ተፈፀመ ከተባለው ድርጊት አኳያ አመልካች በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ ሊባሉ ይገባል ወይ የሚለው ጭብጥ መርምሯል፡፡ አመልካች በሁለቱም ክሶች ፈፀሙ የተባለው ሟችን የቡዳ መድሃኒት ነው ብለው ቅጠላ ቅጠል አጭሰው በማጠንና ማረሻ አግለው ፊትዋን በመተኮስ ለሞት ዳርገዋታል በማለት ነው፡፡ አመልካች በክሱ የተገለፀውን ድርጊት መፈፀማቸው ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ፈጽመዋል የተባለው ይኸው ድርጊትም በግል ተበዳዩዋ ላይ ጉዳት ማድረስ ብቻ ሳይሆን ሞትን በማስከተሉ ሁለት ክስ መቅረቡን ተገንዝበናል፡፡ ነገር ግን በሕግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚደረጉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች የተደረጉት በአንድ የወንጀል ማድረግ ሃሳብ ወይም ቸልተኛነት ሲሆን እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈኑ ሲሆኑ አድራጊው በተመሳሳይ ባህሪ ባላቸው በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ የቅጣት ድንጋጌዎች እንደማይቀጣ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 61/1/ ያመለክታል፡፡ አመልካች መፈፀማቸው የተረጋገጠው የቡዳ መድሃኒት ነው በሚል ቅጠላ ቅጠል አጭሶ በማጠንና ማረሻ አግሎ በመተኮስ የግል ተበዳይ ድርጊቱ ከተፈፀመ ከአንድ ሰአት በኋላ እንድትሞት ማድረጋቸው ነው፡፡ አመልካች በልማዳዊ ድርጊት ጉዳት ያደረሱና ጉዳቱም ሞትን ያስከተለ ቢሆንም ወንጀሉን የፈፀሙት በአንድ ቸልተኛነት ድርጊት በመሆኑ በተደራራቢ ቅጣት ሊቀጡ አይገባም፡፡ በሌላ በኩል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 567 እንደተመለከተው ማንም ሰው ኢሰብአዊነቱ በታወቀና ጉጂነቱ በህክምና ሙያ በተረጋገጠ በልማዳዊ ድርጊት አማካኝነት በሌላ ሰው ላይ አካል ወይም አእምሮ ጉዳት ወይም ሞት እንዲደርስ ያደረገ ከሆነ በወንጀል ይቀጣል፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን አመልካች የፈጸሙት ጉጂ ልማዳዊ ድርጊት ሞትን ያስከተለ ቢሆንም ድርጊቶቹ በሙሉ ከፍ ሲል በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር የሚሸፈን በመሆኑ አመልካች በቸልተኛነት ሰው በመግደል የወንጀል ድርጊት ሊቀጡ የሚገባበት የሕግ መሰረት የለውም፡፡ በመሆኑም አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 543 ጥፋተኛ መባላቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡

በሌላ በኩል ግን የተፈፀመው ልማዳዊ ድርጊት ሞትን ያስከተለ ከሆነ እንደነገሩ ሁኔታ በአንቀጽ 561 ወይም 562 ከተመለከቱት ቅጣቶች አንዱ ተፈፃሚ እንደሚሆን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 567 ያመለክታል፡፡ በዚህም መሰረት ወንጀል ሕጉን 561/2/ ስንመለከት የሞት አደጋ የተከሰተው በቸልተኛነት የሆነ እንደሆነ አንቀጽ 543 ተፈፃሚ ሊሆን እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ በዚህም መሰረት አምልካች ከስድስት ወር እስከ ሶስት አመት ቀላል እስራት ወይም ከሁለት ሺህ ብር እስከ አራት ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ ሊቀጡ እንደሚችሉ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/1/ ያስገነዝበናል፡፡ አመልካች ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው በሕመም ላይ ያለን ሰው ቅጠል አጭሰው በማጠንና ማረሻ አግለው በመተኮስ ለሞት መዳረጋቸው ሲታይ ድርጊቱ አስከፊ መሆኑንና በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቹ ያልተማሩና የ9 ቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሆናቸው ቅጣቱን ሊያቀል የሚችል መሆኑ ከግምት ውስጥ በማስገባት የስር ፍ/ቤት አመልካችን በሁለት አመት ቀላል አስራት እንዲቀጡ የሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የሰሜሽ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 19090 ግንቦት 19 ቀን 2000 ቀን ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 6880 መስከረም 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 00683 ታህሣስ 13 ቀን 2001 ዓ.ም በድምጽ ብልጫ የሰጠው ትእዛዝ ተሻሽሏል፡፡

2. አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 543 ጥፋተኛ ናቸው ተብሎ የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
3. አመልካች የወንጀል ሕግ ቁጥር 567"ን" በመተላለፍ በፈፀሙት በልማዳዊ ድርጊት ጉዳት ማድረስ ወንጀል የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ አመልካች በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ ስለተባሉ በሁለት አመት ቀላል እስራት እንዲቀጡ የተሰጠውም የቅጣት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
4. አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ድርጊት የሚያስቀጣው በቀላል እስራት ወይም በአማራጭ በገንዘብ መቀጮ በመሆኑ አመልካች ብር 300.00 እንዲቀጡ የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 46189

ሚያዝያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ዓብዱራሂም አህመድ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ሐረገወይን ተፈራ - ጠበቃ ጥበቡ ምህረቴ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ ወርቁ ገመቹ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው ጉዳይ የወንጀል ሲሆን አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት በጠበቃቸው አማካኝነት ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ጥቅምት 25 በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ፣ ከበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች እንዲሁም አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች የተከሰሱት፡- በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወ/መ/ሕ/ቁ. 32(1(ሀ) እና (ለ)) እና 692/1/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የማይገባቸውን ብልጽግና ለማግኘት አስቀድሞ በማሰብ ክሱ በስር ፍርድ ቤት ከተቋረጠው ከአቶ ዘላለም ተስፋዬን የሲሊጥ ነጋዴና አቅራቢ በማስመሰል ለግል ተበዳይ ሽቶ በቀለ ካስተዋወቀች በኋላ የግል ተበዳይን በማሳመን ወደ ተሳሳተ እምነት በመምራት ግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 5፡30 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15 ክልል ውስጥ ልዩ ቦታው ከኢምፔሪያል ሆቴል በስተጀርባ ከሚገኘው የግል ተበዳይ ድርጅት በሆነው ፐርፍ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ግቢ ውስጥ ክስ የተቋረጠበት ግለሰብ ለድርጅቱ ብዛቱ 6000(ስድስት ሺህ) ኩንታል ሲሊጥ በብር 3,618,000(ሶስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አስራ ስምንት ሺህ ብር) ለማቅረብ ከተነጋገሩ በኋላ የቅድሚያ ክፍያ ያስፈልገኛል በማለት በእለቱ ብር 500,000(አምስት መቶ ሺህ) የያዘ ቼክ በመቀበል እንዲሁም ግንቦት 24 ቀን 1998 ዓ.ም ብር 50,000(አምሳ ሺህ ብር) ጉንደር ከሚገኘው የአቢሲኒያ ባንክ እንዲቀበል በአቶ

ያለው በቀለ ስም ተልኮለት በአጠቃላይ ብር 550,000(አምስት መቶ አምሳ ሺህ ብር) ወጪ አድርጐ ከወሰደ በኂላ ገንዘቡን ይዞ በመሰወሩ ሁለቱም የማታለል ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ አመልካች በክሱ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ የድርጊት አፈፃፀሙን በመካዳቸው አቃቤ ሕጉ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ለማስረጃነት አቅርቦ አመልካች ክሱን እንዲከላከሉ ተደርጐ የወንጀሉ ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜና ቦታ ተገኝተው በሰሊጥ ውሉ ላይ በእማኝነት መፈረማቸውን በጭብጥነት አሲይዘው የሰነድና የሰው ማስረጃዎችን አቅርበዋል፣ አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም አመልካችን በመከላከያ ማስረጃ በሰሊጥ ውሉ ላይ በእማኝነት ስለመፈረማቸው እና የግል ተበዳይም በአቶ ዘላለም ተስፋዬ የፍትሐብሔር ክስ አቅርበው ገንዘቡ እንዲመለስላቸው ማስፈረዳቸው ቢረጋገጥም የግል ተበዳይን ወደ ስህተት እንዲመሩ አላደረጉም ለማለት የሚያስችል አይደለም በማለት በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቀሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጐ በአንድ ዓመት ቀላል እስራት እንዲቀጡ እና የቅጣቱ አፈፃፀም በሦስት አመት ገደብ እንዲሆን ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የአመልካች በዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር በአመልካች በኩል የተፈፀመው ድርጊት የማታለል ወንጀልን የሚያቋቁም አይደለም በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በአንፃሩ ድርጊቱ የማታለል ወንጀልን የሚያቋቁም ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ይህ ችሎትም በአመልካች ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ የማታለል ወንጀልን ያቋቁማል ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ይዞ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 692/1/ መሰረት ተጠያቂ የሚሆነው የማይገባ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለጽ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው አታልሎ የራሱን ወይም የሦስተኛ ወገንን የንብረት ጥቅም የሚጐዳ አድራጐት እንዲፈፀም ያደረገ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ እንግዲህ አንድ ሰው የወንጀል ተጠያቂነት የሚኖርበት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2/ ስር እንደተመለከተው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ፈፀሙ የተባለው ክሱ የተቋረጠውን አቶ ዘላለም ተስፋዬን የሰሊጥ ነጋዴና አቅራቢ በማስመሰል ለግል ተበዳይ ለአቶ ሽቶ በቀለ አስተዋውቀው የግል ተበዳይ ገንዘብ ላይ ጉዳት አድርሰዋል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አቶ ዘላለም ተስፋዬ የሰሊጥ ነጋዴ አለመሆናቸው ካለመረጋገጡም በላይ አመልካች ይህንኑ እያወቁ ለግል ተበዳይ የተሳሳተ ነገር እውነት አስመስለው የተናገሩበት ሁኔታ ስለመኖሩ አልተረጋገጠም፡፡ ይልቁንም አቃቤ ሕጉ የሰሊጥ ነጋዴ ሳይሆኑ ነጋዴ ናቸው የተባሉትን ግለሰብ በተመለከተ ክሱን ያቋረጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የግል ተበዳይም ከአቶ ዘላለም ተስፋዬ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ፍትሐብሔራዊ የነበረ ስለመሆኑ ተረጋግጦ በፍትሐብሔር ችሎት ውሳኔ ተሰጥቶ ገንዘባቸው እንዲከፈላቸው ተወስኗል፡፡ ይህ ሁሉ የሚያሳየው አመልካች የማታለል ተግባር አለመፈፀማቸውን ነው፡፡ በመሆኑም የአመልካች ተግባር የማታለል ተግባርን የሚያቋቁም ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 23/2/ እና 692/1/"ን" ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 54121 ጥቅምት 25 እና ኀዳር 04 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጠቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 42198 የካቲት 25 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ተግባር የማታለል ወንጀልን የሚያቋቁም አይደለም ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 53612

ሚያዝያ 25 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ኂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች**፡- 1ኛ. አቶ ፍሰሐ ዓባይ
2ኛ. ወ/ሪት ህይወት የሰራው } ጠበቃ አቶ ሰለሞን ደምሴ

**ተጠሪ፡-** የገቢዎችና ጉምሩክ ዓ/ሕግ አቶ ገ/እግዛብሔር ሙናቸው ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር መዝገብ ሊቀርብ የቻለው በአመልካቾች ላይ በቀረበው የወንጀል ክስ ጉዳይ በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች ጉዳዩ ሲታይ ቆይቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ተመልክቶ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ አመልካቾች ቅር ተሰኝተው የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩም አመጣጥ ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡ የገቢዎችና ጉምሩክ አቃቤ ሕግ በአልካቾች ላይ ያቀረበው ክስ አመልካቾች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/1/ እና እንደተሻሻለው አንቀጽ 22/1/ እና መ/ለ/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ፈጽመዋል፡፡ የሚል ሲሆን፣ አመልካቾች ይህንኑ የወንጀል ድርጊት አልፈፀምንም በማለት ክደው በመከራከራቸው ክርክር ቀጥሎ ሁለቱም ወገኖች በየፊናቸው ማስረጃ አቅርበው አሰምተዋል፡፡

የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በኮ/መ/ቁ. 144285 ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ሁለተኛ አመልካች ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ስለመፈጸሟ የተረጋገጠ ሲሆን፤አንደኛ አመልካች

የንግድ ድርጅቱ ላለቤት እንደመሆናቸው ግብይት ያለደረሰኝ እንዳይከናወን አስፈላጊውን ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው በሰራተኛ ለተፈፀመው ድርጊት ኃላፊነት አለባቸው በማለት በሁለቱም ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በቅጣት ረገድም የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት ካገናዘበ በኋላ 1ኛ ተከሳሽ በብር 20,000.00(ሃያ ሺ. ብር) እና በ1(አንድ) ዓመት እስራት ሁለተኛ አመልካች በብር 10,000.00 (መቶ ሺ. ) ብር እና በ1(አንድ) ዓመት እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

በዚህ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ አመልካቾች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ተመልክቶ የአሁን አንደኛ አመልካች በተፈፀመው ድርጊት ቀጥተኛ ተሳትፎ የነበረው ስለመሆኑ በማስረጃ ስላልተረጋገጠ በነፃ ይሰናበታል በማለት ሲወስን፤ከጠቅላይ ፍ/ቤት የውሳኔ ግልባጭ ላይ መረዳት፣ እንደሚቻለው የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ የተሰጠው የእስራት ቅጣት አንሷል በማለት አቅርቦት የነበረው የይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ በጥፋተኝነትም ሆነ በቅጣት ረገድ በሰጠው ውሳኔ የገቢዎችና ጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ ሁለተኛ የይግባኝ አቤቱታ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በማቅረቡ፤የጠቅላይ የፍ/ቤቱ ሁለቱም ወገኖች ክርክር ካዳመጠ በኋላ በወ/ይ/መ/ቁ. 51336 የካቲት 05 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በጥፋተኝነት ውሳኔ አሰጣጥ በኩል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአንደኛ አመልካች ላይ የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ከፀና በኋላ በቅጣት አጣጣል ረገድ አመልካቾች ጥፋተኛ በተባሉበት ድንጋጌ ሥር ከተመለከተው ዝቅተኛ የቅጣት መነሻ በታች ለመውረድ የሚያበቃ ህጋዊ ምክንያት አልተገኘም በማለት የገንዘብ መቀጮውን ሳይነካ ሁለቱም አመልካቾች እያንዳንዳቸው በሁለት ዓመት እስራት እንዲቀጡ በማሻሻል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ዝርዝር ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ለዚህም የሰበር ቅሬታ ተጠሪ የገቢዎችና ጉምሩክ አቃቤ ሕግ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጐ በሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1ኛ. አመልካች ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ተፈጽሟል በተባለበት ጊዜ በተፈፀመው አድራጐት ተሳትፎ የነበረው ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡ የአንደኛ አመልካች የጥፋተኝነት መሰረት ሆኖ የተያዘው በአድራጐቱ የተነሣ ለፈፀመው ጥፋት ሳይሆን በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/1/ እንደተመለከተው ድርጅቱ አዋጁን በመተላለፉ ስለፈፀመው ጥፋት ተተክቶ ተጠያቂ ሊሆን በመቻሉ ነው በዚህ መሰረት ከተጠያቂነት ለመዳን የሚቻለው በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/3/ የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ለማስረዳት የተቻለ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ በጠቅላይ ፍ/ቤት የውሳኔ ሐተታ እንደተመለከተው ይህ ስለመሆኑ አንደኛ አመልካች ሕጉ የጣለበትን ግምት ለማስተባበል የሚያስችል የመከላከያ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 56/1/ "...አንድ ድርጅት...." የሚለውን አባባል ከአንቀጽ 56/4/ ድንጋጌ ሥራ አስኪያጅ የሚለው አባባል ለየትኞቹ ድርጅት የሚለውን ጥያቄ ሊያስነሳ እንደሚችል የተረዳን ቢሆንም በአዋጁ መግቢያ "ትርጓሜ" ለሚለው አንቀጽ 2/5/ እና 2/11/ ጋር አገናዝበን ስንመለከተው ድርጅት ማለት በሽርክና ማህበር በኩባንያ እና በሰዎች ህብረት ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሆኖ አይታይም፡፡

ሁለተኛ አመልካችንም ቢሆን ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ ቦታ ተገኝታ ከፈፀመችው ካደረገችው እና ከተናገረችው አድራጐት አንፃር በድርጊቱ አፈፃፀም ቀጥተኛ ተሳትፎ ስለመሆኑ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት በሥር ጠቅላይ ፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔን አስመልክቶ የተሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል የጠቅላይ ፍ/ቤት በተጠሪ ይግባኝ መነሻ በአመልካቾች ላይ ተጥሎ የነበረውን የአንድ ዓመት እስራት ወደ ሁለት ዓመት እስራት ለውጦ በማሻሻል ሊወስን የቻለው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 82/1//ሀ/ ከተመለከተው ዝርዝር የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች አንዱ የሆነው የጥፋተኛው የዘወትር ጠባይ መልካም መሆን ብቻውን እንደ ቅጣት ማቅለያ ሊወሰድ አይችልም፡፡ የዘወትር ጠባዩ መልካም መሆን ብቻ ሳይሆን ያጠፋውም በእውቀት ማነስ፣ባለማወቅ፣በየዋህነት ወይም ባልታሰበና ድንገተኛ አጋጣሚ እንደሆነ ጭምር መሆን ይገባዋል፡፡ በዚሁ ድንጋጌ የዘወትር ጠባይኑና የአፈፃፀሙን ሁኔታም "እና" በሚለው ምፃሄረ ቃል መያያዙ ሁለቱም ሁኔታዎች ድርብ የቅጣት ማቅለያ ማሟያ ምክንያቶች መሆናቸውን አመልካች ነው የሚለውን በመያዝ እንደሆነ ከመዝገቡ ግልባጭ ተረድተናል፡፡

ይሁን እንጂ ቅጣትን የማቅለልና ለቅጣት ነፃ የማድረግ ደንብን አስመልክቶ በተመለተው የሕግ ክፍል በወ/ሕ/ቁ. 179 ላይ "ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ መሰረት ቅጣትን ለማቅለል እንደሚችል በሕግ በተደነገገ ጊዜ ሁሉ......" ለሚለው አነጋገር "በሕግ በተደነገገ ጊዜ ሁሉ...." የሚለው ሐረግ ስለቅጣት ማቅለል በወ/ሕ/ቁ. 82/1/ሀ/ የተመለከተው ድንጋጌ ብቻ ሳይሆን ከቅጣት አወሳሰን ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ስለቅጣት አጣጣል አግባብነትና ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር አጣቅሶ ማየት እንደሚያስፈልግ አመላካች ነው፡፡

ከዚህም አኳያ በወ/ሕግ ቁጥር 88/2/ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ያለፈ የሕይወት ታሪክ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነ መደንገጉ አንድ አጥፊ ወንጀሉን እስካደረገበት ጊዜ ድረስ የዘወትር ጠባዩ መልካም የነበረ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ለቅጣት ማቅለያነት የማይወሰድበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ይህም ሁሉ ታልፎ በወንጀል ሕግ ቁጥር 82/1/ሀ/ የተመለከተው የቅጣት ማቅለያ ወጥነት ያለው የተጣመረ ምክንያት ነው እንኳ ቢባል በሥር ፍ/ቤቶች የቅጣትን አስተያየት አስመልክቶ በግራ ቀኙ በየደረጃው ከተደረጉት ክርክሮች፣ ከድርጊቱ አፈፃፀም ወንጀሉን ላቋቋመው ድንጋጌ ወይም ሕግ ጋር ሁሉ ተገናዝቦ ሲታይ በዚህ አከራካሪ በሆነው ድንጋጌ "እና" ከሚለው ቀጥሎ ካሉት ወይም በሚል ምሕጻረ ቃል ከተያያዙት አንዱን ምክንያት ቢሆን እንኳ አመልካቾች አላሟሉም ማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም የተነሣ ቅጣቱ በመደበኛ የቅጣት ማቅለያ ደንብ መሰረት ማውረድ አይገባም የሚለውን ታሳቢ በማድረግ አመልካቾች ጥፋተኛ በተባሉት ድንጋጌ ሥር የተመለከተውን መነሻ የሁለት ዓመት እስራት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መጣሉ/መወሰኑ የቅጣት አጣጣል ሥርአትን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## **<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በቅጣት አወሳሰን ረገድ ላይ ብቻ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በወ/ይ/መ/ቁ. 51336 የካቲት 05 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡ በዚህ ረገድ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በክ/መ/ቁ. 144285 ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም የጣለው ቅጣት ፀንቷል፡፡
2. አመልካቾች በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ እንደተገለፀው አንደኛ አመልካች በብር 20,000.00(ሃያ ሺህ ብር) እና በአንድ ዓመት፣ሁለተኛ አመልካች በብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) እና በአንድ ዓመት እስራት ይቀጣሉ በማለት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሰረት አሻሽለን ወስነናል፡፡ ለፌዴራል ማ/ቤቶች ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 41248

ሰኔ 23 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ቡርቄሶ ዋቆ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ዓቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በጋሞ አካባቢ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ ክሱ አመልካች በ1996 ዓ.ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1/ እና 540 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ መጋቢት 09 ቀን 1997 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 12:00 ሰዓት ሲሆን የግል ተበዳይ ሳራ ሳንቃ የተባለ ሰው ለመግደል ሞክሯል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ክሱ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በኋላ በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌለ መሆኑን ገልጾ የወንጀል ድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ ግን የክህደት ቃል ሰጥቷል፡፡ አቃቤ ሕግ በበኩሉ እንደክሱ የሚያስረዱለት የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ያሉት መሆኑን ገልፆ የግል ማስረጃዎቹን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች እንዲከላከል ተደርጐ የመከላከያ ማስረጃ የሌለው መሆኑን በማረጋገጡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት አመልካች በመከላከያ ምስክሮች የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ለማስተባበል ያልቻለ መሆኑን ገልፆ አመልካችን በአቃቤ ሕጉ በኩል ተጠቅሶ በቀረበው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጐ ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን አስተያየት በመቀበል እና ከህጉ ጋር በማገናዘብ አመልካች ቀድሞ የወንጀል ሪኮርድ ያለበት መሆኑን አረጋግጦ በአስራ ስምንት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው የጥፋተኛነትና እና የቅጣት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች መስከረም 13 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸሙ አቃቤ ሕግ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ውጪ ባላስረዳበት ሁኔታ በሐሰተኛ ማስረጃዎች ጥፋተኛ መባሌ ያላግባብ ነው፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም ከብዶ የተወሰነው ከወ/መ/ሕ/አንቀጽ 230 ድንጋጌ ውጪ ነው በማለት ዘርዝሮ ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ፈጸመ የተባለው የወንጀል ተግባር አንዳችም ውጤት ያላመጣ ከመሆኑ እንዣር እና አመልካች በምህረት የተለቀቀበትን ምክንያት የስር ፍርድ ቤት እንደ ቅጣት ማክበጃ ምክንያት አድርጐ በመውሰድ የአስራ ስምንት ዓመት ጽኑ እስራት መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪ ሰኔ 03 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች የወንጀል ድርጊቱን አለመፈጸሙን ገልጾ በመከራከሩ አቃቤ ሕግ ማስረጃ አቅርቦ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈጸሙን በሚገባ አኳኋን ማረጋገጡን የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች በዚህ ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታም ከግል ተበዳይ ጋር በእለቱ ከመገፈታተር ወጪ ሌላ ድርጊት የፈጸመ ስለመሆኑ አልተመሰከረም በማለት የሚከራከር ሲሆን ይህንኑ መከራከሪያ ነጥብ የሚያስረዳ መከላከያ ማስረጃ ግን በስር ፍርድ ቤት አላቀረበም፡፡ በመሆኑንም አመልካች ስለድርጊቱ አፈፃፀም በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የሚያቀርበው ቅሬታ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌ መሰረት ያለው ሥልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም እንጂ የማስረጃ ምዘናን የሚመለከት ጉዳይ የማጣራት ስልጣን ካለመሆኑ አንፃር ሲታይ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሌላው አመልካች በቅሬታ ነጥብነት ያነሳው ክርክር በሌላ የመግደል ሙከራ ተከሶ ጥፋተኛ ተብሎ በስምንት አመት ጽኑ እስራት የተቀጣበት ጉዳይ የእስራት ቅጣቱን ከመጨረሱ በፊት በይቅርታ የተፈታበትን እንደሪኰርድ ተወስዶ ቅጣቱ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎት ለአመልካች የተሰጠው ይቅርታ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ ለአመልካች የተሰጠው ይቅርታ ነው ከተባለ ይቅርታ ጽንሰ ሐሳቡና ውጤቱ ምን እንደሆነ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 230 ስር አስቀምጧል፡፡ በዚህ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር ሁለት ፓራግራፍ ሁለት መሰረት ይቅርታ ሲሰጥ በተቀጪው ላይ የተወሰነው ፍርድ ከሚያስከትለው ውጤት ጋር በወንጀለኞች መዝገብ ላይ ተመዝግቦ እንደሚኖር ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ይቅርታ የጥፋተኛነት ውሳኔ እንዳልነበረ የሚያስቆጥር አይደለም፡፡ በመሆኑም የወንጀለኞች መዝገብ ላይ ተመዝግቦ የሚኖር በመሆኑ በሪኰርድነት የማይያዝበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት በምህረት የወጡበትን ጉዳይ በቅጣት ማክበጃነት ተጠቅመዋል በማለት ያቀረቡት ቅሬታ የስር ፍርድ ቤቱ ሊጽፈው ከፈለገው እና በትክክልም ለአመልካች የተሰጠው ይቅርታ እንጂ መህረት ያለመሆኑ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

አመልካች ተደጋጋሚ ወንጀለኛ መሆኑን የስር ፍርድ ቤቶች መሰረት አድርገው በአስራ ስምንት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ መወሰናቸው ስለቅጣት የተመለከቱትን አጠቃላይ መርሆዎችን ያላገናዘበ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአጠቃላይ አመልካችን የበታች ፍርድ ቤቶች ጥፋተኛ በማለት በአስራ ስምንት ዓመት ጽኑ እስራት መቅጣታቸው ባግባቡ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአመልካች ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 48617

ሰኔ 18 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ተስፋዬ አደላ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** አቃቤ ሕግ (መርማሪ ከሳሽ) - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚሁ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ ያቀረበው ክስ አመልካች በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555(ለ) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ቀኑ ባልታወቀ ጊዜ መስከረም ወር 2001 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 2:00 - 3:00 ባለው ጊዜ ሕጋዊ ባለቤቱን በቦክስ በመምታት አንድ ጥርስ ሲያወልቅ ሌሎች ሁለት ጥርሶች ላይም ጉዳት አድርሶ በሐኪም እንዲወልቅ በመደረጉ በሰው አካል ላይ ከባድ ጉዳት አድርሷል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ክሱ ደርሷቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ በክሱ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልጸው ስለድርጊቱ አፈጻጸም ግን የክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ አቃቤ ህግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡ ከዚያም አመልካች እንዲከላከሉ ተደርጎ የባለቤታቸው ጥርስ በሌላ ምክንያት የወለቀ መሆኑን የሚያሳይ ጭብጥ በማስያዝ የመከላከያ ምስክሮቻቸውን አሰምተዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአመልካች ምስክሮች በግል ተበዳይ ጥርስ በሌላ ምክንያት የወለቀ ስለመሆኑ የማያስረዱና የአቃቤ ሕግ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን የማያስተባብሉ መሆኑን በመግለጽ ውድቅ አድርጎ አመልካችን በአቃቤ የክስ ማመልከቻ በተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ በሁለት አመት ጽኑ እስራት ወይም በብር 500.00(አምስት መቶ ብር) እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለአዋሳ ከተማ መደበኛ ችሎት ይግባኝ አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት አመልካችን በከባድ የአካል ማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ ካለ

በኋላ በድንጋጌው ላይ ያልተመለከተውን የገንዘብ መቀጮ በአማራጭነት በመጠቀም ቅጣት መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ምክንያት ይዞ ቅጣቱን በመጨመር አመልካች በአምስት አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 09 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተተ ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ድርጊቱ የተፈፀመው በቸልተኝነት እንጂ ሆነ ተብሎ አይደለም ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅጣቱን ጨምሮ የወሰነው ባልተጠየቀ ዳኝነት ነው በማለት ምክንያታቸውን ዘርዝረው ውሳኔው እንዲሻርላቸው ወይም በገደብ እንዲለቀቁ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም አመልካች ጥፋተኛ ተብለው በሁለት አመት እስራት ወይም በብር 500.00(አምስት መቶ) እንዲቀጡ በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ላይ አቃቤ ሕግ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጸ 555(ለ) አማራጭ ቅጣት የማይደነግግ ሆኖ ሳለ አማራጭ ቅጣቱን መወሰኑ አግባብነት የለውም በማለት ባቀረበው ይግባኝ መነሻ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አማራጭ ቅጣቱን የመሻር አግባብነት እንደተጠበቀ ሆኖ የስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የወሰነውን የሁለት አመት እስራት ቅጣት ወደ አምስት አመት እስራት ከፍ አድርጎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ አቃቤ ሕግ በቁጥር 1230/85/2002 በቀን 26/04/2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 555(ለ) ስር ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባለ አጥፊ ሊቀጣ የሚገባው እንደነገሩ ሁኔታና እንደ ጉዳቱ ከባድነት ከአስራ አምስት አመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ወይም ከአንድ አመት በማያንስ ቀላል እስራት ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች የተቀመጡት በቀላል እስራት ስለመሆኑ በውሳኔው ላይ አልገለፀም ይህንኑ ተጠቅሞ እስራቱን በገንዘብ በአማራጭ ስለመቀየሩም ያስፈለገው ነገር የለም(ቅጣቱ አንቀጽ 179"ን" መሰረት ተደርጎ የተወሰነ መሆኑን አያሳይም)፡፡ የሆኖ ሆኖ ግን ተጠሪ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲያቀርብ ለይግባኙ ምክንያት ያደረገው አመልካች ጥፋተኛ ከተባሉት ድንጋጌ አንጻር በገንዘብ መቀጮ በአማራጭ ሊቀጣ አይገባም በሚል ስለመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጭ በግልፅ ያሳያል፡፡ ተጠሪም በዚህ ችሎት ባቀረበው መልስ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ተገቢው ቅጣት እንዲወሰን ይግባኝ ብለናል ከማለት ውጪ የእስራት ቅጣቱም ቢሆን ያነሰ ስለሆነ ሊጨምር ይገባል በማለት ይግባኝ አቅርበናል የሚል ክርክር የለውም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበው በአማራጭ የገንዘብ ቅጣት መተላለፉ ያላግባብ ነው በሚል ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ እንግዲህ በወንጀል ጉዳይ ውሳኔ ሲሰጥ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኙን የሚያቀርብበት ሥርዓት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195 ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ስለቅጣት በተለይ የተደነገገው የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር ሁለት በፊደል "መ" ስር የተመለከተው ሲሆን ይዘቱም ቅጣት አነሰ በዛ በሚል በግልጽ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚገባ መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለሆነም በግልፅ ጥያቄው ካልቀረበ ፍርድ ቤት ቅጣት ጨምሮ ሊወሰን የሚችልበት ሥርዓት የለም፡፡ እንዲህ ሆኖ ከተገኘ ባልተጠየቀ ጉዳይ ዳኝነት እንደመስጠት የሚቆጠር ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ በአመልካች ላይ የተጣለው የእስራት ቅጣት አንሷል በሚል የይግባኝ ቅሬታ ባላቀረበበት ሁኔታ የበላይ ፍርድ ቤቶች የሁለት ዓመቱን የእስራት ቅጣት ወደ አምስት አመት እስራት ቅጣት ከፍ አድርጎ መወሰናቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት በመ/ቁጥር 06214 መጋቢት 21 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 28011 ግንቦት 14 ቀን 2001 ዓ.ም በዚሁ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ በመ/ቁጥር 29101 ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(ለ-2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17231 መጋቢት 03 ቀን 2001 ዓ.ም የተሠጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(ለ-2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
3. አመልካች ሊቀጡ የሚገባው በሁለት አመት ፅኑ እስራት ነው ብለናል፡፡
4. አመልካች በጉዳዩ ላይ የታሰሩት ማናቸውም የእስር ጊዜ በቅጣቱ ላይ የሚታሰብላቸው መሆኑን ተገንዝቦ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ተገልፆ ለማረሚያ ቤቱ ይፃፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዘገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 51706

ሐምሌ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ ግርማ ትኩ - ከማረሚያ ቤት ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 45521 ጥቅምት 21 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት የቅጣት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ጥር 4 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ ስለጠየቁ ነው፡፡ ክርክሩ መጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡

በከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 408 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 በመተላለፉ ሁለት ወንጀሎችን እንደፈፀመ በመግለጽ ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ከአቶ መሐመድ ኑር በአቶ ዮናስ ገብርአብ በኩል ብር 2,300(ሁለት ሺህ ሦስት መቶ) ጉቦ ተቀብሏል ተብሎ የተከሰሰበትን ወንጀል ተጠሪ እንደ ክሱ አቀራረብ ባለማሥረዳቱ አመልካች በከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በነፃ እንዲያሰናበት ብይን በመስጠቱና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን ለይግባኝ ሰሚ ችሎት የፀና በመሆኑ በዚህ መዝገብ የግራ ቀኙ የመከራከሪያ ጭብጥ ሆኖ አልተያዘም፡፡

በዚህ መዝገብ አከራካሪ ሆኖ የተያዘው ጭብጥ ተጠሪ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 408 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተውን በመተላለፍ ሐምሌ ወር 1999 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ፍርድ

ቤት ፕሬዚዳንት ሆኖ ሲሰራ በልደታ ምድብ በመዝገብ ቁጥር 03453 እነ ካልዩ ኡመር በሚል በሚጠራው ፋይል ተከሳሽ የሆኑት አቶ አልዬ ኡመር ጉዳዩ እንዲወሰንለት ከፈለገ ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ይክፈል በማለት አብረሐም ገብረክርስቶስ በተባለ አደራዳሪ አማካኝነት ጉቦ እንዲሰጠው በመጠየቅ የሙስና ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት ተጠሪ የቀረበውን ማስረጃ የአመልካችን መከላከያ ማስረጃና በፍርድ ቤት ተጣርተው እንዲቀርቡ የተደረጉ ማስረጃዎችን በመመርመር የከፍተኛው ፍርድ አመልካች በነፃ እንዲሰናበት የሰጠውን ውሣኔ ተጠሪ በይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ፣ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በሥር የተደረገው ክርክር መሰረታዊ ይዘት ስንመለከተው ተጠሪ በአመልካች ላይ የቀረበውን አንደኛ ክስ ለማስረዳት ሶስት ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ አንደኛውን ለማስረዳት የቀረበው የመጀመሪያው የተጠሪ ምስክር ለተጠሪ የወንጀል ክስ በግል ተበዳይነት ስማቸው የተጠቀሰው አቶ ኡመር አልዬ ናቸው፡፡ ምስክሩ 1989 ዓ.ም በሊዝ ቦታ ገዝቶ የነበረ ቢሆንም በፍርድ ቤት ክርክር የነበረበት በመጀመሪያ ጉዳዩን የያዙት ዳኛ ሌላ ዳኛ የነበሩ መሆኑንና አመልካች ጉዳዩን የያዙት ዳኛ በእድገት ወደ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ከተዛወሩ በኋላ ማየት እንደጀመሩ ጉዳዩ ስለተጓተተብኝ ጉዳዩን ብርሃኑ ለተባለ ጠበቃ እንዳማከሩትና ጠበቃውም አብርሐም ገብረክርስቶስ የሚባለውን የተጠሪ ምስክር አመልካችን ስለሚያውቀው ይጨርስልሐል ብሎ ያማከረው መሆኑን አስረድቷል፡፡ ከዚህ በኋላ ምስክሩ ሌላውን የተጠሪ ምስክር አብርሃም ገብረክርስቶስ ደውሎ ለሆነ ጉዳይ እፈልግሐለሁ እንዳለውና ጉዳዩን ለመወሰን ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ) አመልካች እንደሚፈልግ አብርሃም ገብረክርስቶስ የነገረው መሆኑን፣ከአመልካች ቢሮ በመሄድ ገንዘቡ ስለሚበዛ እንዲቀንስለት እንደጠየቀው አመልካችም ስልክህን ስጠኝ እደውልልሃለሁ በማለት እንደጠየቀውና ምስክሩ ስልኩን ሰጥቶት እንደወጣ መስክሯል፡፡ ምስክሩ ከዚህ በኋላ ግንቦት 23 ቀን 1999 የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር እንዳመለከተ ገልፆአል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች ስልክ ደውሎ ተዘጋጅተሐል ወይ ብሎ እንደጠየቀውና ደሴ ሆቴል አካባቢ እንዲመጣ እንደነገረው ምስክሩም ለአመልካች መልሶ ስልክ እንደደወለለትና ደሴ ሆቴል ሄዶ እየጠበቀው እንዳለ አመልካች ስልክ ደውሎ ቆዳ ጃኬትና ነጭ ሸሚዝ ለለበሰ ሰው እንዲልክ የነገረው መሆኑን ምስክሩም በተነገረው ምልክት መሰረት የተላከውን ሰው ደሴ ሆቴል አግኝቶ ሰላሣ ሺህ ብር እንደሰጠው መሥክሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ምስክሩ በዚያው እለት ገንዘቡን ሰጥቶ ተመልሶ ቂራ አካባቢ እንደደረሰ አመልካች ስልክ ደውሎ ገንዘቡ ለምን ከብር 50,000(ሃምሳ ሺህ)እንደቀነሰ እንደጠየቀውና አስር ሺህ ብር ካልጨመረ እንደማያስወስንለት የሰጠው ገንዘብ እንደማይመለስ የገለፁለት መሆኑን ምስክሩም በሐሳቡ በመስማማት ቀደም ብሎ 30,000(ሰላሳ ሺህ ብሩን) የተቀበለው ሰው ደውሎለት ብር 10,000(አስር ሺህ ብር) እንደሰጠ መሥክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ምስክሩ ገንዘቡን የተቀበለውን ሰው አግኝቶት ዓለም ባንክ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ወደሚገኘው የተከሳሹ(አመልካች) መኖሪያ ቤት ውሣኔ ከመስጠቱ ከአንድ ቀን በፊት በግምት ከዘጠኝ እስከ አስር ሰዓት ባለው ጊዜ ሄደው አመልካች ከቤቱ ወጥቶ ተቀብሏቸው መኪና ውስጥ እንደገባ ብር 10,000(አስር ሺህ ብር) ምክስሩን ከዚህ በፊት ገንዘብ ለተቀበለው ሰው እንደሰጠና ሰውየውም ተቀብሎ ለአመልካች እንደሰጠው ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ውሣኔ እንደሰጠው ከዚህ በኋላ ለሥነ- ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት እንዳደረገ መሥክሯል፡፡አመልካች ለተጠሪ ምስክር ኡመር አልዬ ይደውልላቸው የነበረው ቁጥራቸው 0911-18-54-60 እና 0911-64-14-31 በሆኑ የሞባይል ስልኮች እንደነበርና የምስክሩ የሞባይል ስልክ ቁጥር 0911-20-00-79 መሆኑን አስረድተው የተመለሱ መሆኑን ከከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ የቀረበውን አንደኛ ክስ ለማስረዳት አቅርቦ በምስክርነት የሰማው አቶ አስማረ ገበየሁን ሲሆን አመልካችን ከተጠሪ ምስክር አብርሃም ጋር ያስተዋወቀው መሆኑን ከዚያ በኋላ ለአራት ወራት ለመስክ ሥራ መሄዱንና ከመስክ ሲመለስ አብርሃም አመልካች ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ጠይቋል በሚል ምርመራ እየተጣራበት መሆኑን ሲነግረው በመደናገጥ ለአመልካች ደውሎ የሰማውን ሲነግረው አመልካች በመቆጣት መረጃው ሐሰተኛ መሆኑን የማያውቀው ነገር ውስጥ እንዳይገባ እንደነገረው መስክሯል፡፡ ይኸው ምስክር አብርሃምን በመጠራጠር መረጃው የመነጨው ከእሱ አለመሆኑን ተከሳሹን (አመልካችን) ለማሣመን እንድችል አብርሃም መረጃውን በድጋሚ እንድነግረው በማድረግ የአብርሃምን ንግግር በሞባይል ቀድቶ ለአመልካች

እንዳሰማው አመልካች አብርሃም ወስላታ ነው አትመነው እዳለውና ከዚህ በኋላ አብርሃምን ያላየኸውን ያልሰማኸውን የምታወራው ለምንድን ነው ሁለተኛ አትደውል ብሎ የነገረው መሆኑንና የአመልካችና የአብርሃም ግንኙነት እንደተቋረጠ መሥክሯል፡፡ አብርሃምን የቀዳው አብርሃም ሣያውቅ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የፀረ ሙስና ኮሚሽን መርማሪዎች ጠይቀው ሞባይል ውስጥ የነበረውን ንግግር ቅጅ ወስደዋል በማለት የመሠከረ ነው፡፡

የተጠሪ የመጨረሻው ምስክር አቶ አብርሃም ገ/ክርስቶስ ሲሆን ይኸው ምስክር አመልካችን ቀደም ብሎ እንደሚያውቀውና አስማረ ገበየሁ የተጠሪ ምስክር አመልካችን እንዳስተዋወቀው ከገለፀ በኋላ መሐመድ የሚባል የተጠሪ የመጀመሪያ ምስክር የሆኑት የአቶ ዑመር አልዬ ልጅ ጋር ቀደም ሲል ጓደኝነት የነበረው መሆኑንና መሐመድ የሚባለው የዑመር አልዬ ልጅ አሁን አሜሪካን አገር የሚኖር መሆኑን ከገለፀ በኋላ መሐመድ የእኔና የአመልካች ጓደኞሞች መሆናችንን ያውቅ ስለነበር በመጀመሪያ የተጠሪ ምስክር ዑመር አልዬ አመልካች የያዘው ጉዳይ እንዳለው ሲነግረው የእኔና የአመልካች ግንኙነት ንፁህ ጓደኝነት ነው ብሎ እንደመለሰለትና በዳኝነት በያዘው ጉዳይ ማነጋገር እንደማይፈልግ እንደገለፁለት ይህንን ጉዳይ ሁለተኛ እንዳያነሳበት በመግለጽ እንደመለሱለት መሥክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የተጠሪ ምስክር ዑመር አልዬ ልጅ መሐመድ ከአሜሪካን አገር ደውሎ የጓደኛህ በችሎት ላይ እየሰደበው አባቴን አሞታል በማለት የነገረው መሆኑንና እሱም ለማጣራት ለአቶ ዑመር አልዬ ሲደውል ጓደኛህ ከባለጋራዎቼ ፊት በችሎት ስለሰደበኝ በዚህ ምክንያት ታምሜአለሁ ብሎ የነገረው መሆኑን ገልጿል፡፡ ይኸው ምስክር ይህንኑ ጉዳይ ደውሎ ለአመልካች እንደነገረውና ለአመልካች ስም ጥሩ እንዳልሆነ እንደገለፁለት አመልካችም አቶ ዑመር አልዬ ጉዳያቸው በተለየ መልኩ የተያዘ አስመስለው ችሎት ላይ ኦቨር አክት በማድረጋቸው እንደተቆጣቸው የገለፁለትና ቢሮ ሳካቸው አነጋግራቸዋለሁ እንዳለ መስክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የተጠሪ ምስክር ዑመር አልዬ አመልካች ቢሮ በመሄድ እንዳነጋገራቸው ጉዳዩን አመልካች በብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ሊይዝልኝ ነው በማለት አቶ ዑመር እንደነገሩትና ስለዚህ ጉዳይ የማውቀው የለኝም ብሎ ምስክሩ አቶ ዑመርን እንደመለሰሰላቸውና ስለዚህ ጉዳይ አመልካችን እንዳልጠየቀው አቶ ዑመር አልዬ ቤት ሲመጣ የለም ብለው እንዲመልሱት ለቤተሰቦቹ መናገራቸው ስልኩንም ማንሣቱን በማቆም ግንኙነቱ እንዳቋረጥ ከአቶ ዑመር አልዬ ጋር የሚከራከሩት ሙክታርና ሴኮ የሚባሉ ወንድማማቾች አመልካች ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ተቀብሎ ሊወስንብን ስለሆነ አመልካችን አናግርልን ብለው የጠየቁት መሆኑንና አመልካች ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋርጦ የነበረ በመሆኑ ለአመልካች እንዳልነገረው መመሥከሩን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል ተጠሪ አመልካች በመዝገብ ቁጥር 03453 በዳኝነት ተሰይሞ የነበረውና ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ውሣኔ የሰጠ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አስማረ ገበየሁ የተባለው የተጠሪ ምስክርና አብርሃም ገብረክርስቶስ የተባለው የተጠሪ ምስክር የተለዋወጡትን ንግግር ቅጅ የያዘ ሲ.ዲ በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ አመልካች አምስት የመከላከያ ምስክሮች ቃል ያሰማ ሲሆን ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች የመዝገብ ቁጥር 05016 የሰጠው ውሣኔ እንዲያያዝለት አድርጓል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት አንደኛ የተጠሪ ምስክር አቶ ዑመር አልዬ እና በአመልካች መካከል የስልክ ልውውጥ የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ከሚያዝያ 1 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም በተጠሪ ምስክር ዑመር አልዬና በአመልካች መካከል የተደረገ የስልክ ጥሪ መኖሩን አጣርቶ እንዲልክ ለቴሌኮሚኒኬሽን ተደጋጋሚ ትእዛዝ ሰጥቶ መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሸኝ ደብዳቤ ጋር ተያይዞ ስድስት ገጽ ማስረጃ ተልኮለታል፡፡ ከቴሌኮሚኒኬሽን በተላከው ደብዳቤ መሰረት የአመልካች ስልክ ነው በማለት የተጠሪ ምስክር አቶ ዑመር አልዬ ቁጥራቸውን የገለፃቸው ሞባይሎች ቁጥር 0911-18-54-60 የሆነው በአቶ ሰይድ አደም ዑመር ስም ቁጥሩ 0911-64-14-31 የሆነው በአመልካች ስም ያሉ መሆኑን ተረጋግጧል ከዚህ በተጨማሪ፡፡

- የተጠሪ ምስክር የሆነው የአቶ ዑመር አልዬ ነው የተባለው ቁጥሩ 0911-20-00-79 እና የአመልካች ስልክ ናቸው በተባሉት ቁጥራቸው 0911-18-54-60 እና 0911 40-90-99 መካከል የተደረገ የስልክ ግንኙነት ፍርድ ቤቱ በጠየቀው ጊዜ ውስጥ አለመኖሩንና ከተጠሪ ምስክር አቶ ዑመር አልዬ ስልክ ነው በተባለው ቁጥር 0911-20-00-79 የተከሳሹ ስልክ ነው ወደተባለው ቁጥሩ 0911-64-14-31 ወደሆነው

ሞባይል በፈረንጆች አቆጣጠር ጁላይ 8 ቀን 2007 ዓ.ም አንድ ጥሪ ጁላይ 21 ቀን 2007 ዓ.ም ሁለት ጥሪዎች በድምሩ ሶስት ጥሪዎች መደረጋቸው ተረጋግጧል፡፡

- ከዚህ በተጨማሪ የተከሳሽ ነው ከተባለው ቁጥሩ 0911 64-14-31 ከሆነው ሞባይል የተጠሪ ምስክር የአቶ ዑመር አልዪ ስልክ ነው ወደተባለው ቁጥሩ 0911-20-00-79 ወደሆነው ሞባይል የተደረገ የስልክ ጥሪ የሌለ መሆኑን በቀረበው ማስረጃ ተገልጿል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪ ምክስርና የግል ተበዳይ ነኝ የሚሉት አቶ ዑመር አልዪ አመልካች በስልክ ደውሎ ገንዘቡን እሱ በምልክት ለላከው ሰው አቀብያለሁ በማለት የሰጡት ምስክርነት ከአመልካች ወደ ተጠሪ ምስክር ስልክ የስልክ ጥሪ ያልተደረገ መሆኑ ከቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ የምስክሩ ቃል ታዓማኒነት የለውም በማለት አመልካች በነፃ እንዲሰናበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 149/2/ መሰረት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ የይግባኝ ችሎቱ መዝገቡ ለአስራ ሁለት ቀጠሮዎች የተቀጠረ መሆኑ በቴሌኮሚኬሽን የመጣው መረጃ የአቃቤ ሕግ ማስረጃ የሚያጠናክር ሆኖ እያለ ለጉዳዩ ግንኙነት የለውም መባሉ ተገቢ አይደለም የግል ተበዳዩ ቤቱ ድረስ መሄዳቸውን 10,000(አስር ሺ ብር) መስጠታቸው የመሰከሩ በመሆኑንና ምስክሩ እውነቱን ይመሰክራሉ ተብለው ስለሚገመቱ የአቃቤ ሕግ ማስረጃ አመልካች ወንጀሉን መፈፀሙን አረጋግጦል በማለት አመልካች በክሱ የተጠቀሰበትን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 408 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተላለፈ ጥፋተኛ ነው ብሎ በሰባት ዓመት ጽኑ እስራትና በብር 1000/አንድ ሺህ ብር/ መቀጮ እንዲቀጣ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ጥር 4 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በሕግ የተጣለበትን የማስረዳት ሸክም አልተወጣም፡፡ የአቃቤ ሕግ ማስረጃ ወንጀሉን አለመፈፀሜን የሚያስረዱ ናቸው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ችሎት ውሣኔ የሰጠው በአቃቤ ሕግ ምስክሮች የተረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ መሰረት በማድረግ ሣይሆን የራሱን የሕሊና ግምት በውሰድ ነው፡፡ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ የተገለፀው ፍሬ ጉዳይ እና ወንጀሉን የፈፀምኩ ስለመሆኔ ለማቋቋም ብቃት የሌላቸው ናቸው የተጠሪ ምስክር ከግል የነበራቸውን ጥላቻ መነሻ በማድረግ በሰጡት የሐሰት ምስክርነት መነሻ በማድረግ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የቅጣት ውሣኔም የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ያገናዘበ አይደለም የሚል ይዘት ያለው አስራዘጠኝ ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የሰበር ችሎቱን የሚጠይቀው የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ስህተት እንዲታረምለት ነው፡፡ አመልካች የግል ተበዳዩን ከአስራ ሁለት ቀጠሮ በላይ በማጉላላት የግል ተበዳይ ጉቦ እንዲሰጧቸው ያስገደዷቸው መሆኑን በማስረጃ ተረጋግጧል ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለህሊና ግምት ሣይሆን በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ መሰረት በማድረግ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም የሚል ይዘት ያለው ሰፊ የቃል ክርክር አቅርቧል አመልካች በቃል ክርክሩ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የግራ ቀኙ መካከል በሥር ፍርድ ቤት የቀረበው ክርክርና በተጠሪ በኩል የቀረቡትን ማስረጃ ይዘት የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ማስረጃ ተዓማኒነት በመመርመር ረገድ በመለያየት የሰጡት የተለያየ ፍርድ ይዘትና በሰበር አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ አመልካች በክሱ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት የፈፀሙ ስለመሆኑ በሕግ የተጣለበትን ሸክም ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም? የሚለውን ጭብጥ በወንጀል ጉዳይ ተከራካሪዎች ስላለባቸው የማስረዳት ግዴታ ኃላፊነት (Burden of proof) ፍርድ ቤቶች የተከራካሪዎቹን ማስረጃ ታዓማኒነት በሚመረምሩበት ወቅት ሊከተላቸው የሚገባቸውን መሰረታዊ የማስረጃ ሕግ መርሆችንና ሌሎች አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በዝርዝር ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ የከሳሽ(ተጠሪ) የማስረዳት ሸክምና ኃላፊነት የሚወጣው በምን ሁኔታ ነው? የሚለውንና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ነጥቦች መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ነጥብ አንድ ተከራካሪ የማስረዳት ሸክሙን ተወጥቷል ወይም አልተወጣም የሚለው ጭብጥ ለመወሰን የመጀመሪያው ማነፃፀሪያ ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ ለመመለሥ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣንና ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ሰጭ አካላት በትኩረት ሊመረምሩት የሚገባውን ጉዳይ ለማየት ያስችላል፡፡ በወንጀል ጉዳይ ወንጀል ተፈጽሟል በማለት የወንጀል ክስ የቀረበ ተከሳሽ የወንጀሉ ድርጊት ስለመፈፀሙ ብቻ ሣይሆን ወንጀሉ የተፈፀመበትን ጊዜ ወንጀሉ እንዴት እንደተፈፀመና ወንጀሉ በእነማን እንደተፈፀመ ዝርዝር ሁኔታዎችን ግልጽ በሚያደርግ መንገድ የማቅረብ ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡ በኢትዮጵያ የሕግ ሥርአትም አንድ የወንጀል ክስ ውስጥ ሊገለፁ የሚገቡ መሰረታዊ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 111 ተደንግጓል፡፡

የወንጀል ክስ የቀረበ ከሳሽ ጉዳዩን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነቱን ተወጥቷል ወይም አልተወጣም? የሚለው ጭብጥ ለመወሰን የመጀመሪያው የማነፃፀሪያና የመመዘኛ መስፈርት ራሱ ከሳሽ ያቀረበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ ነው፡፡ አንድ ድርጊት የተፈፀመ መሆኑን በመግለጽ ክስ ያቀረበ ወገን በክሱ የገለፀውን ፍሬ ጉዳይ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት አለበት የሚለው የማስረጃ ሕግ መርህ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ ጉዳዩን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነቱን ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም? የሚለው ነጥብ እልባት የሚሰጠው ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ ውስጥ የተገለፁትን ፍሬ ጉዳዮች ትክክለኛነት ተጠሪ የወንጀል ክሱን ለማስረዳት ባቀረባቸው የተለያዩ ማስረጃዎች የሚያረጋግጡና በወንጀል ክሱ ውስጥ የተገለፀው ፍሬ ጉዳይና ክሱን ለማስረዳት ያቀረቡት ማስረጃዎች እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉና ተያያዥነት ያላቸው ሆነው ሲገኙ ነው፡፡ በአጠቃላይ ካሳሽ ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ለጉዳዩ ያላቸው አግባብነት (Relevancy of Evidence) እና የክሳስ ማስረጃ የአስረጅነት ዋጋ ያላቸውና ታዓማኒነት ያላቸው መሆኑ የሚመረመረው ከሳሽ በወንጀል ክስ ማመልከቻው የገለፃቸውን ፍሬ ጉዳዮች መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ተጠሪም ክሱን የማስረዳት ሸክሙን(ክሱን የማስረዳት ግዴታውን) የተወጣ መሆኑ ወይም አለመሆኑ መመርመር ያለበት ተጠሪ በክሱ ማመልከቻው የገለፃቸውን ፍሬ ጉዳዮች እውነት መሆናቸውን በተጠሪ ማስረጃ የተረጋገጡ መሆኑንና ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ተደጋጋፊ እና እርስ በርሳቸው የማይቃረኑ መሆናቸውን መሰረት በማድረግ ማስረጃዎቹን በመመርመር ነው፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት ተመሣሣይ ይዘት ያላቸውን ማስረጃዎች ታዓማኒነት አስመልክቶ የተለያዩበት ዋናው ምክንያት የተጠሪ ማስረጃዎች እውነተኛ መሆናቸው መመርመር ያለበት ከምን አንፃር ነው በሚለው መስፈርት ላይ ከተጠሪ ክስ አንፃር ባለመመርመራቸው ነው፡፡ ተጠሪ በክሱ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 408 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተውን በመተላለፍ በሐምሌ ወር 1999 በመዝገብ ቁጥር 03453 ተከራካሪ የነበሩትን አቶ ዑመር አልዬ( የተጠሪ ምስክር) ብር 50,000(ሃምሣ ሺህ ብር) ይክፈል በማለት በሶስተኛ የተጠሪ ምስክር አብርሃም ገብረክርስቶስ በተባለ አደራዳሪ በኩል ጉቦ ጠይቋል የሚል ክስ አቅርቧል፡፡

የተጠሪ ክስ አመልካች በአብርሃም ገብረክርስቶስ በኩል ጉቦ ጠይቋል በሚል ሲሆን የግል ተበዳዩና አንደኛ የተጠሪ ምስክር አብርሃም እንዲያነጋግርልኝ አድርጌ ብር 50,000(ሃምሣ ሺህ ብር) አምጣ ተብለሐል ብሎ ነገረኝ በማለት የመሰከረ ሲሆን በወንጀል ክሱ አደራዳሪና ጉቦ ለአመልካች የተጠሪ ምስክርና የግል ተበዳዩ እንዲሰጥ ጠየቀ የተባለው ሶስተኛው የተጠሪ ምስክር አብርሃም ገብረክርስቶስ አመልካች የግል ተበዳይ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) ይሰጠኝ ብሎ ያልጠየቀው በመሆኑ በተቃራኒው አመልካች ስለያዘው ጉዳይ የአቃቤ ሕግ ምስክር የሆነው የግል ተበዳይ እንዳያነሳበት እንደነገረው የአቶ ዑመር አልዬ አሜሪካን አገር የሚኖር መሐመድ የተባለ ልጅ አባቴን ጓደኛህ በድሎት ታሞ ተኝቷል ብሎ እንደደወለለት እሱም ወደ አቶ ዑመር አልዬ ስልክ ሲደውል ከባለጋራዎቼ___ ፊት ሰደበኝ አዋረደኝ በዚህ ምክንያት ታምሜአለሁ ብለው እንደነገሩት እሱም አመልካችን ለስሙ ጥሩ እንዳልሆነና የተባለውን ስነግረው ምስክሩ በችሎት ከሥርአት ወጥተው ስለነበር እንደተናገራቸውና ቢሮ ላካቸው አነጋግራቸዋለሁ በማለት እንደነገረውና የተጠሪ አንደኛ ምስክር ዑመር አልዬ ከአመልካች ቢሮው ውስጥ እንዳነጋገራቸውና በብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ሊሰራልኝ ተስማምተናል ብለው እንደነገሩት አብርሃም ገብረክርስቶስ ስለዚህ የሚያውቀው የሌለ መሆኑን ገልፆ ከግል ተበዳይ ጋር የነበረውን ግንኙነት እንዳቋረጠ

መሥክሯል፡፡ በሌላ ጊዜ ከተጠሪ አንደኛ ምስክር ጋር የሚከራከሩ ሰዎች አመልካች ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ተቀብሎ ሊፈርድብን ነው ብለው እንደነገሩት መሥክሯል፡፡

ተጠሪ በክሱ የተገለፀውን ፍሬ ጉዳይ "አመልካች በአብርሃም ገብረክርስቶስ በኩል ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ጉቦ እንድሰጠው የግል ተበዳይ ዑመር አልዬን መጠየቁን ያስረዳልኛል" በማለት ያቀረበው የተጠሪ ምስክር አብርሃም ገብረክርስቶስ አመልካች በዚህ አይነት ጥያቄ ያላቀረበለትን የግል ተበዳዩ ሰደበኝ ብሎ ስሞታ ከተናገረ በኋላ ቢሮው ሄዶ እንዲያነጋግረው ከተደረገ በኋላ በብር 50,000(ሃምሳ ሽህ ብር) ሊይዝልኝ ተስማምተናል በማለት የግል ተበዳይ ራሱ ለተጠሪ ምስክር አብርሃም እንደነገረው መስክሯል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት ያቀረባቸው ምስክሮች ዕርስ በርሱ የሚቃረን ማስረጃ (contradictory evidence) የሰጡ መሆናቸውን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የተጠሪ ማስረጃ ዕርስ በርሱ የሚደጋገፍና በክሱ የተገለፀውን ፍሬ ጉዳይ የማያረጋግጥ በሆነ ጊዜና በተቃራኒው የተጠሪ ማስረጃና በክስ የተገለፀው ፍሬ ጉዳይ በሌላ የተጠሪ ማስረጃ እውነትነት የሌለው መሆኑ በተገለፀ ጊዜ ተጠሪ ክሱን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነትቱን በአግባቡ ተወጥቷል ከሚል መደመደሚያ ላይ መድረስ አይቻልም፡፡ ከዚህ አንፃር የሥር ፍርድ ቤቶች በተጠሪ ክስ የተገለፀውንና በግል ተበዳይ የተሰጠውን የምስክርነት ቃል ተጠሪ ክሴን ያስረዳልኛል በማለት ባቀረበው አብርሃም ገብረክርስቶስ በሰጠው የምስክርነት ቃል እውነትነት የሌለው መሆኑ የተገለፀ ሆኖ እያለ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ብይን መስጠቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ተጠሪ ባቀረበው ክስና በተጠሪ አንደኛ ምስክር ቃልና በተጠሪ ሶስተኛ ምስክር ቃል መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት በማየት ሣይመረምር ማለፉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተጠሪ ይህ ጉዳይ የፍሬ ጉዳይ ክርክር እንጅ የሕግ ስህተት አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

2. ተጠሪ አመልካች በክሱ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት በአጥጋቢ ማስረጃ የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 141 እና 149 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ተጠሪ ክሱን የማስረዳት ሸክሙን ተወጥቷል የሚባለው ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ታዓማኒነት ያላቸውና ክሱን ለማስረዳት የሚችል ሆነው ሲገኙ ነው፡፡ የማስረጃ ታዓማኒነት የሚለካው ማስረጃው በይዘቱ ወጥነት ያለውና ዕርስ በርሱ የሚፋለስ ፍሬ ጉዳዮችን ያልያዘ መሆኑን በመመርመርና በማስረጃው የተገለፀው ፍሬ ጉዳይ ያንኑ ክስ ለማስረዳት ከቀረቡት ሌሎች ማስረጃዎች ጋር የሚጣጣም ተደጋጋፊና ተመሣሣይ ፍሬ ጉዳይ ለማስረዳት የሚችል መሆኑን በማገናዘብ ነው፡፡

ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ አመልካች ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) በመዝገብ ተከራካሪ የነበሩት አቶ ዑመር አልዬ ከሶስተኛ የተጠሪ ምስክር(አብርሃም) አደራዳሪነት እንደሰጡት ጠይቋል ከማለት ውጭ አመልካች ከግል ተበዳይ ገንዘብ የተቀበለ መሆኑ መቼ እንደተቀበለና በማን በኩል እንደተቀበለ የገለፀ አለመሆኑን ከከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ እነዚህ ነገሮች ግልጽ በማድረግ ክሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 119 መሰረት ትእዛዝ መስጠት ነበረበት፡፡ ተጠሪ በወንጀል ክሱ በዝርዝር ያልገለፃቸው ፍሬ ጉዳዮች የግል ተበዳይና የተጠሪ ምስክር በሆኑት አቶ ዑመር አልዬ ተገልፆዋል፡፡ ይኸው ምስክር በአንድ ቀን አመልካች በራሱ ስልክ ሶስት የስልክ ጥሪ ያደረገለት መሆኑን በመጀመሪያ ተዘጋጅተሐል ወይ ብሎ እንደጠየቀውና ደሴ ሆቴል አካባቢ እንደነገረው ከዚያም ምስክሩ ወደ አመልካች ስልክ በመደወል ደሴ ሆቴል እየጠበቀው መሆኑን ነግሮት እንደዘጋ ከዚያ በኋላ አመልካች ስልክ በመደወል ቆዳ ጃኬትና ነጭ ሸሚዝ ለለበሰ ሰው እንዲልክ እንደነገረው ምስክሩ በተነገረው መሰረት ደሴ ሆቴል ሰውየውን አግኝቶ ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) እንደሰጠው ከዚያ በኋላ ተመልሶ ወደ ቂራ አካባቢ ሲደርስ አመልካች ለሶስተኛ ጊዜ ስልክ ደውሎ ገንዘቡ ለምን ከ50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) እንደቀነሰ እንደጠየቀውና አስር ሺህ ብር (10,000) ካልጨመረ እንደማይሰራለት እንደነገረው መሥክሯል፡፡ አመልካች ከግል ተበዳይና የተጠሪ ምስክር ጋር ግንኙኝነት ያደርግ የነበረው በስልክ መሆኑን የተጠሪ ምስክር ገልጿል፡፡ የተጠሪ ምስክር ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ ብር ) ማንነቱን ለማላውቀው ሰው ሌዘር ጃኬትና ነጭ ሸሚዝ የለበሰ የሚል ምልክት አመልካች በስልክ ደውሎ ነግሮኝ ሰጥቻለሁ ያለበትን ቀን ሰዓት አልገለፀም፡፡ ምስክሩ ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) ስሙ ማንነቱ ለማይታወቅ ሰው ሰጠሁ ባሉበት ቀን ብቻ አመልካች በእሱ የስልክ ሞባይል ሶስት ጥሪያዎችን እንዳደረገላቸው መስክረዋል፡፡ ይሕ የተጠሪ ምስክር በእምነታቸው መሰረት ቃለ መሐላ ፈጽመው ለፍርድ ቤቱ የመሰከሩት እና የገለፁት ፍሬ

ጉዳይ ነው፡፡ ሆኖም ይህንን ምስክርነት እውነት ነው ብሎ ለመቀበል ምስክሩ ቃለ መሐላ መፈፀማቸው ብቻ በቂ አይደለም፡፡ የምስክሩ ቃል ታዓማኒነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ከሚያዚያ 1 ቀን 1999 ዓ.ም የምስክሩ ጉዳይ ውሳኔ እስካገኘበት ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ከአመልካች ወደ ምስክሩ የስልክ ጥሪ ስለመደረጉ እንዳያረጋግጥ የቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን ተጠይቆ እንኳንስ በአንድ ቀን አመልካች ለተጠሪ ምስክር ሶስት ጊዜ ስልክ ሊደውል ይቅርና በሶስት ወራት ውስጥ አመልካች ለተጠሪ ምስክር ያደረገው የስልክ ጥሪ የሌለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡፡

ምስክሩ እንደ አውሮፖ አቆጣጠር ጁላይ 8 ቀን 2007 አንድ ጥሪ ጁላይ 21 ቀን 2007 ሁለት ጥሪዎች ወደ አመልካች ማድረጉ ምስክሩ ተጠሪ በቀን ሶስት ጊዜ ያሕል ደውሎ የት ቦታ እንደምጠብቀው ገንዘቡን ለማን እንደምሰጥና ለምን ገንዘቡ 30,000(ሰላሣ ሺህ) ሆነ አስር ሺህ ብር ጨምር በማለት አናግሮኛል በማለት የሰጠው ምስክርነት እውነት መሆኑን አያረጋግጥም፡፡ ስለዚህ የተጠሪ አንደኛ ምስክርና የግል ተበዳይ ነኝ ባዩ ዑመር አልዬ እውነት ነው በማለት ለፍርድ ቤት ስለወንጀሉ አፈፃፀም ያስረዱት ፍሬ ነገር ጭራሹኑ አመልካች የተደረገላቸው የስልክ ጥሪ የሌለ መሆኑ በተረጋገበት ሁኔታ ምስክሩ የሰጡት ቃል ታዓማኒነት ያለው ነው በማለት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መደምደሙ አንድ ማስረጃ ሊመርመርና ሊመዘን የሚገባው ከነ ሙሉ ይዘቱ እንጂ ተከሳሹን የሚጠቅመውን ክፍል ነጥሎ በማውጣትና ከሳሽ ካቀረበው ክስ ጋር የሚጣጣመውን የማስረጃ ክፍልና ይዘት ለይቶ በመያዝ መሆን እንደማይገባው በበርካታ አገሮች ተቀባይነት ያለውን የማስረጃ ታዓማኒነት ምርመራና ምዘና መርህ የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. በያዝነው ጉዳይ አመልካች ጋር ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ተስማማን በማለት ለሶስተኛ የተጠሪ ምስክር የተናገረው የግል ተበዳይ ነኝ ያለው አቶ ዑመር አልዬ እንደሆነ ሶስተኛ ምስክር መስክሯል፡፡ ሁለተኛው የአቃቤ ሕግ ምስክር ሰማሁ የሚለው ከሶስተኛው ምስክር ከአብርሃም ነው፡፡ ለአመልካች እንዲሰጥ በመጀመሪያ 30,000(ሰላሳ ሺህ ብር ) ቀጥሎ አስር ሺ.ር ብር /10,000/ በመጨረሻ አስር ሺህ ብር /10,000/ ከአመልካች መኖሪያ ቤት ሄጀ ሰጠሁ የሚለው ማንነቱን ያልገለፀው የለበሰውን ልብስ ብቻ በምልክት ከገለፀው ሰው ጋር ነው፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ጉቦ ጠየቀኝም ጉቦ ሰጠሁትም የሚለው ወሬ ብቸኛ ምንጭ የግል ተበዳዩ ዑመር አልዬ ሲሆን ሌሎቹ የግል ተበዳይ አወራን ወይም አብርሃም ሲያወራ ሰማሁ በማለት ሁለተኛ ምስክር የመሰከረ መሆኑንና የስሚ ስሚ ማስረጃ መሆናቸው ለመገንዘብ ይችላል፡፡

አንደኛ የተጠሪ ምስክርና የግል ተበዳይ አመልካች ጉቦ የጠየቀው በአብርሃም አደራዳሪነት እንደሆነ በምስክርነቱ የገለጸ ሲሆን አብርሃም የተጠሪ ምስክር ሆኖ በመቅረብ ይህ የግል ተበዳይ ምስክርነት በሚቃረን መንገድ መሥክሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ምስክሩ አመልካች በችሎት ሰደበኝ በሚል ምክንያት ታሞም እስከመተኛት ደርሶ የነበረ መሆኑንና ይህንን ሁኔታ የግል ተበዳይ ውጭ የሚኖር ልጅ ጭምር ሰምቶ ከውጭ አገር አብርሃምን ስልክ ደውሎ እንዳናገረው የተጠሪ ምስክር አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግል ተበዳይ ብር 30,000(ሰላሣ ሺህ ብር) ሰጠሁ ባሉበት አንድ ቀን ውስጥ ብቻ አመልካች በእሱ ስልክ ሶስት ጊዜ ደውሎ ነበር በማለት የሰጡት ምስክርነት ከሚያዚያ 1 ቀን 1999 እስከ ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ አመልካች ለተጠሪ ምስክርና የግል ተበዳይ ዑመር አልዬ ያደረገው የስልክ ጥሪ አለመኖሩን በማረጋገጫ የቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን ከሰጠው ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይህንን ያለፈው ከተጠሪ ምስክር ዑመር አልዬ ቃለ መሐላ ፈጽመው የሰጡት የምስክርነት ቃል እውነት ነው ተብሎ ይገመታል በማለት ነው፡፡ ሆኖም ከላይ የተገለፁት ማስረጃዎች ምስክሩ እውነተኛ አለመሆናቸውን የሚያሣዩ ግምቱን የሚያፈርሱ መሆኑን ሣይመረምር ማለፉ በራሱ ተገቢነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል አንድ ዳኛ የዳኝነት ሥራውን ከማናቸውም ሰው ጣልቃገብነት ነፃ ሆኖና ገለልተኛ ሆኖ ያከናውናል ተብሎ የሚገመት መሆኑ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መርህ ነው፡፡ ዳኛው በጉቦ ወስኗል የሚል ወገን ይህንኑ ፍሬ ጉዳይ ተዓማኒነት ያለው በቂ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡ ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ አመልካች በዳኝነት በያዘው ጉዳይ በችሎት አዋርዶኛል፣ጉዳዩን አጓትቷል የሚል ቅሬታ ያላቸው መሆኑ ተጠሪ ምስክሬ ነው በማለት ባቀረበው አብርሃም ገብረክርስቶስ በኩል ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ሰጥቻለሁ የሚለው አመልካች በዳኝነት ባየው ጉዳይ ተከራካሪ የነበረው አቶ ዑመር

አልዬ ከሰጠው የምስክርነት ቃል ውጭ አመልካች ይህንን ገንዘብ መቀበሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ተጠሪ አላቀበም፡፡ የተጠሪ ምስክር አቶ ዑመር አልዬ ገንዘቡን ሰጠሁ የሚሉበትና አመልካች ጠየቀኝ የሚሉበት ሁኔታ በተለይ አመልካች ስልክ ደውሎ የት ቦታ እንደሚጠብቁት ከዚያም ሁለተኛ ደውሎ ገንዘቡን ለማን እንደሚሰጡ ሶስተኛ ደውሎ ገንዘቡ ለምን አነሰ ብሎ እንደጠየቃቸው የሰጡት ምስክርነት ከአመልካች ወደ ምስክሩ የተደረገ የሥልክ ጥሪ አለመኖሩ ስለተረጋገጠ እውነትነት የሌለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይኸም የተጠሪ ምስክር የአቶ ዑመር አልዬ የምስክርነት ቃል ታዓማኒነት የሌለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሆኖ እያለ ከላይ በተገለፀው መንገድ ተጠሪ ክሱን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነቱን አልተወጣም በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ በመሻር በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 195/2/ለ1/ መሰረት ሽረናል፡፡

2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 195/2/ለ-2/ መሰረት አጽንተናል፡፡

3. አመልካች በነፃ የተሰናበተ ስለሆነ ከእስር እንዲፈታው ለማረሚያ ቤት ይፃፍ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

# ንብረት

የሰ/መ/ቁ 38681

ጥቅምት 3 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሀይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - አልቀረበም

**ተጠሪ፡-** እማሆይ ፀሐይቱ አምበሉ - ወኪል ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 12269 ሰኔ 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቀረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በምዕራብ ጐጃም ዞን አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በጅጋ ከተማ በ500 ካ/ሜትር ቦታ ላይ ያረፈውን ቤት ከሳሽና ሟች ባለቤቴ ቄስ አለሙ ከበደ ወ/ሮ አስካለ አድማሱ ከተባሉት ግለሰብ ገዝተን ባለሀብትነቱን በባለቤቴ ስም አዙረን ከዚያም ባለቤቴ ሲሞቱ በከሳሽ ስም ዞሮ ከነሐሴ 1975 እስከ ሰኔ 1998 ዓ.ም ድረስ ከሳሽ ግብር እየከፈልኩ ለ23 ዓመት በባለሀብትነት ይዤው የምገኝ ሲሆን ቤቱን መያዣ ለማድረግ የሚያበቃ ውክልና ሳይኖር ተከሳሽ መያዣ አድርጌዋለሁ በማለት በጨረታ ለመሸጥ የጋዜጣ ማስታወቂያ ያወጣ ስለሆነ ባንኩ ቤቱን ለመሸጥ ከሕግ ወይንም ከውል የመነጨ መብት ሳይኖረው ሊሸጥ ስለማይችል መብት የለውም ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃም ለተከሳሽ ደርሶ በሰጠው መልስ ክስ የቀረበበትን ቤት ተከሳሽ በሐራጅ ለመሸጥ የተነሳው ከአቶ ምንውየለት ዓለሙ ጋር ባደረገው የብድር ውል ተበዳሪው መጋቢት 4 ቀን 1987 ዓ.ም ለንግድ ሥራ ማስፋፊያ የሚያውሉት ብር 30 ሺህ በብድር ሲወስዱ መያዣ ስለሰጡ ነው፡፡ ይህም የሆነው ቤቱ በተበዳሪው ስም የተመዘገበ ስለመሆኑና ዕዳና ዕገዳ የሌለበት ስለመሆኑም የጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በሰጠው ማረጋገጫ መሠረትና መያዣውም በማዘጋጃ ቤቱ በመመዝገቡ ነው፡፡ ስለሆነም ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የምዕራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር የተነሳበትን ቤት ከሳሽና ባለቤታቸው የገዙት ነው ወይንስ የተበዳሪው የአቶ ምንውየለት ዓለሙ ነው? የሚል ጭብጥ መስርቶ ጉዳዩን በመመርመር ከሳሽ ከባለቤታቸው ቄስ ዓለሙ በላይ ጋር በትዳር አብረው በነበሩ ጊዜ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ከወ/ሮ አስካለ አድማሱ ላይ ገዝተናል ቢሉም ይህንን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካለማቅረባቸውም በላይ ስመ ንብረቱም ከወ/ሮ አስካለ አድማሱ ወደ ቄስ ዓለሙ በላይ ስለመዞሩ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ንብረቱ ባለበት አገር በሚገኘው በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ካልተጻፈ በስተቀር በ3ኛ ወገኖች ዘንድ ውጤት እንደሌለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2878 ላይ የተመለከተ ስለሆነ ከሳሽም በስማቸው ከ1975-1998 ዓ.ም ግብር የከፈሉ ስለመሆኑ ቢረጋገጥም የሽያጭ ውሉ ሥልጣን ባለው አካል ካልተመዘገበ ውጤት የሌለው ነው ካለ በኋላ አቶ ምንውየለት ዓለሙ ከተከሳሽ ገንዘብ ሲበደሩ ይህንኑ ቤት አስይዘው መሆኑን እንደዚሁም የጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ክርክር የተነሳበት ቤት የአቶ ምንውየለት ዓለሙ መሆኑን ያረጋገጠ ስለሆነ ከሳሽ የቤቱ ባለቤት ስለሆንኩ ተከሳሽ መብት የለውም ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ የማስረጃ ድጋፍ የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ጠቅላይ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ለክርክሩ መነሻ ምክንያት የሆነውን ቤት፣የይግባኝ ባይ ባለቤት የነበሩት ቄስ ዓለሙ በላይ ከወ/ሮ አስካለ አድማሱ ገዝተው ስም ንብረቱ መዞሩንና በስማቸው መመዝገቡን በደረሰኝ ቀጥር 29764 በሆነ ለውል ማስመዝገቢያ መክፈል የሚገባውን በማስከፈል የመዘገበ መሆኑን የጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የሰጠው ማስረጃ ያስረዳል፡፡ ከዚያ በኋላም ይግባኝ ባይና ባለቤታቸው የከተማ ቦታ ኪራይ ለመንግስት እየከፈሉ እስከ 1977 ዓ.ም ይዘውት እደቆዩና ከዚያም ቄስ ዓለሙ በላይ ሲሞቱ ይግባኝ ባይ በስማቸው በማዛወር የከተማ ቦታ ኪራይ ለመንግስት ሲከፍሉ እንደነበር የቀረቡት ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ ካለ በኋላ በሌላ በኩልም መ/ሰጭ ቤቱ የተበዳሪው የአቶ ምንውየለት ዓለሙ መሆኑን ያቀረበው ማስረጃ የጅጋ ከተማ ልዩ ቀበሌ ፍርድ ሸንጐ በማስረጃ አረጋግጦ በመስጠቱና የከተማው ማዘጋጃ ቤትም የተበዳሪው ቤት መሆኑን በማረጋገጥ የጻፈውን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ሆኖም ግን ቤቱ የተበዳሪው ቢሆን ኖሮ ጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እያለ የከተማ ቤትና ቦታን የማስተዳደርና የመመዝገብ ሥራ እንደሚሰራ እየታወቀ ከዚሁ አካል ቤቱ የተበዳሪው መሆኑን ማረጋገጥ እየተገባ በቀበሌ ፍርድ ሸንጐ በኩል ይህንን ማረጋገጥ ሥልጣን አለው ለማለት አይቻልም፡፡ የጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤትም ክርክር የተነሳበት ቤት የተበዳሪው መሆኑን ቢገልጽም የመያዣ ውሉን ተቀብሎ ስለመመዝገቡ ያላረጋገጠ ስለሆነ የመያዣ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3052 አግባብ መሠረት ተመዝግቧል ለማለት ስለማይቻል በዚህ ሁኔታ መ/ሰጪ ቤቱን መያዣ አድርጎታል ተብሎ የይግባኝ ባይ መብት ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ በአግባቡ አይደለም በማለት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ቤትና ይዞታው የይግባኝ ባይ ነው ሲል ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

መ/ሰጭም (የአሁን አመልካች) በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ የመያዣ መብት የለውም ተብሎ በአማራ ክልል ጠቅላይና በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መወሰኑ ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የዚህን ሰበር ችሎት ምላሽ የሚሻው የጉዳዩ ጭብጥ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ አመልካች የመያዣ መብት አለው? ወይንስ የለውም? የሚለው ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3041 ላይ እንደተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በቀጥታ ከሕግ፣ ከፍርድ ወይንም ከውል ሊመነጭ ይችላል፡፡ አንድ የመያዣ ንብረት በመያዣ ከተሰጠ በመብቱ ለመገልገል እንዲቻል መያዣው አግባብ ባለው አካል መመዝገብ እንዳለበትም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3052 ላይ ተመልክቷል፡፡

በዚህ ጉዳይ አቶ ምንውየለት ዓለሙ የተባሉት ተበዳሪ ከአመልካች ላይ ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) ሲበደሩ በጅጋ ከተማ ቀበሌ 01 ክልል የሚገኘውንና ቁጥር 835 የሆነውን ቤት በመያዣነት ሲያቀርቡ የከተማው ማዘጋጃ ቤት ይሄው ቤት በተበዳሪው በአቶ ምንውየለት ዓለሙ ስም እንደተመዘገበና ዕዳና ዕገዳም እንደሌለበት ለአበዳሪው ባንክ (ለአመልካች) በማረጋገጥ መያዣውንም የመዘገበ ስለመሆኑ በምዕራብ ጉጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካች ባቀረበው ማስረጃ መረጋገጡን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ የመያዣ መብት የለውም ወደሚል መደምደሚያ ለመድረስ የቻለው ከፍ ብሎ እንደተመለከተው ብድሩ በሚሰጥበት ወቅት ቤቱ የተበዳሪው መሆኑን ያረጋገጠው የከተማው ማዘጋጃ ቤት ሳይሆን የቀበሌው ፍርድ ሸንጐ ስለሆነ ይህ አካል ይህንን የማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን የለውም እንደዚሁም መያዣው ስለመመዘገቡ አልተረጋገጠም የሚሉ ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ሆኖም ግን የቀበሌው ፍርድ ሸንጐ የቤት ባለቤትነትን በማረጋገጥ ማስረጃ የመስጠት ሥልጣን የለውም ቢባል እንኳን ቤቱ በተበዳሪው ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝና ዕዳና ዕገዳም እንደሌለበት የከተማው ማዘጋጃ ቤት ከማረጋገጡም በላይ፤ ተበዳሪው አቶ ምንውየለት ዓለሙ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከፍኖተሠላም ቅርንጫፍ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውንና ቤት በዋስትና አስይዘው ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) ሲበደሩ መያዣውንም ተቀብሎ መመዝገቡንም የከተማው ማዘጋጃ ቤት ያረጋገጠ እንደመሆኑ መጠን ተበዳሪው የቤቱ ባለቤት ስለመሆኑ ሥልጣን ባለው አካል በተሰጠ ማስረጃ አልተረጋገጠም መያዣውም አልተመዘገበም መባሉ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩልም ተጠሪ የዚሁ ቤት ባለሀብት ስለመሆናቸው አጥብቀው የተከራከሩ ቢሆንም የንብረት ባለሀብትነት ከሕግ ወይንም ከውል የሚመነጭ ሲሆን ይህንኑ መሠረት አድርጎ በዚሁ ክርክር ባስነሳ ቤት ላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195(1) መሠረት ከመንግስት አስተዳደር አካል ባለሀብትነታቸውን በማወቅ የተሰጠ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ወይም ባለሀብትነትን የሚያሳይ ማስረጃ በማቅረብ ባለሀብትነታቸውን ያላረጋገጡ ስለሆነ በዚህ ሁኔታ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጠሪ የቤቱ ባለሀብት ናቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሳኔ ማጽናቱ የአመልካችን የመያዣ መብት የሚጻረርና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 12269 ሰኔ 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 32718 ሰኔ 29 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348(1) መሠረት ሽረናል፡፡
2. የምዕራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 14676 የካቲት 27 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348(1) መሠረት አጽንተናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 45161

ታህሣሥ 22 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** 1. እናኑ ጀንበሬ - ቀረቡ፡፡

2. ላቀች ጀንበሬ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** 1. የደሴ ከተማ ቀበሌ 03 ጽ/ቤት - ወኪል በአንተአምላክ አንተነህ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡

አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ የከሳሾች እናትና አባት በሕይወት በነበሩ ጊዜ በደሴ ከተማ ቀበሌ 01 ክልል በገዙት ቦታ ላይ ቁጥር 045 እና 046 የሆኑ ቤቶችን ሠርተዋል፡፡ ከእነዚህ ቤቶች ውስጥ ቁጥር 045 የሆነው ቤት በአዋጅ 47/67 በትርፍነት ያልተወረሰ ሲሆን ከሳሾች በማናውቀው ሁኔታ አንደኛ ተከሣሽ ለሁለተኛ ተከሣሽ አከራይቶት ይገኛል፡፡ ከሣሾች ቤቱ እንዲመለስልን ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አመልክተን ጉዳዩ አይመለከተኝም በማለት ይህንኑ በደብዳቤ አረጋግጠናል፡፡

ስለሆነም አንደኛ ተከሣሽ ቤቱን ይዞ ለሁለተኛ ተከሣሽ በማከራየት ላይ የሚገኘው በአዋጅ ባልተወረሰበት ሁኔታ ስለሆነ ተከሣሾች ቤቱን እንዲያስረክቡን ኪራይም እንዲከፍሉ ይወሰንልን ብለናዋል፡፡

የደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ ክስ የቀረበበት ቤት በአዋጅ ተወርሷል ወይንስ አልተወረሰም? የሚለውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በመመርመር ቀደም ሲል ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ይህንኑ ቤት አስመልክቶ አቤቱታውን ሳይቀበለው መቅረቱ ቤቱ አልተወረሰም ተብሎ ውሣኔ እንደተሰጠ የወረዳው ፍ/ቤት በመቁጠር ለከሣሾች ሊመለስ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የለውም ብሎ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ ሽሯል፡፡

የሥር ከሣሾችም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት አቤቱተው ለሰበር አይቀርብም ብሎ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

ለዚህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ የደሴ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አመልካቾች ከፕራይቤታይዜሽን ኤጀንሲ ውሣኔ አላሰጡም በሚል ምክንያት የወረዳው ፍ/ቤት ውሣኔ መሻሩ አግባብነቱን ለማጣራት አቤቱተው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙንም በቃል አከራክሯል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካቾች ክስ ያቀረቡት በውርስ የተላለፈልንን ቤት ተጠሪዎች ከሕግ ውጭ ይዘው ስለሚኙ ያስረክቡን በማለት ነው፡፡

ከሥር ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክርና በዚህ ችሎትም በተደረገው ማጣራት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ሁለተኛ ተጠሪ ይዘው የሚገኙት ከ1973 ዓ.ም. ጀምሮ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ባደረጉት የኪራይ ውል መነሻነት እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ ክርክር የተነሳበት ቤት ለረጅም ዓመታት በመንግሥት እጅ የቆየ ከሆነ አመልካቾች ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ተፈቅዶላቸው ባለንብረት ስለመሆናቸው ወይንም ደግሞ ከአዋጅ ውጭ ያለአግባብ ተወስዶብናል የሚሉ ከሆነም ለሚመለከተው አካል አቤቱታ አቅርበው ውሣኔ አግኝተው ባለመብት ስለመሆናቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ አመልካቾች በዚህ መልኩ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ካላረጋገጡ ደግሞ ከመነሻውም ቢሆን ክስ ባቀረቡት ነገር መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ለረጅም ጊዜ መንግሥት ተረክቦ ሲያስተዳድራቸው የነበሩ ቤቶች ሊመለስልኝ ይገባል በማለት ክስ የሚያቀርብ ወገንም ከላይ እንደተጠቀሰው በአዋጅ 47/67 የተፈቀደለት ስለመሆኑ ወይንም ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል አቤቱታ አቅርቦ ውሣኔ አንኝቶ ባለመብት መሆኑ ካልተረጋገጠ ክስ በቀረበበት ነገር ላይ መብት ወይም ጥቅም እንደሌለው እንደሚቆጠር ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 14094 የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ስለሆነም በተያዘውም ጉዳይ አመልካቾች ቤቱ ሊመለስልን ይገባል በማለት ክስ ያቀረቡት በቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ባላረጋገጡበት ሁኔታ ስለሆነ የደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ቤቱ ሊመለስላቸው ይገባል በማለት የሰጠውን ውሣኔ የደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በተለየ ምክንያት ቢሽረውም ከውጤት አኳያ ግን የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

የደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 0005 በ19/3/2001 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00751 በ14/5/2001 ዓ.ም. የሰጠውን ትዕዛዝ ምክንያቱን ለውጠን አጽንተነዋል፡፡

አመልካቾች ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ያላቸው መሆኑን ስላላረጋገጡ ክሱ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 43600

ጥር 05 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ዳዊት መስፍን

**ተጠሪ፡-** የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የባለሀብትነት መብትን መሰረት በማድረግ የቀረበው የቤት ይለቀቅልኝ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሳሽ

የነበረው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተው በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 118 ቀበሌ 05 ክልል የሚገኘውን፣ ቁጥር B-8/8008/30 በሚል የሚታወቀውን ቤት እንዲያስረክበው ይወሰንለት ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ ለማስረጃነትም ጥቅምት 23 ቀን 1985 ዓ.ም በከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ተሰጠኝ ያሉትን ቁጥር 18/31246 የሆነ የከተማ ቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አቅርበዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሳሽነት ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መልስ፤ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ ጉዳዮን በመጀመሪየ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677/1/ እና 1845 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት በብይን የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

እኛም አመልካች ጥር 22 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት የሰበር ማመልከቻ ያቀረቡትን ቅሬታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኙ ወገኖች ያሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ብይን እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታው ያነሷቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ለክሱ መነሻ የሆነው ንብረት /ቤት/ የማይንቀሳቀስ ሀብት በመሆኑ ክርክቱ መታየት ያለበት በንብረት ሕግ መሠረት ነው፡፡ ከንብረት ሕጉ አንፃር ሲታይም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 መሰረት የተሰጠኝ የንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አልመነከም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1196 በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት ደብተሩ ይሰረዝልኝ የሚል ጥያቄ ለሚመለከተው አካልም አልቀረበም፡፡ የሚመለከተውን የአስተዳደር ክፍልም ደብተሩ ሕገወጥ ነው አላለውም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1168 መሰረት ንብረቱ የኔ ነው የሚል ጠያቂ ወገን አልቀረቡም የሚሉ ናቸው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ይርጋን በሚመለከት የተያዘው ጭብጥ ላይ ተመስርቶ ክርክሩን አቅርቧል፡፡ በዚህም መሠረት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ድንጋጌ ስር የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነት አለው፡፡ ድንጋጌው ውልን መሰረተ አድርጐ ለሚነሳ ክርክር ብቻ ነው አግባብነት ያለው የሚለው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ግዴታዎች ከውል ባይመነጩም የውል ደንቦች ተፈፃሚ እንደሚሆንባቸው በሕጉ ተደንግጓል የሚሉትን የመከራከሪየ ነጥቦችን አቅርቧል፡፡

ግራ ቀኙ ወገኖች ከስር ጀምረው ያደረጉት ክርክር ተጠቃሎ ሲታይ የሚያስነሳው ጭብጥ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ የሚቀርበው የመፋለም ክስ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት አግባብ አለ ወይ? የሚለው ነው፡፡ ጭብጡ የሕግ ጭብጥ በመሆኑ መልስ ሊያገኝ የሚችለው በዚህ ረገድ አግባብነት ያላቸውን የፍትሐብሔር ሕጉን ድንጋጌዎችን በመፈተሽ ነው፡፡

አመልካች ክሱን የመሰረቱት የቤቱ ባለቤት መሆናቸውን ገልፀውና በዚህ ረገድ የባለቤትነተ ማረጋገጫ ደብተር እንዳላቸው በማመልከት ነው፡፡ ጥያቄው የቤቱ ባለሐብት በመሆኔ ከሕግ ውጪ ይዞብኝ የሚገኘውን ተጠሪ በፍርድ ኃይል እንዲለቅ ይደረግልኝ በሚል በግልጽ የቀረበ ነው፡፡ በመሆኑም ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1206 ድንጋጌ ስር የተመለከተውን የመፋለም ክስ (petitory action) የሚመለከት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ክሱ በዚህ መልክ ቢቀርብም ተጠሪ የክሱ መቅረብ አግባብ አለመሆኑን የሚመለከቱና ይጠቅሙኛል የሚላቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች በማንሳት መከላከያውን ያቀርባል ተብሎ ይገመታል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ለመከላከያ ይጠቅሙኛል ያላቸውን የመከራከሪያ ነጥቦችን ያቀረበ ሲሆን የመጀመሪያው ይርጋን መሰረት ያደረገ መቃወሚያ ነው፡፡ ለዚህ ክርክሩ በዋቢነት የጠቀሰው በፍትሐብሔር ሕጉ በአራተኛ መፀሐፍ "ስለግዴታዎች" በተደነገገው በአንቀጽ 12 ስር ካሉት ድንጋጌዎች ስር የሚገኘውን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ስር የተመለከተውን የአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ገደብ ነው፡፡ እንግዲህ ይህ ድንጋጌ የሚገኘው በፍትሐብሔር ሕጉ ሦስተኛ መፀሐፍ "ስለንብረት" ከሚለው አንቀጽ ስድስት እና "ስለግል ሐብት" ከሚለው ከአንቀጽ ሰባት ውጪ በመሆኑ ከተያዘው የይርጋ መቃወሚያ አግባብነት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ከማየታችን በፊት አግባብነት ያላቸው የንብረት ሕጉ ድንጋጌዎችን ሁኔታ መመርመሩ ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በመሰረቱ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ በሕግ የተከበረ መሆኑ፣ ይህ መብት የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም ወይም

የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረትን የመሸጥ፣ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን የሚያካትት ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት በአንቀጽ 40/1/ ስር በግልጽ አስቀምጧል።

የንብረት ሕጉ በጥቅሉ ሲታይ ደግሞ ንብረት ምንድን ነው?፣ ንብረት ወይም ሀብት የሚገኘው እንዴት ነው?፣ ሀብት ከአንድ ወደ ሌላ የሚተላለፈው በምን አግባብ ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ይመልስልናል። ባለሀብትነት ስለሚቀርበት ሁኔታ እና ስለባለሀብትነት ማስረጃም ዝርዝር ድንጋጌዎችን ያስቀምጣል። በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1126 ስር እንደተመለከተው ንብረቶች ግዙፍነት ያላቸው ሆነው ተንቀሳቃሽ የሆኑና የማይንቀሳቀሱ ተብለው ይከፈላሉ። ይህን ክፍፍል በመከተልም ሐብቶች የሚገኙበትን፣ የሚተላለፉበት፣ ባለሐብትነት ቀሪ የሚሆንበት አግባብ እንደዓይነታቸው የተለያዩ እንደሆኑ በሕጉ ተመልክቷል። የያዝነው የማይንቀሳቀስ ንብረትን /ሀብት/ የሚመለከት በመሆኑ በአብዛኛው ትኩረታችን በዚህ ላይ ይሆናል።

የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብት ከሚሆንባቸው ወይም የማይንቀሳቀስ ሀብት የሚገኝባቸው ሁኔታዎች በበፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1168/1/ ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን የሚያሟላ ይዞታ ስለመሆኑ ሕጉ ያሳያል። ሌላው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1184 እና 1186 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው ሲሆን በዚህ አግባብ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት መሆን የሚቻለው በሕግ ወይም በውል የወይም በኑዛዜ መሰረት ነው። በውል ወይም በኑዛዜ መሰረት ባለሐብት ለመሆንም የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ማስመዝገብ የግድ እንደሚል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1553 እስከ 1646 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ። ባለሐብትነት በእነዚህ መንገዶች ይገኛል ካልን ቀጥለን ደግሞ ባለሐብትንት ቀሪ የሚሆንበት አግባብ ማየቱ ተገቢ ይሆናል። በዚህ ረገድ አግባብት ያላቸው ድንጋጌዎች ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1188 እስከ 1192 ድረስ ያሉ ናቸው። እነዚህ ድንጋጌዎች ሁለቱንም የንብረት አይነቶች የሚመለከቱ ሲሆን ባለሀብትነት ቀሪ ስለሚሆንበት ይርጋም ይጨምራሉ። ከእነዚህ ውስጥ በሕግ መሰረት " ባለሀብትነቱ ለሌላ ሰው የሆነ ወይም የተላለፈ እንደሆነ" በሚል የተደነገጉት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1189 እና 1190 እና ባለሐብትነትን የሚያስቀር የይርጋ ዘመን በሚለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1192 ስር የተመለከተውን መጥቀስ በቂ ይሆናል።

እንደምንመለከተው እስካሁን ድረስ ካየነው ሂደት ንብረቱ የኔ ነው በሚል የመፋለም ክስ የሚመሰረተው ከሳሽ ሊያቀርባቸው የሚችላቸው ሕጉን መሰረት ያደረጉ የመከራከሪያ ነጥቦች ምን ሊመስሉ እንደሚችሉ ግንዛቤ እናገኛለን። ክርክር የንብረት ባለሃብትነትን መሰረት ያደረገ የመፋለም ክርክርን የሚመለከት በመሆኑ ወደሌላው መጽሐፍ ከመሻገራችን በፊት የንብረት ሕጉን መሰረት በማድረግ ሊነሳ የሚችሉ /የሚገባቸው/ የመከራከሪያ ነጥቦችን በቅድሚያ ማየትም ነው አግባብ የሆነው። ተጠሪ በተከሳሽነቱ ያቀረበው የመጀመሪያው የመከራከሪያ ነጥብ ይርጋን የሚመለከት በመሆኑ በንብረት ሕጉ የተቀመጠውን የይርጋ ድንጋጌ አስቀድሞ ማየቱ ተገቢ ይሆናል። ከላይ እንደገለጽነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1192 ስር የተመቀጠው ድንጋጌ ይርጋን የሚመለከት ነው። ባለሀብትነትን የሚያስቀር የይርጋ ዘመን" በሚል ርእስ ያለው ሆኖ ይዘቱም በሚንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለውን መብት በአስር ዓመት የጊዜ ወሰን /ይርጋ/ ቀሪ የሚሆንበትን አግባብ ያመላክታል። የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን ግን አያሳይም። ድንጋጌው ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ለያዝነው ክርክር እልባት ለመስጠት ሁለት አማራጮችን አነፃጽረን ማየት አስፈላጊ ነው። በዚህ ረገድ የተደነገጉትን የንብረት ሕግ ድንጋጌዎች ስንመለከት ባለቤትነት ከሁሉ የሰፋ መብት መሆኑን ያስገነዝባሉ። በሕግ የተቀመጡትን ገደቦችንና ወሰኖችን (Restriction and Limitations) ሳያልፍ የአንድ ንብረት ባለቤት በንብረት እንደፈለገው የመጠቀምና የመገልገል መብቱን ነፃነቱ በሕግ የተከበረለት ስለመሆኑም ድንጋጌዎቹ ያሳያሉ። ለባለሀብቱ የባለቤትነት መብት ከሚሰጣቸው መብቶች መካከልም ንብረቱ ያለእርሱ ፈቃድ ከሕግ ውጪ በሌላ ሰው ወይም ኃይል ከተወሰደ ንብረቱን ካለበት ድረስ በመከታተል የማስመለስ ወይም የመፋለም መብት አንዱ ስለመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1206 ድንጋጌ ያስረዳል። ከዚህ ድንጋጌ ይዘት፣ መንፈስና አቀራረጽ መረዳት የሚቻለው ሁለት መሰረታዊ የሆኑ ነጥቦችን ነው። ይኸውም የመፋለም መብት ባለሐብቱ ንብረቱን ማንም ያልተፈቀደለት ሰው ሕገ ወጥ በመሆነ መንገድ እንዳይነካ፣ በማንኛውም መልኩ ወደ ራሱ ወይም ወደ ሌላ እንዳይዛወር ወይም የንብረቱን ህልውና እና ደህንነት እንዳያውክ በኃይል ተጠቅሞ የማስወገድ (the right to apply force against any act of intervention or usurpation) መብት አንዱ ሲሆን ሌላው ደግመ ያለባለቤቱ ፈቃድ ወይም ከሕግ ውጪ ደንብረቱ ተወስዶ ከሆነ ባለቤቱ ይህን ንብረት የመከተልና እንዲመለስለት በዳኝነት የመጠየቅ መብት (Right to bring petitory action) ነው። የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1206 ባለሀብት የሆነ ሰው መብት ሳይኖረው እጁ ካደረገው ሰው ወይም ከያዘው ሰው ላይ

ሐብቱ ይገባኛል ሲል ለመፋለምና ማናቸውንም የኃይል ተግባር ለመቃወም ይችላል ሲል የማደነግገው እንዝህን ነጥቦች የሚያረጋግጥ ሲሆን የባለቤትነት መብት ከሁሉ የሰፋ መብት መገለጫ ከሆኑትም ዋናው ንብረቱን ተከታትሎ በዳኝነት የመጠየቅና የማስመለስ መብትን ለባለሃብቱ ማጐናፀፉ መሆኑ ይታመናል፡፡

ምንም እንኳ አንድ ሰው በሕግ ያገኘው ወይም በመተላለፍ የተጐናፀፈው የንብረት ባለቤትነት ቋሚነት /ዘላለማዊነት/ (prrpetutiy) እንደለው ቢታወንም በራሲ በባለመብቱ ፈቃድ ወይም ያለፈቃዱ ይኸው በአንድ ወይም በተወሰኑ ንብረቶቹ ላይ የባለቤትነት መብት የሚጠፋበት፣ ቀሪ የሚሆንበት ሁኔታ አለ፡፡ የባለቤትነት መብት ቀሪ (extinction of ownership) የሚሆንባቸው ሁኔታዎች በፍትሐብሔር ህጋችን ከቁጥር 1188 እስከ 1192 ድረስ መመስከታቸውን ከላይ ጠቅሰናል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1190 በተለይ ሲታዩ በማይንሰሳቀስ ንብረት ላይ የተቋቋመ የባለቤትነት መብት ቀሪ የሚሆነው የዚህ ሰው የባለቤትነት መብቱ ከማይንቀሳቀሰው ንብረት መዝገብ ሲሰረዝ /ሲፋቅ/ ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡

እንግዲህ ይህን ያክል በሕጉ ጥበቃ የተደረገው መበት ቀሪ የሚሆነው መቻ ነው? የሚለው ጥያቄ ከመብቱ ጠቅላላ ባህርይና ከሕግ አውጪው ሐሳብ አንፃር ቀጥተኛ፣ ተፈፃሚነትና አግባብነት ካለው የሕጉ ክፍል ጋር ተዛምዶ ታይቶ ተገቢ ምላሽ ሊሰጥበት የሚችለው ነው፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረት በሚመለከት የሚቀርበው የመፋለም ክስ (petitory action) ለመቃወም የሚቀርበው የይርጋ ክርክር መታየት ያለበት በንብረት ሕጉ መሰረት ነው የሚለውን አማራጭ ከያዝን የምንደርስበት መደምደሚያ ግልጽ ነው፡፡ ሕጉ የይርጋ ወሰን ያስቀመጠው ለሚንቀሳቀስ ንብረት ብቻ በመሆኑ የይርጋው መቃወሚያ ለማይንቀሳቀስ ንብረት የመፋለም ክስ አግባብነት የለውም ወደሚለው ነው የምንደርሰው፡፡ የተጠሪን ክርክር በመቀበል ሁለተኛውን አማራጭ ብንይዝ ደግሞ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት በሚመለከት የሚነባው የይርጋ መቃወሚያ ከንብረት ሕጉ ወጥቶ በሌላው የሕጉ ክፍል /አራተኛው መጽሐፍ/ ነው የሚታየው የሚለውን አካሄድ መከተል ሊኖርብን ነው፡፡ ይህ ግን በእርግጥም ሕጉ ሊደርስበት የፈለገው ምክንያታዊ የሆነ አካሄድ ነው ለማለት የሚያስቸግር ነው የሚሆነው፡፡ ምክንያቱም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1192 የሚንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት የሚቀረው በአስር አመት የጊዜ ገደብ ነው ለማለት ካስቀመጠ በኋላ ስለማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሐብትነት ቀሪ መሆን በዝምታ ያለፈው ለጉዳዩ ቀጥተኛ ፈተፃሚነት በሌለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ስር የተመለከተውንና ተመሳሳይ የሆነ የአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ ለማድረግ ነው ብሎ ማሰብ ምክንያታዊ ሊሆን አይችልምና፡፡

ቀደም ሲል ለማመልከት እንደሞከርነው ንብረቶች የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀስ በሚል በሁለት የሚከፈሉ ቢሆንም፣ የሚገኙበት፣ የሚተላለፉትበት እንዲሁም ባለሀብትነታቸው ቀሪ የሚሆኑበት አግባብ በንብረት ሕጉ ነው የሚገዛው፡፡ በዚህ ረገድ ሕጉ ያልታሰበበት ክፍተት ትቶአል ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም፡፡ ይልቁንም የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሚንቀሳቀን ንብረት በተለየ ሁኔታ የዘላቂነት /ነዋሪነት/ ባህሪይ ያለው እና ከትውልድ ወደ ትውልት በቋሚነት የሚተላለፍ በመሆኑ ቀሪ የሚሆንበት አግባብ ከሚንቀሳቀስ ንብረት የጠበበ እንደሆነ ሕጉ ፍልጓል የሚለው አስተሳሰብ ነው ከሕጉ መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1168 በተደነገገው መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት በእጁ አድርጐ እና በተከታታይም ለአስራ አምስት አመታት ያክል በስሙ ግብር የገበረ ሰው የንብረቱ ባለቤት ይሆናል ሲባል የቀድሞው ባለቤት ነኝ የሚል ቢመጣ እንኳን ባለሃብትነቱ ቀሪ ስለሚሆን ንብረቱን ሊያስመልስ አይችልም ማለት ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተቀመጠው የጊዜ ወሰን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ከተቀመጠው የረዘመ ነው፡፡ የንብረቱ ባለሀብት ነው በሚል አሳቤ ለረዥም አመታት በስሙ ግብር እየገበረ ንብረቱን ሲቆጣጠር የቆየው ሰው የሚያቀርበው መከራከሪያ ይህን ያክል ጥብቅ እይታ የሚፈልግ ከሆነ እንዲሁ ማለትም ግብር ሳይገብር የያዘው ሰው የሚያቀርበው መከራከሪያ በቀላል የሚታይ ነው ለማለት የሚያስቸግር ነው የሚሆነው፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች በአጠቃላይ ደምረን ስንመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነት ቀሪ የሚሆነው በይርጋ ሳይሆን በሌሎች ሁኔታዎች ይሆን ዘንድ የሕጉ ፍላጐት እንደሆነ ነው መገንዘብ የምንችለው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የቀረበላቸው ፍርድ ቤቶች ሊያደርጉ የሚገባው ጉዳይ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ክሱን ማቋረጥ ሳይሆን ክሱ እንዲቀጥል በማድረግ ከሳሹ በእርግጥም የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን ማጣራት፣ ባለቤትነት ከነበረም ሕጋዊ በሆነ ስርአት

የባለቤትነት መብቱ መቋረጥ አለመቋረጡን በማስረጃ በማጣራት እና ተገቢ የሆነውን ውሣኔም መወሰን ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የባለቤትነት ባሕርይ ቀጣይነት (perpetuity) በመሆኑ ፍርድ ቤቶች በዚህ የህግ ትርጉም መሰረት አንዴ ክሱ በይርጋ አይታገድም ከማለታቸው በፊት የክሱ መሰረታዊ ይዘት የባለቤትነት መፋለም (petitory action) መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከባለቤትነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ነገር ግን ከመፋለም መብት ውጪ ያሉ ሌሎተ ክሶች እነደሚጠይቁ መፍትሔ (remendy) እና ለክሱ ምክንያት እንደሆነው ጉዳይ አይነት /ጋብቻ፣ ውርስ፣ ሽያጭ ወ.ዘ.ተ../ በሌሎች ል ሕጎች የይርጋ ደንቦች የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የይርጋ ጉዳይ ክስ ይቀጥል አይቀጥል የሚለውን ነጥብ የሚመለከት ብቻ በመሆኑ ሙግቱ ከጠተናቀቀ በኂላ በፍሬ ነገሩ የሚሰጠው ውሣኔ በሕጉ ይዘትና ተከራካሪ ወገኖች በሚያቀርቡት ማስረጃ ጥንካሬ የሚወሰን መሆኑን የሰር ፍርድ ቤቶች የዚህን ውሣኔ የሕግ ትርጉም በዚሀ መንፈስ ሊረዱት ይገባል፡፡ ከላይ ከተሰጠው ትንታኔ አንፃር አቤቱታ የቀረበበት ብይን የንብረት ሕጉን መሰረተ ሐሳብ ያልተከተለ፣ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 93723 ጥር 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 6752 ታህሳስ 09 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የማይንቀሳቀስ ንብረት የመፋለም መብት ክስ (petitory action) በይርጋ ቀሪ አይሆንም ብለናል፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ወደ ክሱ ስረ-ነገር በመግባት ግራ ቀኙን ወገኖች ከአከራከረ በኂላ ተገቢ ነው የሚለውን ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 48699

ሚያዝያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አብዱራሒም አህመድ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ አምሣለ ጀመሪ - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** አቶ ፍርዱ ገበያሁ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 43302 ሰኔ 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ነሐሴ 28 ቀን 2001 ዓ.ም ተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ጉዳዩን አይቶ ጥር 23 ቀን 1998 ዓ.ም ተጠሪንና አመልካችን በማከራከር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም በውሣኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ቀርቦ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በዚህ ክርክር ተካፋይ ያልሆነችው የወ/ሮ አስካለ ወ/አማኑኤል ወራሾችን በክርክሩ ተካፋይ በማድረግ ውሣኔ እንዲሰጥ ትዕዛዝ በመስጠት ጉዳዩን መልሶ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የላከለት መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለመረዳት ችለናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በከፍተኛው ፍርድ ቤት በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የወ/ሮ አስካለ ወ/አማኑኤል ወራሾች እንዲቀርቡ በጋዜጣ ጥሪ አድርጎ ባለመቅረባቸው ጉዳዩን በሌሉበት አይቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ከዚህ በፊት ጥር 23 ቀን 1998 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በወ/ሮ አስካለ ወ/አማኑኤል ወራሾች እንደተሰጠ ይቆጠራል ውሣኔውን የሚያስቀይር ጉዳይ የለም በማለት መጋቢት 23 ቀን 2000 ዓ.ም ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች በወረዳ 20 ቀበሌ 40 በቁጥር 320 የተመዘገበው ቤት የአመልካች መሆኑን የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) ያቀረቡ መሆኑንና ካርታውም ማህተም ያለውና የአመልካች ስም የተፃፈበት መሆኑን በመግለፅ ቤቱ አመልካች ከአገር ከወጣ በኋላ አልተመለሰም በሚል የህዝብ ደህንነትና ጥበቃ አስተዳደር 1970 የተያዘ መሆኑን ገልፆና ጉዳዩ የሁለት ግለሰቦች ክርክር በመሆኑ የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለኝም ያለ በመሆኑ ቤቱ የአመልካች ነው፡፡ ተጠሪ ክርክር ያስነሣውን ቤት ከነቦታው ለይግባኝ ባይ ያስረክቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ "ይግባኝ ባይ (የአሁን ተጠሪ) ቤቱን እንዴት አገኙ የሚለው ጥያቄ እንዳለ ሆኖ መልስ ሰጭ (የአሁን አመልካች) መልስ ሰጭ ቤቱን ያስረክቡኝ በማለት ክስ ሲመሠርቱ በቅድሚያ ከሚመለከተው አካል ቤቱ የተሰጣቸው መሆኑን አረጋግጠው የቤት ባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ማቅረብ ይገባቸዋል፡፡" የሚል ትችት ከሰጠ በኋላ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ለማቅረብ በንብረቱ ላይ ጥቅም ወይም መብት ያላቸው መሆኑን አላስረዱም በማለት በትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 33(2) በመጥቀስ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ በመጀመሪያ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ በጭብጥነት ያልቀረበለትንና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ከዚህ በፊት በመዝገብ ቁጥር 46056 ግንቦት 15 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ ሽሯል፡፡ ተጠሪ ከዚህ በፊት የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 46056 በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ አላቀረበም፡፡ አሁን ባቀረበው ይግባኝ መነሻ በፊት ተሰጥቶ የነበረ ውሣኔ መሻር መሠረታዊ የሆነ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ስህተት ነው፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 46056 በክርክሩ ተካፋይ መሆን የሚገባቸውን ወ/ሮ አስካለ ወልደአማኑኤል በማስገባት ከተከራካሪዎች መካከል የቤቱ ባለሀብት ለመሆን የሚያስችለው ማስረጃ ያለው ማን ነው የሚለውን መዝገና እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) ጭብጥ መሥርቶ የመለሰለት ሲሆን ይህንን ውሣኔ ይግባኝ ሣይቀርብበት መሻሩ የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ለአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 የሰጠው ትርጉም የአዋጁንና የህጉን ድንጋጌ መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ አመልካች ካርታው ሣይለወጥ የቀረው በኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ በብድር መያዣነት ተይዞ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ ሣያስገባ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ቤቱን መንግስት ወርሶት ሲያስተዳድረው የነበረና ለወ/ሮ አስካለ ወ/አማኑኤል በምትክ ትቶ የተሰጠ ነው፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ቤት መታየት የለበትም፡፡ አመልካች ያቀረቡት የባለቤትነት ካርታ በ1953 ዓ.ም የተሰጠና በሚኒስትሩ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ያልፀደቀ በመሆኑ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የለውም ማስረጃውም በማህተም

ያልተረጋገጠ ነው፡፡ ቤቱ 1983 ዓ.ም በቅሎ ቤት አካባቢ ተፈጥሮ በነበረው ከፍተኛ ፍንዳታ ምክንያት የወደመ ሲሆን እኔ ከወ/ሮ አስካለ ወ/አማኑኤል ወራሾች ተከራይቼ ለጋራዥ እየተጠቀምኩበት እገኛለሁ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ክርክር ባስነሳው ቤት ተጠሪ እንዲለቅለት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል የክስ ምክንያትና መብትና ጥቅም አለው ወይስ የለውም በሚለው ጭብጥ እልባት ሊሰጠው የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህንን ጭብጥ እልባት ለመስጠት አመልካች ያቀረበው ክርክር ከአዋጅ ቁጥር 47/67 አጠቃላይ ግብና አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ማገናዘብና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ሌሎች የህግ ማዕቀፎች መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች በቀድሞው ወረዳ 20 ቀበሌ 40 ቁጥር 320 የሆነው ቤትና የቦታው ሥፋት 855 ካሬ ሜትር የሆነው ንብረት ባለቤት መሆኑንና ይህንንም ንብረቱን ለኮንስትራክሽንና ልማት ባንክ በመያዣነት የተያዘ መሆኑን በመግለፅ የተከራከረና ይህንንም የሚያሣዩ ማስረጃዎችን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ጉዳዩን በይግባኝ ላየው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከሰጠው ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች በንብረቱ ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለህ መሆኑን አላስረዳህም በማለት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 33(2) በመጥቀስ ውሣኔ የሰጠው የቤቱና የቦታው ካርታና ፕላን አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት የተሰጠና በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት በሚኒስትሩ አልፀደቀለትም በሚል ምክንያት ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 ተፈፃሚነትና ውጤት አዋጁ አጠቃላይ ግብና ዓላማና አግባብነት ካላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ መተርጎም አለበት፡፡ የአዋጁ ዓላማ አንድ ሰው ወይም ቤተሠብ ለመኖሪያ የሚሆነው አንድ ቤትና ለድርጅት የሚሆነው አንድ ቤት ካለው ይህንን አንድ ቤት መውረስና የመንግስት ማድረግ እንዳልሆነ በመግቢያው በሰፊው ተዘርዝሯል፡፡ የአዋጁ መሠረታዊ አላማ በአንቀጽ 3 ንዑስ አንቀፅ 3 "ትርፍ ቤት" በሚለው ትርጉም የሚሸፈንና ከአንድ በላይ የመኖሪያ ቤት ወይም የድርጅት ቤት ያለውን ሰው ቤትና ቦታ በመውረስ የመንግስትና የሕዝብ ንብረት ማድረግና በከተሞች የሚታየውን የመኖሪያ ቤት እጥረት ማቃለል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ቦታ ያለው ቤተሠብ ወይም ግለሰብ ሌላ መኖሪያ ቤት የሌለው ከሆነ በቦታው ላይ የባለይዞታነት መብት እንደሚኖረው በአዋጁ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 ከላይ የተጠቀሰውን መሠረታዊ ዓላማና አዋጁ ከመታወጁ በፊት አንድ የመኖሪያ ቤትና የይዞታ ቦታ ያላቸው ሰዎች በአዋጁ የተሰጣቸውን መብት ሙሉ በሙሉ በሚያሣጣ መንገድ መተርጎም የለበትም፡፡

ሚኒስትሩ በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረትና በአዋጁ አንቀፅ 35 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በአገሪቱ ከተሞች የሚገኙ ሁሉንም ቤቶች በመመዝገብ አዲስ የባለቤትነት ማስረጃ ለሁሉም በአዋጁ የመኖሪያ ቤት ባለቤት ለመሆን ለሚፈቀድላቸው ሰዎች ሰጥቶ አጠናቅቋል ብሎ መደምደም የማይቻል መሆኑ በዚህ መዝገብና በሌሎች መዝገቦች በቀረቡ ክርክሮች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሚኒስትሩ በነበረበት የማስፈፀም ችግር ወይም ቤቱ በባንክ በመያዣነት በመያዙ ወይም በሌሎች በፍርድ ቤት ሊጣሩና በማስረጃ ሊረጋገጡ በሚችሉ አጥጋቢ ምክንያቶች የቤቱን ባለሀብትነት በማፅደቅ አዲስ የባለቤትነት ማስረጃ ያልሰጠው ሰው በንብረቱ ውስጥ ገብቶ ያገኘውን ማናቸውንም ሰውና በአዋጅ መሠረት ሣይወረስ ቤቱን የያዘውን አካል በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 37 መሠረት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ሰጭ አካል ክስ አቅርቦ ከመጠየቅ የሚገድበው አይደለም፡፡ በያዝነው ጉዳይ ቤቱ በግለሰቦች እጅ በመሆኑ ጉዳዩን አከራክሮ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የሌለው መሆኑን የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በፅሑፍ ላመልካች ያሣወቀው መሆኑን ከከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ስለዚህ አመልካች ከእሱ ፈቃድና ስምምነት ውጭ በቤቱ ውስጥ ገብተውና ቤቱን ይዘው የሚገኙ ሰዎች ከቤቱ ለማስለቀቅና የቤቱ ባለሀብት መሆኑን በፍርድ ለማረጋገጥ በቤቱና መብትና ጥቅም ያለው መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 ተፈፃሚነትና ውጤት አጠቃላይ

አዋጅ ሊያሣካው ከሚፈልገው መሠረታዊ ግብ ከአዋጁ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 3 እና ከአዋጁ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 1 ጋር በተጣጣመ መንገድ መተርጎም ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች ጉዳዩ በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንደማይታይ ከተገለፀለት በኋላ የቤቱ ባለሀብት የነበረ መሆኑን የሚያሣይ ካርታና ፕላን በማስረጃነት በማቅረብ ቤቱ ያልተወረሰ መሆኑንና ከቤቱ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ቤቱን ለመጠቀም የሚያስችላቸው መብትና ጥቅም የሌላቸው በመሆኑ ቤቱን እንዲለቁለት የመጠየቅ መብት አለው፡፡ የቤቱ ባለቤትነት ካርታና ፕላን በሚኒስትሩ አለመፅደቁ በቤቱ ላይ መብትና ጥቅም የለውም ከሚለው መደምደሚያ ላይ አያደርስም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 የሰጠው ትርጉም መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ አመልካች በቤቱ ላይ መብትና ጥቅም ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው ብለናል፡፡
3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት አመልካች ቤቱ ላይ መብትና ጥቅም ያለው መሆኑንና ክስ ማቅረብ እንደሚችል በመገንዘብ በይግባኝ በቀረቡለት ሌሎች ነጥቦችንና ክርክሮችን በመመርመርና በመመዘን ውሣኔ እንዲሰጥባቸው ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 43081

ግንቦት 6 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ኂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ ሳሙኤል ጦኖሮ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- እነ ወ/ሮ አይሻ አርጌሳ (4 ሰዎች) - አልቀረቡም

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከ1957 ዓ.ም ጀምሮ በይዞታቸው ስር ያለው ቤት በእርጅና ምክንያት በመፍረሱ ለማደስ ስራ ሲጀምሩ አመልካች ስራው እንዳይጀመር ሁከት ስለፈጠሩ ሁከቱ እንዲወገድላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ ቤቱ የተጠሪዎች ሳይሆን የአመልካች ባለቤት ወላጆች መሆኑን፣የባለቤታቸው ወላጆች ወደ ውጪ

አገር ሲሄዱ ቤቱን የአመልካች ባለቤት እንዲያስተዳድሩ ውክልና መስጠታቸውን፣የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት በቤቱ በመጀመሪያ በኪራይ በኋላም ኪራይ መክፈል ሲያቅታቸው በነፃ እንዲኖሩበት መፍቀዳቸውን፣ አንደኛ ተጠሪ ባለቤት በ1995 ዓ.ም ታመው አዲስ አበባ ለህክምና እንደሄዱ በዛው መሞታቸውን፣ቤቱ በተጠሪዎች እጅ አለመኖሩን እና ቤቱ በእርጅና ምክንያት በመፍረሱ ፍራሹን ለጐረቤት በአደራ እንዲጠብቁ ማድረጋቸውን በመግለጽ ሁከት እንዳልፈጠሩ ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱን ጉዳዩን መርምሮ ቤቱ አንደኛ ተጠሪ በይዞታቸው ስር አድርገው እየተጠቀሙበት እንደነበር በምስክሮች ተረጋግጧል በማለት አመልካች የፈጠሩት ሁለት እንዲወገድ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለከምባታና ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡ በተመሳሳይ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጐታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው አንደኛ ተጠሪ አካባቢውን ለቀው ከሄዱ ከ15 ዓመት በላይ ቆይቶ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም፣የቤቱ ባለቤቶች የአመልካች ባለቤት ወላጆች ስለመሆናቸው በቂ የሰነድ ማስረጃ ቀርቧል፣እነሱ ወደ ውጪ ሲሄዱ ቤቶቹን የአመልካች ባለቤት እንዲያስተዳድሩት ውክልና ሰጥተዋል፣በዚህ መሰረት የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት እንዲኖርበት አድርገዋል እንዲሁም በቤት ውስጥ ተጠሪዎች ስላልነበሩ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻር በማለት ጠይቀዋል፡፡ ችሎቱም ክርክር ያስነሳው ጉዳይ የዳኝነት ገንዘብ ተከፍሎ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ሊታይ የሚገባው መሆን አለመሆኑን ይህ ቢታለፍ እንኳን አመልካች ሁከት ፈጥረዋል የመባሉን አግባብነት ማየት እንዲቻል አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ በዚህ መሰረት ተጠሪዎች ቀርበው ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በስር ፍ/ቤት ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት ከባለቤታቸው ጋር ከ1957 ዓ.ም ጀምሮ ይዘው የሚገለገሉበት ሁለት ክፍል ቤቶች በእርጅና ምክንያት በመፍረሳቸው ለማደስ ስራ ሲጀምሩ አመልካች ሁከት ፈጥረዋል በማለት ነው፡፡ አመልካች በበኩላቸው ቤቱ የአመልካች ባለቤት ወላጆች እንጂ የተጠሪዎች አለመሆኑና ተጠሪዎች የሚኖሩት በሌላ ቦታ እንደነበር እንዲሁም ቤቱ በተጠሪዎች ይዞታ ስር አለመሆኑ ተከራክረዋል፡፡ አንድ ሰው በይዞታው ላይ ሁከት ሲፈጠር ወይም ይዞታው በሃይል ሲነጠቅ ሁከቱ እንዲወገድ ወይም በሃይል የተወሰደው ነገር እንዲመለስ ክስ ማቅረብ የሚችል መሆኑን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1149 መመልከት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት ሁከት ተፈጥሮብናል በማለት በመሆኑ ሁከት ተፈጠረበት ያሉበት ንብረት በይዞታቸው ስር እንደሚገኝና በዚህ ይዞታቸው ላይ የሁከት ተግባር የተፈፀመበት ስለመሆኑ ማረጋገጥ ይገባቸዋል፡፡ ይዞታ ማለት ደግሞ አንድ ሰው አንድን ነገር በእጁ አድርጐ በእውነት የሚያዝበት ሆኖ ሲገኝ መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1140 የተመለከተ በመሆኑ ተጠሪዎች ክርክር ያስነሳውን ቤት በእጃቸው አድረገው ሲያዙበት የነበረ ስለመሆኑ የማስረዳት ሽክም አለባቸው፡፡ ከክርክሩ ሂደት እንደተረዳነው የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት ቤቱን እስከ 1995 ዓ.ም ድረስ ይኖሩበት እንደነበርና ከዛ በኋላ ታመው ለህክምና አዲስ አበባ ሲሄዱ ቤቱን ለሌላ ሰው አደራ ሰጥተው በመሄዳቸው ቤቱ በተጠሪዎች እጅ አልነበረም፡፡ ተጠሪዎች ለቀረበው የሰበር አቤቱታ በሰጡት መልስ ባለቤታቸው ታመው ወደአዲስ አበባ ሲሄዱ ቤቱን በአደራ ለሌላ ሰው በአደራ ሰጥተው መሄዳቸውን ግልፀዋል፡፡ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክርም አንደኛ ተጠሪ በአላባ ከተማ እየኖሩ ቤቱን እየተመላለሱ ይከታተሉ እንደነበር ምስክሮች ማስረዳታቸው ተመዝግቧል፡፡ ይህም የሚያሳየው ተጠሪዎች በቤቱ ውስጥ ይኖሩ ያልነበረ ወይም ቤቱን በእጃቸው አድርገው በእውነት የሚያዙበት አለመሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ቀድሞውንም ቢሆን ተጠሪዎች ቤቱን በእጃቸው አድርገው የሚያዙበት ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1149 መሰረት ሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚያቀርቡበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ይልቁንም የክርክሩ ሂደት ክርክሩ ከሁከት ጥያቄ ይልቅ ክርክር ያስነሱት ሁለት ቤቶች ባለቤት ማነው? በሚል ጭብጥ ላይ የሚያተኩር ሆኖ ነው ያገኘነው፡፡ ይህ ጥያቄ ደግሞ ንብረቱ ተገምቶ የባለቤትነት መፋለም ክስ የሚቀርብበት እንጂ የሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚቀርብበት ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪዎች በክሳቸው ሁከት ይወገድልኝ በማለት መጠየቃቸው ብቻ የተጠሪዎችን ትክክለኛ ጥያቄ በአግባቡ ሳያገናዝቡና ሳይረዱ ሁከት እንዲወገድ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00928 የካቲት 28 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣የከምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02325 ሐምሌ 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 23840 ኅዳር 23 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ሁከት እንዲወገድ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 42861

ሰኔ 28 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አጤነሽ አበበ - ጠ/ታረቀኝ ተፈራ

**ተጠሪ፡-** አቶ ማንተጋፍቶት አጥላው - ጠ/ደመቀ ሠገዴ - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

ለተጠሪ ባለቤት ያከራዩዋቸውን ቤት ባለቤታቸው ሲሞቱ ተጠሪ ይዘው ኪራይ ስላልከፈሉና ቤቱንም ለመመልቅ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ቤቱን እንዲለቁና ኪራዩን እንዲከፍሉ ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ ስለተወሰነ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 04 ክልል የቤት ቁጥር 34 በሆነው ቤት ውስጥ ያለው ለከብት ቤትነት ይጠቀሙበት የነበረውን ቤት በወር 100.00(መቶ ብር) ለተጠሪ ባለቤት አከራይተው ቆይተው ባለቤታቸው በ1992 ዓ.ም ሲሞቱ ተጠሪ ኪራይ ለመክፈልም ሆነ ቤቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ቤቱን እንዲለቁ ኪራይ የአንድ አመት ብር 1200.00(አንድ ሺህ ሁለት መቶ) እንዲከፍሉ እንዲሁም ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ቤቱን እስከሚያስረክቡ ድረስ የቤቱን ኪራይ እንዲከፍሉ ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ለቀረበባቸው ክስ ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ተጠሪ ቤቱን ከ1974 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን የያዙና ቤቱን በአመልካች ፈቃድ የያዙ ለመሆኑ አመልካች ስላሳዩ ክሱ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1149 መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ውሳኔው ፀንቶባቸዋል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው ለተጠሪ ሚስት ያከራዩትን የግል ቤታቸውን ተጠሪ እንዲያስረክቧቸው እንጂ ሁከት እንዲወገድላቸው ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ማለቱ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ችሎቱም ግራ ቀኙን ከሚያከራክረው ጉዳይ አኳያ ክሱ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149 በይርጋ ቀሪ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርምር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪም ቀርበው አመልካች በክሳቸው ቤታቸውን በተጠሪ በኃይል የተያዘባቸው መሆኑን ገልፀው ክስ የመሰረቱ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ስህተት የሌለበት መሆኑን በመግለፅና በፍሬ ጉዳዩ ላይ ያላቸውን ክርክር በመዘርዘር አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ክስ የመሰረቱት ተጠሪ ቤቱን ባለቤታቸው ከአመልካች ጋር ባደረጉት የኪራይ ውል ሰበብ ይዘው ለመልቀቅ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ኪራዩን ከፍለው ቤቱን እንዲያስረክቧቸው ነው፡፡ ከአመልካች ክስ በግልፅ ማየት የሚቻለው ክሱ ባለሃብት የሆኑበትን ቤት ለማስለቀቅ የቀረበ ባለቤትነትን የመፋለም ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በመልሳቸው አመልካች በክሳቸው ተጠሪ ቤቱን በሃይል መያዛቸውን በመግለፃቸው ክሱ ሁከትን የሚመለከት ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ክስ የመሰረቱት ባለሃብት የሆኑበትን ቤት ለተጠሪ ባለቤት አከራይተው የነበረ ቢሆንም ተጠሪ በዚህ ሰበብ ይዘው አለቅም በማለታቸው ቤቱን እንዲለቁ እንጂ ይዞታዬን በሃይል አስለቅቀውኛል በሚል ያቀረቡት ክስ የለም፡፡ በሃይል ይዘዋል ማለታቸው ብቻ ክሱን የሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚያሰኘው አይደለም፡፡ ባለሃብት የሆነው ሰው መብት ሳይኖረው እጁ ካደረገው ሰው ወይም ከያዘው ሰው ላይ ሃብቱ ይገባኛል ሲል ለመፋለም እና ማናቸውንም የሃይል ተግባር ለመቃወም እንደሚችል ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1206 መገንዘብ ይቻላል፡፡ የስር ፍ/ቤት ግን የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው ይዞታን የሚመለከተውን የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149"ን" መሰረት አድርጎ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ይዞታው በሃይል የተወሰደበት ወይም ሁከት የተፈጠረበት ሰው ለሚያቀርበው ክስ ነው፡፡ ይዞታና ባለቤትነት የሚመለከቱ ጉዳዮች የተለያዩ እንደመሆናቸው የሚሸፈኑት በተለያዩ የህግ ድንጋጌዎች ነው፡፡ በተያዘውም ጉዳይ አመልካች ክስ የመሰረቱት ባለቤትነትን የሚመለከት በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በይዞታ ድንጋጌዎች ጉዳዩን አይቶ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ሲል መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በዋናው ጉዳይ ላይ ዝርዝር ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም ዋናው ጉዳይ በስር ፍ/ቤት ክርክር ተደርጎበት የተወሰነ ባለመሆኑ በአሁኑ ደረጃ የሚታይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 70007 ታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 65433 ጥቅምት 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም ብለናል፡፡ በመሆኑም በፍሬ ጉዳዩ ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሰረት ጉዳዩን ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. *48048*

ሐምሌ *22* ቀን *2002* ዓ.ም

***ዳኞች፣*** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

***አመልካች፣*** ወ/ሮ ገብርኤላ ኒካላ ቶማስ ናክሶ - ጠበቃ አስቴር አርአያ ቀረቡ

***ተጠሪ፣*** የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ሚካኤል ጌታቸው ቀረቡ

***ፍ ር ድ***

አመልካች ተጠሪ በአደራ ያዘ የሚሉትን ቤታቸውን እንዲመልስላቸው ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በመባሉ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የአባታቸው ንብረት የነበረና በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 10 ክልል ውስጥ የሚገኘው ፎቅና ምድር የሆነ የመኖሪያና የድርጅት ቤት አባታቸው ሲሞቱ ልጆቻቸው በአገር ውስጥ ባለመኖራቸው የቤቶቹን ቁልፍ በግሪክ ኤምባሲ እጅ ቆይቶ በመጨረሻ ተጠሪ ቤቱን ከነንብረቱ ወራሾች እስኪመጡ ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በአደራ ተረክቦ በማከራየት ላይ የሚገኝ በመሆኑና የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴርም ቤቱን ተጠሪ ተረክቦ ወራሾች ሲመጡ ቤቱን ባለበት ሁኔታ ለወራሾች እንዲያስረክብ ትዕዛዝ የሰጠ በመሆኑና አመልካችም ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ቢቀርቡም ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ቤቱን በቤቱ ውስጥ ከነበሩት ንብረቶች ጋር እንዲያስረክባቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም አመልካች ቤቱን የሚመለከት የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስላላቀረቡ የመክሰስ መብት የላቸውም እንዲሁም ክሱ የቀረበው ክርክር የተነሳበትን ቤት ተጠሪ ከያዘው ከአስር አመት በኃላ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው የሚሉ የመጀመሪያ መቃወሚያዎች አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱ ቀደም ስል አመልካች ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት ክሱን ውድቅ ያደረገ ሲሆን አመልካች እስከ ፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ቀርበው ተከራክረው በቤቱ ላይ መብት ወይም በጥቅም ስላላቸው ፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራቀኙን አከራክሮ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩ ለስር ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡ በዚህ መሠረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በድጋሚ ካየ በኃላ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677/1/ መሠረት ግዴታዎች ከውል የተገኙ ባይሆኑም በውል ህግ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ስለሚሆኑና አመልካች በውርስ የሚገኝ ንብረት ያለአግባብ በተጠሪ ተይዞብኛል ብለው ያቀረቡት የመብት ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 መሠረት በአስር አመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ሲገባው ከ25 አመት በላይ ቆይተው ያቀረቡ በመሆኑ ጥያቄው በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡት ይግባኝም ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ብይን ላይ ነው ፡፡ የአመልካች ዋነኛ ቅሬታ ተጠሪ ቤቱን የተረከበው ወራሾች እስከሚመጡ በአደራ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ በዚህ መሠረት ችሎቱ የግራቀኙን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ ተጠሪ በክርክሩ የአመልካች አባት የሞቱት በ1973 ዓ.ም በመሆኑና አመልካች ክስ የመሠረቱት በ1998 ዓ.ም በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1677/1/ እና 1845 መሠረት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ በአግባቡ ነው ብሏል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው አመልካች ክስ የመሠረቱት የአባታቸውን ንብረት አባታቸው ሲሞቱ ወራሾቻቸው እስከሚመጡ ተጠሪ በአደራ ተረክቦ እያስተዳደረው የቆየ በመሆኑና አመልካች ወራሽነታቸው አረጋግጠው ስለቀረቡ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስረክባቸው ነው፡፡ ስለሆነም የአመልካች ጥያቄ በይዘቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 999 "ን" መሠረት ያደረገ የወራሽነት ጥያቄ ሳይሆን ተጠሪ በአደራ ተረክቦ የሚያስተዳድረውን ቤት እንዲያስረክብ የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የአመልካች ጥያቄ መታየት የሚገባው አደራን በሚመለከቱ ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ በመሆኑም የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ መሆን አለመሆኑን ስለአደራ ከተመለከቱት የፍ/ብ/ሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ እንመለከታለን፡፡ አደራ ማለት አደራ ተቀባዩ የአደራ አስቀማጩን እቃ ተቀብሎ በአደራ ጠባቂነት እንዲያስቀምጥለት የሚገባ የውል ግዴታ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2779 ይናገራል፡፡ አደራ ተቀባዩም እቃውን ይዞ የሚጠብቅ እንጂ የእቃው ባለቤት ሆኖ የሚቆየው አደራ ሰጪው ነው /የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2781/1/፡፡ በሌላ በኩል አደራ ተቀባዩ በአደራ የሚጠብቀውን እቃ መመለስ ስለሚገደድበት የጊዜ ገደብ ስንመለከት አደራ ተቀባዩ በአደራ የተቀበለውን እቃ የሚመልስበት የጊዜ ገደብ በውሉ ተመልክቶ ከሆነ ይህ ጊዜ ሲያበቃ እቃውን መመለስ የሚገባው ሲሆን /የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2781/2/ ይመለከቷል/ በውሉ ላይ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ ከሌለ ግን አደራ ሰጪው እንደጠየቀ ወዲያውኑ እቃው እንደሚመልስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2989/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ የህጉ ድንጋጌ አደራ ተቀባዩ እቃውን የሚመልስበት የጊዜ ገደብ ከሌለው በቀር አደራ ሰጪው በአደራ እንዲቀመጥ የሰጠው እቃ ያለምንም የጊዜ ገደብ በማንኛውም ጊዜ እንዲመለስለት ለመጠየቅ እንደሚችል መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች የሚከራከሩት ተጠሪ ቤቱን በአደራ የያዘው ወራሾች እስከሚመጡ በማለት ነው፡፡ ከዚህም ክርክር ተጠሪ በአደራ ተረከበ የተባለውን ቤት የሚመልስበት የጊዜ ገደብ ተወስኖ አለመቀመጡን መረዳት የሚቻል ነው፡፡ ተጠሪም የጊዜ ገደብ ተወስኖ ተቀምጧል በማለት ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ቤቱ እንዲመለስላቸው ይርጋ ሳያግዳቸው በማንኛውም ጊዜ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ በእርግጥ ተጠሪ በዚህ የሰበር ችሎት በተደረገው የቃል ክርክር ቤቱን በአደራ መያዛችንን በስር ፍ/ቤት አላምንም በማለት ተከራክሯል፡፡ ይህ ችሎትም

ቢሆን የአመልካች ክስ አደራን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በይርጋ አይታገድም አለ እንጂ ተጠሪ ቤቱን በአደራ ይዟል ወደሚለው መደምደሚያ ላይ አልደረሰም፡፡ ተጠሪ ቤቱን አመልካች በክሳቸው እንደገለፁት በአደራ የያዘው ነው ወይስ አይደለም? ቤቱንስ ሊያስረክብ ይገደዳል? ወይስ አይገደድም? የሚለው ክርክር ወደፊት ፍ/ቤቱ የግራቀኙ ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የሚወሰነው ነው፡፡

ሲጠቃለል የአመልካች ክስ ተጠሪ በአደራ የያዘውን ንብረት እንዲመልስላቸው ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤት ይህንን የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በአግባቡ ሳይረዳ ክሱ የወራሽነት ጥያቄን የሚመለከት ነው በማለት ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸውን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677/1/ እና 1845 "ን" መሠረት በማድረግ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ሲል የሰጠው ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ***<u>ው ሣ ኔ</u>***

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 48823 የካቲት 25 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 45911 ሰኔ 17 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ክስ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ብለናል፡፡ በመሆኑም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ቤቱን በአደራ የያዘው ነው? አይደለም? ቤቱንስ ሊያስረክብ ይገደዳል? አይገደድም? የሚለውን ጉዳይ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ነው ያለውን ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሠረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ም.አ

የሰ/መ/ቁ. 48783

ሐምሌ 27 ቀን 2002 ዓ.ም

***ዳኞች፣*** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

***አመልካች፣*** ወ/ሮ ሶፊያ ሁሴን - ጠ/አሉወርቅ ደጀኔ ቀረቡ

***ተጠሪዎች፣*** 1. የአራዳ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር - ነ/ፈጅ ሰሎሞን ተመቸው --ቀረቡ

2. አቶ ገዛኸኝ ሀብቴ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የመተላለፊያ መንገድ የማግኘት ጥያቄ አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአመልካች ከሣሽነት ነው የዳኝነት ጥያቄያቸውም የመተላለፊያ መንገድ ስለጠበባቸው ለአስተዳደሩ አመልክተው ከሁለተኛ ተጠሪ 1.10 ሜትር ተቀንሶ መንገድ እንዲያገኙ በአስተዳደሩ ከተወሰነ በኃላ ባልታወቀ ምክንያት አፈፃፀሙ በአንደኛ ተጠሪ ስለታገደ እና ሁለተኛ ተጠሪም የፈረሰውን አጥር መልሶ እያሰራ ስለሆነ ሁከት ተወግዶ በቀድሞ የአስተዳደሩ ውሣኔ መሠረት መንገዱ እንዲከፈት እንዲወሰን የሚል ነው፡፡

አንደኛ ተጠሪ ሥር ፍ/ቤት የሰጠው መልስ የአስተዳደሩ ውሣኔ አፈፃፀም በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ከሚያደርስው ጉዳት አንፃር ቴክኒካዊ መፍትሔ በአስተዳደሩ ባለሙያዎች ቀርቦ አመልካች ባለመስማማታቸው ሊፈጸም ያልቻለ መሆኑን ሲገልፅ በሁለተኛ ተጠሪ በኩል ሥር ፍ/ቤት የቀረበው መልስ ለሚፈርሰው አጥርና ቤት እንዲሁም ለሚቀንስበት ይዞታ አመልካች ካሣ እንዲከፍሉ በአስተዳደሩ የተሰጠውን ውሣኔ ባለመፈፀማቸው አፈፃፀሙ እንዲታገድ መደረጉ በአግባቡ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1221 በተደነገገው መሠረት አመልካች /የሥር ከሣሽ/ በቂ መተላለፊያ ለማግኘት ለባለይዞታው ተገቢውን ማካካሻ መክፈል ሲገባቸው ይህንን ለመፈጸም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው መንገድ እንዲከፈትላቸው ማስገደድ አይችሉም በማለት የዳኝነት ጥያቄውን ውድቅ አድርጓል፡፡

የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና የሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ውሣኔ አፅንተዋል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ሲሆን የአመልካች ጠበቃ ጳጉሜ 2 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት አቤቱታ የመተላለፊያ መንገዱን አጠር ለማስገመት ለባለሙያ ሃምሣ ብር /50/ አመልካች መክፈላቸውን ገልፀው ከሁለተኛ ተጠሪ ይዞታ ላይ ለሚቀነሰው 1.10 ሜትር የአጥር ግምት ኪሣራ ለሁለተኛ ተጠሪ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆናቸውን ጠቅሶ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ተሽሮ ሁለተኛ ተጠሪ አጥር እንዲያፈርስ እንዲወስን ጠይቋል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ አመልካች የጉዳት ኪሣራ እከፍላለሁ እያሉ የመተላለፊያ መንገድ መከልከላቸው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ተጠሪዎች ባሉበት ለማጣራት ተጠሪዎችን አስቀርቧል፡፡ ነ/ፈጅ ስለአንደኛ ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች ሥር ፍ/ቤት ላይ

ማካካሻና የአጥር ግምት ለመክፈል ፈቃደኛ አልነበሩም ፍርድ ቤቶቹም ይህንኑ አረጋግጠዋል፤ በዚህ ሰበር ላይ የቀረበው አዲስ ክርክር ነው በማለት ኪሣራ ተወስኖ መዝገቡ እንዲዘጋ ጠይቋል ሁለተኛ ተጠሪ በበኩሉ የመተላለፊያ መንገድ ለመክፈት በአመልካች በኩል እንዲፈፀም የቀረበውን መፍትሄ ባለመፈፀም ግዴታቸውን ሳይወጡ ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ሲል ተከራክሯል፡፡

እኛም የግራቀኙን ክርክር እና ሕጉን በማገናዘብ መርምረናል፡፡ ከሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መረዳት የተቻለው አመልካች መንገድ እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ጥያቄ በአስተዳደሩ ተቀባይነት አግኝቶ በተጓዳኝ ደግሞ አመልካች ሊፈጽሙት የሚገባ ግዴታ በአስተዳደሩ በኩል የተወሰነ ስለመሆኑ ነው፡፡ በአስተዳደሩ የተወሰነው የኪሣራ ገንዘብ ለመክፈል አመልካች ፈቃደኛ መሆናቸውን በሰበር አቤቱታ የገለፁ ሲሆን በተጠሪዎች በኩል የቀረበው ክርክር አመልካች ፈቃደኛ እንዳልነበሩ በሥር ፍ/ቤት ተረጋግጧል የሚል ነው፡፡ በእርግጥም አመልካች በአስተዳደሩ የተወሰነውን ለመፈጸም ፈቃደኛ ያለመሆናቸው የሥር ፍ/ቤት በውሣኔው አረጋግጧል፡፡ አመልካች እዚህ ሰበር ችሎት ላይ ያቀረቡት ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ ሥር ፍ/ቤት ያልተረጋገጠ በመሆኑ በዚህ ደረጃ ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ግዴታቸውን ባልተወጡበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔን መቃወማቸው በሕጉ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘንም፡፡

የሥር ፍ/ቤት በውሣኔው በግልፅ ያመለከተው አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1221 መሠረት ተጠሪ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተገቢውን ካሣ ሳይከፍሉ ተጠሪ መንገድ እንዲሰጣቸው ሊያስገድዱ እንደማይችሉ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው አመልካች በአስተዳደሩ የተወሰነው የመካካሻ ግዴታ ሳይወጡ ተጠሪን ማስገደድ አይችሉም የሚለው የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ሕጉን መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች የሚፈልግባቸው ተነፃፃሪ ግዴታ በአስተዳደሩ ውሣኔ መሠረት ከፈፀሙ በሕጉ መሠረት የመተላለፊያ መንገድ የማግኘት መብታቸው ወደፊትም ሊጠይቁ አይችሉም ተብሎ ውሣኔው የመጨረሻ ሊሆን አይገባም ምክንያቱም አመልካች እዚህ ሰበር ላይ እያቀረቡ ያለው ክርክር ካሣ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆናቸው እና በማንኛውም አካል ያለመጠየቃቸውን የሚያመለክት ሆኖ ስላገኘነው ነው፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ አሁን ባለበት ሁኔታ እንዲፀና ብለን ይህ ውሣኔ ግን የአመልካችን መብት እስከመጨረሻው የሚያሳጣ ሊሆን የሚገባ አይደለም ብለናል፡፡ በዚሁ መሠረት ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 03564 በ23/3/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 09112 በ12/06/2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ የሰበር ችሎቱ በመ/ቁ 9816 የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በአስተዳደሩ ውሣኔ መሠረት ግዴታቸውን ከተወጡ በኃላ የመተላለፊያ መንገድ የማግኘት መብታቸውን ይህ ውሣኔ አይከለክልም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ም.አ

# ከውል ውጭ ኃላፊነት

የሰ/መ/ቁ. 39601

ጥቅምት 5 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - አክሊሉ ተስፋዬ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ገዛኸኝ መንግስቱ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በመዝገቡ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ለንግድ የሚውሉ እህሎችን ይዞ የነበረው መጋዘን በመታሸጉ ምክንያት ደርሶአል የተባለውን ጉዳት(ኪሣራ) ለማስከፈል በሚል የቀረበውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች ላይ አቅርቦት የነበረው ክስ የተለያዩ እህሎችን ሲነግድበት የነበረው የንግድ ቤት መጋዘን ከሕግ ውጪ አሽጐ ሁከት የፈጠረበት መሆኑን፣በዚህ ምክንያትም ሁከቱ ይወገድለት ዘንድ በፍ/ቤት ክስ መመስረቱን፣አመልካች ለክሱ መልስ እንዲሰጥ ታዞ መቅረቡና ክርክር መደረጉን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ሁከቱ ይወገድ ሲል በመወሰኑ መጋዘኑ መከፈቱን በአንድ በኩል ሲገልጽ፤በሌላ በኩል ደግሞ የቀረበው ክስ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ መጋዘኑ ለአራት ወር ያህል ተዘግቶ በመቆየቱ ምክንያት በእህል ዋጋ ረገድ ደረሰ የተባለው ኪሣራ ብር 9,959(ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ) እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ተጠሪ የጠየቀውም ይኸው ብር 9,959(ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ) ከወለድና የጠበቃ አበል ጋር እንዲከፈለው እንዲወሰንለት ሲሆን፣ፍ/ቤቱም በጥያቄው መሰረት ወስኖለታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤትም ውሳኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረም ዘንድ አቤቱታ አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ክርክሩን አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ተጠሪ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ክስ የመሰረተው ሁለት ጊዜ ነው፡፡ የመጀመሪያው ከሕግ ውጪ ተደረገ የተባለውን እሽግ እንዲነሳለት የሚጠይቅ ሲሆን፣ሁለተኛው ደግሞ መጋዘኑ በመታሸጉ ምክንያት ደረሰ ያለውን ኪሣራ እንዲከፈል የሚጠይቅ ነው፡፡ የኪሣራው መጠን ያሰላው የእሕሉን የመሸጫ ዋጋ ነው(ነበር) ያለውን መሰረት በማድረግ እንደሆነም በክሱ ተመልክቶአል፡፡ አመልካች በበኩሉ በሁለተኛው ክስ የተጠየቀው ኪሣራ በመጀመሪያው ክስ ሊጠየቅ ይገባው የነበረ በመሆኑ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና ኪሣራው በእርግጥ ለመድረሱ ማስረጃ አልቀረበም የሚል የፍሬ ነገር ነጥብ በማንሳት ተከራክሮአል፡፡ ፍ/ቤቱ ሁለቱንም የመከራከሪያ ነጥቦች አልተቀበለም፡፡

ክሱን ያስተናገደው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዳየነው ተጠሪ በመጋዘኑ መታሸግ ምክንያት በእህሉ ላይ የደረሰውን ብልሽት ወይም ኪሣራ የሚያሳይ ማስረጃ እንዳላቀረበ ፍ/ቤቱ ስለመገንዘቡ በውሳኔው ላይ በግልጽ አመልክቶአል፡፡ "... ከሣሽ ከተለየ የእህል ንግድ ላይ ያጣውን የገንዘብ መጠን አሚልቶ በዚህ ላይ መዘረዘሩ ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ረገድ ይህንን ያሕል ገቢ ለማግኘቱም ሆነ ለማጣራቱ የተመሰከረ ነገረ የለም፡፡ ይህንን የራሱን ገቢ ተከሣሽ በክርክሩ ላይ እንደተቃወመው የተመዘገበ የገቢ ግብር የተከፈለበት ለመሆኑ ማስረጃ የለም.." በማለትም በውሳኔ ሐተታው ላይ ተችቶአል፡፡ የደረሰበት መደምደሚያ ይህ እንደሆነ ከገለጸ በኋላም ነው ተጠሪ ካሣ(ኪሣራ) ይገባዋል በማለት ገንዘብ እንዲከፈል የወሰነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው ፍ/ቤቱ በተጠሪ ላይ ኪሣራ ለመድረሱ ምንም አይነት ማረጋገጫ አላገኘም፡፡ ይህንንም እንዳመነበት በውሳኔው ላይ አመልክቶአል፡፡ ገንዘቡ መከፈል አለበት ለማለት የቻለው በእርግጥም ኪሣራው ስለመድረሱ በተጨባጭ ማስረጃ አረጋግጦ ሳይሆን፣መጋዘኑ ታሽጐ ከቆየ ተጠሪ ያጣው ማስረጃ አረጋግጦ ሳይሆን፣መጋዘኑ ታሽጐ ከቆየ ተጠሪ ያጣው ነገር የለም ለማለት አይቻልም ከሚል ግምት በመነሳት እንደሆነ በውሳኔው ማጠቃለያ ላይ በግልጽ አመልክቶአል፡፡ ኪሣራ ሊከፈል የሚችለው ጉዳት ስለመድረሱ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2090 እና 2091 ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ግን የደረሰ ጉዳት ለመኖሩ በምንም አይነት መንገድ አልተረጋገጠም፡፡ በመሆኑም ክሱ ለሁለተኛ ጊዜ እንደቀረበ ይቆጠራል ከሚል መነሻ አመልካች አቀርቦት የነበረው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቢታለፍ እንኳ በክርክሩ ፍሬ ነገር ተገብቶ የደረሰ ጉዳት አለ ለማለት የሚያስችል የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት ስለሌለ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለት ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 07105 ኅዳር 12 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 47571 ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የሚከፍለው ኪሣራ የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 42962

ታህሣሥ 28 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ አየለ አድማሱ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አጀቡ ሹሜ ቀረቡ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጉዳት ካሳን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የተጠሪ መኪና ገጭቶ የአካል ጉዳት ስላደረሰባቸው ጉዳት ካሳ ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ) እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ የጉዳት ካሳው መጠን የተጋነነ ነው፣አደጋው በአመልካች ላይ ቀሪ የአካል ጉዳት ለደረሰ በመሆኑና ለህክምና ያወጡት ወጪ ከግንዛቤ ሳይገባ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የተጠሪ መኪና አመልካችን ገጭቶ በአካላቸው ላይ 18% ጉዳት ማድረሱን ካረጋገጠ በኋላ አመልካች ከጉዳቱ በፊት ገቢ ያገኙ እንደነበር ስላላስረዱ በአደጋው ምክንያት ያጡት የገንዘብ ጥቅም ስለሌለ የሚከፈላቸው የጉዳት ካሳ አይኖርም በማለት የአመልካችን የካሳ ጥያቄ ውድቅ አድርጐታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም አመልካች ላይ የአካል ጉዳት መድረሱ ተረጋግጦ እያለ የጉዳት ካሳ ሊከፈላቸው አይገባም የተባለበትን የሕግ አግባብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው የተጠሪ መኪና አመልካችን ገጭቶ የአካል ጉዳት ያደረሰባቸው ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪም ቢሆኑ መኪናቸው አመልካች ላይ ጉዳት ማድረሱን አልካዱም፡፡ አንድ ተሽከርካሪ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት አድርሶ ከተገኘ የተሽከርካሪው ባለቤት ለጉዳቱ አስተዋፆ ባይኖረውም እንኳን የመኪናው ባለቤት በመሆኑ ብቻ ለደረሰው ጉዳት አላፊነት እንደሚኖርበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2981/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ በዚህ ምክንያት ተጠሪ ጥፋት ባይኖርባቸው እንኳን አመልካች ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት የአደጋው አድራሽ መኪና ባለቤት በመሆናቸው ብቻ የጉዳት ካሳ የመክፈል ሃላፊነት አለባቸው፡፡ የስር ፍ/ቤትም ተጠሪ ለጉዳቱ ኃላፊ መሆናቸውን ተቀብሏል፡፡ አከራካሪ የሆነው አመልካች የጉዳት ካሳ ሊከፈላቸው ይገባል አይገባም የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ምንም እንኳን አመልካች የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ቢሆን ከጉዳቱ በፊት ገቢ ያገኙ እንደነበር ስላላረጋገጡ ያጡት የገንዘብ ጥቅም ስለሌለ ካሳው ሊከፈላቸው አይገባም ብሏል፡፡ ይህ የፍ/ቤቱ ውሳኔ አንድ ሰው በደረሰበት አደጋ ምክንያት የአካል ጉዳት ቢደርስበት ካሳ ሊከፈለው የሚገባው ከአደጋው በፊት ገቢ የሚያገኝ መሆኑና ይህም ገቢው የተቋረጠ መሆኑን ካስረዳ ብቻ ነው ወደሚል መደምደሚያ የሚወስድ ነው፡፡ ይህም ድምዳሜ በዋናነት የሚያሳይው የታጣ የገንዘብ ጥቅም ከሌለ በቀር ምንም አይነት የአካል ጉዳት ቢደርስ ካሳ ሊከፈል የማይገባው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ችሎቱ የጉዳት ካሳ የሚከፈለው መቼ ነው? የሚለውን ጭብጥ መርምሯል፡፡

በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 14 ሥር "ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በህይወት የመኖር፣የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት አለው" (ሰረዝ የተጨመረ) ተብሎ የተቀመጠ ሲሆን አንቀጽ 16 የአካል ደህንነት መብት ምን እንደሆነ ያብራራል፡፡ ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት እንዳለው የሃገሪቱ የበላይ ሕግ ያስገነዝባል፡፡ መንግስትም ሆነ ማንኛውም ሰው የሌላውን ሰው የአካል ደህንነት የመጠበቅ የሕግ ግዴታ አለበት፡፡ ይህን ህግ በመተላለፍ በሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ በወንጀል የሚያስቀጣ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለደረሰው የአካል ጉዳት ተጐጂው ካሳ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡ በህገ-መንግስቱ የተቀመጠው ይህን የሰብአዊ መብት ከሚያረጋግጡ ዝርዝር ሕጐች ውስጥ በፍ/ሕጉ ውስጥ የጉዳት ካሳን አስመልክቶ የተቀመጡት ድንጋጌዎች ይገኙባቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ሰው በጥፋቱ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ላደረሰው ጉዳት አላፊ ሆኖ ካሳ ሊከፍል እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2028 አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም በመርህ ደረጃ የጉዳት ካሳ ሊከፍል የሚገደደው በጥፋቱ ጉዳት ያደረሰ ሰው ሲሆን በአንዳንድ የተለያዩ ጉዳዮች ደግሞ አንድ ሰው ጥፋት ሳይኖርበትም ኃላፊ እንደሚሆን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2066 እና ተከታዮቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከእነዚህ ህጉ ለይቶ ካስቀመጣቸው ጉዳዮች አንዱ የተሽከርካሪ ባለቤት ተሽከርካሪው ላደረሰው ጉዳት ጥፋት ሳይኖርበት አላፊ እንደሚሆን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2081/1/ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በሌላ ሰው አካል ላይ ለደረሰ ጉዳት አላፊ የሆነ ሰው ለደረሰው ጉዳት ካሳ የመክፈል ግዴታ በፍ/ሕጉ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ሊታይ የሚገባው የካሳው መጠን ነው፡፡ ለጉዳቱ አላፊ የሆነ ሰው የሚከፍለው የካሳ መጠን ከጉዳቱ ጋር ተመዛዛኝ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2090 እና 2091 ስር ተመልክቷል፡፡ ወደፊት ይደርሳል ተብሎ የሚገመት ጉዳት የተረጋገጠ ከሆነ እስኪፈፀም መጠበቅ ሳያስፈልግ ካሳው ሊከፈል እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2092 ይናገራል፡፡ በሌላ በኩል ካሳ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዘን አለበት ሲባል መታየት ያለበት በአጠቃላይ በተጐጂው ላይ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት እንደሰው በአጠቃላይ የመስራት ኃይል ቅነሳ አንፃር እንጂ ከጉዳቱ በፊት ሲሰራው የነበረውን ስራ ላለመስራት ጉዳቱ ያስከተለው ልዩ ጫናና የቅነሳ መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት አለመሆኑን ለዚህም ምክንያት የሚሆነው እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ስራ ለመስራት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ አንድ ሰው ለመኖር የተለያየ ፋይዳና ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ እንደሆነ ይህ የሰበር ችሎት በመ/ቁ. 19338 ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት 18% ስለመሆኑ ተገንዘበናል፡፡ የስር ፍ/ቤት አመልካች ላይ ጉዳት መድረሱን ቢያረጋግጥም ከፍ ሲል እንደተገለፀው ከጉዳቱ በፊት ገቢ ያገኙ እንደነበር አላስረዱም በሚል ካሳ ሊከፈላቸው አይገባም ብሏል፡፡ ነገር ግን ጉዳት መድረሱ በተጨባጭ እስከተረጋገጠ ድረስ ለተጐጂው ከደረሰበት ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ሊከፈለው ይገባል፡፡ ምክንያቱም መታየት ያለበት ተጐጂው ከጉዳቱ በፊት ያገኘው ገቢ ሳይሆን በጉዳቱ ምክንያት ወደፊት በመስራት ችሎት ላይ ሊያስከትል የሚችለው አሉታዊ ተጽእኖ ነው፡፡ አመልካች ላይ የደረሰው አካል ጉዳት ሙሉ ለሙሉ የመስራትን ችሎታቸውን ያሳጣ ነው ባይባልም በ18% በመቶ የመስራት ችሎታቸውን የቀነሰ ስለመሆኑ በሕክምና ተረጋግጧል፡፡ በእርግጥ ለዚህ ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ለመወሰን አስቸጋሪ ቢሆንም የካሳውን መጠን በትክክል ለመወሰን ያልተቻለ እንደሆነ የካሳው መጠን በርትእ ሊወሰን እንደሚችል የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2102/1/ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም አመልካች ላይ ጉዳት መድረሱና ጉዳቱም 18% የመስራት ችሎታቸውን መቀነሱ ስለተረጋገጠ የካሳውን መጠን በትክክል ማወቅ አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳን በርእት መወሰን ሲቻል አመልካች ገቢ ያልነበራቸው በመሆኑ ብቻ ካሳ አይከፈላቸውን ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የጉዳት ካሳ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት 107806 ሚያዚያ 24 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 68949 ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ላይ 18% የአካል ጉዳት የደረሰባቸው በመሆኑ በርትእ ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 43843

መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ዶ/ር ተስፋነሽ በላይ - ጠበቃ አቶ ይርሣው ጌትነት ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ - ነገረፈጅ መኮንን ሽፈራው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ ያታየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርቦ የመድን ሽፋን የሰጠሁት የሰሌዳ ቁጥር 3-15680 የሆነውን መኪና ንብረትነቱ የተከሳሽ (የአመልካች) የሆነው የሰሌዳ ቁጥር 2-4443 አ.አ የሆነው መኪና ጥቅምት 12 ቀን 1999 ዓ.ም በመግጨት ጉዳት አድርሶበታል፡፡ ጉዳቱ ያደረሰውም የተከሳሽን (አመልካችን) መኪና ያሽከረክር በነበረው ሰው ጥፋት ምክንያት መሆኑ በትራፊክ ሪፖርትና መርመራ የተረጋገጠ ነው፡፡ ከሳሽ (ተጠሪ) ባሉበት የውል ግዴታ መሰረት ብር 116,735.49 (አንድ መቶ አስራ ሰድስት ሺ ሰባት መቶ ሰላሣ አምስት ብር ከአርባ ዘጠኝ ሣንቲም) ወጭ በማድረግ የደንበኛውን መኪና አስጠግኖ ያስረከበ ስለሆነ ይህንን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርበው የእኔን መኪና ያሽከረክር የነበረው ሰው በወንጀል ተከስሶ ነፃ በመሆኑ ጉዳቱ የደረሰው የእኔን መኪና በሚያሽከረክረው አሽከርካሪ ጥፋት ሣይሆን የከሳሽን መኪና በሚያሽከረክረው አሽከርካሪ ጥፋት ነው፡፡ ጉዳቱ በሁለት ተሽከርካሪዎች ግጭት የተከሰተ በመሆኑና የእኔም መኪና ጉዳት ደርሶበት በንብ ኢንሹራንስ የተጠገነ በመሆኑ የየራሳችንን መቻል ይገባናል፡፡ ተጠሪ(ከሳሽ) ፕሮፎርማ ሣይሰበሰብ በሞኤንኮ ኩባንያ ብቻ ጥገናው እንዲከናወን ያደረገ በመሆኑ በቂ ማስረጃ አላቀረቡም የትራፊክ ፖሊስ የምርመራ መዝገብ ቀርቦ ይታይልኝ በማለት የተከራከሩ ሲሆን ንብ ኢንሹራንስ ኩባንያም በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ አለኝ የሚለውን ክርክር አቅርቧል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ያቀረበውን የትራፊክ ፖሊስ የምርመራ ሪፖርት ከመረመረ በኋላ አመልካች የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ይቅረብ ብለው ያቀረቡት ጥያቄ የምርመራ መዝገቡ ከቀረበው ሪፖርት የተለየ የሚያስረዳ ስለመሆኑ አልገለፁም ስለዚህ ክርክራቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ የአመልካችን መኪና የሚያሽከረክረው ሹፌር በወንጀል ተከስሶ ነፃ መውጣቱ የፍትሐብሔር ኃላፊነትን የሚያስቀር አለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2149 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ጉዳቱ የደረሰው በአመልካች ሹፌር ጥፋት ምክንያት መሆኑ ስለተረጋገጠና አመልካች የመኪናው ባለቤት በመሆናቸው ለደረሰው ጉዳት በኃላፊነት ይጠየቃሉ በማለት ከወሰነ በኋላ የካሣውን መጠን በተመለከተ አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ

ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር እንደዚሁም ሌሎች ወጭዎችን ይክፈሉ፣ክስ ከቀረበበት ገንዘብ ውስጥ ጣልቃገቡ ንብ ኢንሹራንስ ኩባንያ ብር 75,000/ሰባ አምስት ሺህ ብር/ ይከፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የእኔ መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር በወንጀል ተከስሶ ነፃ ሆኖ እያለ የወንጀል መዝገብ አስቀርቦ ሣይመለከት ኃላፊነት አለባችሁ ብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ለመኪና መለዋወጫ አውጥቻለሁ በማለት ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ ታአማኒነት የሌለው ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት ተቀብሎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት በርካታ የሕግና የፍሬ ጉዳይ ስህተት ፈጽሞ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሣያርም ማጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሶስት ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ጉዳቱ የደረሰው የአመልካችን መኪና ያሽከረክር በነበረው ሹፌር ምክንያት መሆኑን የተሻለና ሚዛን የሚደፋ ማስረጃ በማቅረብ አስረድተናል፡፡ የፍርድ ቤት የወንጀል ውሣኔ በእኛ በኩል ያቀረበውን የትራፊክ ምርመራ ሪፖርት የሚያስተባብል አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የማስረጃ አቀራረብ ስርአትን ተከትለው በስር ፍ/ቤትም ሆነ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያላቀረቡትን ማስረጃ የበታች ፍርድ ቤቶች እንዳለፉባቸው በመግለጽ በሰበር አመልካች የሚያቀርቡት ክርክር ህጋዊ መሰረት የሌለው ነው፡፡ በማለት መልስ ሰጥቷል አመልካች በጽሑፍ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመነው አመልካች የሥር ፍርድ ቤት ማስረጃ ሣያስቀርብና የእኔን መኪና የሚያሽከረክረው ሰው ከወንጀል ክስ ነፃ ሆኖ እያለ ለጉዳቱ ኃላፊነት አለብሽ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረቡትን የመከራከሪያ ሐሳብ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ ምላሽ ማግኘት ያለባቸው ነጥቦች ሆኖ አግኝተናቸዋል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ በማስቀረብ አመልካች ተጠሪ ያቀረበባቸውን ክስ ለመከላከል በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 234 እና በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 223 ድንጋጌዎች መሰረት ያቀረቡትን የማስረጃ ዝርዝር ተመልክተናል፡፡ አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት የካቲት 19 ቀን 2000 ዓ.ም ባቀረቡት የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ የትራፊክ ፖሊስ የምርመራ መዝገብና አቃቤ ሕግ በቁራ ምድብ ችሎት የወንጀል ክስ አቅርቦ የተከራከረበት የፍርድ ቤት መዝገብ ፍርድ ቤቱ በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 145 መሰረት የጠየቁ መሆኑን በተራ ቁጥር 1 እና በተራ ቁጥር 2 ካቀረቡት የማስረጃ ዝርዝር ለመረዳት ችለናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት እነዚህን መዝገቦች አስቀርቦ ማየት ያላስፈለገበትን ምክንያት በውሣኔው በግልጽ አስፍሯል፡፡ አመልካች እንዲቀርብላቸው የጠየቁት የትራፊክ ፖሊስ የምርመራ መዝገብ በትራፊክ ፖሊስ የሚመለከተው ክፍል ተዘጋጅተው ከተላከው የትራፊክ ፖሊስ ምርመራ ውጤትና መግለጫ ከተገለፀው ፍሬ ጉዳይ ምን የተለየ ፍሬ ጉዳይ ሊያስረዳ እንደሚችል ባቀረቡት የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ አለመገለፁን እንዲሁም የወንጀል ችሎት የአመልካች መኪና ሲያሽከረክር በነበረው ሰውና በዓቃቤ ሕግ መካከል ክርክር የተደረገበት መዝገብ አሽከርካሪው በወንጀል ተከስሶ ነፃ ከመሆኑ ውጭ ሌላ የሚያስረዳው ፍሬ ነገር ያለ መሆኑን የማስረጃ ዝርዝር መግለጫው የማያሣይና በወንጀል ነፃ መሆን የፍትሐብሔር ተጠያቂነት እንደማያስቀር በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2149 የተደነገገ መሆኑን በመግለጽ ውሣኔ እንደሰጠ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

አመልካች አንድ ማስረጃ ቢቀርብ ምን አይነት ጭብጥ ሊያስረዳላቸው እንደሚገባ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 223 እና በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 145/2/ ድንጋጌዎች መሰረት በመግለጽና በመዘርዘር የመጠየቅ ግዴታና ኃላፊነት አለባቸው፡፡ አመልካች መዝገቦቹ ቢቀርቡ ለሥር ፍርድ ቤት በማስረጃነት ከቀረበው የትራፊክ ፖሊስ የምርመራ ውጤት መግለጫ ሊያስረዱ የሚችሉት የተለየ ፍሬ ጉዳይ ስለመኖሩ ሣያረጋግጡና ሣይገልጹ እንደዚሁ በደፈናው መዝገቦቹ ቀርበው ይታዩልኝ በማለት በማስረጃ ዝርዝር መግለጫው ስለጠየቁ ብቻ የሥር ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 145 መሰረት መዝገቦቹን የማስቅረብ ግዴታና ኃላፊነት የለበትም፡፡ ፍርድ ቤቱ መዝገቦቹ እንዲቀርቡ ትእዛዝ የሚሰጠው ይቅረቡ የተባለው ማስረጃ ከክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ ጋር ያለውን አግባብነትና ማስረጃው ቢቀርብ ሊያረጋግጥ የሚችለው ፍሬ ጉዳይ በመጀመሪያ ማስረጃው ይቅረብልኝ የሚለው አካል በበቂ ሁኔታ ዘርዝሮና በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር

145 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት አረጋግጦ ሲጠይቅ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች በፍትሐብሔር በሥነ- ሥርአት ሕግ ቁጥር 145/2/ ድንጋጌዎች መሰረት እንዲቀርቡ የጠየቋቸው ማስረጃዎች ምን አይነት ፍሬ ጉዳይ እና ጭብጥ ለማስረዳት እንደሚጠቅሙ ሣይገልጽና ሣያረጋግጡ የሥር ፍርድ ቤት ማስረጃዬን ሣያስቀርብ ወሰነብኝ በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሰረትና ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ የአመልካችን መኪና ያሽከረክር የነበረው ሹፌር በወንጀል ተከስሶ ነፃ መሆኑ አመልካች በፍትሐብሔር ተጠያቂነት ነፃ የሚያደርግ አይደለም፡፡ አመልካች መኪናቸውን ከሚያሽከረክረው ሹፌር ጥፋት ውጭ በሆነ መንገድ በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳን የመኪናው ባለቤት በመሆናቸው ብቻ ለጉዳቱ ተጠያቂ እንደሚሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2081 ንኡስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አደጋው ያደረሰው የአመልካችን መኪና በሚያሽከረክረው ሹፌር ጥፋት መሆኑን በፍትሐብሔር ክርክር የቀረበውን ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች የወንጀል ችሎት የሰጠው ውሣኔ መኪናቸውን ያሽከረክር የነበረው ሰው ጥፋት የሌለበት መሆኑ የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ (conclusive Evidence) ተደርጐ መወሰድ አለበት በማለት ያቀረቡት ክርክር በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2149 በወንጀል ነፃ መሆን የፍታብሔር ኃላፊነትን የሚያስቀር አይደለም በማለት ሕግ አውጭው በግልጽ የደነገገውን ድንጋጌ ያላገናዘበና የሕግ ድጋፍ የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የክርክሩን ሥርአት በሚመሩበት ጊዜም ሆነ ለጉዳቱ ኃላፊ ያለባቸው አመልካች ናቸው ብለው በሰጡት ውሣኔ የፈፀሙት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ውሣኔያቸውን አጽንተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የካቲት 10 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 45735

መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ ደረጀ ቸርነት - ጠበቃ አቶ በሻዳ ገመቹ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ ሕይወት የኂሳሸት - ጠበቃ አቶ ደሣለኝ ዓለሙ ክብረት ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 22411 ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 40544 የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ የታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች በከሳሽነት ቀርቦ ንብረትነቱ የእሱ የሆነውና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-00055 አዋሣ የሆነ ኤኔትሬ የነዳጅ መጫኛ መኪና ሐምሌ 22 ቀን 1990 ዓ.ም ከተጠሪ የነዳጅ ማደያና ዲፖ ነዳጅ መራገፍ ላይ እያለ በዚህ ክርክር ተሣታፊ ያልሆነውና በሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተከሳሽ በሆነው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የሚባለው የተጠሪ ሰራተኛ በአስነሣው እሳት ምክንያት መኪናው ሙሉ በሙሉ የወደመ በመሆኑ የመኪናውን ዋጋ ብር 200,000(ሁለት መቶ ሺህ ብር) በመኪናው አገኝ የነበረውን ገቢ አደጋው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ክስ እስከተመሰረተበት ጊዜ ድረስ በወር 15,00(አስራ አምስት ሺህ ብር) ሒሳብ 120,000( መቶ ሃያ ሺህ ብር) በሥር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ቶታል ሜር ዩቨ ኤስ ኤ፣ተጠሪና አቶ አስጨናቂ ኩምሣ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ በሥር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ድርጅት አመልካች በእሱ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል በቂ ምክንያት የሌለው መሆኑን በማንሣት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በሁለተኛ ተከሳሽነት ቀርበው ሶስተኛው ተከሳሽ አስጨናቂ ኩምሣ ሰራተኛ ባለመሆኑ በኃላፊነት የምጠየቅበት ምክንያት የለም፡፡ እሳት ሊነሣ የቻለው የከሳሽ(አመልካች) ሰራተኞች በመኪናው ጋቢና በኩል ባስነሱት ምክንያት ነው ስለዚህ ለጉዳቱ አላፊነት የምጠየቅበት ምክንያት የለም በማለትና የመኪናውን ዋጋ ግምትና የመኪናውን ገቢ በመቃወም ተከራክረዋል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበረው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የሁለተኛ ተከሳሽ (የተጠሪ ድርጅት) ሰራተኛና ድርጅቱን በመላላክ የሚያገለግል መሆኑንና ጆሮውም የማይሰማ መሆኑን ገልፆ አደጋው በተከሰበት እለት እኔ በቦታው አልነበርኩም ፍ/ቤቱ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ያቁምልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኂላ በሥር አንደኛ ተከሳሽ ተደርጐ የተጠቀሰው ድርጅት ሙሉ በሙሉ ከክሱ እንዲወጣ ወስኗል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት እሣቱ የተነሳው በአቶ አስጨናቂ ኩምሣ

ኃላፊነት የጐደለው ተግባር መሆኑን በበቂ ማስረጃ መረጋገጡን ወስኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበረው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ ለፖሊስ በሰጠው የተከሳሽነት ቃልና ለፍርድ ቤት በሰጠው መልስ ማረጋገጡንና ሶስተኛው ተከሳሽ የሁለተኛ ተከሳሽ (የተጠሪ) ሰራተኛ መሆኑ በሌላ ምስክር ቃል የተረጋገጠ መሆኑን በመግለጽ በእሳት አደጋው ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ተጠሪ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ሶስተኛ ተከሳሽም ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ ተጠሪና ሶስተኛ ተከሳሽ ለጉዳቱ በአንድነትና በነጠላ በኃላፊነት ይጠየቃሉ ብሎ ወስኗል የካሣውን መጠን በተመለከተ የመኪናው የገበያ ዋጋ ብር 170,000 (አንድ መቶ ሰባ ሺ. ብር) እንደሚያወጣ አግባብ ካለው አካል ተገልጿል፡፡ የመኪናው ወርሃዊ ገቢ ብር 12,000 (አስራ ሁለት ሺ. ብር ነው) ስለዚህ ተጠሪና ሶስተኛ ተከሳሽ የመኪናውን ዋጋ ብር 170,000(አንድ መቶ ሰባ ሺ. ብር) እና የአስር ወር ገቢ ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺ. ብር) እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ በወቅቱ ሥራ ላይ የነበረውን አዋጅ ቁጥር 42/1985 ድንጋጌዎች በመጥቀስና በተጠሪና በአቶ አሰጨናቂ ኩምሣ መካከል ያለው የሥራ ውል በጽሑፍ የተደረገ ስለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑን በመግለጽ አመልካች አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ መሆናቸውን ስላላስረዱ ተጠሪ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለባቸውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በከፍተኛው ፍርድ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተከሳሽ አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ መሆኑን በማመን መልስ ሰጥቷል፡፡ ፖሊስ ባጣራው የወንጀል የምርመራ መዝገብ በሰጠው የተከሳሽነት ቃልም አረጋግጧል በሌላ ማስረጃም ይኸን ፍሬ ጉዳይ አስረድተናል፡፡ ለተጠሪ ያቀረበችው ማስረጃ ሣይኖር ተጠሪ በአስጨናቂ ኩምሣ ስም የከፈላቸው የገቢ ግብር አለመኖሩንና ሌሎች ህጋዊ መሰረት የሌላቸውን ምክንያቶች በማቅረብ ተጠሪ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምኝ በማለት ያላመለከቱ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው የሥር ፍርድ ቤት የምስክሮችን ቃል በአግባቡ አልገለጹም፡፡ መስቀለኛ ጥያቄ ያልቀረበበትን ለፖሊስ የተሰጠ የተከሳሽነትና የምስክርነት ቃል ተጠቅሟል፡፡ ነዳጁ እስከ ታንከሩ ተገልብጦ እስኪያልቅ ድረስ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊነት ያለበት ጫኙ (አመልካች) ነው፡፡ አስጨናቂ ኩምሣ ተቀጣሪ ሰራተኛ አይደለም ስለዚህ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያደረጉት የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው

- ተጠሪ አደጋው ያደረሰው በአመልካች ሰራተኞች ጥፋት ነው በማለት በሰበር ደረጃ ያቀረበው ክርክር ህጋዊ መሰረት አለው ወይስ የለም?

- ተጠሪ በእሳት አደጋው ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ናቸው ወይስ አይደሉም?

የሚሉ ጭብጦችን አግባብነት ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እልባት ማግኘት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪ የእሳት አደጋው የተነሣው በአመልካች ሰራተኛ ጥፋት ነው በማለት በሰበር ሰፊ ክርክር አቅርበዋል፡፡ የእሳት አደጋው የተከሰተው በሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተከሳሽ በነበረው በአቶ አስጨናቂ ኩምሣ ጥፋት ምክንያት መሆኑን በማረጋገጥ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወስኗል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ተጠሪን ከኃላፊነት ነፃ ናቸው በማለት የወሰነው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ አይደሉም በማለት ነው፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የእሳት አደጋው በአቶ አሥጨናቂ ኩምሣ ጥፋት ነው የሚለውን የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ አልሻረውም፡፡ ስለሆነም መኪናውን

ለውድመት የዳረገው እሳት አደጋ የተነሳው በአቶ አስጨናቂ ኩምሣ ጥፋት መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም አደጋው ያደረሰው በአቶ አስጨናቂ ኩምሣ ጥፋት ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ የሚነቀፍ አለመሆኑን "ሌሎቹን በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ የሚነቀፍ ሆኖ ስላልተገኘ ጸንቷል" በማለት በግልጽ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም የእሳት አደጋው በአቶ አስጨናቂ ኩምሣ ጥፋት መሆኑን ማስረጃ የመመዘንና ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ሥልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥተውበት እያለ ተጠሪ አደጋውን ያደረሰው በአመልካች ሰራተኛ ጥፋት ነው በማለት ለሰበር አቤቱታ በሰጠው መልስ ያቀረበው ክርክር ለሰበር ችሎት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንኡስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ የቀረበ ሆኖ ስላገኘነው አልተቀበልነውም፡፡

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የእሳት አደጋው የተነሣው በአቶ አስጨናቂ ኩምሣ ጥፋት መሆኑ በስር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በአመልካች መኪና ላይ በእሳት አደጋው ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለባቸው ወይስ የለባቸውም? የሚለው ጭብጥ የሚፈታው ተጠሪ ለአቶ አስጨናቂ ኩምሣ ጥፋት ምክንያት ለደሰረሰው ጉዳት ተጠያቂነት አለባቸው ወይስ የለባቸውም? የሚለውን ጭብጥ በመመለስ ነው፡፡ አመልካች የጉዳቱን መንስኤና ምክንያት የደረሰውን የጉዳት መጠንና ተጠሪ ለጉዳቱ ኃላፊ መሆናቸውን የማስረዳት ሸክም እንዳለባቸው ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2141 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች ይህንን የማስረዳት ሸክማቸውን ለመወጣት ስለአደጋው በፖሊስ የተጣራው የምርመራ መዝገብ ቀርቦ እንዲታይላቸው አመልክተዋል፡፡

አመልካች ተጠሪ ለደረሰው ጉዳት በኃላፊነት መጠየቅ አለባቸው በማለት የሚከራከሩት ለእሳት አደጋው መከሰት ጥፋት የፈፀሙት አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ ናቸው በማለት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተከሳሽ የነበረው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ ለሥር ፍርድ ቤት በሰጡት መልስ በተጠሪ ድርጅት በተላላኪነት የሚያገለግል ሰራተኛ መሆኑን በመግለጽ መልስ የሰጠ ሲሆን ለፖሊስ ባደረገው ምርመራም አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ እንደሆነ በአቶ አስጨናቂ ኩምሣና በሌሎች ምስክሮች መረጋገጡን በሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገልጿል፡፡

አመልካች አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ የነበረ መሆኑን ሊያስረዳለት የሚችል ማስረጃ ያቀረበ ሲሆን በጥፋቱ የእሳት አደጋውን ያስነሳው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ ለሥር ፍርድ ቤት በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 92 መሰረት አረጋግጦ በሰጠው መልስ የተጠሪ ሰራተኛ እንደሆነ በማመን መልስ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ አቶ አስጨናቂ ኩምሣ ሰራተኛቸው አለመሆኑንና በእለቱ በቦታው የተገኘው በድንገተኛ አጋጣሚ ወይም በሌላ እሳቸው በማያውቁት ሁኔታ መሆኑን ለማስተባበል ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ አመልካች ጉዳቱን ያደረሰው ሰው የተጠሪ ሰራተኛ መሆኑንና ተጠሪም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2130 መሰረት ለጉዳቱ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን ለማስረዳት የሚችል ማስረጃ በማቅረብ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2141 የተጣለበትን የማስረዳት ሸክሙን የተወጣ ሲሆን ተጠሪ የአመልካችን ማስረጃ የማስተባበልና የማፍረስ ግዴታቸውን አልተወጡም፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት በተጠሪና በአቶ አስጨናቂ ኩምሣ መካከል ያለው የሥር ውል በጽሑፍ የተደረገ መሆኑን ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ በአንድ ሰውና በአሰሪው መካከል የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት መኖሩን በጽሑፍ በተደረገ የሥራ ውል በማቅረብ ካልሆነ በስተቀር በሌሎች ማስረጃዎች ለማስረዳት እንደማይቻል በመግለጽ የሰጠው ውሣኔ ህጋዊ መሰረት የለውም፡፡ የሥር ውል ቋሚ ወይም ጊዜዊ ሊሆን እንደሚችልና የሥራ ውሉ በጽሑፍ ወይም በሌላ አይነት ሁኔታ ሊፈጸም የሚችል መሆኑ አሰሪው የሥራ ውሉን በጽሑፍ በማድረግ በአስር ቀናት ውስጥ የመስጠት ግዴታና ኃላፊነት እንዳለበት በወቅቱ ሥራ ላይ በነበረው አዋጅ ቁጥር 42/1985 አንቀጽ 6 እና አንቀጽ 7 የተደነገገ መሆኑን የከፍተኛ ፍርድ ቤት ጠቅሷል፡፡

ሆኖም የከፍተኛው ፍርድ ቤት መልስ ሣይሰጠው ያለፈው አንድ ቁልፍ ጥያቄ ያለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይኸውም አሰሪው በሕግ የተጣለበትን ግዴታና ኃላፊነት ሣይወጣ አንድ ሰራተኛ በቃል ወይም በሌላ

አኳኋን በተደረገ የሥራ ውሉ ከአስር ቀናት በላይ ለወራት ወይም ለአመታት ሲያሰራ ቢቆይ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለው ነው፡፡ አሰሪው በአዋጅ ቁጥር 42/1985 አንቀጽ 6 እና በአንቀጽ 7 የተጣለበትን ግዴታና ኃላፊነት ሣይወጣ መቅረቱ በሥራ ውሉ ህጋዊነት ላይም ሆነ በሰራተኛው መብትና ጥቅም ላይ የሚያስከትለው አንዳችም ጉዳት የሌለ መሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 8 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 48/1985 አንቀጽ 7 የተደነገገውን ግዴታና ኃላፊነታቸውን አለመወጣታቸው የተሰጠሪ ሰራተኛ መሆኑን በመግለጽ የሚከራከረውና የተጠሪ ሰራተኛ መሆኑ በሌሎች ማስረጃዎች የተረጋገጠው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ ጥፋት ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ከአላፊነት ነፃ የሚያደርጋቸው አይደለም፡፡ ስለሆነም በአሰሪውና በሰራተኛው መካከል የሥራ ውል መኖሩን በጽሑፍ የተደረገ የሥራ ውል ለማቅረብ ብቻ ሣይሆን በጽሑፍ የተደረገ የሥራ ውል በሌለ ወይም ሊገኝ ባልቻለ ጊዜ ማናቸውንም ተዓማኒነት ያለውን ማስረጃ በማቅረብ ለማስረዳት የሚቻል በመሆኑና አመልካች ጉዳቱን ያደረሰው ሰው የተጠሪ ሰራተኛ መሆኑን በበቂ ማስረጃ አረጋግጦ እያለና ተጠሪ የአመልካችን ማስረጃ ሊያስተባብል የሚችል ማስረጃ ባላቀረበበት ሁኔታ በሕግ ያልተደነገገ መስፈርት አላግባብ በማውጣት የሥራ ውሉ መደረጉን የሚያሣይ በጽሑፍ የተዘጋጀ የሥራ ውል አመልካች በማስረጃነት ያላቀረበ በመሆኑ አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ አይደለም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሕግ በግልጽ የሥራ ውልን ለማስረዳት ተቀባይነት የላቸውም ያልተባሉ ማስረጃዎች የስራ ውል ለማስረዳት ተቀባይነት እንደሌላቸው በመግለጽ የሰጠው ውሣኔ በአሰሪውና በሰራተኛው መካከል የአሰሪና የሰራተኛ ግንኙነት መኖሩን ስለማስረዳት የተደነገጉ ከላይ የተጠቀሱትን ደንቦችን የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ጉዳቱን ያደረሰው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተከሳሽ የሆነው አቶ አስጨናቂ ኩምሣም በግልጽ በማመን መልስ የሰጠ ሲሆን በሌሎች ማስረጃዎችም ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ማስረጃ የተረጋገጠውን ይህን ፍሬ ጉዳይ የሚያስተባብል ወይም ለማፍረስ የሚችል የተሻለ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ ተጠሪ ሰራተኛው ላደረሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበት መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2130 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የተጠሪ ሰራተኛ የሆነው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የሥራ ተግባሩን ሲያከናውን እሳቱ የተነሣ መሆኑን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2131/1/ እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2032/1/ መሰረት ያስረዳ ሲሆን ተጠሪ ይህንን ለማስተባበል ወይም ለማፍረስ የሚቻል ማስረጃ እንዳላቀረቡ የሥር ፍርድ ቤት አረጋግጦል፡፡ ስለዚህ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ መባላቸው ሕጋዊ መሰረት ያለው ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥራ ውሉ መኖሩን ለማረጋገጥና ለማስረዳት የሚቻለው በጽሑፍ የተደረገ የሥራ ውል በማቅረብ ነው የሚል የተሳሳተ የሕግ ተርጉም በመስጠት ተጠሪ ለጉዳቱ ኃላፊነት የለባቸውም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## **<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰው  ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡
3. ተጠሪ በአመልካች መኪና ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ናቸው ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ  በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 44588

ሚያዝያ 4 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች-** የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት

**ተጠሪ፡-** 1. ኃይለየሱስ ቱኪ

2. አብዲሣ ኦላና

3. ሌሊሣ ለታ

4. ሰብሌ አብዲሣ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ያቀረበው አመልካች የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሾች በመሆን ተክራክረዋል፡፡ አመልካች የተለያዩ አይነት ጤፍ የመሸጫ ዋጋ ከበፊቱ የጨመረ መሆኑ ከተነገራቸውና የፋክስ መልክት ከደረሳቸው በኂላ በፊት በነበረው ዋጋ የሸጡ በማስመሰልና ብር 16,818.10(አስራ ስድት ሺ ስምንት መቶ አሥራ ስምንት ብር ከአስር ሣንቲም) ድርጅቱ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም እንዲያጣ አድርገዋል በማለት አመለከቱ፣ አንደኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች በሥር ቀርበው አልተከራከሩም ሁለተኛ፣ አራተኛ ተጠሪዎች በሥር ቀርበው ተከራክረዋል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ የእጅ በእጅ የጤፍ ሽያጭ እንዲከናውን ትእዛዝ እልሰጠሁም በደረሰኝ ላይም አልፈረምኩም የሥራ ድርሻዬ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አራተኛ ተጠሪ በበኩላቸው በተከሳሽነት ቀርበው ከዚህ በፊት ከሳሼ ማለትም የአሁን አመልካች ብር 4,204.53(አራት ሺ ሁለት መቶ አራት ብር ከሐምሣ ሶስት ሣንቲም) በመክፈል ከሥራ አሰናብቶኝ ነበር፡፡ እኔ ለጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቤ እስከ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ተከራክረን ወደ ሥራ የተመለስኩ ስለሆነና ከዚህ በፊት በጉዳዩ ተከራክረን ፍርድ ያገኘ ስለሆነ ሁለተኛ ጊዜ ክስ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኂላ አራተኛ ተጠሪ ከዚህ በፊት በአሰሪና ሰራተኛ ችሎት ተከራክሮ ተፈፀመ የተባለው ጥፋት የማያስጠይቃት መሆኑ ተረጋግጦ አራተኛ ተጠሪ ወደ ሥራ እንድትመለስ ተወስኗል፡፡ ይህ ውሣኔ እስከ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ድረስ ቀርቦ ፀንቷል ስለዚህ ተከሳሾችን የሚያስጠይቃቸው አይደለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ውሣኔው በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ፀንቷል፡፡

አመልካች ተጠሪዎች ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ከእያንዳንዱ ኩንታል ብር 10.00/አስር ብር / ቀንሰው መሸጣቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርበናል በአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ችሎት አራተኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) ጥፋት

አልፈፀመችም ተብላ ወደ ሥራ እንድትመለስ መወሰኑ የፍትሐብሔር ኃላፊነትን የሚያስቀር አይደለም፡፡ ስለዚህ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ሆነ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት የሰበር አቤቱታውን አቅርቧል አንደኛ፣ ሁለተኛና አራተኛ ተጠሪ በየግላቸው መልስ ሰጥተዋል፡፡ የሰጡት መልስ ይዘትም ከጤፍ ሽያጭ ቀንሰው ለግል ጥቅማቸው ያዋሉት ገንዘብ የሌለ መሆኑንና ይህንንም የሚያስረዳ በቂ ማስረጃ ያላቸው በመሆኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም የሚል ነው፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አራተኛ ተጠሪ አሰሪና ሰራተኛ ክርክር ችሎት ተከራክረው ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል ጥፋት አልፈፀሙም ተብሎ መወሰኑ ተጠሪዎች በድርጅቱ ላይ አድርሰዋል የተባለውን ኪሣራ እንዲከፍሉ አመልካች ካቀረበው ክስ በኃላፊነት አይጠየቁም ብሎ ለመወሰን የሚያስችል ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ እልባት ማገኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ችሎት ሰራተኛው ከሥራ የሚያሰናብት ጥፋት አልፈፀመም በማለት የሚሰጠው ውሣኔ አሰሪው ሰራተኛውን በፍትሐብሔር ክስ አቅርቦ ከመጠየቅ የሚገድብ እንዳልሆነና በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 5 ንኡስ አንቀጽ 1 መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል ከዚህ በፊት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36710 ጥር 21 ቀን 2001 ዓ.ም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ችሎት የሚወስነው መሰረታዊ ጭብጥ ሰራተኛው በፍትሐብሔር ተጠያቂነትና ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? የሚለው ሣይሆን አሰሪው ሰራተኛውን ከሥራ ለማሰናበት የሚያበቃ በቂ ምክንያት አለ ወይስ የለም? የሥራ ስንብቱ የሕጉን ሥርአት ተከትሎ የተፈፀመ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ተጠሪዎች ተሻሽሎ በተተመነው የጤፍ በመሸጫ ዋጋ በታች በመሸጣቸው ብር 16,818.10(አስራ ስድስት ሺ ስምንት መቶ አሥራ ስምንት ብር ከአስር ሣንቲም) በድርጅቱ ላይ ጉድለት አድርሰዋል በማለት ክስ የቀረበ ሲሆን ክሱን ያስረዱልኛል የሚላቸውን ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡ ሁለተኛና አራተኛ ተጠሪ ለጉድለቱ ተጠያቂ አይደለንም በማለት የተከራከሩ ሲሆን ይህንን ክርክር የሚደገፍ ማስረጃ ዝርዝር አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ደረሰ የሚለው የብር 16,818.10(አስራ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ አስራ ስምንት ብር ከአስር ሣንቲም) ኪሣራ በእርግጥ በድርጅት ላይ የደረሰ ጉዳት ነው ወይስ አይደለም? ጉድለቱ የደረሰ ነው የሚባል ከሆነ ተጠሪዎች በኃላፊነት ይጠየቃሉ ወይም አይጠየቁም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመዘን ውሣኔ መስጠት ሲገባው አሰሪና ሰራተኛ ክርክር ችሎት የአራተኛ ተጠሪ ከሥራ መሰናበታቸው አላግባብ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ የፍትሐብሔሩን ክስ የሚያስቀር የመጨረሻ ውሣኔ አድርጐ በመውሰድ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበውን ክስና ማስረጃና ተጠሪዎች የሚያቀርቡትን መልስና ማስረጃ በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ 341/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የራሳቸው ይቻሉ

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 50225

ሐምሌ 5 ቀን 2002 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - የቀረበ የለም፡፡

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ት ዝናሽ አሰፋ
2. አቶ ሙላት አሰፋ
} የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የጉዳት ካሣ ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ ባለቤት ላይ በመሠረቱት ከውል ውጪ ኃላፊነትን መሠረት ባደረገ ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ይዘት ባጭሩ፡- የተጠሪዎች አባት በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ ተገጭታ ሕይወታቸው በማለፉ አባታቸው በሕይወት እያሉ በሚሰሩት ሥራ በቀን ብር 22.00 /ሃያ ሁለት ብር/ እያገኙ ከዚሁ ገቢ ስልሳ ከመቶ የሚሆነውን እየሰጧቸው ያስተዳድሯቸው የነበሩ መሆኑንና ሟች አባታቸው በመኪና ግጭት ሲሞቱ እድሜያቸው 40 ዓመት እንደበሩ፣ ወደፊትም እስከ ስልሳ አምስት ዓመት ሊደርሱ ይችሉ እንደነበር በመግለጽ በዚሁ ጉዳት ምክንያት በአጠቃላይ የብር 125,230.00 /አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሣ ብር/ ጉዳት እንደደረሰባቸው በመጥቀስ ይህንኑ የጉዳት መጠን እንዲተካላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የመኪናው ባለቤትና አሽከርካሪው በሌሉበት ጉዳዩ የታየ ሲሆን የአሁኑ አመልካች በጣልቃ ገብነት ወደ ክርክሩ ገብቶ የተጠሪዎች አባት በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ ተገጭተው ሕይወተቸው ሲያልፍ እድሜያቸው ከአስራ ስምንት ዓመት በላይ የሆኑና ራሳቸውን መቻል እና ማስተዳደር የሚችሉበትና ከዚህም አልፎ አባታቸውን ሊጦሩ የሚችሉ መሆኑን በመግለጽና ለክሱ ኃላፊነት እንደሌለው በመጥቀስ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095/1/ ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ ዋቢ በማድረግ ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መሠረት በማድረግ የተሽከርካሪውን ባለቤት ለጉዳቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2081 መሠረት ኃላፊ አድርጎ አመልካችን ተጠያቂ አድርጎአል፡፡ የጉዳት መጠኑንም በአጠቃላይ ብር 21,000.00 /ሃያ አንድ ሺህ/ አድርጎ አመልካች እስከ ሰላሳ ሺህ ብር በገባው የዋስትና ግዴታ መሠረት እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ሕዳር 01 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪዎች ጉዳቱ ሲደርስ እድሜያቸው ከአስራ ስምንት ዓመት በላይ ሆነው እያለ ጉዳቱ በቀለብ መልክ እንዲከፈል ተብሎ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095/1/ እና ስለቀለብ የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን መንፈስ ያላገናዘበ

በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም እድሜያቸው ከአሥራ ስምንት ዓመት በላይ ለሆናቸው ተጠሪዎች አመልካቹ ከሟቹ አባታቸው ሲያገኙ የነበረውን ቀለብ በካሣ መልክ ይክፈል የመባሉን አግባብነት ለማየት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ ክርክር ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች አባታቸው በአመልካች ደንበኛ ተሽካርካሪ ተገጭተው ሲሞቱ እድሜአቸው ከአሥራ ስምንት ዓመት በላይ መሆኑን፣ በወቅቱ ተማሪዎች ሆነው በሟች አባታቸው ሲረዱና ሲተዳደሩ የነበሩ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ከማረጋገጡም በላይ አመልካች በዚህ የሰበር ችሎትም ሆነ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች እድሜአቸው አስራ ስምንት ዓመት ሞልቷቸዋል ብሎ ከመከራከር ውጪ በእርግጥም ራሳቸውን ይችሉ የነበረ ሁኔታ ስለመኖሩ ግልጽ አለመከራከሩን ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪዎች እድሜአቸው አስራ ስምንት ዓመት በላይ ስለሆነ ብቻ በመኪና ግጭት ሕይወቱን ያጣውን አባታቸውን ካሣ አይገባቸውም ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የጉዳት ካሣ በቀለብ መልክ እንዲከፈል ሕጉ ሲፈልግ እድሜው አስራ ስምንት ዓመት የሞላው ሁሉ ሊጠይቅ አይችልም ማለት እንደሆነ ስለቀለብ የተደነገጉት ድንጋጌዎች የሚያስረዱት ጉዳይ ነው፡፡ ዋናውና ትልቁ ቁም ነገር ቀለብ ጠያቂው ያለበት ሁኔታ ነው፡፡ ቀለብ ጠያቂው ቀለቡን ሊያገኝ የማይችልበት ሁኔታ ውስጥ መሆኑ ከተረጋገጠ አካለ መጠን የመድረሱ ጉዳይ ግምት ውስጥ የሚገባበት ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪዎች በወቅቱ ተማሪዎች የነበሩ መሆናቸው ሲታይም ትምህርታቸውን እየተማሩ በቀላሉ ራሳቸውን የማስተዳደር አጋጣሚ ይኖራቸዋል ብሎ ለመደምደም ከነባራዊ ሁኔታ አንፃር ሲታይ የማያስኬድ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ሟች አባታቸው በመኪና ሲገጩ አስራ ስምንት ዓመት ስለሞላቸው ብቻ የጉዳት ካሣውን በቀለብ መልክ ሊያገኙ አይገባም በማለት አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095/1/ እና ስለቀለብ ስለተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ በመሆኑ ይህ ችሎት የሚቀበለው ሆኖ አላገኘውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሣኔ በተጠሪዎች በኩል የቀረቡትን ክርክሮችንና ማስረጃዎችን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በሕጉ አተረጓጎምና አተገባበር ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01931 ሐምሌ 14 ቀን 1997 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35340 ጥቅምት 19 ቀን 2002 ዓ.ም. የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት ኅዳር 04 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፤ ይፃፍ፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

# የዳኘነት ስልጣን

የሰ/መ/ቁ. 34665

ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- 1. አቶ ናትናኤል ዘውገ
2. አቶ ኃይለየሱስ ዘውገ } ጠበቃ አበራ ጣሰው ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- 1. ወ/ሮ እግዜሩ ገ/ሕይወት ጠ/አለም ወ/አረጋይ ቀረቡ

2. የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ነ/ፈጅ ደስታ ሊበን ቀረቡ

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካቾች በአንደኛ ተጠሪ ላይ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የመሰረቱት ክስ ነው፡፡ አመልካቾች ከሟች አባታቸው በውርስ ያገኙትን በወረዳ 1 ቀበሌ 8 ውስጥ የሚገኘውን የቤ/ቁ 1273 የሆነውን ቤት አንደኛ ተጠሪ ቀድሞ ከሚያስተዳድረው ሁለተኛ ተጠሪ መከራየታቸውን ምክንያት በማድረግ አለቅም ስላሉ የቤቱ ኪራይ ከፍለው ቤቱን እንዲያስረክቡ ክስ መስርተዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ለክሱ መልስ እንዲሰጡና ሁለተኛ ተጠሪም በክርክር ውስጥ እንዲገባ ከተደረገ በኂላ ፍ/ቤቱ የአመልካቾች የቤት ባለቤትነት ደብተር በአ/አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት የስራና ከተማ ልማት ቢሮ የተሰረዘ በመሆኑ አመልካቾች ቤቱን ለመረከብ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች ውሳኔውን ለማስለወጥ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡት ይግባኝም ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ የአሁኑም የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካቾች ዋነኛ ቅሬታ የአ/አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት የስራና ከተማ ልማት ቢሮ የባለቤትነት ደብተሩን ለመሰረዝ ስልጣን የለውም የሚል ነው፡፡ ችሎቱም የስራና ከተማ ልማት ቢሮ ደብተሩን የሰረዘው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲል አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው በሰበር ችሎት ለመመርመር የቀረበው ነጥብ የአ/አበባ ከተማ የስራና ከተማ ልማት ቢሮ የአመልካቾችን የባለቤትነት ደብተር ለመሰረዝ ስልጣን አለው የለውም የሚለው ነው፡፡ ከክርክሩ የአ/አበባ ከተማ ስራና ከተማ ልማት ቢሮ ደብተሩን የሰረዘው የስራና ከተማ ልማት ሚ/ር በ22/07/1991 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በሚ/ር መስሪያ ቤቱ ይገኙ የነበሩ የቤት ጉዳዮች ከስራተኞቹ ጋር ለአ/አበባ መስተዳድር ምክር ቤት እንዲያስረክብ ከጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት በተላለፈው ትእዛዝ መሰረት ከየካቲት 1 ቀን 1991 ዓ.ም ጀምሮ እነዚህ ጉዳዮች በአ/አበባ መስተዳድር ምክር ቤት ስራና ከተማ ልማት ቢሮ እንዲያስተዳድር በመግለፁ ምክንያት መሆኑን

ተገንዝበናል፡፡ የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን ስራ የመከታተልና በበላይነት የመቆጣጠር ስልጣን ያለው እንደመሆኑ መጠን የስራና ከተማ ልማት ሚ/ር ቤቶችን የሚመለከት ጉዳይ ለአ/አበባ ስራና ከተማ ልማት ቢሮ እንዲያስተላልፍ በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ስራውንና ሰራተኞቹን ለቢሮው አስተላልፏል፡፡ በዚህ መሰረት ቢሮው ስራውን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ በዚህም ወቅት ነው የአመልካቾች የቤት ባለቤትነት ደብተር የተሰረዘው፡፡ ስለሆነም አመልካቾች ደብተሩ ስልጣን በሌለው አካል ነው የተሰረዘው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ የስር ፍ/ቤትም አመልካቾች የቤት ባለቤትነት ደብተር ስልጣን ባለው አካል የተሰረዘ በመሆኑ ክሳቸውን ተቀባይነት የለውም ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19448 ሐምሌ 28 ቀን 1996 የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33840 ጥቅምት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 46220

ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የደቡብ ክልል የሐዋሣ ከተማ ማዘጋጃ ቤት - ነ/ፈጅ ከተማ ጌታነህ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የሐዋሳ ደብረ ምህረት ቅ/ገብርኤል ገዳም - ጠበቃ ቸርነት ገ/ሕይወት - ቀረቡ፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነ ተጠሪ በሐዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች እና በሌሎች ሁለት ተከሣሾች ላይ ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በክሷ ከቤ/ክርስቲያኗ ይዞታ 1632 ካ.ሜ. ለሥር አንደኛ ተከሣሽ ለጊዜያዊ ማረፊያነት ተሰጥቷቸው የነበረ መሆኑን፣ ተከሣሹ አሁን ቤት መስራታቸውን፣ ተከሣሹ ካርታና ፕላን ጠፋብኝ ብለው አዲስ ካርታ እንዲሰጣቸው ለወረዳ ፍ/ቤት አመልክተው እንዲሰጣቸው ማድረጋቸውን፣ አመልካችም ተገቢውን ማጣራት ሳያደርግ አንደኛ ተከሣሽ ከያዙት ቦታ ላይ ለ832 ካ/ሜ ይዞታ ካርታ ሲሰጣቸው ቀሪው 800 ካ/ሜ ለሥር ሁለተኛ ተከሣሽ በሊዝ በመምራት ካርታና ፕላን መስጠቱን በመግለጽ ለሁለቱም ተከሣሾች የተሰጠው ካርታና ፕላን ተሰርዞ ይዞታው ለተጠሪ ይመለስ በማለት ጠይቃለች፡፡ አመልካችም ለቀረበው ክስ ቤ/ክርስቲያኗ ያቀረበችው ማስረጃ ከአ/ቁ 47/67 በፊት የተሰጠ ስለሆነ ከአዋጁ በኋላ መሠረዙን፣ ከአዋጁ በኋላ የተሻሻለውን ምስክር ወረቀት አለመወሰዷን፣ ካርታውና ፕላኑ የተሰጠው በፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት መሆኑን፣ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቦታ ከመንግሥት የተወረሰ መሆኑን፣ ለሥር ተከሣሾቹ ካርታና ፕላን የተሰጠው በሊዝ ኮሚቴ ስለሆነ አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው ለሊዝ ቦርድ ኮሚቴ እንደሆነ፣ ለከፍተኛ ፍ/ቤት የሚቀርበው የካሣ ጉዳይ ብቻ እንደሆነ በመከራከር ክሱ ውድቅ እንዲሆንለት ጠይቋል፡፡ ሌሎቹም ተከሣሾች መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ይዞታው ከአ/ቁ. 47/67 ወዲህ በተጠሪ እጅ አይደለም፣ አንደኛ ተከሣሽ ይዞታው በሠራተኛነት ሳይሆን በባለቤትነት የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቷቸዋል፣ ከይዞታቸው ከፊሉ በሊዝ ኮሚቴ ፀድቆ ባለቤት ሆነዋል፡፡ ቀሪውን በሊዝ ኮሚቴ ለሁለተኛ ተከሣሽ ተሰጥቷል፤ አመልካች በሊዝ ኮሚቴ ውሣኔ

መሠረት ነው የሚፈጽመው፣ በሊዝ ኮሚቴ ውሣኔ ቅር ከተሰኘች ቅሬታው ማቅረብ ያለበት ለሊዝ ኮሚቴ ነው፣ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት በፍርድ ሊሰረዝ አይችልም፣ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ተጠሪ ለደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባ ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ይህ ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበች ሲሆን ችሎቱ ይዞታው የተጠሪ መሆኑ ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ፣ ይዞታው የተሰጠው ለሕዝብ አገልገሎት ሳይሆን ለሌላ ግለሰብና መ/ቤት በመሆኑ ሕጋዊ አይደለም፣ ለሕዝብ ጥቅም ቦታ ስለማስለቀቅ በወጣው አዋጅ መሠረት ተገቢው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ እንዲለቁ የተደረገ ስላልሆነ ፍ/ቤቶቹ ስለቦታ ማስለቀቅ የተመለከቱት አዋጆች ተጠቅመው ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም ሊሉ አይችልም በማለት ተከሣሾቹ ይዞታውን ለተጠሪ እንዲመልሱ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ካርታው እንዲሰረዝ በፍ/ቤት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ግራ ቀኙ ቀርበው ክርክራቸው ተሰምቷል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

አመልካች ክስ ያቀረበችው ከይዞታዋ ላይ ተቀንሶ ለሥር አንደኛ እና ሁለተኛ ተከሣሽ የተሰጣቸው ስለሆነ የተሰጣቸው ካርታና ፕላን ተሰርዞ ይዞታውን ተከሣሾቹ እንዲመልሱላት ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የሐዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ የቀረበበትን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ለዚህም መሠረት ያደረገው ሁለት ነገሮችን ነው፡፡ አንደኛው አከራካሪው ይዞታ ለሥር አንደኛ እና ሁለተኛ ተከሣሾች የተሰጠው በሊዝ ቦርድ ኮሚቴ ስለሆነ በኮሚቴው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ቅሬታውን ማቅረብ ያለበት ለቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንጂ ለፍ/ቤት አይደለም የሚል ሲሆን ሁለተኛው የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በፍርድ ለመሠረዝ የማይቻል ለመሆኑ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ ውሣኔ ሰጥቷል በሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም በቅድሚያ ክስ የቀረበበትን ጉዳይ ለማስተናገድ ፍ/ቤቶች ስልጣን ያላቸው መሆን አለመሆኑን መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ ሂደት ተጠሪ ይዞታዬ ነው የምትለውን የቦታ ይዞታ ቀንሶ ለሥር አንደኛ እና ሁለተኛ ተከሣሾች ሰጠው የሊዝ ቦርድ ኮሚቴ መሆኑን ተረድተናል፡፡ የከተማን ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የወጣው የፌዴራል አ/ቁ. 272/2994 እንዲሁም ክልሉ ይህንን አስመልክቶ ያወጣቸው አዋጅና ደንቦች የሊዝ ቦርድ ኮሚቴ በሰጠው የቦታ ማስለቀቅ ውሣኔ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታውን ማቅረብ ያለበት በቅድሚያ ውሣኔውን ለሰጠው አካል ሲሆን በዚህ አካል ምላሽ ካልተስማማ ይግባኙን ለቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ነው፡፡ በካሣ ጉዳይ ላይ ካልሆነ በቀር ጉባኤው የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው ይዞታውን እንዲለቀቅ የተደረገው በሕግ የተመለከቱትን ሥርዓቶች ሳይከተል ከሆነ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ይግባኝ ሊያቀርብ የሚችለው ለጉባኤው ነው፡፡ ለፍ/ቤት ይግባኝ ሊቀርብ የሚችለው የካሣውን ጉዳይ በተመለከተ ብቻ ነው፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ተጠሪ ከይዞታዋ ላይ ተቀንሶ ለሥር ተከሣሾች የተሰጠው በሊዝ መሆኑ ስለተረጋገጠ ይዞታው የተሰጠው በሕጉ አግባብ ካልሆነ ይህንኑ ቅሬታ በቅድሚያ ውሣኔውን ለሰጠው አካል፣ በመቀጠል ደግሞ ለቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ ነበረባት፡፡ በመሆኑም ከጅምሩም ቢሆን ክስ የቀረበበትን ጉዳይ ፍ/ቤቶች አይተው ለመወሰን ስልጣን አልነበራቸውም፡፡ ከፍ ሲል በተጠቀሱት ምክንያቶችም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሊዝ ኮሚቴ የተወሰነውን ጉዳይ አከራክሮ ውሣኔ መስጠቱ ያለስልጣኑ በመሆኑ መሠረታዊ ሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡ ስለዚህም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የደ/ብ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 27382 ሚያዝያ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሐዋሣ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05446 ታህሣሥ 1 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23971 የካቲት 4 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 42928

ጥር 12 ቀን 2002 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ አክሊሉ አበባው - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ድራጋዶስ ኮንስትራክሽን - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከውል ውጪ ኃላፊነትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም. በመሠረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራኒዮ አካባቢ የመንገድ ሥራ ሲያከናውን በአመልካች ንብረት ላይ ግምቱ ብር 25,569.85 /ሃያ አምስት ሺህ አምስት መቶ ስልሣ ዘጠኝ ብር ከሰማኒያ አምስት ሳንቲም/ የሆነ ጉዳት ማድረሱን ገልፆ ይህንኑ ገንዘብ ከነወለዱ ወጪው ጋር እንዲተካ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ ተከሣሽ ድርጅት በግሪክ አገር ሕግ መሠረት የተቋቋመ አድራሻውም አቴንስ የሆነ የውጭ ሀገር ኩባንያ ነው፣ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥም አልተመዘገበም ስለዚህ በመልካችና በተጠሪ መካከል የሚነሳ አለመግባባት በየትኛው ሀገር ሕግ ይታያል፣ በየትኛው ፍርድ ቤት ይታያል የሚል የግል ዓለም አቀፍ ሕግ ስለሚያስነሳ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንስቶ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ይህንኑ የተጠሪን መቃወሚያ መሠረት በማድረግ ጉደዩን መርምሮ ጉዳዩ የግል ዓለም አቀፍ ሕግ የሚያስነሳ በመሆኑና ሥልጣኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለውም ሲል የአመልካችን ክስ በብይን ዘግቷል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት

አቅርቦ ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ብይን ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም. በዓፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ብይን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ በተጠሪና በአመልካች መካከል ያለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ጉዳቱ የደረሰው ተጠሪ ኢትዮጵያ ውስጥ ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት ስለሆነ እና በንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት ደግሞ ክሱ መመስረት ያለበት ጉዳቱ በደረሰበት ሀገር ሕግና ፍርድ ቤት መሆኑ እየታወቀ የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11/2ሀ/ ያላግባብ ተጠቅሶ ክሱ መዘጋቱ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን መዝጋቱ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ጉዳዩ በቃል ሊሰማ በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ ባለመቅረቡ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ብይንና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአመልካች ክስ መሠረት ያደረገው ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚመለከት የሚገዙ ድንጋጌዎች መሆኑ፣ ተጠሪ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ጉዳት ያደረሰው ስራውን በኢትዮጵያ ውስጥ ሲያከናውን መሆኑን ክሱ የቀረበውም ጉዳቱ በደረሰበትና ንብረቱ በሚገኝበት ክልል በሚገኘው ፍርድ ቤት መሆኑን ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተነሳው ክርክር የንብረት ጉዳት ካሣ በመሆኑ ክሱ ሊመሠረት የሚገባው የገንዘቡ መጠን ግንዛቤ ውስጥ ሲገባ የገንዘብ መጠኑን መሠረት አድርጎ የሚወስነው የሥረ- ነገር ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ጉዳቱ በደረሰበትና ንብረቱ በሚገኝበት ክልል በሚገኘው ፍርድ ቤት ነው፡፡ ይህ ስለመሆኑም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 27/1/ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዚህ አንፃር ተገንዝቦ አይቶ የመወሰን ስልጣን የራሱ ሆኖ እያለ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11/2/ሀ/ ድንጋጌን ያለቦታው ጠቅሶ የአመልካችን ክስ መዝጋቱ እና ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ይህንኑ መቀበሉ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 09737 ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 69916 ሕዳር 15 ቀን 2001 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው በመሆኑ የአመልካችን ክስ ተቀብሎ ግራ ቀኙን በቀሪ መከራከሪያ ነጥቦች ላይ በማከራከር ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 42866

መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ብርሃነ ጥዑም - ሙሉጌታ ወንድም ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የጉምሩክ ባለሥልጣን - ዳንኤል ጥበቡ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ያላግባብ የተከፈለ ቀረጥ ይመለስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባሁኑ ተጠሪ ላይ ሚያዝያ 01 ቀን 1990 ዓ.ም በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም በዲክላራሲዮን ቁጥር 718/90፣ 719/90 እና 1600/90 የተመዘገቡትንና በቻይና፣ ማለዥያ፣ ኮሪያ እና ጃፓን ሃገር የተሰሩትን የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ከባንክ በተገኘ የውጭ ምንዛሬ በመግዛት በምፅዋ ወደብ በኩል ወደሃገር ውስጥ ሲያስገቡ የተጠሪ ድርጅት ዛለአንበሳ ጣቢያ ብር 87,760.65(ሰማንያ ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ ከስልሳ አምስት ሳንቲም) የቀረጥ ክፍያ አመልካች እንዲከፍሉ ጠይቋቸው ክፍያ ከፈፀሙ በኂላ ተጠሪ ቀሪ የቀረጥ ሂሳብ አለብህ በማለት እቃዎችን በመያዙ ምክንያት ያላግባብ ብር 244,866.10(ሁለት መቶ አርባ አራት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ስድስት ብር ከአስር ሳንቲም) እንዳስከፈላቸው ገልፀው ይህንኑ ገንዘብ ተጠሪ ከነወለዱ እና ከክሱ ወጪና ኪሳራ ጋር ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚይሳይ ነው፡፡ ተጠሪም ለክሱ በሠጠው መልስ ቀረጡን በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ያስከፈለ መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃዎችን በመመርመር ተጠሪ ቀረጡን ያስከፈለበት አግባብ ከመመሪያ ቁጥር 10/96 ውጪ ነው በማለት የተጠሪን ክርክር ውድቅ አድርጎ ለክሱም ኃላፊ በማድረግ ክሱ የተመሰረተበትን ገንዘብ ከሚያዝያ 08 ቀን 1990 ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ 9% (ዘጠኝ በመቶ) ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ

ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር ተጠሪ የቀረጡን ገንዘብ የሚመልስበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥር 04 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበውን የተጠሪ መከራከሪያ ነጥብ መሰረት አድርጎ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ መሻሩ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ስነ-ስርዓታዊ የሆነውን ምክንያት መነሻ በማድረግ የሠጠውን ዳኝነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) አንፃር አግባብነቱንና የጉዳዩን ፍሬ ነገር የሕግ ክርክር ተመልክቶ ውሳኔ መስጠት ነበረበት ወይስ አልነበረበትም? የሚሉትን ነጥቦች ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ ተጠሪም በነገረ ፈጁ አማካኝነት ጥር 27 ቀን 2002 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው መልስ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ የአዋጅ ቁጥር 68/89 አንቀፅ 48(7/11)፣ 53 እና መመሪያ ቁጥር 10/1996 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ውሳኔው ሊፀና ይገባዋል በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች ጠበቃም የካቲት 15 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል ወይስ አልተፈፀመበትም? የሚለው ጥቅል ጭብጥ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ክሱን ሊመሰርቱ የቻሉት ያላግባብ የከፈልኩት የቀረጥ ገንዘብ ሊመለስልኝ ይገባል በሚል ሲሆን አመልካች በበኩሉ ክፍያውን ያስፈፀመው በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የዋጋ መረጃን በማየት መሆኑን ገልፆና ያላግባብ የተከፈለ የቀረጥ ገንዘብ የሌለ መሆኑን ጠቀሶ ተከራክሯል፡፡

የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋም እና አሰራሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀፅ 47 ላይ እንደተመለከተው ወደ ሃገር ውስጥ ለሚገባ ማናቸውም ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ የሚሆነው በትክክል ለዕቃው የተደረገ ጠቅላላ ወጪ ነው፡፡ ዕቃው የተገዛበት ዋጋ ደግሞ ከወጪዎች አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም ለቀረጥ ማስከፈያ መሰረት የሚሆነው ትክክለኛ የዕቃው ዋጋ ስለመሆኑ ሕጉ በዋናነት ያስቀመጠው አሰራር ነው፡፡ ከዚሁ የሕጉ መንፈስ መረዳት የሚቻለው ሌላው ቁም ነገር ደግሞ በአስመጪው የሚቀርበው የእቃው ዋጋ ግምት ትክክለኛውንም የዕቃውን ዋጋ የማይናገር መሆኑ ከተረጋገጠ የቀረጥ ሂሳብን ለማስላት መነሻ (መሰረት) ሊሆን የማይችል መሆኑን ነው፡፡ በመሰረቱ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ዕቃ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ምን ያህል እንደሆነና እንዴት እንደሚሰራ በአዋጅ ቁጥር 60/1989 አንቀፅ 48 ስር ተዘርዝሯል፡፡ የተጠቀሰው የአዋጁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 እና 8 ድንጋጌዎች ሲታዩም የጉምሩክ ባለስልጣን በአስመጪው የቀረበለትን የዋጋ ግምት አልቀበልም በማለት የቀረጥ ሂሳቡን ለማስላት ሌሎች አማራጭ መንገዶችን መከተል የሚችል ስለመሆኑ ያስገነዝባሉ፡፡ የተጠቀሰው የአዋጅ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር 6 ድንጋጌ ደግሞ የጉምሩክ ባለስልጣን በአስመጪዎች የቀረበለትን የዋጋ ግምት አልቀበልም ስለሚልበት ሁኔታ የገቢዎች ቦርድ መመሪያ ማውጣት የሚችል መሆኑን ደንግጓል፡፡ በዚሁ ሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረትም የተጠቀሰው አካል መመሪያውን ማውጣቱ የተረጋገጠ ሲሆን በዚህ መመሪያ መሰረትም በትራንዛክሽን ዋጋ ላይ የተመሰረተ የጉምሩክ ዋጋ አተማመን ተግባራዊ የማይሆንባቸው ምክንያቶች ተቀምጠዋል፡፡ ከእነዚህም ምክንያቶች መካከል ወደ አገር ውስጥ የገባው እቃ ዋጋ ከአንድ ዓይነት እና ከተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ በጉምሩክ ከሚፈቀደው ልዩነት በላይ አንሶ መገኘት ስለመሆኑ መመሪያው በአንቀፅ 1(5) ስር አስቀምጧል፡፡ ወደ ሃገር በገባ ወይም ከሀገር በወጣ ዕቃ ላይ የተከፈለው ቀረጥ በማናቸውም ምክንያት ሊከፈል

ከሚገባው ቀረጥ ያነሰ መሆኑ በምርመራ የተደረሰበት እንደሆነ ደግሞ ባለሥልጣኑ የእቃውን ባለቤት ወይም ወኪሉን በልዩነት ያልተከፈለውን ቀረጥ ማስከፈል እንደሚችል በአንቀጽ 57(1) ስር በግልፅ አስፍሯል፡፡ የዋጋ ኢንቮይስ ውድቅ የሆነበት ቀረጥ ከፋይ ቅሬታ ካለው በአዋጅ ቁጥር 60/1989 አንቀጽ 53 መሰረት ለተጠሪ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ አቅርቦ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ የሚችል ሲሆን፤ በዚሁ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ቅሬታ ካለው ብቻ ወደሚመለከተው ፍርድ ቤት መሄድ የሚችል መሆኑን ተመልክቷል፡፡ ይህ ስርዓት ሳይፈፀም በቀጥታ በፍ/ቤት ክስ የሚመሰረትበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከተጠቀሰው ድንጋጌ መንፈስ እና ይዘት መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ በሕጉ ላይ የተመለከተው የስነ-ስርዓት ጥያቄ ነው፡፡ ይኸው የስነ-ስርዓት ጉዳይም በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት ባግባቡ መፈፀም አለበት፡፡ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎም ይታሰባል፡፡

በብልጫ የተከፈለ የቀረጥ ገንዘብ ለከፋዩ ሊመለስ እንደሚገባ አዋጁ በአንቀፅ 55 ስር በግልፅ ደንግጓል፡፡ ተጠሪ ቀሪ የቀረጥ ክፍያ መኖሩን አረጋግጦ ተገቢ ነው ያለውን የክፍያ ጥያቄ አመልካች እንዲፈፅሙ ጠይቋል፡፡ ይህም የሚያሳየው የአመልካች ኢንቮይስ ውድቅ የተደረገ መሆኑን ሲሆን አመልካች በአዋጁ አንቀፅ 53(1) መሰረት ያነሱት እና የተጠቀሙበት ተቃውሞ አለመኖሩን ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ክስ የመሰረቱበትን የቀሪ ቀረጥ ክፍያ ጥያቄ በተጠሪዎች በኩል በአዋጁ አንቀጽ 53(1) መሰረት ተቃውሞ ቀርቦ ተገቢው ለውጥ ባልተደረገበት ሁኔታ በፍርድ ቤት ክስ መስርተው ተቀባይነት ማግኘታቸው ስነ ስርዓቱን ያልጠበቀ ነው በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መወሰኑ የሚነቀፍበት የስነ-ስርዓትም ሆነ የመሰረታዊ ሕግ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሠጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 36410 ሕዳር 16 ቀን 2000 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35369 ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 48111

ሚያዝያ 13 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ታሪኳ ላዕከ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ቂጤሳ ገብሬ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድን የሚመለከት ነው፡፡

ተጠሪ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ክሱን ያቀረቡት በአመልካች ድርጅት በጥበቃ ስራ ላይ ተመድቤ በማገልገል ላይ እያለሁ አመልካች በብረታ ብረት ብየዳ ስራ ሰራተኞችን አወዳድሮ ለማሳደግ የካቲት 19 ቀን 1999 ዓ.ም ባወጣው የውስጥ ማስታወቂያ የተጠየቀውን መስፈርት አሟልቼ በመስሪያ ቤቱ የውስጥ አሰራር መመዘኛ መሰረት 30% ሲቀየር 11/40/30 አምጥቻለሁ፣ ይህ ውጤት ከሌላው የስራ ምዘና ውጤት ጋር ሲደመር 54.76% በመሆኑ የሚያሳልፈኝ ሆኖ ሳለ አመልካች የተግባር ፈተና ማለፊያ ነጥብ 60% በላይ መሆን ስላለበትና የስራ መደቡም ከፍተኛ ችሎታና ጥንቃቄ የሚጠይቅ ስለሆነ በተግባሩ ስላላለፍክ እድገቱን ልታገኝ አይገባም በማለት ማስታወቂያ ስላወጣ ማስታወቂያ ተሰርዞ እድገቱ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በሚል ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ በዚህም መሰረት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የሌለው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ተጠሪ ዝቅተኛ ነጥብ ያመጡ በመሆኑ ቦታ ሊሰጣቸው እንደማይገባ እና በውድድር ቅጥሩን ለመፈፀም ማስታወቂያን ማውጣቱ ተገቢ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ በግራ ቀኙ በኩል

የቀረቡትን ማስረጃዎችን በመመርመር ተጠሪ የተግባርና የፁሑፍ ፈተናውን ስለማለፋቸው ያቀረቡት ማስረጃ አለመኖሩን፣ በተቃራኒው አመልካች ድርጅት ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች የሚያስረዱት ተጠሪ ፈተናውን ወስደው ከተቀመጠው መስፈርት ዝቅተኛ ያመጡ መሆኑን ጠቅሶ ክሱን ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ብቸኛ ተወዳዳሪ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በጠቅላላ ውጤት ከመቶ 54.76 በማግኘት ከ50% በላይ ያገኙ ሆኖ እያለ በተግባርና በፁሑፍ ፈተና ከመቶ 60 ስላጡ በሕብረት ስምምነት ወይም በሌላ መመሪያ በግልጽ እስካልተደነገገ ጊዜ ድረስ ይህንን ስላላሟላ ተብሎ ከውጪ ተወዳዳሪ እንዲቀርብ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚለውን ምክንያት በመያዝ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ የቦታውን መስፈርትና ውጤት ስለሚያሟሉ ሊሰጣቸው ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሐምሌ 14 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ጉዳዩን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት ያሁኑ አመልካች ያቀረበው መቃወሚያ መታለፉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ሕዳር 09 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ ተጠሪ ክሱን የመሰረቱት የእድገት ደረጃ ይሰጠኝ በሚል ሲሆን አመልካች ለተጠሪ ደረጃው ሊሰጥ አይገባም በማለት የሚከራከረው ተጠሪ የተወዳደሩበት የብየዳ የሥራ መደብ በወጣው የውስጥ ማስታወቂያ ሆኖ እንዲወዳደሩ እድል ተሰጥቷአቸው በሕብረት ስምምነት አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ 2፣ 3 እና 7 ድንጋጌዎች መሰረት ከመስፈርቶቹ አንዱ የሆነውን የተግባርና የፅሑፍ ፈተና ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምርታማነት ማሻሻያ ማዕከል ፈተና እንዲወስዱ ተልከው ፈተናውን ተፈትነው ያገኙት ውጤት 38% በመሆኑና የማለፊያ ነጥብ ደግሞ 60% እንደሆነ፣ ተጠሪ ያገኙት ነጥብም ዝቅተኛ መሆኑን ማዕከሉ በፅሁፍ የገለፀው ውጤትም ለመራጭ ኮሚቴ ቀርቦ የተወዳደሩበት የስራ መደብ የብየዳ ስራ በመሆኑ እና ይህ ደግሞ የተግባር ስራ ሆኖ ከፍተኛ እውቀትና ችሎታ እንደሚያስፈልገው ገልጾ ተጠሪ ይህንን ባለማለፋቸው ለቦታው ብቁ እንዳልሆኑ በመግለፅ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የተቻለው አመልካች ድርጅት ለቦታው ብቁ የሆነ ሰው ለመምረጥ የራሱ የሆነ መስፈርትና ሥርዓት የዘረጋ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ የሚከራከሩት መስፈርቱና ሥርዓቱን ስለማሟላ ቦታው ይገባኛል በማለት ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 18180 አግባብነት ያላቸውን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ድንጋጌዎችን በመመርመር የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን የወል የስራ ክርክሮችን ማየት መሆኑን፣ አንድ የስራ ክርክር የወል የስራ ክርክር ነው የሚባለው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ የሆነ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ መሆኑን፣ ባንፃሩ አንድ የስራ ክርክር የወል ሳይሆን የግል የስራ ክርክር ነው ሊባል የሚችለው የክርክሩ ውጤት በተከራካሪው ሰራተኛ (ሰራተኞች) ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሆኖ ሲገኝ ነው በማለት አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በሌላ በኩል አንድ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከማየቱ በፊት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ በራሱ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231(1(ሀ)) ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ ያስገነዝባሉ፡፡ ክርክሩ በየትኛውም ደረጃ ቢገኝ ይኸው መረጋገጥ አለበት፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ የስራ መደቡ ይሰጠኝ በማለት ያቀረቡት ክስ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆኖ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሲሆን የወል የስራ ክርክር ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው የሰራተኛ እና አሰሪ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ እንጂ ፍርድ ቤት አይደለም፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን ፍርድ ቤቱ አይቶ የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 31367 ጥቅምት 05 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 73044 ግንቦት 14 ቀን 2001 ዓ.ም የተሻረው ውሳኔ ፍርድ ቤቶቹ ስልጣን ሳይኖራቸው የተሰጠው በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተነሳው ክርክር የወል የስራ ክርክር እንጂ የግል ባለመሆኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

 መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 52600

ሚያዝያ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ቆዳ አክሲዮን ማህበር - ጠበቃ ጌታቸው ዓለሙ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ተስፋዬ ኃይሌ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድን ስልጣን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ክሱን ያቀረቡት በወጣው ክፍት በሌጦ ክረስት አዘገጃጀት ምርት ፎርማን ስራ መደብ ላይ ከሌሎች ሰራተኞች ጋር ተወዳድሬ በማሸነፍ እድገቱ እንዲሰጠኝ መደረግ ሲገባው ስለተከለከልኩ እድገቱ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ በዚህም መሰረት የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ተጠሪ ለግሉ ባቀረበው ጥያቄ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የሌለው መሆኑን፣ በሕብረት ስምምነቱ ደንብ አንቀፅ 15(4) እና በደረጃ እድገት አፈጻፀም መመሪያ አንቀጽ 11/1 እና 11/2 መሰረት የተጠሪ የደረጃ እድገት ኮሚቴ ውሳኔ የአሰሪው ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ ሳያፀድቅ የሻረው በመሆኑ ከሕግና ስርዓት ውጪ ተጠሪ የደረጃ እድገቱ በወሳኝ ቦርዱ እንዲወሰንላቸው ክስ ማቅረባቸው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመግለፅ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምስራቅ ሸዋ ዞን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድም የአመልካችን መከራከሪያ ነጥቦች ውድቅ አድርጎ ለተጠሪ የስራ መደቡ እንዲሰጣቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ቦርዱ የሠጠው ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የካቲት 04 ቀን 2002 ዓ/ም በጻፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ጉዳዩን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ለማየት ስልጣን የነበረው መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ መጋቢት 29 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃም ሚያዚያ 08 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 18180 አግባብ ያላቸውን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ድንጋጌዎችን በመመርመር የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን የወል የስራ ክርክሮችን ማየት መሆኑን፣ አንድ የስራ ክርክር የወል የስራ ክርክር ነው የሚባለው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ የሆነ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ መሆኑን፣ ባንፃሩ አንድ የስራ ክርክር የወል ሳይሆን የግል የስራ ክርክር ነው ሊባል የሚችለው የክርክሩ ውጤት በተከራካሪው ሰራተኛ (ሰራተኞች) ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሆኖ ሲገኝ ነው በማለት አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ የስራ መደቡ ይሰጠኝ በማለት ያቀረቡት ክስ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆኖ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ባለመሆኑ የወል የስራ ክርክር አይደለም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት እንጂ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አይደለም፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን ቦርዱ ለማየት ስልጣን አለው ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ሸዋ ዞን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመ/ቁጥር 650/01/2001 መስከረም 29 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 87699 ጥር 25 ቀን 2002 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተነሳው ክርክር የግል የስራ ክርክር እንጂ የወል ባለመሆኑ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 47134

ግንቦት 06 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈስ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የድሬዳዋ አስተዳደር ቀበሌ 06 አስተዳደር ጽ/ቤት - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ፋንታዬ ምትኩ - ወኪል ሻ/ል አባይነህ መብራቱ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች በሌሎች የቤቱ ተከራይ በተባሉት አራት ግለሰቦች ላይ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- የሚች አባታቸውን ወራሽነት በፍርድ ቤት ያረጋገጡ መሆኑን፣አባታቸው በሕይወት እያሉ በቀድሞ ቀበሌ 15(በአሁኑ ቀበሌ 05) ክልል ውስጥ ከአዋጅ ቁጥር 47/67 በፊት በቦታ ካርታ ቁጥር 3911 የሚታወቅ፣በቦታ ስፋት 136 ካሬ ሜትር ውስጥ የተሰራ ቤትና ቦታ እንዳፈሩ፣ይህንኑ ቤትና ቦታ በተጠሪ ስም ካርታ ተሰርቶ እንዲሰጣቸው ለቀድሞ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ለአሁኑ የቦታ አስተዳደርና የመሬት ልማት አቤቱታ አቅርበው ይኸው አካል ካርታው በተጠሪ ስም ተሰርቶ እንዲሰጥላቸው ለድሬዳዋ አጠቃላይ ምክር ቤት ደብዳቤ የፃፈላቸው መሆኑን፣ተጠሪም ሟች አባታቸው በቤቱ የበሉትን አበል በደረሰኝ ለቀበሌው ገቢ ማድረጋቸውን፣ሆኖም ከዚህ በኋላ እንዲመለስላቸው የተባለውን ቤት ቀበሌው ከተከራዮች አስለቅቆ ለተጠሪ ሊያስርክባቸው ያልቻለ መሆኑን ገልፀው ቤቱን እንዲያስረክባቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክሮችን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ የተከራከረው ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተወረሰ በመሆኑ ተጠሪ ክስ ለመመስረት መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑን፣ጉዳዩም በይርጋ የታገደ መሆኑን፣ጉዳዩን ለማየትም ፍርድ ቤት ስረ-ነገር ስልጣን የሌለው መሆኑን

የሚያሳዩ ነጥቦችን ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ ተጠሪ ቤቱ እንዲመለስላቸው ተወስኗል የሚሉት ስልጣን ያላቸው አካላት የሰጡትን ውሳኔ መሰረት በማድረግ አለመሆኑንና ክርክራቸው በተገቢው ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን በመጥቀስ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የድሬዳዋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር በአመልካች በኩል የቀረቡትን የክርክር ነጥቦችን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጐ አከራካሪውን ቤት አመልካች ተከራዮችን አስለቅቆ ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ውሳኔው ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ወኪል ሰኔ 19 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አከራካሪው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሶ ለረዥም አመታት ቀበሌው ሲያስተዳድር የቆየው እና ተጠሪ ቤቱ እንዲመለስ ተወስኖልኛል በማለት ያቀረቡት ክርክር ሥልጣን የሌላቸው አካላት የሰጡት ውሳኔ ሁኖ እያለ ቤቱ እንዲመለስላቸው ተወስኗል ተብሎ ቀበሌው ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክብ ተብሎ መወሰኑ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት አመልካች ለተጠሪ ያስረክብ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ የተጠሪ ወኪል ቀርበው ሕዳር 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ አራት ገጽ ማመልከቻ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ አግባብነት ያሳያሉ ያሏቸውን ነጥቦች በማንሳት መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ወኪል በበኩላቸው መጋቢት 08 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ ጉዳዩን የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ለማየት የሥረ-ነገር ስልጣን አለው ወይስ? የለውም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት አመልካች ሊያስረክብ ይገባል የሚሉት ቤቱ በወቅቱ ሥልጣን ባላቸው አካላት እንዲመለስ ተወስኖ የቤቱ ካርታም በተጠሪ ስም ተሰርቶ በቤቱ ማህደር ጋር ተያይዞ ይገኛል በሚል ሲሆን አመልካች በበኩሉ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት መንግስት ወርሶት ቀበሌው የሚያስተዳድረውና ለተጠሪ ቤቱ እንዲመለስ ውሳኔ ተሰጥቷል የሚባለው ስልጣን ባላቸው አካላት አለመሆኑን ገልፆ የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በሚገኙ ንብረቶች ወይም መነሻቸው በዚሁ አስተዳደር ክልል በሆኑ እጅግ በርካታ አይነት ጉዳዮች ላይ ሰፊ የዳኝት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አሉ፡፡ ከዚህ ደግሞ መገንዘብ የሚቻለው በዚህ ረገድ በተለይ የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን በሚመለከት ተገቢው ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባ መሆኑን ነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስም የከተማው አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ያላቸው የዳኝነት ሥልጣን በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/96 አንቀጽ 33 ሥር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በዚህ አንቀጽ ለፍርድ ቤቶቹ የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን በንኡስ አንቀጽ 1/ሪ/ የተመለከተው የከተማው አስተዳደር ከሚያስረዳድራቸው የመንግስት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱት ጉዳዮችን ያጠቃልላል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ሲታይም የከተማው አስተዳደር ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን የሚኖረው አከራካሪው ቤት ባለቤትነቱ የመንግስት ሆኖ በከተማው አስተዳደር የሚተዳደር መሆን የሚገባው መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ይህም ማለት ቤቱ የማን ንብረት ነው የሚል ወይም ስለቤቱ ባለሐብትነት በተመለከተ የሚነሳ ክርክር ሊኖር አይገባም፡፡ ክርክር ቢነሳ ሊሆን የሚችለው ከባለቤትነት መብት በመለስ ያሉትን ለምሳሌ ከኪራይ ውል ጋር በተያያዘ የሚነሱትን ጉዳዮች በተመለከተ ብቻ ነው፡፡ በከተማው ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቀውም ይኸው ከባለቤትነት በመለስ ያለ ክርክር ብቻ ነው፡፡ ክሱ ወይም ክርክሩ የባለሃብትነት ጥያቄ የሚያስነሳ ከሆነ ግን ከከተማው ፍርድ ቤቶች የስረ-ነገር የዳኝነት

ሥልጣን ውጭ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሚነሳ ክርክር የስረ-ነገር የዳኝት ሥልጣን የሚኖራቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡

እኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ባለቤትነት አከራካሪ የሆነ በመሆኑ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ክርክሩን የሰሙት የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ሳይኖራቸው ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሌላቸው በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00423/99 ሚያዝያ 12 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00299/2001 ሰኔ 15 ቀን 2001 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ሥር የሚወድቅ ባለመሆኑ ፍርድ ቤቶቹ ወደ ክሱ ስረ ነገር ገብተው ውሳኔ የሚሰጡበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ለክርርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 52041

ሰኔ 29 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የእርሻ መሣሪያዎችና የቴክ/አ/ማኀበር - ነ/ፈጅ ጌታቸው ደጉ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኢት/መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ጽጌረዳ ተሻገር - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲመረመር የቀረበው የአ/አ/ ከተማ ማኀበራዊ ፍ/ቤት የግራ ቀኙ ክርክር የመዳኘት ሥልጣን በተመለከተ ነው፡፡ የጉዳዩ አጀማመር ሲታይ ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ ነበር፡፡ የተጠሪ የክስ ምክንያት ንብረትነቱ የአመልካች የሆነው መኪና የተጠሪን ደንበኛ መኪና ገጭቶ ጉዳት አድርሷል በሚል ተጠሪ የከፈለውን ብር አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ሰባት /4977.00/ አመልካች እንዲተካ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን የተመለከተው በአ/አ ከተማ በቂርቆስ ክ/ከተማ የቀበሌ 04 ማኀበራዊ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ እንደ ክሱ አቀራረብ ወስኗል፡፡ በይግባኝ ሰሚ የአ/አ ከተማ ፍርድ ቤቶችም ይኸው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ከቀረበው አቤቱታ አንፃር ይህ ችሎት የተመለከተው ማኀበራዊ ፍ/ቤቱ ይህንን ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ሲሆን በዚህ ረገድ የተጠሪ ነ/ፈጅ ባቀረቡት የክርክር መልስ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 50 መሠረት ማኀበራዊ ፍርድ ቤት እስከ ብር አምስት ሺህ በሆነ የፍትሐብሔር ጉዳይ አከራክሮ የመወሰን ሥልጣን አለው ሲሉ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል ባጭሩ የተመለከትነው ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ሕጉን አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው የተጠሪ ክስ ምክንያት ከውል ውጪ ኃላፊነት የሚመለከት ሲሆን ለመክስ መነሻው ግን ተጠሪ ከደንበኛው ጋር አለኝ በሚል የመድን ውል መነሻ በንግድ ሕጉ በተመለከተው የመዳረግ መብት የቀረበ ስለመሆኑ ነው፡፡ በዚህ መዝገብ የቀረቡት ተከራካሪ ወገኖች አንደኛው ብቻ ሳይሆን ሁለቱም በፌዴራል መንግሥት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ ስለመሆናቸውም መረዳት ችለናል፡፡ ስለሆነም በዚህ መነሻ የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ተቀብሎ ለመወሰን የአ/አ ከተማ ማኀበራዊ ፍ/ቤት ሥልጣን አለውን? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት በተጠሪ የተጠቀሰውን አዋጅ ቁጥር 361/95 ከአዋጅ ቁጥር 25/88 ጋር በማገናዘብ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ የአ/አ ከተማ ፍርድ ቤቶችና የመዳኘት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት አደረጃጀት እና ሥልጣንና ኃላፊነት በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 361/95 ከአንቀጽ 39-50 ድረስ ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የዳኝነት አካላቱ ሥልጣን መሠረት ያደረገው የከተማው አስተዳደር ተቋማት ተግባር እና ኃላፊነት በሚመለከቱ አስተዳደራዊ ጉዳዮች እንዲሁም በከተማው ነዋሪዎች መካከል የሚነሱ የፍትሐብሔር እና የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች ላይ አከራክሮ የመወሰን ኃላፊነት የተሰጠ ስለመሆኑ ነው፡፡ በተለይም ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው የአዋጁ አንቀጽ 50/1/ የክርክር መጠኑ ከብር አምስት ሺህ ያልበለጡ የንብረት እና የገንዘብ ክርክሮችን ማኀበራዊ ፍ/ቤቶች እንዲዳኙ ሥልጣን ሲሰጥ ከፍ ሲል ከተመለከተው አጠቃላይ ዓላማ እና ወሰን ጋር መታየት ያለበት መሆኑን መገንዘብ አዳጋች አይደለም፡፡

በዚህም እጅግ ቀላል የሆኑ ጉዳዮች እና ውስብስብ የሕግ ጥያቄ የማያስነሱ ክርክሮች በአጭር እና በቅርበት ለማኀበረሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል ስለመሆኑ መረዳት የሚቻል ነው፡፡ የአዋጁ ግብ ይህ መሆኑ የሚታወቅ ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር አምስት ሺህ በታች በመሆኑ ብቻ በማናቸውም ጉዳዮች ላይ የመወሰን ሥልጣን ያስጠዋል የሚለውን የተጠሪ ክርክር ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንፃር መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 25/88 የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን ሲዘረዝር በዋነኛነት ታሳቢ ያደረገው የፌዴራል መንግሥት አወቃቀር እና የፌዴራል ሥርዓቱን የሥልጣን ክፍፍል መርህ በመጠበቅ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ወሰን በግልጽ በሌላ ሕግ እስካልተሻረ ድረስ በዝምታ ወይም ኂላ በወጣ ሕግ ተተክቷል ሊባል አይችልም፡፡ ስለሆነም በተጠሪ በኩል የቀረበው ክርክር ማለትም በአዋጅ ቁጥር 25/88 የተደነገገው ቢኖርም አዋጅ ቁጥር 361/95 ኂላ የወጣ በመሆኑ ተፈፃሚነት አለው የሚለው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ይልቁንም በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6/ እና 5/9/ ሥር በግልጽ እንደተደነገገው በፌዴራል መንግሥት የተቋቋመ ተቋም ተከራካሪ የሆነበት ጉዳይ ከመሆኑ አንፃር እና የክርክሩ መነሻም የመድን ውል መሆኑ ሲታይ በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች መሆኑ በግልጽ በሕግ የተደነገገ ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡

ስለሆነም ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች በግልጽ በተሰጠ የዳኝነት ሥልጣን የገንዘብ መጠኑን ብቻ መሠረት በማድረግ የአ/አ ከተማ ማኀበራዊ ፍ/ቤት ሥልጣን ነው በማለት በተጠሪ በኩል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም ብለናል፡፡

ስለዚህ በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ላይ ያሉት ተከራካሪ ወገኖች ማንነት እና በክርክሩ የሚነሳው የሕግ ጥያቄን መሠረት በማድረግ ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንፃር ተመልክቶ ባለው አግባብ ሊስተናገድ የሚገባው ሆኖ ሳለ የአ/አ ከተማ ማኀበራዊ ፍ/ቤት ተቀብሎ የሰጠው ፍርድ የሥረ-ነገር ሥልጣን በሕግ በግልጽ ያልተሰጠው በመሆኑ ሊፀና የሚችል ፍርድ የለም ብለናል፡፡

ስለሆነም የማኀበራዊ ፍርድ ቤቱ ይህንኑ ተገንዝቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 231/1/ለ/ መሠረት መዝገቡን መዝጋት ሲገባው በጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠቱ የመሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

በቂርቆስ ክ/ከተማ የቀበሌ 04 ማኀበራዊ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 953/97 የሰጠው ውሣኔ፣ የአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02451 የሰጠው ፍርድ እና የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08207 በ20/02/2002 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 43912

ሰኔ 15 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሒጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ - ጠበቃ ረዳኢ ባራኺ ቀረበ

**ተጠሪዎች**፡- 1. የአቶ ኢብራሂም ሙሣየ- ወራሾች በሌሉበት

2. ሰይድ ኢብራሂም - በሌለበት

መዝገቡን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በመኪና ላይ ደረሰ የተባለውን ጉዳት መሰረት በማድረግ የቀረበ የካሣ ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ከሣሽ የነበረው አመልካች ነው፡፡ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረተው የመድን ዋስትና የገባለት የደንበኛው መኪና በሁለተኛ ተጠሪ ሾፌርነት ሲሽከረከር በነበረው በአንደኛ ተጠሪዎች መኪና ተገጭቶ ጉዳት ስለደረሰበትና በዚህ ምክንያትም መኪናውን ለማስጠገን ወጪ በማድረጉ ይህንኑ እንዲተኩለት ነው፡፡ በአንደኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ባለመቅረባቸው ክርክሩ በሌሉበት የተሰማ ሲሆን፣ሁለተኛ ተጠሪ ግን ቀርቦ መልሱን እንደሰጠ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ከሁለቱ ወገኖች የቀረበለትን ክርክር ከመረመረ በኂላ፣ሁለተኛ ተጠሪን ከክሱ ነፃ በማድረግ በአንደኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ብር 22,387.79(ሃያ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ሰማኒያ ሰባት ብር ከሰባ ዘጠኝ ሣንቲም) ከነወለዱ እንዲከፍሉ ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በውሳኔው ስላልተስማማ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ የነበረ ሲሆን፣ፍ/ቤቱ ክሱ የቀረበው የግዛት ሥልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ይግባኙን ካለመቀበሉም በላይ፣በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔም ሽሮታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች በሥር ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ እኛም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ተጠሪዎች በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ባለመቅረባቸው ክርክሩ የተሰማው በሌሉበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግዛት ሥልጣንን መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን የተመለከተው ክሱን የሰማው ፍ/ቤት የግዛት የዳኝነት ሥልጣን ነበረው ወይስ አልነበረውም? የሚለው ጭብጥ አንፃር ነው፡፡ ለሰጠው ውሳኔ በዋቢነት የጠቀሰውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥሕ/ቁ. 27/1/ የተመለከተው ድንጋጌ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን ድንጋጌ ለመጥቀስ የበቃው የክሱ መነሻ በሚንቀሳቀስ ንብረት የደረሰ ጉዳት ነው የሚል ምክንያት በመያዝ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁንና በተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ድንጋጌ በቁጥር 27/1/ የተመለከተው ሳይሆን፣በቁጥር 24/3/ የተመለከተው እንደሆነ ነው በበኩላችን ለመገንዘብ የቻልነው፡፡ አመልካች በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ የንግድ ማህበር እንደመሆኑ ጉዳዩ በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(6) መሰረት በፌዴራል ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 24/3/ በግልጽ እንደተቀመጠው በኢንሹራንስ ውል አፈፃፀም ምክንያት ክርክር የተነሳ እንደሆነ ክሱ የኢንሹራንሱ ኩባንያ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት ቦታ ባስቻለው ባለሥልጣን ፍ/ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች የኢንሹራንስ ኩባንያ ነው፡፡ ዋና መሥሪያ ቤቱ በዚህ በአዲስ አበባ ስለመሆኑም ይታወቃል፡፡ ክሱም የቀረበው በዚህ በአዲስ አበባ ላስቻለው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ የግዛት ክልል የዳኝነት ሥልጣን የለውም የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ያየው የተሳሳተ ወይም ለጉዳዩ ተገቢነት የሌለውን ሕግ መሰረት በማድረግ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 48183 ኀዳር 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከፈተው የይግባኝ መዝገብ ጉዳዩን እንዲቀጥል በማድረግ እና ወደ ጉዳዩ ሥረ ነገር በመግባት ክርክሩን ሰምቶ ተገቢው ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ ይመለስለት ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር አመልካች ወጪና ኪሣራውን ራሱ ይቻል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 48018

ሐምሌ 7 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ተከተል ዘካሪያስ - ወኪል አዳነች ቀረቡ

**ተጠሪዎች**፡- 1. ወ/ሮ አስቴር ታደሰ - ጠበቃ አቶ ፍቃዱ ያሚ ቀረቡ

2. አቶ ገነነ ደምሴ - በሌሉበት ይታያል

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቹ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን ገልፀው በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው ስለጠየቁ ነው፡፡ በሥር ክርክሩ የታየው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ንብረትነቱ የአንደኛ ተጠሪ የሆነ ተሽከርካሪ በሁለተኛ ተጠሪ ሹፌርነት ሲሽከረከር በሰበታ ሐዋሳ ወረዳ ቀበሌ 01 ገጭቶ ጉዳት ያደረሰብኝ ስለሆነ ካሣ ይከፈለኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ አመልካች ክሱን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 27 መሰረት ጉዳቱ በደረሰበት ቦታ የሥረ-ነገርና የክልል ግዛት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ አለባቸው በማለት ተቃውመዋል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ጉዳዩን ለማየት የግዛት ክልል ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ያቅርብ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይኑ በይግባኝ መርምሮ አጽንቷል፡፡

አመልካች በሁለት ክልል ኗሪዎች መካከል የሚነሣው ክርክር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች መታየት እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 25/88 ደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 10 እና በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 19 ሊወድቅ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ ጉዳቱ የደረሰበት ቦታ ብቻ ነው መክሰስ ያለባቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል አንደኛ ተጠሪ በበኩላቸው የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 27 በጉዳት ካሣ ጊዜ የክልል ሥልጣን ያለው የትኛው የፍርድ ቤት እንደሆነ የሚደነግግ ልዩ ድንጋጌ ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የሕግ ትርጉም መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ በሌለበት ጉዳዩ ታይቷል፡፡

በሥር የቀረበው ክርክርና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አከራካሪው ጭብጥ ጉዳዩን የማየት የግዛት ክልል ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የትኛው ነው? የሚለው ነው፡፡ በመርህ ደረጃ በሰዎች ወይም በሚንቀሣቀስ ሐብት ላይ በደረሰ ጉዳት ካሣ ለማግኘት የሚቀርብ ክስ ጉዳቱ በደረሰበት ሥፍራ የሥረ-ነገረ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት መቅረብ እንዳለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 27 ንኡስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ ይህም የሆነው የደረሰው የጉዳት እና ከጉዳቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ላይ ጉዳቱ በደረሰበት አካባቢ በቀላሉ ማስረጃ ለማግኘትና ማስረጃም ለማቅረብ የሚቻል በመሆኑ ነው፡፡ ሆኖም የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 27 ንኡስ አንቀጽ 1 ከላይ የተገለውን የሕጉን ዓላማ በአግባቡ ማሣካት የማይከለክል በሆነ ጊዜ በሰው ወይም በሚንቀሣቀስ ንብረት ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሣ ለማግኘት የሚቀርብ ክስ ተከሳሽ በሚኖርበት ቦታ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ጉዳቱ የደረሰው ሰበታ አካባቢ መሆኑ የተጠሪዎች የመኖሪያ ቦታ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ መሆኑና ምስክሮችና ሌሎች ማስረጃዎችን ለማቅረብ የሚያጋጥም የትራንስፖርትና ሌሎች ችግሮች ቀላል በመሆኑ አመልካች ክሱን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ማቅረባቸው በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 27 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ የሚቃረን ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ክሱን ተቀብሎና አከራክሮ በፍሬ ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠት ሲገባው የግዛት ክልል ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ስህተቱን ማረም ሲገባው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን ማጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ብይንና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት የክልል ግዛት ሥልጣን አለው ብለናል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪዎች በፍሬ ጉዳይ ላይ የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 341 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት መልሰንለታል ይፃፍ፡፡

በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 45806

ሀምሌ 8 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ፍፁም በርታ - አልቀረቡም

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ ሶፊያ ዱላ

2. ወ/ሪት መሪማ በርታ

3. አቶ ሚፍታ በርታ - ጠበቃ አቶ ታየ ቀረቡ

4. አቶ ማርዬ በርታ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች የሰበር አቤቱታ ስላቀረበ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አባቴ አቶ በርታ ሰይድ ሀምሌ 24 ቀን 1995 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ ሟች አባቴ በውልና ማስረጃ መጋቢት 5 ቀን 1985 ዓ.ም ኑዛዜ ያደረጉ ስለሆነ ኑዛዜው ፀድቆ የኑዛዜ ወራሽነቴ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት ለአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበው ማመልከቻ ነው፡፡ ተጠሪዎች በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት አመልክተው በክርክሩ ጣልቃ

እንዲገቡ ከተፈቀደላቸው በኂላ ተጠሪዎች በሸሪዓ ፍርድ ቤት የሟች ወራሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አቤቱታ አቅርበው አመልካቹ በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እየተከራከረ ስለሆነ ጉዳዩ በአንድ ጊዜ በሁለት ፍርድ ቤቶች መታየት የለበትም የሚል መቃወሚያና በአማራጭ ሌሎች መከራከሪያዎችን አቅርበዋል፡፡ አመልካችና ተጠሪዎች በዚህ መዝገብ በተያዘው ጉዳይ ላይ በመከራከር እያሉ የአሁን ተጠሪዎች አመልካች የአሁን አመልካች ጣልቃገብ ተከራካሪ የሆኑበት በሸሪዓ ፍርድ ቤት የተያዘው መዝገብ መስከረም 25 ቀን 1997 ዓ.ም ውሣኔ አግኝቷል፡፡ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በሸሪዓ ፍርድ ቤት የተወሰነ መሆኑን በመግለፅና አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ላይ ማከራከር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 8(1)"ን" የሚጥስ መሆኑን በመግለፅ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎበታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙን አልተቀበለውም፡፡ አመልካች ለአዲስ አበባ አስተዳደር የሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ የሰበር አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት ግንቦት 6 ቀን 2001 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ እኔ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ሆኜ የገባሁት ወላጅ አባቴ በፍትሐብሔር ህጉ መሠረት ያደረገው ኑዛዜ ስላለ ውርሱ መታየት የሚገባው በመደበኛው ፍርድ ቤትና በፍትሐብሔር ህጉ መሠረት መሆን አለበት የሚለውን መቃወሚያ ለማቅረብ ነው፡፡ እኔ በአዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት መጥሪያ ተልኮልኝ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆኔን በመግለፅ ፎርም ሞልቼ ያላቀረብኩ በመሆኑ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ሙሉ ፈቃድን አልሰጠሁትም፡፡ መቃወሚያ ለማቅረብ ጣልቃ መግባቴ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃድ ሰጥቷል ተብሎ የተሰጠው የህግ ትርጉም አባቴን የመውረስ መብቴን የሚያሣጣና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው እኛ የአንደኛ ተጠሪ የሟች ሚስትና ወራሽ ከሁለተኛ ተራ ቁጥር እስከ አራተኛው ተራ ቁጥር ስማችን የተገለፀው ተጠሪዎች የሟች ልጆችና ወራሾች መሆናችንን በሸሪዓ ፍርድ ቤት በሸሪዓ ህግ መሠረት ለማረጋገጥ ባቀረብነው ማመልከቻ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመታየት ላይ እያለ አመልካች ነሐሴ 27 ቀን 1995 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት አመልክቷል፡፡ አመልካች ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ከተፈቀደለት በኂላ አንደኛ ተጠሪ የሟች ሚስት አይደለችም ሟች በህይወት በነበሩበት ጊዜ ያደረጉት ኑዛዜ ስላለ ኑዛዜው ይፅደቅልኝ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ስለጉዳዩ በሽማግሌዎች እንዲጣራ በማድረግ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎበታል፡፡ አመልካች በሙሉ ፈቃዱ በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ ኑዛዜው እንዲፀድቅለትና አንደኛ ተጠሪ የሟች ሚስት አይደሉም ተብሎ እንዲወሰንለት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አመልክቶ ውድቅ ከተደረገበት በኂላ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ስምምነት አልሰጠሁም በማለት ያቀረበው አቤቱታ ተገቢ አይደለም በማለት በፅሑፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች ሟች አባቴ ኑዛዜ ያደረጉ በመሆኑ በሸሪዓ ህግ መሠረት የሟች ውርስ መታየት የለበትም የሚል መቃወሚያ ለማቅረብ በክርክሩ ጣልቃ መግባቴ በሸሪዓ ህግ መሠረት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃድ እንደሰጠሁ ሊቆጠር አይገባውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኑዛዜው በሸሪዓ ፍርድ ቤት ታይቶ ውሣኔ አልተሰጠበትም የሚል ይዘት ያለው የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ በፅሑፍ ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በሸሪዓ ህግ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃዱን ሰጥቷል ወይስ አልሰጠም? የሸሪዓ ፍርድ ቤት ሟች አድርገውታል የተባለውን ኑዛዜ አይቶ ውሣኔ ሰጥቶበታል ወይስ አልሰጠበትም? የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ማመልከቻ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ጭብጦች መታየት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

1. አመልካች በሸሪዓ ሕግ መሠረት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃድ አልሰጠሁም በማለት ሰፊ ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች በሸሪዓ ህግ ለመዳኘት ፈቃዱን ሰጥቷል ወይስ አልሰጠም? የሚለውን ጭብጥ ለመፍታት አመልካች ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ተከራካሪ ሆኖ የገባበትን ሁኔታና አመልካች በሸሪዓ ፍርድ ቤት ተከራካሪ ሆኖ ከገባ በኂላ ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ያቀረበውን ጥያቄና ክርክር ይዘት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ አመልካች አንደኛ ተጠሪ የሟች አቶ በርታ ሠይድ ሚስትና ወራሽ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ እና አራተኛ ተጠሪዎች የሟች ልጆችና ወራሾች

መሆናቸው በሸሪዓ ህግ መሠረት ተረጋግጦ እንዲወሰንላቸው ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 7/96 ባስከፈቱት ክርክር ጣልቃ ለመግባት የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ እንዲፈቅድለት አመልክቷል፡፡ አመልካች በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 41 መሠረት ተጠሪዎችን ወራሽነት ጥያቄና ክርክር ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር ሲጠይቅ በክርክሩ ሒደት በአዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀፅ 6(1) መሠረት የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ለውሣኔአቸው መሠረት ሊያደርጉት በሚገባው በሸሪዓ ህግ መሠረት ለመዳኘት ፍላጎትና ፈቃድ ያለው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ምክንያቱም የክርክሩን የአመራር ሥርዓት ካልሆነ በስተቀር የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በሥረ-ነገር ሥልጣናቸው ሥር የሆኑ ጉዳዮች የሚቀርብላቸውን አቤቱታና ክርክር የሚወስኑት የሸሪዓ ህግን መሠረት በማድረግ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 188/92 በአንቀፅ 6(1) በግልፅ የተደነገገ በመሆኑ አንድ ሰው ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ ሲያቀርብ ሥነ ሥርዓታዊ ከሆነው ጭብጥና ጥያቄ ውጭ የሆኑት ጉዳዮች በሸሪዓ ህግ ለመዳኘትና ፈቃድ የሰጠ መሆኑን የሚያሣይ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በሸሪዓ ህግ መሠረት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃዱን የሰጠ መሆኑን ወይም አለመሆኑን አመልካች በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ከፈቀደለት በኋላ ያቀረበውን ክርክር ይዘትና የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኝነት በማየት እንዲወስንለት ያቀረበውን ጭብጥ በመመርመር ውሣኔ መስጠት ግድ ይላል፡፡

አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ከፈቀደለት በኋላ ሁለት መሠረታዊ ጭብጦች ፍርድ ቤቱ አይቶ ውሣኔ እንዲሰጥለት ጠይቋል፡፡ የመጀመሪያው አንደኛ ተጠሪ የሟች አባቴ አቶ በርታ ሠይድ ሚስት አይደሉም፡፡ ስለሆነም አንደኛ ተጠሪ የሟች ሚስትና ወራሽ ነኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ የሚል ሲሆን ሁለተኛው ሟች አባቴ በህይወት እያለ ያደረገው የኑዛዜ ሰነድ ስላለ የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ያፅድቅልኝ የሚል መሆኑን በመዝገብ ቁጥር 7/96 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች የሸሪዓ ፍርድ ቤት ጣልቃገብ ተከራካሪ እንዲሆን የጠየቅሁት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በሸሪዓ ህግ መሠረት ጉዳዩን እንዳይወስን ተቃውሞ ለማቅረብ ነው በማለት በሰበር አቤቱታው ያቀረበው መከራከሪያ ተገቢነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች ለፌዴራል የሸሪዓ ፍርድ ቤት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ ክርክሩን እንዲያሰማ ያቀረበው ማመልከቻና አመልካች በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ከተፈቀደለት በኋላ የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ የጠየቀው ዳኝነትና ያቀረበው ክርክር በአንድነት ሲታዩ አመልካች በሸሪዓ ህግ መሠረት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ሙሉ ፈቃድን የሰጠ መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡

አመልካች በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆኔን በአዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀፅ 5(1) እና ከአዋጁ ጋር በተያያዘው አባሪ(ፎርም) በመሙላት አልሰጠሁም በማለት ክርክር አቅርቧል፡፡ ሆኖም ከአዋጁ ጋር የተያያዘውን ፎርም በመሙላት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ከቀጠሮ ቀን በፊት ለሬጅስትራር እንዲገልፅ የሚገደዱት በጉዳዩ ተከሳሽ ወይም በተጠሪነት ቀርበው መልስ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች መሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀፅ 5(1) በግልፅ ተደንግጓል፡፡ አስፈላጊ የሆነ ሥነ ሥርዓቶችና ፎርማሊቲዎች በማሟላት ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ ያቀረበ ከሳሽ ወይም አቤቱታ አቅራቢ ክሱን ወይም አቤቱታውን ለሸሪዓ ፍርድ ቤት እንዲታይ ፈቃደኛ መሆኑን ፎርም በመሙላት መግለፅ አያስፈልገውም፡፡ ስለሆነም አመልካች የሸሪዓ ፍርድ ቤት አቤቱታውን አይቶና በአቤቱታው ዳኝነት የጠየቀባቸውን ጉዳዮች አጣርቶ እንዲወስንለት ግልፅ ጥያቄ አቅርቦና ተከራክሮ ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘትና ጉዳዩ በሸሪዓ ህግ መሠረት እንዲወሰን ፈቃዱን አልሰጠሁም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የአዋጁን አንቀፅ 5(1) ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና የህግ መሠረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. የሸሪዓ ፍርድ ቤት ሟች አቶ በርታ ሠይድ መጋቢት 5 ቀን 1985 ዓ.ም አድርገውታል የተባለው ኑዛዜ በሸሪዓ ህግ መሠረት ህጋዊ ውጤት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝና አግባብነት ያላቸውን የሀዲስ ድንጋጌዎች (በሸሪዓ) ስለ ኑዛዜ ዋጋ መኖር ከተደነገጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ያልፀደቀ በመሆኑ በሸሪዓ መሠረት ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት ያለው አይደለም በማለት እንደወሰነ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት መስከረም 25 ቀን 1997 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ በፊቱ የቀረበለትን የኑዛዜ ወይም ያለኑዛዜ ወራሽነት ጥያቄ የሚወስነው የሸሪዓ ህግን መሠረት በማድረግ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀፅ 6(2) የተደነገገ በመሆኑ አመልካች የሟች ኑዛዜ

ይፅደቅልኝ በማለት ያቀረበውን ጥያቄ አግባብነት ያላቸውን የሸሪዓ ህግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መርምሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሟች አቶ በርታ ሠይድ ያደረጉት ኑዛዜ የሸሪዓ ህግ የሚጠይቀውን መሥፈርት ያሟላና ህጋዊ ውጤት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ሲወስን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አግባብነት ያላቸውን የሸሪዓ ህግ ድንጋጌዎች አልጠቀሰም ወይም የሸሪዓ ህግ ድንጋጌ ሲተረጉም ሥህተት ሠርቷል የሚል ሀሳብ ካላቸው አመልካች ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የማረም ሥልጣን ላለው የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ነበረባቸው፡፡ አመልካች ይህንን በማድረግ ፋንታ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በጭብጥነት በመያዝ ግልፅ ውሣኔ የሰጠበት የሟች ኑዛዜ እንደተጠቃሚ መሆናቸውን እንዲረጋገጥላቸው ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ጥያቄ የህግ መሠረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡት ክርክር በሚሰማበት መዝገብ ጣልቃ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸውና የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ የሟች ያደረገው ኑዛዜ ስላለ በኑዛዜ ተጠቃሚ መሆናቸው እንዲወሰን ጥያቄ አቅርበው ጉዳዩ በሸሪዓ ፍርድ ቤት በመታየት ላይ እያለ የሟች ኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ ውሣኔ እንዲሰጥላቸው ለአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ ይኸ የአመልካች የክርክር ስልት በአገሪቱ ሰዎች በፈቃዳቸው በሀይማኖት ወይም በባህል ህግ መሠረት የመዳኘት መብት እንዳላቸው በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀፅ 5 የተረጋገጠውን መብት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሞከሩ መሆናቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ ምክንያቱም ህገ-መንግስቱ ሰዎች የግልና የቤተሰብ ጉዳይ በተመለከተ በፈቃደኝነት በሀይማኖት ወይም በባህል ህግ መሠረት የመዳኘት መብት ያላቸው መሆኑን የደነገገው ተከራካሪዎቹ ጉዳያቸውን የሚያቀርቡበትን ፍርድ ቤትና ጉዳያቸው በየትኛው ህግ መሠረት መታየት እንዳለበት በሙሉ ፈቃድና ፍላጎታቸው እንዲመርጡ እድል ለመስጠት እንጅ በአንድ ጊዜ አንድ ጉዳይ በሀይማኖት ህግ መሠረት እንዲታይ ለሀይማኖት የዳኝነት ተቋማትና በሌሎች ህጎች መሠረት እንዲታይ ለመደበኛ ፍርድ ቤት አቅርበው እንዲከራከሩ ለመፍቀድ አይደለም፡፡ አመልካች የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበውንና የሸሪዓ ፍርድ ቤት መሠረታዊ ጭብጥ አድርጎ ይዞ በማጣራት ላይ የነበረውን ጉዳይ በተመሣሣይ ጊዜ ውስጥ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን ያቀረበው ጥያቄ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀፅ 5 እና የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 8 ንዑስ አንቀፅ 1 የሚጥስ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁለቱም ፍርድ ቤቶች የሟች ኑዛዜ በጭብጥነት ይዘው በማጣራት ላይ እያሉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ቀድሞ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ቀድሞ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ የሸሪዓ ፍርድ ቤት በፍርድ የተቋጨ ጉዳይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መታየቱ እንዲቀጥል ማድረጉ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ የሚጥስና አስቀድሞ በፍርድ የተቋጨ ጉዳይ በድጋሚ በሌላ ፍርድ ቤት እንዲወሰን የቀረበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የሰበር ችሎት አመልካች ሟች አባቱ ያደረጉት ኑዛዜ ተጠቃሚ መሆኔ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት ያቀረበውን አቤቱታ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢና የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት አፅንተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት፣ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማ ነክ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. *49152*

ሐምሌ *07* ቀን *2002* ዓ.ም

***ዳኞች፣*** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

***አመልካች፣*** የኮንስትራክሽን ስራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት መሠረታዊ ሠራተኛ ማህበር - ወኪል አህመድ በዳኔ ቀረቡ

***ተጠሪ፣*** የኮንሽትራክሽን ስራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት - ጠበቃ መንበረስላሴ በዛብህ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሠረት ያደረገ የቦነስና የደመወዝ ጭማሪ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ አካል ክሱን ያቀረበው የአሁኑ አመልካች ሲሆን ተጠሪ ከሣሽ ነበር የአመልካች የክሱ ይዘት ተጠሪ ድርጅት በ1999 ዓ.ም የበጀት ዓመት ተጠሪ ካገኘው ትርፍ በሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 24/1/ መሠረት የደመወዝ ጭማሪና የቦነስ ክፍያ ተጠሪ እንዲከፍል ይወሰንልን የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበው ክርክር የደመወዝና የቦነስ ጭማሪ ጉዳይ ለማየት ፍርድ ቤቱም ሆነ ቋሚ ቦርዱ ሥልጣን የለውም የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በአዋጁ አንቀጽ 138 መሠረት ስልጣን የሌለው መሆኑን

በመግለጽ ክሱን ዘግቶታል፡፡ ይህ ብይን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ቀርቦም ፀድቋል፡፡ ከዚህ በፊትም ጉዳዩ ለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ቀርቦ ቦርድም የአዋጁን አንቀጽ 147፣ 142/1/ሀ/2/3// እና 136/2/ ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ ቦርዱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት ክሱን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራቀኙ ከተከራከሩ በኃላ የቦርዱ ውሣኔ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀርቦ በታየው ጉዳይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ነው፡፡

የአመልካች ነገረፈጅ መስከረም 07 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ጥያቄው የጋራ ጥቅምን የሚነካ የወል የስራ ክርክር ነው ተብሎ ተወስኖ ሆኖ እያለ ጥያቄው በፍርድ ቤቱም ሆነ በቦርዱ የሚታይ አይደለም ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ጉዳዩ በቋሚ ቦርድ ቀርቦ ሊታይ በሚችል አኳኋን ሕጉ ሊተረጎም ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጥያቄ ለማየት እንዲቻል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ በጠበቃው አማካኝነት ህዳር 02 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሱን ሰጥቷል፡፡ የመልሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ጉዳዩ ከአዋጅ ቁጥር 136/2/ እና 147/1 ሀ/፣ 147/2/ አንፃር ሲታይ በሁለቱም አካላት የሚታይ ባለመሆኑ አመልካች ያለው መብት በአዋጁ አንቀጽ 157 መሠረት መብቱን ማስከበር ነው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአመልካች ማህበር የዳኝነት ጥያቄ መሠረት ያደረገው ከተጠሪ ጋር ያለውን የሕብረት ስምምነት መሆኑን ጥያቄውም በ2000 ዓ.ም የበጀት ዓመት ተጠሪ ድርጅት ከብር 78,000,000 (ሰባ ስምንት ሚሊዮን) በላይ ማትረፉን በግልፅ በማረጋገጡ በህብረት ስምምነቱ መሠረት ለሁሉም ሠራተኛ የደመወዝ ጭማሪና ቦነስ የመስጠት ግዴታ ያለበት መሆኑን አመልካች ጠቅሶ የሚከራከር መሆኑና ተጠሪ እንደዚህ አይነት ጥያቄ በቋሚ ቦርድ ሊታይ አይገባም በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 138፣142 እና 147 ድንጋጌዎች መሠረት የስራ ክርክር ጉዳዩች የሚታዩበትን ስርዓት ሲዘረጋ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባው የወልና የግል የስራ ክርክሮች በሚል ነው፡፡

የስራተኞችን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም አወሳሰን በሚመለከት የሚነሳውን የወል የስራ ክርክር በቋሚው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሊታይ እንደማይችል በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 147/1/1ሀ/ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ የደመወዝ ጭማሪና የቦነስ ጥያቄን ማስተናገድ የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 142/3/ በተጠቀሰው መሠረት በአዋጅ አንቀጽ 136/2/ ስር እጅግ አስፈላጊ የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ተብለው የተጠቀሱትን ድርጅቶች የሚመለከት ሲሆን ብቻ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ሕግ አውጪው ድርጅቶችን ሙሉ በሙሉ ለይቶ ዘርዝሮ አስቀምጧል፡፡ ተጠሪ ደግሞ ከእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ የሚካተት አይደለም፡፡ በአዋጅ አንቀጽ 136 ስር ከተዘረዘሩት እጅግ አስፈላጊ የሆነ የሕዝብ ግልጋሎት ሰጭ ድርጅቶች ውጪ ያሉትን ድርጅቶች ጋር ሰራተኛው የሚያነሳውን የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም ጉዳይ ቋሚ ቦርዱ ጉዳዩን ለማየት ግልፅ የሆነ የሕግ አውጪ ክልከላ ከላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ሲሆን የእነዚህ ድርጅቶ ጉዳይ በየትኛው አካል ሊታይ አንደሚገባ ሕጉ ያስቀመጠው ስርዓት መኖሩንና አስፈላጊነቱ ምን እንደነበር መመለከቱ የግድ ይላል፡፡

ጉዳዩ የወል የስራ ክርክር መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ሆኖም የወል የስራ ክርክር ሆነውም በቦርዱ በተለየ ሁኔታ የማይታዩት ጉዳዩች በሕጉ ተለይተው ተቀምጠዋል ወይስ አልተቀመጡም? የሚለው ጥያቄ መነሳት ያለበት ነው፡፡ በዚህ ችሎት እምነት ከላይ እንደተጠቀሰው ሕግ አውጪው ክርክሩ የወል የስራ ክርክር ቢሆንም በቋሚ ቦርዱ ሊታይ የማይገባበትን ሥርዓት ዘርግቷል፡፡

የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 141 እና 142 ሲታዩ ይህንኑ የሚመልሱ ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት በአዋጅ አንቀጽ 136/2/ ድንጋጌ ስር ከተዘረዘሩት ድርጅቶች ውጪ ያሉ ድርጅቶች የደመወዝና የጥቅማጥቅም ጉዳይ የአስማሚ ተግባርና ኃላፊነት ሆኖ ሊታይ የሚገባው በአዋጁ ምዕራፍ ሶስት በፌዴራሉ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚመድበው አስማሚ ነው፡፡ በአዋጅ አንቀጽ 142/1ሀ/ ከተጠቀሰው የደመወዝና የጥቅማጥቅም ጉዳዮች ብቻ አሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ማቅረብ ይቻላል ይህንኑም ከተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሶስት ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ ጉዳዩ የሚታየው በአዋጁ ምዕራፍ ሶስት በሚቋቋም አስማሚ እንጂ በአዋጅ ምዕራፍ አራት ስር በሚቋቋም ቦርድ /ቋሚም ይሁን ጊዜያዊ/ አይደለም ይህ ስለመሆኑም አንዳንድ በዋቢነት የሚጠቀሱት ነገሮች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል አዋጅ ቁጥር 377/96 ማሻሻያ ላይ የቀረበው ውይይት አንዱ ነው፡፡ ከአዋጁ ማሻሻያ ሐሳቦች አንዱ የደመወዝና የጥቅማጥቅም ጉዳይ በአስማሚ ሊታይ አይገባውም የሚል እንደነበር ይታወቃል ማሻሻያው ተቀባይነት ያለማግኘቱ የሚታወቅ ነው፡፡ የማሻሻያው ጥያቄ ውድቅ የተደረገበት አብይ ምክንያትም የደመወዝና የጥቅማጥቅም ጉዳይ ከአለው እጅግ አስፈላጊና ወሳኝነት ባህርይው የተነሳ በተደጋጋሚ ሠራተኞች የደመወዝ ጭማሪና ጥቅማጥቅም በፈለጉ ቁጥር በአሰሪዎቻቸው ላይ የሚያነሷቸው የማያባሩ ጥያቄዎች ስለሆኑ ሁለቱም ወገኖች በፈቃዳቸው በመረጧቸው አስማሚዎች የሚስማሙባቸው ወይም የሚኒስትሩ መ/ቤት በሚመድበው አስማሚ እንዲያልቅ በማስፈለጉ መሆኑ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ለወሳኝ ቦርድ ይቅረቡ ቢባል ሰራተኞችና አሰሪዎች ጊዜያቸውን ከመስማማት ይልቅ በመካሰስ ያላግባብ እንዲያጠፉና በድርጅቶች ምርትና ምርታማነት ላይም አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ግን ስምምነት ላይ ባይደርሱ ሠራተኞች የሚወስዱት እርምጃ በአገልግሎት ላይ ችግር ስለሚያስከትል የደመወዝና ጥቅማጥቅም ጉዳይ ከመንግስት ፖሊሲ /Public polic/ አንጻር የእነዚህ ድርጅቶች ጉዳይ ብቻ በቦርድ እንዲታይ ሕግ አውጪው ያደረገው ሊፈጠር ከሚችለው ችግር አንጻር መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት መሆኑን ሀተታ ዘምክንየት ያሳያል፡፡ የአዋጅ አንቀጽ 147/1/ ድንጋጌ ሲታይ ሥልጣንን በተመለከተ ቋሚው የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ከሚመለከቱት የስራ ክርክር ጉዳዮች ውጪ በአዋጁ በአንቀጽ 142 ንዑስ አንቀጽ አንድ ስር የተመለከቱትን ጉዳዮች ማየትና ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን እንዳለው ተመልክተዋል፡፡ የደመወዝ ጭማሪ እና የጥቅማ ጥቅም ጥያቄን የሚመለከቱት የስራ ክርክሮችን ቋሚ ቦርዱ የማየትም ሆነ አከራክሮ የመወሰን ስልጣን እንዳይኖረው ማድረግ ያስፈለገውም የደመወዝ ጭማሪ እና የጥቅማ ጥቅም ጥያቄ ጉዳይ የአሰሪውና የሰራተኛው ወገኖች በሚያደርጉት ድርድር አሊያም አንዱ ወገን በሌላው ላይ በሕጋዊ መንገድ ተጽእኖ በማሳደር ኢኪኖሚያዊ ጥቅሙን ለማግኘት ሊወሰድ በሚችል እርምጃ ሊፈታ የሚገባው እንጂ በቦርድ መወሰን የሚገባው ባለመሆኑ ስለመሆኑ የሕጉ ማሻሻያ ሀተታ ዘምክንያት ያሳያል፡፡ በአሰሪና ሠራተኛ ወገኖች መካከል በደመወዝና በጥቅማ ጥቅም ጉዳዮች ላይ አለመግባባትና ክርክር ሲፈጠር በዚህ አካል ጉዳዩ እንዲታይ ማድረግ የኢንዱስትሪ እርምጃዎችን /ስራ ማቆም ሆነ ስራ መዝጋት/ መብቶች ይገደባል የሚል እሳቤ አለ፡፡ ስለሆነም የተከራካሪ ወገኖች ስምምነት በሌለበት ሁኔታ ወይም ስራ ማቆምና ስራ መዝጋት መብቶች የሌላቸው አካላት ካልሆነ በስተቀር ተከራካሪ ወገኖች በአስገዳጅ የግልግል ዳኝነት ስር እንዲወድቁ ማድረግ አግባብነት እንደሌለው በመታመኑ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ እነዚህ ጉዳዮችን እንዳይመለከት መደረጉን ሐተታ ዘምክንያቱ ያሳያል፡፡ የስራ መቆምና የስራ መዝጋት መብቶች በአዋጅ አንቀጽ 157 እና ተከታዩቹ ጥበቃ ያገኙ ጉዳዩች ናቸው በዚህም መሠረት ሕግ አውጪው በአዋጅ አንቀጽ 147/2/ መሠረት እጅግ አስፈላጊ የሕዝብ አገልግሎት ድርጅቶች የሚባሉት ድርጅቶች ውስጥ ያሉ የሠራተኞችም ሆኑ የአሰሪው ወገን በተጠቀሱት የደመወዝና የጥቅማጥቅም ጉዳዮች ላይ የሚነሳን ክርክር በድርድር ለመፈታት ባይችሉ እንደሌሎቹ የስራ ማቆም ወይም የስራ መዝጋት እርምጃ የመወስድ መብት የሌላቸው በመሆኑ ሰራተኞቹም ሆነ አሰሪዎቹ ለጉዳዩ መፍትሄ እንዲያገኙ ክርክር በተፈጠረ ቁጥር በጊዜያዊነት ሊቋቋም ለሚችለው የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን መስጠቱ ታምኖበት ግልጽ ድንጋጌ አስቀምጧል፡፡ ስለሆነም የአዋጅ አንቀጽ 147/2/ ከአንቀጽ 142/3/ ጋር ተጣምሮ ሲነበብ ሊኖረው የሚገባው ትርጉም በአንቀጽ 136/2/ ስር እጅግ አስፈላጊ የሕዝብ አገልግሎት ድርጅቶች ተብለው ከተዘረዘሩት ተቋማት ጋር ተያይዞ የሚቀርበውን የደመወዝ እና የሌሎች ጥቅማጥቅሞች ጥያቄ ጋር ተያይዞ የሚነሳን የወል የስራ ክርክር ካልሆነ በስተቀር ከሌሎች ድርጅቶች የሚቀርበውን የደመወዝና የሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን የወል የስራ ክርክሮችን አይቶ የመወሰን የስረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አይደለም፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳ የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም ጥያቄ የወል የስራ ክርክር ነው ቢባልም ሕግ አውጪው በተለየ ሁኔታ በቋሚ ቦርዱ

ሊታዩ ይገባል ብሎ ከዘረዘራቸው ድርጅቶች ውጪ ያሉ ድርጅቶችን በተመለከተ ቋሚ ቦርዱ ሊመለከት አይገባም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 18180 እና 38933 የሰጠውን ውሣኔ ለዚህ ጉዳይ ያለውን አግባብነት ስንመለከተውም በእነዚህ መዛግብት የተሰጠው ውሣኔ የወል የስራ ክርክር ብሎ ለመለየት የሚቻልባቸውን መንገዶች ተንትኖ ውሣኔ የሰጠበት ሁኔታ እንጂ ያሁኑ አይነት ክርክር ቀርቦ በቦርዱ ሊታይ የሚገባው ነው በማለት ግልፅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ጉዳዩ በቋሚ ቦርድ ሊታይ የሚገባው አይደለም ከተባለ ሊታይ የሚገባው በየትኛው አካል ነው የሚለው ጥያቄ መነሳቱ የግድ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ የሚገኘውም ከአዋጅ አንቀጽ 142/1ሀ/ ስር ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ስለደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች አወሳሰን በተመለከተ የሚቀርብ የወል የስራ ክርክር መታየት ያለበት ተከራካሪዎችን በማስማማት ለጉዳዩ እልባት በሚሰጠው በአዋጅ አንቀጽ 141/1/ መሠረት በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚሰየም አስማሚ ቦርድ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 466/1997 አንቀጽ 2/2/ ሲታይም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ ቋሚ ቦርዱም ሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

በጉዳዩ ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡

በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ም.አ

# ባንክና ኢንሹራንስ

የሰ/መ/ቁ. 38572

ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - አቶ ናሆም ሽዋንግዛው

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ወ/ሮ ሀና አባይ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት የትሐታብሔር ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ሰኔ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ የአሁን ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርቦ አቶ ሐጎስ ተድላ ከንፋስ ስልክ ቅርንጫፍ ለወሰዱት ብር 75,000 (ሰባ አምስት ሺ ብር) ንብረትነቱ የተበዳሪው የአቶ ሀሰን አብደላ የሆነ የሠሌዳ ቁጥሩ 3-16015 እና የተሳቢው መለያ ቁጥር 3-03383 የሆነ መኪና በመያዣነት ይዞናል፡፡ ተጠሪ

እና ተበዳሪው አቶ ሐጎስ ተድላ መያዣው የመድን ዋስትና እንደገባለት በተስማሙት መሠረት በመያዣነት የተያዘው መኪና በተከሳሽ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ምስራቅ አብይ ቅርንጫፍ ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ተገምቶ ኢንሹራንስ መድን ተገብቶ የአረቦን ክፍያ ስንከፍል ቆይተናል፡፡ የመድን ውሉ እየታደሰ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ህዳር 28 ቀን 1988 ዓ.ም መኪናው በደረሰበት የመገልበጥ አደጋ ከጥቅም ውጭ ስለሆነና ተከሳሽ (አመልካች) ከመያዣው ግምት ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) እንዲከፍል ብንጠይቀው ፈቃደኛ ስላልሆነ እና ተበዳሪው ብድሩን ያልከፈሉ በመሆኑ በመያዣነት የያዝነውን የመድን ዋስትና የገባለትን መኪና ዋጋ እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ከተጠሪ ጋር ቀጥተኛ የሆነ የውል ግንኙነት ስለሌለኝ ክስ የማቅረብ ችሎታ የለውም፡፡ መኪናው የተገለበጠው አሽከርካሪው መሪ እንቢ ብሎኝ ነው በማለት ያቀረቡት መግለጫ በቴክኒክ ማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ሀላፊነት የለብንም፡፡ በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት በባለሙያ አልተረጋገጠም፡፡ መክፈልም ካለብን ሰባ አምስት ሺ ብር ነው የሚሉ መከራከሪያዎችን አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በአመልካች በኩል የቀረቡትን መከራከሪያዎች ውድቅ በማድረግ አመልካች ለተጠሪ መያዣው በአደጋ በመውደሙ ምክንያት የደረሰበትን ጠቅላላ ጉዳት ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀሣሳ ሺ ብር) ከህዳር 8 ቀን 1988 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቦ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የጉዳቱ መጠን አልተረጋገጠም በሚልና በሌሎች ነጥቦች የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ በመሻር ጉዳዩ እንደገና ታይቶ እንዲወሰን ጭብጦችን በመለየት ለሥር ፍርድ ቤት መልሷል፡፡ ተጠሪ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት አቅርቦ ችሎቱ የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ይህንን ውሣኔ በመቃወም ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በተበዳሪው ብድሩ ያልተከፈለው መሆኑን ሣያረጋግጥ ክስ እንዲያቀርብና እንዲከራከር መደረጉ መሠረታዊ የሆኑ የኢንሹራንስ መርሆችና ዓላማ የሚቃረን ነው፡፡ ተጠሪ ተበዳሪው ከተበደረው ውስጥ የከፈለውን ያልከፈለውን ለይቶ አላቀረበም ተጠሪ ያበደረው 75,000 (ሰባ አምስት ሺ ብር) ሆኖ እያለ ተገቢ ያልሆነ ክፍያ ጠይቋል ተጠሪ ብድሩ ባለመከፈሉ የነበረውን ወለድ እና ትርፍ መጠየቁ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት አግባብነት ያላቸውን የፍትሐብሔር ህግ እና የንግድ ህግ በመተላለፍ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት በፅሑፍ ያመለከተ ሲሆን ይህንኑ የሚያጠናክር የቃል ክርክር አቅርቧል ተጠሪ በበኩሉ ተበዳሪው እዳውን በወቅቱ ባለመክፈሉ ምክንያት ወለዱና ሌሎች በብድሩ አለመከፈል ምክንያት መከፈል ያለበት ገንዘብ ሲታሰብ ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ጉዳት የደረሰብን መሆኑን አስረድተናል፡፡ ተጠሪ የመድን ሽፋን ለማግኘት ከአመልካች ጋር የመድን ውል እንደገባ ያደረገውና የአረቦን ክፍያ ሲከፍል የኖረው ለተበዳሪው ለሰጠው ብር 75,000 (ሰባ አምስት ሺ ብር) ሣይሆን ይህ ብድር በወቅቱ ባይከፈል ለብድሩ መያዣ ለሆነውና ዋጋው ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ለሆነው በመያዣነት ለያዝነው መኪና ነው፡፡ የጠየቅነው ገንዘብ በመድን ውሉ ከተሰጠው ሽፋን የበለጠ አይደለም ስለዚህ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው ክርክር ተጠሪ ሳበደረው ብድር በመያዣነት የያዘው መኪና ለሚደርሰው ጉዳት እስከ ብር 350,000 አመልካች የመድን ሽፋን ሊሰጥ፣ መኪናውን ያስያዘው ሰው ወይም ተጠሪ በየጊዜው መክፈል የሚገባውን አረቦን ሲከፍሉ ነው፡፡ ተጠሪ የመድን ሽፋን ለተገባለት ንብረት መከፈል የሚገባውን አረቦን ያለ ማቋረጥ የከፈለ መሆኑንና በዚህ ሒደት መኪናው አደጋ የደረሰበት መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

አመልካች መኪናው ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ አልሆነም የሚል መከራከሪያ ያቀረበ ቢሆንም ተጠሪ ካቀረበው ማስረጃ የተሻለ ማስረጃ በማቅረብ ክርክሩን ያላስረዳ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ በዚህ በኩል አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተጠሪ የመኪናው ባለቤት ለሆኑት ተበዳሪ ብር 75,000 (ሰባ አምስት ሺ ብር) ሲያበድሩ ለብድሩ አከፋፈል ዋስትና ይሆነው ዘንድ ግምቱ 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) የሆነ መኪና በመያዣነት ይዟል፡፡ አመልካች ላበደረው ብድር አከፋፈል ዋስትና እንዲሆነው በመያዣነት በያዘው ንብረት ላይ ያለው መብት ብድሩ ባለመከፈሉ ቀሪ የሆነ ዋናው ገንዘብ፣ ይህ ብድር በብድር ውሉ መሠረት ባለመከፈሉ የሚወልደው ወለድ፣ የወለድ ወለድ መቀጫና ሌሎች ወጭዎችን ሁሉ ባለመከፈላቸው መያዣውን ሸጦ ገቢ የማድረግ መብቱን የሚያጠቃልል መሆኑና ጠቅላላ ጣሪያው በመያዣ ውሉ የተገለፀው የገንዘብ መጠን እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2858 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ተጠሪ ተበዳሪው ብድሩን ባለመክፈሉ ምክንያት ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ዋናው ብድር ወለድና ሌሎች ክፍያዎች ከተበዳሪው እንደሚፈልግ በሥር ፍርድ ቤት አስረድቷል፡፡ ተጠሪ ለዚህ ገንዘብ አከፋፈል ይረዳው ዘንድ በመያዣነት የያዘው ንብረት የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በመያዣነት የያዘው ንብረት በባህሪው ተንቀሳቃሽና ለአደጋ ተጋላጭ መሆኑን በመረዳት በመያዣነት የያዘውን ንብረት በብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) የመድን ሽፋን እንዲገባለት አድርጓል፡፡ ይህንንም ያደረገው ተጠሪ ያበደረውን ገንዘብ፣ ወለድና ሌሎች ክፍያዎች የማስመለስ እድሉን ለማስፋት እና እርግጠኛ ለመሆን ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አመልካች እንድከፍለው የጠየቀውና የሥር ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ለተጠሪ ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ከህዳር 8 ቀን 1988 ዓ.ም ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል የወሰኑት የንግድ ህግ ቁጥር 678 ድንጋጌ መሠረት በማድረግና የኢንሹራንስ ውሉን መሠረት በማድረግ በመሆኑ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላላገኘነው በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት አፅንተነዋል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎትና በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 44164

ታህሳስ 8 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነገረ ፈጅ ቀርበዋል

**ተጠሪ፡-** አቶ ሐሰን ኢብራሂም - ጠበቃ ስለሺ ዘዮሐንስ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የብድር ውልን የተመለከተ ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው የአሁን አመልካች የአሁን ተጠሪ በ05/08/87 ዓ.ም በተፈረመ ውል ብር 200,000.00(ሁለት መቶ ሺ.ህ) ተበድረው በየወሩ ብር 18,000(አስራ ስምንት ሺ.ህ) እየከፈሉ ከሚያዝያ ወር 1988 ዓ.ም የተስማሙ ቢሆንም ብድሩን በውሉ መሠረት አልከፈሉም፡፡ በመሆኑም በመያዣነት ለአመልካች ከሰጧቸውና አመልካች የመድን ሽፋን ከገዛላቸው ተሽከርካሪዎቻቸው ውስጥ ሁለቱን ያስረከቡ ቢሆንም በሊብሬያቸው ላይ የተጭበረበረና የተምታታ ነገር በመኖሩ ሊሸጡ አልቻሉም፡፡ ስለዚህ ተጠሪ በዓመት 14% ወለድና 3% የወለድ መቀጫ ለመክፈል በተስማሙት መሠረት የሚፈለግባቸውን ብር 396,904.52(ሦስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺ.ህ ዘጠኝ መቶ አራት ብር ከሃምሳ ሁለት ማንቲም) እና ሌሎች ወጪዎችን እንዲከፍሉ ይወሰንልን ሲል ባቀረበው ክስ ነው፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ተሽከርካሪዎቹ ለፎርክሎዠር የሐራጅ ሽያጭ የቀረቡ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 244(2/ሐ) መሠረት አንደኛው የህግ እርምጃ እየተካሄደ ሳለ በተደራቢነት ክስ ሊመሠረትብኝ አይገባም በማለት ቅድመ መቃወሚያ አቅርበው በፍሬ ጉዳዩ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም አመልካች ለተጠሪ ገንዘብ በብድር ሰጥቶ ለብድሩም መያዣዎችን ይዟል፡፡ ብድሩ ባልተከፈለው ጊዜ በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ወይም በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት የያዘውን ንብረት በሐራጅ በመሸጥ ገንዘቡን ማስመለስ ይችላል፡፡ ይህ ማለት ግን ሁለቱንም አማራጮች በአንድ ጊዜ በአንድ ላይ ይጠቀማል ማለት አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች ያበደረውን ገንዘብ ለማስመለስ በፍ/ቤት ክስ ያቀረበው በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት የያዘውን ንብረት ተረክቦ በሐራጅ ለመሸጥ በእንቅስቃሴ ላይ እያለ ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ በሌላ በፍ/ቤት (በባንኩ በራሱ) ተይዞ እያለ እና ተሽከርካሪዎቹ ተሸጠው የሚያወጡት ገንዘብ ለብድሩ ወይም ለዕዳው በቂ መሆን አለመሆኑ ሳይረጋገጥ በዚህ ፍ/ቤት ክስ ማቅረቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 244(2/ሐ) መሠረት ተቀባይነት ስለሌለው ክሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 245(2) መሠረት ተዘግቷል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ብድሩን ሲወስዱ ለመያዣነት ከአስያዟቸው መኪናዎች መካከል የሰሌዳ ቁጥር 2-13518 አ.አ. በብር 17,500.00(አስራ ሰባት ሺ.ህ አምስት መቶ) የካቲት 29 ቀን 1998 ዓ.ም በወጣው ጨረታ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-26916 የሆነው ደግሞ ነሐሴ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በወጣው ጨረታ በብር 152,000.00(አንድ መቶ ሃምሳ ሁለት ሺ.ህ) መሸጣቸው እና ሌላው መኪናም ሊገኝ አለመቻሉ ተገልጾ እያለ፣ አዋጅ ቁጥር 97/90 ባንክን ክስ ከመመስረት የሚከለክለው ባለመሆኑ የብድር እዳ እንዲመልሱ በተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ የፎርክሎዠር ሥርዓቱን ሳይጨርስ መቅረብ የለበትም ተብሎ ውድቅ መደረጉ የአዋጁን መንፈስ ያላገናዘበ ስለሆነ ሊሻር ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ክሱ ከቀጠለ በኋላ አመልካች በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች ሸጧል መባሉ በክርክሩ ሂደት የሚቀር ዕዳ መኖሩንና አለመኖሩን አረጋግጦ ክስ እንዲቀጥል ወይም እንዲቋረጥ በማድረግ ፋንታ በመያዣ የተያዙ ንብረቶች መሸጫውን ብቻ መነሻ በማድረግ ክርክሩን የሚያቋርጥ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ ክርክር ሐምሌ 08 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊመረመር ይገባዋል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከአመልካች የወሰዱትን ገንዘብ በወቅቱ ባለመመለሳቸው አመልካች በመያዣነት ከያዛቸው ተሽከርካሪዎች መካከል በሕጉ በተሠጠው ሥልጣን መሰረት ራሱ ለመሸጥ እንቅስቃሴ እያደረገ ባለበት ጊዜ በፍ/ቤት ተጠሪ ብር 396,904.52(ሦስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አራት ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንቲም) ከወለድና ከሌሎች ወጪዎች ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ በተጠሪ ላይ ክስ በመመስረቱ ፍርድ ቤቱ አመልካች የፎርክሎዠር ሥልጣኑን ሳይጨርስ በፍ/ቤት ክስ መመስረትን ስነ-ሥርዓቱ አይፈቅድም በማለት ክሱን ለጊዜው የዘጋው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ባንክ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች የፍርድ ሂደትን ማለፍ ሳያስፈልግ በሐራጅ የመሸጥ ሕጋዊ መብት ያለው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 97/90፣ 98/90 እና 216/92 ድንጋጌዎች መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በእነዚህ ህጎች በተሠጠው ሥልጣን ባንኩ ሲጠቀም ሊከተለው የሚገባው ሥነ-ሥርዓትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 394 እስከ 449 ድረስ ያሉትን ድንጋጌዎች ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 ድንጋጌ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የሚገኙት ደግሞ ስለፍርድ አፈፃፀም በሚገዛው የተጠቃሽ ሥነ-ሥርዓት ሰባተኛ መፅሐፍ ስር ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው የባንኩ ስራ ተበዳሪውን በመወከል የመያዣ ንብረቱን ሸጦ ለብድሩ ዕዳ እንዲውል ማድረግ ሲሆን ይሕም በይዘቱ የአፈፃፀም አካል ሊባል የሚችል ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱት አዋጆች ባንኮች በራሳቸው ምርጫ በብድር የሰጡትን ገንዘብ የመሰብሰብ ተግባር እንዲከተሉ አስገዳጅ መንገድ ስለመሆኑ የሚያሳይ ድንጋጌ አልያዙም፡፡ በሌላ አገላለፅ ባንኮች ብድራቸውን ለማስመለስ በፍርድ ቤት በኩል ክስ ሲመሰርቱ ጉዳዩ በአዋጅ መሰረት ሊፈፀም ይገባል ሊባል የማይችል ሲሆን መያዣ ንብረቶች ላይ ከአዋጁ ባገኙት መብት መሰረት እንቅስቃሴ ማድረግ መጀመራቸው በሁለት መንገድ ክስ ቀርቧል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ባንኮች በራሳቸው ምርጫ በብድር የሰጡትን ገንዘብ የመሰብሰብ ተግባር ሳይፈፅሙ በፍርድ ቤት ክስ ቢመሰርቱ ወይም በመረጡት መንገድ የመሄድ ሁኔታ አዋጁ ከወጣበት ዓላማ ጋር ሊፃረር ይችላል ተብሎ የሚታሰብ አይደለም፡፡ የአዋጁ አይነተኛ ዓላማ ባንኮች በተቻለ ፍጥነት በብድር የሠጡትን ገንዘብ በመሰብሰብ እንደገና መዋዕለ ንዋዩን ለኢንቨስትመንት ስራ እንዲውል በማድረግ በአገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ አዎንታዊ ሚና መጫወት ነው፡፡ ስለሆነም ባንኮች በአዋጁ የተሠጣቸውን ሥልጣን በመተው ወይም እንቅስቃሴውን ጀምረው እያለም ቢሆን በፍርድ ቤት ክስ ቢመሰርቱ ተቀባይነት የለውም ወይም በቅድሚያ የተጀመረው እንቅስቃሴ ሊያልቅ ይገባል የሚባልበት ሕጋዊ መሰረት ያለው ምክንያት የለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244(2/ሐ) ድንጋጌም በአንድ ፍርድ ቤት የቀረበ ክስ በሌላ ፍርድ ቤት እየታየ ከሆነ የሚከለክል እንጂ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ላለው አይነት ክርክር አግባብነት ያለው አይደለም፡፡

አመልካች በአዋጁ በተሠጠው ሥልጣን መሰረት እንቀስቃሴን ቀጥሎ በፍርድ ቤት ክስ ከመሰረተ በኋላ መያዣ ንብረቶችን ለመሸጥ እንቅቃሴ እያደረገ በፍርድ ቤት ክስ ቢመሰርት ወይም የመያዣ ንብረቶችን ክሱ እየቀጠለ ባለበት ሁኔታ መሸጡ ቢረጋገጥ ሊኖረው የሚችለው ውጤት የሚቀር እዳ መኖሩንና አለመኖሩን አረጋግጦ ክስ እንዲቀጥል ከማድረግ ወጪ ክሱን ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም፡፡ ንብረቶቹ የሚሸጡበት ዋጋ በአፈጻጸም ጊዜ የሂሳብ መተሳሰብ ተሰርቶበት ሊቀናነስ የሚችል ከመሆኑ ውጪ የአመልካችን በፍ/ቤት ክስ ከመቀጠል የሚያግደው አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት ባንክ ሊከተለው የሚገባው መንገድ አንድ ብቻ ነው ተብሎ ባልተደነገገበት ሁኔታ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244(2/ሐ) ድንጋጌን ያለቦታው በመጥቀስ በአመልካች ባንክ የተፈፀመ ድርጊት የተጠሪን የሂሳብ እንተሳሰብ ጥያቄ በአፈፃፀም ከማንሳት የማይከለክልባቸው ሆኖ እያለ የአመልካችን ክስ ማቋረጡ ሕጋዊ ባለመሆኑ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ከአመልካች ባንክ የወሰዱት የገንዘብ ብድር አለመከፈሉን ሳይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት በመያዣ የተያዙ ንብረቶች በሓራጅ መሸጣቸውን በመግለፅ በመሆኑና ይህ ደግሞ በኃላፊነታቸው መጠን ካልሆነ በሌላው ላይ የተለየ ውጤት ሊያስከትል የማይችል በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሠጥበት ጉዳዩን እንደገና መመለሱ የፍትሃ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረታዊ ዓላማ ክርክሮች በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ እልባት እንዲያገኙ ማስቻል ከመሆኑ አንፃር ሲታይ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊያን ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 58998 ታህሳስ 02 ቀን 2000 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 64410 የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ሚያዝያ 05 ቀን 1987 ዓ.ም በተፈረመ የብድር ውል ከአመልካች ለወሰዱት ገንዘብ የከፈሉት ማንኛውም ገንዘብ እና የመያዣ ንብረቶች ሽያጭ ዋጋን በአፈፃፀም ወቅት ከአመልካች ጋር የመተሳሰብ መብታቸው የተጠበቀ ሆኖ በስር ፍርድ ቤት ክስ የቀረበበትን ብር 396,904.52(ሦስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አራት ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንቲም) ወለድን በስምምነታቸው መሰረት ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ፣ እንዲሁም የመድን አረቦኑን ለአመልካች እንዲከፍሉ በማለት ወስነናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 46778

የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ኂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ**፡- አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአረቦን ክፍያን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ ኀዳር 01 ቀን 2000 ዓ.ም በአሁኑ አመልካች እና በአቶ አህመድ ማሞ ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪ የሰሌዳ ቁጥር 3-33558 ሆኖ ንብረትነቱ የአቶ አህመድ ማሞ ለሆነው ተሽከርካሪ አመልካች ጋር በጠየቁት መሰረት የመድን ውል ማድረጉን፣ከኢ.ኤ.አ ከ18/08 እስከ 18/08/2004 ድረስ ከሚፈለግባቸውን የአረቦን መድን ክፍያ ውስጥ ብር 24,472.89(ሃያ አራት ሺህ አራት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከሰማንያ ዘጠኝ ሳንቲም) ያልከፈሉ መሆኑን ገልፆ ይህንኑ ገንዘብ ከነ ሕጋዊ ወለድና ከልዩ ልዩ ወጪዎች ጋር አመልካችና አቶ አህመድ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሳሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መከላከያ መልስ፤የተጠሪ ጥያቄ በይርጋ የታገደ መሆኑን፣የመድን ውሉ ተዋዋይ ባለመሆኑ ክስ ሊቀርብበት እንደማይገባ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም የተጠየቀው የአረቦን ገንዘብ ክፍያ ጥያቄ የውል ዘመኑ አልፎ ውሉ ከተፈፀመ በኋላ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት እንደሌለው፣ውሉ በሁለት ምስክሮች ፊት ያልተደረገ በመሆኑ በሕግ ፊት የሚፀና አለመሆኑን፣የአረቦን ክፍያ አልከፈለም ከተባለ ተጠሪ ውሉን ከማቋረጥ ውጪ አረቦን ይከፈለኝ በማለት ክስ ማቅረብ እንደማይችል ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የአሁኑን አመልካች መከራከሪያ ነጥቦችን ውድቅ በማድረግ ለክሱ ገንዘብ ኃላፊ አድርጐ ብር 24,472.89(ሃያ አራት ሺህ አራት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከሰማንያ ዘጠኝ ሳንቲም) ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ 9%(ዘጠኝ ከመቶ) ወለድና ከልዩ ልዩ ወጪዎች ጋር ከአቶ አህመድ ማሞ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍል ሲል ወስኖበታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ድርጅት ነገረ ፈጅ ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡-ጉዳዩ በሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ የሚታገድ ሆኖ እያለና ውሉም መሰረትም የተፈፀመ ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የን/ሕ/ቁ. 666 እና 674 እንዲሁም ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያደረገው የመድን አረቦን ውል ሳይኖር የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731 እና 1952 ድንጋጌዎችን ባላገናዘበ መልኩ አመልካችን ለአረቦን ገንዘብ ክፍያ ጥያቄ ኃላፊ ማድረጋቸው ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የተከራከረው ክርክር መታለፉ ከን/ሕ/ቁ. 674 ድንጋጌ አንፃር አግባብ መሆን ያለመሆኑን ለመመረመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐ የተጠሪ ነገረ ፈጅ ኀዳር 10 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የጽሑፍ መልስ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ አግባብነት ይደግፋሉ ያሏቸውን ምክንያቶች በመዘርዘር ውሳኔው ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች አቶ አህመድ ማሞ ከተባሉ ግለሰብ ጋር በመሆን የመድን አረቦን ገብቶ የተዋዋለ መሆኑን፣የመድን ውልም እንዲታደስ ጥያቄ አቅርቦ በጥያቄው መሰረት ተጠሪ ማደሱን፣ግራ ቀኙን የሚያከራክረው የአረቦን ገንዘብ ክፍያ መከፈል በነበረት ጊዜ ባለመከፈሉ ተጠሪ የይከፈለኝ ጥያቄ ማቅረቡ በይርጋ የታገደ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው የሕግ ጥያቄ ነው፡፡

በመሰረቱ አመልካች ለክርክሩ መሰረት ያደረገው የን/ሕ/ቁ.674/1/ ሲሆን የድንጋጌው ሙሉ ይዘትም፡- በኢንሹራንስ ውል ምክንያት የሚቀርብ ማንኛውም ክስ የሚታገደው ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳት ከተደረገበት ወይም በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያላቸው ወገኖች ጉዳቱን ካወቁበት ቀን ጀምሮ ከሁለት አመት በኋላ ነው የሚል ሲሆን የእንግሊዝኛው ትርጉምም፡-

Any claim arising out of a contract of insurance shall be barred after two years from the occurrence giving rise to the claim or from the day when the parties knew of the occurrence. በሚል ተቀምጧል፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሰረት በኢንሹራንስ ውል ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ ማንኛውም ክስ ጥያቄውን ለማቅረብ የሚያስችለው ምክንያት በተከሰተ ወይም ጥቅም ያላቸው ወገኖች ጉዳዩን ካወቁበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በተያዘው ጉዳይ የመድን አረቦን መከፈል የነበረበት ጊዜ ሁለት ዓመት ያለፈው ስለመሆኑ ተጠሪም የማይክደው ፍሬ ጉዳይ ሲሆን ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው ለጉዳዩ

አግባብነት ያለው ድንጋጌ በንግድ ሕጉ የተመለከተው ሳይሆን በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 1845 ስር የተመለከተው ነው በማለት ነው፡፡ ሆኖም ጉዳዩ የኢንሹራንስ ውልን መሰረት ያደረገ እንደመሆኑ መጠን በንግድ ሕጉ የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ ተፈፃሚነት የማይኖርበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ከላይ የተመለከተው ድንጋጌ ግልጽ ከመሆኑ አንፃር የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 754/1/ ስር የተመለከተው ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677 እና 1845 መሰረት በማድረግ አመልካች ያቀረበውን የይርጋ ክርክር ውድቅ ያደረገው ያላግባብ ስለሆነ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 102951 ጥቅምት 05 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 72894 ግንቦት 03 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ የጠየቀው የመድን አረቦን ይከፈለኝ ጥያቄ በሁለት አመት ይርጋ ጊዜ የታገደ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 46808

ሚያዝያ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ጫልቱ ሚደግሳ - በሌሉበት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የመድን ሰጪ የኃላፊነት መጠን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው የሰሌዳ ቁ 3ኦሮ 03004 የሆነ የሕዝብ ማመላለሻ ንብረትነቱ የአቶ ሐብታሙ አለነህ ሆኖ በአቶ ጌታነህ አለነህ ሲሽከረከር የሰሌዳ ቁጥር 3 ኢት 16818 የሆነ መኪና ገጭቶ በመኪናው ውስጥ የነበሩ አቶ ተመስገን ሚደግሳ እና ወ/ሮ ስኳሬ ዲቲን የገደለ በመሆኑ የካሣ ጥያቄ ክስ በወራሾች ቀርቦ አመልካችም በመድን ውል መነሻ በክርክሩ እንዲገባ መደረጉን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ የአሁን አመልካች ኃላፊነት እና የካሣ መጠንን አስመልክቶ ክርክር ያቀረበ ቢሆንም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን የተመለከተው የኢሉባቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሳሾች ለጉዳቱ ኃላፊ ናቸው ካለ በኋላ የካሣ መጠኑም ብር 106,400(አንድ መቶ ስድስት ሺህ አራት መቶ) ብር እንዲከፈል ወስኗል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የካሳ መጠኑን በማሻሻል ባጠቃላይ ብር 68,200(ስልሳ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ) እንዲከፈል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል ሲል ሰኔ 16/2001 ዓ.ም በጠበቃው አማካይነት ባቀረበው አቤቱታ የሟች ወራሾች በቀጥታ ክስ ማቅረብ እንደማይችሉ፣ የካሳ መጠን አስመልክቶ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ስሕተት እንደሆነ እና ካሣ መክፈል አለበት ከተባለም የአመልካች የኃላፊነት ወሰን ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) ለአንድ ሰው እንደመሆኑ በጠቅላላ ከስልሳ ሺህ(60,000) በላይ የሚከፍልበት አግባብ ባለመኖሩ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ በዚህ ረገድ እንዲታረም ሲል አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ የአመልካች የኃላፊነት ወሰን ከብር 60,000(ስልሳ ሺህ) በላይ መወሰኑ በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪ እንዲቀርቡ አዝዟል፡፡ ተጠሪ ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲወሰን ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡

የአመልካች ኃላፊነት የመነጨው ከመድን ውል ስለመሆኑ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ አመልካች ለሥር ተከሳሽ የሰጠው የመድን ሽፋን የሦስተኛ ወገን ኃላፊነት ስለመሆኑ እና ለአንድ ሰው የሚከፈለው ካሣ መጠን ጣሪያው ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) ስለመሆኑም አላከራከረም፡፡ አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው የሥር ተከሳሽ መኪና ጉዳት ያደረሰው በሁለት ሰዎች ላይ ስለመሆኑም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡

ስለሆነም በውሉ መሠረት የአመልካች ኃላፊነት ወሰን ብር 60,000(ስልሳ ሺህ) መሆኑ ታውቋል፡፡ በንግድ ሕግ አንቀጽ 665(2) መሠረት ደግሞ የመድን ሰጪው ኃላፊነት በመድን ውሉ የተመለከተውን የገንዘብ ወሰን መሠረት ካሣ መክፈል ግዴታ አለበት፡፡ አመልካችም እየተከራከረ የነበረው የኃላፊነት መጠን በውል ከተወሰነው በላይ ሊሆን እንደማይገባ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች በግልፅ ውሉን እና ሕጉን መሠረት አድርጐ ክርክሩን አቅርቦ እያለ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ባለማገናዘብ አመልካች ከውል ግዴታው በላይ ብር 68,200(ስልሳ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ) እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

ስለሆነም በዚህ ረገድ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማረም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አመልካች በዋስትና ውል በተመለከተው መሠረት ለመክፈል የሚገደደው ብር ስልሳ ሺህ (60,000) ብቻ ነው ብለን የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት የመ/ቁ 62171 መጋቢት 22/2002 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስነናል፡፡
2. በኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት የተወሰነውን ቀሪ የካሣ ገንዘብ የሥር አንደኛ ተከሳሽ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ተሻሽሎ በተወሰነው መሠረት የኢሊባቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 48698

ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ - አልቀረቡም

**ተጠሪ፦** አቶ ሣሙኤል ዓለሙ - ጠበቃ ፈቃዱ አሰፋው ቀረቡ

*መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡*

## ፍ ር ድ

*ይህ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ኩባንያ የመድን ሽፋን የገባሁለት የሠ.ቁ 3-34603 የሆነ መኪና በደረሰበት አደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶበታል፡፡ በመድን ውሉ መሠረት ተከሳሽ ተገቢውን ካሣ እንዲከፍለኝ ብጠይቅም ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ ጉዳት የደረሰበትን መኪናዬን ሙሉ ዋጋ ብር 235,000(ሁለት መቶ ሠላሣ አምስት ሺህ) እንደዚሁም መኪናው በጊዜው ባለመጠገኑ ወይንም ዋጋውን ባለመክፈሉ ምክንያት በከሳሽ ላይ የደረሰውን የጥቅም መቋረጥ ብር 58,000(ሃምሣ ስምንት ሺህ) ጨምሮ ክሱ ካስከተለው ወጭና ኪሳራ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡*

*የከሳሽ ክስና ማስረጃ ለተከሳሽ ደርሶ በሰጠው መልስ በከሳሽ መኪና ላይ ጉዳት የደረሰው ከመድን ውሉ ውጭ ሁለት ሰዎችን ጭኖ ሲያጓጉዝ ሲሆን የመድን ሽፋን የተገባው ጭነት ጭኖ ሲጓጓዝ ለሚደርስ ጉዳት ነው፡፡ ስለሆነም የከሳሽ መኪና ሰው ጭኖ ሲጓጓዝ ለደረሰው ጉዳት ከመድን ውሉ አኳያ ተከሳሽ ካሣ ለመክፈል ግዴታ የለበትም፡፡ የክፍያ መጠኑን በተመለከተም ከሳሽ የደረሰበት መኪና ሊጠገን የማይችል ስለመሆኑ ባላስረዱበት ሁኔታ ሙሉ ዋጋ እንዲከፈላቸው መጠየቃቸው ተገቢነት የለውም፡፡ በመድን ውሉ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠንም መኪናው የመድን ሽፋን በተሰጠው ጊዜ የተገመተ እንጂ አሁን ያለውን የመኪና ዋጋ ስለማያስረዳ በዚህ ልክ ካሣ ሊከፈል አይገባም፡፡ በመድን ውሉ መሠረትም ተከሳሽ ለተቋረጠ ጥቅም ኃላፊነት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡*

*የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ኃላፊነትን በተመለከተ ተከሳሽ በከሳሽ መኪና ላይ ጉዳት የደረሰው ሰው ጭኖ ሲጓዝ እንጂ ዕቃ ጭኖ ሲጓዝ ስላልሆነ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ቢከራከርም ሰው ጭኖ ጉዳት ስለመድረሱና የሰዎችን መጫን ከአደጋው ጋር ያለውን ግንኙነት አላስረዳም፡፡ ይልቁንም በማስረጃነት የቀረበው የትራፊክ ፖሊስ ሪፖርት በከሳሽ መኪና ላይ ጉዳት የደረሰው መሐል መንገድ ላይ የገባን ሰው ለማዳን ሲሞክር መኪናው መንገዱን ስቶ ከዛፍ ጋር በመጋጨቱ ምክንያት እንደሆነ የሚያረጋግጥ ስለሆነ ሰው ጭኖ መጓዙ የአደጋው መንስኤ ባለመሆኑ ተከሳሽ በመድን ውሉ መሠረት በመኪናው ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡*

*የካሣ መጠኑን በተመለከተ ፍ/ቤቱ ጉዳት የደረሰበትን የከሳሽ መኪና በባለሙያ እንዲገመት አድርጎ ጉዳቱ በመቶኛ ሲሰላ 83.48% በገንዘብ ሲሰላ ደግሞ ብር 196,546.98(አንድ መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ አምስት መቶ አርባ ስድስት ሺህ ከዘጠና ስምንት) አረጋግጦ ከ75% በላይ ጉዳት ከደረሰ እንደ ሙሉ ውድመት /Total loss/ ስለሚቆጠር የመኪናውም ግምት ብር 235,000(ሁለት መቶ ሠላሳ አምስት ሺህ) እንደሆነ ግራ ቀኙ ባደረጉት የመድን ውል ላይ ስለተመለከተ ተከሳሽ ይህንኑ ገንዘብ ለከሳሽ እንዲከፍል የተቋረጠ ጥቅምን በተመለከተ ግን በመኪናው ላይ የደረሰው ሙሉ ውድመት ስለሆነ ተከሳሽ ለመክፈል አይገድድም በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡*

*ተከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው  ነው በማለት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡*

*የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በተጠሪ መኪና ላይ በአደጋ ምክንያት ጉዳት በደረሰ ጊዜ 2 ሰው ጭኖ መገኘቱ ከመድን ውሉ አኳያ አመልካች ኃላፊ ነው መባሉ ተገቢነቱን ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጐ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡*

*በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን በበኩላችንም ጉዳዩን እንደሚከተው መርምረናል፡፡*

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው መባሉ በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም? በአግባቡ ነው ከተባለስ የካሣ ክፍያው መጠን ተገቢነት አለው ወይንስ የለውም? የሚሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች ኃላፊ መባል የለብኝም በማለት አጥብቆ የሚከራከረው በተጠሪ መኪና ላይ ጉዳት ያደረሰው ሰው ጭኖ ሲጓዝ እንጂ ዕቃ ጭኖ ባለመሆኑ ከመድን ውሉ አኳያ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በበኩሉ በመኪናው ላይ 2 ሰዎች ተጭነው እንደነበረ አምኖ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች የተጫኑት የመኪናውን አገልግሎት ከዕቃ መጫን ሰው ወደመጫን አገልግሎት በመቀየር ሳይሆን በወቅቱ ተጭኖ የነበረው የመብራት ኃይል መ/ቤት ምሶሶዎችን ለመደገፍ፣ ለመጫንና ለማውረድ ተብሎ የጭነት ሥራ ለመሥራት ነው በማለት መከራከሩን ተገንዝበናል፡፡

አመልካች በመድን ውሉ መሠረት ካሣ ለመክፈል የምንገደደው መኪናው ዕቃ ጭኖ ሲጓዝ ለሚደርስበት ጉዳት እንጂ ሰው ጭኖ በሚጓዝበት ጊዜ አይደለም የሚል ክርክር ቢኖረውም የተጠሪ መኪና ሁለቱን ሰዎች የጫነው ከጭነት ሥራ ጋር በተያያዘ ያልተጫኑ ስለመሆኑና ሰዎችን ለማጓጓዝ ታስቦ የተጫኑ ስለመሆናቸው ማስረዳት የሚጠበቅበት ከመሆኑም በላይ ሰው የመጫኑም ሁኔታ ለአደጋው መንስኤ /Risk Possibility/ መሆኑንም ጭምር ማስረዳት ይጠበቅበታል ሆኖም ግን አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ይልቁንም ጉዳት የደረሰው በጉዞ ላይ መሐል መንገድ ላይ የገባን ሰው ለማዳን ሹፌሩ ጥረት ሲያደርግ መንገዱን ስቶ በመውጣት ከዛፍ ጋር በመጋጨቱ ምክንያት እንደሆነ በትራፊክ ፖሊስ ሪፖርት ላይ የተገለፀ ስለሆነ በተጠሪ መኪና ላይ የተጫኑት ሰዎች ኃላፊነቱን ከሚያስከትለው ሁኔታ ጋርም ሆነ ከካሣ ክፍያው ጋር ምንም የሚያገናኛቸው ስለሌለ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የካሣ ክፍያ መጠኑን በተመለከተ የተጠሪ መኪና ከአደጋው በኋላ ተገምቶ ጉዳቱ በድምሩ ብር 196,546.98(መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ አምስት መቶ አርባ ስድስት ብር ከዘጠና ስምንት ሣንቲም) መሆኑ ተረጋግጧል የሥር ፍ/ቤቶች ለተጠሪ ካሣ እንዲከፈላቸው ውሣኔ የሰጡት የመኪናው ዋጋ ብር 235,000(ሁለት መቶ ሠላሳ አምስት ሺህ) እንደሆነ በመድን ውሉ ላይ ስለተመለከተ ይህንኑ አመልካች ለተጠሪ መክፈል አለበት በማለት ነው፡፡

ሆኖም ግን ለአንድ ንብረት ወይም ዕቃ መድን የገባ ሰው ካሣ ሊከፈለው የሚችለው ጉዳት በደረሰ ጊዜ ዕቃው ከሚያወጣው ዋጋ ሳይበልጥ እንደሆነ በንግድ ሕግ ቁጥር 678 የተመለከተ ሲሆን የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም ጉዳት የደረሰበት የተጠሪ መኪና በባለሙያ እንዲገመት ትዕዛዝ ከሰጠ በኃላ ግምቱ ሲቀርብ በዚሁ ግምት መሠረት ካሣ እንዲከፈል መወሰን ሲገባው ከግምት በኋላ ተመልሶ በመድን ውሉ ላይ የተቀመጠው የመኪናው ግምት እንዲከፈል መወሰኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 108121 በ12/2/2001 ዓ.ም. የሰጠው የኃላፊነት ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 80957 ሐምሌ 28 ቀን 2001 ዓ.ም. ይህንኑ የኃላፊነት ውሣኔ በማጽናት የሰጠውን ትዕዛዝ አጽንተናል፡፡ በሌላ በኩልም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ በተጠቀሰው የመ/ቁጥር በ28/7/2001 ዓ.ም. አመልካች ብር 235.00 ካሣ ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ ከንግድ ሕግ ቁጥር 678 ጋር ያልተገናዘበ ስለሆነ በፍብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348/1/ መሠረት አሻሽለን የተጠሪ መኪና በጉዳቱ ጊዜ በተገመተው መሠረት ብር 196,546.98/አንድ መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ብር አምስት መቶ አርባ ስድስት ከዘጠና ስምንት ሣንቲም/ ካሣ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 39902

ሰኔ 18 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አልማው ወሴ

**አመልካች፡-** የኢት/መድን ድርጅት - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ብሬ ሙሲሳ - በሌሉበት

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች ለፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ለደንበኛው ለኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት ናፍጣና ቤንዚን የጉዞ መድን ሽፋን የሰጠ ሲሆን ከነዳጁ ውስጥ 31,513 ሊትር የስር ተከሳሾች በሆኑት መኪና ሲጓጓዝ መኪናው ተገልብጦ 18,153 ሊትር የፈሰሰ በመሆኑና የነዳጁን ዋጋ ብር 45,927.09(አርባ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ሰባት ብር ከዘጠኝ ሣንቲም) ለደንበኛው ስለከፈለ ይህንኑ ገንዘብ ከተከሳሾች መኃከል ኃላፊነት ያለበት ተለይቶ እንዲከፍሉ እንዲወሰንለት አመልክቷል፡፡ የስር ሁለተኛ ተከሳሽ ከክሱ ወጪ የሆኑ ሲሆን ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ ጉዳዩ በእርቅ ማለቅ ያለበት ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡ ተጠሪ በዋናው ጉዳይ ላይም በሰጡት መልስ ነዳጁን የጫነው መኪና ባለቤት ስላልሆኑ ኃላፊነት እንደሌለባቸው ከነዳጁ ባለቤት ጋር ያደረጉት የማጓጓዝ ውል አለመኖሩን እንዲሁም ተዋዋይ ወገኖቹ የኢት/ነዳጅ ድርጅትና የጣና ፈሳሽ ማጓጓዣ ባለንብረቶች ማህበር ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ጠይቀዋል፡፡ ሦስተኛ ተከሳሽ የነበረው ወይራ ትራንስፖርት ድርጅት ክስ የተመሰረተበትን ነዳጅ የጫነው ተሳቢ ነዳጁ ፈሰሰ ከተባለበት ቀን በፊት ለስር ሁለተኛ ተከሳሽ ያስተላለፈ በመሆኑ ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የተጠሪ ጭነት መኪና ወደኋላ ተንሸራቶ እየተገለገሉበት ያለውን ነዳጅ የጫነውን ተሳቢ እንዲገለበጥ በማድረጉ ተጠሪ ለጉዳቱ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2081(1) እና (2) መሰረት ኃላፊ ናቸው ሦስተኛ ተከሳሽ የነበረው ተሳቢውን አደጋው ከመድረሱ በፊት ለስር ሁለተኛ ተከሳሽ ያስተላለፈ በመሆኑ ኃላፊነት የለበት በማለት ተጠሪ በክስ የተጠቀሰውን ገንዘብ ለአመልካች እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከተመለከተ በኋላ በኢት/ነዳጅ ድርጅትና በጣና ፈሳሽ መጓጓ ዣ ባለንብረቶች ማህበር መኃከል በተደረገው ውል አንቀጽ 18 መሰረት ከውሉ ትርጉምና አፈፃፀም ጋር ግንኙነት ባላቸው ምክንያቶች የሚነሳ አለመግባባት ሁለቱ በመረጧቸው ገላጋይ ዳኞች አማካኝነት እንደሚታይ ስምምነት ተደርጓል፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተው በን/ህ/ቁ 683 ባገኘው የመዳረግ መብት በመሆኑና ይህ የመዳረግ መብት ደንበኛው ባለው መብት ልክ ስለሆነ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የሚነሳው ክርክር በስምምነት ማለቅ ስላለበት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ የይግባኝ ሰሚውን ፍ/ቤት ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታው በአመልካች ደንበኛና በጣና ፈሳሽ ማጓጓዣ ባለንብረቶች ማህበር መሃከል የተደረገው ውል ተፈፃሚነት የሚኖረው በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መሃከል ለሚነሳ ክርክር እንጂ ለተያዘው ጉዳይ አይደለም፡፡ በተጠሪ ላይ ክስ የቀረበው የተረከቡት ነዳጅ ላይ ጉዳት በመድረሱ የአጓጓዥ ኃላፊነት ስላለባቸው በመሆኑ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለውን ውል መሰረት በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ነው፡፡ ችሎቱም የአመልካች ደንበኛ ከጣና ፈሳሽ መጓጓዣ ባለንብረቶች ማህበር ጋር ጉዳዩን በእርቅ ለመጨረስ ስለተስማማ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ በፍ/ቤት ሊታይ አይገባም በሚል የተሰጠው ውሳኔን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪ በህይወት ስለሌሉ ወራሾቻቸው እንዲቀርቡ በጋዜጣ ጥሪ ቢደረግም ስላልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ክስ የመሰረተው በተጠሪ የጭነት መኪና እየተሳበ በነበረው ተሳቢ ላይ ተጭኖ የነበረው ነዳጅ ተሳቢው በመገልበጡ ምክንያት ፈሶ ስለባከነ ለደንበኛው የከፈለው ገንዘብ ተጠሪ እንዲተኩ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የአመልካች ክስ በፍ/ቤት ቀርቦ ሊታይ አይገባም በማለት የወሰነው የአመልካች ደንበኛ ከጣና

ፈሳሽ ማንንዣ ባለንብረቶች ማህበር ጋር ባደረገው ውል በሁለቱ መሃከል የሚነሳ ማንኛውም አለማግባባት በእርቅ ለመጨረስ ያደረገው ስምምነትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ውል በአመልካችና በተጠሪ መሃከል ላለው ክርክር ተፈፃሚነት አለው? የለውም? የሚለውን ጭብጥ ችሎቱ መርምሯል፡፡

ውል ተዋዋዮች የገቡባቸው ግዴታዎች በመሃከላቸው አስገዳጅ እንዲሆኑ ወደውና ፈቅደው የሚመሰርቱ በመሆኑ ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታቸውን በፈቃዳቸው ወስነው ያቋቋሙት ውል ሌላ ሦስተኛ ወገንን ሊያስገድድ የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡ በዚህም ምክንያት ነው ውሎች ተፈፃሚነታቸውና አስገዳጅነታቸው ውሉን ባቋቋሙ ተዋዋይ ወገኖች መሃከል ብቻ መሆኑ ፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731 ስር ተደንግጎ የምናገኘው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የአመልካች ደንበኛና ጣና ፈሳሽ ማንንዣ ባለንብረቶች ማህበር ባደረጉት ውል በሁለቱ መሃከል የሚነሳ ማንኛውም አለመግባባት በእርቅ ለመጨረስ ተስማምተዋል፡፡ የዚህ ውል ተዋዋዮች ሁለቱ ብቻ ሲሆኑ ተጠሪ ተዋዋይ ወገን አልነበሩም፡፡ ስለሆነም ይህ ውል ተፈፃሚነቱ ወይም አስገዳጅነቱ ውሉን ባቋቋሙት ተዋዋይ ወገኖች ላይ ብቻ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይህ ውል በአመልካችና በተጠሪ መሃከል ተፈፃሚነት አለው የሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ለማቅረብ የቻለው በደንበኛው መብት ተደርጎ ስለሆነ የሚኖረው ደንበኛው ያለው መብት ነው በማለት ነው፡፡ በእርግጥ በን/ህ/ቁ 683(1) መድን ወጪው ለደንበኛው በከፈለው የካሳ መጠን ልክ ለጉዳቱ ኃላፊ የሆነውን ሰው የሚጠይቀው በደንበኛው መብት ተደርጎ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ግን መድን ሰጪው የከፈለውን የካሳ መጠን በሚመለከት ብቻ እንጂ የደንበኛው ሌሎች መብቶችና ግዴታዎችን ሁሉ የሚመለከት ስላልሆነ በተያዘው ጉዳይ የአመልካች ደንበኛ ከጣና ፈሳሽ ማንንዣ ጋር ያደረገው ውል አመልካች በተጠሪ ላይ ለመሰረተው ክስ ተፈፃሚነት ሊኖረው አይችልም፡፡ ተጠሪ በዚህ ውል ተዋዋይ ወገን አልነበሩም፡፡ ምንም እንኳን አመልካች በከፈለው የካሳ መጠን ልክ የደንበኛውን መብት ተደርጎ የቀረበ ቢሆንም የአመልካች ደንበኛ ከተጠሪ ጋር የሚነሳ አለመግባባትን በእርቅ ለመጨረስ የተስማማበት ውል የለም፡፡ በመሆኑም የአመለካች ደንበኛ ከሌላ 3ኛ ወገን ጋር የተደረገው ውል ከተያዘው ጉዳይ ጋር ግንኙነት ስለሌለው አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ በእርቅ ሊያልቅ የሚገባው ስለሆነ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የላቸውም መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 44024 ሰኔ 4 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 32239 ግንቦት 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ስላለው ይግባኝ ሰሚው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ይግባኝ ተቀብሎ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 52910

ሐምሌ 28 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ አንዳርጌ ታደሰ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነ/ፈጅ - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

ጉዳዩን የጀመረው በባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር በመኪናቸው ላይ ለሚደርስ አደጋ ለአስራ ሁለት አመታት የቆየ የመድን ውል ግንኙነት የነበራቸው መሆኑን ገልፀው በመኪናቸው ላይ በደረሰው የመገልበጥ አደጋ መኪናው ከጥቅም ውጪ በመሆኑ ተጠሪ ብር 400,000(አራት መቶ ሺህ) እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ የመድን ውሉ የተቋረጠው ኀዳር 7 ቀን 2000 ሆኖ አደጋው የደረሰው ኀዳር 26 ቀን 2000 ዓ.ም በመሆኑ አመልካች ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቦ በአማራጭም ሌሎች ክርክሮች አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካች ታህሳስ 15 ቀን 2001 ዓ.ም ለተጠሪ ባቀረቡት ማመልከቻ ለአስራ ሁለት አመት በነበራቸው ውል ምንም አደጋ ባለመድረሱ ውሉ ሳይታደስ ጊዜው ቢያልፍም ኀዳር 26 ቀን 2000 ዓ.ም ለደረሰው አደጋ ድርጅቱ አስተያየት አድርጐ ብር 100,000(መቶ ሺህ) እንዲከፍላቸው መጠየቃቸውን፣እንዲሁም የአመልካች ምስክር አመልካች ውሉን ሊያድሱ ተጠሪ ዘንድ ሂደው መኪናው ላይ አደጋ በመድረሱ ክፍያ አንቀበልም ማለቱን መመስከራቸውን ገልፆ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል ያለው የውል ግንኙነት በመቋረጡ አመልካች ክሱን ለማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል መዝገቡን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በአቤቱታቸው የውሉ ዘመን ከማለቁ በፊት ባሉት ጥቂት ቀናት ውሉን እንዳድስ ጠይቆኝ ስምምነቴን ስለገለጸኩ አረቦን ባለመክፈሌ ብቻ ውሉ ሊቋረጥ እንደማይችል የን/ህ/ቁ. 666/2//3/ አይችልም፣የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች ጥያቄ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ከን/ህ/ቁ. 666 አኳያ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪም ቀርቦ በሰጠው መልስ የን/ህ/ቁ. 666 ተፈፃሚነት የሚኖረው ውሉ ፀንቶ ባለበት ጊዜ መሆኑንና የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል የሚልባቸውን ሌሎች ክርክሮች አቅርቧል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው አመልካች በባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ የመሰረቱት ተጠሪ ለመኪናቸው የመድን ሽፋን ለመስጠት በገባው ውል መሰረት መኪናቸው ላይ አደጋ በመድረሱ የመድን ዋስትና እንዲከፍላቸው ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አደጋው በደረሰበት እለት በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የነበረው የመድን ውል ተቋርጦ ስለነበር አመልካች ክስ ለማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ክሱን ተቃውሟል፡፡ በመሰረቱ ማንኛውም ሰው ክስ ለማቅረብ የሚፈቀድለት ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ወይም ክሱ በተመሰረተበት ሃብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ሲኖረው እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ ድንጋጌ መረዳት የሚቻል ነው፡፡ አመልካችም ግራ ቀኙ ካደረጉት የመድን ውል የሚመነጭ መብት ያላቸው መሆኑን በማመን ነው ክስ የመሰረቱት፡፡ ነገር ግን በግራ ቀኙ መሃከል የተደረገው የመድን ውል ኀዳር 7 ቀን 2000 ዓ.ም ማብቃቱን ከመዝገቡ ተመልክተናል አመልካች ይህንን አላስተባበሉም፡፡ ክርክራቸው ውሉ ሊያበቃ ጥቂት ቀናት እንደቀሩት ተጠሪ ውሉ እንዲታደስ ጠይቆኝ ፈቃደኛነቴን የገለጽኩ ስለሆነ አረቦን ክፍያ ባለመክፈሌ ብቻ ውሉ ሊቋረጥ አይችልም በማለት ነው፡፡፡ ነገር ግን አመልካች በመኪናቸው ላይ አደጋ የደረሰው ውሉ ከመታደሱ በፊት በመሆኑና ቀደም ሲል በነበረው የ12 አመታት የመድን ውል ግንኙነት በመኪናቸው ላይ አደጋ ባለመድረሱ ድርጅቱ አስተያየት አድርጐ ብር 100,000(መቶ ሺህ) እንዲከፈላቸው ማመልከታቸውን የስር ፍ/ቤት አረጋግጧል፡፡ ይህንም በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የነበረው የመድን ውል ከተቋረጠ በኋላ አደጋው መድረሱን አመልካች ራሳቸው አምነው የተቀበሉት መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በሌላ በኩል ውሉ እንደታደሰ የሚቆጠረው ተጠሪ ውሉ እንዲታደስ አመልካችን ስለጠየቀ ብቻ ሳይሆን አመልካች ውሉን ለማደስ ፈቃደኛ ሆነው በሕጉ አግባብ ውሉን ሲያደርጉ ነው፡፡ ይህን ስለማድረጋቸው አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ በአጠቃላይ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የተደረገው የመድን ውል ኀዳር 7 ቀን 2000 ዓ.ም ካበቃ በኋላ ውሉ ስላልታደሰ የውል ግንኙነታቸው ተቋርጧል፡፡ አመልካች የጠቀሱት የንግድ ሕጉ ቁጥር

666 ስንመለከተውም ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የለውም፡፡ ምክንያቱም ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው በመድን ሰጪውና በመድን ገቢው መሃከል የፀና ውል ኖሮ መድን ገቢው በውሉ በተመለከተው መሰረት የአረቦን ክፍያ መክፈል ሲያቋርጥ እንጅ የመድን ውል በሌለበት ሁኔታ አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን በአመልካችና በተጠሪ መሃል የነበረው ውል ጊዜው አብቅቶ ተቋርጧል፡፡ ስለሆነም አመልካች ይህንን ድንጋጌ መሰረት አድርገው ያቀረቡት ክርክር የድንጋጌውን መንፈስ ያላገናዘበ ነው፡፡ በሌላ በኩል የመድን ዋስትና እንዲከፈለው የተጠየቀበት መኪና አደጋ የደረሰበት ኀዳር 26 ቀን 2000 ዓ.ም ስለመሆኑ በግራ ቀኙ የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አደጋው የደረሰው በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መሃከል የነበረው የውል ግንኙነት ከተቋረጠ በኂላ በመሆኑ አመልካች የመድን ዋስትና እንዲከፈላቸው ለመጠየቅ የሚያስችል መብት የላቸውም፡፡ በዚህም ምክንያት የስር ፍ/ቤቶች አመልካች ክስ ለማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 06284 ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 77050 ኀዳር 16 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

# ጉምሩክ (ግብር)
# ታክስ

የሰ/መ/ቁ. 39574

ጥቅምት 03 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ነ/ፈጅ ጌታቸው ምንተስኖት - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ ምልእተፀጋ ቢዘን - አልቀረቡም

2. አቶ ፍፁም ገዛኸኝ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት ለአንደኛ ተጠሪ በወር ብር 350.00(ሦስት መቶ ሃምሳ ብር) ያከራያቸው ሲሆን ተከራይዋ ቤቱን ለሁለተኛ ተጠሪ ያስተላለፉ በመሆኑ የሚፈለግባቸውን ውዝፍ የቤት ኪራይ፣ቅጣት፣የውሃ እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍሉ እና ቤቱን እንዲያስረክቡ፣በተጨማሪም ቤቱን እስኪያስረክቡ ላለው ጊዜ ኪራይ እንዲከፍሉ በማለት ጠይቋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ተጠርተው ስላልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት የታየ ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ ግን ቀርበው ለቀረበባቸው ክስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ እንዲከፈል ሳይጠየቅ 2 አመት ያለፈው የቤት ኪራይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024(መ) መሰረት እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው፣ ቀሪውን ውዝፍ የቤት ኪራይ፣የውሃ ክፍያና ተጨማሪ እሴት ታክስ ተጠሪዎች ይክፈሉ፣የኪራይ ውሉ ተቋርጧል፣ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች ያስረክቡ፣ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ ያለውን የቤት ኪራይ ሁለተኛ ተጠሪ ይክፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካችም አንደኛ ተጠሪ ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ በየወሩ የቤት ኪራይ እንዲከፍሉ ቢወሰንም ከኪራዩ ጋር ተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍሉ ውሳኔ ስላልተሰጠ ይኸው እንዲታረምለት ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታም አመልካች ለንግድ አገልግሎት ከሚያከራያቸው ቤቶች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመሰብሰብ ግዴታ በአዋጅ የተጣለበት በመሆኑ ቤቱን እስኪረከብ ድረስ ተጠሪዎች ከውርሃዊ ኪራይ ጋር ተጨማሪ እሴት ታክስ ሊከፍሉ ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረጉ ሁለተኛ ተጠሪ ቀርበው መልስ የሰጡ ሲሆን አመልካችም የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ግን ተጠርተው መልስ ያልሰጡ በመሆኑ ችሎቱ መዝገቡን መርምሯል፡፡

ይህ ችሎት ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ ወርሃዊ ኪራይ እንዲከፍሉ ሲወሰን ተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍሉ ሳይወሰን መታለፉ አግባብ ነው? አይደለም? የሚለውን ነጥብ መርምሯል፡፡

አመልካች ለንግድ ድርጅትነት የሚያከራያቸው ቤት ላይ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 መሰረት ታክስ የመሰብሰብ ግዴታ ያለበት ለመሆኑ ያቀረበውን ክርክር ሁለተኛ መልስ ሰጪ ክደው አልተከራከሩም፡፡ የሁለተኛ መልስ ሰጪ ክርክር ፍርድ ቤቱ የኪራይ ውሉን ያፈረሰው በመሆኑ በሌለ የኪራይ ውል የተጨማሪ እሴት ታክስ መሰብሰብ አይችልም በማለት ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 መሰረት የንግድ ቤቶች የማከራየት የንግድ እንቅስቃሴ ከታክስ ነፃ ከሆኑት ግብይቶች ውስጥ እንደማይካተት የአዋጁ አንቀጽ 8 ያመለክታል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ቢሆን ይህንኑ የአመልካች ግዴታ ተገንዝቦ የኪራይ ውሉ እስከተቋረጠበት እለት ድረስ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተጠሪዎች እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል አንደኛ ተጠሪ የኪራይ ገንዘቡን ባለመክፈላቸው የኪራይ ውሉ የፈረሰ ቢሆንም ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ይዘው እየተገለገሉበት በመሆኑ ላገኙት ግልጋሎት የቤቱን ኪራይ በየወሩ እንዲከፍሉ ተወስኖባቸዋል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪው ያቀረቡት ቅሬታ የለም፡፡ የንግድ ቤቱ ይዘው ስለሚገለገሉበት የኪራይ ገንዘብ የሚከፍሉ ከሆነ ደግሞ ኪራዩን ተከትሎ የሚመጣውን ተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ሊወጡ ይገባቸዋል፡፡ ይህ ግዴታ ደግሞ ከውል ሳይሆን ከሕግ የመነጨ ግዴታ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የኪራዩ ገንዘብ እንዲከፈል ሲወስን የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፈለው ሳይወሰን ማለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

## ው ሳ ኔ

መ/ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 43032 ጥር 19 ቀን 2000 ዓ.ም ሰጠው ውሳኔና የፌ/ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 65580 ግንቦት 08 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሻሽለዋል፡፡

ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ ከሚከፍሉት የኪራይ ገንዘብ ጋር ተጨማሪ እሴት ታክስ ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡

ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 45882

ታህሳስ 06 ቀን 2002 ዓ.ም.

**ዳኞች፡** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - ነ/ፈጅ ወንዱ ለማ ቀረቡ

**ተጠሪ፡** 1. ወ/ሮ እጅጋየሁ አራምዴ - ጠበቃ ብስራት ወ/መስቀል

2. ጌታቸው ተ/አረጋይ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ - የተመለከተው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ ከጉምሩክ ቀረጥ አከፋፈል ጋር የተያያዘ ሲሆን አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ በቀረበው ክስ አንደኛ ተጠሪ የተለያዩ ኤሌትሮኒክስ ዕቃዎችን በሕጋዊ መንገድ ወደ አገር ውስጥ አስገብተው በወኪል ደንበኛቸው ሁለተኛ ተከሣሽ አማካይነት ዲክለራሲዮን በመሙላት ቀረጥና ታክስ ለመክፈል ከሚያስፈልጉ ሠነዶች ጋር በማቅረብ የዕቃዎቹ ዝርዝር ዋጋቸው በዳታ ቤዝ ሲፈለግ 23 የሚሆኑት ዕቃዎች ዋጋቸው ባለመገኘቱ ትክክለኛ ዋጋቸው ከዋናው መ/ቤት እስከሚላክልን ድረስ ዕቃው እንዳይቆይ ዋጋው በኘሮፖርሽን ተሰልቶ ብር 285,259.85(ሁለት መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ብር ከሰማንያ አምስት ሣንቲም) ከፍለው ንብረቱን ተረክበው ወስደዋል፡፡

ሆኖም የእነዚህ 23 ዕቃዎች ዋጋቸው ከዋናው መ/ቤት ተገልጾልን በዚሁ መሠረት ቀረጥና ታክስ ሲሰራ መክፈል የነበረበት ብር 47,638.34 ሳይከፈል የቀረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ቀረጥና ታክስ በማንኛውም ምክንያት ከዋጋቸው በታች የተከፈለ መሆኑ በምርመራ የተደረሰበት ከሆነ ያልተከፈለውን ቀሪ ቀረጥ ወይም ታክስ የማስከፈል ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 60/89 በአንቀጽ 57/1/ መሠረት ለከሣሽ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ በዚሁ መሠረት ተከሣሾች በቀሪነት የሚፈለገውን ክስ የቀረበበትን ብር 47,638.34(አርባ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሣ ስምንት ብር ከሰላሳ አራት ሣንቲም) ከነወለድ እንዲከፍሉ እንዲወሰንባቸው በማለት ጠይቀዋል፡፡

አንደኛ ተጠሪም ቀርበው በሰጡት መልስ ተከሣሽ አሟልቶ ማቅረብ የሚገባውን ሠነዶች በሙሉ ለከሣሽ አቅርቦ ከሣሽም ሂሳቡን አሰልቶ የሸቀጡን ዋጋ ትክክለኛነት አረጋግጦ ቀረጡን የተቀበለ ስለሆነ በቀረጥ ሰብሳቢው ታምኖበት ቀረጥ ተከፍሎ ዕቃው ከወጣ በኋላ ቀሪ ሂሳብ ለመጠየቅ ከሣሽ መብት የለውም፡፡ ከሣሽ በክሱ ኘሮፖርሽን ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ በምን ሂሳብ ስሌት እንደተሰላ እና የዕቃዎቹን ዋጋ ግኝት ምንጩን በመጥቀስ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 48 መሠረት ወደ አገር ስለሚገባ ዕቃ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ በዝርዝር አላስረዳም፡፡ ስለሆነም ከሣሽ በክሱ በሕጉ መሠረት እንዴት ተመርምሮ ቀሪ ሂሳብ እንደተገኘ በአዋጅ መሠረት ያላስረዳ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ሁለተኛ ተከሣሽም የቀረበልኝ ዶክመንት ትክክል መሆኑን አረጋግጪ ለከሣሽ መ/ቤት በማቅረብ በየደረጃው ያሉ የጉምሩክ ሠራተኞች አይተው የዋጋ ማስተካከያ ካደረጉ በኋላ የቀረጡን ትክክለኛነት አምነውበት በፊርማቸው ካረጋገጡ በኃላ ክፍያው የተፈጸመ ስለሆነ ክሱ ያላአግባብ የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ጉዳዮን ከሣሽ ቀሪ የቀረጥ ክፍያ ጥያቄው እንዴት እንደተገኘ እንዲያስረዳ በታዘዘው መሠረት የከሣሽ መ/ቤት የታሪፍና ትመና መምሪያ ክፍል ሠራተኛ ቀርበው ሲያስረዱ አንደኛ ተከሣሽ ያስገቡት ዕቃ የዋጋ ስጋት ካለባቸው አገር የመጡ በመሆኑ በጉምሩክ መመሪያ ቁጥር 3/1996 አንቀጽ 8 ከተራ ቁጥር 1-3 በተመለከተው መሠረት ቀረጡ በፕሮፖርሽን የተሰራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ሆኖም ግን ፍ/ቤቱ የተባለውን መመሪያ አስቀርቦ እንደተመለከተው መመሪያው የወጣው ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎች ለሌላ ወገን በሚተላለፋበት ጊዜ የእርጅና ቅናሽ ስለሚታሰብበት ሁኔታ ሲሆን የመመሪያው አንቀጽ 8 ቀረጥ በፕሮፖርሽን እንደሚለካ የማይደነግግ በመሆኑ የከሣሽ ክርክርም ሆነ የምስክርነት ቃሉ ተቀባይነት የለውም ካለ በኃላ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 48/1/ መሠረት ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ዕቃ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ሆኖ የሚወሰደው ለዕቃው መግዣ፣ዕቃውን እስከ ኢትዮጰያ የመጀመሪያ የጉምሩክ ወደብ ድረስ ለማጓጓዝ እንደዚሁም ለመድን ዋስትና አረቦን የወጣው ወጭ ድምር እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን ነገር ግን እነዚህ በአስመጪው በኩል የሚቀርቡት ሠነዶች ተቀባይነት የላቸውም ተብሎ በጉምሩክ ባለሥልጣን ከተወሰነ ቀረጡ ሊለካ የሚገባው በአንቀጽ 48/3/ እስከ 10 ድረስ በተመለከተው አኳኃን መሆን እንዳለበት ተመልክቶአል፡፡ ሆኖም አንደኛ ተከሣሽ ከውጭ አገር ያስገባው ዕቃ ዋጋ ተቀባይነት የለውም፡፡ ተብሎ ቀሪ ቀረጥ እንዲከፍል የተጠየቀበት አግባብ በአንቀጽ 48 ላይ በዝርዝር በተደነገገው መሠረት ስለመሆኑ የባለሙያ ማስረጃ በማቅረብ ከሣሽ ያላስረዱ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ከሣሽ በውሣኔው ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 337 መሠረት ይግባኙ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ ተጠሪዎች ተጨማሪ ቀረጡን ሊከፍሉ አይገባም ተብሎ ውሣኔ መሰጠቱ ከሕጉ አኳያ ተገቢነቱ ተመርምሮ ሊወሰን እንደሚገባው በመታመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የአመልካች የቀሪ የቀረጥ ክፍያ ጥያቄ አግባብነት ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ወደ አገር የሚገባ ዕቃ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ምን ያህል እንደሆነና እንዴት እንደሚሰራ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 48 ሥር ተዘርዝሯል፡፡ በሌላ በኩልም ወደ ሃገር በገባ ወይም ከሀገር በወጣ ዕቃ ላይ የተከፈለው ቀረጥ በማናቸውም ምክንያት ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥ ያነሰ መሆኑ በምርመራ የተደረሰበት እንደሆነ ባለሥልጣኑ የዕቃውን ባለቤት ወይም ወኪሉን በልዩነት ያልተከፈለውን ቀረጥ ማስከፈል እንደሚችል በአንቀጽ 57/1/ ላይ ሥልጣን ተሠጥቶታል፡፡

አመልካች በቀሪነት የሚፈለግ የቀረጥ ክፍያ ስላለ ተጠሪዎች ይህንኑ ቀሪ ክፍያ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ክሱ የተመሠረተው ተጠሪዎች ያስገቡት ዕቃ ኢንቮይሳቸው ዋጋው በመ/ቤቱ ከሚገኘው ዳታ ቤዛችን ጋር ሲወዳደር አንሶ በመገኘቱ ውድቅ ተደርጎ በዳታ ቤዙ መሠረት ዋጋ ሲፈለግ የተወሰኑት ዕቃዎች ዋጋቸው ስላልተገኘ በተገኙትና ባልተገኙት መካከል ያለውን ልዩነት የመ/ቤቱ መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት በፕሮፖርሽን ተሰርቶ ቀረጡን እንዲከፍሉ ከተደረገ በኃላ ዝራዝራቸው በዳታ ቤዝ ያልተገኙ ዕቃዎች ዋጋቸው ከዋናው መ/ቤት ሲላክልን በልዩነት የሚፈለግ ቀሪ የቀረጥ ክፍያ መኖሩን አረጋግጠናል በሚል ነው፡፡

ተጠሪዎችም አመልካች በፕሮፖርሽን ቀረጥ ለማስከፈል የሚያስችል የሕግ ድጋፍ የለውም ተገቢ ሰነዶችንም አቅርበን ቀረጡ የተከፈለ ስለሆነ ቀሪ ክፍያ አለ ተብሎ የቀረበው ክስ የሕግ መሠረት የለውም በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡

ሆኖም ግን የአመልካች መ/ቤት የዋጋ ዝርዝራቸውን በዳታ ቤዝ በተገኘውና ባልተገኘው መካከል ልዩነቱን በኘሮፖርሽን ስሌት መሠረት እንደሚያስከፍል ለተጠሪዎች ሲገልጽ ተጠሪዎች ተቀብለው ቀረጡን ከፍለዋል፡፡ አመልካች ቀረጡን የማስከፍላችሁ በኘሮፖርሽን ስሌት ነው ካለ በሌላ አገላለጽ የተጠሪዎችን ኢንቮይስ ውድቅ ማደረጉን የሚያመለክት ስለሆነ በአዋጁ አንቀጽ 53/1/ በተቀመጠው አግባብ መሠረት ተቃውሚቸውን አስመዝግበው የጉምሩክ ሹሙ በሚወሰነው መሠረት ቀረጥ መክፈል ይገባቸው የነበረ ሲሆን በዚህ መልኩ ተቃውሞ ካላደረጉ በኘሮፖርሽን ስሌት የተጠየቀውን የቀሪ ቀረጥ ክፍያ ጥያቄ እንደተቀበሉት የሚቆጠር ነው፡፡

ስለሆነም አመልካች ክስ የመሠረተበትን የቀረጥ ክፍያ ጥያቄ በተጠሪዎች በኩል በሕጉ አንቀጽ 53 አግባብ ተቃውሞ ያልቀረበበት እንደመሆኑ መጠን የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪዎች ተቃውሞ ባላቀረቡበት ሁኔታ አመልካች በኘሮፖርሽን ቀረጥ ለማስከፈል የሚችልበትን አግባብ አላስረዳም በማለት የክፍያ ጥያቄውን ሳይቀበለው መቅረቱ ከአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 57 እና 53/1/ አኳያ ተገቢነት የሌለውና የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 68030 ሕዳር 19 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 76136 መጋቢት 2 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች አመልካች ክሰ ያቀረበበትን ብር 47,638.24/አርባ ሰባት ሺ ስድስት መቶ ሠላሳ ስምንት ብር ከሀያ አራት / ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሠብ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ሽ

የሰ/መ/ቁ. 44862

ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- አሸናፊ አበበ - ጠበቃ ኒቆዲሞስ ጌታሁን ቀረበ

**ተጠሪ**፡- የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ - ታደለ ተስፋዬ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የጉምሩክን ሕግ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሞአል በማለት ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበውን ክስ መነሻ በማድረግ የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ አመልካች እና በወቅቱ ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው ታደለ ገብሬ ኪዳኔ የተባለው ግለሰብ የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሰራርን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 228 እና 66/2/ ላይ የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የጉምሩክ ሥነ-ሥርአት ያልተፈጸመባቸውን አልባሳት ይዘው የማስተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋልና ቅጣት ይወሰንባቸው በማለት ጠይቆአል፡፡

ተከሣሾቹ ለክሱ በሰጡት መልስ በክሱ የተነገረውን ድርጊት አልፈጸምንም፤ ጥፋተኛም አይደለንም በማለት በመከራከራቸው ፍ/ቤቱ በዓቃቤ ሕጉ የቀረቡትን ማስረጃዎች ከሰማ በኂላ ተከሣሾች ሊከላከሉ ይገባል በማለት ብይን ሰጥቶአል፡፡ በዚህ መሰረትም የመከላከያ ማስረጃዎች የሰማ ሲሆን፣በመጨረሻም ተከሣሾች እንደክሱ አቀራረብ ተመስክሮባቸዋል፡፡ ለማስተባበልም አልቻሉም በማለት በተጠቀሰባቸው ሕግ መሰረት ጥፋተኞች ናቸው ብሎአቸዋል፡፡ ሲያስተላልፉት የተገኘው አልባሳት እንዲወረስ፣ለአልባሳቱ ሊከፈል ይገባ የነበረው የቀረጥና ታክስ መጠን በሚያህል ገንዘብ ብር 10,520.33(አስር ሺህ አምስት መቶ ሃያ ብር ከሠላሣ ሦሥት ሣንቲም) ለመንግስት እንዲከፍሉ እና በአስራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኖባቸዋል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን የሰማ ሲሆን፣በመቀጠልም ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች መጋቢት 28 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ለተፈጸመው ድርጊት በአቃቤ ሕግ የተጠቀሰው የአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 66/2/ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ዓቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ የጠቀሰው ድንጋጌ አግባብነትን ለመመርመር የክስ ቻርጁን ይዘት ማየት አስፈላጊ በመሆኑ ተመልክተነዋል፡፡ በቻርጁ ላይ የተገለጸው አመልካች አልባሳቱ ተጭነው የተገኙበትን መኪና

ሲያሽከረክር እንደነበር፣አብሮ የተከሰሰው ታደለ ገብሬ ኪዳኔ የተባለው ደግሞ አልባሳቱን ያስጫነ እንደሆነ፣ መኪናው የመጣው ከናዝሬት መስመር ወደ አዲስ አበባ ሲሆን፣አመልካች አቃቂ የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ኬላ ላይ እንደደረሰ የጉምሩክ ሰራተኞች ለፍተሻ እንዲቆም ሲጠይቁት ኬላውን ጥሶ መሄዱን፣በኋላም በተደረገው ክትትል በተለምዶ ሃና ማሪያም አካባቢ ተይዞ ፍተሻ ሲደረግ አልባሳቱ መገኘታቸውን ነው፡፡ ዓቃቤ ሕግ ባቀረባቸው ማስረጃዎች ልክ እንደ ክሱ እንዳስረዳ አቤቱታ በቀረበበት ውሳኔ ተመልክቶአል፡፡ በክሱ የተጠቀሰው የጉምሩክ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 66/2/ የኮንትሮባንዱ ድርጊት/ጥፋት/ የተፈጸመው ሃይል በመጠቀም ወይም ከሌሎች ጋር በማበር ሆኖ በተገኘ ጊዜ የሚጠቀስ እንደሆነም ከድንጋጌው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በመሆኑም መጠቀሱ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ አቤቱታ በቀረበበት ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 136351 ጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 76902 መጋቢት 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕግ ሥ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው የሰበር ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 48693

ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-**ነኢማ አወል

**ተጠሪ፡-** የገቢዎች እና ጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ ኃ/ስላሴ ገ/መድህን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መሰረት የሆነው ጉዳይ የጉምሩክ አዋጅ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽማለች በማለት ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሰረተውን የወንጀል ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች የተከሰሰችው በጉምሩክ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 66/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ከዱባይ ወደ ኢትዮጵያ በቦሌ አለም አቀፍ አየር ማረፊያ ስትገባ የጉምሩክ ሥነ-ሥርአት ያልተፈጸመባቸው የተለያዩ የሞባይል መለዋወጫዎችን እና የተዘጋጁ አልባሳቶችን ይዛ ተገኝታለች ተብላ ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠችው መልስ በአቃቤ ሕግ ክስ የተነገረውን ወንጀል አልፈጸምኩም በማለት በመከራከርዋ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎች ሰምቶአል፡፡ ከዚህ በኋላም አመልካች ልትከላከል ይገባል በማለት ብይን በመስጠት የመከላከያ ማስረጃዋን ሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች ጥፋተኛ መሆንዋን በማረጋገጡ ይዛው የተገኘችው እቃ እንዲወረስ፣በእቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በሚያህል የገንዘብ መቀጮ ብር 114,076.46(አንድ መቶ አስራ አራት ሺህ ሰባ ስድስት ብር ከአርባ ስድስት ሳንቲም) እንድትከፍል እና በሁለት ዓመት እስራት እንድትቀጣ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ነሐሴ 26 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች የተከሰሰችበት የወንጀል ድርጊት መታየት ያለበት በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሰረት ነው ወይንስ በጉምሩክ አዋጅ ቁ. 60/89? የሚለውን ጭብጥ ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ፣እንደዚሁም የሰበር ችሎቱ በሰበር መ/ቁ. 42753 እና 43806 ከሰጣቸው ውሳኔዎች ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው የሥር ፍ/ቤቶች ክርክሩን የሰሙትና በመጨረሻም ውሳኔ የሰጡት የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/89 በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡ የሰበር ችሎቱ ከፍ ሲል በተጠቀሱት መዝገቦች ተመሣሣይ አቤቱታ ቀርቦለት በእርግጥም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የጉምሩክ አዋጅ አንደሆነ በመግለጽ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ በዚህም ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት ያለው አዲሱ የወንጀል ሕግ ነው በሚል የቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርጐአል፡፡ በያዝነው ጉዳይም ይኸው ቀደም ሲል የተሰጠው የሕግ ትርጉም አስገዳጅነት ያለው ስለሆነ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልቻልንም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 139937 መጋቢት 21 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 79028 ነሐሴ 2 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 195/2/ለ(2) መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. አመልካች ያቀረበችው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 54061

ሚያዝያ 26 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገብረሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ መስፍን ሽፈራው

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎች ባለሥልጣን - ገብረእግዚአብሔር ሙናቸው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት መጋቢት 13 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች የዘሸ ትሬዲንግ ሥራ አስኪያጅ መሆናቸውን ገልፆ ድርጅቱ ሚያዝያ 8 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ አራት ሠዓት ከአርባ ደቂቃ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ፈፅሟል፡፡ ስለዚህ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 56(1) መሠረት የወንጀል ተጠያቂነት አለበት በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክረዋል ድርጅቱ ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱን ዐቃቤ ህግ ገልጿል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ሥራውን በውክልና ለወ/ሮ ድርሻዬ ከበደ ለተባለች ሠራተኛ በውክልና ሰጥቻለሁ የሚል ክርክር ያቀረቡ ሲሆን የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመዘነ በኋላ አመልካች ለሥራው ሙሉ ውክልና አልሰጠም፡፡ የቃል ማስጠንቀቂያ ከመስጠት ውጭ የዘረጋው ሥርዓት የለም በማለት በክሱ በተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ ጥፋተኛ ብሎ በአንድ ዓመት ከስድስት ወር እሥራትና በብር 20,000(ሀያ ሺህ ብር) እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች በውሣኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ትክክለኛ ፍትህ ይረዳሉ የተባሉ የማጣሪያ ምስክሮች በመስማት የሥር ፍርድ ቤት

የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች የሥር ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የድርጅቱ ሠራተኛ ወ/ሮ ድርሻዬ ከበደ ሥራውን ወክያት እየሠራች የነበረ ሲሆን በዚሁ ጉዳይ ጥፋተኛ ተብላ ተቀጥታለች፣ ወንጀሉ ሲፈፀም እኔ በቦታው አልነበርኩም፣ ግብይቱ የተፈፀመው ያለ እኔ ፈቃድና ስምምነት ነው፣ ከድርጅቱ ሠራተኞች ያለቫት ደረሰኝ ግብይት እንዳይፈፅሙ ማስጠንቀቂያ ሰጥቻለሁ፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 34 እና የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 56(1) የማይጣጣሙ በመሆኑ ተከሳሹን በሚጠቅም መንገድ መተርጎም አለባቸው፡፡ ቅጣቱ ውሣኔም ተገቢ አይደለም መገደብ ነበረበት በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የሚመራው ድርጅት በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ተቀጥቷል ስለዚህ አመልካችን ተጠያቂ ለማድረግ ሌላ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ የለብንም አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት ተገቢውን ቁጥጥር ባለማድረግና ሥርዓት ባለመዘርጋታቸው ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ተገቢውን ማጣራት አድርጎ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 56(1) እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀፅ 3 መካከል የሀሳብ አለመጣጣም አለ በማለት ያቀረበው ክርክር በወንጀል ህጉ አንቀፅ 3 የተደነገገውን ከግንዛቤ የማያስገባና የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ አመልካች በሥራ አስኪያጅነት የሚመሩት የንግድ ድርጅት የአመልካች ሠራተኛ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት በመፈፀም ወንጀል ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ በመርህ ደረጃ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 56(1) ጥፋተኛ የሚባሉ መሆኑ በህጉ ተደንግጓል፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 56 ንዑስ አንቀፅ 3 የተመለከቱትን ልዩ ሁኔታዎች በማስረዳት ከተጠያቂነት ነፃ ለመሆን የመከላከያ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡ ሆኖም አመልካች ለድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ያልቀጠሩና ያልወከሉ መሆኑና የአስተዳደር ሥራዎን ብቻ ለወ/ሮ ድርሻዬ ከበደ የወከሉ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ለሠራተኞቹ የቃል ማስጠንቀቂያ የሰጠ መሆኑን ያስመሠከረ ቢሆንም አመልካች የቃል ማስጠንቀቂያ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 56 ንዑስ አንቀፅ 3(ለ) በተደነገገው መሠረት ማንኛውም በጎ አሳቢ ሰው ሊያደርገው የሚችለውን ጥንቃቄ ያደረገና ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ ድርጅቱን በመምራት ኃላፊነቱን የተወጣ መሆኑን የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላላገኘነው በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 2(ለ)(2) መሠረት አፅንተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፍርድ ፀንቷል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 49889

ሰኔ 28 ቀን 2002 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት - የቀረበ የለም፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ዛኪ ሰይድ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሕጉ በተሰጠው ስልጣን ተግባሩን በሚፈጽምበት ጊዜ ለሚደርሰው የገቢ መቋረጥና የንብረት ጉዳት ያለውን ኃላፊነት ስለሚገዛ የሕግ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበሩት ያሁኑ ተጠሪ ሲሆን ተከሣሽ የአሁኑ አመልካች ነበር፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘት ባጭሩ፡- ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነ ቁጥሩ 3-24062 ኢት መኪና አመልካች ከሕግ ውጪ በማቆሙ በፍርድ ቤት ውሣኔ የተሰጠ ቢሆንም መኪናው በቆመበት ጊዜ ተጠሪ በአጠቃላይ ብር 216,250.00 /ሁለት መቶ አስራ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሣ ብር/ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ገልጸው ይህንኑ ገንዘብና መኪናውን እስኪረከቡ ድረስ ያለውን ገቢ ከመጠየቅ መብታቸው ጋር አመልካች እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያነት የቀረበው ክርክር ቀድሞ ተጠሪ ክስ አቅርበው ባለቀ ጉዳይ ላይ ድጋሚ ክስ ማቅረብ የማይችሉ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ አመልካች መኪናውን ይዞ ሊያቆም የቻለው መኪናው ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ እቃ ጭኖ ወደ ውጪ ሊወጣ ሲል በመሆኑና ይህን ዓይነት ተግባር ደግሞ አመልካች ለመቆጣጠር ተገቢ ነው ያለውን እርምጃ ለመውሰድ በሕጉ ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝም፣ መኪናው መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. በቁጥጥር ሥር ከዋለ በኋላም በዚሁ ጊዜ ለፍርድ ቤት ያሳወቀ በመሆኑ ጥፋት የለብኝም ብሎ መከራከሩን የሚገልጽ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበውን ክርክር የተጠሪ የቀድሞ ክስና የበኋለኛው ክስ ፍሬ ነገር ተመሣሣይ ባለመሆኑ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት አይቻልም በሚል ምክንያት ውድቅ አድርጎ የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር አመልካች የተጠሪ መኪናውን ያላግባብ በማቆም ገቢ እንዲያጡ አድርጓል፤ በመኪናው ሸራ እና ባትሪ ላይም ጉዳት

ማድረሱን አላስተባበለም በማለት ብር 52,019.40 /ሃምሳ ሁለት ሺህ አስራ ዘጠኝ ብር ከአርባ ሳንቲም/ አመልካች ለተጠሪ ይክፈለው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥቅምት 18 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ከአዋጅ ቁጥር 60/1989 አንቀጽ 58/ለ/ አንፃር /በሰ/መ/ቁጥር 22317 ከተሰጠው ትርጉም/ ሲታይ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ የካቲት 04 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ ሦስት ገጽ ማመልከቻ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሣኔ ተገቢ ነው የሚሉበትን ምክንያት ገልጸው ውሣኔው ሊጸና ይገባል ሲሉ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ ማንም ሰው በራሱ ጥፋት ወይም በሌሎች ሰዎች ጥፋት የተነሳ በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ካደረሰ ከውል ውጪ ኃላፊነት የሚከተልበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2027/1/ እና /3/ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ ጥፋት ደግሞ ታስቦ ወይም በቸልተኝነት ሊፈፀም እንደሚችል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2028/1/ ድንጋጌ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ የጥፋት ትርጉም ደግሞ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2028 እስከ 2037 ሥር የተመለከተ ሲሆን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2038 እስከ 2065 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች የተፈፀመው ተግባር ጥፋት መሆን አለመሆኑን የሚገዙ ናቸው፡፡ አመልካች ለተጠሪ ክስ ኃላፊነት አለበት የተባለው ከውል ውጪ ኃላፊነትን የሚገዙት የሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ያሳያል፡፡ አመልካች ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ተገቢነት የለውም በማለት የሚከራከረው በአዋጅ ቁጥር 60/1989 ከተሰጠው ኃላፊነት እና ተግባር አንፃር ነው፡፡ በዚህ አዋጅ አመልካች በጉምሩክ ወደቦች በወሰን አከባቢዎች እንዲሁም በሌሎች የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችና ማቋረጫ መስመሮች በኩል የሚገቡና የሚወጡ ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመፈተሽ፣ የጉምሩክ ስነ ሥርዓት ተፈጽሞባቸው መግባታቸውንና መውታቸውን የማረጋገጥ ስልጣንና ተግባር ተሰጥቷል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 74 በተለይ ሲታይ አመልካች የሕገ ወጥ እቃዎችን ዝውውር የመቆጣጠር ኃላፊነትና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 6/5/ እና 58 ስርም ይኸው ተግባር የአመልካች ሕጋዊ ግዴታ ስለመሆኑም የሚያስገነዝብ የሕጉ አቀራረጽ ይታያል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 25 ድንጋጌ ያሻሻለው የአዋጅ ቁጥር 368/1995 አንቀጽ 78 ድንጋጌም አመልካች ኮንትሮባንድ ወይንም ሕገ-ወጥ እቃ ጭኗል ብሎ ያመነበትን ተሽከርካሪ በቁጥጥር ሥር ማዋል እንደሚቻል በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ይህንኑ በሕጉ ተለይቶ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በተገቢው መንገድና በተገቢው ጊዜ ያከናውናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ አመልካች ይህንኑ ስልጣንና ተግባሩን በተገቢው ጊዜና ሁኔታ ባለማከናወን በሌላ ሰው ንብረት ላይ በሚያደርሰው ጉዳት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2027/1/ እና /3/ ድንጋጌዎችና አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች የማይጠየቅበት ወይም ኃላፊ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በሕጉ ተለይቶ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር ያላግባብ ባለመወጣቱ በሰው ንብረት ላይ ጉዳት ማድረሱ ከተረጋገጠ ካሳ የማይከፍልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በዚህም መሠረት በአመልካች ተገቢ ያልሆነ ተግባር ጉዳት ደርሶብኛል የሚል ሰው የአመልካች ተግባር በሕጉ ከተሰጠው ኃላፊነትና ተግባር የሚፃረር ወይም በምክንያታዊ መንገድ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ማስረዳት ከቻለ በአመልካች ሊካስ የሚገባው መሆኑን ይህ ችሎት ያምናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የተጠረጠረውን ማንኛውንም ዕቃ ይዞ የመፈተሽና እቃውን የጫነውን ተሽከርካሪም ይዞ የማቆየት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶችም የተቀበሉት ጉዳይ ሲሆን ፍርድ ቤቶቹ የአመልካችን ተግባር ኃላፊነትን የሚያስከትል ነው ለማለት የቻሉት የተጠረጠረውን መኪና ለአንድ መቶ አስራ ሰባት ቀናት ያሕል መያዙ ተገቢነት የለውም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ይህን የሚያሕል ጊዜ መኪናው ተይዞ እንዲቆይ ያደረገው የወንጀሉ ጉዳይ በፍርድ ቤት ተይዞ እየታየ ባለበት ጊዜ ሲሆን በፍርድ ቤት

ውሣኔም መኪናውን እንዲለቅ መወሰኑ የክርክሩ ሂደት ያስገነዝባል፡፡ አመልካች ከዚህ ጊዜ ውጪ መኪናው ያላግባብ የተያዘ ስለመሆኑ ለማስረዳት ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ የወንጀል ጉዳይ ሲታይ በነበረበት ጊዜ ደግሞ ጉዳዩ የኮንትሮባንድ አይደለም ተብሎ ስለተወሰነ ብቻ በአመልካች ላይ የፍትሐብሔር ተጠያቂነት ሙሉ በሙሉ ያስከትላል ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ አመልካች በሕጉ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ባግባቡ ለመወጣት እንዲቻል መኪናውን ይዞ ማቆሙ ተገቢ ሲሆን በዚህ ጊዜ ለታጣ ገቢ ደግሞ የሚጠየቅበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 22317 በቀረበው ተመሣሣይ ጉዳይ አግባብነት ያላቸውን የአዋጅ ቁጥር 60/1989 ድንጋጌዎችን በመመርመር በአዋጅ ቁጥር 454/1997 መሠረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ አመልካች መኪናውን ይዞ ጉዳዩ በወንጀል ችሎት እየታየ መቆየቱን ከክርክሩ መገንዘብ የምንችለውና በዚህ ሂደት የባከነው ጊዜ ከነባራዊው ዓለም አንፃር ሲታይ ምክንያታዊ ነው ከሚባል በስተቀር ያላግባብ የዘገየ ነው ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 69/1989 አንቀጽ 6/5/፣ 58፣ 74 ድንጋጌዎች እና ከአዋጅ ቁጥር 368/1995 አንቀጽ 78 ድንጋጌ አንፃር ሲታይ መኪናውን ማቆሙ በሕጉ መሠረት የተሰጠውን ስልጣን በሕጉ አግባብ ለመወጣት እንዲያስችለው የወሰደው እርምጃ ያላግባብ ያልተከናወነ እና በተገቢው ጊዜ ውስጥ የተፈጸመ ነው ከሚባል በስተቀር በውሉ ውጪ ኃላፊነትን የሚያስከትል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ምክንያት በዚህ ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው በታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ አመልካች በተጠሪ መኪና ባትሪና ሸራ ላይ ጉዳት አድርሷል ተብሎ ግምቱን እንዲከፍል ነው፡፡ አመልካች በዚህ ረገድ የተሰጠውን የበታች ፍርድ ቤቶችን ሕጋዊ መሠረት የለም በማለት በዚህ ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በግልጽ ያልተከራከረበት ሲሆን በሥር ፍርድ ቤት በቀረበው ክርክርም ቢሆን በመኪናው ባትሪና ሸራ ላይ መኪናው በአመልካች ቁጥጥር ሥር ውጪ በነበረበት የደረሰ ወይም በራሱ ቁጥጥር ሥር ውስጥ እያለ በሌላ ምክንያት የደረሰ ነው የሚል ክርክርም አላቀረበም፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ንብረቶች ጉዳት የደረሰ ስለመሆኑ ማስረጃን የማጣራትና የመመዘን ስልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ ሲሆን አመልካች ጉዳቱ በሌላ ምክንያት የደረሰ ስለመሆኑ የሚያሳይ ክርክርና ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ በመሆኑም አመልካች በኮንትሮባንድ ድርጊት /ሥራ/ ተሰማርቶ የተገኘን ተሽከርካሪ ለጊዜው ማቆም የሚችል መሆኑን ሕጉ ስልጣን ቢሰጠውም ንብረቱን ግን ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡ መኪናው በራሱ ቁጥጥር ስር በነበረበት ጊዜ ለሚደርሰው የመኪናው አካል ጉድለት ጉድለቱ በሌላ ሕጋዊ ምክንያት የደረሰ ስለመሆኑ እስካላስረዳ ድረስ ኃላፊነቱ የአመልካች የማይሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በአጠቃላይ ከፍ ብለው በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ሊሻሻል የሚገባው በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## **<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በቦረና ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04134 ሐምሌ 10 ቀን 2001 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 72896 ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የተጠረጠረውን ዕቃ ይዞ የመቆየት ሥልጣንና ተግባር በአዋጅ ቁጥር 69/1989 አንቀጽ 6/5/፣ 58/1/ለ/ እና 74 እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 368/1995 አንቀጽ 78 መሠረት ያለው በመሆኑና ጊዜውም ምክንያታዊነት የሌለው ነው ለማለት የሚቻል ባለመሆኑ መኪናው በቆመበት ጊዜ ለታጣ ገቢ ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
3. አመልካች መኪናውን ይዞ ባለበት ጊዜ ለደረሰው የመኪና ባትሪ እና ሸራ ጉዳት ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ የሁለት ባትሪ ዋጋ ብር 4,500.00 /አራት ሺህ አምስት መቶ/ እና የሸራ ዋጋ ብር 7000.00 /ሰባት ሺህ/ በድምሩ ብር 11,500.00 /አስራ አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ ለተጠሪ እንዲከፍል ብለናል፡፡ በዚህ መሠረት ያስፈጽም ዘንድ የዚህ ችሎት ውሣኔ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ ብለናል፡፡
4. ለክርክሩ የወጣን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## **<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>**

- በዚህ ችሎት ጥቅምት 19 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፤ ይፃፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 48621

ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሓጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ አብደላ ሁሴን ከለር ላብራቶሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ አቶ ሣሙኤል ኤፍሬም - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን - ዓቃቤ ሕግ ግርማ ወልደማሪያም -ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፣የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሰጠው የገቢ ግብር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ማስታወቂያ ባለመስማማት ይግባኝ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ለማቅረብ በሕጉ መሰረት ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ በወቅቱ አስይዘዋል ወይስ አላስያዙም የሚለው ነጥብ ነው፡፡

አመልካች የገቢ ግብር ማስታወቂያና የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ማስታወቂያ ከደረሳቸው በኋላ በሰላሣኛው ቀን ማለትም ሰኔ 8 ቀን 1999 ዓ.ም ለሁለቱም ግብሮች CPO በማሰራት ከተጠሪ ቢሮ ድረስ መሄዳቸው ለገቢ ግብር ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ 8/10/99 አስይዘው የጨረሱ መሆኑንና ለተጨማሪ እሴት ታክስ ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ ሰኔ 8 ቀን 1999 ዓ.ም ለማስያዝ ከተጠሪ ቢሮ አስራ አንድ ሰዓት በኋላ ያቀረቡ ቢሆንም ሰራተኞችና የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ወጥተው ስለነበር ሣያስይዙ ተመልሰው ተከታዮቹ ቀናት የቅዳሜና እሁድ ስለነበሩ 11/10/99 ገንዘቡን የማስያዝ ሂደቱን አጠናቅቀው ይግባኙ እንዲታይላቸው ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አቅርበዋል፡፡ የግብር ይግባኝ ሰሚ ይግባኙ የቀረበው በአዋጅ ቁጥር

285/94 አንቀጽ 43 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት በሠላሣ ቀን ውስጥ መያዝ ያለበት ገንዘብ ተይዞ ባለመሆኑና ጊዜው ካለፈ በኋላ ያቀረበ በመሆኑ ይግባኙ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው አልፏል ወይስ አላለፈም የሚለው ክርክር የፍሬ ጉዳይ ክርክር እንጅ የሕግ ነጥብ ባመለሆኑ ይግባኙን አልተቀበልኩትም በማለት ይግባኙን ውድቅ አድርጐታል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት ይግባኝ አቅርበው ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች የገቢ ግብር ማስታወቂያ ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ ያለብንን CPO እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ ያለብንን ገንዘብ በCPO አሰርተን ተጠሪ መሥሪያ ቤት የቀረብነው 8/10/99 ነው፡፡ የገቢ ግብሩን ተቀብሎ ደረሰኝ ሲሰጠን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመክፈል ያቀረብነውን CPO በተመለከተ ኮንፒውተር ብለሽት አጋጥሞታል በሚልና በሌሎች ምክንያቶች ደረሰኝ ሣይሰጠን ተመልሰናል፤እለቱ አርብ ስለነበር ቅዳሜና እሁድ ቆይተን ሰኞ 11/10/99 ደረሰኝ ተቆርጦ የተሰጠን ሲሆን ለክፍያ ያቀረብነው 8/10/99 መሆኑን በደብዳቤ ገልፆ ጽፎልናል፡፡ የተጠሪ ምስክሮችም ይህንን አስረድተዋል፡፡ በግብር ተቀባዩ መሥሪያ ቤት (ተጠሪ)ለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ደረሰኝ ሣናገኝ 8/10/99 መመለሳችንና ደረሰኙ 11/10/99 ተቆርጦ የተሰጠን መሆኑ በእኛ ቸልተኝነት ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው እንዳለፈ የሚያስቆጥር አይደለም፡፡ ይህ የሕግ ትርጉም የሚጠይቅ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ እያለ የፍሬ ጉዳይ ክርክር ነው ተብሎ መታለፉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ለተጨማሪ እሴት ታክሱ ደረሰኝ የተሰራላቸው 11/10/99 መሆኑን አመልካች አምነዋል፡፡ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ጊዜው አልፏል ወይስ አላለፈም የሚለውን አጣርቶ መያዣው በወቅቱ ያልተከፈለ መሆኑን በማረጋገጥ መያዣቸው ጊዜው ካለፈ በኋላ የተከፈለ መሆኑን አረጋግጦ የሰጠው ውሣኔ የፍሬ ጉዳይ ክርክር እንጅ የሕግ ክርክር ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የፈጸሙት የሕግ ስህተት የለም በማለት መልስ ሰጥቷል አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ ያለባቸውን ገንዘብ ያስያዙት መቼ ነው? ይግባኝ ለማቅረብ መያዝ የሚገባው ገንዘብ ጊዜው ከማለፉ በፊት በማስያዝ አመልካች ይግባኝ አቅርቧል ወይስ አላቀረበም የሚለው ነጥብ የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ በCPO ለማሰራት ከተጠሪ ቢሮ ሰላሣ ቀን ከማለፉ በፊት ቀርበው የገበሩ መሆኑና ተጠሪ የገቢ ግብር ይግባኝ ለማቅረብ በCPO ያቀረቡትን መያዣ ደረሰኝ ቆርጦ 8/10/99 ዓ.ም የሰጠ ሲሆን የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ በመያዣነት ያቀረቡትን CPO 8/10/99 ከተቀበለ በኋላ በተለያየ ምክንያት ደረሰኝ ቀርቦ መስጠት እንዳልቻለና ደረሰኙን 11/10/99 ዓ.ም ቆርጦ የሰጠ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡

እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ አመልካች ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ መያዣው በሚፈፀምበት ሥርአት በCPO አሰርተው ለተጠሪ ጊዜው ከማለፉ በፊት ማቅረባቸው ከተረጋገጠ CPO ለክፍያ ያቀረበውን ገንዘብ አወራርዶ ደረሰኝ ለመስጠት ተጠሪ በአጋጠመው የአሰራር ወይም ሌላ ችግር ምክንያት ቀናት ወይም ወራት ቢወስድበት ይግባኝ ባዩ ይግባኝ ለማለት መክፈል ያለበትን ገንዘብ በጊዜው አልከፈለም ሊባል ይገባዋል ወይ? የሚለው ነው፡፡ ይህ ጥያቄ ከሕጉ አጠቃላይ መንፈስና ዓላማና ሕግ አውጭ ሊያሣካው ከሚፈልገው ግብ አንፃር መመርመርና ውሣኔ ማግኘት አለበት፡፡ ሕግ አውጭው የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ የደረሳቸው ሰዎች የውሣኔ ማስታወቂያ በደረሳቸው በሰላሣ ቀን ውስጥ ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ 50% ለግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት በማስያዝ ይግባኝ ማቅረብ እንዳለባቸው በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 43/1/ ሲደነግግ ግብር ከፋዩ ለግብር አስገቢው መሥሪያ ቤት ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግ ለማስገደድ እንጅ ገንዘቡ ገቢ ሆኖ ግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ደረሰኝ ሣይሰጥ ቢቆይ ለመሥሪያ ቤቱ የአሰራር ድክመትና ችግር ምክንያት ግብር ከፋይ ይግባኝ የማቅረብ መብቱ እንዲጣበብ በማሰብ አይደለም፡፡ ስለዚህ አመልካች ተጠሪ ክፍያ በሚቀበልበት ሥርአት በማሟላት ማለትም በCPO መክፈል አለብህ ተብሎ የተወሰነበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ 50% የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ በደረሰው በሰላሣኛው ቀን ማለትም 8/10/99 ለተጠሪ ገቢ አድርጓል፡፡ የህም አመልካች ከላይ ከተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ የተወሰነው ጊዜ ከማለፉ በፊት ለተጠሪ ገቢ አድርገዋል፡፡ ተጠሪ ሰላሣ ቀኑ ከማለፉ

በፊት በCPO ገቢ ለሆነለት ገንዘብ ደረሰኝ ቆርጦ ያሰጠው ከሶስት ቀን በኋላ ማለትም 11/10/99 መሆኑ ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ ያለበትን ገንዘብ አመልካች ከሰላሣ ቀን በኋላ ነው ገቢ ያደረገው ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ በግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት በኩል ያሉ የአሰራር ችግሮችና ጉድለቶች መሰረታዊ የሆነውን የአመልካችን ይግባኝ የማቅረብ መብት በማያጣብብ ሁኔታ በመተርጐም የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠው ውሣኔ የሕጉን ድንጋጌ አተረጋጐምና ተፈፃሚነት የሚመለከት እንጅ የፍሬ ጉዳይ ክርክር አይደለም፡፡ በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ጉዳዩ የፍሬ ጉዳይ ክርክር ነው በማለት ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ለአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 43 ንኡስ አንቀጽ 1 የሰጠውን የተዛባ ውሣኔ ሣያርሙ ማለፋቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. አመልካች የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ከማለፉ በፊት የመያዣነት መከፈል የሚገባውን ገንዘብ ለተጠሪ ያስያዙ በመሆኑ የቀረበለትን ይግባኝ በመመርመርና የግራ ቀኙን ክርክር በማስማት ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት መልስን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

# ውክልና

የሰ/መ/ቁ. 48269

የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሸረፈዲን አብደላ - ጠበቃ አብዶ መሐመድ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ማርታ አሰፋ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በሐዋላ የተላከውን ገንዘብ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ናቸው፡፡ ተከሳሽ ደግሞ የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ የአመልካች የስር ክስ ይዘት ባጭሩ፡- አቶ አህመድ ኢሳ ኪይሮ የተባሉ ግለሰብ በተጠሪ ባንክ ሚዛን ተፈሪ ቅርንጫፍ ታህሣሥ 16 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. በ25/12/2006) በመቅረብ ብር 145,860.00(አንድ መቶ አርባ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ብር) ለአመልካች ገቢ በማድረግ ማስተላለፋቸውን፣አመልካች ይሕንን ገንዘብ ለማውጣት ገንዘቡን እንዲከፍል ለታዘዘው አየር ጤና ቅርንጫፍ ቢሄዱ ገንዘቡን ለሌላ ግለሰብ እንደከፈለ በመግለጽ ክፍያው ለአመልካች ሊፈፀምላቸው የማይችል መሆኑን የገለፀ መሆኑን በመግለጽ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ክፍያው ይፈፀም ይችል ከነበረበት ከጥር 01 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድና ከተለያዩ ወጪዎች እና ኪሳራዎች ጋር ተጠሪ እንዲከፍል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም አመልካች በገንዘቡ ላይ መብት ወይም ጥቅም ስለሌላቸው ክስ ለመመስረት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አለመኖሩን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ክፍያው ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግና የተለመደውን አሰራር በመከተል የፈፀሙ መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ክፍያውን የፈፀመው ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግና የተለመደውን አሰራር በመከተል በመሆኑ ለክሱ ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 12 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ ክፍያውን የፈፀመው ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግና የተለመደውን አሰራር በመከተል ነው ተብሎ ገንዘብ ላኪው ግለሰብ እንኳ ቀርቦ እንዲመሰክር ሳይደረግ ውሳኔ መሰጠቱ ያላግባብ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ተጠሪ ገንዘቡን እንዲከፍላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ተገቢውን ጥንቃቄ ወስዶ በሐዋላ የተላከውን ገንዘብ በመክፈሉ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ባግባቡ መሆኑ ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐ የተጠሪ ነገረ ፈጅ ጥር 07 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ ማመልከቻ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አመልካችም በ11/06/2002 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀ ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ለክሱ መሰረት ያደረጉት ምክንያት ገንዘቡ በስህተትና በሐሰት ለሌላ ሰው ተከፍሎብኛል የሚለውን መሆኑን፣ተጠሪም ገንዘቡ በላኪው ግለሰብ በተላለፈው መሰረት ገንዘቡ ለተላከለት ሰው ከፍያለሁ ብሎ የሚከራከር መሆኑን፣የስር ፍርድ ቤትም በተጠሪ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎችን በመመርመር ተጠሪ ገንዘቡን ለተላከለት ሰው ከፍያለሁ የሚለው ከአመልካች ጋር ተመሳሳይ ስም ላለው ሰው ተገቢውን ጥንቃቄ እና የተለመደውን አሰራር በመከተል ስለመሆኑ መረጋገጡን በምክንያትነት በመያዝ ተጠሪን ከክሱ ኃላፊነት ነፃ ማድረጉን ነው፡፡

በመሰረቱ ባንክ በሐዋላ የተላከውን ገንዘብ ለተላከለት ሰው በትክክል የማድረስ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ይታመናል፡፡ ባንኩ በሐዋላ ለማድረስ የተቀበለውን ገንዘብ ለተገቢው ሰው ካላደረሰ ኃላፊነት የሚኖርበት ሲሆን ኃላፊነቱ የሚከተለው ግን ተገቢውን ጥንቃቄ እና የተለመደውን አሰራር ሳይከተል መቅረቱ ወይም ራሱ ባንኩ መጭበርበሩ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ባንክ ተገቢውን ጥንቃቄ እና የተለመደውን አሰራር መከተሉን የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን አመልካች ገንዘቡን ከባንኩ የወሰዱት ግለሰብ ባንኩን ያጭበረበሩት ስለመሆናቸውን በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ ገንዘቡን ለአመልካች ላኩ የተባሉት ሰው ለማስረጃነት አመልካች የቆጠሯቸው ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የማያሳይ በመሆኑ አመልካች የስር ፍርድ ቤት

እኚህን ግለሰብ ሳይሰማ ማለፉ ያላግባብ ነው በማለት ያቀረቡት ቅሬታ ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባበል የተደነገጉትን የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ይህ ችሎት የሚቀበለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የማስረጃው አቀባበልና አመዛዘኑ ባግባቡ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕግ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 እና 22 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው ይዘትና መንፈስ እንደሚያስገነዝበው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ጉዳይ ሳይሆን የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ሆኖ ስለአገኘን የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና የሚገባው ነው፡፡ በዚህ መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 100405 ግንቦት 04 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 69684 ግንቦት 14 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 50440

ግንቦት 16 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሃብቱ ወልዱ - ጠ/አማረ ተሻለ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ መሰሉ ደስታ
2. ወ/ሮ አማከለች ገ/ሕይወት
} አልቀረቡም

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በመቐለ መካከለኛ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት አመልካች ሲሆኑ በክሳቸው በመቀሌ ከተማ ቀበሌ 1ይ ወያን የሚገኝ የህብረት ስራ ማህበር ውስጥ የሚገኘውን በቁጥር ሐ/116 በስማቸው የተመዘገበውን ቤት አንደኛ ተጠሪ እንዲያስተዳድሩ፣ እንዲቆጣጠሩ፣ እንዲሸጡና እንዲለውጡ ውክልና ሰጥተዋቸው የነበረ ቢሆንም ከውክልናቸው ውጪ እናታቸው ለሆኑት ለሁለተኛ ተጠሪ በስጦታ በመስጠት ስሙን ያዛወሩ በመሆኑ የስጦታው ውሉ ፈርሶ የማህበሩ ቤት ከሁለተኛ ተጠሪ ወደ ስማቸው እንዲዞርላቸው ጠይቀዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ በተሰጣቸው ውክልና መሰረት ቤቱን ለሁለተኛ ተጠሪ ከመሸጥ በቀር በስጦታ እንዳልሰጡ፣ ሽያጩ ሊከናወን የሚገባውም በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ እና በንግድ ህጉ እንጂ በፍ/ህጉ አለመሆኑንና በተሰጣቸው ውክልና መሰረት በህጉ አግባብ ያደረጉ ሽያጭ በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪም አመልካች በቤቱ ላይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ስለሌላቸው የመክሰስ መብት የላቸውም፣ አንደኛ ተጠሪ በተሰጣቸው ውክልና መሰረት በሽያጭ እንጂ በስጦታ አልተላለፈም፣ ቤቱም ሊሸጥ የሚችለው በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብና በንግድ ህግ እንጂ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 መሰረት አይደለም፣ ቤቱ በስማቸው ስለተመዘገበ ሽያጩ ሊፈርስ አይገባም፣ ይፈርሳል የሚባል ከሆነ መቀጫ ብር 20,000(ሃያ ሺህ) ሊከፍሉ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ በስር ሦስተኛ ተከሳሽ የነበረው 1ይ ወያነ ቤት ስራ ህብረት ስራ ማህበር የተደረገ የስጦታም ሆነ የሽያጭ ውል የለም፣ አንደኛ ተጠሪ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የተቀመጠ ውሳኔና በመሸጫ አሰራር ከትዳር ነፃ መሆናቸውን በማምጣት ስም ማዛወሪያ ሞልተው ወደ ሁለተኛ ተጠሪ አዘዋውረዋል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ አንደኛ ተጠሪ ለእናታቸው ለሁለተኛ ተጠሪ ሽጫለሁ ያሉት በተዘዋዋሪ የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ስለሆነ የጥቅም ግጭት አለ፣ የተሸጠውም ቤትና ቦታ በመሆኑ ሽያጩ ለማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጫ የሚመለከተውን የህጉን ድንጋጌ አያሟላም፣ በመሆኑም ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት ቤቱ ከሁለተኛ ተጠሪ ወደ አመልካች ስም እንዲዛወር ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ላይ ለትግራይ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ ተጠሪዎች በመቀጠል ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ክስ የመሰረቱት አንደኛ ተጠሪ ከተሰጣቸው ውክልና ውጪ ቤታቸውን በስጦታ ለሁለተኛ ተጠሪ ስለሰጡ የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ ሆኖ ሳለ ፍ/ቤቶቹ ከክሱ ውጪ በመውጣት የሽያጭ ውሉ ይፍረስ ብሎ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ውጪ ነው በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር የሽያጩ ውል የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው አንደኛ ተጠሪ ከአመልካች በተሰጣቸው ውክልና ስልጣን ለወላጅ እናታቸው ያደረጉት የሽያጭ ውል የጥቅም ግጭት ያለበት ነው፣ በምንም አይነት ውል የጥቅም ግጭት ካለ ለውጥ ስለማያመጣ የሰበር ችሎቱ የጥቅም ግጭት መኖር አለመኖሩን መመርመር ሲገባው ወደ ውሉ አይነት ገብቶ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል ብለዋል፡፡ ይህ ችሎትም የጥቅም ግጭት መኖር አለመኖሩን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይገባል በማለቱ ተጠሪዎች መልሳቸውን በፅሁፍ አቅርበዋል፡፡ በመልሳቸውም ቤቱን አንደኛ ተጠሪ በተሰጣቸው ውክልና መሰረት አትርፈው የሸጡት እንጂ በስጦታ ያስተላለፉ ባለመሆኑ የጥቅም ግጭት አለ ሊባል አይችልም፣ አመልካች በተደረገው ሽያጭ ውል መሰረት የደረሰባቸው ጉዳት ስለመኖሩ በማስረጃ አስደግፈው አላረጋገጡም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አመልካች ክስ የመሰረቱት አንደኛ ተጠሪ እንዲያስተዳድሩላቸው፣ እንዲቆጣጠሩላቸው፣ እንዲሸጡላቸውና እንዲለውጡላቸው ውክልና የሰጧቸውን ቤት ከውክልናቸው ውጪ በስጦታ ለሁለተኛ ተጠሪ ስላስተላለፉ ውሉ እንዲፈርስላቸው ነው፡፡ ተጠሪዎቹ በሰጡት መልስ ቤቱን ለሁለተኛ ተጠሪ የተላለፈው በሽያጭ እንጂ በስጦታ አለመሆኑ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በስር ፍ/ቤት በተደረገው የቃል ክርክር የሽያጭ ውልም ቢሆን አንደኛ ተጠሪ ውሉን ያደረጉት ከእናታቸው ጋር በመሆኑ የጥቅም ግጭት አለ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት ቤቱ የተላለፈው በሽያጭ መሆኑን ተቀብሎ ነገር ግን አንደኛ ተጠሪ ከእናታቸው ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል የጥቅም ግጭት ያለበት በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ ይገባል የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ የሰበር ችሎቱ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ የሻረው ክሱ የስጦታ ውል ይፍረስልኝ ሆኖ ሳለ

የሽያጭ ውል እንዲፈርስ መደረጉ በክሱ ከተጠየቀው ዳኝነት ውጪ ነው በማለት ነው፡፡ በእርግጥ አመልካች ቤታቸው ለሁለተኛ ተጠሪ የተላለፈው በስጦታ ነው በሚል ክስ ቢመሰርቱም ዋናው ጥያቄአቸው ቤቱ ወደ ሁለተኛ ተጠሪ የተላለፈበት ውል እንዲፈርስ ነው፡፡ በቃል ክርክሩ በሚሰማበት ጊዜም አመልካች ቤቱ በሽያጭ መተላለፉን ሲረዱ የሽያጩም ውል ቢሆን የጥቅም ግጭት ያለበት ነው በማለት ይኸው ነጥብ ክርክር ተደርጎበታል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ባልተነሳ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሰጥቷል በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የተሳሳተ ነው፡፡

በሌላ በኩል ይህ ችሎት አንደኛ ተጠሪ ለሁለተኛ ተጠሪ ያደረጉት የሽያጭ ውል የጥቅም ግጭት አለበት ወይ? የሚለውን ነጥብ ተመልክቷል፡፡ ተወካዩ በፈፀመው ውል ምክንያት የወካዩና የወኪሉ ጥቅሞች የሚቃወሙ የሆኑ እንደሆነ ይህን ውል የፈረመው 3ኛ ወገን ሁኔታውን ያወቀና ሊያውቀው የሚገባ የሆነ እንደሆነ ወካዩ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1) ያስረዳል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አንደኛ ተጠሪ የአመልካች ወኪል ሲሆኑ በተሰጣቸው ውክልና መሰረት የአመልካችን ቤት ለእናታቸው ሸጠዋል፡፡ ውክልና ተወካዩ ለወካዩ እንደራሴ ሆኖ አንድ ወይም ብዙ ህጋዊ ስራዎችን በወካዩ ስም ለማከናወን የሚደረግ ስምምነት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2198 ያመለክታል፡፡ ይህም ስምምነት ወካዩ የውክልናው ስራ በሚፈፅምበት ጊዜ የወካዩን ህጋዊ ሁኔታዎች የመለወጥ ስልጣን የሚሰጠው በመሆኑ ተወካዩ የውክልናውን ስልጣን ተጠቅሞ ሲሰራ ለወካዩ ፍፁም ታማኝ እና በስራው ሁሉ የወካዩን ጥቅም ብቻ ለማስጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ይህንን ለወካዩ ፍፁም የሆነ ታማኝነቱንና ሙሉ ለሙሉ የወካዩን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚከለክለው ፍላጎት ወይም ታማኝነቱን የሚከፋፍል ሁኔታ የሚያስከትል የጥቅም ግጭት ሲፈጠር ተወካዩ በስራው አፈፃፀም ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡ እነዚህም ግዴታዎች በፍ/ብ//ህ/ቁ. 2208 እና 2209 ስር ተመልክተው የምናገኛቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም ተወካዩ የራሱን ጥቅም ብቻ ሳይሆን የቤተሰቡ፣ የጓደኛው ወይም ቅርብ ግንኙነት ያለው ሰው ጥቅምን በሚመለከት ጉዳይ ሲያጋጥመው ሁኔታውን ለወካዩ ሳያሳውቅና ሳይስማማ ስራውን እንዳይሰራ ይከለከላል፡፡ ይህም የሚሆነው የውክልና ስራውን በሚሰራበት ጊዜ የራሱን ወይም ከራሱ ጋር ቤተሰባዊ ወይም ሌላ ጥብቅ ግንኙነትና ትስስር ያለው ሰውና የወካዩ ጥቅም በሚጋጭበት ጊዜ ከራሱ ወይም ከቤተሰቡ ጥቅም ይልቅ የወካዩን ጥቅም በማስቀደም ለወካዩ ጥቅም ብቻ ይሰራል ተብሎ ስለማይገመት ነው፡፡ በመሆኑም ወኪሉ በፈፀመው ውል ምክንያት የወካዩ እና የተወካዩ ጥቅሞች የሚጋጩ ከሆነ ውሉን የፈረመው 3ኛ ወገን ይህን ሁኔታ ያወቀውና ሊያውቀው የሚገባ የሆነ እንደሆነ በወካዩ ጥያቄ መሰረት ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል በህጉ ተካቷል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች አንደኛ ተጠሪን ክርክር ያስነሳውን ቤት እንዲያስተዳድሩ እንዲሸጡና እንዲለውጡ የውክልና ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ በመሆኑም አንደኛ ተጠሪ በወካያቸው ስም ሲዋዋሉ ፍፁም ታማኝና ሙሉ ለሙሉ የወካያቸውን የአመልካችን ጥቅም በሚያስጠብቅ ሁኔታ ውሉን የመፈፀም ግዴታ አለባቸው፡፡ አንደኛ ተጠሪ ከአመልካች በተሰጣቸው ውክልና መሰረት ቤቱን የሸጡ እናታቸው ለሆኑት ለሁለተኛ ተጠሪ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ደግሞ አንደኛ ተጠሪ በውክልናቸው መሰረት ቤቱን የሸጡት የቤተሰባዊ ጥብቅ ትስስር ላላቸው እናታቸው በመሆኑ በወካያቸው ጥቅምና ውሉን ባደረጉት እናታቸው ጥቅም መሃከል ግጭት መኖሩ የሚታመን ነው፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ አንደኛ ተጠሪ ሁኔታውን ለአመልካች ሊያሳውቁና የአመልካችን ይሁንታ ሊያገኙ ይገባል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ውሉን ከመፈፀማቸው በፊት ለአመልካች ያሳወቁና ስምምነታቸውን ያገኙ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ወይም አንደኛ ተጠሪ ቤቱን የአመልካችን ጥቅም ብቻ በሚያስጠብቅ መልኩ ተገቢው ጥንቃቄ በማድረግ ቤቱ በተሸጠበት ጊዜ ሊያወጣ በሚችለው የገበያ ዋጋ ሽያጩን ያከናወኑ መሆኑና የአመልካች ጥቅም በምንም መልኩ ያልተጎዳ መሆኑን በስር ፍ/ቤት ሊያስረዱ ይገባል፡፡ ይህ ለመሆኑ ደግሞ ተጨባጭ ማስረጃ አቅርበው ያስረዱት ነገር ስለመኖሩ መዝገቡ አያሳይም፡፡ በሌላ በኩል አንደኛ ተጠሪ ቤቱን በውክልና ስልጣናቸው የሸጡላቸው በመሆኑ የጥቅም ግጭት እንደሚኖር ሁለተኛ ተጠሪ ያውቃሉ ወይም ሊያውቁ ይገባል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ከአመልካች በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን መሰረት የአመልካችን ቤት ለእናታቸው ለሁለተኛ ተጠሪ መሸጣቸው የጥቅም ግጭት መኖሩን የሚያሳይ በመሆኑም አመልካች ውሉ እንዲፈርስላቸው ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል አንደኛ ተጠሪ ከቤቱ ሽያጭ ያገኙትን ገንዘብ ለአመልካች የከፈሉ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ባለመረጋገጡ የተከፈለ ገንዘብ ካለ አንደኛ ተጠሪ አመልካችን ከሰው የመጠየቅ መብታቸውን ፍ/ቤቱ

ጠብቆላቸዋል። ሁለተኛ ተጠሪም ቤቱ ለመግዛት የከፈሉትንና በቤቱ ላይ ተጨማሪ ወጪ አውጥቻለሁ የሚሉ ከሆነ ያወጡትን ወጪ አንደኛ ተጠሪን ከሰው የመጠየቅ መብታቸው የተጠበቀ ነው።

በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤት የሽያጩ ውል ሲፈርስና በሁለተኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበው የቤትና የቦታ እጣ በአመልካች ስም እንዲመዘገብ የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት የህግ መሰረት የለም።

## ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 32155 ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል።
2. የመቐሌ መሃከለኛ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 00654 ሰኔ 5 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የትግራይ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 07667 ሰኔ 8 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል።
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
   መዝገቡ ተዘግቷል። ለመዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ራ/ታ

# የንግድ ሕግ

የሰ/መ/ቁ. 46358

የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ብርሃን ፀጋዬ - አልቀረቡም ከተባለ በኂላ ጠበቃ ቀረቡ

**ተጠሪዎች**፡- 1ኛ. አቶ ሚካኤል ፍስሐ - ቀረቡ

2ኛ. ናሰው ኮንስትራክሽን - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሽርክና ውል የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ክስ የተመሰረተው በአመልካች አማካይነት ነው፡፡ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ያቋቋሙት የሽርክና ውል ፈርሶ የተገዛው ንብረት ተሸጦ እንዲከፋፈሉ እንዲወሰን የሚል ነበር፡፡ አንደኛ ተጠሪ የሽርክና ውል የለንም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ የአሁን ሁለተኛ ተጠሪ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትን ኤክስካቫተር ማሽን ባለቤት መሆኑን በመጥቀስ በክርክሩ ገብቶ ለመከላከል ጣልቃገብ ሆኖ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል የተፈረመው ውል የሽርክና ውል እንጂ የአሽሙር ማህበር አይደለም በማለት የሽርክና ውሉ ደግሞ በንግድ ሕግ አንቀጽ 219 /ሐ/ መሰረት አልተመዘገበም በሚል ምክንያት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛው ፍ/ቤትም ይህንኑ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ በአመልካች እና በአንደኛ ተጠሪ መካከል መጋቢት 4/1994 ዓ.ም የተፈረመው ውል

"የአሽሙር ሽርክና ማህበር" መሆኑን አጥብቀው በመከራከር የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ተሽሮ እንደክሱ የዳኝነት ጥያቄ እንዲወሰን አመልክቷል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በግራ ቀኙ

መካከል የተደረገው ውል በሕግ ረገድ የሚኖረው ውጤት ምንድነው? የሚለውን ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ የአንደኛ ተጠሪ ወኪል ታህሣሥ 30/2002 ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት መልስ የሥር ፍ/ቤት ክርክርን አጠናክረው አቅርበዋል፡፡

እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ አመልካች ከአንደኛ ተጠሪ ጋር የሽርክና ማህበር ያቋቋሙ ስለመሆኑ ለማስረዳት መጋቢት 3 ቀን 1994 ዓ.ም የተፃፈ ውል አቅርበዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የሽርክና ውል የለኝም ይበል እንጂ የቀረበውን ሰነድ ለማስተባበል በሥር ፍ/ቤት ያቀረበው

ክርክርም ሆነ ማስረጃ ስለመኖር የሥር መዝገብ አያስረዳም፡፡ የሥር ፍ/ቤት የቀረበውን ሰነድ ውድቅ ያደረገው ሰነዱ የእሽሙር ማህበር ስለመኖሩ አያስረዳም በሚል ነው፡፡

ከቀረበው ሰነድ መረዳት የተቻለው አመልካችና አንደኛ ተጠሪ የሽርክና ማህበር ለማቋቋም ውል ማድረጋቸውን ነው የውል ሰነድ "የሽርክና ውል ስምምነት" ከሚል በስተቀር ምን ዓይነት የሽርክና ማህበር እንደሆነ አያመለክትም፡፡ ከንግድ ሕግ አንቀጽ 211 መረዳት የሚቻለው የሽርክና ማህበር ጠቅላላ ስያሜ እንጂ የማህበሩን ዓይነት ለይቶ የሚያመለክት አለመሆኑን ነው፡፡ የማህበሮቹ ስያሜ እና ዓይነታቸውን በተመለከተ የንግድ ሕጉ ድንጋጌ ቁጥር 212 በዝርዝር አመልክቷል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል አለ የተባለው የሽርክና ማህበር ስያሜው ተለይቶ አልተመለከተም፡፡ ከዚህ መነሻ ሲታይ የሽርክና ውሉ አልተመዘገበም የሚለው የሥር ፍ/ቤት አቋም ምን ዓይነት የሽርክና ውል የሚለውን አልለየም፡፡ ምክንያቱም ምዝገባ የሚያስፈልገው እና ምዝገባ የማያስፈልገው የሽርክና ማህበር በንግድ ሕጉ ተለይቷል፡፡

በግራ ቀኙ ክርክር ይዘት ከመዝገቡም መረዳት እንደተቻለው የአመልካች ክርክር የሽርክና ማህበሩ የእሽሙር የሽርክና ማህበር ስለሆነ ምዝገባ አያስፈልገውም ሕጉ አያስገድድም የሚል ነው፡፡ በአንደኛ ተጠሪ በኩል ያቀረበው ዋነኛ ክርክር እስከነጭራሹም የሽርክና ውል የለም የሚል ነው፡፡ በዚህ ረገድ በአመልካች በኩል የቀረበው ሰነድ

የሽርክና ውል ስለመኖሩ የሚያስረዳ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤትም ተቀባይነት ያገኘ ፍሬ ነገር ነው፡፡ የሽርክና ውሉ የእሽሙር ሽርክና ማህበር ወይንስ ሌላ አይነት ማህበር አቋቁሟል? የሚለውን ለመለየት የሥር ፍ/ቤት በውሳኔው በዝርዝር አላመላከተም፡፡

በሕጉ አገላለጽ ሌሎች የሽርክና ማህበራት ምዝገባ የሚያስፈልግ ሲሆን የእሽሙር ሽርክና ማህበር ግን ምዝገባ አያስፈልገውም፡፡ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 219 ይመለከቷል፡፡

አመልካች ያቀረቡት ሰነድ የሽርክና ማህበር መመሥረቱን የሚያመላክት ሲሆን ባለመመዝገቡ የእሽሙር ሽርክና ማህበር ነው ተብሎ በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክር አንደኛ ተጠሪ በማስተባበል ያቀረበው ክርክር የለም፡፡

ስለሆነም በስምምነት የተቋቋመው ማህበር የእሽሙር ሽርክና ማህበር ስለመሆኑ ከቀረበው ሰነድ ለመረዳት ችለናል፡፡ ስለሆነም የሽርክና ውሉ አልተመዘገበም በሚል ምክንያት የሥር ፍ/ቤት የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 15059 የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 61426 የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካች እና በአንደኛ ተጠሪ መካከል መጋቢት 3 ቀን 1994 ዓ.ም የተደረገው የሽርክና ውል የእሽሙር ክርክር መሆኑ በዚህ ፍ/ቤት ውሳኔ ስለተረጋገጠ የፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት የመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ተቀብሎ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341/1/ መሰረት እንዲመለስ ታዟል፡፡

ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 39608

የካቲት 11 ቀን 2002 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አስቴር አርአያ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ አምሳለ በላይ - ጠበቃ ተሾመ ገ/እግዚአብሔር ቀረቡ፡፡

2. ወ/ሮ ጥበበ ተገኜ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የንግድ ማኀበር ሥራ አስኪያጆች ለማያደርሱት ጥፋት ለአባላቱ ያለባቸውን ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የጀመረው በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት ከሳሾች የነበሩ ሲሆን ክስ ያቀረቡት በአሁኗ አመልካችና ዶ/ር አለኸኝ መኮንን በተባሉት ግለሰብ ላይ ነው፡፡ በክሳቸውም ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሣ ሺህ/ የሚያወጡ እጣዎችን ለመግዛት ተስማምተው በተለያዩ ጊዜ ለተከሣሾቹ በቀጥታና በሌሎች ሰዎች አማካኝነት የአሜሪካን ዶላር እንደከፈሉ፣ እንዲሁም ለጋዜጣ ማውጫና ለኮምፒውተር መግዣ ለተከሳሾቹ ገንዘብ መክፈላቸውን፣ ዶ/ር አለኸኝ መኮንን የማኀበሩ ሥራ አስኪያጅ ሲሆኑ በዚህ መዝገብ አመልካች የሆኑት ደግሞ ከታህሣሥ 24 ቀን 1999 ዓ.ም. ከሥራ አስኪያጁ በተቀበሉት ውክልና መሠረት ማኀበሩን በሥራ አስኪያጅነት ሲመሩ እንደነበረ፣ ተከሣሾቹ ማኀበሩን አቋቁመናል ከሚሉ በቀር እንዳችም እንቅስቃሴ እንዳላደረጉ፣ የማኀበሩ ካፒታል ነው የተባለው አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ብር (1,100,000)የማኀበሩ ደረሰኝ እንዲቆረጥለት ተጠይቀው ፈቃደኛ አለመሆናቸውን፣ በዚህ ምክንያት ማኀበሩ ስለከሰረ እንዲፈርስ መወሰኑን፣ ተከሣሾቹ ማኀበሩን ያቋቋሙት በቅን ልቦና ነግዶ ለማትረፍ ሳይሆን የንግድ ስሙን ሽፋን በማድረግ ከሌሎች ሰዎች ላይ ገንዘብ ለመውሰድ መሆኑን በመግለጽ ተከሣሾቹ የወሰዱትን ገንዘብ በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ ወለድን ጨምሮ ብር 912,733(ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ ሶስት) እንዲከፍሉ ጠይቀዋል፡፡ የሥር አንደኛ ተከሣሽ የነበሩት ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ ተጠሪዎች አዋጣን የሚሉት ገንዘብ ከ10 ዓመት በፊት ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ነው፤ ገንዘቡን አዋጣን የሚሉትም ለማኀበሩ ስለሆነ ማኀበሩን ከሚጠይቁ በስተቀር አንደኛ ተከሣሽን መጠየቅ አይችሉም፣ አንደኛ ተከሣሽ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከተጠሪዎች ገንዘብ አልተቀበሉም፣ ስለሆነም የአንድነት ኃላፊነት የለባቸውም፣ አንደኛ ተከሣሽ ሥራ አስኪያጅ የነበሩ ቢሆን ሥራውን የካሄዱ የነበሩት ሥር ሁለተኛ ተከሣሽ /በዚህ መዝገብ አመልካች/ ስለሆኑ ስለ ሂሣቡ ሊጠየቁ የሚችሉት እሳቸው ናቸው በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ተከፈለ የተባለውን ገንዘብ ተከሣሽ አንድ ላይ የተቀበልነው ስላልሆነ ተጣምረን ልንከሰስ አይገባም፤ ተጣምረን ባንከሰስ ኖሮ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አይኖረውም፤ ገንዘቡ ተሰጠ ከተባለ 10 ዓመት ስለሚያልፈው ይርጋ ያግደዋል፤ ክሱ ሊቀርብ ይገባ የነበረው ማኀበሩ እንዲፈርስ በተጠየቀበት መዝገብ ስለነበር በድጋሚ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም፣ ተጠሪዎች ለአመልካች በሁለት ቼክ ከፈልን ካሉት በስተቀር ገንዘብ ስለመክፈላቸው የቀረበ ማስረጃ የለም፣ የተቀበልኩትንም ገንዘብ ለማኀበሩ ገቢ አደረኩ እንጂ በግሌ አልበለፀኩም፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማኀበርተኛ

ካዋጣው መዋጮ በላይ ኃላፊ ሊሆን የማይችልበት ነው፣ ማኅበሩ በመፍረሱ አመልካችም እንደ ሌሎቹ አባላት ጉዳት የደረሰብኝ በመሆኑ ሥራ አስኪያጅ ስለነበርኩ ብቻ በክስ ለተጠየቀው ገንዘብ ኃላፊ ልሆን አይገባም በማለት ክሱ እንዲሰረዝላቸው ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ መቃወሚያዎቹን ውድቅ ካደረገ በኋላ ተከሣሽ በሕግና በንግድ ልማድ አግባብ መሠረት የማኅበሩን ሂሣብ የመያዝና የሂሣብ መዛግብት ሪኮርድ የማስቀመጥ ግዴታ እንዳለባቸውና የሥራ አስኪያጅነት ኃላፊነታቸውን በትጋትና በጥንቃቄ መሥራት እንዳለባቸው በመመስረቻ ጽሁፉና በንግድ ሕጉ ላይ የተመለከተውን ግዴታቸውን ባለመወጣት የማኅበሩን ንብረት ለግል ጥቅማቸው አውለውም ሆነ በሌላ መልኩ አለአግባብ እንዲበካክን አድርገዋል ስለዚህ በን/ሕ/ቁ 530 መሠረት በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ናቸው በማለት ተከሣሾች ብር 300,000 /ሦስት መቶ ሺህ/ ገንዘብ ገቢ ተደርጓል ከተባለበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን የሥር አንደኛ ተከሣሽም በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 32488 ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ በሁለቱም መዝገቦች የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 31907 በሰጠው ውሣኔ በዚህ መዝገብ አንደኛ ተከሣሽ የነበሩት ደግሞ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 32488 በሰጠው ውሣኔ ላይ ቅር በመሰኘት በመ/ቁ 40866 የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም በሁለቱም መዝገቦች አመልቾች ኃለፊ የመባላቸውንና ሌሎች ተያያዥ ነጥቦችን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት በሁለቱም መዝገቦች ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ በሁለቱም መዝገቦች የቀረበው ጉዳይና ተከራካሪዎቹም ተመሣሣይ በመሆናቸው ችሎቱ ሁለቱን መዝገቦች አጣምሮ መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው ተጠሪዎች ክስ የመሠረቱት ከሥር ተከሣሽ ጋር በመሆን "ፈታሄ ቴክኒካል ኢንኮርፖሬትድ /ኢትዮጵያ/ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር" የተባለ የንግድ ድርጅት ለመመስረት በመስማማት እያንዳንዳቸው ብር 150,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) የሚወጣ እጣ ለመግዛት ገንዘብ አዋጥተው የነበረ ቢሆንም የማኅበሩ ሥራ አስኪያጆች የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ባለመወጣት ገንዘቡን ስላባከኑና ድርጅቱ ስለፈረሰ ገንዘቡን እንዲከፍሉ ነው፡፡ ተጠሪዎች ድርሻቸውን ብር 300,000(ሦስት መቶ ሺህ) ስለማዋጣታቸው በጋዜጣ ማስታወቂያ ከመገለጹም በተጨማሪ የሥር ፍ/ቤት የማኅበሩ ሂሣብ በባለሙያ ተጣርቶ ከቀረበው ሪፖርት ተጠሪዎች ገንዘብ ማዋጣታቸውን አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከክርክሩ ሂደት የሥር አንደኛ ተከሣሽ የነበሩት የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ እንደነበሩና እሳቸውም በነበራቸው ስልጣን በዚህ መዝገብ አመልካች ለሆኑት ውክልና ሰጥተዋቸው አመልካችዋ በውክልና ማኅበሩን ሲያስተዳድሩ የነበሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ሥራ አስኪያጆች ማኅበሩን ሲያስተዳድሩ በሰሩት ሥራ ኃላፊ የሚሆኑበትን የሕግ አግባብ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተከሾች ሲያስተዳድሩት የነበረው ማኅበር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሲሆን የዚህ ማኅበር ሥራ አስኪያጆች ያለባቸው ኃላፊነትም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 530 ሥር ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሠረት በንግድ ሕጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ወይም የማኅበሩን የመተዳደሪያ ደንብ በመጣስም ቢሆን በሥራ አስኪያጅነታቸው በሰሯቸው ጥፋቶችም ስህተቶችም ቢሆን በማኅበሩና በ3ኛ ወገኖች ፊት በየራሳቸው ወይም በአንድነት ሳይከፋፈል እንደ ነገሩ ሁኔታ ኃላፊዎች እንደሆኑ ያመለክታል በተያዘው ጉዳይ የሥር ተከሣሾች ማኅበሩን በሥራ አስኪያጅነት በጋራ ሲመሩ እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የማኅበሩን ሂሣብ የሰሩት የሂሣብ ባለሙያዎች የማኅበር ሂሣብ መርምረው ማኅበሩ የገቢና ወጪ ሰነድ እንደሌለው፣ ኦዲት ተደርጎ እንደማያውቅ፣ ማኅበሩ ገንዘብ የሚያስቀምጥበት የባንክ ሂሣብ እንደሌለው አወጣሁ ለሚላቸው ወጪዎችም በሕግ አግባብ የወጪ ሰነዶች እንደሌሉት፣ ማኅበሩ ምንም ሥራ ያልጀመረ ቢሆንም ለደመወዝ፣ለቤት ኪራይና ለአበል የካፒታሉን 88.38% ወጪ ማድረጉንና በአጠቃላይ የማኅበሩ አሰራር ትክክል እንዳልነበረ አብራርቷል፡፡ ተጠሪዎች በሥራ አስኪያጅነታቸው የማኅበሩን ሥራ አካሄድ፣ የማኅበሩን የሂሣብ አሰራር እና አያያዝ ሌሎችንም የማኅበሩን ሥራዎች ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ በትጋትና በቅን ልቦና መስራት በሕግም በመተዳደሪያ ደንባቸውም የተጣለባቸው ኃላፊነት ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ግን ሥራ አስኪያጆቹ ማኅበሩ ሥራ ሳይጀምር የካፒታሉን 88.38% ለቤት ኪራይ፣ ለደመወዝና ለአበል ወጪ በማድረግ፣ በአጠቃላይ የማኅበሩ አሰራር ኃላፊነት

በጎደለውና በማንኛውም መለኪያ ትክክል ባልሆነ መንገድ ሲሰሩ እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የሥር ተከሳሽ ሥራ አስኪያጆች ሆነው ሲሰሩ በሰሩት ጥፋትም ሆነ ስህተት በግል ሆነ በአንድነት ተጠያቂ ሊሆኑ እንደሚችሉ የንግድ ሕጉ ቁጥር 580 ስለሚያስረዳ የሥር ፍ/ቤት በዚህ መዝገብና በመ/ቁ. 40866 አመልካቾች ኃላፊነት አለባቸው በማለት ውሣኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች ለአመልካቾች ከድርሻቸው መጠን ካዋጡት ገንዘብ ሌላ ተጨማሪ ገንዘብ ለሁለቱ አመልካቾች መስጠታቸውን በመግለጽ ገንዘቡ እንዲከፈላቸው የጠየቁ ቢሆንም ለዚህ ያቀረቡ በቂ ማስረጃ ባለመኖሩ አመልካቾቹ ማዋጣታቸው የተረጋገጠው ብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ/ ብቻ ገንዘቡ ከተዋጣበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር እንዲከፍሉ መወሰኑ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤት በሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 44250 ግንቦት 27 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 31907 እና 32488 ሐምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. የዚህ ውሣኔ ግልባጭ ከመ/ቁጥር 40866 ጋር ይያያዝ
4. በዚህ መዝገብ ጥር 7 ቀን 2001 ዓ.ም. የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ትዕዛዙ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

# ለእምሯአዊ ንብረት

የሰ/መ/ቁ. 44520

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት - ጠበቃ አርአያ ጌታሁን - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ዶ/ር ጌታሁን ሽብሩ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁ. 410/96 በተመተላለፍ የመብት ጥሰት ተፈጽሞአል በሚል የቀረበውን የካሣ ጥያቄ መነሻ በማድረግ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ከሣስሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ ክሱም እንዳየነው ርቱዐ ኢምላክ በሚል የብዕር ስም "የተሰበሩ ክንፎች" በሚል ርዕስ ትርጉም መጽሐፍ አዘጋጅቶ መስከረም 24 ቀን 1999 ዓ.ም በተደረገ ውል ተከሣሽ(የአሁኑ አመልካች) 5000(አምስት ሺህ) ኮፒ እንዲያትምለት መስጠቱን፣ተከሣሽም በስምምነቱ መሰረት የህትመቱን ጠቅላላ ዋጋ ግማሽ ብር 14,929.50(አስራ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ዘጠኝ ብር ከሃምሣ ሣንቲም) ተቀብሎ ህትመቱን በሦስት የስራ ሳምንት ጊዜ ውስጥ አጠናቆ ለማስረከብ ግዴታ መግባቱን፣ነገር ግን ስራው ተጠናቆ ተጠሪ ከመረከቡ በፊት "የተሰበሩ ክንፎች" በሚል ስያሜ የታተመው መጽሐፍ ቅጂዎች በሌሎች ሰዎች (ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሣሽ ተብለው በክሱ ተመዝግበው በነበሩት) አማካይነት በገበያ ውስጥ ሲሸጥ መገኘቱን ይገልፃል፡፡ በመጨረሻም ቁሳዊ እና የሞራል ጉዳት ደርሶብኛል በማለት በጠቅላላው ብር 160,079.50 (መቶ ስልሳ ሺህ ሰባ ዘጠኝ ብር ከአምሳ ሳንቲም)እንዲከፈል እንዲወሰን ይጠይቃል፡፡

አመልካች እና ተጣምረው የተከሰሱት ሰዎችም የየበኩላቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች በማንሳት ከክሱ በነጻ ይሰናበቱ ዘንድ የተከራከሩ ሲሆን፣ፍ/ቤቱም ክርክሩንና ክርክሩን ለመደገፍ የቀረቡትን ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ፣መጽሐፉን ሲሸጡ ተገኝተዋል የተባሉትን ተከሣሾች በነፃ በመልቀቅ አመልካች ላይ ለደረሰው የመብት ጥሰት ተጠያቂ ነው ብሎአል፡፡ በዚህ መሰረትም ተጠሪ በቁሳዊ እና በሞራል ረገድ ለደረሰበት ጉዳት ካሣ እንዲከፈለው ወስኖአል፡፡ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም የአመልካችን ክርክር ባለመቀበል ውሳኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፊው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው በቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀጽ 8 መሰረት የሞራል ካሣ የማግኘት መብት ተፈፃሚ የሚሆነው ለስራው ተርጓሚ ጭምር ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡

ተጠሪ መጽሐፉን ተርጉሞ እንዲታተምለት ለአመልካች በውል ስለመስጠቱ አከራካሪ አይደለም፡፡ መጽሐፉ ታትሞ ለተጠሪ ከመድረሱ በፊት በገበያ ሲሸጥ ስለመገኘቱም በስር ፍ/ቤቶች በማስረጃ ተረጋግጦአል፡፡ በሰበር ችሎቱ ከቀረበው አቤቱታ ዋነኛ መሰረት ሆኖ በአመልካች የተጠቀሰው የመከራከሪያ ነጥብ ተጠሪ የመጽሐፉ ደራሲ ሳይሆን፣ተርጓሚ በመሆኑ እንደ ድርሰቱ አመንጪ ተቆጥሮ የሞራልና የቁሳዊ ጉዳት ካሣ ሊወሰንለት አይችልም የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ የቅጅ መብትም እንደድርሰት መብት እውቅና ያገኘና ጥበቃ የተደረገለት በመሆኑ የሞራልም ሆነ የቁሳዊ ጉዳት ካሣ እንዳገኝ መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት የመከላከያ ክርክሩን አሰምቶአል፡፡

ለክርክሩ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ሕግ የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁ.410/96 ነው፡፡ ይህን አዋጅ ማውጣት ያስፈለገው የአንድን ሃገር ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ ልማትን በማፋጠን ረገድ ትልቅ ሚና የሚጫወቱት የስነ ጽሁፍ፣የኪነጥበብ እና ተመሣሣይ የፈጠራ ስራዎች የሚበረታቱበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንደሚያስችል በመታመኑ እንደሆነ ከአዋጁ መግቢያ አጠቃላይ መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ አዋጅ የሕግ እውቅና ሊሰጣቸውና ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል ከተባሉት የፈጠራ ስራዎች አንዱ የስነ ጽሑፍ ስራ ሲሆን፣ይህም ከድርሰት ስራዎች ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ የቀረበው ነጥብም ድርሰትን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በተጠሪ የተሰራው የትርጉም ስራ በሕጉ እውቅና የተሰጠውና ጥበቃ የሚደረግለት ስለመሆን አለመሆኑ በተመለከተ መልስ ሊገኝ የሚችለው የአዋጁን ዝርዝር ድንጋጌዎች በመመልከት ነው፡፡

አመልካች የተጠሪ ስራ በሕጉ ጥበቃ የተደረገለት አይደለም በማለት የተከራከረው ተጠሪው በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተሰራውን የድርሰት ስራ ወደ አማርኛ ቋንቋ መለስ(ተረጐመ) እንጂ ስራውን (ድርሰቱን) አላመነጨም ከሚል መነሻ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው የአንድ ስራ አመንጪ ወይም የፈጠራ ባለቤት ነው ሊባል የሚችለው ምን አይነት ስራ ሰርቶ ሲገኝ ነው? የሚለው ነጥብ አግባብነት ካለው የአዋጁ ድንጋጌ ጋር አገናዝቦ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ "የሥራ አመንጪ" የሚለው ሐረግ በአዋጁ አንቀጽ 2/2/ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡ በዚህ ትርጓሜ መሰረት የስራ አመንጪ የሚባለው የአንድን የአእምሮ ውጤት የሆነን ስራ የፈጠረ ማንኛውም ግለሰብ ነው፡፡ እዚህ ላይ ግልጽ ሆኖ የሚታየው ስራው የአእምሮ ውጤት መሆን እንዳለበትና ይህ ሁኔታ መሟላቱ ሲረጋገጥም በሕግ እውቅና የሚያገኝና ጥበቃም የሚደረግለት እንደሆነ ነው፡፡ ጥበቃ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መመዘኛዎችም በአዋጁ አንቀጽ 6 የተቀመጡ ሲሆን፣ለያዝነው ጉዳይ አግባብነት ያለው ንኡስ አንቀጽ/1/ ማንኛውም የስራ አመንጪ የስራው አላማና የጥራት ደረጃ ግምት ውስጥ ሳይገባ ስራውን በማውጣቱ ምክንያት ብቻ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ጥበቃ እንደሚያገኝ ያመለክታል፡፡ በእርግጥ ስራው ጥበቃ ያገኝ ዘንድ ወጥ(ኦርጂናል) ሊሆን ይገባል፡፡ እንደዚሁም የተቀረጸ ወይም ግዙፍነት ያገኘ መሆን ይኖርበታል፡፡ በማለትም ሕጉ ደንግጓል፡፡

ተጠሪ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተሰራውን ድርሰት(መጽሐፍ) ወደ አማርኛ ቋንቋ ለመተርጐም ሲነሳ ዓላማ ያደረገው መጽሐፉ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ በሆነ ህብረተሰብ ዘንድ እንዲታወቅና እንዲነበብለት እንደሆነ መገመቱ አይከብድም፡፡ ቋንቋ የተናጋሪውን ህብረተሰብ ባህልና ወግ መሰረት ያደረገ ወይም ከእነዚህ ጋር ከፍተኛ ትስስር ያለው በመሆኑ በአንድ ቋንቋ የተፃፈን መጽሐፍ(ድርሰት) ወደ ሌላ ቋንቋ ሲተረጐም ባህልና ወጉም ግምት ውስጥ እየገባ እንደሆነ ወይም ሊሆን እንደሚገባም መገመት ይቻላል፡፡ ተጠሪ የሰራው ስራ መታየት ያለበትም ከዚህ አንፃር ነው፡፡ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተፃፈውን መጽሐፍ ወደ አማርኛ ቋንቋ ሲመልስ(ሲተረጉም) የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪው (አንባቢው) የድርሰቱን ባህርይ በትክክል እንዲገባውና ከራሱ ባህልና ወጉ ጋር አገናዝቦ እንዲያጣጥመው በሚያስችለው ሁኔታ አመቻችቶ እንደሚያዘጋጀው ይታወቃል፡፡ ይህን ስራ የሚሰራው አእምሮው በፈቀደለት መጠን እውቀቱን በመጠቀም ነው፡፡ በአጭሩ የትርጉም ስራው የአእምሮው ጭማቂ ወይም ውጤት የታከለበት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ መልክ ያለው ስራም በአማርኛ ቋንቋ የተፃፈ(ከእንግሊዝኛው የተለየ) መጽሐፍ በመሆኑ በአንቀጽ 6/1/ እንደተደነገገው ወጥ(ኦርጅናል) የሆነና ግዙፍነትም ያገኘ ስራ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የስራው

አመንጪ አይደለምና ጥበቃ አይደረግለትም በማለት አመልካች ያቀረበው የመከራከሪያ ነጥብ የሕግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ሕጉን መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ ስንመለከትም መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል ለማለት አልቻልንም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 54181 ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39233 መጋቢት 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ጸንተዋል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡
3. ተጠሪ የሞራልና የቁሳዊ ጉዳት ካሣ ሊያገኝ ይገባል መባሉ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪራሣቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

# ልዩ ልዩ

የሰ/መ/ቁ. 53459

ሚያዝያ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ማሞ ገ/ማሪያም

**ተጠሪ፡-** የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድና የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ችሎት የሰጡት ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች በተከሰሰበት የወንጀል ክስ በቀነ ቀጠሮ እየቀረበ የሚከራከር ስለመሆኑ ዋስትና ይሆን ዘንድ በሞዴል 85 በደረሰኝ ቁጥር 109993 ያስያዘው ብር 200/ሁለት መቶ/ ብር ነው፡፡ አመልካች በተከሰሰበት ወንጀል ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 58128 ታህሣሥ 9 ቀን 2002 ዓ.ም በነፃ የተሰናበት መሆኑን በመግለጽ ያስያዘው ገንዘብ እንዲመለስለት ሲጠይቅ ገንዘብ ያስያዝክበት ዋናውን ደረሰኝ ካላቀረብክ አይመለስልህም በማለት የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ጥያቄ በድምጽ ብልጫ ውድቅ አድርጐታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለተጠሪ ያቀረበ ቢሆንም የሰበር ችሎቱ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡ አመልካች በተከሰስኩበት ወንጀል በነፃ የተለቀቅሁ መሆኑን በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ በማቅረብ አስረድቻለሁ፡፡ ገንዘብ ያስያዝኩበት ደረሰኝ ስለጠፋብኝ ኮፒውን ይዤ በመቅረብ እንዲከፈለኝ ያቀረብኩት ጥያቄ የበታች ፍርድ ቤቶች አለመቀበላቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር አመልካች ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ቀርቦበት የነበረውን የወንጀል ክስ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠውን ቀነ ቀጠሮ እያከበረ የሚቀርብና የሚከታተል ለመሆኑ ዋስትና ይሆን ዘንድ ብር 200/ሁለት መቶ ብር/ በሞዴል

ሰማኒያ አምስት እስይዞ ጉዳዩን ሲከታተል የነበረ መሆኑንና ከተከሰሰበትም ወንጀል በነፃ የተሰናበት መሆኑን የመንግስት ሰነድ የሆኑት የፍርድ ቤት መዝገቦችና በውሣኔው ግልባጭ በማየትና በማጣራት ለማረጋገጥ ይቻላል፡፡

አመልካች ያስያዘው ገንዘብ አይመለስልህም የተባለው ገንዘቡን ገቢ ያደረገበት ዋናው ደረሰኝ ሣይሆን የዋናው ኮፒ ይዞ በመቅረቡ ነው፡፡ በአርግጥ በሰነድ የተገለፀን ፍሬ ጉዳይ ለማስረዳት ማቅረብ የሚገባው ዋናው ሰነድ መሆን እንዳለበት (Best evidence rule) መሰረታዊ መርህ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ሆኖም ዋናው ሰነድ ሊገኝ በማይችልበት ሁኔታ የዋናው ሰነድ ኮፒ/Secondary evidence/ በማቅረብ ጉዳዩን ከማስረዳት የማይከለክል መሆኑን በስፋት ተቀባይነት ያላቸውን የማስረጃ ሕግ መርሆች በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ገንዘቡን ያስያዘው አመልካች ስለመሆኑ አመልካች ይዞት በቀረበው የደረሰኝ ኮፒ ብቻ ሣይሆን በወንጀል ተከስሶ ጉዳዩ ከታየበት የጊዜ ቀጠሮ መዝገቦችና ክርክሩን ተከታትሎ በነፃ ከተለቀቀበት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል መዝገብ ጋር በአንድነት አጣምሮ በመመዘን ለማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች በአደራ በሞዴል 85 ብር 200/ሁለት መቶ ብር/ ያስያዘ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርቦ እያለ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ያቀረብከው ማስረጃ ዋናውን ደረሰኝ ሣይሆን ፎቶ ኮፒውን ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የሰበር ችሎት የሰጡት ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በሞደል 85 በደረሰኝ ቁጥር 109993 ያስያዙት የዋስትና ገንዘብ ብር 200/ሁለት መቶ ብር/ ይመለስላቸው ብለናል፡፡

ይኽ ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 43781

ሐምሌ 14 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - ዐ/ህግ ወርቅነህ

ዓለማየሁና ታደለ ተስፋዬ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ዳንኤል መኮንን አልቀረቡም

በዚህ መዝገብ የቀረበውን ጉዳይ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው አቤቱታ ተጠሪ የተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት በሕግ አያስጠይቀውም በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው ሲል አመልካች ይኸው እንዲታረም በመጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ ተጠሪው ነሐሴ 22 ቀን 1996 ዓ.ም መጠኑ 46.96(አርባ ስድስት ነጥብ ዘጠና ስድስት) ኪ.ግ የሆነ የሀገር ውስጥ ጥፍጥፍ ወርቅ በሕገወጥ መንገድ ከአገር ለማስወጣት ወደ ጅቡቲ በማጓዝ ላይ እያለ በክትትል በወለንጪቲ እና በመተሐራ መካከል በመያዙ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 60/89 በአዋጅ ቁጥር 368/95 እንደተሻሻለው አንቀጽ 2(28) እና አንቀጽ 66/2/ በመተላለፍ የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈጽሟል በማለት ክስ የቀረበበት ሲሆን በአማራጭ የገንዘብ እና የባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59/2/ለ ሥር የተጠቀሰውንና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስለወርቅ ግብይት ቁጥጥር ያወጣውን መመሪያ ቁጥር CTG/001/97 አንቀጽ 1 እና 2 በመተላለፍ በሕገ-ወጥ መንገድ ወርቅ ሲያዘዋውር በአገር ኢኮኖሚ ላይ ከባድ ወንጀል ፈጽሟል በማለት አመልካች ተጠሪ ላይ ክስ መስርቷል፡፡

ተጠሪ ሥር ፍ/ቤት ቀርቦ ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛም አይደለሁም ብሎ ክዶ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የመጀመሪያውን ክስ በተመለከተ ተጠሪ በመከላከያ ማስረጃ አስተባብለዋል በማለት ከክሱ በነፃ እንዲሰናበቱ ወስኗል፡፡ በአማራጭ የቀረበውን ክስ በተመለከተ በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት በክሱ መሠረት ጥፋተኛ ነው ሲል ፈርዷል፡፡ ቅጣቱንም በተመለከተ ጥፋተኛ በተባለበት አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59/2 (ለ) መሠረት በአምስት ዓመት (5) ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ብር አንድ ሚሊዮን የገንዘብ መቀጮ እንዲከፍል የተያዘው ወርቅ በመንግሥት እንዲወረስ እና ለሦስት (3) ዓመት ጊዜ ምስክር ከመሆን መምረጥ እና ከመመረጥ መብት ተገድቧል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ ላይ ተጠሪ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ 1ኛው ክስ የኮንትሮባንድ ወንጀል ስለመፈጸሙ የዐ/ሕግ ማስረጃ አላረጋገጠም በማለት ሲወስን በአማራጭ የቀረበውን ክስ በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59/2/(ለ) ላይ ወርቅን አስመልክቶ ያስቀመጠው ክልከላ የለም፤ መመሪያ ቁጥር 001/97 ሕግ ሆኖ አስገዳጅነት እንዲኖረው በአዋጅ ቁጥር 3/87 እና 14/88 መሠረት በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ያልወጣ እንዲሁም በአማርኛ ቋንቋ ያልተፃፈ በመሆኑ ሕግ ሆኖ ቅጣት ሊጥል አይችልም በወንጀል ተጠያቂ ሊያሰኝ አይችልም በሚል ምክንያት ተጠሪው እንዲከለከል ብይን መስጠቱ ተገቢ አልነበረም ሲል በውሳኔው ሐተታ ገልጿል፡፡

በፍሬ ነገር ረገድም ወርቁን ወደ ጅቡቲ ሳይሆን ወደ ጎንደር ያጓጓዘ መሆኑን በመከላከያ ማስረጃ በተሻለ ሁኔታ አረጋግጧል በሚል የሥር ፍ/ቤት ጥፋተኛ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት እንደሌለው ወስኗል፡፡ ባጠቃላይ በሕግም ሆነ በፍሬነገር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ ስሕተት ነው በማለት ተጠሪ(ተከሳሽ) በነፃ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ጠቅላይ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ተጠሪ በአማራጭ የተከሰሰበት ድርጊት መመሪያው በሕግ መልክ ስላልወጣ የወንጀል ክልከላ ተደርጓል ሊባል አይችልም በማለት የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ አፅንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሕገወጥ የወርቅ ዝውውር አስመልክቶ አዋጅ ቁጥር 52/85 እና 83/86 መሠረት አድርጐ የወጣው የብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር CTG/001/97 ተፈጻሚነት ያለው ስለመሆኑ መመሪያው በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ያለመውጣቱ ሕጋዊነቱን እንደማያሳጣው፣ መመሪያው በአማርኛ ቋንቋ ያልተፃፈው ከብሔራዊ ባንክ የሥራ ባህርይ የተነሳ ስለመሆኑ እንዲሁም ወንጀል ድርጊቱ የቅጣት አወሳሰን አዋጁ ወይም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 357 እና 358 ተፈጻሚነት ሊኖረው እንደሚገባ በመጥቀስ የይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተሽሮ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና አመልክቷል፡፡

የሰበር ችሎቱም የቀረበውን አቤቱታ ከመረመረ በኋላ በዚህ ጉዳይ በአማራጭ የቀረበውን ክስ አስመልክቶ በአዋጅ መሠረት የወጣው መመሪያ በአማርኛ ተተርጉሞ ያለመገኘቱ ሁኔታ በጉዳዩ ላይ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? መመሪያው ተፈጻሚ ነው ከተባለ ተፈፀመ የተባለውን ድርጊት ሊሸፍን የሚችል ነው ወይስ አይደለም? ይህም ቢታለፍ የገንዘብ እና የባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 በ1949 ዓ.ም ከወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 357 እና 358 አንፃር ሲታይ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ጥፋተኛ ሊባል አይገባም በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ የተጠሪ ጠበቃ ህዳር 23 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ቀርበው የግራ ቀኙ ክርክርም በችሎቱ ተሰምቷል፡፡

በተጠሪ ጠበቃ በኩል የተነሱት የመከራከሪያ ነጥቦች ሥር ፍ/ቤት የባንክ ሥራ ሰርቷል ተብሎ ክስ ያልቀረበ ስለመሆኑ የኮንትሮባንድ ወንጀል ነው ተብሎ የቀረበው ክስ ውድቅ ስለመደረጉ በአማራጭ የቀረበው ክስም አዋጅ እና መመሪያ ከመጥቀስ ውጪ ድርጊቱን በተመለከተ ጥፍጥፍ ወርቅ አዘዋውሯል እንዳልተባለ መመሪያው ተፈጻሚነት ሊኖረው እንደማይገባ እንዲሁም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 357 እና 358 መመሪያው ሕጋዊነት የሌለው በመሆኑ ተፈጻሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በዚሁ አግባብ

የሥር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና አመልክተዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍሲል በአጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከፍሲል እንደተጠቀሰው በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመር የተያዘው የመጀመሪያው ጭብጥ በብሔራዊ ባንክ የወጣው መመሪያ ቁጥር ሲቲጂ/001/97 በአማርኛ ተተርጉሞ ያለመውጣቱ በጉዳዩ ላይ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? የሚለውን አስቀድመን እንመረምራለን፡፡ ለዚህ ጭብጥ ምላሽ ለማግኘት የሕጎች ተዋረድ እና አወጣጥ በመጠኑም ቢሆን መዳሰስ ተገቢ ይሆናል፡፡ በመርህ ደረጃ ሕግ የማውጣት ሥልጣን በሥልጣን ክፍፍል መርህ መሠረት የሕግ አውጪው አካል ስለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በሕግ አውጪው የመንግስት አካል የሚወጡ ሕጎች ቀዳማዊ /primary legislations/ ተብለው የሚታወቁ ሲሆን ሌሎቹ እንደአስፈላጊነታቸው አግባብ ባለው አካል የሚወጡ የበታች ሕጎች (subsidiary legislations) ተብለው የሚታወቁ ናቸው፡፡ ሕግ አውጪው የመንግሥት አካል በተለያዩ ቴክኒካዊና ማህበራዊ ምክንያቶች ቀዳሚውን ሕግ ለማስፈጸም የሚያስችሉ ዝርዝር ሕጎች ያስፈልጋሉ ብሎ ባመነ ጊዜ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው አካል የበታች ሕጎችን እንዲያወጣ ሥልጣን ሲሰጥ ይስተዋላል፡፡ ይህ አሰራር በሕግም በምክንያትም የተደገፈ እና የዳበረ ልምድ ስለመሆኑ ግልፅነው፡፡ አሁን በተግባር ሥራ ላይ ያለው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሕግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 14/88 አንቀጽ 2(1) እንደሚያመለክተው ሕግ የሚላቸው አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሲሆኑ እነዚህ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሲወጡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ መውጣት እንዳለባቸው ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ከፍ ሲል እንደተመለከትነው በሌሎች የመንግሥት አካላት የሚወጡት የበታች ሕጎች ማለትም ደንቦች እና መመሪያዎች በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጡ የሚያስገድድ ድንጋጌ በዚህ አዋጅ አልተመለከተም፡፡ ከዚህም ሌላ ከመነሻውም ይህ አዋጅ ቁ.14/88 የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሕግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት የሚመለከት እንደመሆኑ በሌሎች አካላት የሚወጣን የበታች ሕግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት አስመልክቶ ምላሽ የሚሰጥ አይደለም፡፡ በርግጥ በዚህ ረገድ የሌሎች ሀገሮች ልምድ ሲታይ በመንግሥት አስፈጻሚ አካላት የሚወጡት የበታች ሕጎች ሥነ ሥርዓታዊ ጉዳዮች የሚወሰነው የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት ሕግ በሚሰኝ የሕግ ዓይነት መሆኑን የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በሀገራችን የወጣ ሕግ የለም፡፡ ይህም በመሆኑ በየአስፈጻሚ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚወጡ የበታች ሕጎች እንዲታተሙ እና በተወሰነ ቋንቋዎች እንዲፃፉ የሚያስገድድ ሕግ የለንም፡፡ ከዚህም የተነሳ በርካታ የበታች ሕጎች በተለያዩ ተቋማት በተለያየ መልክ ወጥተው በተግባር ላይ ውለው እናገኛለን፡፡ በተለይም መመሪያ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ሲወጣ አልተስተዋለም፡፡

በተግባር ያለው እውነት ይህ መሆኑን የምንረዳው ከመሆኑ አንፃር አሁን በእጃችን ያለው ጉዳይ ስንመለከት ብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመሪያ ቁጥር ሲቲጂ/001/97 በአማርኛ ቋንቋ አልተፃፈም በነጋሪት ጋዜጣም አልታተመም ሲሉ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ይህ እንዲደረግ የሚያስገድድ ግልፅ ሕግ በሌለበት ሁኔታ እና በተግባር ያለውን እውነታ ባለማገናዘብ በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ይህ አካሄድም በተግባር ሥራ ላይ ያሉትን በርካታ መመሪያዎች ተፈጻሚነት ዋጋ የሚያሳጣ ነውና፡፡ ይልቁንም ለዚህ መመሪያ መውጣት ዋና ወይም እናት ሕግ የሆነው አዋጅ ቁጥር 83/86 ለባንኩ ሥልጣን ስለመስጠቱ መመሪያው በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን ለማስፈጸም በሚያስችል መልኩ የተቀረፀና የሚጣጣም ስለመሆኑ በማገናዘብ ውጤት በሚያስገኝ እና የእናት ሕግ ዓላማና ግብ ለማስፈጸም በሚያስችል አግባብ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ይገባል የሚል እምነት አለን፡፡ ስለሆነም መመሪያው በአማርኛ ቋንቋ አልተፃፈም በሚል ምክንያት ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የተያዘው ጭብጥ የመመሪያውን ተፈጻሚነት የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶቹ መመሪያው የወንጀል ድንጋጌ የለውምና ተፈጻሚነት የለውም በማለት የመ/ደረጃ ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽረዋል፡፡ በዚህ መሠረት በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ምክንያት አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 39/2/ እና ተያያዥ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መመርመር ተገቢ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ባንኩ ተጠቃሹን መመሪያ ያወጣው በአዋጁ አንቀጽ 39/2/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ስለመሆኑ የመመሪያው መግቢያ ዐረፍተነገር ያመለክታል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 39/2/ የተመለከተው ድንጋጌ የሚያስገነዝበን ስለወርቅና ስለውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ባንኩ መመሪያ ማውጣት ስለመቻሉ ነው፡፡ ከዚህ ድንጋጌ እና ከአዋጅ

አጠቃላይ መንፈስ መረዳት የሚቻለው የገንዘብ እና የወርቅ ሥራ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ያለውን አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት በመመልከት በተለየ ሁኔታ ሥርዓት እንዲበጅለት እና ቁጥጥር እንዲደረግበት የታሰበ ስለመሆኑ ነው፡፡ ይህንንም ለማሳለጥ ይቻል ዘንድ በአዋጁ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች በተጨማሪ ባንኩ በዝርዝር መመሪያ ሊወሰን እንዲችል ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም መመሪያው በአንቀጽ 1 እና 2 ስለወርቅ ንግድና ዝውውር መያዝ ወይም ማኖር የባንኩ ፈቃድ አስፈላጊነት እና የመጠኑም ገደብ አስመልክቶ ድንጋጌ ይዟል፡፡ ይህ ድንጋጌ ሲጣስ በየትኛው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚሰጠው ደግሞ ራሱ ዋናው አዋጅ ሆኖ እናገኛለን፡፡ ይህም አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(1)(ሸ) ላይ እንደተመለከተው አዋጁን ወይም አዋጁን ተከትሎ የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የተላለፈ ሰው የሚቀጣበትን አግባብ ደንግጓል፡፡ ስለሆነም የወንጀል ተጠያቂነትን አስመልክቶ የተደነገገው በአዋጁ መሠረት መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከዚህ አንፃር በመመሪያው የተመለከተውን ገደብ በመተላለፍ ለተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ተጠያቂነት በአዋጁ በተመለከተው አግባብ የሚፈፀም በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ ላይም መመሪያው ተፈጻሚነት አለው ብለናል፡፡

መመሪያው ተፈጻሚነት አለው ካልን በኋላ በተጠሪ ተፈፀመ የተባለው ድርጊት በዚህ መመሪያ የሚሸፈን ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ በተጠሪ ላይ ሥር ፍ/ቤት በአማራጭ የቀረበው ክስ በባንኩ የወጣውን መመሪያ በመተላለፍ ያለባንኩ ፈቃድ ከአሥር(10) አውንስ በላይ ወርቅ ሲያዘዋውር ተገኝቷል የሚል ሲሆን ተጠሪም በክሱ የተጠቀሰውን 46.96 ኪ.ግ ወርቅ ይዞ መገኘቱን አልካደም፡፡ ይልቁንም ጎንደር ከተማ ለሚገኝ ደንበኛው የሸጠ መሆኑንና ወደዚያው እንዲጓጓዝ ማድረጉን የእምነት ቃሉን ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም በፍሬ ነገር ረገድ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠው ባንኩ ካወጣው መመሪያ ውጭ ያለባንኩ ፈቃድ እውቅና ከፍተኛ ዋጋ ያለው የወርቅ መጠን ማዘዋወሩና ስለመያዙ ነው፡፡ ይህ ድርጊቱ በመመሪያው አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተውን ክልከላ የተላለፈ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡ ስለዚህም የተጠሪ ድርጊት በመመሪያው የሚሸፈንና የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ሆኖ አግኝተናል፡፡

ተጠሪ የፈፀመው ድርጊት በአዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 39/2/ ለባንኩ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የወጣውን መመሪያ ቁጥር ሲቲጂ 001/97 አንቀጽ 1 እና 2 የተላለፈ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 59/1//ሸ/ መሠረት ጥፋተኛ የሚያሰኝና ቅጣት የሚያስከትል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የቅጣት አወሳሰን በተመለከተ በዐ/ህጉ በሥር ፍ/ቤት በቀረበው ክስ እና የመ/ደረጃ ፍ/ቤት ከወንጀሉ አፈጻጸም ባህሪይ እና ከተፈፀመው ድርጊት ዓላማና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ከደረሰ ጉዳት አንፃር በአዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(2)(ለ) ሥር በተመለከተው አግባብ የተወሰነው ጥፋተኛነት እና ቅጣት ዓይነትና መጠን መሠረታዊ የሕግ ጉድለት አለው ለማለት የሚያስችል የሕግ ምክንያት ስላላገኘንበት ባለበት እንዲፀና ብለናል፡፡

የተጠሪ ጥፋት እና የቅጣት አወሳሰን በአዋጅ ቁ.83/86 እና በመመሪያው የተሸፈነ መሆኑን ከፍሲል ስለተመለከትን ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ /የ1949 ዓ.ም ወ/መ/ሕግ/ አንቀጽ 357 እና 358 አንፃር ለመመርመር የተያዘው ጭብጥ መመርመር አስፈላጊ ስላልሆነ አልፈነዋል፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ በአማራጭ በቀረበበት ክስ ጥፋተኛ አይደለም ሲሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከፍሲል በዝርዝር በተመለከቱት ምክንያቶች መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ በዚሁ መሠረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይ/ወ/መ/ቁ 56547 ሐምሌ 23 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/መ/ቁ 32664 ህዳር 26 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)ሀ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ 46204 ግንቦት 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ እና ቅጣት ፀንቷል፡፡

3. ተጠሪ ላይ የተሰጠው የእስራት ቅጣት በዚህ ወንጀል እስከ አሁን የታሰረው ታሳቢ ተደርጐ ቀሪው እንዲፈፀምበት ብለናል፡፡ የፌዴራል ፖሊስ ተጠሪን ይዞ ለማረሚያ ቤት እንዲያስረክብ እና ማረሚያ ቤቱም ይህንኑ እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የገንዘብ መቀጮ እና የሚወረሰውን ንብረት በተመለከተ አመልካች ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ብለናል፡፡ ይፃፍ

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 42239

ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ
ሓጎስ ወልዱ
ተሻገር ገ/ሥላሴ
በላቸው አንሺሶ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡-ብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኃላ.የተ. የግል ኩባንያ
ተጠሪ፡- ዳኒ ድሪሊንግ ኃላ.የተ. የግል ኩባንያ

*መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡*

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወርቅ ማዕድን ፍለጋ የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ውል ስምምነትን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በግልግል ዳኝነት ጉባኤ ነው፡፡ በአመልካችና በተጠሪ የተቋቋመው የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ/ም በሠጠው ውሣኔ አመልካች ለተጠሪ ብር 579,450.35(አምስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ብር ከሠላሣ አምስት ሣንቲም) እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ይህንኑ ውሳኔ አመልካች በመቃወም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 351 መሠረት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሠርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ታኅሣስ 17 ቀን 2001 ዓ/ም በፃፉት አራት ገፅ የሠበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሣኔ በፍሬ ነገር እና በሕግ ረገድ ተፈፀሙ የሚሉባቸውን ስህተቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ በራሱ አነሳሽነት ውሉን ባቋረጠበትና ዉሉን ለማቋረጥ በቂ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ተጠሪ ስራ ለፈታበት ሰላሳ አምስት ቀናት ብር 700,000. 00 ቅጣት አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ የውልም ሆነ የሕግ መሠረት የሌለው መሆኑን፣የግልግል ጉባኤ ዳኝነቱን የመራው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 317(1) ስር በተመለከተው ሣይሆን ከዚህ ውጪ ተገቢውን ጭብጥ ሣይይዝ መሆኑን፣ውሣኔው በፍትሐብሔር ሕጉ የተመለከቱትን የውል አተረጓጎም ድንጋጌዎችን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ መሆኑን፣ተጠሪ በወቅቱ ማስጠንቀቂያ ባልሰጠበት ሁኔታም ቅጣት መጠየቅ እንደማይችል፣ተጠሪ ውሉ አልተፈፀመልኝም የሚል እንደመሆኑ መጠን ሊደርስ የሚችለውን ኪሣራ ለመቀነስ በሕጉ ግዴታ ያለበት ሲሆን ጉዳት ሳይደርስበት ቅጣት እንዲከፈለው መጠየቁ ያላግባብ መሆኑንና በውሉ ላይ ዓይነተኛ መጣስ የሌለ ስለሆነ ውል እንዲፈርስ ዳኞች ውሣኔ ማሳለፍ እንደማይችሉ፣እንዲሁም በጉዳዩ የተሠጠው ውሣኔ የቀረቡትን ማስረጃዎችን በሚገባ ያልመዘነ መሆኑን በሰፊው በመዘርዘር የግልግል ዳኞችና ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሠጡት ውሣኔ በማስረጃ ምዘናም ሆነ በሕጉ አተረጓጎም እንዲሁም አፈጻጸም ረገድ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ ሊሻር ይገባዋል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮም ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ ጠበቃው መጋቢት 01 ቀን 2001 ዓ/ም በተፃፈ አራት ገፅ ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡ የመልሱ ይዘትም የጉባኤው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑን 23-05-1998 ዓ/ም ግራ ቀኙ በፈፀሙት ውል የተስማሙ መሆኑን ገልፀው ለሠበር ችሎቱ የሠበር አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለሆነ በዚህ ምክንያት ችሎቱ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ እንዲያደርግ፣ይህን የሚያልፍ ከሆነም ለአቤቱታው መሠረት የሆኑት የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ክርክሮች ተቀባይነት የሌላቸው በመሆኑ ውድቅ ሊደረጉ ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው የሠበር ችሎቱ ጉዳዩን ለማየት ሕገ-መንግስታዊ ሥልጣን ያለው መሆኑን በመዘርዘር የተጠሪ ጠበቃ መቃወሚያ የሕግ መሠረት የለውም በማለት የተቃወሙ ሲሆን ሌሎችን ነጥቦችን በተመለከተም የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር መጋቢት 18 ቀን 2001 ዓ/ም በተፃፉት የመልስ መልስ ማመልከቻ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልጉት አበይት ጭብጦች፡-

1ኛ/ ግራ ቀኙ ባደረጉት ስምምነት መሠረት አመልካች ቅሬታውን ለሠበር ችሎት ለማቅረብ ይችላል? ወይስ አይችልም?፣

2ኛ/ አመልካች ለሰላሳ አምስት ቀናት የጉዳት ካሳ ለተጠሪ እንዲከፈል ተብሎ የተወሰነው የውሳኔ ክፍል በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው ውል መሰረት አመልካች ግዴታውን ስለአለመወጣቱ ተጠሪ አስረድቶ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ሲሆን ሌሎች ነጥቦች በዚሁ ጭብጥ ስር እልባት ሊያገኙ የሚችሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

**<u>1.የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፡- ይህን** ጭብጥ ለመመለስ በአገራችን ውስጥ የሰበር ስርኣት እና ስለአማራጭ ሙግት መፍቻ ዘዴዎች አላማና በሕጉ ያላቸውን ማእቀፍ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

የሰበር ስርዓት አይነተኛ አላማ ከሆኑት አንዱ በአንድ ሀገር ውስጥ ወጥ የሆነ የሕግ አተረጎጎም እና አፈጻጸም(Uniform interpretation and application of the law ) መኖሩን ማረጋገጥ መሆኑ እሙን ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሰበር ሥርዓት የሕግ የበላይነት ማረጋገጫ ዘዴ ነው ተብሎም ሊታሰብ የሚችል ነው፡፡ የሕግ የበላይነት በሰበር ሥርዓት ሊከበር ወይም ሊረጋገጥ የሚችለው ደግሞ ጥራት፣ወጥነት ያለው ፍርድ/ ውሳኔ ለመስጠት ሥልጣን በተሰጣቸው አካለት በሰጡት ውሳኔ ላይ የዳኝነት አካሉ በራሱ ዳኝነታዊ ቁጥጥር(Judicial Control) ሲኖረው መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተመሳሳይ ጉዳዮች በተመሳሳይ መንገድና ሁኔታ ማየትን የፍትሕ አሰጣጥ ሥርዓት የግድ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የፍትሕ መሰረቱ ተመሳሳይ ጉዳዮችን በተመሳሳይ መንገድ ማስተናገድ ነው ተብሎም ይታሰባል፡፡ ይህ የሚተገበረውም አዋጆች፣ደንቦችና መመሪዎች እንዲሁም ፖሊሲዎች በትክክልና በወጥነት ሲተረጎሙና ሲፈጸሙ ነው፡፡ ወጥነትና ትክክለኛነት ያለው የሕጎች አተረጎጎምና አፈፃፀም መኖሩ የሚረጋገጠው ደግሞ በዳኝነት አካሉ በመጨረሻ ደረጃ በሚገኝ በሰበር ተቋም ነው፡፡

ሌላው ጉዳይ የሕጎች ወጥነት ያለው አተረጎጎምና አፈፃፀም መኖር የዜጎችን በሕግ ፊት እኩል የመሆን መብት የሚጠበቅ መሆኑ የሚታመን ሲሆን የዳኝነት አካሉ የዜጎችን በሕግ ፊት እኩል የመሆን መብት የማክበርና የማስከበር ሕገ-መንግስታዊ ግዴታ የመወጣት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ደግሞ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 13(1)፣ 25 እና 85(1) ድንጋጌዎች ስር ከአሰፈረው ሁኔታ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የሰበር ሥርዓት ይህንኑ ግዴታ የዳኝነት አካሉ የመወጣቱን ሁኔታ የሚቆጣጠርበት መሆኑም የሚታመን ነው፡፡ ሌላው በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ ተቀባይት ያለው ጉዳይ የሕግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ፀንቶ ሊቆይ የማይገባው ጉዳይ መሆኑ ነው፡፡ የሕግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ፀንቶ እንዲቆይ ማድረግ በዳኝነት አካሉ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ያስከትላል፡፡ ምክንያቱም የሕግ ስህተት ያለበትን ውሳኔ ጸንቶ እንዲቆይ ማድረግ ሕብረተሰቡ በዳኝነት አካሉ እምነት እንዳይኖረው የሚያደረግ ነውና፡፡ በመሆኑም የሰበር ሥርአት የሕግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ፀንቶ እንዳይቆይ በማድረግ የዳኝነት አካሉ በሕብረተሰቡ ዘንድ የሚታመን፣ከበሬታ የተቸረው እንዲሆን ያደርጋል፡፡

ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው የሰበር ሥርአት ለሕግ ስርዓቱ፣ለዳኝነት አካሉና ለሕግ የበላይነት መረጋገጥ ተብሎ የሚቋቋም መሆኑን ነው፡፡ ይህ ስርአት በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት ውስጥ ተካቶ ለረዥም ጊዜያት ሲሰራበት የቆየ ሲሆን በ1987 ዓ/ም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት በአንቀፅ 83 ስር ተመልክቶ ከመገኘቱም በላይ ዝርዝሩ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 እና አዋጅ ቁጥር 454/97 የተደነገገለት ሥርዓት ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀፅ 80 ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ ስር የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን እንዳለው ሲደነግግ በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር ደግሞ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልሉ ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል ሲል ደንግጓል፡፡ ሕገ-መንግስቱ በፌዴራልና በክልል ጉዳዮች የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ያላቸውን ፍርድ ቤቶች ለይቶ ካስቀመጠ በኂላ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ስልጣን ያለው መሆኑን በአንቀጽ 80(3(ሀ)) ስር ደንግጓል፡፡ ሰበር ችሎት ይህ ስልጣን የተሰጠው ከላይ የተመለከቱትን አላማዎች ለማሳካት መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ በተለይ አዋጅ ቁጥር 454/1997 ሲታይ ከአምስት ያላነሱት ዳኞች በተሰየሙት ችሎት የሚሰጥ የሕግ ትርጉም ይኸው ችሎት ራሱ በሌላ ጊዜ እስካልለወጠው ድረስ በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤት ላይ የአስገዳኝነት ኃይል(Precedence) ያለው ስለመሆኑ በአንቀፅ 2(4) ስር አስቀምጧል፡፡ ይህም የሰበር ስርዓት በዳኝነት ስልጣን ተዋረድ በመጨረሻ እርከን ላይ ሆኖ ሕጎች በትክክልና በወጥነት መተርጎማቸውንና መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል፣ለተከራካሪ ወገኖች ጥቅም ወይም መብት ብቻ ሳይሆን ለዜጎች ጥቅም ተብሎ የተዘረጋ ሥርአት ወይም አሰራር መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ሰበር ሕጋዊ ያልሆኑ ውሳኔዎች የሚሰበሩበት ወይም ጸንተው እንዳይቆዩ የሚደረግበት ሥርአት ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ሰበር መደበኛ የይግባኝ ማቅረቢያ አሰራር ሳይሆን ፍርድ ቤቶች በውሳኔዎቻቸው ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል በሚባልበት ልዩ ሁኔታ ብቻ የሕጉ አተረጎጎም ወይም አተገባበር የሚቃናበት ወይም የሚታረምበት ሥርዓት ነው፡፡ በዚህም ሥርአት የሕግ አንድ ወጥ አተረጎጎምና አፈፃፀም በፍርድ ቤቶች ሁሉ ይረጋገጣል፡፡

ወደ አመራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች አላማ ስንመለስ ደግሞ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን ከፍርድ ቤት ውጪ በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ የመስማማት መብት ያላቸው መሆኑን ያሳዩናል፡፡ የግልግል ዳኝነት የሚቋቋምበት አይነተኛ አላማ ተካራካሪዎቹ ወገኖች ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት በመሄድ የሚያጠፉትን ጊዜና ገንዘብ ለማስቀረት መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ጉባኤው የሚቋቋመውም በተካራካሪ ወገኖች ስምምነት ሲሆን ተካራካሪዎቹ ባላቸው የመዋዋል ነፃነት ጉዳያቸውን ከፍርድ ቤት ውጪ በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ የሚስማሙት ሁኔታ መኖሩ በራሳቸው ፍላጎትና ምርጫ የተቋቋመው ጉባኤ በተገቢው ጊዜና በአነስተኛ ወጪ ጉዳያቸውን ለመወሰን ይችላል የሚል እምነት ኑራቸው ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 3325 እስከ 3346 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንዲሁም በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከቁጥር 315-319 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ይህንኑ የሚያስገነዝቡን ሲሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 350(2) በተለይ ሲታይ ደግሞ ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ጉባኤ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል በሚል ለመስማማት መብት ያላቸው ስለመሆኑ ያስረዳናል፡፡ በዚህ ሁኔታ ስምምነት ከተደረሰም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 356 ስር በተመለከቱት ሁኔታዎች በስተቀር የጉባኤው ውሳኔ በፍርድ እንዲሻርላቸው ለመጠየቅ እንደማይችሉ ተደንግጓል፡፡ ይህ ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ ስምምነት ያላቸው ከሆነ የሚፈፀም ስነ ስርዓት ሲሆን ስምምነት ባይኖርም ይግባኝ የሚቻለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 351 ስር በተመለከቱት ውስን ምክንያቶች ብቻ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 351"ም" ሆነ 356 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ሲታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለው የግልግል ጉባኤ ውሳኔ በሰበር ስርዓት የሚታይበት አግባብ ስለመኖሩ አይጠቁምም፡፡ በሌላ አገላለፅ ድንጋጌዎች የሚያወሱት በግልግል ታይቶ የተወሰነ ጉዳይ በይግባኝ የሚታይበትን ሥርዓት ብቻ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 3325 እስከ 3346 ድረስ በተመለከቱት ድንጋጌዎችና በፍትሓ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በግልግል ለመጨረስ መሰረቱ ሕጋዊ ውል መኖሩ ሲሆን ውል ደግሞ የተከራካሪ ወገኖች መብትና ጥቅም ማስገኛ ምንጭ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ውሉ መብትና ጥቅም የሚሰጠው ለተዋዋይ ወገኖች ወይም መብትና ጥቅሙ በሕጉ አግባብ ለተላለፈላቸው ለሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ነው(የፍ/ህ/ቁጥር 1731 እና 1957 ይመለከቷል)፡፡እ ንዲሁም ተዋዋይ ወገኖች ጉዳያቸውን ከፍርድ ቤት ውጪ ለመጨረስ መብት ያላቸው መሆኑ በሕጉ ተቀባይነት ያለው ሲሆን ሕጉ ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ ያላቸውን ሚናም ደንግጓል፡፡

እነዚህ ድንጋጌዎች በ1952ቱ የፍትሐብሔር ሕግና በ1958ቱ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕጋችን ውስጥ ያሉት ሲሆኑ ከእነዚህ ሕግጋት በኋላ የወጡት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስትና አዋጅ ቁጥር 25/1988 እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 454/97 ስለሰበር ሥርዓት ደንግገው እናገኛለን፡፡

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ስልጣን ያለውና የሚሰጠው የሕግ ትርጉምም በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት እስካልተለወጠ ድረስ የፌዴራልንም ሆነ የክልል ፍርድ ቤቶችን የሚያስገደድ መሆኑ በሕጉ የተቀመጠና አላማው በአገሪቱ ወጥ የሆነ የሕግ አተረጓጎምና አፈጻጸም እንዲኖር ማረጋገጥ ነው ከተባለ ተከትሎ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ከሆኑት አንዱ በሆነው በግልግል ዳኝነት (arbitration) ጉዳዩ ቢታይና ይኸው አካል በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የሌለው የመጨረሻ ስለመሆኑ(Arbitration Finality Clause) ተከራካሪ ወገኖቸ ገልፀው ስምምነት ቢያደርጉ ጉዳዩ በሰበር ሊታይ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለው ነው፡፡ ይኸው ጥያቄም ስለሰበር ሥርዓት አላማና ከሕጎዎቹ አወጣጥ ቅደም ተከተል እንዲሁም በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ውስጥ ፍርድ ቤቶች በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ላይ ካላቸው ሚና አንፃር ታይቶ ምላሽ የሚሰጠው ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከላይ እንደተመለከተው የሰበር ሥርዓት ዓላማ ወጥ ለሆነ የሕግ ትርጉም እና አፈፃጸም ከፍተኛ ሚና መጫወት ሲሆን ይህንንም በ1987ቱ ሕገ-መንግስትም ሆነ ይህንኑ ተከትለው ከወጡ አዋጆች(25/1988 እና 454/97) የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ እነዚህ አዋጆች ከ1958ቱ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ በሁዋላ የወጡ ሲሆን ተቀባይነት ባለው የሕግ አተረጓጎም ደንብ መሰረትም ከ1958ቱ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ቅድሚያ ተፈጻሚነት ያላቸው ናቸው፡፡ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች በኢትዮጵያ የሕግ ስርዓት ውስጥ ተካተው የሚገኙ ሲሆን እነዚህን የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ፍርድ ቤቶች የሚያበረታቱበት ሁኔታ እንዳለ ሁሉ የሚቆጣጠሩበት አጋጣሚም ያለ መሆኑን ከላይ የተመለከቱት የፍትሓ ብሔር ሕጉም ሆነ የፍትሓ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የአንድ ጉዳይ ለሰበር የመቅረብ ሁኔታ በሕገ መንግስቱ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠ በመሆኑ ሥርዓቱ ሊጫወተው ከተፈለገው አቢይ አላማ አንፃር ሲታይ ጉዳያቸው በግልግል ዳኝነት እንዲታይላቸው የተስማሙበት ወገኖች የግልግል ዳኝነቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው በማለት ስለተስማሙ ብቻ ጉዳዩ በሰበር ሥርዓቱ እንዳይታይ ፍላጎት አሳይተዋል ተብሎ መሰረታዊውን የሕግ ስህተት ላለማረም ምክንያት ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 21849 በቀረበው ጉዳይ ሁለት ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት( Arbitration) ለመጨረስ ከተዋዋሉና የግልግል ዳኝነት ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል በማለት በውላቸው ላይ ከተስማሙ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ውሳኔ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ አይገባም በማለት የሠጠው ውሳኔ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997

አንቀፅ 2(4) መሰረት መለወጥ ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የአመልካች አቤቱታ በሰበር ችሎት ሊቀርብና ሊታይ የሚገባ አይደለም በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

**2.ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-**

ተጠሪ ውሉን ማቋረጡን ሳይክድ የሰላሳ አምስት ቀናት ቅጣት አመልካች እንዲከፍለው ዳኝነት የጠየቀውንና የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ብር 700,000.00(ሰባት መቶ ሺህ) አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ውሳኔ ያሳረፈው በአመልካችና በተጠሪ መካከል በጥር 23 ቀን 1998 ዓ/ም የወርቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ውል ተፈፅሞ፣ቅድሚያ ክፍያ በየካቲት 09 ቀን 1998 ዓ/ም ተከፍሎ ስራው መጀመር ከሚገባበት ቀን ሰላሳ አምስት ቀናት በመዘግየት በ30–7-1998 ዓ/ም ለመጀመሩ ምክንያቱ አመልካች ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ነው፡፡ አመልካች በዚህ ረገድ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን ገልፆ የሚከራከረው የማዕድን ፍለጋ ጉድጓድ ቁፋሮ ወደሚካሄድበት ቦታ የሚያድረሰውን ለተሽከርካሪ እንቅስቃሴ አመቺ የሆነ መዳረሻ መንገድ የማዘጋጀት ኃላፊት የራሱ መሆኑ በውሉ መገለጹን ሳይክድ ይህንኑ ግዴታ ለመወጣት ቡልዶዘሩን ከተጠሪ መከራየቱን፣ሆኖም በሁለት ቀናት ውስጥ ቡልዶዘሩን ወደ መቀሌ ለማጓጓዝ የሚያስችል መኪና አዘጋጅቶ ለማስጫን በሚሄድበት ጊዜ የቀረበው ቡልዶዘር ለታቀደው ስራ ብቃት የሌለው መሆኑ በአመልካች ኤክስፐርት በመረጋገጡና ይህ ሁሉ ሲደረግ ተጠሪ የወሰዱት አንዳችም እርምጃ የለም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክር የአመልካች ክርክር በስር የግልግል ዳኝነት ያልተነሳ ነው በማለት ከመከራከር ውጪ ከላይ የተመለከተው ግዴታ በግራ ቀኙ መካከል መገባቱን በግልፅ አይክድም፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በስር የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ከላይ የተመለከተውን ክርክር ያነሳ መሆኑን የግልግል ጉባኤ ውሳኔ ግልባጭ በገጽ 3 እና 4 ያሰፈረው በመሆኑ ተጠሪ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1)መሰረት በማድረግ ያነሳው ተቃውሞ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር ውድቅ ሆኖ ለሰላሳ አምስት ቀናት የቅጣት ገንዘብ እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ስንመለከተው ደግሞ ምላሹ ከግራ ቀኙ ውል፣ክርክርና ስለውሎች አተረጓጎም በጠቅላለው በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጥር 23 ቀን 1998 ዓ/ም የተደረገው ውል አመልካችን ለባከነ ጊዜ ክፍያ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ በአንቀጽ 4፣3.11 እና 9.1 ስር ካስቀመጣታቸው ድንጋጌዎች እንገነዘባለን፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት አመልካች ለተጠሪ ኃላፊነት የሚኖረው የመቆፈሪያው መሳሪያ ከአመልካች ጋር በተያያዘ ኃላፊነት ያለስራ ቢቀመጥ ስለመሆኑ ተቀምጧል፡፡ድንጋጌዎቹ በግልፅ እንደሚያሳዩት የባከነ ጊዜ ክፍያ(Idle time Payment) የመቆፈሪያው መሳሪያ በስራ ላይ እያለ ውል ሰጪ በሆነው አመልካች ምክንያት ቢቆም፤መሳሪያው ስራ ለመስራት እየቻለ ቁሞ ያላግባብ ለጠፋው ጊዜ፣አመልካች ኃላፊ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በሌላ አገላለፅ የመቆፈሪያ ማሽን(Rig) በስራው ቦታ ላይ ተገኝቶ በአመልካች ምክንያት ስራ ቢፈታ አመልካች ኃላፊነቱን የሚወሰድ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ለሰላሳ አምስት ቀናት ስራ ፈታሁ ይበል እንጂ በአመልካች ምክንያት ስራ መፍታቱን በፍሬ ነገር ደረጃ አልተረጋገጠም፡፡ ተጠሪ ስራውን የፈታሁ በአመልካች ምክንያት ነው ብሎ እስከተከራከረ እና አመልካችም ለመሳሪያው መቆም ምክንያት የሆነው ድርጊት በራሱ በኩል የተፈጸመ አለመሆኑን ገልፆ እስከተከራከረ ድረስ ክሱን የማስረዳት ሸክም ከሳሽ የሆነው ወገን የተጠሪ ግዴታ ነው፡፡ የመቆፈሪያው መሳሪያ ከስራ ቦታ አለመድረሱ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የግልግል ጉባኤው አመልካችን መሳሪያው ስራውን ለፈታበት ጊዜ ኃላፊነት አለበት በማለት ውሳኔ ላይ የደረሰው ከላይ የተጠቀሱትን የውሉን ድንጋጌዎች በመጥቀስና መቆፈሪያ መሳሪያ ወደ ስራ ቦታ ተጓጉዞ የሚሄድበትን መንገድ አመልካች ሊያዘጋጅ አልቻለም፣የዶዘር ኪራይ ውልን መሰረት በማድረግ ክስ አልመሰረተም በሚል ነው፡፡ ሆኖም ተጠሪ ስራውን ከሚያዚያ 01 ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ መስራት እንደሚችል በፁሑፍ ተነግሮት ሚያዚያ 12 ቀን 1998 ዓ/ም ስራው መጀመሩ፣የሰላሳ አምስት ቀናት ጊዜ ባክኗል የተባለው ደግሞ ከየካቲት24 ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ እስከ መጋቢት 30 ቀን 1998 ዓ/ም ድረስ ስለመሆኑ በስር ክርክር የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የመቆፈሪያ ማሽኑ ወደ ስራ ቦታው በመሄድ በአመልካች ምክንያት ስራውን መስራት ያልቻለ መሆኑን ሳይሆን ከመነሻውም መቆፈሪያ ማሽኑ ወደ ስራ ቦታ ያልተጓጓዘ መሆኑን ነው፡፡በግራ ቀኙ ውል አንቀፅ 3.11 ስር የተቀመጠው ድንጋጌ የመቆፈሪያ መሳሪያ ከአሰሪው ጋር በተያያዘ ኃላፊነት ያለስራ ቢቆም ....በሚል ሐረግ የተቀመጠ ሲሆን ይህም ድንጋጌ በግልጽ መሳሪያው ከስራ ቦታ መድረሱንና ደርሶ ስራ መስራት እየቻለ በአመልካች ምክንያት ስራውን ሳይሰራ ቢቀር አመልካች ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ግልፅ ውል ሊተርጎም የማይገባ መሆኑን ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1733 ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ የግልግል ጉባኤ ውሉ ግልፅ ሆኖ እያለ እና ተጠሪ አመልካች ለባከነው ጊዜ ምክንያት መሆኑን ባላስረዳበት ሁኔታ የተጠሪን የማስረዳት ሸክም ወደ አመልካች በማዞር አመልካች ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት የደረሰበት መሆኑን አላስረዳም በማለት ለባከነ ጊዜ ቅጣት እንዲከፍል ሲል የሠጠው የውሳኔ ክፍል የግራ ቀኙን ክርክርና የውል ይዘት በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች ስለማስረዳት ሸክም የተቀመጡትን ሥርዓቶች፣በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 1732 እስከ 1738

ድረስ ስለውሎች አተረጎጎም ከተመለከቱት ደንቦች ጋር ያላገናዘበና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም አመልካች መቆፈሪያ ማሽኑ ስራ ሳይሰራ በመቆሙ ምክንያት ባከነ ለተባለው ለሰላሳ አምስት ቀናት ብር 700,000.00(ሰባት መቶ ሺህ ብር የሚከፍልበት ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ በዚህ ረገድ የተሰሠጠው የውሳኔ ክፍል ሊለወጥ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ለተጠሪ በውሉ መሰረት ለተከናወኑ ስራዎች መከፍል አለባቸው ተብለው የታሰቡት፤የሞቢላዜሽን ሂሳብ( ብር 90,000.00)፣ለ661.77 ሜትር ጥልቀት ጉድጓድ ቁፋሮ ሂሳብ(ብር 704,124.00)፣ለኬዚንግ ስራ(ብር138,000430.00)፣ለቁፋሮ ስራ ከጉድጓድ ወደ ጉድጓድ ለተደረገ እንቅስቃሴ የሚታሰብ(ብር 4,150.00)፣ስራ ላይ ለዋለ አምስት ከረጢት ሲሚንቶ የሚታሰብ(ብር 750.00)፣ከውሃ ቦቴ ኪራይ የሚታሰብ(50,000.00)እና የዶዘር ኪራይ(ብር 3,818.40) በጠቅላላ ድምር ብር 991,272.40(ዘጠኝ መቶ ዘጠና አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከአርባ ሳንቲም) ተጨማሪ እሴት ታክስ ተጨምሮበት ብር 1,139,962.86 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰላሳ ዘጥ ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ሁለት ብር ከሰማኒያ ስድስት ሳንቲም)እንዲከፍል የተወሰነውን የውሳኔ ክፍል ስንመለከተው በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን ውል፣ክርክርና ማስረጃ መሰረት አድርጎ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች የሰበር ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አመልካች ክፍያ ለዘገዪበት ብር 40,321.60(አርባ ሺህ ሶስት መቶ ሃያ አንድ ብር ከስልሳ ሳንቲም) ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑም ፍሬ ነገርን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊታይ የሚገባው ባለመሆኑ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

ሌላው አመልካች ተጠሪ ውሉን በራሱ ጊዜ አቋርጦ መሄዱ ያላግባብ ነው በማለት በተከሳሽ ከሻስነት በግልግል ጉባኤው ያቀረበው ክርክር የታለፈው ባግባቡ አይደለም በማለት የሚከራከርበትን ነጥብ ስንመለከተውም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1786 እና 1788 ድንጋጌዎች አንጻር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ በግልግል ጉባኤ ታይቶ በሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑን አንድ ተከራካሪ ወገን ቢስማማም ጉባኤው በሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ቅሬታውን ለሰበር ችሎቱ ከማቅረብ የሚከለከል ባለመሆኑና ጉባኤው አመልካች የሰላሳ አምስት ቀናት መቆፈሪያው ያለስራ ለቆመበት አመልካችን ተጠያቂ ያደረገበት አግባብ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ በመገኘቱ፣እንዲሁም ጉባኤው ወጪና ኪሳራ ያሰላበት አግባብ ይህ ችሎት ለአመልካች የሚቀንሰውን የገንዘብ መጠን መሰረት ባደረገ መንገድ የሚሰራ ሆኖ በሌሎች ነጥቦች ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሣኔ

1.ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 21849 በቀረበው ጉዳይ ሁለት ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት( Arbitration) ለመጨረስ ከተዋዋሉና የግልግል ዳኝነት ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል በማለት በውላቸው ላይ ከተስማሙ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ውሳኔ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ አይገባም በማለት የሠጠው ውሳኔ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2(4)መሰረት ተለውጧል፡፡

2 ሁለት ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት(Arbitration) ለመጨረስ ከተዋዋሉና የግልግል ዳኝነት ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል በማለት በውላቸው ላይ ከተስማሙ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ውሳኔ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ የሚችል ነው ብለናል፡፡

3.አመልካች ለተጠሪ የሰላሳ አምስት ቀናት ቅጣት የተባለውን ብር 700,000.00(ሰባት መቶ ሺህ ብር) ለተጠሪ ለመክፈል የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት በዚህ ረገድ የግልግል ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ሽረነዋል፡፡

4.ወጪና ኪሳራን በተመለከተ የግልግል ጉባኤው የሰጠው የውሳኔ ክፍል አመልካች ብር 700,000.00(ሰባት መቶ ሺህ ብር) ለተጠሪ ሊከፍል አይገባም ተብሎ በዚህ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ ግንዛቤ ባስገባና በጉባኤው ስሌት መሰረት የሚሰራ ሁኖ በወጪና ኪሳራ፣በጠበቃ አበል እንዲሁም በሌሎች ነጥቦች ላይ የግልግል ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

5.በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

*መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡*

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

<u>የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎችን /ከቅጽ 1 - 7 / ዝርዝር የሚያሳይ ሰንጠረዥ</u>

**ቅጽ - 1**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 18180 | የኬ.ኬ ብርድ ልብስ ፋብሪካ መሰረታዊ ሰራተኞች ማህበር እና የኬ.ኬ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ | የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የዳኝነት ስልጣን፣ የሰራተኛ ቅነሳ ጉዳይን በሚመለከት ስለሚነሳ ክርክር<br>አዋጅ ቁ.42/85 አንቀፅ 138(1),147 | ሐምሌ 29/1997 |
| 2 | 15493 | አቶ ጳውሎስ ሩምቾ እና ወ/ሮ ጫልቱ መርዳሳ | በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845,2024 | ሐምሌ 29/1997 |
| 3 | 17361 | ወ/ሮ ጋዲሴ ኢርጌ እና ወ/ሮ ወርቅአንጥፉ በቀለ | በስነ-ስርዓት ህጉ የጊዜ ገደብን በሚመለከት የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነት ተፈፃሚ ስለማድረጉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.49, የፍ/ብ/ህ/ቁ.1856 | ሐምሌ 25/1997 |
| 4 | 17352 | ዋዜማ የልብስና ሽራ ምርቶች ኃ/የተ/ የግ/ ማህበር እና የነገው ሰው ትምህርት ቤት | ተገቢው ዳኝነት ክፍያ ሳይፈፀም በፍ/ቤት በቀጠለ ክርክር ስለሚፈፀም ስርዓት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.215,320(2),207,211(2) | ሐምሌ 28/1997 |
| 5 | 14605 | የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት እና እነ ኮሜት ትራንስፖርት ድርጅት (ስድስት ሰዎች) | በመጓጓዝ ላይ የነበሩ ዕቃዎች መጓዳት በሰው ላይ ሊደርስ ይችል የነበረን የግጭት አደጋ ለማስወገድ በተወሰደ ርምጃ የደረሰ የመኪና መገልበጥ ከዓቅም በላይ በሆነ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ስላለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 590,591, የፍ/ብ/ህ/ቁ.1792 | ሐምሌ 29/1997 |
| 6 | 17068 | የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና ሚ/ር ቢሮኒ አቲክፖ | በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ የህግ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1856,2024, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 89 | ሐምሌ 19/1997 |
| 7 | 14974 | ወ/ት ማህሌት ገ/ስላሴ እና እነ አቶ መንግስቱ (ሁለት ሰዎች) | አንድ ተወካይ በወካዩ ላይ ባቀረበው ክስ ወካዩን ወክሎ መከራከር ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2188, 2189, 2208, 2209, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 57,58 | ሐምሌ 28/1997 |
| 8 | 14184 | አቶ ውርጌሳ ታደሰ እና እነ አቶ መለስ ተካ (ዘጠኝ ሰዎች) | ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን የከሳሽ አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73 | ሐምሌ 29/1997 |
| 9 | 14047 | ዶ/ር ዳንኤል አለሙ እና እነ ወ/ሮ ሮማን ወርቅ የማነብርሃን (ሦስት ሰዎች) | በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ የህግ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1856, 2024 | ሐምሌ 28/1997 |
| 10 | 15835 | ሼል ኢትዮጵያ አ/ማ እና ወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ | ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን የተከሳሽ አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70,233 | ሐምሌ 29/1997 |
| 11 | 15992 | የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና ወ/ት ሶስና አስፋው | በህግ የተደነገገው የውል አፃፃፍ /ፎርም/ የተቀመጠ ደንብ አለመፈፀም ስለሚያስከትለው ውጤት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719, 1720 (1), 1723, 1726, 1727, 1845 | ሐምሌ 19/1997 |
| 12 | 17191 | ወ/ሮ አስቴር አርአያ እና አቶ ግርማ ወይጆ | በአንዳንድ ውሎች የተመለከተን የአገልግሎት ክፍያ መጠን ለመቀነስ ፍ/ቤት ስላለው ስልጣን<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1711, 1731, 1676(2), 2635, 2640, 2646 | ሐምሌ 29/1997 |

**ቅጽ 2**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 13 | 13223 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ አስፋው አበበ | ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በተከራካሪ ወገኖች ባይቀርብለትም ተገቢ በሆነ ጊዜ ማንኛውም ዓይነት ሰነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ አይነት ማስረጃ በተጨማሪ እንዲቀርብለት መስጠት ስላለበት ትዕዛዝ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(2) 342, 345(1)(ለ) | ጥቅምት 9/1998 |
| 14 | 14414 | የጊምቢ ከተማ አስተዳደር ጽህፈት ቤት | በሕዝብ አስተዳደር አካል ውስጥ የሚሰራ ሰራተኛ ከመ/ቤቱ ጋር ባለው ስራ ክርክር የአዋጅ ቁ. 42/85 ተፈፃሚ ስለመሆኑ | ጥቅምት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እና ወ/ሮ መረርቱ ፈቃዱ | አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 2(1),3(2)(ሠ) | 1/1998 |
| 15 | 15270 | የመቶ አለቃ ተሻገር አስታጥቄ እና አቶ አዊል አው አብዲ | በከተማ ቦታ ላይ ስለሚኖር መብት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33(2), 231, (1)(ሀ), አዋጅ ቁ.47/67 | ጥቅምት<br>28/1998 |
| 16 | 15410 | አቶ ተሾመ ጅፋር እና የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን | አጠቃላይ የአሰሪን የደመወዝ ጭማሪ አወሳሰን ስርዓትን ሳይሆን የግል ጥቅምን መሰረት አድርጐ የሚቀርብን የደመወዝ ጭማሪ ክስ የማየት ስልጣን የስራ ክርክር ችሎት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 147 | ጥቅምት<br>1/1998 |
| 17 | 16273 | የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና<br>አቶ ገንታ ገምአ | ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠርኩ እንደሆንኩ ብቻ ይወሰንልኝ በሚል የሚቀርብ ጥያቄን የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ እና የግል ጥቅምን መሰረት አድርጐ የሚቀርብን የጥቅማጥቅም ክስ የማየት ስልጣን የስራ ክርክር ችሎት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 9,10, 138, 142, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33 | ጥቅምት<br>22/1998 |
| 18 | 16624 | ወ/ት አጅጋየሁ ተሾመ እና የእቴነሽ በቀለ ሞግዚት ወ/ሮ<br>እታገኝ ዘነበ | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1) መሰረት ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ጥያቄው የሚቀርበው ይግባኝ ከመቅረቡ በፊት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1) | ጥቅምት<br>18/1998 |
| 19 | 16720 | ወ/ሮ አበራሽ ጉቱ እና እነ የመካከለኛው አዋሽ እርሻ<br>ልማት ድርጅት (አራት ሰዎች) | በከፊል የፍርድ ባለመብት የሆነ ሰው ባለመብት የሆነበት የፍርድ ክፍል እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም ክስ ካቀረበ በኂላ በመጀመሪያ የፍርድ ባለዕዳ የሆነበትን ፍርድ በይግባኝ አሸሮ የፍርድ ባለመብት ሲሆን አዲስ የአፈፃፀም መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው ቀደም ሲል የተከፈተው የአፈፃፀም መዝገብ ቢዘጋም እንኳን ማንቀሳቀስ ስለመቻሉ እና በአፈፃፀም ደረጃ ወለድ የሚከፈለው በዋናው ፍርድ ወለድ እንዲከፈል ከተወሰነ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378(3)(ሰ) | ጥቅምት<br>22/1998 |
| 20 | 16896 | ዘምዘም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር<br>እና የኢሊባቦር ዞን ትምህርት መምሪያ | የተዋዋዮች በውሉ አለመግባባት ሲፈጠርና ጉዳዩን በገላጋይ ዳኞች እንዲታይ ሲስማሙ ፍ/ቤት ይህንን ስምምነት ማስፈፀም ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1711,1731(1) | ጥቅምት<br>16/1998 |
| 21 | 17077 | ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ | የዕዳ መክፈያ ጊዜ ካለፈ በኂላ ባለገንዘቡ ለባለዕዳው የሚያደረገው የዕዳ ክፍያ ጊዜ ማራዘም ዋሱን ከዋስትናው ነፃ የሚያደርገው ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1928(1)እና(2) | ጥቅምት<br>14/1998 |
| 22 | 17189 | የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጭ ድርጅት እና አቶ ንጉሴ<br>ዘለቀ | በአሰሪ "ገንዘብ" ላይ ሰራተኛው ያደረሰው ጉዳት በአሰሪው "ንብረት" የደረሰ ጉዳት ስለመሆኑ እና ሰራተኛ የስራ ውሉ ተቋርጦ ስራ ላልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የሚያገኝበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 27(1) (በ), 53(1),54 | ጥቅምት<br>17/1998 |
| 23 | 17429 | ወ/ሮ ሎሚ ሆርዶፋ እና አቶ ተስፋዬ ከበደ | በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ ኑዛዜው መነበቡን የሚያመለክት ከሆነ በግልጽ "ተነቧል" የሚል ቃል አለመኖሩ ኑዛዜውን ፈራሽ የሚያደርግ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881 | ጥቅምት<br>21/1998 |
| 24 | 17533 | የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና<br>ሙሉ ብርሃን | የጉምሩክ ባለስልጣን በህጉ መሰረት የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃ ከጉምሩክ መጋዘን እንዳይወጣ በማድረጉ ወይም ዴክላራሲዮን ባለመስጠቱ ምክንያት በዕቃው ባለቤት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 2(18), 43(1) (ሀ) | ጥቅምት<br>18/1998 |
| 25 | 17712 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና የወ/ሮ ሳዲያ እስማኤል ወራሾች | በተሰረዘ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚገኝ የባለሀብትነት መብት ስላለመኖሩ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195(1), 1196 (1) | ጥቅምት<br>16/1998 |
| 26 | 18307 | ንብ ትራንስፖርት አ.ማ.<br>እና<br>አቶ ተገኑ መሸሻ | በድርጅት ውስጥ የስራ መሪ የሆነ ሰራተኛ ከአሰሪው ጋር ያለው የስራ ክርክር የሚገዛው በፍትሐብሔር ህጉ የስራ አገልግሎት መስጠትን ስለሚመለከቱ ውሎች ክፍል በተመለከቱት ድንጋጌዎች ስለመሆኑ እና የስራ ውሉ ተቋርጦ የስራ መሪው ስራ ላልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የሚያገኝበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2534, 2540 ,2541(1) | ጥቅምት<br>25/1998 |

**ቅጽ 3**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 27 | 15815 | አርሲ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ ሰለሞን አበበ | የስራ ውሉ በህግ ወጥ መንገድ የተቋረጠ የስራ መሪ ስለሚያገኘው መፍትሔ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2570, 2573, 2574,2571 | ታህሳስ<br>10/1998 |
| 28 | 16648 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ<br>አንለይ ያየህ (ሃያ ሰባት ሰዎች) | ስለ ስራ ክርክር የይርጋ ጊዜ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 162,163,164,165,166, አዋጅ ቁ. 377/96 | ታህሳስ<br>20/1998 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 29 | 17483 | የኦሮሚያ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን እና ወ/ሮ ሮማን ደምሴ | የስራ ውል በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል በሚል የሚቀርብ ክስ መቅረብ ስላለበት የጊዜ ገደብ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 162(1) | ታህሳስ 20/1998 |
| 30 | 11924 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ት ትዕግሥት ወርቁ | ለተወሰነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ስለማድረግ<br>አዋጅ ቁ.42/85 አንቀፅ 9,10 እና 24 | ህዳር 15/1998 |
| 31 | 14057 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና አቶ ጌታሁን ኃይሉ | አንድ ሰራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበት የአመት እረፍት ቀናት በገንዘብ ተቀይሮ ስለሚከፈልበት የህግ አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 79(2)እና (5), 77(5),77(3) | ጥቅምት 30/1998 |
| 32 | 16270 | አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ መሐሪ ማታ | በመኪና ግጭት ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳት ካሣ ለማግኘት የመኪናው ባለቤት ጥፋት እንዳለበት ማስረዳት የማይኖርበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2066(2),2086(2),2081,2091,2102 እና 2092 | ታህሳስ 17/1998 |
| 33 | 18581 | በአዲስ አበባ እስላማዊ ድርጅት የአወሊያ ጤና ጥበቃ እና ሲ/ረ ቀቡላ ከድር | በህገ ወጥ መንገድ የስራ ውሉ የተቋረጠ ሰራተኛ ወደ ስራ እንዲመለስ ስለሚወሰንበት የህግ አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 23(1),43(3),40(1) እና (2),44 | ህዳር 20/1998 |
| 34 | 15631 | እነ የሻረግ መንግስት (ሁለት ሰዎች) እና እማሆይ የሻረግ ፈረደ | የወራሽነት ጥያቄን ለማቅረብ ስለተወሰነ ጊዜ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1001(2),1168,1845,1853 | ታህሳስ 17/1998 |
| 35 | 15551 | ዮናይትድ ቴክኒካል ኢኩፐመንት ኩባንያ እና የኢትዮጵያ መተርና መሐንደስነት ኩባንያ | ውል እንዲፈርስ ከተወሰነ በኋላ ተዋዋዮች ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሚወሰነው በውሉ መሰረት የተሰራውን ስራ ለማፍረስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ካልሆነ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1716(1), 1815,1816 እና 1817 | ጥቅምት 29/1998 |
| 36 | 16062 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ አረጋሽ ከበደ | ከውል ውጭ በደረሰ ጉዳት ካሣ በመጠየቅ የሚቀረብ ክስ መቅረብ ስለሚኖርበት ጊዜ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143(1),2143(2) | ህዳር 19/1998 |
| 37 | 14554 | ወ/ሮ ጽጌ አጥናፌ እና ባላምባራስ ውቤ ሽበሽ | ፍርድ ቤት በአስተዳደር አካል የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርን የመሰረዝ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808(2),1198(2) | ታህሳስ 20/1998 |
| 38 | 15672 | አቶ ታደለ ገለቻ እና አቶ ውድመጣስ ኑሮ | ንብረት በሐራጅ ስለሚሸጥበት የህግ አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 442 | ታህሳስ 27/1998 |
| 39 | 16301 | ተገኘ እንግዳ እና አስናቀች ኬዳኔ | መጥሪያ አደራረስን አስመልክቶ የሚቀርብ ጥያቄ ስለሚስተናገድበት መንገድ<br>የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ. 99, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 103,105 | ህዳር 2/1998 |
| 40 | 10797 | ሼክ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ እና እነ ወ/ሮ ሻዲያ ናዲም (ሦስት ሰዎች) | ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በወንጀል ጉዳዩ በፍርድ የተወሰነው ገንዘብ እውነተኛ ባለቤት በቀረበ ጊዜ በቀጥታ የሚመለስ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378 | ታህሳስ 27/1998 |
| 41 | 18199 | ዶ/ር ምናሴ እሸቱ እና እነ ግርማ አያና ( ሰባት ሰዎች) | በጨረታ ለገዛው ንብረት ገገር ዋጋውን ሳይከፍል ወይም ግዴታውን ሳይፈጽም ከቀረ ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት ሊከተለው ስለሚገባው ስነ-ስርዓት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 429 | ህዳር 7/1998 |
| 42 | 16378 | የ10 አለቃ ጌታቸው ባዩ እና የቤ/ጉ/ክ/መ ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን | የመንግስት ሰራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ መስራቱ ስለሚኖረው ውጤት<br>ድንጋጌ ቁጥር 46/53, አዋጅ ቁ. 209/55 አንቀፅ 30(2) | ታህሳስ 17/1998 |
| 43 | 18342 | የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን እና እነ አቶ ብርሀኑ ህሩይ (ሁለት ሰዎች) | የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ ይግባኝ የማይባልበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.38/88 አንቀፅ 11(1) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 4 | ታህሳስ 17/1998 |
| 44 | 14699 | የኢንጂነር ወርቁ መኮንን ወራሾች እና የቦሌ ክፍለ ከተማ ገቢዎች መምሪያ | ገቢን ለመፍጠር የሚወጣን ወጪ በትክክለኛ ሰነድ እንዲረጋገጥ ህጉ ስለሚያስቀምጠው ሁኔታ<br>ደንብ ቁጥር 258/55 አንቀፅ 29 | ህዳር 7/1998 |

**ቅጽ 4**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 45 | 20885 | የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ገቢሳ የማነ | ለተወሰነና ላልተወሰነ ጊዜ ስለሚደረግ የስራ ውል<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 9,10 | ጥር 3/1999 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 46 | 15531 | የኢት/ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ አዱኛ ገመዳ | የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን | የካቲት 6/1999 |
| 47 | 21730 | ወ/ሮ ፍሬህይወት እርቂ እና የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን | ወደ ሥራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሰራተኛ የሚከፈለው ውዝፍ ደሞዝ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(5) | መጋቢት 11/1999 |
| 48 | 21119 | ቃሊቲ ምግባ አክሲዮን ማህበር እና ማስተዋል ጫኔ | የህመም ፈቃድ ጊዜ አቆጣጠር<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ (2) | መጋቢት 18/1999 |
| 49 | 21961 | አቶ ግርማ ነጋሽ እና ቢግ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር | የስራ ውልን ስለማቋረጥ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1) ሐ | መጋቢት 18/1999 |
| 50 | 20457 | የኢት/ንግድ ባንክ እና ወ/ሮ አለሚቱ ሞገስ | የስራ ውል በተቋረጠ ጊዜ ስራ ሳልተሰራበት ውዝፍ ደሞዝ የሚከፈል ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 43,53(1), 54 | መጋቢት 20/1999 |
| 51 | 24153 | አቶ መንግስቱ አባተ እና የባህር ትራንዚት ድርጅት | ስለ መሠረታዊ የህግ ክርክር<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)ሐ | መጋቢት 26/1999 |
| 52 | 16653 | ግዮን ሆቴሎች ድርጅት እና ወ/ሮ ስለእናት ወርቅነህ | የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን | መጋቢት 27/1999 |
| 53 | 25526 | መምህር ጥላሁን አስፋው እና አዲስ ኮሌጅ | ሰራተኛው በየአመቱ ውሉ እየታደሰ ሲሰራ መቆየቱና የሰራተኛው የቅጥር ውል በጊዜ የተገደበ መሆኑ ብቻ ለተወሰነ ጊዜ ተቀጣሪ የሚያደርገው ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 9,10 | ሚያዝያ 16/1999 |
| 54 | 15662 | የኢት/ልማት ባንክ እና ሐጂ አብዲራህማን ቴሲሳ | ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ለመተርጐም ስላለመቻላቸው<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2298,1733 | መጋቢት 13/1999 |
| 55 | 19081 | አቶ ዓሊ ቃሴብ አህመድ እና እነ አቶ ሚሊዮን ተፈራ (ሦስት ሰዎች) | ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የተገናኙ ተከሳሾች በአንድ ላይ በተከሰሱ ጊዜ አንዱ ተከሳሽ የሚያነሳውን የይርጋ መቃወሚያ በሌሎች ላይ ስላለው ውጤት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677,1901 | መጋቢት 18/1999 |
| 56 | 23320 | አቶ ገብሩ አብሴ እና እነ የአቶ ሁሴን አብዲረህማን ወራሾች (ሦስት ሰዎች) | የኪራይ ውል በአከራይና በተከራይ መካከል የሚደረግ ስለመሆኑ | መጋቢት 20/1999 |
| 57 | 14493 | የኢት/ልማት ባንክ እና አቶ ሚደቅሳ ቱለማ | ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ለመተርጐም ስላለመቻላቸው<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.2298,1733 | መጋቢት 13/1999 |
| 58 | 18786 | ወ/ሮ አለሚቱ አግዛቸው<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ዝናሽ ሐይሌ | የውል አብዛኛው ግዴታ በተፈፀመ ጊዜ የተወሰነ ቀሪ ገንዘብ አለመከፈሉ ውሉን ለማፍረስ የሚያበቃ መሰረታዊ የሆነ የግዴታ መጣስ የሚያሰኝ ምክንያት ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771(1), 1785(2), 1789 | ሚያዝያ 18/1999 |
| 59 | 21448 | ወ/ሮ ጉርፌ ወርቅነህ እና እነ ወ/ሮ አበራሽ ዱባርጌ (ሁለት ሰዎች) | የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት ፊት መደረግ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723, 1727 ,2877, 2878 | ሚያዝያ 30/1999 |
| 60 | 15557 | ወ/ሮ አልማዝ ዓለማየሁ እና አቶ ብርሀኑ ተሊላ | በአፈፃፀም ጉዳይ በስህተት በፍ/ባለመብት እጅ ስለገባ የከተማ መሬት ይዞታ | መጋቢት 11/1999 |
| 61 | 22260 | የጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ገደሪፍ ውብነህ (ሦስት ሰዎች) | የወጪና ኪሣራ አወሳሰን<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 463 | መጋቢት 18/1999 |
| 62 | 17984 | የጌዲዮን ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት እና ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ | ጉድለት ያለበት ሀራጅ ቀሪ ሲደረግ ሻጭና ገገርን ወደነበሩበት ለመመለስ ስላለመቻል<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1817(1) እና (2) | መጋቢት 20/1999 |
| 63 | 19205 | አቶ ሽኩር ሲራጅ እና አቶ ሙሳት ካሣ | አንድ ፍርድ ተፈፀመ ሊባል የሚገባው ለፍርድ ቤቱ ገቢ የተደረገ ገንዘብ ለፍርድ ባለመብቱ ሲደርሰው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 395 | መጋቢት 25/1999 |
| 64 | 19479 | ወ/ሮ አመለወርቅ ገለቴ ወራሾች እና እነ አቶ ቢሻው አሻሜ (አራት ሰዎች) | አከራካሪ የሆነው ቤት የግልም ሆነ የጋራ ቤቱ ያረፈበት ቦታ የመንግስት በመሆኑ ከቤቱ ተነጥሎ እንዲገመትና አስፈላጊም ከሆነ እንዲሸጥ የሚያደርግ ውሣኔ መሬትን የመንግስት ለማድረግ የወጣውን ሕግ የሚፃረር ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 47/67 | መጋቢት 20/1999 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 65 | 16109 | አቶ ከበደ አርጋው እና የኢት/ንግድ ባንክ | የሽያጭ ውል በሶስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው ተዋዋዮች ውላቸውን በመዝገብ እንዲፃፍ ከማድረግ የዘለለ ግዴታ የማይጥልባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1587, 1620, 1613, 2878 | ሚያዝያ 12/1999 |
| 66 | 14094 | የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት<br>እና<br>የአቶ ሰለሞን ወረዳ ወራሽ | ለረጅም አመታት በመንግስት እጅ የነበረ ቤትን በተመለከተ ባለቤት ነኝ የሚል ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁ. 47/67 የተፈቀደለት መሆኑን ወይም ያለአግባብ ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሣኔ አግኝቶ ባለመብት ስለመሆኑ ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, አዋጅ ቁ 47/67,ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33/2/ | ሚያዝያ 18/1999 |
| 67 | 17937 | ወ/ሮ ድንቁ ተድላ<br>እና<br>አቶ አባተ ጫኔ | ጋብቻ በአንደኛው ተጋቢ ሞት ምክንያት በፈረሰ ጊዜ የጋራም ሆነ የግል ንብረት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677 መሠረት በቁ. 1845 ላይ የተቀመጠው ይርጋ ተፈፃሚ ስለመሆኑ<br>ፍ/ብ/ህ/ቁ. 17,68, 100,1677,1845 | መጋቢት 20/1999 |
| 68 | 20938 | ወ/ሮ ሸዋዬ ተሰማ እና ወ/ሮ ሣራ ልነጋነ | ስለ ጋብቻ መፍረስ | ሚያዝያ 11/1999 |
| 69 | 22243 | ወ/ሮ ደሐብ ሰኢድ እና አቶ አብርሃም ካሣ | ልጅነትን ስለማስረዳት<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 126(1),143(መ) እና (ሠ) | ሚያዝያ 16/1999 |
| 70 | 17058 | አቶ አንበሶ ወ/ገብርኤል እና አቶ መሣይ መኮንን | ኑዛዜ ህጋዊ ነው መባሉ ሌሎች ሰዎች በሰነዱ ላይ ተቃውሞ ካላቸው ጉዳዩ በዳኝነት መታየትን የሚከለክል ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881, 884, 892, 996-1000, ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | መጋቢት 25/1999 |
| 71 | 22712 | አቶ እንደሻው በቀለ<br>እና<br>እነ ወ/ት አይናለም ያለው<br>( ሁለት ሰዎች) | የኑዛዜ እያንዳንዱ መስፈርት መሟላት መመዘን የሚገባው የኑዛዜውን አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከትና ተናዛዥም ሆነ ምስክሮች /እማኞች/ በኑዛዜ ባሰፈሩት ቃላትና ሃረጐች ሊሰጡ የሚችለውን ትርጉም ግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881 | ሚያዝያ 9/1999 |
| 72 | 22162 | አፍሪካ ኢንሹራንስ እና አቶ ብስራት ጉላ | መድን ሰጭ የካሣን ክፍያ በተመለከተ በመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው በላይ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ | ሚያዝያ 9/1999 |
| 73 | 23339 | የኢት/ጉምሩክ ባለሥልጣን እና እነ አበሮ ኢርጋኖ | የጉምሩክ ባለስልጣን ሰራተኞች የፌዴራል ገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚተዳደሩ ስለመሆናቸው<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀፅ 6(2)ለ | መጋቢት 13/1999 |
| 74 | 16195 | የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና እነ ልዕልት ተናኘወርቅ ኃ/ስላሴ (ስድስት ሰዎች) | ሚኒስቴር መ/ቤቶች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የፈፀሙትን ስህተት ማረምና ማስተካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 4187 አንቀፅ 11(1), አዋጅ ቁ.47/67 አንቀፅ 21(2), የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 74(4) | ሚያዝያ 11/1999 |
| 75 | 22317 | የምስራቅ ጉምሩክ የሐረር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ<br>እና<br>አቶ አብዱ አሉ አዩ | የጉምሩክ ባለስልጣን በኮንትሮባንድ ወደ ሀ-ገር የሚገቡትን ወይም ከሀገር የሚወጡትን እቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣ የሚንቀሳቀሱ እቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣን የተሰጠው ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 5-6 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2010(2) | ሚያዝያ 18/1999 |
| 76 | 12025 | አቶ ምናሴ አልማው እና ዓቃቤ ህግ | ጥብቅና ፈቃድ ከተሰረዘ በኋላ የጥብቅና ስራ እሰራለሁ ብሎ ገንዘብ መቀበል የማታለል ወንጀል ስለመሆኑ<br>የ1949 ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ.656(ሀ) እና (ለ) | መጋቢት 18/1999 |

**ቅጽ 5**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 77 | 17320 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ዶ/ር ሻውል ገብሬ (ሁለት ሰዎች) | ንብረትን ለመሸጥ ለመለወጥ ብሎም ለሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ በሚል የተሰጠ ውክልና ንብረቱን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችል ስልጣን እና ችሎታን የሚያጐናጽፍ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3049(2),2206(1) | መጋቢት 18/2000 |
| 78 | 20809 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ አለምነሽ ሃይሌ | በባለስልጣን ፊት በተረጋገጡ ሰነዶች ላይ ያሉትን ፊርማዎችና የሰነዶቹን ይዘት ማስተባበል ስላለመቻሉ | ሐምሌ 10/2000 |
| 79 | 23861 | ሊቀ ስዩማን አሰፋ ባሻህውረድ እና የሣህሊተ ምህረትና ክርስቶስ ሣምራ ደብር አስተዳደር | ወኪል የሆነ ሰው ውክልናውን በሚገባ እስካሳየ ድረስ በማመልከቻው ላይ የራሱን ወይም የወካዩን ስም አስቀድሞ መፃፉ ወኪልነቱን ለውጦ ባለቤት የሚያደርገው ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 58 | ጥቅምት 14/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 80 | 26399 | አቶ ኃ/ማርያም ባዩ እና እነ አቶ ሣሙኤል ጉግሳ (አምስት ሰዎች) | የውክልና ስልጣኑ ቀሪ ከተደረገበት እንደራሴ ጋር በቅን ልቦና ውል ፈፅመው በተገኙ ጊዜ ውሉ እንዲፈርስ ሳይወሰን የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808, 1816, 2191(2), 2193 | ህዳር 5/2000 |
| 81 | 32241 | ወ/ሮ ካሰች ተካልኝ<br>እና<br>እነ አቶ ኃ/ማርያም አበበ<br>(ሁለት ሰዎች) | • እንደራሴ የሆነ ሰው የውክልና ስልጣኑን መሠረት በማድረግ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቃዋሚ ጥቅሞች (Conflict of interest) ማስወገድ ያለበት ስለመሆኑ<br>• ከእንደራሴው ጋር ውል የፈፀመው ሦስተኛ ወገን እንደራሴው የውክልና ስልጣኑን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቃዋሚ ጥቅሞችን የማስወገድ ግዴታውን አለመወጣቱን ማወቁ ወይም ማወቅ የሚገባው መሆኑ ያደረጉትን ውል ፈራሽ ስለማድረጉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1) | መጋቢት 9/2000 |
| 82 | 21355 | አንበሳ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ | የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና የሰጠ ወገን ከዋናው ውል አለመፅናት ጋር በተያያዘ የዋስትና ውሉ እንዲፈርስ ሊጠይቅ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1923(2) | ሐምሌ 3/2000 |
| 83 | 25115 | አቶ ማሞ ጉበና እና አቶ ወርቅነህ ተክለማርያም | ተራ ዋስ የሆነ ሰው ከባለዕዳው ጋር ተጣምሮ ክስ በቀረበበት ጊዜ ከገባው የዋስትና ግዴታ ሙሉ በሙሉ ከኃላፊነት ነፃ ሊደረግ የሚችለው ዋናው ባለዕዳ ግዴታውን ለባለገንዘቡ ከመወጣቱ ጋር በተያያዘ ስለመሆኑ | ጥቅምት 5/2000 |
| 84 | 26565 | ግሎባል ኢንሹራንስ /አ.ማ/<br>እና<br>ንብ ትራንስፖርት /አ.ማ/ | ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገመት ወይም ሊታሰብና ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚቻል ሁኔታ ድንገተኛ ደራሽ ቢሆን እንኳ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ (Force majeure) ተብሎ የማይወሰድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 1792(2) | ጥቅምት 19/2000 |
| 85 | 17742 | ወ/ሮ አበበች ታደሰ እና እነ አስር አለቃ ሲሳይ ካብትህይመር (አራት ሰዎች) | በህግ በተቋቋመ ፍርድ ቤት የሚያስችል ማንኛውም ዳኛ ውል የማዋዋል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1678(ለ) እና 1715 | መጋቢት 2/2000 |
| 86 | 23921 | ወ/ሮ ዘለቃሽ መንግስቱ እና አስር አለቃ ታደሰ ወርቁ | የስጦታ ውሉ በስጦታ ተቀባዩ ላይ ግዴታ ያልጣለ ቢሆንም እንኳን ስጦታ ሰጪው በድህነት ላይ መሆኑ ከተረጋገጠ ተቀባዩ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2458(1) | ጥቅምት 12/2000 |
| 87 | 32337 | ወ/ሮ ፀሐይነሽ ይህደጉ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ትሕሽ በርሔ | "የቁም ኑዛዜ ስጦታ" ተራ የክፍያ ደንብ እንጂ ሌሎች ወራሾች ያላቸውን ውርሱን የመካፈል መብት የማይገድብ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 913 | ግንቦት 21/2000 |
| 88 | 22891 | ወ/ሮ ማና ኃ/ሚካኤል እና እነ አቶ ገ/ማርያም ከበደው (ሁለት ሰዎች) | በጋብቻ ወቅት በአንደኛው ተጋቢ ምክንያት የተፈጠረ ዕዳ ለጋራ ጥቅም መዋሉ በተረጋገጠ ጊዜ የዕዳው ወደ የጋራ ንብረት ወይም ወደ ሌላኛው ተጋቢ የግል ንብረት በመሄድ ሊከፈል የሚችለው በፍርድ አፈፃፀም ላይ ስለመሆኑና ከዚህ ጋር በተያያዘ በሌላኛው ተጋቢ ላይ ዕዳውን መሠረት በማድረግ ክስ ሊመሰረትበትም ሆነ ፍርድ ሊሰጥበት የማይገባ ስለመሆኑ | ህዳር 24/2000 |
| 89 | 31737 | አቶ ገብሩ ገ/መስቀል እና ቄስ ገ/መድህን ረዳ | በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2472 መሠረት በባንክ የተሰጠ የሃዋላ ወረቀት ብድርን ለማስረዳት ስለመቻሉ | የካቲት 27/2000 |
| 90 | 24173 | የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና ወ/ሮ አይዳ ሐሰን | በኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት የተላከ ፖስታ /ዕቃ/ በመጥፋቱ፣ መሠረቁ፣ በመበላሸቱ፣ ወዘተ ምክንያት ካሣ የሚጠየቀው መጠኑም የሚወሰነው የፖስታ አገልግሎት ሕግን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 24/58 መሠረት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 24/58 አንቀፅ 50,51,53 እና 54 | ህዳር 11/2000 |
| 91 | 24574 | የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ/ቤ/መ/ፖ/ጠ/ጽ/ቤት እና አቶ ይትባረክ ሣህሉ | በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሣኔ ሳይሰጥበት የታለፈ ጉዳይ እንደተነፈገ ይቆጠራል የሚለው የሥነ- ሥርዓት ህግ ድንጋጌ ሊተረጉም የሚችልበት አግባብ | ህዳር 11/2000 |
| 92 | 25434 | የአዲስ አበባ ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን<br>እና<br>ፋሬተርስ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግል ማህበር | በውል ውስጥ አጠራጣሪና ግልፅነት የጐደላቸው ጉዳዩች በፍ/ብ/ህ/ቁ.1738 መሠረት እልባት ሊሰጣቸው የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1738 | መጋቢት 25/2000 |
| 93 | 29369 | በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሆለታ የግብርና ምርምር ማዕከል<br>እና<br>አቶ ተመስገን አድነው | • የባለዕዳው ቀጥተኛ የውል ፈፃሚነት ከውሉ ባህሪ አኳያ ማስፈፀም አለመቻል ውሉ እንዲሰረዝ መጠየቅ ሳያስፈልግ ኪሣራ ካለ መጠየቅ ስለመቻሉ<br>• በውል መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ ወገንን አስገድዶ ለማስፈፀም የማይቻል በሆነ ጊዜ በውሉ ግዴታውን የተወጣው ወገን ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰውን ኪሣራ ለመጠየቅ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771(1) እና (2) | መጋቢት 9/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 94 | 19338 | ዘይነባ ሐሰን<br>እና<br>ፍሬው ተካልኝ | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ተጐጂ የሆነ ወገን የወደፊት ህይወት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚኖር ስለመሆኑ ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለ እንደሆነ ዳኞች ለተጐጂው የሚከፈለውን ካሣ በርትዕ መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102 | መጋቢት<br>2/2000 |
| 95 | 21296 | የኔዘርላንድ ልማት ድርጅት እና ውበት አድባሩ | የፍ/ብህ/ቁ. 2089 ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089(1) እና (2) | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 96 | 22509 | አቶ ግርማ ኃ/ጊዮርጊስ እና ዳርጊ ሰምሮ | የቀረበን ክስ ለማስረዳት አግባብነት የሌለው ማስረጃን መሠረት በማድረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | ጥቅምት<br>7/2000 |
| 97 | 24818 | ይልቃል በእውቀቱ እና ስዩም አባዲ | ጥቅም በሌለው ግንኙነት በመኪና ተሣፍሮ ሲሄድ አደጋ በመድረሱ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው ካሣ ሊጠይቅ የሚችለው የመኪናው ባለቤት ወይም ጠባቂው ጥፋት መፈፀሙን በማስረዳት ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089(2) | የካቲት<br>4/2000 |
| 98 | 27565 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ አቶ ደምሴ ወርቅነት<br>(ሁለት ሰዎች) | ጉዳት ሊካስ የሚገባው ለደረሰ ጉዳት ብቻ ሳይሆን በጉዳቱ ምክንያት ለሚመጣ ኪሣራ ጭምር ስለመሆኑ | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 99 | 27623 | ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ<br>እና<br>ወ/ሮ ውባየሁ አበበ | • የማህበራዊ ዋስትና መብት ጥቅምን በሚመለከት የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንጂ መደበኛ ፍርድ ቤቶች የመዳኘት የሥረ ነገር ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>• የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 38/88 አንቀፅ 5,8 እና 11 | ህዳር<br>24/2000 |
| 100 | 28612 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና<br>የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን | ለደረሰ ጉዳት ሃላፊ የተባለ ሰው ላደረሰው ጉዳት ካሣ አይከፍልም ሊባል የሚችልበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2091 | የካቲት<br>25/2000 |
| 101 | 28750 | የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ከውልና ከውል ወጪ በሆነ ግንኙነት ከሁለት የተለያዩ የክስ ምክንያቶች የሚመነጭ ኃላፊነትን መሠረት በማድረግ በአንደኛው ግንኙነት ብቻ ተጠያቂ የሆነን ወገን ሁለቱን የኃላፊነት ምክንያቶች መሠረት በማድረግ ካሣ እንዲከፍል በአንድነትና በነጠላ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2035, 1896 | ህዳር<br>24/2000 |
| 102 | 28865 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>አቶ ካሣ ግዛው | ንብረትን ከመስሪያ ቤት በኃላፊነት የተረከበ ሰው ንብረቱ በጠፋ ጊዜ ከንብረቱ መጥፋት ጋር በተያያዘ ጥፋት ያልፈፀመ መሆኑን ወይም ንብረቱ ከሥራ ሰዓት ውጪ የጠፋ መሆኑን የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2027 | ህዳር<br>24/2000 |
| 103 | 30032 | የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ<br>እና<br>ወ/ሮ ምንትዋብ የኔነህ | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት የክልሉ መንግስት ቋሚ ሠራተኛ በስራ ላይ በደረሰበት ጉዳት የሞተ እንደሆነ ለተተኪዎች የጡረታ አበል እንጂ ሌላ ተጨማሪ ካሣ ሊከፈል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የአማራ ክልል አዋጅ ቁ.74/1994 አንቀፅ 46(5) (ሀ) | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 104 | 30442 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ሰሜን ምዕራብ ሪጅን<br>እና ወ/ሮ ድንቋ አመኔ | • ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት የሞት አደጋ በደረሰ ጊዜ የሟች የቅርብ ዘመዶች ሊኖራቸው የሚችለው መብት እና<br>• የደረሰውን የሞት አደጋ ተከትሎ የሚቀርብ የቀለብ ጥያቄ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095 807, 812 | ህዳር<br>3/2000 |
| 105 | 31099 | የተንዳሆ እርሻ ልማት አ/ማ<br>እና<br>ወ/ሮ ርሻን አለማየሁ | ሟች ከመሞቱ በፊት ቀለብ የማይሰፈርለት ግለሰብ በሟች ሞት ምክንያት የጉዳት ካሣ በቀለብ መልክ እንዲከፈለው ለመጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095, 2069(1) | ግንቦት<br>14/2000 |
| 106 | 32144 | ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር<br>እና<br>ወ/ሮ ኢልሻ ሲራጅ | • በሞት ምክንያት ቀረ የሚባል ጥቅም የሚሰላው ከጠቅላላው የሟች ደሞዝ ላይ የሚቀነሱት በህግ የታወቁት ተቀናሾች ተቀንሰው የሚገኘውን የተጣራ ገቢ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ<br>• የህሊና ካሣ ከአንድ ሺህ ብር ሊበልጥ የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2116 | መጋቢት<br>23/2000 |
| 107 | 32250 | ወ/ሮ አስናቀ ወ/ማሪያም እና እነ አቶ ከተማ ተሰማ<br>(ሁለት ሰዎች) | በሞት አደጋ ምክንያት የተቋረጠ የመተዳደሪያ ጥቅም ጋር በተያያዘ በየወሩ የሚከፈል ካሣ አከፋፈል ስርአት በፍርድ ቤት የተወሰነውን ካሣ አጠቃሎ በባንክ ወይም በሌላ የገንዘብ ተቋም በማስቀመጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095(2) | መጋቢት<br>25/2000 |
| 108 | 33975 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>ወ/ሮ አበበች ስዩም | የመሬት ይዞታ ባለቤት የሆነ ሰው ለህዝብ ጥቅም በሚል ይዞታውን በተጨባጨ እንዲለቅ ባልተደረገበት ሁኔታ ሊጠይቅ የሚችለው የካሣ ክፍያ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.455/97 አንቀፅ 7(1) | መጋቢት<br>25/2000 |
| 109 | 34138 | እነ ሲስተር ገነት ጌታቸው (ሁለት ሰዎች) እና | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት የደረሰበት ሰው ከደረሰበት የአካል ጉዳት በተጨማሪ በደሞዝ ረገድ የቀረበት ጥቅም | ግንቦት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወንድወሰን ኃይሉ ወልደ ማሪያም | (ገቢ.) መኖሩ ከተረጋገጠ ሲካስ የሚገባ ስለመሆኑ | 26/2000 |
| 110 | 34906 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የምስራቅ ሪጅን ጽ/ቤት እና ወ/ሪት ፍሬሕይወት እርቂ | በሥራ ግንኙነት ውስጥ የቅርብ አለቃ የሆነ ሰው በሥሩ ያሉ ሠራተኞችን አስመልክቶ ለበላይ ኃላፊዎች የሚፅፈውና የሚልከው ሪፖርት ሥም ከማጥፋት ጋር በተያያዘ የፍትሐብሔር ሃላፊነት ሊያመጣበት የማይችል ስለመሆኑ | ግንቦት 5/2000 |
| 111 | 21740 | ወ/ሮ አስረስ መስፍን እና ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ | የጋብቻ ጽሁፍ በሌለ ጊዜ ጋብቻ መኖሩን ለማስረዳት የሚቻለው የባልና ሚስትነት ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 699(1), (2) | ጥቅምት 28/2000 |
| 112 | 23021 | ወ/ሮ አበባ ወርቅ ጌታነህ<br>እና<br>ወ/ሮ ዋጋዬ ኃይሌ | በፍቺ ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ የቀድሞ ተጋቢዎች እንደ ገና አብሮ መኖር የትዳር ሁኔታ መኖሩን የሚያስገነዝብ ከሆነ ጋብቻ መፈፀሙን የህግ ግምት መውሰድ የሚቻል ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 96 እና 97(1) | ሐምሌ 12/1999 |
| 113 | 23493 | ወ/ሮ እንማው ዘገየ እና ወ/ሮ ወርቂ መኮንን | በፍርድ ቤት ያልፈረሰ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በፈፃሚው ሞት ምክንያት የፈረሰ እንደሆነ የሚች ባለቤቶችን እኩል የጡረታ አበል የመከፈል መብት የሚሰጥ ስለመሆኑ | ሰኔ 26/1999 |
| 114 | 23632 | ወ/ሮ ፀዳለ ደምሴ<br>እና<br>አቶ ክፍሌ ደምሴ | ወላጆች ለህፃናት ልጆቻቸው ሞግዚትና አስተዳዳሪ የመሆን መብታቸው ሊከበር የሚችለው ለህፃናቱ ጥቅምና ደህንነት እስከሰሩ ወይም ሊሰሩ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ሲቻል ብቻ ስለመሆኑ<br>የደቡብ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስተ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 75/96 አንቀፅ 235(1), የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 36(2) | ጥቅምት 26/2000 |
| 115 | 24625 | ወ/ሮ ሳድያ አሕመድ እና ወ/ሮ ሊህማ አሊ. | በህግ ፊት ያልፈረሰ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በፈፃሚው ሞት ምክንያት የፈረሰ እንደሆ የጋራ ሀብትን ሁለቱ ባለቤቶች ግማሹን ለሁለት ቀሪውን ግማሽ ልጆች የሚካፈሉ ስለመሆኑ | ጥቅምት 28/2000 |
| 116 | 25005 | መኮንን በላቸው እና ወ/ሮ አለሚቱ አደም | በጋብቻ ውል ላይ የግል ተብሎ ያልተመለከተና ጋብቻ ከመፈፀሙ በፊት ግንባታው የተጀመረ ቤት ግንባታው የተጠናቀቀው በጋብቻ ወቅት ከሆነ የጋራ ንብረት ተደርጐ የሚወሰድ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(1) , 63(1) | ህዳር 3/2000 |
| 117 | 25281 | ወ/ሮ መሠረት ፍስሐ<br>እና<br>አቶ ቀልቤሣ አለሙ | የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ነው በሚል የተወሰነ መኖሪያ ቤት ጋር በተያያዘ አንደኛው ተጋቢ ቤቱ የተሰራበትን መሬት (ቦታ) ከጋብቻው በፊት የተመራ በመሆኑ ሌላኛው ተጋቢ የቤቱን ግማሽ ዋጋ ተቀብሎ እንዲለቅ በሚል የሚሰጥ ውሣኔ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 92<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. አንቀፅ 1131,1132 | ጥር 29/2000 |
| 118 | 25588 | መርየንሃሰን ዑመር እና መውሊድ ተኸልእስማን | አንድ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን ያለው መሆኑና አለመሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ጉዳዩን ማየት ከመጀመሩ በፊት እንጂ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ስላለመሆኑ | የካቲት 6/2000 |
| 119 | 26839 | ወ/ሮ አስካለ ለማ<br>እና<br>ሣህለ ሚካኤል በዛብህ | ጋብቻ ከመመስረቱ በፊት የግል የነበረ ሃብት ከጋብቻ በኃላ የጋራ ከሆነ ንብረት ጋር ተቀላቅሎ በተገኘ ጊዜ የግል የሆነው ንብረት ተለይቶ የግሉ ለሆነው ተጋቢ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 57,86(1) | ህዳር 10/2000 |
| 120 | 26953 | አቶ ብዙነህ ጨርቆሴ እና ወ/ሮ መዓዛ እንግዳዬ | በጋብቻ/በትዳር ላይ/ ከተጋቢዎች መካከል በአንደኛው ተጋቢ አማካኝነት በካሣ መልክ የተገኘ ሃብት የጋራ ሃብት/ንብረት/ ተደርጐ የሚቆጠር ስለመሆኑ | ህዳር 13/2000 |
| 121 | 27697 | አቶ ርዕሶም ገ/መድህን እና ወ/ሮ አልማዝ ጊላ ሚካኤል | ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የጋራ ንብረት የተሸጠ ቢሆንም የሽያጩ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል እንደሚገኝ ካልተረጋገጠ ለጋራ ትዳር ጥቅም እንደዋለ የህግ ግምት የሚወሰድበት ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 85 -93 | ጥቅምት 19/2000 |
| 122 | 27869 | ፍቅርና ሠላም ኃ/የተ/የግ/ማ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ<br>(ሁለት ሰዎች) | • የማይንቀሳቀስ ንብረት ለንግድ ማህበር በመዋጮ መልክ የተሰጠ ሆኖ ሲገኝ የንብረቱ ስም በኩባንያው ተመዝግቦ ያለመገኘቱ በ3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ለመሆን የማይችል ቢሆንም ንብረቱ በአይነት መዋጮ መስጠቱን የሚያስቀረው ስላለመሆኑ<br>• የጋራ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ያለ አንደኛው ተጋቢ ፈቃድ ለንግድ ማህበር በዓይነት መዋጮ የተሰጠ እንደሆነ ንብረቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 517(ሠ),(ረ)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2878<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68(1), 69(2) | ህዳር 10/2000 |
| 123 | 29343 | እነ ወ/ሮ አምሳለ ተፈራ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ት አበባ አድማሱ | ተጋቢዎች በጋብቻ ወቅት የተፈራ ቤታቸውን በትርፍነት ለመንግስት ያስረከቡ እንደሆነ የአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረት የሆነን ቤት ያለምንም ተጨማሪ ስምምነት የጋራ የሚያደርገው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 47/67 አንቀፅ 11(1) | ሚያዝያ 7/2000 |
| 124 | 29402 | ወ/ሮ ሐዳስ ታረቀ እና የ፱ አለቃ አስመላሽ ኃይለስላሴ | ቤት የጋራ ሃብት ነው ከተባለ ቤቱ የተሰራበት መሬት ላይ የጋራ ባለሃብቶቹ እኩል የመጠቀም መብት የሚኖራቸው | ጥቅምት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ስለመሆኑ | 19/2000 |
| 125 | 30959 | እነ ወ/ሮ ተወዳጅ ገ/ሥሌሴ (ሁለት ሰዎች) እና<br>እነ አቶ ዘለቀ ዘውዴ( ሁለት ሰዎች) | • ሟች በኑዛዜው አንድን ሰው ልጄ አይደለም በማለት መግለፅ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማፍረስ የሚያበቃ ስላለመሆኑ<br>• በቤተሰብ ህጉ ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቻልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154,156,157 | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 126 | 31430 | ወ/ሮ አዲስአለም አከለ እና የመቶ አለቃ አክሊሉ አበበ | ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የሚገኝ ድጐማ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ስለመሆኑ<br>የአማራ ብ/ክ/መ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 73(1) እና (2) | ሚያዝያ<br>7/2000 |
| 127 | 31891 | እነ አቶ አንለይ እንየው (ሰባት ሰዎች) እና ወ/ሮ መሬም ጠሃ | የተጋቢዎች ተለያይቶ ለረዥም ጊዜ መኖርና በዚህም ጊዜ ሌላ ትዳር መስርቶ መገኘት የቀድሞው ጋብቻ በህጋዊ መንገድ ተቋርጧል የሚያስብል ስለመሆኑ /የሰ/መ/ቁ. 14290/ | ሚያዝያ<br>14/2000 |
| 128 | 31946 | ወ/ሮ ዘውዲቱ ጌታቸው እና ተመስገን ደሳለኝ | የጋብቻ ውል በህግ አግባብ  አልተደረገም በሚል ተቃውሞ ያቀረበ ተጋቢ በውሉ መሠረት ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 34(2), 35(2) እና 9(1) | ግንቦት<br>14/2000 |
| 129 | 32130 | እነ እማዋይሽ ካሣ (ስድስት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ አስቴር አህመድ | አንድን ሰው አባት ነው ብሎ ለማለት ለልጅ እንክብካቤ ማድረጉና ልጁም በእሱ ስም መጠራቱ ብቻ ሣይሆን ግለሰቡ ድርጊቱን አባት ነኝ ከሚል ስሜትና መንፈስ በመነጨ ያደርግ የነበረ መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የአማራ ክ/መ/ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 79/95 አንቀፅ 154(ሐ)(ሠ) | መጋቢት<br>18/2000 |
| 130 | 33411 | ወ/ሮ ሙሉብርሃን አባዲ  እና አለቃ ኪሮስ ገብሩ | ተጋቢዎች ጋብቻቸው ፀንቶ ባለበት ወቅት የገዙት ንብረት በስማቸው ያልዞረ ቢሆንም እንኳን ንብረቱ የእኔ ነው በሚል የቀረበ የ3ኛ ወገን ተቃውሞ እስካልቀረበ ድረስ ንብረቱ የጋራ ሀብት ተደርጐ የሚወሰድና ሊከፋፈል የሚገባ ስለመሆኑ | መጋቢት<br>25/2000 |
| 131 | 33440 | ወ/ሮ ኪሮስ ገ/ማርያም እና አቶ ግርማ ገብረ ስላሴ | • ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ ጥያቄ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት  ቀርቦ ሊስተናገድ የሚገባ ስለመሆኑ<br>• ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ የልደት ምስክር ወረቀት ተቃውሞ የማይቀርብበት የመጨረሻ ማስረጃ ተደርጐ ሊወሰድ የማይችል ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ  አንቀፅ 154 | ሚያዝያ<br>21/2000 |
| 132 | 33875 | ወ/ሮ የሻረግ አባትኩን እና ወ/ሮ መሠረት አድማሱ | ጋብቻ በባህላዊ መንገድ ተመስርቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብና መመስረቱን ማስረዳት የሚቻልበት ሁኔታ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 4 እና 97(2) | መጋቢት<br>25/2000 |
| 133 | 34149 | እነ ወ/ሮ ዘለቃሽ በቀለ እና አቶ አለሙ በቀለ | የአንድ ሰው አባት ነኝ በሚል የሚቀርብ ሰው አባትነቱን በህግ አግባብ በማስረጃ ማስረዳትና ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የአማራ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 147(1), 97(2) | መጋቢት<br>25/2000 |
| 134 | 34387 | አቶ ከበደ መሔ እና ወ/ሮ ፋናዬ ብዙነህ | የጡረታ አበል እንደማንኛውም ገቢ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ተደርጐ የሚወሰድ ስላለመሆኑ | ግንቦት<br>14/2000 |
| 135 | 35376 | እነ አቶ ዳንኤል አሰፋ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ ሔለን ውብቱ | ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት ላይ ያለን ዕዳ ለመወጣት ከጋብቻ በኃላ ከባልና ሚስት የጋራ ገንዘብ መከፈሉ ንብረቱን የጋራ ንብረት የማያደርገው ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(1) እና 70(1) | ግንቦት<br>28/2000 |
| 136 | 23389 | የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማ<br>እና<br>እነ ባህሩ አብርሃም (አስራ ሁለት  ሰዎች) | የአክስዮን ማህበር አባላት የአክስዮን አስተዳዳሪዎች መብታቸውን በሚጐዳ መልኩ መስራታቸውን ማረጋገጥ ከቻሉ በቀጥታ መክሰስ የሚችሉ ስለመሆናቸው<br>የንግድ ህግ ቁ. 367 | ሐምሌ<br>10/1999 |
| 137 | 25306 | አቶ ተስፋዬ ገለቴ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ገንዘብን በአደራ ለማድረስ የተቀበለ ባንክ አደራ አስቀማጩ ይሰጥልኝ ላለው ሰው እስካልሰጠ ድረስ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 898(1) | ህዳር<br>12/2000 |
| 138 | 27161 | አቶ ኤልያስ ከፈለ<br>እና<br>እነ አቶ ከድር አህመድ (አራት ሰዎች) | የክሱ መሠረት የሆነው ጉዳይ መቅረቱን በክሱ ሂደት በማንኛውም ደረጃ የተረዳ ፍ/ቤት ክሱን መሰረዝ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280 | ህዳር<br>12/2000 |
| 139 | 28923 | የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር እና<br>.እነ የባህር ዳር ልዩ ዞን አስተዳደር          (ሁለት ሰዎች) | የመንግስት ልማት ድርጅት ወደ አክሲዮን ማህበራት ሲቀየር በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ያልታወቀና ውሣኔ ያልተሰጠበት እንኳን ቢሆን የልማት ድርጅቱ ዕዳ ወደ አክሲዮን ማህበር የማይተላለፍ ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 208/92 አንቀፅ 5(1), 6(1)ሐ | ግንቦት<br>7/2000 |
| 140 | 23608 | የኢትዮጵያ ፕራይቬተይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ እና የአቶ ኑርበዛ ተረጋ ወራሾች | በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲም ሆነ በኤጀንሲው ስራ አመራር ቦርድ ቀርቦ ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ እንደገና ለማየት ፍ/ቤቶች ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ.110/87 አንቀፅ 4(1) እና 5(3) | ህዳር<br>3/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 141 | 27548 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ቆፀላ መርሻ (ሁለት ሰዎች) | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አጠራጣሪነቱ በታወቀ ጊዜ ከሚመለከተው አካል ተገቢውን ማብራሪያና ማስረጃ ሳይጠየቅ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1196(1) | መጋቢት<br>18/2000 |
| 142 | 29822 | የወረዳ 6 ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>ወ/ሮ በቀለች አማረብህ | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት ስልጣን ላለው የአስተዳደር ክፍል መመለስና መሰረዝ ጋር በተያያዘ ፍ/ቤቶች የባለቤትነት ደብተሩ እንዳይመለስ በሚል ውሣኔ ለመስጠት የማይችሉ ስለመሆናቸው<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1196(1) | ግንቦት<br>28/2000 |
| 143 | 29860 | ወ/ሮ አስናቀች ሲሻው<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አሰለፈች ከተማ (አራት ሰዎች) | በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የባለቤትነት መብት ለመንግስት የተላለፈ መሆኑን እንደመከራከሪያ በማንሳት መሟገት የሚችለው የሚመለከተው የመንግስት አካል እንጂ ግለሰብ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ 47/67 አንቀፅ 13(1) | መጋቢት<br>18/2000 |
| 144 | 31490 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>ሴርኮ እስራኤላዊያን | ተከሳሽ የሆነ ወገን ካቀረባቸው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች መካከል ፍ/ቤቱ አንዱን ብቻ መሠረት በማድረግና ሌሎቹ ላይ ብይን ሣይሰጥ ክሱን ውድቅ ያደረገው እንደሆነ ብይን ባልተሰጠባቸው መቃወሚያዎች ላይ ይግባኝ ማቅረብ የማይጠበቅበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244,341 | ሚያዝያ<br>2/2000 |
| 145 | 31682 | አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ ዘላለም ይልማ ባልቻ<br>( ሦስት ሰዎች) | ተወርሰዋል ተብለው በመንግስታዊና ህዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ሥር ያሉ ቤቶች ጋር በተያያዘ ይመለሱልኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መሠረት በማድረግ ፍ/ቤቶች መወረስና አለመውረስን በተመለከተ ማስረጃዎችን መርምሮ ውሣኔ ለመስጠት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 47/67<br>አዋጅ ቁ.110/87 | መጋቢት<br>12/2000 |
| 146 | 32376 | አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ ሸዋንግዛው | የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በባለቤትነት የሚያስተዳድራቸው ቤቶች ላይ የባለቤትነት /የባለቤትነትን መፋለም/ ክርክር በተነሣ ጊዜ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የማይኖራቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀፅ 41(ረ) | ግንቦት<br>19/2000 |
| 147 | 34249 | እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ<br>እና<br>እነ አቶ አለሙ ወንድሙ | በክርክር ተካፋይ እንዲሆን የሚያስፈልግ ወገንን ተከራካሪ ወገኖች እንዲገባ ያልጠየቁ ቢሆንም ፍ/ቤቶች ይህንኑ ወገን በራሳቸው ተነሣሽነት በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ማድረግ ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2) | ሚያዝያ<br>28/2000 |
| 148 | 22857 | እነ አቶ ተክሌ ደግፌ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>እነ አቶ በፍቃዱ ኃይሌ<br>(ሁለት ሰዎች) | • በፍርድ ሂደት ላይ ያለ ጉዳይን ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች በክርክሩ ማናቸውም ደረጃ ላይ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ውጪ በእርቅ እንዲያልቅ ለመጠየቅ የሚችሉ ስለመሆናቸው<br>• በፅሁፍ ተዘጋጅቶ የቀረበ የእርቅ ስምምነት ለፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቱ ስምምነቱ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑን አረጋግጦ በፍ/ቤት የተያዘውን ጉዳይ ማቋረጥ የሚገባው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 274(1),275,(1),277(1) | ታህሳስ<br>15/2000 |
| 149 | 25912 | አቶ ብሩ ቆርቾ  እና  አቶ ክፍሌ ሐብደታ | የግልግል ስምምነት እንደመጨረሻ ፍርድ የሚቆጠር ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3312 | ሚያዝያ<br>2/2000 |
| 150 | 29386 | ወ/ሮ ወለላ ተሰማ<br>እና<br>እማሆይ በላይነሽ መለሰ | ከወራሾች መካከል አንዱ በሌለበት የተካሄደ የንብረት ክፍፍል በሌለበት ክፍያው የተፈፀመበት ወራሽ በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1080 | የካቲት<br>25/2000 |
| 151 | 30536 | ወ/ት አለምነሽ ዋቅቶላ  እና አቶ ይልቃል ጌጤ (ሁለት ሰዎች) | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት ላደረሰ ወገን የመድን ሽፋን የሰጠ አካል በሃላፊነቱ መጠን ለተጐጂው መካሱ ተጐጂው በጉዳት አድራሹ ላይ የሚያቀርበውን ተጨማሪ (ቀሪ) የካሣ ጥያቄ የሚከለክል ስላለመሆኑ | መጋቢት<br>23/2000 |
| 152 | 20036 | ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ<br>እና<br>ወ/ሮ ወለተብርሃን ካሣዬ | ጋብቻ የትዳር ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ለማሳየት /ለማረጋገጥ/ የሚቻል ስለመሆኑና ይህንንም ለማስረዳት ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ ሊቀርብ ስለመቻሉ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ  95,96 እና 97 | ግንቦት<br>16/1998 |
| 153 | 25899 | የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ር ስዩም ካሣ | የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ ደሞዝ በሚያስገኝ የመንግስት ስራ ላይ ከተቀጠረ የቅጥሩ ሁኔታ በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት ከደሞዝ በተጨማሪ የወሰደውን የጡረታ አበል መመለስ ያለበት ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 209/55 አንቀፅ 30(2) | ግንቦት<br>28/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 154 | 26480 | የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ<br>እና<br>አቶ ቢንያም አለማየሁ | ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ የተሰጠባቸው ጉዳዩችን አይተው ለመወሰን ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ<br>አዲስ አበባ አስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 12/91 አንቀፅ 9(4) | ጥቅምት 14/2000 |
| 155 | 28883 | ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>ሚስተር ኒኮላ አስፓፓቻት ዚስ | ከተከራካሪ ወገን አንዱ የውጭ ሀገር ዜጋ ስለሆነ ብቻ ክርክሩ ሁልጊዜ የግለሰብ አለማቀፍ ሕግ ጥያቄ ያስነሳል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 11(2)ሀ | ህዳር 26/2000 |
| 156 | 29005 | አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ግርማቸው ይላላ (ሁለት ሰዎች) | በክፍለ ከተማ ስልጣን ክልል ውስጥ የሚነሱ ክርክሮች ላይ ክፍለ ከተማው ጣልቃገብቶ የመከራከር መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 361/95 አንቀፅ 10(2),30<br>አዋጅ ቁ. 18/97 አንቀፅ | ሚያዝያ 14/2000 |
| 157 | 30298 | አቶ የሲወንድም አቡሕይ<br>እና<br>አቶ አየነው ማለደ | ጠፋ የተባለ ሰው በተመለሰ ጊዜ ንብረቶቹ የተሸጡ ከሆነ ለማግኘት መብት የሚኖረው የንብረቶቹን የሽያጭ ዋጋ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 171(1) | ጥር/2000 |

**ቅጽ 6**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 158 | 08751 | ወ/ሮ አበበች በጅጋ እና እነ ዶ/ር ተስፋዬ አካሉ<br>(ሁለት ሰዎች) | • ፍርድ ከተሰጠ በኂላ አዲስ ማስረጃ ተገኝቷል በሚል የተሰጠው ፍርድ በድጋሚ ሊታይ የሚችልበት አግባብ<br>• ውሣኔ ያልተሰጠበት ጉዳይ በድጋሚ ዳኝነት እንዲታይ አቤቱታ ሊቀርብበት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6 | ግንቦት 26/2000 |
| 159 | 19142 | አቶ መላኩ ማሞ እና እነ ወ/ሮ ፈለቀች ማሞ<br>( ሦስት ሰዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ጋር በተያያዘ በሚሰጥ ብይን ላይ ፍ/ቤቱ በሥረ- ነገር ረገድ የመጨረሻ ውሣኔ ሣይሰጥ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320 (3) | ጥቅምት 26/2000 |
| 160 | 20465 | አዋሽ ኢንተርናሽናል ኩባንያ እና<br>ፀሐይ ዮሐንስ የህፃን ተመስገን ቱጂ ሞግዚትና አሳዳሪ | በአዋጅ ቁጥር 322/95 መሠረት የቤንሻንጉልን ጨምሮ የአምስት ክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ባላቸው የውክልና ስልጣን ያዩዋቸውን የፌዴራል ጉዳዩች በይግባኝ ተቀብለው የማየት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 322/95, የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 80(2) | ሰኔ 26/2000 |
| 161 | 21270 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ<br>እና<br>ወ/ሮ ወይንሸት አበራ | አንድ ንብረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከመታገዱ በፊት በባንክ በመያዣነት የተያዘ እንደሆነ ባንኩ በህግ ተሰጠው መብት መገልገል ይችል ዘንድ ፍ/ቤት የሰጠውን የእግድ ትዕዛዝ ማስነሳት የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 158, አዋጅ ቁ. 97/90 | ሐምሌ 30/1999 |
| 162 | 22556 | ታደሰ አብዛ እና እነ የአቶ ጉሳዬ ሩገቶ ወራሾች<br>(ሁለት ሰዎች) | በክርክር አመራር ሂደት የተከራካሪ ወገኖች የመሰማት መብት ተግባራዊ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ | ጥቅምት 14/2000 |
| 163 | 22603 | የድሬዳዋ ጊዜ/አስ/ቀበሌ 20 ጽ/ቤት<br>እና<br>ወ/ሮ ሽሪፍ አሊ | ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ልዩነት ያላቸው በመሆናቸው ጥርጣሬን የፈጠሩ እንደሆነ ፍ/ቤት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ ጥርጣሬ ያለበትን ጉዳይ አጥርቶ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 255,257 | ሐምሌ 26/1999 |
| 164 | 23363 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ አቶ ፈርሀን አህመድ<br>(ሦስት ሰዎች) | የመድን ሰጪ አካል ኃላፊነት በመድን ሽፋን ፖሊሲው ላይ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በላይ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 665(2) | ግንቦት 26/2000 |
| 165 | 23628 | ሶሎ ሲርካርና ኤ.ኤስ እና እነ.ጌትያን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ<br>(ሁለት ሰዎች) | በውጭ ሀገር ተመዝግቦ የህግ ሰውነት ያገኘ ኩባንያ በኢትዮጵያ የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ አቅርቦ በሂደት ላይ ያለ መሆኑ በውጭ አገር ያገኘውን የህግ ሰውነት ቀሪ የሚያደርገው ስላለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 100 | ጥቅምት 21/2000 |
| 166 | 23692 | አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ | • የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 ሊተረጐም የሚችልበት አግባብና አፈፃፀሙ | ሐምሌ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እና<br>እነ አሊ መሐመድ | • በሦስተኛ ወገን ተከሳሽነት በክርክር ውስጥ እንዲገባ የተደረገ ወገን ከተከሳሽ ጋር ከመሟገት በቀር ተከሳሹን ተክቶ ከሣሽን መከራከር አይችልም ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 687, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2), 43 | 03/1999 |
| 167 | 23744 | አቶ በቀለ በድዬ እና እነ ወጋገን ባንክ አዋሳ ቅርንጫፍ (ሦስት ሰዎች) | ዳኝነት ሣይከፈል በነፃ ክስ እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ በሚል አቤቱታ አቅርቦ ጥያቄው በፍ/ቤት ትዕዛዝ /ውሣኔ/ ውድቅ የተደረገበት ተከራካሪ ይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320(1), (3) | ሐምሌ 26/1999 |
| 168 | 23769 | ኢንጅነር ጋሪፉፋ እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ጥናት ኢንስቲትዮት | ከአገልግሎት ብዛት ከጥቅም ውጭ የሚሆኑና ሊያስረክቧቸው የማይችሉ ዕቃዎች ላይ የዋጋ ግምታቸውን መጠየቅ የክሱ ምክንያት ቀሪ በሆነ ነገር ላይ ክስ እንደመመስረት የሚቆጠር ስለመሆኑ | ሐምሌ 12/1999 |
| 169 | 24111 | የቂርቆስ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን<br>እና<br>ወ/ሮ የዕለተወርቅ ገ/አብ | የተከሳሽን መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ተከሳሽ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ተከሳሹ ሊያጣ የሚችለው መልሱን በፁሁፍ የማቅረብ መብቱን ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70(ሀ), 195 | የካቲት 11/2000 |
| 170 | 24627 | ዶ/ር ቤተልሄም ታደሰ እና የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ | ከቤት ባለቤትነት ክርክር ጋር በተያያዘ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት በመመሪያ፣ በቀላጤ ወይም በቃል ትዕዛዝ ከግለሰቦች የተወሰደና በመንግስት ቁጥጥር ሥር ያለ መሆኑ ካልተገለፀ በስተቀር ጉዳዩን ለማስተናገድ ፍ/ቤቶች ስልጣን የሚኖራቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.110/ 87 አንቀፅ 3(1) | ሚያዝያ 30/2000 |
| 171 | 24775 | ማታዶር አዲስ ጉማ<br>እና<br>ቢተው ረታ | ተከሳሽ መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘበት ዕለት ባለመቅረቡ ብቻ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ በሚል የሚሰጥ ትዕዛዝ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241(1), 233 | ጥቅምት 21/2000 |
| 172 | 25026 | ወ/ሮ ሁዳ መሐመድ<br>እና<br>ሃጂ አህመድ አህመዲን | ተከሳሽ በራሱ ቸልተኝነት በታችኛው ፍርድ ቤት መከራከሪያ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ነጥቦችን በስር ፍርድ ቤት ባላነሳበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት አንስቶ ውሣኔ መስጠት የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 328(2) እና 182(2) | ግንቦት 14/2000 |
| 173 | 25890 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ዝናሽ አሰፋ (ሁለት ሰዎች) | ሌሎች ተከራካሪዎች በፍርድ ቤት በማካሄድ ላይ ባሉት ክርክር ያገባኛል የሚል 3ኛ ወገን ከውሣኔ በፊት ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41 | መጋቢት 18/2000 |
| 174 | 26670 | አዲስ አለም ሲሳይ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ልማት ባንክ | ባለገንዘብ በፍርድ አፈፃፀም ከፍርድ ባለዕዳው የተረከበው ንብረት ከዕዳው በላይ ከሆነ ልዩነቱን ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 428(2) | ህዳር 03/2000 |
| 175 | 27739 | አቶ ድንቁ ገላው<br>እና<br>ወ/ሮ ዋለ እሸቴ | ከመሬት ሽያጭ ውል ጋር በተያያዘ የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለውና በፍ/ቤት ሊስተናገድ የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231(2) | ጥቅምት 28/2000 |
| 176 | 27808 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ ማይገነት ብርሃኑ (ሁለት ሰዎች) | ከፍርድ በፊት የሚሰጥ የማገጃ ትዕዛዝ በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነን ወገን የእግድ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት ያገኘውን መብት የማይነካ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 153 (2) | የካቲት 7/2000 |
| 177 | 28522 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ የሞያሌ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት (አራት ሰዎች) | ውሣኔ የተሰጠበትና አዲስ ክስ የቀረበበት ክርክር የሥረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ የተለያየ ከሆነ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | ህዳር 3/2000 |
| 178 | 28802 | እነ ወ/ሮ በየነች ይገዙ እና አቶ ሳሙኤል ዝቅአርጋቸው | በክስ በተጠየቀውና በታመነው መሰረት ውሣኔ መስጠት የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.182(2) | ታህሳስ 8/2000 |
| 179 | 29738 | የአፓርታማ 79/6 የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት እና ወ/ት ዘርአዳም አሰገኸኝ | የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይግባኝ አይቶ መወሰን የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 10(1) | ግንቦት 14/2000 |
| 180 | 29761 | እነ አቶ ዳባ ደበሌ (አምስት ሰዎች) እና እነ የአቶ ደበበ ተፈራ ወራሾች (ሁለት ሰዎች) | ያላግባብ በመንግስት የተወረሰ ንብረትን ለማስመለስ ሲባል የሚቀርበው የፍትሐብሔር ክርክር በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ስር የማይወድቅ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 41(ሀ) | ጥቅምት 14/2000 |
| 181 | 29780 | እነ ወ/ሮ ሙሉነሽ አለሙ እና ወ/ሮ ከተማሽ ቸርነት | አስቀድሞ ውሣኔ ከተሰጠበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሌላ የክርክር ጭብጥ ማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | ጥር 29/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 182 | 30631 | ወ/ሮ ዘቢዳ ሙሣ እና እነ ወ/ሮ አሻ የሱፍ (ሁለት ሰዎች) | በህገ ወጥ መንገድ ተወስዷል /ከአዋጅ ውጭ ተወርሷል/ የተባለ ቤትን ባለቤትነት በማጣራት ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 110/87 | ህዳር 10/2000 |
| 183 | 30704 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ የአቶ በቀለ ወ/ማሪያም ወራሾች<br>(ሦስት ሰዎች) | • አዋጅ ቁጥር 47/67"ን" መሠረት አድርጐ የምርጫ ቤቱ ተወስዷል /ተወርሷል/ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርበው መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ<br>• በመንግስታዊና በህዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ስር ያሉ ቤቶች ይመለሱልኝ እንዲሁም ውዝፍ ኪራይ ይከፈለኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይ ውሣኔ መስጠት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ የፍ/ቤት ስልጣን ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 110/87, አዋጅ ቁ. 47/67 | መጋቢት 18/2000 |
| 184 | 31547 | አቶ ኪዳኔ ገ/ጊዮርጊስ እና ወ/ሮ አብርሃ ተስፋሁን | ተከራካሪ ወገኖች በግልጽ ባላመለከቱት ነገር ላይ ተመስርቶ ውሣኔ መስጠት ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.182 | መጋቢት 7/2000 |
| 185 | 31833 | ሀጅ አብዱልቃድር አህመድ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ደስታ ገ/ዮሐንስ (ሁለት ሰዎች) | በቤት ላይ የተደረገ እድሳትና ለውጥ ምን ያህል የመጠንና የአይነት ለውጥ እንዳመጣ ክርክር በተነሣ ጊዜ ልዩ አዋቂ መድቦ በማስጠናት መወሰን የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136 | ግንቦት 14/2000 |
| 186 | 32147 | አቶ መሐመድ አብዱ<br>እና<br>አቶ አብዱራሂም አብዲ | የክስ ምክንያት የሌለው አቤቱታ ተቀባይነት የማይኖረው በመሆኑ ተከሳሽ የሆነውን ወገን መጥራት ሳያስፈልግ መዝገቡ ሊዘጋ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231(1) (ሀ) | መጋቢት 9/2000 |
| 187 | 32376 | የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ ሸዋንግዛው | ከቤት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ባለቤትነትን የመፈለም ክስ ለማየት የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የስረ-ነገር ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 41(ረ) | ግንቦት 19/2000 |
| 188 | 32638 | የቂርቆስ ክ/ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ጉዳይ ጽ/ቤት እና እነ አቶ ይርጋ ንጋቴ (አራት ሰዎች) | ወደ ክርክር መግባት ያለበት አካል በክርክሩ ተሳታፊ ሳይሆን የተወሰነው ውሣኔ መብቱን የሚነካ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔው ከመፈፀሙ በፊት ውሣኔው እንዲነሳና ክርክሩ እርሱ ባለበት እንዲቀጥል መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 | መጋቢት 12/2000 |
| 189 | 33606 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ አቶ ደጀኔ አበበ (አምስት ሰዎች) | በጊዜያዊነት የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሣ ጥያቄ ቀርቦ ውድቅ ከተደረገ በኋላም ቢሆን በድጋሚ በተመሳሳይ ሁኔታ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሣ ጥያቄ ሊቀርብ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 158 | የካቲት 20/2000 |
| 190 | 34249 | እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ<br>እና<br>እነ አቶ አለሙ ወንድሙ | ለክርክር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ የሚታመን ወገን በመካሄድ ላይ በሚገኝ ክርክር ተካፋይ እንዲሆን መደረግ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2) | ሚያዝያ 28/2000 |
| 191 | 34313 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>ከበደ ታደሰ | የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብ ተከሳሽ ኃላፊነት የሚመነጨው ከተከሳሹ ኃላፊነት ስለመሆኑ እና የሦስተኛ ወገን ተከሳሽ ተጠያቂ የሚሆነው ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ ሲኖር ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.43(1) | መጋቢት 25/2000 |
| 192 | 35403 | አቶ አብዱልነጠፍ ሙሔ<br>እና<br>እነ ትዕግስት በርሄ<br>(ሁለት ሰዎች) | • ተከሳሽ ቀርቦ ያልተከራከረው በበቂ ምክንያት ማለትም መጥሪያ ሳይደርሰው መሆኑ ከተረጋገጠ የተወሰነውን ውሣኔ በማንሳት ግራ ቀኙን ማከራከር የሚገባ ስለመሆኑ<br>• ፍ/ቤት ተከራካሪ የሆነን ወገን መከላከያ ክርክር ሳይሰማ በማለፍ ውሣኔ ለመስጠት የሚችለው ተከራካሪው በችሎት ሳይቀርብ የቀረው በቂ ባልሆነ ምክንያት መሆኑን በቀረቡለት ማስረጃዎች ማረጋገጥ ሲችል ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.78 | ግንቦት 14/2000 |
| 193 | 22008 | የኪራይ ቤቶች አ/ድርጅት እና እነ አቶ ኦላና ጥርቅ ( ሦስት ሰዎች) | መክፈል የማይገባውን የከፈለ ወገን እንዲመለስለት መጠየቅ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.2164 | ሐምሌ 3/1999 |
| 194 | 22297 | የጅሚ ከተማ የአካባቢ አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ሸዋረገድ አድብር | በፍ/ብሔር ክርክር ሂደት ማን ክርክር መጀመርና ማስረዳት እንዳለበትና የተሻለ ማስረጃ ከማቅረብ አንፃር ለማን ፍርድ ሊሰጥ እንደሚገባ በተመለከተ አግባብነት ያላቸውን የህግ መርሆዎች ወደጐን በመተው የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የማይኖረው ስለመሆኑ | ሐምሌ 24/1999 |
| 195 | 22469 | የጀጀጋ ደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክ እና እነ አዳነት መንግስቱ (ሰባት ሰዎች) | • የህዝብ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ሊረጋገጥ የሚችልበት አግባብ<br>• የቤተክርስቲያንን የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ለማረጋገጥ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ አስገዳጅ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1578 | ሐምሌ 5/1999 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 196 | 22719 | የአ/አ ከተማ አስተዳደር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ተተኪ የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ ነጋሽ ዱባለ | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን አስመልክቶ በሚመለከተው አካል የሚሰጠው የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከተሰረዘ በኂላ በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የማይኖረው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195 | ጥቅምት 14/2000 |
| 197 | 23608 | የኢትዮጵያ ፕራይቬታዜሽና የመንግስት ልማት ድርጅት<br>እና<br>አቶ ኑርበዛ ተረጋ | • የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በሰጠው ውሣኔ ላይ ቅሬታ ሊቀርብ የሚችለው ለኤጀንሲው የስራ አመራር ቦርድ እንጂ ለፍ/ቤት ስላለመሆኑ<br>• የኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻና አሣሪ (Binding) ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.110/87 | ህዳር 3/2000 |
| 198 | 24269 | የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር እና<br>ተክለማሪያም መኮንን | • ግለሰቦች በከተማ ቦታ የመጠቀም /የመያዝ/ መብት የሚኖራቸው አግባብ ባለው መንግስት አካል /ባለሥልጣን/ ተፈቅዶ ሲሰጣቸው ስለመሆኑ<br>• ከሚመለከተው ባለስልጣን ፈቃድ ሳይኖር የተሰራ የከተማ ቤት ህጋዊነት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 292/78 አንቀፅ 7(1) | ህዳር 24/2000 |
| 199 | 26130 | አቶ ገ/እግዚያብሔር ከበደው<br>እና<br>ወ/ት ሰላማዊት ወ/ገብርኤል | • የከተማ ቦታ በግል ባለቤትነት ሊያዝ የማይችል ስለመሆኑ<br>• ግለሰቦች በመሬት ላይ ሊኖራቸው የሚችለው የይዞታ መብት እንጂ የባለቤትነት መብት ስላለመሆኑ<br>• ከጋብቻ በፊት በአንደኛው ተጋቢ የግል ይዞታ ሥር የነበረ መሬት ላይ በጋብቻ ወቅት የጋራ ቤት የተሰራ እንደሆነ ተጋቢዎቹ በመሬቱ ይዞታም ሆነ በቤቱ ላይ እኩል መብት የሚኖራቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 47/67<br>የኢ...ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 40(3)<br>የትግራይ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 85 | የካቲት 4/2000 |
| 200 | 27506 | እነ ሣሙኤል ውብሸት<br>እና<br>ብዙነህ በላይነህ | • ሁከት እንዲወገድ በሚል በቀረበ ክስ ላይ ተከሳሽ የሚያነሳው ባለቤትነትን የተመለከተ ክርክር አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ<br>• ሁከት ይወገድልኝ በሚል ክስ በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቱ ሊይዝ የሚገባው ጭብጥ ሁከት ተፈጥሯል ወይስ አልተፈጠረም የሚል ጥያቄ አዘል መሆን ያለበት ስለመሆኑ | ሐምሌ 19/1999 |
| 201 | 27600 | ሕብረት ባንክ አክሲዮን ማህበር እና<br>እነ አቶ ጀማል መሐመድ<br>(ሁለት ሰዎች) | በመያዣ በተያዘ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በማሻሻልም ሆነ ሌሎች አዲስ የሚሰሩ ስራዎች መያዣው የሚያጠቃልላቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.3066 | ታህሳስ 06/2000 |
| 202 | 29005 | አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና እነ ግርማቸው ይላላ<br>(ሁለት ሰዎች) | በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚገኙና በየክፍለ ከተማው የተደራጁ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤቶች ራሳቸውን የቻሉ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ስለመሆኑና በስልጣን ክልላቸው ሥር በሚነሱ ክርክሮች ተካፋይ የመሆን መብት ያላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 36/95 አንቀፅ 10(2)<br>አዋጅ ቁ. 1/95 /አዋጅ ቁ. 18/97 | ሚያዝያ 14/2000 |
| 203 | 30101 | አቶ ገዛኸኝ አድነው እና እነ ወ/ሮ ዳሳሽ ባይነሳኝ<br>(ሦስት ሰዎች) | በሌላ ሰው የመሬት ይዞታ ላይ በባለይዞታው ፈቃድ ህንፃ የሠራ ሰው የህንፃውን ግምት ተቀብሎ ህንፃውን ለማስረከብ የማይገደድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179(1) እና (2) | ህዳር 24/2000 |
| 204 | 30461 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ ኢሣ መሐመድ | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን መሬትና ድንጋይ ነክ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶችን በነፃ መጠቀም የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 80/89 አንቀፅ 6(18) | ህዳር 3/2000 |
| 205 | 33499 | አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ ዶቶር ደሌቦ | ለጊዜው ለመኖሪያነት የተሰጠ ቦታ ላይ ሳያስፈቅዱ ቤት መስራት የተሰራውን ቤት በገንቢው ወጪ እንዲፈርስ የሚያስደርግ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1178(2) | መጋቢት 25/2000 |
| 206 | 33711 | በቀድሞ ወረዳ 3 ቀበሌ 07 አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ክብርነሽ ቀደመ | የቤት ባለቤት ሳይሆን ወይም ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ለኪራይ የተከፈለ ገንዘብ እንዲመለስ የሚቀርብ አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ | መጋቢት 23/2000 |
| 207 | 33831 | ሃሰን ኢብራሂም እና ኢብራሂም ይመር ሃሰን | በህግ በግልጽ የተረጋገጠ መብት እያለ በህሊና ግምት ላይ የተመሰረተ ፍርድ መስጠት አግባብ ስላለመሆኑ | ሚያዝያ 14/2000 |
| 208 | 33924 | ወ/ሮ ገብርኤላ ኒኮላቶማስ<br>እና | ከቤት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ ክስ የሚያቀርብ ሰው የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካላቀረበ በስተቀር ሁልግዜም ቢሆን በጉዳዩ ላይ መብት ወይም ጥቅም ሊኖረው አይችልም ብሎ ለመደምደም የማይቻል ስለመሆኑ | ሚያዝያ 16/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | የኪራይቤቶች ኤጀንሲ | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195(1) | |
| 209 | 34406 | ወ/ሮ መገርቱ ነጋሣ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ፀሃይ ልጋ | ያላግባብ መበልፀግ ጋር በተያያዘ የሚነሳ የካሣ ጥያቄ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብ ከውል ውጭ በሚደርስ ሃላፊነት ሥር የተመለከተው የይርጋ ዘመን ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143(1) | ሚያዝያ<br>7/2000 |
| 210 | 20295 | አቶ ደጀኔ ለገሠ<br>እና<br>እነ አቶ መላኩ ጌታቸው | ወራሽነትን ካረጋገጡ በኋላ ንብረት ተይዞብኛል ይመለስልኝ የሚል ጥያቄ ከሦስት አመት በኋላ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(1) | ሐምሌ<br>5/1999 |
| 211 | 25567 | ወ/ት አይናለም አበበ<br>እና<br>አቶ ደገፉ ጉርሙ | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000 ወራሽ ነኝ ወይም ወራሽነቴ ይረጋገጥልኝ ከሚል ጥያቄ ጀምሮ የውርስ ንብረት ያለ አግባብ ተይዞብኛል በሚል ለሚቀርብ አቤቱታ ጭምር ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 999, 1000 | ህዳር<br>12/2000 |
| 212 | 25664 | አቶ ተገኝ ይማም<br>እና<br>እነ አቶ ካሣሁን ደሳለኝ | በወራሾችና ወራሽ ባልሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሳ የውርስ ንብረትን የተመለከተ ክርክር በአሥር ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 | ግንቦት<br>7/2000 |
| 213 | 26422 | ወ/ሮ ስንልሽ ማዘንጊያ<br>እና<br>እነ አቶ ተስፋ ማዘንጊያ | ከውርስ ሀብት ጋር በተያያዘ ወራሽ ነኝ የሚል ወገን መብቱንና የውርስ ንብረቶቹ በሌላ ወራሽ መያዛቸውን ካወቀ ከሦስት ዓመት በኋላ የሚያቀርበው የወራሽነት ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(1) | ጥቅምት<br>28/2000 |
| 214 | 28686 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>አቶ ግዛው መንጀታ | ውል የመጣስ ተግባር ተጀምሮ ያልቆመ ይልቁንም በመቀጠል ላይ ያለ ተግባር መሆኑ በማናቸውም ጊዜ ግዴታን ለመጠየቅ የሚያስችል ስለመሆኑና በይርጋ ታግዷል ለማለት የማያስችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845, 1846 | ህዳር<br>24/2000 |
| 215 | 28997 | ስለ አሶሳ ዞን ግብርና እና ትምህርት መምሪያ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል መንግስት ፍትህ ቢሮ<br>እና በላይ ወርቁ | የመብት ጥያቄን ከፍርድ ቤት ውጪ ላሉ አስተዳደር አካላት ማቅረብ የይርጋ ጊዜን የማያቋርጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1851(ለ) | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 216 | 29920 | የባህር ዳር ጨ/ጨ/አ/ማኀበር እና አቶ አመሸ ሰይድ | ዳኝነት የተጠየቀበት ነገር ተቀባይነት ሣያገኝ የታለፈ እንደሆነ እንደተከለከለ የሚቆጠር ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(3) | ጥቅምት<br>26/2000 |
| 217 | 31185 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ይርጋ በተቋረጠ ጊዜ ቀድሞ የነበረው የይርጋ ጊዜ እንደ አዲስ መቆጠር የሚጀምር ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1852(1) | ግንቦት<br>12/2000 |
| 218 | 31217 | የቴሌኮምኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ጫሊ ሐሰን | የደሞዝ ጭማሪና ቦነስን የተመለከተ ክስ በስድስት ወር ውስጥ አለመቅረቡ መብቱን በይርጋ የሚያሳግድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 162(3) | ግንቦት<br>14/2000 |
| 219 | 31857 | መሐመድ አብደላ<br>እና<br>የድሬዳዋ ኢትዮ ጂቡቲ ምድር ባቡር | የአሰሪ የስራ ስንብት እርምጃ የመውሰድ መብት ለስንብቱ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ከተከሰተበት ጀምሮ በሰላሳ የስራ ቀናት ውስጥ ተግባራዊ ካልሆነ መብቱ በይርጋ የሚቀር ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/97 አንቀፅ 27(3) | መጋቢት<br>17/2000 |
| 220 | 32788 | የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት<br>እና<br>አቶ ግርማ ተገኝ | አሠሪ የሠራተኛን መብት በጽሁፍ ያወቀ መሆኑ ሠራተኛው በሚያቀርበው አቤቱታ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን የይርጋ ገደብ የሚያቋርጥ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 164(3) | መጋቢት<br>18/2000 |
| 221 | 34011 | እልፍነሽ አማረ እና አቶ ግርማ አማረ | ቤት በፍ/ብሔር ህጉ ውስጥ እንደ ርስት የማይቆጠርና የይርጋ መርሆ ተፈፃሚ የሚሆንበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(2) | መጋቢት<br>25/2000 |
| 222 | 31748 | ይስማው ድረስ<br>እና<br>ይበልጣፍ ፍቅር | ክርክር የቀረበበትን ጉዳይ የሚገዛው የህግ ክፍል ይርጋን አስመልክቶ በተለይ የሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ በሌለ ጊዜ የአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677(1),1845 | የካቲት<br>18/2000 |
| 223 | 18832 | የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>እነ አቶ ከበደ ቱሉ<br>(ስድስት ሰዎች) | ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛ የተወሰነው ጊዜ ከማብቃቱ በፊት የስራ ውሉ ያለ በቂ ምክንያት ከተቋረጠ ሠራተኛው የውሉ ጊዜ ወይም ስራው እንኪያልቅ ቢቆይ ያገኘው የነበረውን ደሞዝ የሚያህል ደሞዝ የሚከፈለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 43(4)(ለ) | ህዳር<br>3/2000 |
| 224 | 20416 | አቶ ቢንያም ገረመው | ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ፍርድ ቤት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ | ታህሣሥ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እና<br>የቻይና መንገድና ድልድል ስራ ድርጅት | ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራ ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ከሆነ ክሱ እንዲሻሻልና ክርክሩ እንዲለወጥ ሊፈቀድ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91 | 8/2000 |
| 225 | 21329 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ በቀለ ኩምሳ | የሥራ መሪ የሆነ ሰው የሥራ ውሉ ተቋርጧል በሚል ሣይሰራ ለቆየበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈለው የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ | ጥቅምት 19/2000 |
| 226 | 22275 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>አቶ ኃይሌ ገ/ሥላሴ | • አሰሪ የሥራ ውሉ ዘመን ከማለቁ በፊትም ቢሆን በቂና ህጋዊ ምክንያት ካለው የሠራተኛን የሥራ ውል ሊያቋርጥ ስለመቻሉ<br>• በበቂ ምክንያት የተደረገ የሥራ ውል ማቋረጥ ማስጠንቀቂያ አልተሰጠም በሚል ህገ-ወጥ ስንብት ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ<br>• በአንድ ድርጅት ውስጥ ያለን የስራ መደብ በሌላ ሦስተኛ ወገን እንዲከናወን አስተላልፎ መስጠት (out sourcing) የሥር ውል ለማቋረጥ ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 35 | ሐምሌ 10/1999 |
| 227 | 25317 | ጥቁር አባይ ትራንስፖርት እና ደሳለኝ አብርሃ | በህገ ወጥ መንገድ የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ በሞተ ጊዜ ለጥገኞቹ ክፍያ የሚፈፀምበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/ 96 አንቀፅ 39(2),110(2), 40 | ህዳር 10/2000 |
| 228 | 25511 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና አቶ አብራራው ከፍያለው | በህጋዊ መንገድ የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋድ ቁ. 377/96 አንቀፅ 39 | ጥቅምት 2/2000 |
| 229 | 26077 | አቶ አይናለም ባይሌ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ከተደነገገው ይልቅ በአሰሪና ሠራተኛው መካከል የሚደረገው የህብረት ስምምነት ለሠራተኛው የተሻለ መብትና ጥቅም የሚያስገኝ በሆነ ጊዜ የህብረት ስምምነቱ ተፈፃሚ የሚሆን ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 134(2) | ሐምሌ 12/1999 |
| 230 | 27704 | ድራጋዶስ ጂ እና ፒ የመንገድ ስራ ድርጅት<br>እና<br>አብዲ ሁሴን | የሥራ ውሉ በህገ-ወጥ መንገድ ተቋርጧል በሚል ወደሥራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሠራተኛ ካልሆነ በስተቀር ውዝፍ ደመወዝ የማይከፈል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(5) | ጥቅምት 5/2000 |
| 231 | 27959 | የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>አቶ አሊ መሐመድ | • አንድ ሠራተኛ የሥራ ውሉ ተቋርጦ ለነበረበት ጊዜ የዓመት ዕረፍት ሊያገኝ የማይችል ስለመሆኑ<br>• የዓመት ፈቃድ ከሁለት ዓመታት በላይ ሊተላለፍ የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 79(5) | ህዳር 3/2000 |
| 232 | 29692 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ አለማየሁ ከበደ | አሠሪ ቋሚ ስራ ሆኖ እየተቋረጠ አልፎ አልፎ የሚሰራ ስራ እንዳለቀ የሠራተኛን ውል ለማቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ | ጥቅምት 12/2000 |
| 233 | 29740 | አቶ ስሜነህ ተክሉ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ | ፍርድ ቤቶች በቀረበ ክስ ላይ የዕዳ ማቻቻል ጥያቄ በተነሣ ጊዜ ማስረጃዎችን በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ | ሚያዝያ 2/2000 |
| 234 | 29866 | ቻይና ዋንቦ ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን እና ወርቅነህ ምህረቱ | የውክልና ስልጣን ማስረጃ በወካይና በተወካይ መካከል የቅጥር ውል ስለመኖሩ የሚያስረዳ ስላለመሆኑ | ግንቦት 7/2000 |
| 235 | 29949 | የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ዋሲሁን አዳነ | ፍርድ ባልተሰጠበት ጉዳይ ላይ የሚሰጥ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ | ሐምሌ 19/1999 |
| 236 | 30956 | የወረዳ 5 አጠቃላይ ነጋዴዎች ማህበር እና አቶ በድሉ ጫላ | ዳኝነት ባልተጠየቀበት ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠት አግባብ ስላለመሆኑ | ሚያዝያ 9/2000 |
| 237 | 31402 | የኢትዮጵያ አገር አቋራጭ ከፍተኛ አውቶብስ የግል ባለንብረቶች ማህበር እና አቶ አያሌው ይርጉ | በጡረታ የተገለለን ወይም የጡረታ ዕድሜው ያለፈን ሠራተኛ ወደ ሥራ መልስ ተብሎ አሰሪ የሚገደድበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 24(3)<br>አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀፅ 12(1)(ሐ) | ሚያዝያ 30/2000 |
| 238 | 32545 | አቶ ግርማ ሽፈራው<br>እና<br>የክርስቲያን በጐ አድራጐት ልማት ድርጅት | የፕሮቪደንት ፈንድ ባለመብት የሆነ ሰው በአስር አመት ውስጥ መብቱን ካልጠየቀ መብቱ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 162<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677(1),1845 | ግንቦት 14/2000 |
| 239 | 33314 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ አቶ አለማየሁ ወልዴ | በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ሥራውን በማከናወን ላይ የነበረን ፋብሪካ የተረከበ ባንክ ከሠራተኞች መብቶች ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጥ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 16 | ግንቦት 28/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | (አስር ሰዎች) | አዋጅ ቁ. 97/90 | |
| 240 | 33513 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>ዘውዴ ተናኘ | በአንድ የስራ መደብ ላይ በቋሚነት የደረጃ እድገት ይሰጠኝ በማለት የሚቀርብ ክስን ለማየት የክልል ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 138 | ጥር<br>27/2000 |
| 241 | 34588 | የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>ደረጀ ወልደ ኪዳን | በወንጀል ጉዳይ ተከሶ ነፃ የተባለ ሰው በፍትሐብሔር ረገድ ከቀረበበት ክስም የግድ ነፃ ይሆናል ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ የሚችል ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27 | ግንቦት<br>5/2000 |
| 242 | 35440 | የዋልያ አገር አቋራጭ አውቶቡስ ድርጅት<br>እና<br>ብርሃኑ አለሜ | ከሠራተኞች ማህበር ወይም ተወካይ ጋር በመመካከር በአሰሪ የሚደረግ የሠራተኞች ቅነሳ የህግ አግባብ ያለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 28(1) | ግንቦት<br>19/2000 |
| 243 | 29415 | ዋተር አክሽን እና ይልማ አሰፋ | አዲስ ወደ ተዛወሩበት ቦታ በመሄድ ስራ አለመጀመር እና ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በስራ ገበታ ላይ አለመገኘት በአሰሪው አነሳሽነት የስራ ውልን ለማቋረጥ በቂና ህጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(2)(ለ) | ጥር<br>27/2000 |
| 244 | 32822 | ጂ.ሰቨን የንግድና ኢንዱስትሪ የመኸር ቃጫ ውጤቶች ፋብሪካ እና መኮንን አበራ | ያለ በቂ ምክንያት ከስራ መቅረት አሠሪ የስራ ውልን ለማቋረጥ የሚያስችለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1) (ለ) | ጥር<br>27/2000 |
| 245 | 32229 | መሪጌታ ልሣነወርቅ በዛብህ<br>እና<br>ጠቅላይ ቤ/ክህነት ጽ/ቤት | የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ውሣኔ መሻር ሳያስፈልገው ጉዳዩ ስልጣን ወዳለው አካል ቀርቦ መታየት የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | ሚያዝያ<br>30/2000 |

**ቅጽ 7**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 246 | 12719 | ሉክሰር የቱሪስትና የጉዞ ወኪል ኃላ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>ብሩኔይስ ኃ/የተ/የግ/ማኀበር | በሁለት ወገኖች መካከል የተፈረመ ሰነድን እንደ ህጋዊ ስምምነት ለመውሰድ የፈራሚ ወገኖችን ሃሳብና ፍላጐት መመርመር አስፈላጊ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1734, 1952/1/ | ታህሳስ<br>17/2000 |
| 247 | 20232 | አቶ ትዕግስቱ ብዛ<br>እና<br>አቶ ይሃ ይብሬ | የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታዎች የሚፈጠሩባቸውና የሚረጋገጡባቸው በመሆናቸው የውል ህግ መሰረታዊ ድንጋጌዎች መሟላታቸው አስፈላጊ ሁኔታ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 715, የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1706, 1679 | ሐምሌ<br>24/1999 |
| 248 | 23609 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና አቶ አሰበወርቅ ዘገዬ | የስራ መሪ የሥራ ውል ያለአግባብ በተቋረጠ ጊዜ የስራ መሪው ሊያገኝ ስለሚገባው ልዩ ልዩ ክፍያዎች እና ጥቅማጥቅም<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2573, 2574/2/, 2570/2/, 2577, 2562 | ታህሳስ<br>15/2000 |
| 249 | 30298 | አቶ የሺወንድም አቡሃይ<br>እና<br>አቶ አየነው ማለደ | የመጥፋት ውሣኔ የተሰጠበት ሰው ንብረቱ ወደ 3ኛ ወገን የተላለፈ በሆነ ጊዜ የንብረቱን ዋጋ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 171 | ጥር<br>20/2000 |
| 250 | 16218 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አስካለ ሁንዴ(ሁለት ሰዎች) | ባንኮች ከሚሰጡት ብድር እና የመያዣ ውል ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች አዋጅ ቁ. 97/90"ን" ዓላማ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በባንኮች የሚወጡትን የፎርክሎዠር መመሪያዎችና አግባብነት ያላቸውን ህግጋት ግምት ውስጥ በማስገባት እልባት ማግኘት ያለባቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3 እና 4, አዋጅ ቁ. 216/92 | መጋቢት<br>16/2000 |
| 251 | 25863 | የኢት/ልማት ባንክ እና የኢት/ንግድ ባንክ (ሁለት ሰዎች) | ለባንክ በመያዣነት በተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚኖር የቀዳሚነት መብት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3088, 3052, 3081,3059 | ጥቅምት<br>26/2000 |
| 252 | 29269 | የኢት/ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ አቶ ዋለልኝ አያሌው(ሁለት ሰዎች) | • በፍርድ የተቋቋመ መያዣ ላይ ፍርዱ እንዲሰጥ ያደረገው ባለገንዘብ መያዣ በሆነው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ስለመሆኑ እና<br>• የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403 ተፈፃሚነት የአንድ ፍርድ ባለዕዳ ንብረት በእርሱ ላይ የቀረቡትን ገንዘብ ጠያቂዎች | ጥቅምት<br>15/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ፍላጐት የሚያሟላ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ክፍፍሉ ጋር በተገናኘ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3041, 3044, 3059/1/, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403,154 | |
| 253 | 29375 | የት/ንግድ ባንክ<br>እና<br>ተስፋዬ ገ/ጊዮርጊስ | የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣነት ከተሰጠ በኋላ በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ የሚደረግ ማናቸውም የማሻሻል ሥራ የመያዣ ውሉ አካል ተደርጐ የሚወሰድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3066 አዋጅ ቁ. 97/90 | ጥቅምት<br>19/2000 |
| 254 | 33295 | ወ/ሪት ብርሃኔ አበበ እና እነ አቶ ማርቆስ ተርፋ (አራት ሰዎች) | የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በማንኛቸውም ሰነድ ላይ የተመሰረተ ቢሆንም ከተፃፈበት ቀን አንስቶ የማይንቀሳቀሰው ንብረት በሚገኝበት አገር ባለው በማይንቀሳቀስ ርስተ መዝገብ ካልተፃፈ በቀር ምንም አይነት ውጤት የማያስገኝ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3052, 3053,1605, 1607, 1606 | ግንቦት<br>21/2000 |
| 255 | 23024 | ወ/ሮ ፋጤ በሽር እና መልዓክ ገነት ዮሐንስ አምባው<br>እና<br>የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ | በጣልቃ ገብነት ተሳታፊ ሆኖ የፍርድ ተጠቃሚ የሆነ ወገን ዋና ተከራካሪ ከሆኑት ወገኖች መካከል በአንዱ አነሣሽነት ጉዳዩ በይግባኝ በሚታይበት ጊዜ በሥር ፍርድ ተጠቃሚ የሆነው ጣልቃ ገብ ባልተጠራበት ሁኔታ የሚሰጥ ውሣኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 40/5/"ን" የሚፃረር ስለመሆኑ | ሐምሌ<br>24/1999 |
| 256 | 24221 | ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና 4እነ ወ/ሮ አረጋሽ አምደሚካኤል | ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር ጋር የተደረገን የኪራይ ውል መሰረት በማድረግ የተያዘ ቤትን ያለአከራዩ ፍቃድ ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ለኪራይ ውሉ መሰረዝ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ | ህዳር<br>24/2000 |
| 257 | 25938 | ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና<br>የአቶ ገ/ሕይወት ከ7ዶም ወራሾች<br>(ሁለት ሰዎች) | የኪራይ ውል የተለየ ፎርም መከተል እንዳለበት የሚያስገድድ የህግ ድንጋጌ የሌለ ስለመሆኑ እና በሁለት ተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚፀና ውል /ህጋዊ ውጤት ያለው ውል/ ለመመስረት በሁለቱም መካከል ስምምነት መኖሩ ብቻ በቂ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719/1/,1719-1930, 2898/3/ | መጋቢት<br>25/2000 |
| 258 | 28025 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>አቶ ታደለ አበበ | ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ለተከራዩ በሚሰጥ ማስታወቂያ በማናቸውም ጊዜ ሊቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ እና የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ/ለማፍረስ ለተከራዩ ማስታወቂያ /ማስጠንቀቂያ/ መስጠት አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966/1/ | ጥር<br>20/2000 |
| 259 | 31601 | ወ/ሮ መዓዛ ይሕደጐ እና እነ አየለ ወልዴ (ሁለት ሰዎች) | የኪራይ ውል ተቋርጦ ውዝፍ ኪራይ እንዲከፈለኝና ቤቱንም ልረከብ በሚል የሚጠየቅ ዳኝነት የኪራይ ገንዘብ የተጠየቀበትን ቤት ግምት ጭምር ታሳቢ ተደርጐ የዳኝነት ክፍያ ሊቀርብበት የሚገባ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 227/2/, 226 | የካቲት<br>11/2000 |
| 260 | 31634 | ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ የአቶ ወርቁ ሚስት ወ/ሮ ጽጌ በየነ<br>(ሰባት ሰዎች) | መጠየቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ እስከ 2 ዓመት ድረስ ሳይከፈል የቀረ የኪራይ ዕዳ እንደተከፈለ የህግ ግምት ይወሰድበታል ማለት ባለገንዘቡ /አከራዩ/ ክስ መስርቶም ቢሆን ዕዳውን ለማሰብሰብ የማይችል መሆኑን ለማመላከት እንጂ ተከራዩ /ባለዕዳው/ ግዴታውን እንደተወጣ የሚያስቆጥረው ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024/መ/ | መጋቢት<br>4/2000 |
| 261 | 32521 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና ዳባ ኢጃቶ | የታወቀ የኪራይ ውል ግንኙነት ሳይኖር ወይም ባለቤት ሳይሆኑ በማይንቀሳቀስ ንብረት መገልገል የተገለገለውን ወገን በንብረቱ በበለፀገው መጠን ኃላፊ የሚያደርገው ስለመሆኑ | ሚያዝያ<br>7/2000 |
| 262 | 34456 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>ወ/ት ደብሪቱ ወልደሃና | ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ውሉ የተደረገበት ጊዜ ካለቀና ውሉ ወደ ያልተወሰነ ጊዜ ከተቀየረ የኪራይ ውሉን በማናቸውም ጊዜ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ የሚቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966 | ግንቦት<br>14/2000 |
| 263 | 18380 | አቶ ማሞ ደምሴ እና እነ አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሔር<br>(ሁለት ሰዎች) | ውል ይጽደቅልኝ በሚል ለፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231/1//ሀ/ | ጥቅምት<br>5/2000 |
| 264 | 22448 | ኦርቢስ የንግድና ቴክኒክ ክፍል አ/ማህበር እና አቶ ሙሉነህ ካሳ | ፍርድ እንዲፈፀም ለመጠየቅ ችሎታ ያለው ፍርድ የተፈረደለት ሰው /ወገን/ ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378/1/ | ጥቅምት<br>28/2000 |
| 265 | 22860 | ሰንላይት ኢንዱስትሪና ማከፋፈያ ኩባንያ<br>እና<br>አቶ ካሣዬ ዘውዴ | አንድ ግዴታ መኖሩን ለማስረዳት ህጉ የተለየ ማስረጃ እንዲቀርብ ያዘዘ ካልሆነ በቀር ግዴታው መኖሩን በጽሁፍ፣ በምስክር፣ በህሊና ግምት በተከራካሪው ወገን እምነት ወይም በመሃላ ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2002 | የካቲት<br>18/2000 |
| 266 | 23331 | ጀማል ሐሚድ እና እነ ወ/ሮ ለተሃይማኖት ተክሌ<br>(አምስት ሰዎች) | በህግ ፀንቶ ያለ የሽያጭ ውልን መሰረት በማድረግ የተገኘ መብት ውሉ ፈራሽ እስካልተደረገ ድረስ የሚቀጥል ስለመሆኑ | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 267 | 24974 | እነ አቶ ፈቃዱ ደሬሴ (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ ንጉሴ ወርቁ<br>(ሁለት ሰዎች) | በውል ከተገባ ግዴታ አመዛኙ ክፍል ተፈፀመ ወይም/እና አይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ተከስቷል ለማለት ባልተቻለ ጊዜ ውል እንዲሰረዝ ለመወሰን የማይቻል ስለመሆኑ | ታህሳስ<br>8/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771,1784, 1785 | |
| 268 | 26996 | አቶ በቀለ ደቦጭ እና እነ ወ/ሮ አዛለች ደሣለኝ (ሰባት ሰዎች) | ውል የተደረገበት ጉዳይ ሊፈፀም የማይችል ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተዋዋይ ወገኖችን ወደ ነበሩበት ቦታ የመመለስ ውጤት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1715, 1815 | የካቲት 18/2000 |
| 269 | 27349 | ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኪባንያ እና ዘላቂ ግብርና ተሐድሶ ኮሚሽን | ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው የሚፈጠርን አለመግባባት በስምምነት ወይም ደግሞ በአስታራቂ አማካኝነት ለመፍታት የተስማሙ ከሆነ ይኼው ስምምነት ተፈፃሚ መሆን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1765, 1731/1/ | ታህሳስ 8/2000 |
| 270 | 28663 | አቶ ካሣሁን ገዛኸኝ እና ወ/ሮ አልማዝ ወልዴ | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 658 ተ.ጋቢ. ወገን ከሦስተኛ ወገን ጋር ያደረገውን ውል ለማፍረስ ምክንያት ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 658, 686 | ጥር 27/2000 |
| 271 | 29233 | አቶ ሙሂዲን ፋሪስ እና አቶ እያሱ በዕደ ማርያም | በተዋዋይ ወገኖች መካከል የተደረገ ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 መሰረት የተሟላ አይደለም በሚል ውሣኔ ሲሰጥ ተዋዋይ የነበሩ ወገኖች በፍ/ብ/ህ/ቁ 1815 መሰረት ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723, 1720/1/, 1815 | ግንቦት 7/2000 |
| 272 | 32222 | አቶ መሐመድ ኢብራሂም እና አቶ ታይደር ማች | ያልነበረ ቤትን ሠርቶ ለማስተላለፍ በሚል የሚደረግ ስምምነትን በተመለከተ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2876, 1723, 3019, 3020/2/ | የካቲት 4/2000 |
| 273 | 32899 | ወ/ሮ አስካለ ማርያም ታደሰ እና አቶ ተሾመ ካሣዬ | የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን በተመለከተ የተደረገ የሽያጭ ውል ተቀብሎ ከማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ላይ ከማያያዝና ከመፃፍ በስተቀር የሽያጭ ውሉን የማዋዋልና የማረጋገጥ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ | ግንቦት 21/2000 |
| 274 | 23322 | ወ/ሮ አዳነች ወርዶፋ እና እነ ወ/ሮ አስናቀች ወርዶፋ | የውርስ ሀብት አጣሪ የንብረት ባለቤትነትን የመወሰን ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 956 | ሰኔ 19/2000 |
| 275 | 25869 | ወ/ሮ አየለች አልታዬ<br>እና<br>ወ/ሮ አስናቀች አየለ | የማይንቀሳቀስ ንብረት የጋራ ባለሀብት የሆኑ ሰዎች ንብረቱን በአይነት ለመከፋፈል ባልቻሉ ጊዜ ንብረቱ በሃራጅ ተሸጦ ገንዘቡን መካፈል ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1272, 1273 | ሰኔ 19/2000 |
| 276 | 30158 | እነ ወ/ሮ ፀሐይነሽ አደም ሞግዚት ሐይሉ ሲሳይ<br>እና<br>የኮ/ል እሸቱ ተስፋዬ ወራሾች | በፍ/ብ/ህጉ ውስጥ “ከዘር የወረደ ርስት” በሚል የተቀረበው አገላለጽ በህገ-መንግስቱ የተሻረ ወይም ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000/2/ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 40 | ሰኔ 19/2000 |
| 277 | 32414 | ወ/ሮ ባዩሽ ደጀኔ እና እነ ወ/ሮ ሃሳብከፋይ ጌራወርቅ (ሁለት ሰዎች) | ኑዛዜ ፈራሽ ነው ይባል በሚል የሚቀርብ ክስ እና የተሰጠ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ በሚል የሚቀርብ ተቃውሞ የተለያዩ ይዘትና ውጤት ያላቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996/1/, 998/1/, 973, 996/2/ | ሰኔ 24/2000 |
| 278 | 34076 | ወ/ሮ ዘነበወርቅ ወልዱ ፀጋ እና እነ እማሆይ ድብቅነሽ ግዛው (ሁለት ሰዎች) | የውርስ ሃብቶች በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ በሆነ ጊዜ የሚነሱ ክርክሮች የውርሱ ክፍያ በተጀመረበት ቦታ ለሚገኝ ፍ/ቤት የሚቀርቡና የሚስተናገዱ ስለመሆናቸው<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 23 | ሰኔ 10/2000 |
| 279 | 24703 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ት/ቢሮ | በህግ ተቀባይነት ያለው የኢንሹራንስ ውል የሚቋቋምበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1725, 1727 የንግድ ህግ ቁጥር 651, 654, 657 | ሚያዝያ 9/1999 |
| 280 | 22069 | የአማራ ብ/ክ/መንግስት ፍትሕ ቢሮ እና አቶ አስማማው አራጌ | በወንጀል ህግ የሃሳብ ክፍል የሚረጋገጠው ከወንጀል ድርጊት አፈፃፀሙ በመነሳት ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ቁ. 522 /1/ /ሀ/ | ጥቅምት 28/2000 |
| 281 | 22452 | የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና አሣምነው ገ/መስቀል | በወ/መ/ህ/ቁ. 522/1/ /ሀ/ ሥር የተመለከቱት የወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦች ለየራሳቸው የሚቆሙ ስለመሆናቸው<br>የወ/መ/ህ/ቁ. 522/1/ /ሀ/ | ሐምሌ 30/2000 |
| 282 | 23855 | የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ<br>እና<br>አቶ ፀጋሁን መንግስቱ | የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሳይፈፀምበት የመንግስት ቀረጥ ያልተከፈለበት መኪና ይዞ የተገኘ ግለሰብ በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ ያልተባለ ቢሆንም ግለሰቡ ተገቢውን ቀረጥ ከፍሎ መኪናውን መረከብ አልያም ደግሞ መኪናው መወረስ ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 74 አዋጅ ቁ. 388/95 አንቀጽ 80/3/ | ጥቅምት 26/2000 |
| 283 | 24278 | ሰለሞን ሄርጃቦ<br>እና የደ/ብ/ብ/ ሕ/ክ/መ/ የሥ/ፀ/ሙ/ኮ/ዓ/ሕግ | በአዋጅ ቁ. 214/74 አንቀጽ 13/1/ መሠት የተከሰሰ ሰው ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው እንዲጠብቃቸው በአደራ የተረከባቸውን ወይም በሥራው አጋጣሚና ምክንያት በእጁ የገቡትን ንብረቶች የወሰደው/የሰወረው/ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ | ህዳር 10/2000 |
| 284 | 28952 | የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ<br>እና | በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 122/2/ መሠረት ከሣሽ አቅርቦት የነበረውን ክስ ካነሣ በኋላ እንደገና ክሱን ለመቀጠል የሚችል ስለመሆኑ | መጋቢት 16/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አቶ ባንቲ ታኤራ | የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 122/2/, /5/ | |
| 285 | 29325 | ኤርምያስ ካሣ ተፈራ እና ዓቃቤ ሕግ | በወንጀል ክስ የቀረበበት ሰውን አስመልክቶ ጉዳዩ በሌለበት ነው የታየው ሊባል የሚችልበት አግባብ<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ. 161/1/ | የካቲት 18/2000 |
| 286 | 31734 | አቶ አስናቀ በቀለ እና ዓቃቤ ሕግ | በወንጀል ተከሶ የተያዘ ሰው ዋስትና በጠየቀ ጊዜ ፍ/ቤት ተከሳሹ ተመልሶ ሊቀርብ አይችልም የሚል ግምት ለመውሰድና ዋስትናን ለመከልከል በቂ ምክንያት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 67/ሀ/ | ጥቅምት 15/2000 |
| 287 | 34077 | አቶ ሰይድ ይመር እና የአማራ ክልል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን | በወንጀል የተከሰሰ ሰው የሚያነሳው የዋስትና ጥያቄ መታየት ያለበት ሊወሰንበት ከሚችለው ቅጣት አንፃር ስለመሆኑ | መጋቢት 9/2000 |
| 288 | 34280 | አቶ ግርማይ ደስታ እና ዓቃቤ ሕግ | በወንጀል ህግ ቅጣት ሊገደብ የሚችልበት አግባብ<br>የወንጀል ህ/ቁ. 192,194 | ግንቦት 14/2000 |
| 289 | 34521 | የአማራ ብ/ክ/መ/ፍትሕ ቢሮ እና ስንታየሁ ተፈራ | በወንጀል ህግ ቅጣትን በልዩ የህጉ ክፍል ከተወሰነው መነሻ ዝቅ አድርጐ በማቅለል ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ<br>የወ/ህ/ቁ. 184, 179 | ሰኔ 3/2000 |
| 290 | 35611 | ሻለቃ ታደሰ ካሕሳይ እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ | በወንጀል ህግ ጉዳዩን ለመስማት በተቀጠረበት ዕለት አቤቱታ አቅራቢው ባልቀረበ ጊዜ አቤቱታው እንዲሰረዝ የሚደረገው አቤቱታ አቅራቢው ጉዳዩን በትጋት ያልተከታተለ ወይም በቸልተኝነት የተወው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ 193/1/ | ሰኔ 19/2000 |
| 291 | 18809 | አቶ ሚሊዮን ዑመር<br>እና<br>ዮፌዴራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን | በደንብ ቁጥር 75/1993 ኮምፒዮተርን ጨምሮ ከተለያዩ መሳሪያዎች ህንፃዎችና ሌሎች ዕቃዎች ኪራይ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ለመሰብሰው የተደነገገው መኪናን በማከራየት የሚገኝን ገቢ የሚያካትት ስለመሆኑ<br>ደንብ ቁጥር 75/93 አንቀጽ 2/9/ ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 24/2/ /ሸ/ | ሰኔ 12/2000 |
| 292 | 19258 | አቶ ተክሌ ዋቅጅራ እና አቶ ሾንጣ ጉቡ | የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር መዋጮ መከፈል ያለበት ማህበሩ ሲቋቋም እንጂ ተቋቁሞ ሥራው ከተጀረ በኂላ ስላለመሆኑ | ሐምሌ 12/1999 |
| 293 | 23389 | የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማኀበር እና እነ ባህሩ አብርሃም (ሁለት ሰዎች) | የአክሲዮን ማህበር አባላት መብታቸውን የሚነካ ድርጊት በማህበሩ አስተዳዳሪዎች በተከናወነ ጊዜ በቀጥታ አስተዳዳሪዎቹን ሊከሱ ስለመቻላቸው<br>የንግድ ህ/ቁ. 364,365,367 | ሐምሌ 10/1999 |
| 294 | 28923 | የባህር ዳር ጨ/ጨ አክስዮን ማሕበር እና የባህር ዳር ልዩ አስተዳደር እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ | የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታ ከመቀየራቸው በፊት ያለባቸውን የዕዳ ክርክር በኃላፊነት ይዞ መከራከር ያለበት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባላደራ ቦርድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 208/1992 አንቀጽ 5/1/, 6/1/ /ሐ/, አዋጅ ቁ. 182/1992 | ግንቦት 7/2000 |
| 295 | 10489 | የስራና ከተማ ልማት ሚ/ሮ ተተኪ መሠረተ ልማት ሚ/ር<br>እና<br>የቀድሞ ብሐራዊ መሐንዲሶችና ሥራ ተቋራጮች ኃ/የተ/የግ/ማ | በበጀት የሚተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤት የፍርድ ባለዕዳ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔውን ለማስፈፀም ለሌላ ጉዳይ በበጀት የተያዘውን እና የሰራተኛ ደመወዝን የሚያካትተውን ገንዘብ ከብሔራዊ ባንክ ወጪ ሆኖ እንዲከፈል ለማዘዝ ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 404 | ሐምሌ 24/1999 |
| 296 | 18576 | ወ/ሮ ደስታ መኮንን<br>እና<br>ወ/ት መሰሉ ጌታሁን | የውርስ ማጣራት ሪፖርት ከፀደቀ ወይም በፍ/ቤት ተቀባይነት ካገኘ በኂላም ቢሆን እንደ ፍርድ ተቆጥሮ በቀጥታ የአፈፃፀም አቤቱታ ሊቀርብበት ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 944, 946, 956, 960, 996 | ግንባት 26/2000 |
| 297 | 19283 | ወ/ሮ መድሐኒት ኃይሉ<br>እና<br>የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ | ባንክ ለሰጠው ብድር በመያዣነት እጁ ያስገባውን የተበዳሪ ንብረት በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛው የሃራጅ ጨረታ ለሽያጭ አቅርቦ ገገር ያልተገኘ እንደሆነ ንብረቱን ሊያስቀር የሚችለው ለመጀመሪያው ጨረታ መነሻ በተሰጠው የዋጋ ግምት መሰረት ስለመሆኑ | መጋቢት 9/2000 |
| 298 | 22481 | አቶ ክፍሌ ወልዴ<br>እና<br>ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | በሀራጅ ጨረታ የአሻሻጥ ስርዓት ላይ "ግዙፍ የሆነ ጉድለት" ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር እንደተፈፀመ ሊቆጠር የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 422/3/, 428/5/, 455, 428/1/ | መጋቢት 4/2000 |
| 299 | 22930 | ወ/ሮ ታድሬ አባተ<br>እና<br>ወ/ሮ ዓለም ገ/የሱስ | ባልና ሚስት በፍቺ ከተለያዩና የንብረት ክፍፍል ከተደረገ በኂላ ከአንደኛው ተጋቢ የግል ተግባር የሚመነጭ ዕዳ አፈፃፀም የተጠየቀው /የቀረበው/ ከፍቺ በኂላ እስከሆነ ድረስ ለዕዳው ምክንያት ከሆነው ተጋቢ ብቻ የሚጠየቅ ስለመሆኑ | ሚያዝያ 30/2000 |
| 300 | 23733 | እነ ሃፍቶም ገ/እራሃ (ሁለት ሰዎች)<br>እና | ከንብረት ክፍፍል ጋር በተያያዘ በዋናው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ንብረት መካፈል ከተቻለ እንዲካፈል ካልሆነ ደግሞ በባለሙያ ተገምቶ እንዲካፈሉ በሚል የተሰጠን ፍርድ መነሻ በማድረግ የአፈፃፀም ችሎት /ፍ/ቤት/ ከተከራካሪ | ህዳር 24/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እነ ሙሉ ካሣ (አራት ሰዎች) | ወገኖች መካከል አንደኛው ግምቱን ከፍለው ንብረቱን እንዲያስቀሩ በሚል ትዕዛዝ ለመስጠት የማይችል ስለመሆኑ | |
| 301 | 23989 | አቶ ደስታ ሠርዳ እና<br>የመተከል ዞን ፍትህ መምሪያ | የማይንቀሳቀስ ንብረት ስመ ንብረት /ባለቤትነት/ ከሻጭ ወደ ገዥ ያለመዛወሩ ብቻ ሦስተኛ ወገኖች በሻጭ ላይ ሽያጭ የተካሄደበት ንብረት ላይ የጀመሩት አፈፃፀም እንዲቀጥል ለማስደረግ በቂ ሁኔታ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2878 | ታህሳስ<br>17/2000 |
| 302 | 25031 | ወ/ሮ አልታየወርቅ ኃ/ማርያም እና<br>አቶ ዓለማየሁ ገለቱ | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 መሰረት አቤቱታ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358,418 | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 303 | 26553 | የባህርዳር ልዩ ዞን ገንዘብ መምሪያ እና የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ እና<br>ሙክታር መሐመድ | • የማይንቀሳቀስ ንብረት በሃራጅ በሚሸጥበት ጊዜ በሃራጅ እንዲሸጥ የሚወጣው ማስታወቂያ ለ30 ቀናት መቆየት ያለበት ስለመሆኑ<br>• ንብረቱ በመያዣ የተያዘ እንደሆነም የመያዣው ልክ ምን ያህል እንደሆነ በጨረታ ማስታወቂያ ላይ መገለጽ ያለበት ስለመሆኑ<br>• ሽያጩ ባልተገባ መንገድ ተከናውኗል ከተባለም ጨረታው በድጋሚ  መካሄድ ያለበት ስለመሆኑ<br>• በመያዣ የተያዘን ንብረት በሌላ ባለገንዘብ ጠያቂነት እንዲሸጥ ሊደረግ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/1/, 3084, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418, 426, 423/2/ /ለ/, 445-447, 415 | ሐምሌ<br>3/1999 |
| 304 | 27574 | ወ/ሮ አለሚቱ ተረፈ እና የትግል ፍሬ ልብስ ስፌት ማኅበር | በሽምግልና ጉባኤ አማካኝነት የተሰጠ ውሣኔ በፍ/ቤት ሊፈፀም የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 215/1/, 319/2/ | ጥቅምት<br>26/2000 |
| 305 | 28019 | አቶ ብርሀኑ ገ/እግዚአብሔር እና ወ/ሮ ገርጊስ ናይዝጊ | ፍርድን በአግባቡ ውጤት ለመስጠት የአፈፃፀም ችሎት የፍርዱን ትክክለኛ ቃል እና መንፈስ መከተል ያለበት ስለመሆኑ | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 306 | 28154 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ 3ኛ ወገኖች መብት ያቋቋምን ስለሆነ አፈፃፀም ሊቀጥል አይገባም በሚል አቤቱታ ያቀረቡ እንደሆነ ፍ/ቤት ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች በአቤቱታው ላይ ያላቸውን ክርክር በቅድሚያ በመስማት መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418/1/, 419 | ሚያዝያ<br>14/2000 |
| 307 | 29344 | ወ/ሮ ዝማም ህሉፍ<br>እና<br>አቶ መረሣ ገ/ዮሐንስ | ውሣኔን የሚያስፈጽም ፍ/ቤት በውሣኔው መሰረት ከማስፈፀም ወጪ በአፈፃፀም ጊዜ ዋናውን ፍርድ ሊለውጥ የሚችልበት የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418 | ግንቦት<br>5/2000 |
| 308 | 29653 | አቶ ነጋ ደምሴ<br>እና<br>ሃምሳ አለቃ አዲሱ ደምስ | በዋናው ክርክር ገብቶ ተከራክሮ ውሣኔ ያላገኘ ተከራካሪ ወገን በአፈፃፀም ጊዜ ውሣኔ እንዲፈፀምለት ጥያቄ የሚያቀርብበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418 | መጋቢት<br>9/2000 |
| 309 | 33760 | ሐጂ ታጁ ለገሠ<br>እና<br>የጎንደር ከተማ የመሃል አራዳ ቀበሌ አስተዳደር | የንግድ ድርጅት /መደብር/ ላይ ያለ መብት የድርጅቱ ንግድ የሚካሄድበትን ቤት የኪራይ መብት የሚያካትት ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 127 | መጋቢት<br>18/2000 |